www.chilot.me

# የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



## ቅጽ -22

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት**

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች

ቅጽ 22




የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ድረ-ገጽ፡- www.fsc.gov.et
ስልክ፡- +251 111 55 34 00
ፋክስ፡- +251 111 56 55 83
የመ.ሣ.ቁ፡- 6166
ነፃ የስልክ ጥሪ፡- 992

www.chilot.me

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

# ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ-22

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

መስከረም 2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ



## <u>የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሥልጣኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚሰጥባቸውን የሰበር ውሳኔዎች አሳትሞ የማሰራጨት ኃላፊነት እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) ሥር ተመልክቷል፡፡

ይህንን የሕግ ግዴታ ለመወጣት አስገዳጅ የሆኑ የተለያዩ ውሳኔዎችን በቅጽ መልክ በማደራጀትና ለህትመት በማብቃት ለተጠቃሚው ህብረተሰብና ለተለያዩ የፍትህ አካላት እንዲደርስ ለማድረግ በተቋሙ ድህረ ገጽ እንዲሁም በሜጋ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር ባሉት 32 ቅርንጫፎች እንዲሰራጭ በማድረግ የፍትህ ሥርዓቱ ወጥነት እና ተገማችነት እንዲኖረው ለማድረግ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም አገልግሎቱን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ የምትሰጡን ገንቢ አስተያየቶች ወሳኝ መሆናቸውን እየገለጽኩ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እገልጻለሁ፡፡

**ዳኜ መላኩ**

**የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት**

# የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 22/

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ውል** | | | | | 1 |
| 1. | የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ውልን የሚመለከቱ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት (አርቢትሬተር) እንዳይዳኙ የተጣለው ገደብ ወይም ክልከላ ገላጋይ ዳኛ (አድጁዲኬተር) ጋር በተያያዘም ተፈጻሚነት ያላቸው ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 315/2/፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678/ለ፣3131 እና 3132/ለ/ | 127459 | ጣና የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ኢንዱስትሪ ሀ/የተ/የግ/ማህበር | መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም | 2 |
| 2. | በሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣዉ የትግራይ ክልል ደንብ መሰረት የአምልኮ ቦታዎች በመንግስት የሚሰጡ መሆናቸዉን ቢደነግጉም ከግለሰቦች እንዳይገዛ በግልጽ ክልከላ የማያደርግ ስለመሆኑ፡- | 124725 | የሽሬ እንደስላሴ አንዋር መስጊድ እና እነ ወ/ሮ ትኑር ፍትዊ /6 ሰዎች/ | ጥቅምት 29 ቀን 2010 ዓ.ም | 8 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አንድ ውል ህገወጥ ነው በሚል ምክንያት ፈራሽ ሊሆን የሚችለው የውሉ መሰረት የሆነው መብትና ግዴታ በህግ በተከለከለ ነገር ላይ መደረጉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣<br>ሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ የትግራይ ክልል ደንብ ቁጥር 62/2002<br>እና የፍትሐብሄር ህግ አንቀጽ 1716 | | | | |
| 3. | ከቤት ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ የይርጋው ጊዜ ስለሚታሰብበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 | 131151 | እነ አቶ ከፍያለው አየለ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ወርቅነሽ በላይ | ታህሳስ 25 2010 ዓ.ም | 15 |
| 4. | አንድ የመሬት ሽያጭ ውል ህገ ወጥ ውል መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ገዥ ወገን በመሬቱ ላይ የሰራው ቤት በሻጭ ፈቃድ እንደተሰራ ተደርጎ የህግ ግምት የሚወሰድበት አግባብ የማይኖር ስለመሆኑ<br>የኢፌድሪ ህ/መ አንቀፅ 40 (3) እና የፍ/ብ/ህ ቁጥር 1678 (ለ) እና 1716 | 141606 | አቶ ማሞ ቱሉ<br>እና<br>አቶ አበበ አበራ | መስከረም 25/2010 ዓ.ም | 19 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 5. | የዕቃ ማጓጓዝ ውል በማጓጓዣ ሰነድ ወይም መሰል ሰነዶች ሊረጋገጥ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>በየብስ የዕቃ ማጓጓዝ ስራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር 547/99 አንቀጽ 4፣8 | 130676 | ጅቡቲ ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ 3-ለ የደ/ጭ/ማ/ባ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ሞላደርጎ | ጥቅምት 27/2010 | 22 |
| 6. | አንድ ሥራን ለመስራት የመተባበርና የመተጋገዝ ስምምነት ማድረግ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ስምምነት ነው ከሚባል በስተቀር አስገዳጅነት ያለው በሕግ ፊት ግዴታን የሚፈጥር ውል አለ ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678፣1731፣1771 | 120468 | አቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ክርስቶስ<br>እና<br>አቶ ሐረጎ ገ/እግዚአብሔር | መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም | 27 |
| 7. | አንድ የሽያጭ ውል ያደረገ ወገን የተደረገው የሽያጭ ውል ያለመመዝገቡን የማይንቀሳቀስ ንብረት በእጁ ባስገባ 3ኛ ወገን ላይ በመቃወሚያነት ለማንሳት የማይችል ስለመሆኑ፣ | 123761 | ወ/ሮ እናኒ ተሰማ እና እነቁስ ገብረማርያም | መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም | 33 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሽያጭ ውል ያደረገ ወገን በውሉ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ የተከናወኑ ተግባራትን ሁሉ ለመቃወም የሚችለው የተደረገው የሽያጭ ውል የተመዘገበ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878 | | | | |
| 8. | አንድ ውል ሳይፈጸም በቀረ ጊዜ እንደውሉ አልተፈጸመልኝም የሚለው ተዋዋይ ወገን ሳይፈጸምልህ ቀርቷል በማለት ክርክር ለማቅረብ በቅድሚያ ውሉን ያልፈጸመው አካል ግዴታውን እንዲፈጸምለት ለማድረግ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑና በዚህ መሰረት ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ወለድ የሚሰላበትን ጊዜ በመወሰን ረገድ ጠቀሜታ ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 1772 | 133203 | ኢትዮ ቴሌኮም ጋምቤላ ሪጅን እና አዱራ ኮንስትራክሽን አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ | ጥቅምት 29 ቀን 2010 ዓ.ም | 39 |
| 9. | በመርህ ደረጃ አንድ ዉል ለአንደኛው ወገን የበለጠ ጥቅም | 138591 | ሼህ አደም ፋረስ | የካቲት | 44 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ይሰጣል በሚል እንደማይፈርስ ነገር ግን ፈቃድ የተገኘዉ በዕድሜ መግፋት ወይም የንግድ ልምድ ዕዉቀቱ ማነስ ካለና በሕሊና ግፍ መስሎ ከታየ ዉሉ የሚሰርዝበት ሁኔታ ስለመኖሩ፡- አንድ ተዋዋይ የዉል ይሰረዝልኝ ክስ ዉሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ዉስጥ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ ፡- የፍ/ሕ/ቁ. 1710(1)እና(2) ፤ የፍ/ሕ/ቁ.1810(1) | | እና ሼህ ሙስጠፋ ፍሊ | 27/2010 ዓ.ም | |
| 10. | ዉል እንዲፈርስ ጥያቄ የሚያቀርብ ወገን ዉሉ ሊፈርስ የሚችልበት በህግ ተቀባይነት ያለዉ ምክንያት ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም ለዉሉ መፍረስ በምክንያትነት የተጠቀሰዉ ሁኔታ ዉሉ እንዲፈርስ ለማድረግ በህግ ተቀባይነት ያለዉ እና በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ የህጉ ድንጋጌዎች ድንጋጌዎች | 138386 | እነ አቶ ረጋሣ ጉርሙ (2 ሰዎች) እና እነ አቶ ተሾመ አፈወርቅ (2 ሰዎች) | የካቲት 26 ቀን 2010 ዓ.ም | 48 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጋር አገናዝቦ የማጣራት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ ህግ አንቀጽ 347(1)፣ 347(2) እና ፍ/ህ አንቀጽ 1710(2) | | | | |
| 11. | የማይፀናና ህገ ወጥ የሆነ የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ሆኖ ግራ ቀኙ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ውሳኔ ሲሰጥ በህገ ወጥ በመንገድ በተገኘው ባዶ ቦታ ላይ ቤት የገነባው ወገን ቤቱን በራሱ ወጪ በማፍረስ ለባለይዞታው እንዲያስረክብ ከማድረግ ባለፈ ለግንባታው ያወጣውን ወጪ ባለይዞታ የሆነው ወገን እንዲከፍለው ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕ/መ አንቀፅ 40(3) እና የፍ/ብ/ህ ቁ 1815 | 128650 | ወ/ሮ እቴናት አድማሱ እና አቶ ደመቀ ይዘንጋዉ | መስከረም 26 2010 ዓ.ም | 54 |
| **ፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት** | | | | | 59 |
| 12. | ለቀጠሮ ምክንያት የሆነ ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም | 138479 | ወ/ሮ ሸዋዬ ገ/እግዚአብሔር እና ተጠሪ - ወ/ሮ ብርሃኔ | የካቲት 26 ቀን 2010 ዓ.ም. | 60 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንኳ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ የመሰለውን ውሳኔ መስጠት ስለመቻሉ፡- የፍ/ብ/ስ/ሥ/ህ/ቁ 199(1) | | ፀአዱ | | |
| 13. | አንድ ወራሽ በሟች የውርስ ንብረት ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲጣራ በግልፅ ተስማምቶና ውክልና ሰጥቶ በሚጣራው የውርስ ፋይል ተሳታፊ ሆኖ እያለ ከሚጣራው ንብረት ላይ የግል ንብረት ያለ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት የሚያቀርበውን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ የቀረበውን ሪፖርት ተቀብሎና መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ የጣልቃ ገብ ክርክሩን ሊቀበለው የማይገባ ስለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ቁ. 947 | 133708 | እነ ወ/ሮ ጣይቱ ደያሳ እና አቶ ጉደታ ደያሳ | ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ.ም | 64 |
| 14. | አንድ ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልስ ወይም በማናቸዉም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ | 138717 ፡ | ብርክቲ ግደይ እና | የካቲት 28 ቀን 2010 | 69 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ሌላኛዉ ተከራካሪ ወገን በዚህ እምነት መሰረት ዉሳኔ እንዲሰጠዉ መጠየቅ እንደሚችል እና ፍ/ቤትም ሌላ በማስረጃ የሚረጋገጥ ነገር ቢኖርም እንኳን በታመነዉና ዉሳኔ እንዲሰጥበት በተጠየቀዉ ጉዳይ ብቻ ፍርድ መስጠት የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242 | | እነ አቶ ሽምሱ ኑሪ(2 ሰዎች) | ዓ/ም | |
| 15. | በትግራይ ክልል የጎጆ መውጫ ይዞታና ቤት የሚመለከትን ጉዳይ የቀበሌ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ጉዳዩን ተቀብሎ አይቶ ውሳኔ ከሰጠ በኂላ በተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል በማለት የመቃወሚያ ማመልከቻ ሲቀርብ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻውን ተከትሎ የቀደመዉን ዉሳኔ የማጽደቅ ወይም የማሻሻል ወይም የመለወጥ ወይም የመሰረዝ ስልጣን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የቀበሌ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ስለመሆኑ፡- | 131832 | ወ/ሮ መረሳ አማረ<br>እና<br>እነ ቄስ ሃይለ ገብረ ( 2 ሰዎች) | ታህሳስ 23 2010 ዓ.ም | 74 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 ፣ 360(2) | | | | |
| 16. | የይዞታ ክርክርን በተመለከተ አንድ ተከራካሪ ወገን ካርታዉ እንደተሰረዘ እና በዚያ ካርታ ይዞታዉን ለመጠየቅ መብት እንደሌለዉ ዉሳኔ ተሰጥቶ እያለ ተከራካሪ ወገን በመቀየር ክስ ስላቀረበ ብቻ የክርክሩ ጭብጥና ተከራካሪ ወገን ስለሚለያይ ከዚህ ቀደም ዉሳኔ ተሰጥቷል የሚያስብል አይደለም በማለት አዲስ ክስ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፡- <br> የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5(1) | 13041 0 | ሱፍያን አቡበከር <br> እና <br> እነ አቶ ክፍሉ ጋሼ (2 ሰዎች) | ታህሳስ 30 2010 ዓ.ም | 78 |
| 17. | •ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተለይ ካልፈቀደ በቀር ይግባኝ ባይ በይግባኝ ማመልከቻ ላይ ዘርዝሮ ያልገለጸውን አዲስ ነገር በማንሳት ወይም መሠረት በማድረግ ለመከራከር የማይችል ስለመሆኑ፡- <br> •ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ ማመልከቻ ተዘርዝሮ ከተገለጸ ወይም ክርክር ከተነሳበት ውጭ በሆነ ነገር ፍርድ | 137831 | ወ/ሮ ለተብርሃን ያይንሸት <br> እና <br> አቶ የማነ በየነ | ህዳር 28 ቀን 2010 ዓ/ም | 83 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መስጠት የማይችል ስለመሆኑ፡- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 328 /2/፤328 /3/ | | | | |
| 18. | የተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት የክርክር አመራር የሰዎችን የመከላከልና የመሰማት ሕገ መንግስታዊ መብትን በሚነካ መልኩ መተርጎም እና ሥራ ላይ መዋል የማይገባው ስለመሆኑ፡- ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.284-287 | 131498 | አቶ መሳይ ቦጋላ እና ወ/ሮ አይናለም አለሙ | መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም | 90 |
| 19. | የዕግድ ትእዛዝ በባህሪው ጊዜያዊ በመሆኑ ለዕግዱ ምክንያት የሆነው ክርክር ዕልባት ሲያገኝ የሚነሳ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 | 135590 | ፋንታሁን ተፈሪ እና አበባ ገ/ማርያም | ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም | 96 |
| 20. | አንድ ጉዳይ በማንኛውም የክርክር ደረጃ ላይ በሚገኝበት ወቅት ተከራካሪ ወገኖች በእርቅ ወይም በግልግል ስምምነት የመጨረስ መብት ያላቸው ቢሆንም፤ ክሱን በእርቅ ለመጨረስ ቀጠሮ ያስለወጠ ወገን ቀጠሮ | 136901 | እነ ሕጻን ቤተልሄም ሰለሞን (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ጌታቸዉ | መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም | 101 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በተሰጠበት ቀን ፍ/ቤትን ቀርቦ የተደረሰበትን ደረጃ ያለማሳወቅ እና ለረጅም ጊዜ ጉዳዩን ያለመከታተል ኪሳራ እንዲከፈል ሊወሰንበት ከመቻሉ በላይ አዲስ ክስ መመስረት የማይቻል ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 69 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ቁ. 275 እና 79/1/ | | ገ/መስቀል(3 ሰዎች) | | |
| 21. | በአንድ ክርክር ውስጥ የከሳሾች ወይም የተከሳሾች ብዛት ከአንድ በላይ ሲሆንና ክርክሩም ከሳሾችን ወይም ተከሳሾችን በአንድ ዓይነት መልክ የሚመለከታቸው ሲሆን ከሳሾቹ ወይም ከተከሳሾቹ አንዱ በጠቅላላው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሲጠይቅና ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት ፍርዱን በመለወጥ ያሻሻለው ወይም የለወጠው ወይም ያጸናው ፍርድ ይግባኙን ባላቀረቡት ከሳሾች ወይም ተከሳሾች ላይም በይግባኝ ደረጃም በቀረበው ጉዳዩ ከከሳሾቹ መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የሚሰጠው ውሳኔ ሌሎችንም የሚያካትት | 139138 | አቶ ኃይሉ ሂንጌ እና አመርቲ ነሼ የፊንጫኣ ሀይል መመንጫ ፕሮጀክት | ህዳር 20 ቀን 2010 ዓ/ም | 108 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 35 እና 331 | | | | |
| 22. | ለአንድ ክርክር መነሻ የሆነ ቤትና ይዞታ በክልል የሚገኝ ሲሆንና የስረ ነገር ስልጣኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ንብረቱ በሚገኝበት ክልል የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ፡- | 139942 | ወ/ሮ ዘይባ ሳኒ እና ወ/ሮ ለይላ ዘይኑ | ህዳር 27 ቀን 2010 ዓ/ም | 112 |
| 23. | በአንድ ክርክር ከሳሽ የሆነው ወገን ጣልቃ በገባ ተከራካሪ ወገን ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ከማንሳት የሚከለከልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁ.39፣40፣41 | 135254 | አቶ ይስሃቅ ተክለ ፃዲቅ እና እነ ወ/ሮ ሃረገወይን አሸኔ | የካቲት 29 ቀን 2010 ዓ.ም | 115 |
| 24. | ሰበር ችሎቶች ሥነ ሥርዓታዊ የሆነ የህግ ጥያቄን ብቻ ለማየት ስልጣን እንዳላቸው ግንዛቤ በመውሰድ በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ስነ-ስርዓታዊ ሕጎችን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን መመርመር አንጂ | 138340 | እነ ሶፍያን ከማሎ(6ሰዎች) እና ወ/ሮ ጀሚላ ቃሲም | ህዳር 19 ቀን 2010 ዓ.ም | 121 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከዚህ ውጪ መደበኛ ሕጎችን መሰረት አድርገው በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሊመረምሩ የሚችሉበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፡- በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))፣ 80(3(ለ)) እና አዋጅ ቁጥር 53/94 እና አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6 | | | | |
| 25. | ሁከት ተወግዶ ይዞታ እንዲለቀቅ ክስ ቀርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኂላ በድጋሚ ይዞታ ይለቀቅልኝ በሚል ክስ መመስረት ዳኝነት በተሰጠበት ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5፣ 244(ለ) | 138062 | የሰቆጣ ከተማ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት እና ወ/ሮአድና ምህረቱ | ህዳር 26 ቀን 2010 ዓ.ም. | 125 |
| 26. | አንድ ሰው ቀድሞ በቀረበ ክርክር ጣልቃ ገብ በመሆን ክርክር ያቀረበ ወይም በጉዳዩ ተሳታፊ የነበረ መሆኑ በጣልቃ ገብነት በቀረበበት ክርክር ግልጽ ዳኝነት ባልተጠየቀባቸው ጉዳዮች በሌላ ጊዜ ክስ ለማቅረብ የሚችል | 137401 | ወ/ሮ ጀምላ ጀብር እና አቶ ሶፊያ ጅማ | የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም | 129 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑና በዚህ አግባብ የሚቀርብን ክስ በቀድሞው ክርክር ተጠቃሎ መቅረብ የነበረበትና ተከፋፍሎ ዳኝነት ሊቀርብበት አይገባም በሚል አቤቱታን ዉድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41፣216 እና 218 | | | | |
| 27. | አንድ ውል በይዘቱ የአስተዳደር ውል ሲሆን የአስተዳደር አካል ወይም መንግስት ውሉን ለመሰረዝ መብት ያለው ስለመሆኑና ሌላኛው ወገን በውሉ መፍረስ የደረሰበት ጉዳት ካለ ከመጠየቅ በስተቀር ውሉ እንዲሻሻል ሆነ ለስራ ማስኬጃ የተቀበለውን ቅድመ ክፍያ ላለመመለስ የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ ህ/ቁጥር 1815፣3180 እና 3181 | 129534 | የሊቦከምከም ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ እናትነሽ ዘለቀ (2 ሰዎች) | መስከረም 24 ቀን2010 ዓ.ም | 134 |
| 28. | የኦዲት ሪፖርት የሚያሻማና ግልጽነት የሌለው በሆነበትና በሪፖርቱ የቀረበውን ሀሳብ ይዘት እንዲያስረዱ ሪፖርቱን ያዘጋጁ የሂሳብ ባለሙያዎች ቀርበው እንዲያስረዱ | 128746 | ሻምበል መሐመድ ብርሃን ረዳ<br>እና | መስከረም25 ቀን 2010 | 138 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ባልተደረገበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች የኦዲት ሪፖርቱን ራሳቸው በተረዱት አግባብ ተርጉመው የሚሰጡት ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 133 (3) | | ወ/ሮ ዘምዘም መኮንን | ዓ.ም. | |
| 29. | በቀድሞ ክርክር ጊዜ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት በዝምታ የታለፈ ጉዳይ በሌላ ጊዜ የክስ እና የክርክር ምክንያት ሊሆን አይችልም ማለት እንጂ ፍ/ቤቶች በተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ በዝምታ ማለፍ የማይችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ስ/ስ/ሕ ቁጥር *5 (3) ፤*182 (1) | 131950 | ወ/ሮ የሺመቤት ገ/ፃዲቅ<br>እና<br>ወ/ሮ ፋንታዬ ሽጉልቱ | መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም | 144 |
| **ወንጀል** | | | | | 149 |
| 30. | በይግባኝ ፍ/ቤቶች አንድ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ውሳኔ ለመስጠት የሚችሉ ቢሆንም የሚሰጠው ውሳኔ የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች የይግባኝ መብት የሚያጣብብ ሆኖ ሲገኝ የቀረበው ማስረጃ ተገቢ በሆነ ምክንያት ድጋሚ | 127484 | አቶ ተስፋዬ በቀለ<br>እና<br>የፌ/ዐ/ህግ | መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም | 150 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንዲጣራ እና ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት ለመመለስ የሚችሉ ስለመሆኑ፣<br>የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 143 እና 195/2/ለ//2/ | | | | |
| 31. | የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እና የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን የተለያየ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና የሠራዊት አባላት በፋውንዴሽኑ ንብረት ላይ የሚፈጽሟቸው ማንኛውም ወንጀሎች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ላይ እንደተፈጸሙ ተደርጎ የማይቆጠሩ ስለመሆናቸው፡-<br>የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት በመከላከያ ሰራዊት ፋውንዴሽን ንብረት ላይ የሚፈጽማቸው ወንጀሎችን የማየት ስልጣን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ሆኖ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን የማስተናገድ የመጀመሪያ ደረጃ የፍርድ ስልጣን የሚኖረው ስለመሆኑ፡-<br>የአዋጅ ቁጥር. 434/1997 አንቀጽ 7/1/ እና የአዋጅ ቁጥር. | 141663 | ሻ/ቃ አለማየሁ ወንጅሉ<br>እና<br>የፌ.ጠ.ዐ/ህግ | መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም | 155 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | 809/2006 አንቀጽ 28 እና 38 ደንብ ቁ. 179/2002 | | | | |
| 32. | "…ማናቸውም የግል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ይቀጣል.." የሚል አገላለጽ በውስጣቸው የሚገኙ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ በግል አቤቱታ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት ሰው በቀር በሌላ በማንም ሰው የክስ ጉዳይ ሊንቀሳቀስ የማይችል ስለመሆኑና የግል ከሳሽ የሆነው ሰውም የማመልከቻውን አዘገጃጀት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 150-153 መሰረት መምራት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣<br><br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2/ እና 575/2/ሀ/ መሰረት ተደርጎ የቀረበ የወንጀል ክስ በግል ተበዳይ ወይም ህጋዊ ወኪሉ አማካይነት የሚቀርብ እና በግል አቤት ባይ የቀረበ ክስ በሚመራበት ስነ-ስርዓት የሚመራ ሳይሆን በዓቃቤ ህግ | 141978 | የፌ.ጠ.ዓ/ህግ<br>እና<br>እዮኤል ተስፋዬ የሺጥላ | መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም | 161 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወይም በመንግስት የሚቀርቡ የወንጀል ክሶች በሚመሩበት ስርዓት የሚስተናገዱ እና በግል ተበዳይ ፍላጎት መሰረት ሊቋረጡ የማይችሉ ወንጀሎች ስለመሆናቸው፣ የወ/ህ/ስ/ስ/ህ/ቁ 150-153 እና የወ/ህ/ቁ. 559/2/ እና 575/2/ሀ/፣ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 132-135፣ 185፣196፣ 117 94.88 123-131 እና 186-149 | | | | |
| 33. | በወንጀል የተከሰሰ ሰው የግል ተበዳይን በመከላከያ ምስክርነት ያቀረበና የግል ተበዳይም ድርጊቱ ያለመፈፀሙን በመግለጽ የምስክርነት ቃል የሰጠ ከሆነ ዓ/ህግ የግል ተበዳይ የምስክርነት ቃል በድለላ ወይም በጥቅም የተገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ እስካልቻለ ድረስ ተከሳሽ ክሱን አላስተባበለም ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ፡- የወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ/ ቁጥር 149 (2) | 137545 | አቶ አሸብር መለስ እና የፌዴራል ዓቃቤሕግ | መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም | 165 |
| 34. | አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በመግደል ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ሊደረግ የሚገባው የወንጀሉ አፈፃፀም ጠቅላላ | 127505 | አበራ ዋቅጅራ እና | መስከረም 25/2010 | 174 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሁኔታ እና በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት አንፃር እውነትም ወንጀሉን ለመፈፀም ሀሳብ የነበረው እና የተፈለገው ውጤት ያልተገኘው ሀሳቡን ለማሳካት የማያስችል ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት መሆኑን ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 555 (1) እና 540፣ 27(1) | | የቤ/ጉ/ክልል ፍትህ ቢሮ | | |
| 35. | በአንድ የወንጀል የማድረግ ሃሳብ ወይም ቸልተኝነት የተፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት በሕግ በተጠበቀ አንድ መብት ላይ በሚሆንበት ጊዜ እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር መሸፈን ከተቻለ፤ ፈጻሚዉ የሚቀጣዉ ድርጊቶቹ በሚሸፈኑበት በአንድ ድንጋጌ ስር እንጂ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች ስላለመሆኑ፡-<br>በወንጀል ሕግ አንቀጽ 61(1) | 134549 | አቶ አበበ ተፈራ አለሙ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ | መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም | 178 |
| 36. | ተሻሽሎ የቀረበ አንድ የወንጀል ክስ የተከሳሹ መሰረታዊ | 141677 | ያዕቆብ አብዱ | ህዳር 29 | 184 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መብት ላይ የሚኖረዉ አሉታዊ ተጽእኖ ጋር ተመዛዝኖ በስነስርዓት ህጉ የተጠበቀለት የመሰማት መብቱን በጥብቅ ተግባራዊ በማድረግ ክሱ እንደገና ተሰምቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ 118፤119/2/ ፤120 እና 121 | | እና<br>የደቡብ ክልል አቃቤ ህግ | ቀን 2010 ዓ.ም | |
| 37. | የተከሰሰ ሰው የዓቃቤ ህግ ማስረጃ ሲሰማ በመገኘት የዓቃቤ ህግና ምስክሮች የመጠየቅና የመመርመር መብቱን በአግባቡ ከተጠቀመና መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ እንዲከላከል ተፈቅዶለት ቀጠሮውን አክብሮ ያልቀረበ በሆነበት አግባብ ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ አይደለም በማለት የሚሰጡት ውሳኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፡-<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 161 እና 164 እና የህ/መ አንቀጽ 20/4/ | 127313 | የአ/ብ/ክ/መ/ፍ/ቢሮ እና<br>አቶ አንዱአለም ገናናው | መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም | 187 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 38. | ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በማከማቸት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ የማስረዳት ግዴታ ዐቃቤ ሕግ በክሱ ከገለፀውና በማስረጃ ካረጋገጠው ውጭ ተከሳሽ ሌላ ገቢ የሚያገኝበት ስራ ወይም የገቢ ምንጭ ያለው መሆኑን ብቻ ለፍርድ ቤቱ በማሳየት የሚወሰን ሳይሆን፣በዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ከተረጋገጠው ገቢ ውጭ በእጁ እንደተገኘ የተረጋገጠው ገንዘብና ሀብት ትክክለኛ ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፡- <br> የወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 /1//ሀ/ እና /ለ/ | 137672 | ብርሃነ ሀለፎም ገ/መድህን <br> እና <br> የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ህግ | ህዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም. | 192 |
| 39. | ማንኛውም ሰው አግባብነት ካለው አካል ፍቃድ ባላገኘበት ሁኔታ የተሸከርካሪውን የሞተር፣ የሻንሲ ቁጥር እና መሠለ መረጃዎችን የመቀየር ተግባር የፈጸመ ከሆነ አደራጎቱ የተከለከለና በወንጀል ህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ | 122595 | የገ/ጉ/ባለስልጣን ዓ/ህግ <br> እና <br> 1ኛ አቶ ፋሲል ጥላሁን <br> 2ኛ አቶ ካሊድ ሳቢት | መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም | 197 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አንድ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ መግባቱ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ የጉምሩክ አዋጅ በሚደነግገዉ አግባብ መኪናዉ በመንግስት ከመወረስ ሊድን የሚችልበት ሁኔታ ስላለመኖሩ<br>የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 104/3/ /ሀ/ ፤ ስለተሽከርካሪዎች መለያ፤መመርመሪያ እና መመዝገቢያ የወጣ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 42/5/ እና 48/2/ /ሐ/ | | | | |
| 40. | ወንጀል መፈጸሙን ለማጣራትና ምርመራ ለማጠናቀቅ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎች በህግ ጥበቃ የሚደረግላቸው እና ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ለማግኘት የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች የሚቀርብላቸውን ጥያቄ በአግባቡ በማጤን ተገቢውን ትእዛዝ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የአ.ቁ 592/2000 አንቀጽ 28/4/ /ሠ/ አ.ቁ 720/2004 | 139107 | የጉለሌ ክ/ከ ፖሊስ መምሪያ<br>እና<br>ተጠሪ የለም | መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም | 204 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አንቀጽ 6 | | | | |
| 41. | ተከሳሽ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ጠይቆ የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት ጠብቆ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት በመጠበቅ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በሰጠው ውሳኔ ላይ ተከሳሽ ይግባኝ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ፡-<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 | 146727 | አቶ አክሊሉ አፈወርቅ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕ | ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም | 208 |
| 42. | በትምህርት ደረጃው ከፍተኛ የሆነና በባህሪው ለህብረተሰብ አርአያ ሊሆን የሚገቡ ሰዎች ፍፁም ነውረኛ በሆነና ጨካኝነት በተሞላበት ሁኔታ የፈፀሙት ከባድ የወንጀል ድርጊት የወንጀል አፈጻጸሙን ከባድነት እና የወንጀለኛውን አደገኛነት የሚያሳይ በሆነ ጊዜ ወንጀለኛው ላይ የቀረበ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ያለመኖር ወንጀለኛው ጥሩ ፀባይ ወይም መልካም ፀባይ ያለው ነው የሚል ግምት | 135787 | አበባየሁ ሳሙኤል<br>እና<br>የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ | መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም | 211 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለመውሰድ የማያበቃ ስለመሆኑ፣<br>-የወ/ህ/ቁ. 184/1/ሀ/ እና ለ ቁ. 539 ቁ. 671/1/0/<br>የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 15 እና የወ/ህ/ቁ. 117 | | | | |
| 43. | በወንጀል ህግ አንቀጽ 620/3/ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት በግል ተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአይምሮ ጉዳት ወይም ሞት የደረሰ መሆኑ ሊረጋገጥ የሚገባ ስለመሆኑ እና አንድ የወንጀል ክስ የወ/ህ/አንቀጽ ቁጥር 620/2/መ/ መሰረት በማድረግ በቀረበበት ሁኔታ ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጡ የክስ መሰረት የሆነውን አንቀጽ ወደ አንቀጽ ቁጥር 620/3 በመቀየር ውሳኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆኑ፣<br><br>የወንጀል አፈጻጸሙ አፀያፊነት ከወንጀል ፈጻሚው ድርጊት | 137262 | እነ ሀይላይ ወ/ገብርኤል እና የት/ብ/ክ/መ/ፍትህ ዐ/ህግ | መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም | 219 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከተረጋገጠና በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በወጣው ደረጃ መሰረት ቅጣቱ ቢወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት አላማና ግብ የሚያሳካ የማይሆንበት ሁኔታ ሲኖር ቅጣቱን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ መወሰን የሚቻል ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/ቁ. 620/2/ መ፣ 620/3/ እና የወ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 113/2/ የወ/ህ/ቅ/አ/መ/ቁ.2/2006 27/1/ እና 4/9/ የወ/ህ/ቁ. 539/1/2//ሀ/፣ የወ/ህ ቁ. 82 | | | | |
| **አሰሪና ሰራተኛ** | | | | | 226 |
| 44. | አንድ ድርጅት በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው መዘጋት ሠራተኞችን የሥራ ውልን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለማቋረጥ የሚያስችል ሲሆን መረጋገጥ ያለበት መሰረታዊው ነጥብ የአሰሪው ድርጅት ለዘለቄታው መዘጋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24(4) | 143334 | ዋኢል አብዱጌት አብዱላዚዝ ፕላስቲክ ፋብሪካ እና እነ አበራ አመዩ (8 ሰዎች) | ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም | 227 |
| 45. | የሙከራ ጊዜ ቅጥር ሲፈጸም ሰራተኛው በግልጽ | 126667 | ኤልያስ ባርና ሬስቶራንት | መስከረም | 232 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንዲያውቀው ሳይደረግና ስምምነት ሲደረግም በጽሁፍ ተደርጎ በሁለት ምስክሮች ባልተረጋገጠበት አሰሪው ሠራተኛው ለተቀጠረበት የሥራ መደብ ተስማሚ ሆኖ አልተገኘም በሚል የቅጥር ውሉን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በህጉ መብት ያልተሰጠው ስለመሆኑ፣<br>የአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 1/1/ /2/ እና /3/ | | እና<br>እነወ/ሮ ምርትነሽ አጥናፉ | 26 ቀን 2010 ዓ.ም | |
| 46. | አንድ ሠራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የጡረታ መብት ተጠቃሚ ከሆነ አሰሪው የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የመክፈል ግዴታ የሌለበት ሲሆን በራሱ ፍላጎት እና ፈቃደኝነት የስራ ስንብት ክፍያን በተደራቢነት እንዳይከፍል ክልከላ የሚያደርግ ስላለመሆኑ፡-<br>አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 2 (ሰ) | 151474 | ቦሰት የሕጻናትና ቤተሰብ በጎ አድራጎት ድርጅት<br>እና<br>ወ/ሮ ዓለም ሽመልስ ቀረቡ | መጋቢት 14 ቀን 2010ዓ.ም. | 239 |
| 47. | አንድ ሠራተኛ መደበኛ የጡረታ ዕድሜው ደርሶ የመብቱ ተጠቃሚ መሆኑ በተረጋገጠበት አግባብ ለጡረታ መብት ላልተያዘለት ጊዜ የሥራ ስንብት ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል | 132280 | እነ አቶ አስቻለው አስማማው (2 ሰዎች )<br>እና | መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም | 246 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ፡-<br>የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39፤ 43 (4)ፈ<br>አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ እና /ሽ/፤ | | የደቡብ ሥራዎች<br>ኮንስትራክሽን ድርጅት | | |
| 48. | ሠራተኛ በህይወቱ ላይ አደጋ ሊደርስበት በሚችል አኳኋን እንዲሰራ ማድረግ ህገወጥ ድርጊት ስለመሆኑና ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ ውል እንዲያቋርጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ፣<br>የአ/ቁ. 14/ሠ/ እና አንቀጽ 32/1/ለ | 136571 | እድገት ተስፋ ሁለገብ<br>ሀ/የተ/የህ/ ስራ ማህበር<br>እና<br>እነ አቦዬ ለሜሳ | መስከረም 27 ቀን 2010 ዓ.ም | 250 |
| 49. | ለአንድ ሠራተኛ ማስጠንቀቂያ መፃፍ ብቻውን “የስራ መሪ” የማያስብልና ጉዳዩ በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም የሚባልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፡-<br>አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 3/2/ /ሐ/ ስ እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ /ሐ/ | 140677 | አቶ ብርሃኑ ጌቱ<br>እና<br>ብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት<br>አ/ማ ሰራተኛ ማሕበር | ህዳር 22 ቀን 2010 ዓ.ም | 256 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 50. | በአዋጅ ቁ 515/1999 መሰረት በህመም ምክንያት ለ8 ወራት ፍቃድ ሊሰጠው የሚገባ ሰራተኛ የ8 ወር ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት በህመም ምክንያት ወደ ስራ ለመመለስ ያልቻለ እንደሆነ የስራ ውሉ ሊቋረጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ/ቁ 515/1999 አንቀጽ 79/1ለ፤/አንቀጽ 42/2/፣/3/ እና/5/ | 140461 | አቶ ንጉሴ ዘርይሁን እና የኢ/መን/ ባለስልጣን | መስከረም 29 ቀን 2010 ዓ.ም | 259 |
| 51. | ሠራተኞች በሙሉ እውቀታቸውና ብቃታቸው ሰርተው እኩል የምርት ጥራትና መጠን ያመርታሉ ተብሎ የማይገመት ስለመሆኑና የአንደኛው ሠራተኛ ያመረተው ምርት መጠንና ጥራት ብቻ ለሌላው ሠራተኛ ከአቅም በታች ሰርቷል ለማለት በቂ መሰፈርት ሆኖ ሊወሰድ የማይገባ ስለመሆኑ፡- | 150947 | ሚሮና ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ እና እነ ጫልቱ ዓለሙ (4 ሰዎች) | መጋቢት12 ቀን 2010 ዓ/ም | 264 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **የንግድ ህግ** | | | | | 268 |
| 52. | በአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ ሰነድ ላይ የአክስዮን ማህበሩ ማህተም ማረፉ አልያም ዝውውሩ ፀድቋል ወይም ተመዝግቧል የሚል ምልክት መደረጉ ብቻውን በንግድ ህግ ስር በአዛዥ ሁኔታ የተቀመጠውን በባለአክሲዮኖች መዝገብ የመመዝገብ ግዴታን የማይተካ ወይም ቀሪ የማያደርግ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ 331 (1) እና 341 (2) | 139385 | ወ/ሮ መዋዕል ተኩዕ መርሻ<br>እና<br>አንበሳ ኢንተርናሽና ባንክ | መጋቢት 12/2010 | 269 |
| 53. | የአክሲዮን ማህበር ህልውና ከተቀጣሪዎች እና በአጠቃላይ ከሚኖሩ ተያያዥ እንቀውስቃሴዎች ጋር ጭምር በአንድም ሆነ በሌላ አግባብ ግንኙነት የሚኖረው በመሆኑ የማህበር መፍረስ አለመፍረስ አከራካሪ ሆኖ በቀረበ ጊዜ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚገባው ተከሰተ የተባለው ችግር ማህበሩን እንዲፈርስ በመወሰን ካልሆነ በስተቀር በሌላ የህግ አግባብ መፍታት ወይም ማስወገድ እንደማይቻል | 127352 | እነ አቶ ታደሰ አይችሉህም /4 ሰዎች/<br>እና<br>አቶ ዘውዴ ታደሰ | መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም. | 275 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣<br>የማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድም .ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አንድ ማህብር ከተቋቋመ ጀምሮ ተደርጎ አያውቅም በሚል ምክንያት ብቻ አንድ ማህበር እንዲፈርስ ሊወሰን የማይገባ ስለመሆኑና በንግድ ህጉ መሠረት እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ 217 እና 218፣ 495/1/ እና /3/ | | | | |
| 54. | አንድ ሰው የትራንስፖርት ክፍያ ከፍሎ በመኪና ሲጓዝ በነበረበት ወቅት የአካል ጉዳት ቢደርስበት የንግድ ህጉን መሠረት ያደረገና በውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በተጎጂው እና በአጓዡ መካከል ተመስርቷል ማለት ስለሚቻልበት ሁኔታና አጓዡ ለመንገደኛው ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ኃላፊነቱ ሊታይ የሚገባው በንግድ ህጉ ስለ አጓዥ እና ተጓዥ በተደነገገው ድንጋጌ መሠረት መሰረት ስለመሆኑ፡- | 136030 | ወ/ሮ ምስራ መሐመድ<br>እና<br>እነ አቶ አብደላ አሜ ( 2 ሰዎች) | ህዳር 20 2010 ዓ.ም | 282 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የንግድ ሕግ ቁጥር 561፣ 595 ፣596 ፣ 597 እና 599 | | | | |
| **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | | 287 |
| 55. | በተጎጂ ላይ ከደረሰ የሞት አደጋ የተነሳ በራሳቸው ስም ሆነው በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ የሚችሉት፤ የተጎጂ ባል ወይም ሚስት፤ ወይም ወላጆቹና ልጆቹ ብቻ እንጂ ወንድም ወይም እህት መጠየቅ ስላለመቻላቸው፡- የፍ/ብ/ህ/ቁ.2095/1/ | 134240 | አቶ ፍቃዱ በለጠ እና እነ ወ/ሮ አለሚቱ አድራሮ(4 ሰዎች) | መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም | 288 |
| 56. | የባንኮችን መልካም ስም፣ የአገልግሎት ብቃት፤ ታማኝነት እና የሥራ እንቅስቃሴን ሌሎች ሰዎች እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ ተግባር መፈጸም የፍትሐብሄር ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 2109 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | 137918 | የድሬደዋ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የዳሽን ባንክ አክሲዮን ማህበር | መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም | 293 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 57. | የመንግስት ተቋማት ሠራተኞቻቸውን የመቆጣጠር እና የመከታተል ግዴታቸውን ሳይፈጽሙ ቀርተው በተገልጋዮች ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ጉዳዩ አይመለከተንም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፡-<br><br>የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) እና 2127 (1) | 137589 | በደሴ ከተማ የአራዳ ክፍከተማ ገቢዎች ፅ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ዘይነባ ሰይድ (2ሰዎች) | ህዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም. | 298 |
| 58. | በግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መኪና በወቅቱ ተጠግኖ ወደ ስራ ቢመለስ በአደጋው ምክንያት የተቋረጠን የገቢ መጠን ለመቀነስ ወይም ለማቅለል በቅን ልቦናና በማስተዋል የተደረገ እንቅስቃሴ ከሌለ በደረሰ ጉዳት መጠን በሙሉ ካሳ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ፡-<br>በፍ/ብ/ህ/ቁ.2098 /1/፤2097(2) | 132017 | እነ አቶ ማቲያስ ወልደየስ (2 ሰዎች)<br>እና<br>አቶ መላኩ መኬ ማዶ | መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም | 303 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| ቤተሰብ | | | | | 309 |
| 59. | ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ፣ የግል ጠባይ ያለው እና በሟች ብቻ የሚፈፀም በመሆኑ ብዙ ሰዎችን አንድ በሆነ ፅሁፍ በጋራ ማናዘዝ የማይቻል እና ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስለመሆኑ፡-<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 857፣858 እና 880 | 134836 | አቶ አባተ ሀይሉ<br>እና<br>አቶ አስረስ ረታ (4 ሰዎች) | መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም | 310 |
| 60. | ባል እና ሚስት በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሬት ጋብቻው በአንደኛው ተጋቢ ሞት የተቋረጠ ቢሆንም ሌላኛው ተጋቢ በሌላ ህጋዊ ምክንያት መብቱ እስካልተቋረጠ ድረስ ይዞታው በስሙ ተመዝግቦ ደብተር ለማግኘት እና በይዞታው ለመጠቀም የሚችል ስለመሆኑ፣ ሴቶች መሬትን በመጠቀም፤በማስተላለፍ፤በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕ/መ አንቀጽ 35/7/፣ የኦሮሚያ የገጠር | 138286 | እነ ጫሉሜ ሙለታ<br>እና<br>ጫለሽ ቁልበሻ | መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም | 314 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መሬት አዋጅ ቁ. 130/99 አንቀጽ 6/3/ እና ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 15 | | | | |
| 61. | በነባር ይዞታ ላይ ያረፈ ንብረት በውርስ የሚተላለፍ እንደሆነ ወደ ሊዝ ስሪት ማስገባት የማይችል እና ለጉዳዩ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ተፈጻሚነት የሌለው ስለመሆኑ፡- | 131677 | የወ/ሮ ጌጤ ካሳ ወራሾች እና የኮ/ቀ ክ/ከ መሬትና አስተዳደር ጽ/ቤት | ጥቅምት 28 ቀን 2010 ዓ.ም | 318 |
| 62. | በጋብቻ በተሳሰሩ ባልና ሚስት መካከል ከአንዱ ጋር የውል ግዴታ የገባ ሰው በዋናው ክርክር ሁለቱን አጣምሮ ሊከስ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ እንዲሁም ተዋዋይ በሆነው ተጋቢ ላይ የተሰጠ ውሳኔ የተጋቢዎች የጋራ እዳ ነው ወይስ የተወሰነበት ተጋቢ የግል እዳ ነው የሚለው ክርክር ሊነሳ የሚችለው በአፈጻጸም ወቅት እንጂ ሌላኛው ተጋቢ ሊከሰስም ሆነ ሊፈረድበት ስላለመቻሉ፡- | 132518 | እነ ተኽሉ አስፍሃ(6 ሰዎች) እና እነ አቶ ስብሃቱ ገ/መስቀል(2 ሰዎች) | መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም | 323 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 63. | የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ለአፈፃፀም የቀረበ አከራካሪ የሆነ ቤት ሊካፈልም ሆነ ሊሸጥ የማይችል ሲሆን ሊካፈል የሚችለው በፐሮፖርሽን /በተነጻጻሪ ካርታ / ነው በማለት ባለሙያ አስተያየት በተሰጠበት ሁኔታ በዚሁ አግባብ ክፍፍሉ ሲደረግ የበለጠ ይዞታ የደረሰው ወገን ለሌላው ወገን ግምቱን እንዲከፍል በማድረግ መፈፀም የሚገባው እንጂ በፍርዱ በተቀመጠው ሌላ አማራጭ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም ማድረግ የማይገባ ስለመሆኑ፡- <br> የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 91(1)እና(2) | 141527 | አቶ እለፋቸው ታምሩ <br> እና <br> ወ/ሮ እመቤት ተሾመ | ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም | 329 |
| 64. | አንድ የንግድ ቤት በኪራይ የተሰጠው በትዳር ግንኙነት ወይም በጋብቻ ውስጥ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ከትዳር ግንኙነት በፊት መሆኑ ብቻ የንግድ ሱቅ ከጋብቻ በፊት የተገኘ የግል ንብረት ነው ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ፣ | 136872 | ህንጻ እስጢፋኖስ ሀይሉ <br> እና <br> ወ/ሮ ሸቱ ቦንገን | መስከረም 21 ቀን 2010 ዓ.ም | 333 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 65. | ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነትን ለማስረዳት የቀረበ ማስረጃ ግንኙነቱን የማሳየት ብቃት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ የግንኙነቱን ያለመኖር በማንሳት የሚከራከረው ሌላኛው ወገን በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ግንኙነት ስላለመኖሩና ንብረቶችም የግል ስለመሆናቸው የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 75/1995 117/4/ እና 114 እና 97<br>አንቀጽ 109፣110፣113 እና 117 | 126411 | አቶ ተስፋጊዮርጊስ አዳነ<br>እና<br>ወ/ሮ አሰፋ ግርማ | መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም | 336 |
| 66. | በፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ የጉዲፈቻ ውልን መሰረት በማድረግ ወራሽነትን ያረጋገጠ ወገን የውርስ ንብረት ድርሻን ለማግኘት ያቀረበው ጥያቄ ቀድሞ በጉዲፈቻ ውል የፀደቀበት ውሳኔ መብቴ ተነካ በሚል ወገን በቀረበ መቃወሚያ መሰረት እንዲፈርስ እንዲሻር ባልተደረገበት የውርስ ድርሻ ክፍያ ጥያቄው ውድቅ ማድረግ ህግን መሰረት ያላደረገ ስለመሆኑ | 137853 | በለጠ ነጋሽ<br>እና<br>እጅጋየሁ ላቀው | መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም | 341 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለ አንቀጽ 202. የፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ. 41፣358 | | | | |
| 67. | በውርስ የተላለፈን የመንግስት ንግድ ቤት የማከራየት መብትን ከወራሾች መካከል አንዱ ያለ ከተማ አስተዳደሩ እውቅና ያከራየ እንደሆነ ፤ የተከራይነት መብት የሚቋረጠው ያከራየው ወራሽን በተመለከተ ብቻ እንጂ ሌሎች እሱ በሞግዚትነት የሚያስተዳድራቸው ወራሾች የመከራየት መብታቸው የሚቀጥል ስለመሆኑና ፤አከራዩ ሞግዚታቸው ባከራያቸው ወገኖች ላይ በንግድ ቤት የኪራይ ውል መነሻነት ክስ ለማቅረብ የሚያበቃ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ፡- | 133736 | እነ አቶ መዚድ ተስፋዩ ( 2 ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ ዘይነባ ለካ | ታህሳስ 26 2010 ዓ.ም | 345 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 68. | የውርስ ሰርተፊኬት አንድ ሰው የራሱን ወራሽነት ለማስረዳት የሚወስደው ማስረጃ እንጂ ሌሎች ወራሾች አለመኖራቸውን የሚያሳይ ሰነድ ስላለመሆኑ፣ እና በግራ ቀኙ የሟች ወራሾች መሆናቸው በማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከማስረጃነት በዘለለ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ በሚያዘው መሰረት ከሌሎች ሰዎች ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ ያገኘና በፍርድ ያለቀ መቃወሚያ የማይቀርብበት ተደርጎ ሊወሰድ የማይገባ ስለመሆኑ፡- ፍ/ህ/ቁ. 996/1/ እና ተከታዬቹ | 130284 | እነ አቶ ክንፈ ሐጎስ /3ሰዎች/ እና ወ/ሮ ሃና ሐጎስ | ጥቅምት 30 ቀን 20010 ዓ.ም | 351 |
| 69. | በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ ጋብቻ በፍቺም ሆነ በሞት ምክንያት ሲፈርስ ንብረት የሚጣራበት አግባብ በውል ወይም በስምምነት ተለይቶ ባልተቀመጠበት ሁኔታ የባልና ሚስት ሀብት የሚጣራው በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 113 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ስለመሆኑ፡- ኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር | 137869 | ወ/ሮ ቦንሲቱ ዱፌራ እና ወ/ሮ ታምሪ ረጋሳ | ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም | 357 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | 83/96 እንደተሻሻለው አንቀጽ 93 | | | | |
| 70. | የጉዳት ካሳ ጥያቄ ከጋብቻ ፍቺ ጋር ተያይዞ የቀረበ በሆነበት እና ጉዳቱም የደረሰው ከፍቺው ጋር ተያያዞ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ጥያቄው የባልና ሚስት ፍቺን ተከትሎ ከሚነሳ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ጋር በአንድ ላይ ሊስተናገድ አይችልም በሚል የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ:-<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 84 | 135902 | ወ/ሮ መስከረም ጫካ-<br>እና<br>አቶ አክሊሉ ሽፈራው (2 ሰዎች) | መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም | 362 |
| ግብር | | | | | 367 |
| 71. | ከቀረጥ ነጻ መብትን በመጠቀም ወደ ሀገር የገባን እቃ ለመሸጥ ወይም ወደ ሌላ ለማስተላለፍ ከተፈለገ ቀድሞ ቀረጡን በመክፈል ነጻ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ:-<br>አዋጅ/ቁ 859/2006 አንቀጽ 30(1) | 138837 | እነ አቶ ብሩክ ገ/ሥላሴ (2 ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ዳዊት ተሰማ ቡታ | ጥር 23 ቀን 2010 | 368 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 72. | አንድ ኩባንያ በደረሰበት ችግር ምክንያት ከገበያ እንዳይወጣ እና ተወዳዳሪ መሆን እንዲችል ተሰጥቶት የነበረው የኪሣራ ማሸጋገር መብት፣ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተለወጠ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ኩባንያው አስቀድሞ ከነበረበት ኪሣራ ወጥቶ በተጨባጭ ያደገ መሆኑ የሚገመት ከሆነ በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉት የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት አስቀድሞ ተሰጥቶት የነበረው ኪሣራ የማካካስ መብት የሚቋረጥ ስለመሆኑ፡-አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28(1)(2) | 131900 | የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር | ጥቅምት 22/2010 ዓ.ም | 374 |
| 73. | አንድ ግብር ከፋይ ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ እንዲደረግለት ለንግድ ስራው ያወጣውን ወጪ ማስረዳት የሚችለው በሚያቀርበው በስሙ ወጪ በሆነ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ደረሰኝ ስለመሆኑ፤- | 139334 | የኢ/ገ/ጉ/ባለስልጣን እና ሻንዶንግ ሃይወይ ኢንጂነሪንግ | ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም. | 380 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 20 የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 22(2) ፤ደረሰኝ አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 28/2001 አንቀፅ 4(1) | | | | |
| | **አፈጻጸም** | | | 384 | |
| 74. | በሀራጅ አካሄድና ሽያጭ ስርዓት ተገቢ ያልሆነ ድርጊት፣ ማጭበርበር ወይም ማታለል መኖሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ ጨረታውን ለማፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ፣ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 445 | 136092 | ሙሉአለም ግዛው ወልዴ እና እነ ዙፋን ዘለቀ /2ሰዎች / | መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም | 385 |
| 75. | በአፈፃፀም ሂደት ንብረቴ አላግባብ ተሸጠ ወይም መብቴ ተጎዳ የሚል ሰው ፤ አቤቱታውን አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት ወይም አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ስህተት የፈፀመ ነው በማለት በይግባኝ እንዲታረም ማድረግ እንጂ የአፈፃፀሙ መዝገብ ከተዘጋ እና አመታት ካለፉ በኃላ መብቴ ይከበረልኝ በማለት አዲስ ክስ ማቅረብ የማይችል | 131084 | አቶ ጌታቸው ይርገቡስ እና እነ በላይ ናማጋ ( 3 ሰዎች) | 131084 | 389 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ፤<br>በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 404 እና 231(1) (ሀ) | | | | |
| ልዩ ልዩ | | | | | 394 |
| 76. | በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1) የተመለከተው የይርጋ ዘመን አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ እና ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የአስር ዓመት የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ፤<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1)፤1845 | 78629 | የአቶ ካሣ አበበ ወራሽ<br>አቶ ሰለሞን ካሣ<br>እና<br>ወ/ሮ አያልነሽ ስፍራ | ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም | 395 |
| 77. | ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሟል የሚል ክስ ለፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት ማቅረብና አስተዳደራዊ እርምጃና ቅጣት እንዲጣል የማድረግ ስልጣን ያለው የባለስልጣኑ ዓቃቤ ህግ ስለመሆኑ፣ | 128035 | ምስኪ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ቤካስ ኬሚካልስ ሀ/የተ/የግ/ማህበር | ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም | 401 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 813/2006 አንቀጽ 37/1 | | | | |
| 78. | ገንዘብ የተከፈለ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ወይም ደብዳቤ ሰነዱን ባዘጋጀዉ ወይም ደብዳቤዉን በፃፈዉ ሰዉ ላይ ማስረጃ የሚሆን ስለመሆኑ፡-<br>ፍ/ሕ /ቁ 2018(1) | 136245 | በደሌ ቢራ አ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ገብረመድህን ገ/ሕይወት | ጥር 23 ቀን 2010 | 406 |
| 79. | የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዥያ በማናቸዉም አይነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ከተጻፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰዉ ንብረት በሚገኝበት ሀገር ባለዉ በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ማንኛውንም አይነት ውጤት የማያስገኝ ስለመሆኑና ዕዳው እንዲከፈል በተወሰነበት ጊዜ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው የመያዣ መብት ያገኘበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይወስዳል የሚል ስምምነት ሁሉ ተቀባይነት የማይኖረዉ ስለመሆኑ፡-<br>ፍ/ሕ/ቁ 3052 እና 3060 | 135197 | አቶ ደለሳ ሌጅሳ<br>እና<br>እነ አቶ ፍቃዱ ጫላ -(2 ሰዎች) | ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም | 410 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 80. | ወጣት ጥፋተኞችን የተመለከቱ የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈጻጸም በተቻለ መጠን አጥፊውን በማረም መልካም ውጤት ሊያስገኝ በሚያስችል አግባብ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>ለወጣት ጥፋተኞች የሚያገለግል የጠባይ ማረሚያ ተቋም በሌለበት ፣ በወላጅ ቁጥጥር ስር ሆኖ የሚደረግ የባህሪ ሁኔታ ክትትል የተሻለ ውጤት እንደማይመጣ እና የጥፋተኛው አደገኛነት በተገቢው አግባብ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱ በአዋቂዎች እስር ቤት እንዲፈፀም የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፡-<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 168/2 | 136262 | የወ/ጉ/ክ/ ዐ/ህግ<br>እና<br>መህሪ ታደሰ | መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም | 416 |
| 81. | አንድ ቀድሞ በነበረ መመሪያ ዋጋ የወጣለትን ንብረት የተረከበ ወገን የንብረቱን መጥፋት ተከትሎ ክስ ሲመሰረት የንብረቱ ዋጋ በሌላ አዲስ መመርያ የተሻሻለበት ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ ንብረቱ የጠፋበት ወገን ተጠያቂ | 126529 | የሰቆጣ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት<br>እና<br>ቄስ ሙሉጌታ ተፈራ | ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም | 421 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚሆነው አዲስ በወጣው መመርያ መሠረት በወጣው የዋጋ ተመን አግባብ ስለመሆኑ፣ | | | | |
| 82. | በሁለት የህግ ሰውነት በተሰጣቸው አካላት መካከል የኢንቨስትመንት መሬት ያላግባብ ተይዞብኛል በሚል የሚነሳ ክርክርን በተመለከተ ክርክር ባስነሳው መሬት ላይ ግራ ቀኙ ያወጡት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የፌዴራል ከሆነ ጉዳያቸው ሊታይ የሚችለው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሲሆን፣ ፈቃድ ያገኙት ግን በክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ ከሆነ በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታይ ስለመሆኑ፤ እንዲሁም ከሁለቱ አንዱ ወገን የፌዴራል ተመዝጋቢ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6 መሠረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ የፌደራል ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 ፣የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 138/2000 | 13366 7 | ብዙአየሁ ሾኔ የቡና ተከል ልማት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ቢ.ዲ.ኤፍ.ኤስ ኢትዩጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ታህሳስ 24 2010 ዓ.ም | 425 |
| 83. | የድሬድዋ ከተማ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 416/96 | 134681 | ሳዲቅ አብዱሪህማን | ጥቅምት 21 | 431 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መሰረት የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ለማስፈፀም ሲባል ከይዞታ ባለቤትነት፣ ከፈቃድ አሰጣጥ እና ከቦታ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚነሱ ክርክሮችን ከማየት ባለፈ በእርሻ መሬት ባለይዞታነት ይገባኛል ጥያቄን መሰረት ያደረገ ክርክርን ለማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፡-<br>የአ/ቁ 416/1996 አንቀፅ 31(1) | | (ሰዎች)<br>እና<br>የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት | ቀን 2010 ዓ/ም | |
| 84. | በከተማ አስተዳደር ወይም በቀበሌ ያላግባብ የተያዘን የምርጫ ቤት ለማስመለስ የሚቀርብን ክስ የማየት ስልጣን በህግ ለሌላ የመንግስት አካል ባልተሰጠበት ሁኔታ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፡-<br>ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 37 | 137353 | ወ/ሮ አዛለች አጎናፍር<br>እና<br>ገብርኤል አካባቢ ቀበሌ ጽ/ቤት | ጥር 22 ቀን 2010 | 436 |
| 85. | አንድ የመንግስት ቤት ተከራይ የራሱ ቤት ካገኘ የመንግስት ቤትን በተከራይነት ይዞ መቀጠል የማይችል | 133309 | አቶ ለማ ማሙዬ<br>እና | ጥር 24 ቀን 2010 | 441 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ፡- መመሪያ ቁጥር 10/2006 አንቀፅ 15(2) | | በአዳማ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 12 ጽ/ቤት | | |
| 86. | በኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም ለረጅም ጊዜ በሌላ ሰው የተያዘና ጥቅም ላይ ሲውል የነበረን የገጠር መሬት የተያዘው ሕገወጥ ውልን መሰረት በማድረግ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ መሬቱ እንዲለቀቅ የሚቀርብ ክስ በአስራ ሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፣ የኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32 | 140538 | አቶ ወርቁ ታደሰ እና አቶ ጅራተ አፈልታ | መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም | 445 |
| 87. | የአ/ብ//ክ/መ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ “በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል” በሚል ተገልጸው የሚገኙት ድንጋጌዎች በይግባኝ ደረጃ ቀርበው ለመታዬት የማይችሉ የመጨረሻ ውሳኔዎች መሆናቸውን የሚገልጽ | 149962 | አቶ ስለሽ ዋለልኝ እና የአ/ብ/ክ/መ. ሥ/ምግባርና ፀረ ሙስና ኮምሽን ዐ/ህግ | መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ/ም | 449 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንጂ በሰበር ሰሚው ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ጉዳዮች ለማረም የሚቀርቡ ጉዳዮችን የሚጨምር ስላለመሆኑ፡- የአ/ብ//ክ/መ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር104/2004 አንቀጽ 75(3) | | | | |
| 88. | የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በህጉ አግባብ በሁለት ኢንዱስትሪዊ ንድፎች መካከል ተመሣሣይነት አለ ወይስ የለም የሚለውን ለመለየት የአከራካሪውን ንድፍ አዲስነት ለመወሰን የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ዋና ዋና ባህሪያት በመለየት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ ወይም ተመሳሳይነት ያለው ስለመሆኑ በዘርፉ ያለውን የዳበረ እውቀት እና ልምድ መሰረት በማድረግ ማጣራት አድርጎ ውሳኔ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ | 137939 | ፍፁም ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት | ጥቅምት 20/2010 | 454 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የአነስተኛ ፈጠራና ኢንዱስትሪ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(1)፤ 48(1) ፤ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 320/1995 | | | | |
| 89. | የአገልግሎት ድርጅት ያከራየ ወገን ያከራየው ድርጅት ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጥና ታሽጎ እንዲቆይ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረቡን ተከትሎ እግድ የተሰጠ በሆነበት እና ተከራዩም ከድርጅቱ ገቢ ባላገኘበት ሁኔታ ድርጅቱ ታሽጎ ለቆየበት ጊዜ ተከራይ የኪራይ ክፍያ እንዲከፍል የማይገደድ ስለመሆኑ፡- | 136024 | አቶ ቢልልኝ ጌታነህ እና አቶ ገብራይ ተከስተ | ጥቅምት ቀን 21 2010 ዓ.ም | 464 |

www.chilot.me

# ውል

www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ 127459

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ረታ ቶሎሳ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነአ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- ጣና የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር

- ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን - ዐ/ሕግ አብይ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 117051 የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ሚያዚያ 26 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ 06 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች በአድጁዲኬሽን የሙግት መፍቻ ዘዴ መዳኘት የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው አመልካች ለተጠሪ 12 ውሃ ጉድጓድና 2 የውሃ ጉድጓድ መቆጣጠሪያ ለመገንባት፤ ተጠሪ ደግሞ ብር 59,922,705 /ሃምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ አምስት ብር/ ለመክፈል ስምምነት

አድርገው እንደነበር በመግለፅ በተጠሪ ጥፋት የተነሳ ሥራው በስምምነቱ መሠረት ሊፈፀም ባለመቻሉ የውል ጊዜው ለተጨማሪ ስድስት ወራት እንዲራዘም፤ የዋጋ ለውጥ እንዲደረግ፤ ካሳና ወለድ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል በመጠየቅ የቀረበ ክስ ነበር፡፡

ተጠሪም በበኩላቸው ጥፋት አለመኖሩን፤ችግሩ የተፈጠረው በአመልካች የቴክኒክ ብቃት ችግር መሆኑን በመጥቀስ የካሳ ክፍያም ሆነ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲሆን መልስ አቅርቧል፡፡

ግራቀኙ ወገኖች አስቀድሞ ባደረጉት ውል አንቀጽ 24 መሠረት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት የተመደበው አድጁዲኬተር ጉዳዩን እንዲዳኝ ተደርጎ በሰጠው ውሳኔ ስለጉዳዩ ተገቢውን ማጣራት ሲያደርግ ቆይቶ አመልካች በጠየቁት መሠረት የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ በስድስት ወራት እንዲራዘም፤ተጠሪ ቅድመ ክፍያ ላዘገየበት ወለድ እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ይግባኝ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል መሆኑን ጠቅሶ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን በሚመለከቱ አለመግባባቶች የግልግል አካል ዳኝነት መስጠት እንዳይችል በህግ ክልከላ የተደረገ በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ አድጁድኬተር ጉዳዩን ያየው ስልጣን ሳይኖረው ነው የሚልና ሌሎች ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱ ቅሬታው መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሲያበቃ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል የአስተዳደር ውል ነው፡፡ የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የማይገባቸው ለመሆናቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 315(2) ደንግጓል፡፡ ስለሆነም አድጁዲኬተር ጉዳዩን ያያው በህግ በተከለከለ ጉዳይ ላይ በተደረገው ውል መነሻነት በመሆኑ ሥልጣን ሳይኖረው ነው በማለት የአድጁዲኬተሩን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ፡- አድጁዲኬሽን በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዓለም አለመግባባቶችን ለመፍታት ጠቃሚ የሆነና ከግልግል ዳኝነት የተለየ የአለመግባባት መፍቻ መንገድ ሆኖ እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

አድጁዲኬሽንን ከግልግል ዳኝነት ጋር በማመሳሰል የተያዘውን ጉዳይ አድጁዲኬተር ማየት አይችልም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው የሚሉና ሌሎችንም የቅሬታ ነጥቦች አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ በግራቀኙ ተከራካሪዎች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በውላቸው አንቀጽ 24 መሠረት በአድጁዲኬተር መታየቱ ያላግባብ ነው ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አድጁዲኬተር (ገላጋይ ዳኛ) የአስተዳደር ውልን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮችን ለመዳኘት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከመዝገብ ምርመራው መገንዘብ እንደተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል እ.አ.አ አፕሪል 06 ቀን 2013 የተደረገ ውል ለመኖሩ በግራቀኙ ወገኖች የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚሁ ውል አንቀጽ 24 ሥር አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አግባብ በተመለከተ አስቀድሞ በአድጁዲኬተር ወይም በገላጋይ ዳኛ ሊታይ እንደሚገባው፤ይህ ገላጋይ ዳኛም በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ሊመደብ የሚገባው መሆኑን እንዲሁም በገላጋይ ዳኛው ውሳኔ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ምን ሊሆን እንደሚገባ ጭምር ስምምነት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ሲሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነው የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮም ለህዝብ ጥቅም ለመስጠጥ የታሰበ በመሆኑ ውሉ ለህዝብ ጥቅም የተደረገ ውል መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3132(ለ) ሥር እንደተመለከተው ከህዝብ አግልግሎት ሥራ ጋር የተያያዙና ለውሉ አፈፃፀምም የተዋዋዩን የድሬዳዋ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ያልተቋረጠ ተካፋይነት የሚጠይቅ በመሆኑ ውሉ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪው ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል አስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ነው መባሉ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 315(2) ሥር በግልፅ እንደተመለከተው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ ህግ ክልከላ አድርጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አለመግባባትን ለመዳኘት በውል ሥልጣን የተሰጠው አድጁዲኬተር ወይም ገላጋይ ዳኛ ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 315(2) የአስተዳደር ውልን አስመልክቶ የሚነሳ አለመግባባትን ለመዳኘት የማይችለው የግልግል ዳኝነት አካል ወይም አርቢትሬተር ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ዋናው ነጥብ የአድጁዲኬተር እና የአርቢትሬተር አንድነትና ልዩነታቸው ምንድን ነው አርቢትሬተር የአስተዳደር ውሎችን እንዳይዳኝ በህግ ክልከላ ከተደረገበት ዓላማ አንፃር አድጁዲኬተር የአስተዳደር ውሎችን እንዲዳኝ ሊፈቀድለት ይገባል ወይ? ከዚህ አንፃር አመልካችና ተጠሪ ስለአለመግባባት አፈታት በውላቸው አንቀጽ 24 ያደረጉት ስምምነት በህግ ተቀባይነት ያለው ነው ማለት ይቻላል ወይ? የሚሉት ነጥቦች ናቸው፡፡

በመሠረቱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ የሆኑ የተለያዩ አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች እንዳሉ የሚታወቅ ነው፡፡ ከእነዚህ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስልቶች ውስጥ በአገራችን የሥነ ሥርዓት ህግ ዕውቅና ያገኙት ድርድር፤እርቅ፤ግልግል እና ስምምነት ሲሆኑ አድጁዲኬሽ ወይም ጉዳዩን በገላጋይ ዳኛ የመፍታት አሰራር በብዙ የዓለም ሀገሮች የሚሰራበት ከመሆኑም በላይ በንግዱ ህብረተሰብ መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በኩል ደንብ ወጥቶለት እየተሰራበት ይገኛል፡፡

አለመግባባት የተፈጠረበትን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ሂደት አድጁዲኬሽን እንደሚባል የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባወጣው ደንብ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከተ ሲሆን ግልግል በግራቀኙ ወገኖች መካከል የሚፈፀም ውል ሲሆን ውሉን መሠረት በማድረግ የግልግል ዳኛ የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅ ውጤት እንዳለው ከፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 3325 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ ስለ ሁለቱ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች አንድነት ስንመለከት ውሳኔው አስገዳጅነት ያለው መሆኑ እና ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ በሆነ ሁኔታ አለመግባባት የሚፈታባቸው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 315(2) ድንጋጌ በግልግል የዳኝነት ሥርዓት የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች ሊዳኙ እንደማይገባ የደነገገበት አግባብ ፍትህ ከአማራጭ የሙግት መፍቻ የሚገኝ መሆኑን በመዘንጋት ሳይሆን የአስተዳደር ውሎች ጉዳይ የህግ የበላይነትን መርህ በአደረገው መደበኛ ፍርድ ቤት መታየቱ በውሎቹ ሊደረስበት የታሰበውን ዓላማ ለማሳካት እንደሚያስችል ታምኖበት የተወሰደ የመንግስት ፖሊሲ አማራጭ እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች የራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ ያላቸው የመሆኑን ያህል የጎንዮሽ ጉዳትም ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ ይገባል፡፡ በተለይም በአገራችን ሥርዓት ተበጅቶላቸው በጠነከረ አኳኋን የሚመሩ የመንግስትንና ህዝብን ጥቅም ሊያስጠብቁ የሚችሉ የተሟላ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የተሰጣቸው አማራጭ ሙግት መፍቻ ተቋማት ከአለመጠናከራቸው አንፃር የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት አካል እንዳይታዩ ህግ አውጭው አካል ለመምረጡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 315 ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡

የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የማይገቡ ስለመሆኑ በህግ ከተመለከተና ዓላማውም የህግ የበላይነትን ለማስከበር ህግ አውጭው ለአስተዳደር ውሎች ዳኝነት የመረጠው ስለመሆኑ ግንዛቤ ከተወሰደ አድጁዲኬተር ማለትም የአርቢትሬተር ዓይነት አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጥ አካል የአስተዳደር ውሎችን እንዲዳኝ የሚያስችሉ ስምምነቶች የህግ ውጤታቸው ምን ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ ምላሽ መስጠት ይጠይቃል፡፡ አርቢትሬተር የአስተዳደር ውሎችን በተመለከተ መዳኘት የማይችል ከሆነ አድጁዲኬተር ከሚሰጠው የዳኝነት ባህሪ አንፃር የአስተዳደር ውሎችን ሊዳኝ የሚችል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አድጁዲኬተርም ሆነ አርቢትሬተር አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጡ አማራጭ የሙግት መፍቻ አካላት ስለሆኑ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አድጁዲኬተር ከአርቢትሬተር የተለየ አማራጭ የሙግት መፍቻ ተቋም ተደርጎ ሊወሰድ ስለማይችል የሥር ፍርድ ቤቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ ውል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል በመሆኑ በገላጋይ ዳኛ እንዲታይ ህጉ አይፈቅድም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 315(2)ን፣የፍትሐ ብሔር ህጉን አንቀጽ 1678(ለ) 3131፣3132(ለ) ያገናዘበ በመሆኑ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡

ለማጠቃለል ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነውን ዳኝነት የሰጠው ገላጋይ ዳኛ በተያዘው ጉዳይ ላይ የመወሰን ስልጣን የሌለው ነው፡፡ ገላጋይ ዳኛ ሥልጣን አልነበረውም የሚል ድምዳሜ ላይ ከተደረሰ በአመልካች በኩል የሚቀርቡ ሌሎች የቅሬታ ነጥቦችን በጭብጥነት ይዞ መወሰን ተገቢ አይሆንም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 117051 የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

2. የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን አስመልክቶ የሚነሳ አለመግባባትን አይቶ ለመወሰን ገላጋይ ዳኛ (Adjudicator) ሥልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡተዘግቷል፤ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ/ - 124725

**ቀን** - 29/02/2010

ዳኞች፡-

ዳኜ መላኩ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች**፡- የሽሬ እንደስላሴ አንዋር መስጊድ-አልቀረበም

**ተጠሪዎች**፡- 1. ወ/ሮ ትኑር ፍትዊ

2. አቶ አደም ዓብደልባቂ

3. አቶ ስራጅ ዓብደልባቂ

4. ወ/ሮ ዘቢባ ዓብደልባቂ

5. ወ/ሮ ሰትኑር ዓብደልባቂ

(1-5) አልቀረቡም

6. አቶ ኑርሁሴን ዓብደልባቂ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በትግራይ ክልል ሽሬ እንደስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ እና የተከሳሽ ከሳሽ እንዲሁም 2ኛ-6ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ ገቦች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘትም በአጭሩ፡- ከአመልካች ጋር በ25/08/98 ዓ.ም ሽያጭ እና የልዉጫ ዉል አመልካች ቤትና ይዞታ በብር 175,000.00 ገዝቶ ብር 20,000.00 ቀብድ ከፍሎ ቀሪዉን ገንዘብ ባለመክፈሉ እና ልዉጫዉንም በዉሉ መሠረት ባለመፈጸሙ፣ ቀሪዉን ብር 155,000.00 እንዲከፍል እና በልዉጫ ዉሉ መሠረትም ቤቱን እና ቦታዉን የሚመለከቱ ማስረጃዎችን እንዲያስረክቡኝ፤ ዉሉ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ካለም አመልካች ቀብድ ተቀጥተዉ ግራ ቀኝ ከዉሉ በፊት ወደ ነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካች በበኩሉ በስሙ ዉሉን ያደረጉት ሀጂ ዑስማን ዓብዱልቃዲር አመልካችን ወክለዉ ዉሉን ለማድረግ የሚያስችል ዉክልና የሌላቸዉ በመሆኑ በ1998 ዓ.ም ተደረገ በተባለዉ ዉል የማይገደድ መሆኑን፤ በቀን 16/03/2000 ዓ.ም ከተጠሪዎች ጋር ተደርጎ በዞን ፍትሕ መምሪያ በጸደቀዉ ዉል በክሱ የተመለከተዉን ቤትና ቦታ አመልካች በብር 20,000.00 ገዝቶ ቤትና ቦታዉ ተላልፎለት ግብር እየገበረበት በመሆኑ ዉሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የ1ኛ ተጠሪ ክስ ዉድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡ በበኩሉ ባቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ፣ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገ ዉል መሠረት ከተጠሪዎች ገዝቶ ሳይት ፕላን በስሙ ተሰርቶለት ግብር የሚከፍልበትን ቤትና ቦታ ተጠሪዎች እንዲለቁለት ማስጠንቀቂያ የሰጣቸዉ ቢሆንም ለመልቀቅ ፍቃደኛ ባለመሆናቸዉ ቤትና ቦታዉን ለቀዉ እንዲያስረክቡት ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ፤ በ1998 ዓ.ም በተፈረመ ዉል መሠረት የሽያጭ እና የልዉጫ ዉል በብር 175,000.00 ዋጋ ተስማምተዉ ብር 20,000.00 ቀብድ ተከፍሎአቸዉ ቀሪዉ ብር 155,000.00 ሲከፈል የቦታ ርክክብ እንደሚፈጸም ተስማምተዉ እያለ በዉልና ማስረጃ በብር 20,000.00 ብቻ እንደተስማሙ ተደርጎ መገለጹ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በተንኮል የተደረገ መሆኑን፣ የመኖሪያ ቦታን በኃይማኖት ቦታ መለወጥ በህግ የተከለከለ መሆኑን በመግለጽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ዉድቅ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡ ከ2-6ኛ ያሉት ተጠሪዎችም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በክርክሩ ጣልቃ በመግባት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር በማንሳት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኝ በዚህ መልኩ ያቀረቡትን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፤ በ25/08/98 ዓ.ም የተደረገዉ ዉል ሐጂ ዑስማን ዓብዱልቃዲር ህጋዊ ዉክልና ሳይኖራቸዉ ያደረጉ በመሆኑ አመልካችን ሊያስገድድ አይችልም፡፡ በቀን 25/08/98 ዓ.ም የተደረገ የሽያጭ እና የልዉጫ ዉል ዋጋዉ ብር 175,000.00 ሆኖ አመልካች ለተጠሪዎች ብር 20,000.00 ሆኖ በዉልና ማስረጃ ስጸድቅ ዋጋዉ ብር 20,000.00 ብቻ እንደሆነ የተገለጸዉ የስመ ሀብት ዝዉዉር በሚፈጸምበት ጊዜ ለመንግስት የሚከፈሉትን የተለያዩ ክፍያዎችን ለመቀነስ ሲባል መሆኑ፣ እንዲሁም አመልካች ቤት እና ቦታዉን የገዛዉ ለማምለኪያ ስፍራ መሆኑ በመረጋገጡ ዉሉ ህጋዊ አይደለም፡፡ በመሆኑም ዉሉ ፈርሶ ተጠሪዎች ብር 20,000.00 የተቀበሉትን ለአመልካች እንዲመልሱ እንዲሁም የቤቱና የይዞታዉ ስመ ሀብት በተጠሪዎች ሆኖ ሳይት ፕላን እንዲሰራላቸዉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለሰ/ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ዉሉ ሊፈርስ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ያመለከተዉን ቤትና ቦታ ተጠሪዎች ለቀዉ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ ዉሉ ፈራሽ ነዉ በማለት በወረዳዉ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የወሰነ ሲሆን፣ አመልካቾች ይህን ዉሳኔ ለማስለወጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በቅደም ተከተል የሰጡትን ዉሳኔ እና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 05/07/08 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በተወካዩ አማካይነት በቀረበ 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የሽያጭ እና የልዉጫ ዉል ፈራሽ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ መሠረት የሌለዉ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ማረም ሲገባዉ የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል የሰጠዉ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ዉሉ እንዲፈርስ በስር ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸዉ 1ኛ ተጠሪ ለብቻ፣ 2ኛ-5ኛ ተጠሪዎች በአንድነት በቀን 04/09/08 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ባቀረቡት መልስ፤ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤትና ቦታ በብር 175,000.00 ለመግዛት ተስማምተዉ በቅድሚያ ብር 20,000.00 ከፍሎ ቀሪዉን ብር 155,000.00 ከህዝብ ሰብስቦ እንደሚከፍላቸዉ ተስማምተዉ ግን ስመ ሀብቱን ለማዛወር የሚከፈሉትን ክፍያዎች ለመቀነስ በሚል ሃሳብ ብር 20,000.00 እንዲሆን መደረጉ ዉሉ በተንኮል የተደረገ መሆኑን የሚሳይ ከመሆኑም በላይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሻጭ ወደ ገዥ ሲተላለፍ የሚከፈሉ ክፍያዎች ጋር በተመለከተ ከወጡ ህጎች እንዲሁም መኖሪያ ቤትን ለመስጊድ መሸጥም ሆነ መለወጥን ከሚከለክለዉ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና የክልሉ ደንብ ቁጥር 62/2002ን የሚፃረር በመሆኑ ዉሉ እንዲፈርስ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ መሆኑን ገልጸዉ ፀንቶ እንዲወሰንላቸዉ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ያቀረበዉ የመልስ መልስም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አለ? ወይስ የለም? የሚለዉ ጭብጥ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል በግራ ቀኝ መካከል ስለመደረጉ ግራ ቀኝ አልተካካዱም፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት፣ ለዉሉ መነሻ የሆነዉን ቤት ለአመልካች የሸጡት በብር 175,000.00 ሆኖ ብር 20,000.00 ቀብድ የተሰጣቸዉ መሆኑን ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ቤቱ የተሸጠዉ በብር 175,000.00 ሳይሆን በብር 20,000.00 መሆኑን እና ገንዘቡንም ከፍሎ የቤቱ ስመ ሀብት በስሙ ተመዝግቦ ሳይት ፕላን ተሰጥቶት በስሙ ግብር ሲከፍልበት የነበረ መሆኑን በመግለጽ ይከራከራል፡፡ በግራ ቀኝ መካከል በጽሁፍ ተደርጎ በቁጥር 319/02/2000 በቀን 16/03/2000 በሰ/ምዕራብ ዞን ፍትሕ መምሪያ ጽ/ቤት መጽደቁ የተረጋገጠዉ ዉል ለክርክር መነሻ የሆነዉን ቤት እና ቦታ አመልካች የገዛበት ዋጋ ብር 20,000.00 መሆኑን እንደሚያሳይ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል

የጽሑፍ ሰነድ በላዩ ስለሚገኘዉ የስምምነት ቃል ሙሉ እምነት የሚጣልበት መሆኑን እና የሰዉ ወይም ሌላ የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል እንደማይቻል በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2005(1) እና 2006(2) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በግራ ቀኝ መካከል በጽሑፍ ተደርጎ ዉል እና ማስረጃን ለማጽደቅ በህግ ስልጣን በተሰጠዉ በዞኑ ፍትሕ መምሪያ በፀደቀ ዉል ላይ የተመለከተዉ ዋጋ ብር 20000.00 ሆኖ እያለ፣ ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎችን በመስማት ዋጋዉ ብር 175,000.00 ሆኖ ብር 20,000.00 ተብሎ እንዲመዘገብ የተደረገዉ በስመ ሀብት ዝዉዉር ሂደት ሊከፈል የሚችል ክፍያን ለመቀነስ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌ ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ዉሉ እንዲፈርስ ከመደረጉ ጋር በተያያዘ ወደ ተያዘዉ ጭብጥ ስንመለስ፤ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሉ እንዲፈርስ ለመወሰን በምክንያትነት ከጠቀሷቸዉ ነጥቦች ዉስጥ አንዱ የዉሉ ዋጋ ብር 175000.00 ሆኖ እያለ በዞኑ ፍትሕ መምሪያ በፀደቀዉ የዉል ሰነዱ ላይ ብር 20000.00 ተብሎ የተገለጸዉ በስም ማዛወር ሂደት ሊከፈል የሚገባዉን ገንዘብ ለመቀነስ እና አመልካች ቀሪዉን ገንዘብ ብር 155000.00 ርክክቡ በሚፈጸምበት ወቅት እንደሚከፍላቸዉ አመልካች ቃል በመግባቱ አምኖ እንደፈረሙ እና ብር 20000.00 መሆኑን ቢያዉቁ ኖሮ ዉሉን እንደማይፈርሙ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር መሠረት በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ ነዉ፡፡ በርግጥ ተንኮል ለዉል መፍረስ ምክንያት ሊሆን የሚችል ሲሆን፣ ይህም የሚሆነዉ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ አንዱ ተዋዋይ ዉሉን እንደማያደርግ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 1704 ስር ተመልክቷል፡፡ ይሁንና በግራ ቀኝ መካከል በጽሑፍ ተደርጎ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ቀርቦ የፀደቀዉ ዉል ይዘቱ የሚያሳየዉ ግራ ቀኝ ወደዉ እና ፈቅደዉ የዉሉ ዋጋ ብር 20000.00 በመሆኑ ላይ ተስማምተዉ እንደሆነ የሚያሳየዉ የጽሑፍ ሰነድ እምነት የሚጣልበት ነዉ፤ ከፍ ሲል በተመለከተዉ ምክንያት ይዘቱን በሌላ ማስረጃ ማስተባበል አይቻልም፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ዉል በተንኮል የተደረገ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይሆንም፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች በተለይም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሉ ፈራሽ ነዉ ለማለት የቻለበት ሁለተኛዉ ምክንያት ዉሉ ህገ ወጥ እንደሆነ በመግለጽ ነዉ፡፡ በርግጥ ህገ ወጥ ዉሎች

ህጋዊ ዉጤት እንደማያስከትሉ እና ፈራሽ መሆናቸዉ በህጉ አንቀጽ 1716 ስር ተደንግጓል፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሉ ህገ ወጥ ነዉ ለማለት የጠቀሰዉ አንዱ ምክንያት፣ አመልካች ለአምልኮ የሚሆን ቦታ ከግለሰቦች መግዛት እንደማይችል በመግለጽ ሲሆን፣ ይህን የሚከለክል ህግ የትኛዉ እንደሆነ ግን አልጠቀሰም፤ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና አዋጁን ለማስፈጸም በክልሉ የወጣዉን ደንብ በመጥቀስ ተጠሪዎች የሚከራከር ቢሆንም እነዚህ ህጎች የአምልኮ ቦታዎች በመንግስት የሚሰጡ መሆናቸዉን ቢደነግጉም አንድ የኃይማኖት ተቋም የማምለኪያ ቦታን ከግለሰቦች እንዳይገዛ በግልጽ ክልከላ አያደርጉም፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሉ ህገ ወጥ ነዉ ለማለት የጠቀሰዉ ሁለተኛ ምክንያት፣ ዉሉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ሀብትን ከገዥዉ ወደ ሻጩ በማስተላለፍ ሂደት ሊከፈሉ ከሚገባቸዉ ክፍያዎች ጋር በተያያዘ ከወጡት አዋጆች ጋር የሚፃረር መሆኑን ነዉ፡፡ ተጠሪዎችም በዚሁ ችሎት ባቀረቡት ክርክር ይህንኑን በማጠናከር ይከራከራሉ፡፡ በሌላ በኩል አንድ ዉል ህገ ወጥ ነዉ በሚል ምክንያት ፈራሽ የሚሆነዉ፣ የዉሉ መሠረት የሆነዉ መብትና ግዴታ (the object of the contract) በህግ በተከለከለ ነገር ላይ መደረጉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከህጉ አንቀጽ 1716 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ስመ ሀብት ለማስተላለፍ ሊከፈሉ የሚገባቸዉን ክፍያዎች በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎች፣ ተዋዋይ ወገኖች በሚያደርጓቸዉ የሽያጭ ዉሎች ላይ ስለሚወስኗቸዉ መብትና ግዴታዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡ ይህ በመሆኑም፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ ግራ ቀኝ የዉሉ ዋጋ ብር 20000.00 ሊሆን የቻለዉ ስመ ሀብትን ለማዘዋወር የሚከፈለዉን ክፍያ ለመቀነስ ሲባል ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቢረጋገጥ እንኳን በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉን ዉል ፈራሽ የማድረግ ዉጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡

ለማጠቃለል፣ ከፍ ሲል በዝርዝር ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ፣ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሉ ፈራሽ ነዉ በማለት በሽሬ እንደስላሴ ወረዳ ተወስኖ የነበረዉን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ ዉል ፈራሽ የሚሆንባቸዉን ምክንያቶች በተመለከተ በህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ፣ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሲሆን፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር

ሰሚ ችሎትም ይህን ማረም ሲገባዉ አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል የሰጠዉ ትዕዛዝ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/78476 ላይ የሽሬ እንደስላሴ ወረዳዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/81259 በቀን 20/05/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የሰ/ምዕራብ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/20471 በቀን 06/01/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. በአጣሪ ችሎት በቀን 20/07/08 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ.131151

ታህሳስ 25 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካቾች - 1ኛ. አቶ ከፍያለው አየለ ከጠበቃ ብውድነሽ ማሞ ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ አሰገደች መኮንን

ተጠሪዎች - 1ኛ. ወ/ሮ ወርቅነሽ በላይ - ተወካይ ጉደታ ቶልቻ ቀረቡ

2ኛ. አቶ ቶልቻ ባልቻ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 103817 መጋቢት 8/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን እንዲሁም ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 172804 ሰኔ 14/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልን በሚል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

አመልካቾች ጥቅምት 5/2008 ዓ.ም ያቀረቡት የተሻሻለ የክስ ማመልከቻ ይዘት፡- ከተጠሪዎች ጋር ህዳር 22/1997 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር 1352 ከሆነው የተጠሪዎች መኖሪያ ቤት ላይ በ 130 ካ.ሜ ይዞታ ያረፈ ሰርቪስ ቤታቸውን በብር 70.000.00 ሸጠውልን ለዚህ ለተሸጠው ቤት ይዞታ ማረጋገጫውን አስቆርጠው እንዲሰጡን የጠየቅን ቢሆንም ፍቃደኛ ስላልሆኑ በሸጡልን ይዞታ ልክ ካርታውን አስቆርጠው ስም እንዲያዛውሩ እንዲወሰን እና የገደብ መቀጮ በውሉ መሰረት ብር 10000.00 (አስር ሺህ) እንዲከፍሉ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ ባቀረቡት መቃወሚያ ውሉ የተደረገው ህዳር 22 ቀን 1997 ዓ.ም በመሆኑና ውሉን መሰረት በማድረግ ክስ የቀረበው ከ10 ዓመት በኋላ ጥቅምት 5/2008 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ብለዋል፤ በአማራጭም መልስ አቅርበዋል።
የሥር ፍርድ ቤት መቃወሚያውን በተመለከተ የቀረበውን ክርክር ከመረመረ በኋላ ውሉን መሰረት በማድረግ የሚቀርብ ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ሲሆን አመልካቾች ክስ ያቀረቡት 10 ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል። አመልካቾች ይህን በመቃወም ቅሬታቸውን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ብይኑ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት አልተገኘም ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙ ተሰርዟል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካቾች ሀምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን አመልካቾች መብታቸውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ነው፤ ይህ ጊዜ ደግሞ ተጠሪዎች ካርታ ያሰሩበት ጊዜ ነው፤ ምክንያቱም አመልካቾች ንብረቱ በእጃችን ስለሚገኝ እና ጥያቄያችንም እንደውሉ ቤት ያስረክቡን ሳይሆን ለይዞታው ማረጋገጫ የሆነውን ካርታ ከራሳቸው ካርታ ጋር ጠቅልለው ስላሰሩት በሽያጭ ስላስተላለፉልን በ130 ካ.ሜ ላይ ያረፈ ሰርቪስ ቤትና ይዞታ እንዲያስቆርጡ የሚል በመሆኑ፤ አመልካቾችም ይህን ለመጠየቅ የምንችለው ተጠሪዎች ካርታውን ካሰሩ በኋላ በመሆኑ እና ውል በፈፀምንበት ጊዜ ይዞታቸው ሰነድ አልባ በመሆኑ ካርታ አስቆርጡልን ብለን መጠየቅ የማንችል በመሆኑ ይርጋው መቆጠር ያለበት ተጠሪዎች ካርታ ካሰሩበት ጥር 4 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ መሆን ሲገባው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምረው ቆጥረው ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ይታረምልን ብለዋል።

የሰበር ማመልከቻው ተመርምሮ ውሉ ከተደረገ 10 ዓመት ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። ተጠሪዎች ሚያዚያ 12 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጡት መልስ ጊዜው መቆጠር ያለበት ተጠሪዎች ለይዞታው ካርታ ከወሰዱ ጊዜ

ጀምሮ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ካርታው ከተሰራ ጀምሮ ነው ቢባል እንኳ ካርታ ከተሰራ ጀምሮ ክስ እስከቀረበ ድረስ ያለው ጊዜ 10 ዓመት የሚያልፈው በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ብይን ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም በይርጋው ጉዳይ ላይ መከራከሪያቸውን ከስር ጀምሮ ማቅረባቸውንና የይርጋ ጊዜው እንዳላለፈ በመግለፅ ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካቾች በሰርቪስ ቤት ሽያጭ ውሉ መሰረት ንብረቱን ተረክበው በእጃቸው እንደሚገኝ ገልፀው ይዞታው ሰነድ አልባ እንደነበርና ተጠሪዎች አጠቃለው ካርታ ያወጡት ጥር 4 ቀን 1998 ዓ.ም በመሆኑ ለተሸጠው ቤት ይዞታ ማረጋገጫውን አስቆርጠው እንዲሰጧቸው ላቀረቡት ክስ ይርጋው መታሰብ ያለበት ተጠሪዎች ካርታ ካሰሩበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ውሉ ከተደረገበት ህዳር 22/1997 ዓ.ም ጀምሮ ሊሆን አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው ይህ ክርክር በሥር ፍርድ ቤት አለመነሳቱንና ካርታ ከተሰራ ጀምሮ ያለው ጊዜም ቢታሰብ ክስ የቀረበው የይርጋ ጊዜው ካለፈ በኋላ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1846 ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ለክሱ የይርጋ መቃወሚያ በቀረበ ጊዜም ፍርድ ቤቱ የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምርበትን ቀን በአግባቡ በመለየት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ካርታ ያወጡት ጥር 4 ቀን 1998 ዓ.ም መሆኑ እና ውል በተደረገ ጊዜ ይዞታው ሰነድ አልባ እንደነበር ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ ካርታው ከመውጣቱ በፊት ለይዞታው ተጠሪዎች አጠቃለው ካርታ አውጥተዋል በተሸጠልን ይዞታ ልክ ካርታውን አስቆርጠው ስም እንዲያዛውሩ ይወሰንልን ብለው ሊከሱ የሚችሉበትና ዳኝነት የሚጠይቁበት ምክንያት አልነበረም፡፡

ተጠሪዎች ካርታ ካወጡበት ጥር 4 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት ክሱ ቢቀርብ ኖሮ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስላለመሆኑ ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ካርታ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ነሐሴ 18/2007 ዓ.ም እንዲሁም ክሱ ተሻሽሎ እስከቀረበበት ጥቅምት 5/2008 ዓ.ም ድረስ ሲሰላ የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜው አልፏል የሚባል ሆኖም አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ይርጋው መቆጠር ያለበት ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት በማለት ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት ያሳለፉት ብይንና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 103817 መጋቢት 8 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 172804 ሰኔ 14/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካቾች የቀረበው ክስ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው የቤት ሽያጭ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ህዳር 22/1997 ዓ.ም ሳይሆን ተጠሪዎች ካርታ ካወጡበት ጥር 4/1998 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑና አመልካቾችም በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት ነሐሴ 18/2007 ዓ.ም በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት የይርጋው ጊዜ ያለፈበት አይደለም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የኮ/መ/ቁ 103817 በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ቀሪ ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ /ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ካ/የ

የሰ/መ/ቁጥር 141606

ቀን 25/01/2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ረታ ቶሎሳ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች ፡- አቶ ማሞ ቱሉ ቀርቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አበበ አበራ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቤትና ቦታ ክርክር ሲሆን የጀመረው በኦሮሚያ ክልል የሙሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው ፡፡ በሥር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በ28/04/2009 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በቃል ውል የቤትና ቦታ ሽያጭ አድርገው አመልካች ብር 30,000 ለመክፈል የተሰማሙ ቢሆንም ገንዘቡን አልከፈሉም፡፡ በመሆኑም አመልካች የሽያጭ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ወይም ቤቱን ለቀው እንዲያስክቧቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2. የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ከተጠሪ ቤት እንዳልገዙ ነገር ግን በ2002 ዓ.ም ባዶ ቦታ በብር 13,000.00 የገዙ ስለመሆኑ በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡
3. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የስር ወረዳ ፍርድ ቤት የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ሕ/ቁ 1723 መሰረት ካለመደረጉ በተጨማሪ የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች ሸጡት የተባለው ቤት ሳይሆን ቦዶ መሬት በመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) እና በፍ/ህ/ቁ

1808(2) መሰረት ውሉ በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የሽያጭ ተግባር ከመከናወኑ በፊት ወደ ነበሩበት ይመለሱ፡፡ በዚህም ተጠሪ የተቀበሉት ብር 13,000.00 እንዲመልሱ ፤ አመልካች ደግሞ ገዛሁት ባሉት ይዞታ ላይ ያላቸው ንብረት ሁሉ በማንሳት መሬቱን ለተጠሪ ይልቀቁ በማለት ወስኗል ፡፡

አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

4. አመልካች በ9/09/2009 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም፡- የከተማ ቦታ መግዛት የሚከላከል ህግ እንደሌለ፤ የተጠሪ ክስ ከሁለት ዓመት በኋላ እንደቀረበ፤ ቤቱን ለመሰራት ወጪ ማውጣታቸውን ገልጸው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ እንዲሻር መጠየቃቸውን ያሳያል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከጠየቀው ዳኝነት አኳያ አመልካች ቤቱን አፍርሰህ ሄድ የመባሉ አግባብነት ከፍ/ህ/ቁ 1178 እና ተከታዮቹ አኳያ ጉዳዩን ተጠሪ ባሉበት ማጣራት ይቻላል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በ16/10/2009 ዓ.ም የጽሑፍ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ዋና ይዘቱም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ የሚነቀፍ ነጥብ የለውም የሚል ክርክር ማቅረቡን ያሳያል፡፡ አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2009 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡

5. የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለው መርምረናል ፡፡

6. እንደመረመርነውም፡- በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተደረገው ሽያጭ ውል በባዶ መሬት ላይ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመከላከያ መልስም ከተጠሪ የገዙት ቤት ሳይሆን ባዶ መሬት ስለመሆኑ በግልጽ አምነው ተከራክሯል፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ ተደረገ የተባለው የማይቀሳቀስ

ንብረት ሽያጭ ውል በቃል ብቻ ስለመደረጉም ግራቀኙ አልተካከዱም፡፡ በመሰረቱ ግራቀኙ ያደረጉት የሽያጭ ውል በባዶ መሬት ላይ ከሆነ ህጋዊ ውጤቱ ምንድነው? የሚለው ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) እና የፍ/ህ/ቁ 1678(ለ) እና 1716(1) ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ያደረጉት የመሬት ሽያጭ ውል ሕገ መንግስቱን በሚቀረን መልኩ የፈፀሙት በመሆኑ በሕግ ፊት የማይጸና ነው፡፡ አመልካች ባዶ መሬት በመግዛት የሰሩት ቤት ካለም በተጠሪ ፈቃድ እንደተሰራ ተቆጥሮ ህገወጥ የመሬት ሽያጭ ውል በውጤቱ ህጋዊ የሚሆንበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ከፍ/ሕ/ቁ 1178 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አኳያ እንዲመረመር ያቀረበው ቢሆንም የውለታው መነሻ ህገወጥ የመሬት ሽጭ ከመሆኑ አንፃር አመልካች ቤቱን በተጠሪ ፈቃድ የሰራው ነው ተብሎ የህግ ግምት የሚወሰድበት ሥርዓት አይኖርም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ውለታው ፈራሽ ነው ግራቀኙ ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል ፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሙሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 07958 በ22/07/2009 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 29090 በ28/07/2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፤የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 262665 በ08/09/2009 ዓ.ም ሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ ፡፡

## ተጨማሪ ትዕዛዝ

በዚህ ችሎት ሰኔ 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰ/መ/ቁ.130676

ጥቅምት 27ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች- ዳኜ መላኩ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካች - ጅቡቲ ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ 3-ለ የደ/ጭ/ማ/ባ/ማህበር ጠ/ግርማ ስላሴ አርአያ ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ሞላ ደርጎ ከደነው ጠበቃ /ሳሙኤል አስፋው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 22591 መጋቢት 6/2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 176735 ሰኔ 23/2008 ዓ.ም የፀናውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ባደረጉት ውል ንብረትነቱ የአረብ ኮንስትራክሽን የሆነ አንድ ኮንቴነር ከጅቡቲ ወደብ ወደ ይርጋ ጨፌ እንዲያጓጉዝላቸው በተስማሙት መሰረት ከሳሽ አጓጉዣ አስረክቤያለሁ፤ ተከሳሽ ይህን ያዘዘው በ16/04/07 ዓ.ም ሲሆን በቀን 29/05/07 ዓ.ም በርክክብ ሰነዱ ላይ ፈርሞ የክፍያ ቀጠሮ ሰጥቷል፤ ነገር ግን ክፍያ ለመፈፀም ፈቃደኛ ስላልሆነ ጭነቱ ለተጓጓዘበት ለ300 ኩንታል በብር 150.00 ሂሳብ ብር 450.00.00፣ ኮንቴነር መመለሻ ብር 8.000.00፤ እና ጭነት ለዘገየበት ዲመሬጅ ክፍያ ብር 20.400.00፤ በአጠቃላይ ብር 73,400.00 (ሰባ ሶስት ሺህ አራት መቶ) ከነወለዱ እንዲከፍል እንዲወሰን መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ከሳሽ ዕቃዎቹን ከጂቡቲ ወደብ ለማጓጓዝና የማጓጓዣውን ሰነድ (Way Bill) የተቀበለው ከአረብ ኮንትራክተር ኃ/የተ/የግ/ማህበር መሆኑን ሰነዱ ያስረዳል፤ ከሳሽ እቃዎቹን አጓጉዞ ያስረከበው ለዚሁ ድርጅት ነው፤ ስለሆነም ተከሳሽ የተጓጓዙትን ዕቃዎች ያልተረከበ በመሆኑ በንግድ ህጉ አንቀፅ 581 እና 582 መሰረት ተከሳሽን ለመጓጓዣው ሊጠይቅ አይችልም፤ በተከሳሽ ትዕዛዝ ተሰጥቷል እንዲሁም ርክክቡም መፈፀሙን ያስረዳሉ ተብሎ የቀረቡት ሰነዶችም የማጓጓዣውን ሂሳብ እኔ የምከፍል ስለመሆኑም ሆነ ከከሳሽ ጋር ውል መግባቴን የሚያረጋግጡ አይደሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃውን ከመረመረ በኋላ በከሳሽ በኩል የቀረቡት ምስክር ከሳሽ ከጂቡቲ ዕቃ ጭነው ይርጋጨፌ አጓጉዘው ያስረከቡት ከተከሳሽ ጋር ባላቸው ስምምነት መሆኑን፤ ስለማጓጓዙና ክፍያውን በተመለከተ የተነጋገሩትም ከተከሳሽ ጋር መሆኑን ማስረዳታቸውን እና ይህ ምስክርነት በተከሳሽ በኩል አለመስተባበሉን፤ በሰነድ ማስረጃነት የቀረቡት ሰነዶች ሲታዩም የጭነት ሰነዶችን የተረከበው ተከሳሽ መሆኑን፤ ተከሳሹ ከሳሽ አጓጉዘው ያስረከቡ መሆናቸውን ገልጾ ተከሳሽ ክፍያ ለመክፈል ቀጠሮ መስጠቱን የሚያስረዳ መሆኑን፤ በተለይ ክፍያ ለመክፈል የሰጠው ሰነድ የማጓጓዣ ውልን የሚተካ ደረሰኝ መሰል ነገር ሊባል እንደሚችል፤ በአጠቃላይ ከሳሽ የመጓጓዣ ውል መኖሩን ለማስረዳት ስለቻሉ ፍርድ ቤቱ በግራ ቀኙ መካከል የመጓጓዣ ውል አለ የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱን በመግለፅ ተከሳሽ ገንዘቡን ከነወለዱ ለከሳሽ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በበኩሉ ክርክራቸውን ሰምቶ የቀረቡት ሰነዶች እና የሰው ማስረጃዎች እንዲሁም ክርክሩ የሚያሳየው ተጠሪ የማጓጓዝ ውል ያላቸው ከአመልካች ጋር መሆኑን ነው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በአሰራር አስጫኙ ክፍያ ሲከፍለን ብቻ ነው ለተጠሪ የምንከፍለው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ ተጠሪ ውል ያላቸው ከአመልካች ጋር በመሆኑ አረብ ኮንትራክተርስ ከፈለም አልከፈለም ተጠሪን የሚመለከት አይደለም፤ እንዲሁም አመልካች ተጠሪን ወክሎ ገንዘብ ለመቀበል ሳይሆን ሰነዱን የተቀበለው እራሱ ለመክፈል

ስለሆነ ተጠሪ ያጓጓዘበትን ክፍያ ይክፈል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡
የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ሀምሌ 18/2008 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ቅሬታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ሥህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር ባደረጉት ስምምነት መሰረት ንብረትነቱ የአረብ ኮንስትራክሽን የሆነ ዕቃ ከጅቡቲ ይርጋ ጨፌ አጓጉዘው ማስረከባቸውንና ተጠሪም በርክክብ ሰነዱ ላይ ፈርሞ ገንዘቡን ለመክፈል የክፍያ ቀጠሮ መስጠቱን ገልፀው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ የማጓጓዣ ውል አለማድረጉን፤ ተጠሪ የማጓጓዣውን ሰነድ የተቀበለው ከአረብ ኮንትራክተር መሆኑንና እቃዎቹም ተጓጉዘውለት የተረከበው ይኸው ድርጅት መሆኑን በመግለፅ ሊጠየቅ እንደማይገባ ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙ በተጠቀሰው መልኩ ያቀረቡትን ክርክር በቅድሚያ የመረመረው የሥር ፍርድ ቤት የተለያዩበትን ፍሬ ነገር በማስረጃ በማጣራት የጭነት ሰነዶችን የተረከበው አመልካች መሆኑን፤ አመልካች ተጠሪ አጓጉዘው ያስረከቡ መሆናቸውን ገልጾ ክፍያ ለመክፈል ቀጠሮ መስጠቱ በሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን፤ ክፍያ ለመክፈል የሰጠው ሰነድ የማጓጓዣ ውልን የሚተካ ደረሰኝ ሊባል እንደሚችል፤ በዚህም ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የመጓጓዣ ውል መኖሩ መረጋገጡን ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አመልካች አጓጓዥ እንጂ አረብ ኮንስትራክሽንን ወክሎ ስራ የሚሰራ ወይም ትራንዚተር አለመሆኑን በማረጋገጥ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ ውል ስለመደረጉ በማስረጃነት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የጭነት ማጓጓዣ ሰነዱን እና አመልካች ክፍያ ለመክፈል ቀጠሮ መስጠቱን ለማስረዳት የቀረበውን ነው፡፡ በየብስ የዕቃ ማጓጓዝ ስራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣው

አዋጅ ቁጥር 547/99 በንግድ ሕግ አማካኝነት በ1952 ዓ.ም ወጥቶ በሥራ ላይ ያለውን ሕግ በተለይም የአጓጓዦችን የኃላፊነት መሠረት፣የኃላፊነት መጠንወሰንና ሌሎች መብቶችና ግዴታዎችን አስመልክቶ ዓለም ዓቀፍ ይዘት ካለውና ወጥ የሆነና የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት በሚያስችል መልኩ አሻሽሎ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተሻሽሎ መደንገጉን በአዋጁ መግቢያ ከተመለከተው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ መልኩ ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 547/99 በአንቀጽ 4 ሥር እንደተመለከተው የእቃ ማጓጓዝ ውል የሚረጋገጠው በማጓጓዣ ሰነድ መሆኑን፤ ነገር ግን ይህ ሰነድ አለመኖሩን ወይም ያልተሟላ መሆኑ ወይም መጥፋቱ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የተደረገውን ውል ዋጋ አልባ ሊያደርገው እንደማይችልና ሊያስቀረው እንደማይችል የሚደነግግ ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 8 ሥር እንደተመለከተው ደግሞ ላኪው እና አጓጓዡ ከተስማሙ የማጓጓዣው ሰነድ አጓጓዡ በሚሰጠውና ላኪው ተገቢ የሆኑትን ፅሁፎች በሚያሰፍርበት እንደ ደረሰኝ ባሉ ሰነዶች ሊተካ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም የእቃ ማጓጓዝ ውል በማጓጓዣ ሰነድ ወይም መሰል ሰነዶች ሊረጋገጥ እንደሚችል ከተሻሻለው የአዋጁ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ፍሬ ነገሩን የማጣራት ሥልጣን በህጉ የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ ተመልክተው ከፍ ሲል እንደተገለፀው የጭነት ሰነዶችን የተረከበው አመልካች መሆኑን፤ አመልካች ተጠሪ አጓጉዘው ያስረከቡ መሆናቸውን ገልጾ ክፍያ ለመክፈል ቀጠሮ መስጠቱን፤ እንዲሁም አመልካች አጓጓዥ እንጂ አረብ ኮንስትራክሽንን ወክሎ ስራ የሚሰራ ወይም ትራንዚተር አለመሆኑ አረጋግጠዋል፡፡ ይህ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የህጉ ግልፅ ድንጋጌ አንፃር ተገናዝቦ ሲታይ የሥር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል የመጓጓዣ ውል አለ የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ አመልካች ገንዘቡን ከነወለዱ ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰናቸው ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነምተከታዩንወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 22591 መጋቢት 6/2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 176735 ሰኔ 23/2008 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡተዘግቷልወደመዝገብቤትይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

የሰ.መ.ቁ 120468

መስከረም 23/2010 ዓ.ም

ዳኞች 1. ዳኜ መላኩ

2. ሪታ ቶለሳ

3. ተኽሊት ይመስል

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች......... አቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ክርስቶስ → ከጠበቃ አቶ ዝናቡ ይርጋ ጋር ቀረበዋል፡፡

ተጠሪ .................. አቶ ሐረጎት ገ/እግዚአብሔር → ቀረበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ቤት ለመስራት የወጣውን የጉልበት ዋጋና የገንዘብ ወጪ ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 78992 በ11/2/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በናዕዴር ዓዴት ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣ የአሁን አመልካች ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበው ክስ ከሳሽ እና ተከሳሽ በ1995 ዓ.ም በጽሑፍ በተደረገ ውል ተከሳሽ በሰመማ ከተማ በስሙ በተሰጠው ቦታ እኔ እንዳሰራው እና ለእኔም እንደሚሰራ ተስማምተን፣ በዚህ መሰረት አጥር እና ሁለት ክፍል ቤት በብር 80,000.00 /ሰማኒያ ሺህ/ የሚገመት ሰርቼ የእኔን አሰራኝ ስለው

እምቤ ስላለ የጉልበቴን ዋጋ እና ለሰራሁት ግንብ ለሚሆኑት ዕቃዎች ዋጋ ድርሻዬን ብር 40,000 እንዲከፍለኝ በማለት ከሷል፡፡ ተከሳሽ የጽሁፍ መልስ ባለማቅረቡ ታልፏል፡፡ ግራ ቀኛቸው በቃል ባደረጉት ክርክር ከሳሽ ሁለት ክፍል ቤት እና አጥር የስራሁበትን ገንዘብ እንዲከፍለኝ በማለት ሲጠይቅ፣ ተከሳሽ ደግሞ ከሳሽ የስራው ቤት የለም፣ የ1995 ዓ.ም አሁን ሊጠይቀኝ አይችልም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የከሳሽን የሰው ምስክሮች በመስማት በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ እና ተከሳሽ ተባብረው ለሰሩት ሁለት ክፍል ቤት ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 40,000 / አርባ ሺህ/ እንዲከፍለው በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አክሱም ምድብ ችሎት እና የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ቢሆንም ቅሬታው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በ27/3/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡- የአሁን ተጠሪ በውሉ መሰረት ቤት ተሰርቷል ያለው በ1995 ዓ.ም ሲሆን ገንዘብ እንዲከፈለው የጠየቀው 10 ዓመት ካለፈው በኋለ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚቋረጥ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የወረዳ ፍ/ቤት የተዘጋው መዝገብ ይከፈት አይከፈት የሚለውን በተመለከተ ግራ ቀኛቸውን አከራክሮ እንዲወስን መልሶለት እያለ ይህን ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረምልኝ፤ ተጠሪ ባቀረበው ክስ በመካከላችን ያለው የመተጋገዝ ውል እንዳለ የገለጸ ሲሆን ይህ ደግሞ ስምምነት እንጂ በሕግ ፊት አሰገዳጅነት ውጤት ያለው ውል አይደለም፣ ተጠሪ የጽሑፍ ውል አለ እያለ ስለሆነ በዚህ አግባብ ማስረዳት ሲገባው የሰው ምስክሮች ብቻ በመስማት የተጠየቀው 40,000 መኖሩን አግባብነት ባለው ማስረጃ ሳያስረዳ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎት አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘው መሰረት ጥር 16 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡- የአሁን አመልካች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ቢላክላቸውም

እምቢ አልቀበልም ማለታቸው በምስክሮች የተረጋገጠ ስለሆነ ጉዳዩን እንዳመኑበት የሚያስቆጥር ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአመልካች በኩል የቀረበውን የይርጋ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው፡፡ መዝገብ ማስከፈት በተመለከተ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመለሰለት መሰረት የወረዳው ፍ/ቤት እንደገና አጣርቶ የአሁን አመልካች በቀጠሮ ቀን ያልቀረቡት በበቂ ምክንያት እንዳልሆነ አይቶ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለው ነው፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው ውል የመተጋገዝ ውል ሳይሆን ሁለታችን በቤቱ ላይ ያለን መብት የሚያስረዳ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ተጠሪ ውል ስለመኖሩ በሰው ምስክሮች ያስረዳ ሲሆን አመልካች ውል መኖሩን ስላልካደ፣ ተጠሪ ውል በጽሑፍ አላስረዳም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም የሥር ውሳኔ አግባብነት ያለው ስለሆነ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎት ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ የሥር መዝገብ የመ.ቁ 02823 አስቀርቦ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዟል እንዲሁም ግራ ቀኛቸውን በቃል ሰምቷቸዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸውን ክርክር አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው በዚህ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በሕግ ፊት ግዴታን የሚፈጥር ውል አለ ወይስ የለም? የሚለው ነጥብ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ በዚህ መሰረት ተዋዋይ ወገኖች ውልን በሚያደርጉበት ጊዜ በሕጉ የተመለከተውን የውል አመሰራረት ሥርዓት ተከትሎ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 ሥር እንደተመለከተው በሕግ ፊት የሚጸና ውል ለማቋቋም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ተዘርዝሮ እናገኛለን፡፡ ከእነዚህ መሰረታዊ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ውል መደረግ ያለበት "በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለው የሚቻልና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ" በተመለከተ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በሕግ የተመለከቱትን አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች በጠበቀ መልክ እና ፈቃጅ የሆኑ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ በመሰላቸው ተነጻጻሪ መብትና ግዴታ በማስቀመጥ መዋዋል እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አግባብ ያቋቋሙት ውል ያንን ጉዳይ በተመለከተ በመካከላቸው ሕግ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731 ድንጋጌ የሚያስገናዝበው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ከሆነ

ተዋዋይ ወገኖች በውሉ በተፈጠረው መብት ተጠቃሚ የሚሆኑበት እና በግዴታው ደግሞ የሚገደዱበት ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው፡፡ በዚህ ውል መሻነትም ግዴታውን የተወጣው ወገን ሌላኛው ወገን ደግሞ ግዴታውን እንዲወጣ የመጠየቅ መብት እንደሚሰጠው ግልጽ ነው፡፡ በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ የአሁን አመልካች ቤቴን አስራኝ የአንተን ደግሞ አሰራአለሁ ብሎ በራሱ ይዞታ ላይ በሰማኒያ ሺህ ብር ቤት ሰርተን በውሉ መሰረት የእኔን ቤት አሰራኝ ቢለው እምቢ ስላለ የጉልበቴን ዋጋ እና ለስራሁት ግንብ የሚሆነውን ዕቃዎች ዋጋ እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡ ከዚህ ክስ መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ እና አመልካች አንዱ የሌላውን ቤት ለመስራት ለመተጋገዝ ያደረጉት ውል እንደሆነ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አመልካች በዚህ አግባብ ስላልሰራልኝ ገንዘብ እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪው የጉልበቱን ዋጋ እና ዕቃዎቹን በምን አግባብ ገምቶ እንዳቀረበ የሚያመለክት ነገር መኖሩን የሥር ውሳኔ የሚያመለክተው ነገር የለም፡፡ በዚህ ረገድ የአሁን አመልካች የቀረበው የጽሁፍ መልስ ባይኖርም በቃል ባቀረበው ክርክር ከሳሽን ያሰራሁት ቤት የለም ያቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት አመልካች ውል መኖሩን የካደ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰሙት የሰው ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል 1ኛ ምስክር አመልካች እና ተጠሪ ሚያዚያ ወር 1995 ዓ.ም ሁለት ክፍል ቤት አብረው በአመልካች ይዞታ ለይ እንደሰሩ፣ 2ኛ ምስክር በ1995 ዓ.ም ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ ሁለት ክፍል ቤት እንደሰራ፣ 3ኛ ምስክር በ1995 ዓ.ም በሰመማ ከተማ በአመልካች ቦታ ላይ አመልካች እና ተጠሪ ሁለት ክፍል ቤት እንደሰሩ ተጠሪ ገንዘቤን አካፍለኝ ሲለው እምቢ እንዳለው መመስከራቸውን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡ ከእነዚህ የምስክሮች ቃል መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ ለሰራው ሥራ የጉልበት ዋጋ በስንት ብር እንደተስማሙ፣ ምን ምን ዕቃዎችን ለቤቱ ግንባታ እንዳቀረበ እና ግምታቸው ምን ያህል እንደሆነ የመሰከሩት ነገር የለም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የግራ ቀኛቸውን ክርክር እና የምስክሮች ቃል መነሻ በማድረግ በደረሰበት ድምዳሜ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በትብብር ቤት የመስራት ስምምነት እንዳለ ማረጋገጡን አመልክቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ችሎት በቃል ባቀረበው ክርክር ከአመልካች ጋር ተባብረው ቤት ለመስራት እንደተስማሙ የአመልካች ቤት ከሰሩ በኋላ አመልካች የተጠሪን ለመስራት ፈቃደኛ ባለመሆኑ፣ የጉልበቱን ዋጋ እና ያቀረባቸውን ዕቃዎች ዋጋ እንደጠየቀ ገልጾ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ

እንደሚለው አብረን ቤት ለመስራት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ያደረግነው ስምምነት የለም፣ ቤቱን በገንዘቤ የሰራሁት እኔ ራሴ ነኝ ተጠሪ በሰራተኝነት ለስራው ሥራ በአካባቢ ዋጋ ተከፍሎታል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ እንደሚቻለው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል አንዱ ቤት ሲሰራ ሌላው ሊያግዘው እንደዚሁም ሌለው ቤት ሲሰራ መጀመሪያ የተሰራለት ሰው አብረው ሊሰራ እና ሊያግዘው መስማማታቸውን በዚህ ረገድ የመተባባርና የመተጋገዝ ስምምነት ማድረጋቸውን ያመለክታል፡፡ ይህ የመተጋገዝ ወይም የመተባበር ስምምነት በአካባቢው ልማድ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ከሕግ አንጻር ግን አንዱ ወገን ሌላውን ወገን ግዴታውን አልፈጸመልኝም እና እንዲፈጽምልኝ በማለት ለማስገደድ የሚያስችል አይደለም፡፡ አንዱ ወገን በዚህ በመተባበር ስምምነት መሰረት ሥራው ተሰርቶለት ሌላውን ያለገዘ እንደሆነ ምናልባት በአካባቢው ልማድ የሚያመጣው ትጽእኖ ሊኖር ቢችልም ይህ ስምምነት ከሕግ አንጻር የግራ ቀኛቸዉን ተነጻጻሪ መብትና ግዴታ የፈጠረ ነው እና አንዱ ወገን ሌላውን ወገን እንደውሉ እንዲፈጽምልኝ በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771 በሚደነግገው አግባብ ለመጠየቅ የሚያስችለው የሕግ መሰረት የለም፡፡ ይህ ማለት በግራ ቀኛቸው መካከል የተደረገው የመተባበር የመተጋገዝ ስምምነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው ከሚባል በስተቀር አስገዳጅነት ያለው በሕግ ፊት ግዴታን የሚፈጥር ውል አለ ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ ከዚህም በላይ የአሁን ተጠሪ የጉልበት ዋጋ በስንት ብር እንደተስማሙ እና ያቀረባቸው ዕቃዎች ምን እንደሆኑ እና ግምታቸው በማስረጃ ማረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚያመለክተው ነገር የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ የአሁን ተጠሪ እንደውሉ ገንዘብ እንዲከፍለኝ በማለት አመልካችን ለመጠየቅ የሚያስችለው የሕግ አግባብ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኛቸው መካከል የመተባበርና የመተጋገዝ ስምምነት እንጂ ግዴታን የሚፈጥር ውል በሌለበት ተጠሪ ደግሞ የጉልበት ዋጋ በስንት ብር እንደተስማሙ እና ያቀረባቸው ዕቃዎች ዓይነት እና ግምት በማስረጃ ባላረጋገጠበት ያቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው ክሱን በመቀበል አመልካች ብር 40,000 /አርባ ሺህ/ እንዲከፍል መወሰናቸው ከላይ የተመለከቱትን የውል ሕግ ድንጋጌዎችን ያላገናዘብ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የናዕዴር ዓዴት ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 02823 በ1/10/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ይህን ውሳኔ በማጽናት የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አክሱም ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 20724 በ5/12/2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 78992 በ11/2/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪ እና በአመልካች መካከል የነበረው ስምምነት በመተጋገዝና በመተባበር ቤት ከመስራት ውጭ በሕግ ፊት መብትና ግዴታን የሚፈጥር ውል ስላልሆነ አመልካች ለተጠሪ ብር 40,000 / አርባ ሺህ/ ለመክፈል የሚገደድበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኛቸው በዚህ ችሎት የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የመ.ቁ. 02823 ለናዕዴር ዓዴት ወረዳ ፍ/ቤት ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 123761

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ረታ ቶሎሳ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አብዩ ካሳሁን

ፀሐይ መንክር

**አመልካች፡-** ወ/ሮ እናኒ ተሰማ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ቄስ ገብረማርያም ደመቀ
2. ወ/ሮ ሙሉወርቅ ጂዳ
3. አቶ ዩሴፍ ጉታ
} አልቀረቡም

4. የቢሾፍቱ ከተማ ልማትና ማናጅመንት ኤጀንሲ ነገረ ፈጅ ሽመልስ ግዛው ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩየቀረበውን የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ. 44309 ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፤ የምስራቅ ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 41878 ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 240297 የካቲት 09 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል

በማለት አመልካች የካቲት 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸውነው፡፡

ክርክሩ የቤት ሽያጭ ውልን የሚመለከት ሲሆን በአደአ ወረዳው ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው አመልካች ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ ክስ በአሁን ተጠሪዎች ላይ በማቅረባቸው ሲሆን የክሱ ይዘት በአጭሩ፡-1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ለአሁን አመልካች በብር 32,000/ሰላሳ ሁለት ሺህ ብር/ የሸጡላቸውን በቢሾፍቱ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ኤ/05/026 የተመዘገበ በ105 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰራ ቤት በአንድ በኩል ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችንና ስም ለማዞር የሚያስችል ውክልና ለአሁን አመልካች ከሰጡ በኋላ በሌላ በኩል ከአሁን 3ኛ ተጠሪ ጋር ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የአከራካሪው ቤት ሽያጭ ውል መነሻነት ቤቱን ለ3ኛው ተጠሪ በመሸጥ ስመ ንብረቱ በ3ኛው ተጠሪ እንዲመዘገብ ያደረጉ በመሆናቸው፤ 4ኛው ተጠሪም ስለ ቤቱ በአግባቡ ሳያጣራ ስመ ንብረቱን በአሁኑ 3ኛ ተጠሪ መመዝገቡ ተገቢ ባለመሆኑ በ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎችና በ3ኛው ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ቀሪ ሆኖ በአመልካችና በ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ተፈፃሚነት እንዲኖረው በመጠየቅ ያቀረቡት ክስ ነበር፡፡

1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች በአቀረቡት ክርክር ቤቱን ለአሁን አመልካች መሸጣቸውን አምነው 3ኛው ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ውስጥ የነበሩ በመሆናቸው በወቅቱ ስሙ እንዲዞርላቸው የተደረገ መሆኑን ገልፀው ሲከራከሩ 3ኛው ተጠሪ በበኩላቸው አከራካሪውን ቤት አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ከተለያዩ በኋላ የገዙት ሆኖ እያለ ያላግባብ 3ኛው ተጠሪ ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም ከ4ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር በስማቸው በማስመዝገብ የገዙት መሆኑን በመጥቀስ አመልካች ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ተቀባይነት ቢያገኝ እንደማይቃወሙ በመከራከር መልስ አቅርበዋል፡፡ 4ኛውም ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካች ክርክር ቅን ልቦና የጎደለውና አከራካሪውን ቤት ከልዩ ልዩ ዕዳ ለማዳን የሚደረግ እንጂ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባልና ሚስት በነበሩበት ወቅት በባላቸው ስም ቤቱን መመዝገቤ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

የ3ኛው ተጠሪ ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ሕይወት አውዴ ጣልቃ ገብተው ከ3ኛው ተጠሪ ጋር ከጥር 19 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ ቆይተው በፍች የተለያዩ በመሆናቸው አከራካሪው ቤት የጋራ ሀብት ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ተወስኖ ለመካፈል በሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ የአመልካች ክስ አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

በጣልቃ ገቢዋ አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጡበት የታዘዙት 1ኛና 2ኛ መልስ ሰጭዎች የአከራካሪው ቤት ስመ ንብረት የተመዘገበው በ3ኛው ተጠሪ ስም በመሆኑ የጣልቃ ገብ አቤቱታ ተቀባይነት ቢያገኝ እንደማይቃወሙ ሲከራከሩ 3ኛው ተጠሪ በበኩላቸው አከራካሪው ቤት አመልካች የገዙት የግል ሀብታቸው ሆኖ እያለ 3ኛው ተጠሪ በማሳሳት በስማቸው ያስመዘገቡት በመሆኑ አከራካሪው ቤት የአመልካች ሀብት ነው ተብሎ ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌላቸው ተከራክረዋል፡፡ 4ኛው ተጠሪ ከጣልቃ ገብ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው አቤቱታቸው ውድቅ እንዲሆን አመልክተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤትምየግራቀኙን ወገኖች የቃልክርክርእናማስረጃዎችበመመርመር አመልካች ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር የቤት ሽያጭ ውል አድርጌአለሁ ቢሉም የተመዘገበ የቤት ሽያጭ ውል የሌለ በመሆኑ አቤቱታቸው ተቀባይነት የለውም፤ጣልቃ ገብ ከአከራካሪው ቤት ድርሻ አለኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታም በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የንብረት ክፍፍል ጉዳይ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችንም ሆነ የጣልቃ ገብን ክርክር ባለመቀበል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅርበመሰኘትለምስራቅ ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸውፍርድ ቤቱተጠሪዎችን አስቀርቦ ሲያከራክር ቆይቶ እንዲሁም አከራካሪውን ቤት በ3ኛው ተጠሪ ዕዳ ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወጣ ሀራጅ ገዝቸዋለሁ ያሉትን አቶ ሀይሉ ሳህሌን በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ አስገብቶ ግራቀኙንአከራክሮሲያበቃ አከራካሪው ቤት 1ኛና በ2ኛ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም በአደረጉት የሽያጭ ውል ለአመልካች መሸጣቸው ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል

አከራካሪው ቤት ለ3ኛ ተጠሪ ተሸጧል፡፡ ይህ ቤት የ3ኛ ተጠሪና የወ/ሮ ሕይወት አውዴ የጋራ ንብረት ለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪና ወ/ሮ ሕይወት አውዴ በአደረጉት የጋብቻ ሀብት ክርክር ተረጋግጧል፡፡ ከ3ኛ ተጠሪ ዕዳ ጠያቂ የሆኑ በርካታ ሰዎችም ቤቱን በፍርድ ቤት አስከብረው ክርክር እያደረጉ ቆይተዋል፡፡ የአሁን አመልካችም 3ኛ ተጠሪ ከገንዘብ ጠያቂዎች ጋር ሲከራከሩ የ3ኛው ተጠሪ ሚስት ነኝ፤ ድርሻም በአከራካሪው ቤት ላይ አለኝ በማለት ጣልቃ ገብተው ክርክር ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ስለሆነም አከራካሪው ቤት በ3ኛው ተጠሪ ተመዝግቦ እንደሚገኝ ያውቁ ነበር፡፡ አከራካሪው ቤት በብር 240,000/ሁለት  መቶ አርባ ሺህ ብር/ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በጨረታ ተሸጦ አቶ ሀይሉ ሳህሌ የተባሉት ገዝተውታል፡፡ ስመ ንብረቱም በአቶ ሀይሉ ሳህሌ ስም ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አመልካች የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው ውል ፀንቶ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው ውል እንዲፈርስ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት በውጤት ደረጃ የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘትና መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ለማሳረም ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

አመልካች ይህንን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታቸው በአጭሩ፡- አመልካች ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል እያለ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ያላግባብ ያደረጉት ሽያጭ የቤት ውል መነሻ ተደርገው በተከናወኑት ተግባራት የተነሳ አመልካች መብቴን እንዳጣ የተደረገ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አከራካሪው ቤት ለአመልካች ይገባል ተብሎ ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ አመልካች ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር በፈፀሙት የቤት ሽያጭ መነሻነት ውክልናና ሰነዶችን ተረክበው እያለ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ለ3ኛው ተጠሪ እንደገና ቤቱን መሸጣቸው አግባብነቱ ሊጣራ ይገባል በማለት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪዎች የሥር ክርክራቸውን በማጠናከር መልስአቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ ከመዝገብ ምርመራው መገንዘብ እንደተቻለው አከራካሪውን ቤት በተመለከተ የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሽያጭ ውል ተደርጎ እንደነበር፤ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ደግሞ በ3ኛ ተጠሪና በ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች መካከል ሌላ የሽያጭ ውል መደረጉን፤ 3ኛ ተጠሪ ሚስታቸው ከነበሩት ወ/ሮ ሕይወት አውዴ ጋር ፍች ሲፈፅሙ ይኸው ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው ተብሎ በፍርድ ቤት መወሰኑን፤3ኛው ተጠሪ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ጋር ባደረጉት ክርክር ተፈርዶባቸው አከራካሪው ቤት በጨረታ ተሸጦ አቶ ሀይሉ ሳህሌ የተባሉት ግለሰብ ገዝተው ስመ ንብረቱ በአቶ ሀይሉ ሳህሌ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የአሁን አመልካች በ3ኛው ተጠሪና በገንዘብ ጠያቂዎቹ መካከል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ከ3ኛው ተጠሪ ጋር ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ባልና ሚስት ሆነን እየኖርን በመሆኑ አከራካሪው ቤት የአመልካች ድርሻ ያለበት ነው በሚል በ2004 ዓ.ም ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው መከራከራቸውን የሥር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ከመሆኑም በላይ ይህ ችሎትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 187233 የሆነውን አስቀርቦ ተገንዝቧል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን መሠረት አድርገን እንደመረመርነው 3ኛው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ባልና ሚስት ሆነው ባሉበት ጊዜ አከራካሪውን ቤት በባል ስም የተመዘገበ ነው ከሚባል በስተቀር 3ኛው ተጠሪ የአመልካችን ቤት ያላግባብ በስማቸው አስመዝግበዋል ለማለት የሚበቃ ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም አመልካች ራሳቸው በ2004 ዓ.ም አከራካሪው ቤት የአመልካችና የ3ኛው ተጠሪ ንብረት ስለመሆኑ አምነውበዚሁ ቤት ላይ ያላቸውን ድርሻ ከ3ኛው ተጠሪ ገንዘብ ጠያቂዎች ለማስቀረት ሲከራከሩ ለመቆየታቸው በፌዴራል ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ የሚገኙ ማመልከቻዎች ያስረዳሉ፡፡

በሌላም በኩል ሲታይ አከራካሪው ቤት ወደ ሶስተኛ ወገኖች በመተላለፍና የፍርድ ቤት ውሳኔም አርፎበት በአሁኑ ጊዜ ለአቶ ሀይሉ ሳህሌ በሀራጅ ተሸጦ ስመ ንብረቱ ከ3ኛው ተጠሪ ወደ አቶ ሀይሉ ሳህሌ ተላልፎ የሚገኝ ለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 2878 ሥር እንደተመለከተው አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በሶስተኛ ወገኖች መቃወሚያ ሆኖ እንዲነሳ ከተፈለገ ውሉ

በማይንቀሳቀስ መዝገብ መፃፍ አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች በወቅቱ ባላስመዘገቡት ሽያጭ መነሻነት ህጉን ተከትሎ ቤቱን ለ3ኛው ወገን ለማስተላለፍ የተከናወኑ ተግባራትን ሁሉ ሊቃወሙ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም ፡፡

ለማጠቃለል ከአጠቃላይ የክርክር ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ሆነው እስከ 2004 ዓ.ም የቆዩ መሆናቸውን ሲሆን አከራካሪው ቤት በ3ኛው ተጠሪ ስም የተመዘገበውም አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ሆነው ባሉበት ጊዜ ነው፡፡ በሌላም በኩል ሲታይ አከራካሪው ቤት ወደ ሶስተኛ ወገን እጅ የገባ በመሆኑ አመልካች የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የሽያጭ ውል አለመመዝገቡ አከራካሪውን ቤት በሂደት ወደ እጃቸው በአስገቡት ሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ መነሳት የሚገባው ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ. 44309 ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፤ የምስራቅ ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 41878 ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 240297 የካቲት 09 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔያቸው የፀና መሆኑን እንዲያውቁት የዚህ ችሎት ውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍላቸው፡፡

3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

4. በዚህ ችሎት የተሰጠው እግድ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ.133203

ጥቅምት 29ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች- ዳኜ መላኩ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካች - ኢትዮ ቴሌኮም ጋምቤላ ሪጅን-ነ/ፈ ሰለሞን በንቲ ቀረቡ

ተጠሪ - አዱራ ኮንስትራክሽን አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ-አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ቅሬታ በማቅረቡ ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በጋምቤላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት ባጭሩ አመልካች በጋምቤላ ከተማ 04 ቀበሌ ለሚያሰራው የኔትወርክ ታወር ማቆሚያ መሰረት ፎርም ዎርክ (Form work) ለማሰራት የግንባታ ውል ስምምነት ፈፅመን በገባነው ውልና በተሰጠን ትዕዛዝ መሰረት ግንባታውን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ርክክብ የተደረገ ቢሆንም ተከሳሽ በውላችን ከተስማማነው ክፍያ ውስጥ 70 በመቶ ከፍሎን ቀሪውን 30 በመቶ ክፍያ እንዲከፍለን ጥያቄ ብናቀርብም ለመክፈል ፈቃደኛ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሊከፍለን የሚገባውን ብር 284,471.03 ከህጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በመላ ጋምቤላ እና አካባቢዋ ለታወር ማቆሚያ ፎርም ወርክ ያስጠናው የዋጋ ተመን ለአንድ ሜትር ስኩዌር ነጠላ ዋጋ ብር 296.95

መሆኑን፤ ከውሉ ጋር በተያያዘ ቢል ኦፍ ኳንቲቲ ላይ ለኮንክሪት ሙሊት ሥራ ተመን ለአንድ ሜትር ኩብ ነጠላ ዋጋ ብር 4112.11 የተቀመጠውን ዋጋ በስህተት ለታወር ማቆሚያ ፎርም ወርክ ብር 4112.11 እንዲሆን ተደርጎ በውሉ ላይ በመፃፉ ከተሰራው ስራ ዋጋ ውጪ ተሰልቶ የቀረበ የክፍያ ጥያቄ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ በውሉ መሰረት የመጨረሻ ክፍያ የሚከፈለው አድ ሜጀርመንት (መሬት ላይ የተሰራ ስራ እየተለካ የሚከፈል) ሲሆን ከሳሾች የተሰራውን ሥራ እና ልኬት አስለክተው ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ ቀሪ ክፍያ አልተከፈለንም በማለት ያቀረቡት ክስ ተገቢ አይደለም፤ በውሉም መሰረት ክፍያ የሚፈፀምላቸው ለተሰራው ሥራና ልኬት የሚገልፅ መረካከቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለተከሳሽ ሲቀርብ ሲሆን ይህን ሳያቀርቡ ክፍያ እና ወለድ መጠየቃቸው ከውሉ ውጪ ነው፤ በተሰራው ሥራ መያዣ የሚሆን የአንድ አመት ዋስታና እንደሚያዝ በውሉ አንቀጽ 52 ተመልክቶ እያለ በደፈናው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፤ ከሳሽ የሰራው ሥራም በገለልተኛ ወገን ይታይልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተከሳሽ ድርጅት ራሱ ባወጣው የዋጋ ተመን ብር 4112.11 የተዋዋለ በመሆኑና ውሉ በህግ የተመለከተው ሥርዓት ተጠብቆ የተደረገ በመሆኑ ተከሳሽ ከውሉ ውጪ በብር 296.95 እንዲከፈል ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ ስራው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል ወይስ አልጀመረም? የሚለውን በተመለከተም ፍርድ ቤቱ ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደረገ ሲሆን በሪፖርቱ ሙሉ በሙሉ እንደ ውሉ ሥራው ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሽ አልተረከብኩም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በሌላ በኩል የሥራ ዋስትና መያዣውን በተመለከተ በውሉ አንቀጽ 52 መያዣ ወይም ጋራንቲ መተው እንዳለበት የተመለከተ በመሆኑ በዚህ ረገድ ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ይኖረዋል በማለት በአጠቃላይ ተለክቶ ለቀረበው ዋጋውን ብር 233,498.99 ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል፤ ከዚህ ገንዘብ ላይ የአንድ ዓመት ጋራንቲ ብር 15,792.82 እንዲቀነስ፤ እንዲሁም ቀሪውን ክፍያ መፈፀም ከነበረበት ዕለት አንስቶ የሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፈል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክራቸውን ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 15/2009 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ተጠሪ በገባው ውል መሰረት ግንባታውን አጠናቆ ባላስረከበበትና መረካከቢያ ሰነድ ቴክ ኦፍ ሽት (take off sheet) አዘጋጅቶ ባላቀረበበት ሁኔታ ቀሪ ክፍያ እንዲከፈለው መወሰኑ ውሉን ያላገናዘበ ነው፤ የሥር ፍርድ ቤት የባለሙያ ምስክርነት ሪፖርት ብቻ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የህግ አግባብ የለውም፤ እንዲሁም ርክክብ ባልተደረገበት ሥራ ላይ ወለድ እንዲከፈል መወሰናቸው የህግ አግባብነት የለውም፤ ስለሆነም ውሳኔው ተሽሮ የተሰራው ሥራ ተለክቶና ርክክብ ተደርጎ በሚታወቀው መጠን እና ገለልተኛ ባለሙያ በጥልቀት አጥንቶ በሚያቀርበው መሰረት ተሰልቶ ቀሪ ክፍያ ካለ እንዲከፈል ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ታህሳስ 25/2009 ዓ.ም በሰጠው መልስ አመልካች በውል የተመለከተውን አገልግሎት ማግኘቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ፤ በውሉ ከተወሰነው እና አምኖ ሲከፍል ከቆየው መጠን በላይ ሌላ ክፍያ ሳይጠየቅ በቂ ባልሆነ ምክንያት ላለመክፈል ሞክሮ በፍርድ ኃይል እንዲከፍል መደረጉ ተገቢ በመሆኑ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለፅነው የክርክሩን አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያደረጉትን ክርክር ሲሆን በበኩላችን በሥር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ሥህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤት አከራካሪ የሆነው የግንባታ ስራ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል ወይስ አልጀመረም የሚለውን በተመለከተ በባለሙያ ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብለት በማድረግ ሙሉ በሙሉ እንደ ውሉ ሥራው ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ፍሬ ጉዳዩን ለማጣራትና ማስረጃ ለመመርመርና ለመመዘን በህጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተደረሰበትን መደምደሚያ ይህ ፍርድ ቤት የሚቀበለው ይሆናል፡፡ በሌላም በኩል ከውሉ ጋር በተያያዘ ለኮንክሪት ሙሊት ሥራ ተመን ለአንድ ሜትር ኩብ ነጠላ ዋጋ ብር 4112.11 የተቀመጠው ዋጋ በስህተት ለታወር ማቆሚያ ፎርም ወርክ

እንዲሆን ተደርጎ በውሉ ላይ የተጻፈ በመሆኑ ዋጋው እንደገና ተሰልቶ ቀሪ ክፍያ ካለ እንዲከፈል እንዲደረግ አመልካች አጥብቆ የተከራከረ ቢሆንም ውሉ ጉድለት የሌለበት መሆኑና አመልካችም ራሱ ባወጣው የዋጋ ተመን የተዋዋለ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠበት ከመሆኑም በላይ ግራቀኝ የተስማሙበት በውሉ የተመለከተ ዋጋ እያለ እንደገና ዋጋው እንዲተመን የሚደረግበት የህግ ምክንያት ባለመኖሩ በዚህም ረገድ በአመልካች የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በውሉ መሰረት ያልከፈለውን ቀሪ ክፍያ የተሰራው ሥራ ዋጋ 30% ለተጠሪዎች እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ወለድን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ቀሪው ክፍያ መፈፀም ከነበረበት ዕለት አንስቶ የሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፈል የወሰነ ሲሆን አመልካች በሰበር ቅሬታው ርክክብ ባልተደረገበት ሥራ ላይ ወለድ እንዲከፈል መወሰኑ የህግ አግባብነት የለውም እንዲባል ጠይቋል፡፡ ተጠሪም በውሉ መሰረት አገልግሎት በማግኘታቸው እና ለመክፈልም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በህጉ የተቀመጠውን ወለድ የማይከፍሉበት ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ ባለዕዳው በውል ባይመለከት እንኳ ህጋዊውን 9% ወለድ እንዲከፍል የሚጠበቅ ቢሆንም ወለድ መታሰብ የሚኖርበትን ጊዜ በተመለከተ ቀሪው ክፍያ መፈፀም ከነበረበት ዕለት አንስቶ እንዲታሰብ መወሰኑ ህጉን የተከተለ ስለመሆኑ መርምረናል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1772 ሥር እንደተደነገገው እንደውሉ ሳይፈፀምልኝ ቀርቷል በማለት ክርክር ለማቅረብ የሚፈልገው አንደኛው ወገን ተዋዋይ የተዋዋለው ሌላው አካል ግዴታውን እንዲፈፅምለት ለማድረግ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ ማስጠንቀቂያ መሰጠቱ ወለድ የሚሰላበትን ጊዜ በመወሰን ረገድ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ስለመስጠቱ ወይም ማስጠንቀቂያ መስጠት የማያስፈልግ ስለመሆኑ በመግለፅ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ክፍያ መፈፀም ከነበረበት ዕለት አንስቶወለድ እንዲታሰብ የሚደረግበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በዚህ ረገድ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰኔ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 02034/08 መስከረም 1 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተለክቶ ለቀረበው የግንባታ ዋጋውን ብር 233,498.99 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል፤ ከዚህ ገንዘብ ላይ የአንድ ዓመት ጋራንቲ ብር 15,792.82 እንዲቀነስ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ይህ የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. ወለድ ክስ ከቀረበበት ከግንቦት 10 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ 9% ሊከፈል ይገባል ብለናል፡፡
4. አፈፃፀሙ ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 18/2009 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ.መ.ቁ. 138591

ቀን፡- 27/6/2010ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ሼህ አደም ፋረስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሼህ ሙስጠፋ ፍሊ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

1. ጉዳዩ በጋራ ንብረት ላይ ተደረገ የተባለዉ ስምምነት እንዲፈርስ የቀረበ ክስ የሚመለከት ክርክር ነዉ፡፡ ክርክሩ የጀመረዉ በቤ/ጉ/ክ/መንግስት የአሶሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስም በአሶሳ ዞን አሶሳ ከተማ 03 ቀበሌ ክልል ዉስጥ በ 1000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ አንድ ወፍጮ ቤት ህዳር 08 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገዉ ስምምነት በጋራ የያዙት ሲሆን ጥር 16 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈዉ ዉል ንብረቱ ብር 90,000 ተገኝቶ አንዱ ወገን ንብረቱን እንዲያጠቃልል ስምምነት መደረጉን ከዚህ ገንዘብ ለጥገና ብር 20,000 ዉጪ ሆኖ ቀሪዉ 70,000 ለግራ ቀኙ የተከፋፈለ ሲሆን በግራ ቀኙ ስምምነትም ተጠሪ ለጊዜዉ ብር 15,000 ከፍለዉ ቀሪዉ 20,000 በሁለት ወር እንዲከፍሉ ስምምነት የተደረገ ቢሆንም ክፍያዉ አልተፈፀመም፡፡ የአመልካች ዕድሜ 80 ዓመት ሲሆን ዉሉም በዉልና ማስረጃ ያልተደረገ በመሆኑ ዉሉ ፈርሶ የንብረቱ ግምት አመልካች ከፍለዉ ንብረቱ እንዲያስቀሩ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

2. ተጠሪ በበኩላቸዉ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ጉዳዩ መልስ ሰጥቷል፡፡ ባቀረቡት የመጀመሪያ መቃወሚያ ስምምነት ከተደረገ 6 ዓመት ያለፈዉ በመሆኑ በይርጋ እንደሚታገድ በፍሬ ጉዳዩ ደግሞ አመልካች የጠየቁት ቀሪ ክፍያ ብር 20,000 ለልጃቸዉ ወ/ሮ ሩቅያ አደም መክፈላቸዉን በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡

3. መጀመሪያ ጉዳዩን የተመለከተዉ የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከመረመረ በኃላ ግራ ቀኙ ያደረጉት ዉል ጥር 15 ቀን 2002 ዓ/ም መሆኑን አመልካች የዉል ይሰረዝልኝ ጥያቄ ያቀረቡት በ 2008 ዓ/ም እንደሆነ በመግለጽ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 244/2/ እና የፍ/ሕ/ቁ. 1810(1) መሰረት በማድረግ የአመልካች ዉል ይሰረዝልኝ ጥያቄ የሁለት ዓመት ይርጋ ጊዜ ያለፈበት ነዉ በማለት በብይን ዉድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ብይን ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም የስር ፍ/ቤቶች ብይንና ትእዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነዉ፡፡ አመልካች የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የአመልካች ዕድሜ መግፋት ተጠቅሞ ያታለሉ በመሆኑ ዉሉ እንዲሰረዝ የቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ መደረጉ በአግባቡ አለመሆኑን ይህ ቢታለፍ ቀሪ ክፍያ ብር 20,000 የመጠየቅ መብት ሊታለፍ እንደማይገባ በመግለጽ የሥር ፍ/ቤቶች ብይን እንዲሻር ጠይቋል፡፡ ጉዳዩ ያጣራዉ ችሎትም የሥር ፍ/ቤት ጭብጥ አመሰራረትና የፍ/ሕ/ቁ. 1810 ለተያዘዉ ጭብጥ ያለዉ አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ለመመርመር ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም በ 10/11/2009ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች ዉል ይሰረዝልኝ ጥያቄ በይርጋ ዉድቅ ማድረጋቸዉ ተገቢ መሆኑን ቀሪ ብር 20,000 በሴት ልጃቸዉ ወይዘሪት ሩቅያ አደም በኩል የተላከላቸዉ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡ አመልካች አቤቱታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. የጉዳዩ አመጣጥም አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀዉ ሲሆን እኛም የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

5. እንደመረመርነዉም አመልካች ከተጠሪ ጋር ህዳር 8 ቀን 1998ዓ/ም ባደረጉት ስምምነት 1000 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈዉ ወፍጮ የጋራ ያደረጉ መሆኑን የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች እና ተጠሪ ጥር 16 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ ዉል ንብረቱ ብር 90,000 ዋጋ እንዳለዉ በመገመት አንዱ ወገን እንዲያጠቃልለዉ ተስማምተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ የአመልካች ድርሻ ብር 35,000 ከፍለዉ እንዲጠቀልሉት ስምምነት መደረጉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነዉ አመልካች በአንድ በኩል ዉሉ እንዲሰረዝ ሲጠይቁ በሌላ በኩል ደግሞ ቀሪዉ ገንዘብ ብር 20,000 ያልተከፈላቸዉ ስለመሆኑ ካደረጉት ክርክር መገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ዉሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ መነሻ ያደረጉት ዕድሜያቸዉ ከ 80 ዓመት በላይ ከመሆኑም በላይ የንግድ ልምድም የለኝም በሚል ስለመሆኑ መዝገቡ ያሳያል፡፡ በመርህ ደረጃ ዉል ለአንድ ወገን የበለጠ ጥቅም ይሰጣል በሚል እንደማይፈርስ ነገር ግን ፈቃድ የተገኘዉ በዕድሜ መግፋት ወይም የንግድ ልምድ ዕዉቀቱ ማነስ ካለና በሕሊና ግፍ መስሎ ከታየ ዉሉ የሚሰርዝበት ሁኔታ መኖሩን የፍ/ሕ/ቁ. 1710(1) እና (2) ድንጋጌዎች ያስገነዝበናል፡፡ የዉሉ ይሰረዝልኝ ጥያቄ መቅረብ ያለበትም በሕጉ በተደነገገዉ ጊዜ ገደብ ዉስጥ መሆን ያለበት ሲሆን በተያዘዉ ጉዳይ ስምምነት የተደረገዉ ጥር 2002 ዓ/ም ሲሆን የዉል ይሰረዝልኝ ክስ ያቀረበዉ ሚያዝያ 10 ቀን 2008 ዓ.ም መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አንድ ተዋዋይ የዉል ይሰረዝልኝ ክስ ዉሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረቡት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ዉስጥ ማቅረብ ያለበት መሆኑን በፍ/ሕ/ቁ.1810(1) ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የዉል ይሰረዝልኝ ክስ በሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ አለማቅረባቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተያያዘ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ግልጽነት የሌለዉ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ምክንያቱም አመልካች ብር 20,000 እንዲከፈላቸዉ የጠየቁ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የተጠሪ ድርሻ ብር 35,000 ከፍለዉ ንብረቱ እንዲያስቀሩ ዳኝነት መጠየቃቸዉን ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ፈፀምኩት ያሉትን ዉል ችግር ያለበት ከሆነ ዉሉ ይሰረዝ ብለዉ ከሚጠይቁ በቀር በተለየ አግባብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት የለዉም፡፡ አመልካች ክሱን መብታቸዉን ለማስከበር በህጉ የተመለከተዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ገደብ ጠብቀዉ ያላቀረቡት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በብይን ዉድቅ ማድጋቸዉ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

6. አመልካች የወፍጮዉ የጥገና ወጪ ብር 20,000 ከተቀነሰ በኃላ ከሚደርሳቸዉ ብር 35,000 ብር 15,000 ብቻ የተከፈላቸዉ መሆኑን በመግለጽ ቀሪ ብር 20,000 እንዲከፈላቸዉ መጠየቃቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ተጠሪ በሰጡት መልስ ብር 20,000 ተከፍሏል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

አመልካች ያቀረቡት የዉል ይሰረዝልኝ ክስ በይርጋ ዉድቅ መደረጉ ተገቢ ቢሆንም አመልካች የጠየቁት ብር 20,000 ያልተከፈላቸዉ ከሆነ ተገቢዉን ዳኝነት ከፍለዉ ክስ የማቅረብ መብታቸዉ ሊጠበቅ ይገባ ነበር፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ዉል ለማሰረዝ ያቀረበ ክስ ዉድቅ ማድረጋቸዉ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ቢሆንም አመልካች አለኝ የሚሉትን ቀሪ ገንዘብ የመጠየቅ መብታቸዉ ግን ሊጠበቅ ይገባል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. በቤ/ጉ/ክ የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍረድ ቤት በፍ/መ/ቁ 10579 በ25/09/2008 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ 07624 በ24/2/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ሰ/መ/ቁ 07939 በ5/05/2009 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር አደረጉት ባሉበት የጋራ ሀብት በአንድ ወገን የመጠቅለል ዉል ያልተከፈለኝ ያሉትን ብር 20,000 ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸዉ ይህ ዉሳኔ አያግዳቸዉም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

**የሰ/መ/ቁ/** -138386

**ቀን** - 26/06/2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካቾች**፡- 1. አቶ ረጋሣ ጉርሙ - ጠበቃ አቶ ኃይሉ ቡራዩ
2. አቶ ፀጋዬ ገ/መንፈስ - ጠበቃ አቶ አማሬ ኑሪዬ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1. አቶ ተሾመ አፈወርቅ
2. ወ/ሮ ዘነበች ገ/መንፈስ - ጠበቃ ዘነበ ፍቅሬ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄን መሠረት በማድረግ የተሰጠዉን ፍርድ በመቃወም የቀረበን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በቀን 20/08/05 ዓ.ም ጽፈዉ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ አመልካቾች የማይገባቸዉን ጥቅም ለማግኘት የተጠሪዎችን በዕድሜ መግፋትና ነገሮችን የማመዛዘን አቅማቸዉ እየቀነሰ መሄድን በተለይም 1ኛ ተጠሪ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ፓርኪንሰስ በሚባል የማስታወስ አቅምን በሚያሳጣ በሽታ በመጠቃቱ የአእምሮ እና የነርቭ በሽተኛ መሆኑን በመጠቀም እና 2ኛ ተጠሪን ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ በማሳመን

እና በማግባባት በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 2 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤ/ቁ/047/26 የሆነዉን ቤት ነሐሴ 06 ቀን 1996 ዓ.ም እራሳቸዉ ባዘጋጁት የሽያጭ ዉል ላይ ተጠሪዎችን አስፈርመዉ ግን በዉሉ ላይ የተጠቀሰዉን ገንዘብ ሳይከፍሉ የቤቱን ካርታ እና ተያያዥ ሰነዶችን መቀበላቸዉን ጠቅሰዉ በተንኮል፣ያልተገባ ተስፋ በመስጠት ዉል ለመዋዋል ችሎታ በሌላቸዉ ሰዎች መካከል የተደረገዉ ዉል ፈራሽ ነዉ ተብሎ ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካቾች ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ፤ ዉሉ ተደርጎ ከሁለት ዓመት በኋላ የቀረበዉ የዉል ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ጠቅሰዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተዉ የተከራከሩ ሲሆን፣ ፍሬ ነገሩን በተመለከተም ቀደም ሲል በመንደር የተፃፈዉን የሽያጭ ዉል ህጋዊ ለማድረግ በዉልና ሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት መመዝገቡን እና ተጠሪዎች ገንዘቡን መቀበላቸዉን እና 1ኛ ተጠሪ የአእምሮ በሽተኛ ነዉ በሚል ዉሉ እንዲፈርስ የቀረበዉም ዳኝነት ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ከግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ፤ 1ኛ ተጠሪ ዉሉ በተደረገበት ወቅት ነገሮችን የማገናዘብ እና የማስተዋል ችግር በሚያስከትል ፓርክንስንስ በሚባል በሽታ መጠቃታቸዉ በሕክምና ማስረጃ መረጋገጡን እና በወቅቱ ዕድሜያቸዉ በ90 ዓመት የሚጠጋ መሆኑ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ ዉሉን ያደረጉት ህጋዊ ዉጤቱን ለማወቅ የሚያስችል ጤነኛ የአእምሮ ሁኔታ እና አቅም ሳይኖራቸዉ መሆኑን ጠቅሶ ዉሉ ፈራሽ ነዉ በማለት ተጠሪዎች በዉሉ ምክንያት የተቀበሉትን ብር 700,000.00 ለአመልካቾች እንዲመልሱ፣አመልካቾችም ለዉሉ መነሻ የሆነዉን ቤት ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህኑን አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 21/06/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቆቻቸዉ አማካይነት ባቀረቡት 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ፤ 1ኛ ተጠሪ በዕድሜ መጃጃታቸዉ እንዲሁም የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸዉ እና ዉሉም በጫና የተደረገ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የሽያጭ ዉሉን ያደረጉት ወደዉ እና ፈቅደዉ በሰነዶች ምዝገባ እና

ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተረጋገጠ ዉል ሆኖ እያለ ዉሉ ተደርጎ ከሁለት ዓመት በኂላ የቀረበን የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ በመቀበል ዉሉ እንዲፈርስ በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ በመሆኑ ተሽረዉ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታዉ ተመርምሮ ዉሉ የተደረገዉ ተጠሪዎች በዕድሜ መጃጃት እና አእምሮ መታወክ ላይ በነበሩበት ወቅት ነዉ በሚል ምክንያት ዉሉ ተደርጎ ከሁለት ዓመት በኂላ የቀረበዉን የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ በመቀበል ዉሉ እንዲፈርስ የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት የስቀርባል በመባሉ፣ ተጠሪዎች ቀርበዉ በቀን 15/09/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት ባቀረቡት 9 ገጽ የጽሑፍ መልስ፤ 1ኛ ተጠሪ የማሰብ እና የማስታወስ አቅም በሚያሳጣ ፓርክንሰስ በሚባል የአእምሮ ህመም ተጠቅቶ ባሉበት ወቅት ዉሉ መደረጉ በመረጋገጡ በፍቃድ ጉድለት ምክንያት ዉሉ እንዲፈርስ መደረጉ እና ክሱም በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን የማይገባዉ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ፀንቶ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች በቀን 12/10/09 ዓ.ም ጽፈዉ ባቀረቡት የመልስ መልስ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ መዝገቡን ለማስቀረብ ከተያዘዉ ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከግራ ቀኝ ክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ላቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል የተደረገዉ ተጠሪዎች በዕድሜ ጃጅተዉ ባሉበት ወቅት በተለይም 1ኛ ተጠሪ ፓርክንስንስ በሚባል አእምሮን በሚያጠቃ በሽታ ተጠቅተዉ የዉሉን ህጋዊ ዉጤት ለማወቅ በሚያስችል ጤነኛ የአእምሮ ሁኔታ እና አቅም ሳይኖራቸዉ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ሲሆን፣ አመልካቾች በበኩላቸዉ ዉሉ በህግ አግባብ የተደረገ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነዉ፡፡

በመሠረቱ ዉል እንዲፈርስ ጥያቄ የሚያቀርብ ወገን ዉሉ ሊፈርስ የሚችልበት በህግ ተቀባይነት ያለዉ ምክንያት ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን የዉል

ይፍረስልኝ ጥያቄ የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም ለዉሉ መፍረስ በምክንያትነት የተጠቀሰዉ ሁኔታ ዉሉ እንዲፈርስ ለማድረግ በህግ ተቀባይነት ያለዉ እና በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ የፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ የማጣራት ግዴታ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ በመቀበል ዉሉ እንዲፈርስ የመወሰኑን አግባብነት መመርመሩ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክሳቸዉ አጠቃላይ ይዘት መረዳት የሚቻለዉ ተጠሪዎች ለዉሉ መፍረስ የጠቀሱት መሠረታዊ ምክንያት ዉሉ በተደረገበት ወቅት ዉል ለማድረግ የሚያስችል ችሎታ የሌላቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ዉሉ እንዲፈርስ ሲል ለደረሰበት ድምዳሜ በመሠረታዊነት የጠቀሰዉ ምክንያት ይህኑን ስለመሆኑ ተመልክተናል፡፡ በርግጥ ህጋዊ ዉልን ለማቋቋም አስፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱ ዉሉ ዉል ለማዋዋል ችሎታ ባላቸዉ ሰዎች መካከል የተደረገ መሆኑ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 1678(ሀ) ተመልክቷል፡፡ አንድ ሰዉ ዉል መዋዋልን ጨምሮ ሌሎች ህጋዉያን ተግባራትን (juridical acts) ለማከናወን ችሎታ የለዉም ማለት ስለሚቻልባቸዉ ሁኔታዎች የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2 ስለ ችሎታ በሚል ርዕስ ከአንቀጽ 192 ጀምሮ ባሉት አንቀፆቹ የሚደነግግ ሲሆን፤ ከአእምሮ ችግር ጋር በተያያዘ በህጉ አንቀጽ 339 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ዉል ከአእምሮ ጉድለት ጋር በተያያዘ ምክንያት ሊፈርስ የሚችለዉ የአእምሮ ጉድለቱ በግልጽ የታወቀ ሲሆን (notorious insanity) ወይም በፍርድ ክልከላ (judicially interdicted) ሲደረግ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 347 (1) እና 372 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ በግልጽ የታወቀ የአእምሮ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለበት መሆኑ ታዉቆ በፍርድ ክልከላ የተደረገ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 339፣ 340 እና 351 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በርግጥ ዉሉ በሚደረግበት ወቅት በነበረበት የአእምሮ ችግር (ህጉ "እብድ" በሚል ይገልፀዋል) የነበረበት በመሆኑ ምክንያት ጉድለት የሌለበትን ፍቃድ ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ ላይ እንደነበረ ለማስረዳት ከቻለ ዉሉን ማስፈረስ የሚችል ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 347(2) ስር

ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ይህ ድንጋጌ፣ የአእምሮ ችግሩ በግልጽ የታወቀ ካልሆነ በስተቀር ወይም በፍርድ ካልተከለከለ በስተቀር የአእምሮ ችግር መኖሩ መረጋገጡ ብቻዉን ዉልን ለማፍረስ ምክንያት እንደማይሆን በህጉ አንቀጽ 347(1) ስር ለተመለከተዉ ድንጋጌ ልዩ ሁኔታ (exception) በመሆኑ፣ በጠባቡ መተርጎም እንደሚገባዉ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ተዋዋዩ ዉሉን ያደረገዉ ነፃ ፍቃድ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ላይ መሆኑን በማስረዳት ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚቻለዉ ዉሉ በተደረገበት ወቅት ተዋዋዩ እብድ (የአእምሮ ችግር ያለበት) መሆኑን እና ዉሉም የተደረገዉ ተዋዋዩ በዚህ የአእምሮ ሁኔታ ዉስጥ ሆኖ ባለበት ወቅት ስለመሆኑ በማያጠራጥር አኳያ በማስረጃ ማረጋገጥን እንደሚጠይቅ ከፍ ሲል ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማ እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የቀረበ የህክምና ማስረጃ ግለሰቡ አእምሮን ሊያጠቃ በሚችል በሽታ መያዛቸዉን እንጂ በርግጥም ዉሉ በተደረገበት ወቅት በህጉ አጠራር እብድ በመሆን አእምሮአቸዉን መቆጣጠር በማያስችል ደረጃ ላይ የነበሩ መሆናቸዉን አያሳይም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ተጠሪዎች ዉሉ እንዲፈርስ በምክንያትነት ከጠቀሱት ዉስጥ አንዱ በዕድሜያቸዉ የገፉ ወይም የጃጁ መሆናቸዉን በመግለጽ ነዉ፡፡ በርግጥ መጃጀት ለዉል መፍረስ አንዱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1710(2) ስር ተመልክቷል፡፡ ይሁንና መጃጀት ለዉል መፍረስ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉ ዉሉ ለአንደኛዉ ወገን የበለጠ ጥቅም የሚሰጥ ሆኖ ይህም ሊሆን የቻለዉ የአንደኛዉን ወገን (የተጎጂዉን) መጃጀት ወይም በዕድሜ መግፋቱን መሠረት በማድረግ የተደረገ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 1710 (1 እና 2) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዕድሜ መግፋትን ወይም መጃጀትን መሠረት በማድረግ ዉል እንዲፈርስ ጥያቄ የሚያቀርብ ወገን በዕድሜ መግፋቱ ወይም መጃጀቱ መኖሩን ብቻ ሳይሆን ዉሉም ለተከሳሽ የበለጠ ጥቅም በሚሰጥ መልኩ የተደረገ ስለመሆኑ ጭምር የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ተጠሪዎች ዉሉ አመልካቾችን በይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ስለመሆኑ ለማሳየት ቤቱ 10,000,000.00 እንደሚያወጣ በክሳቸዉ ያመለከቱ ቢሆንም ይህ ግምት መሠረት የሚያደርገዉ ክሱ በተመሰረተበት ወቅት፣ በ2005 ዓ.ም፣ ያለዉን የቤቱን ዋጋ እንጂ ዉሉ በተደረገበት ወቅት በ1996 ዓ.ም

የነበረዉን ዋጋ አለመሆኑን ከክሱ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ዉሉ አመልካቾችን በይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ስለመሆኑ ባላሳዩበት ሁኔታ የተጠሪዎችን መጃጀት ወይም በዕድሜ መግፋት ብቻ መሠረት በማድረግ ዉሉ እንዲፈርስ ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥያቄም ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልበትን እና በህግ ተቀባይነት ያለዉ ተጠሪዎች ምክንያት በማቅረብ ባላስረዱበት ሁኔታ ያዉም ዉሉ ዉልን ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ማለትም በዉል እና ሰነዶች ማረጋገጫ የተደረገ ሆኖ እያለ፣ ዉሉ ተደርጎ ከ9 ዓመት በኋላ እንዲፈርስ ያቀረቡትን ክስ ተቀብሎ ዉሉ እንዲፈርስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ ዉል ሊፈርስ የሚችልበትን ሁኔታ በተመለከተ ከላይ በፍትሐብሔር ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.128919 በቀን 24/04/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 134268 በቀን 03/08/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰተዉን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. እግድ ተነስቷል፤ይፃፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

የሰ/መ/ቁጥር 128650

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች:...1.ረታ ቶሎሳ

2. ተኽሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች :- ወ/ሮ እቴናት አድማሱ - ቀርበዋል ።

ተጠሪ :- አቶ ደመቀ ይዘንጋዉ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የመኖሪያ ቤት ክርክርን መነሻ ያደረገ ሲሆን፣ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.45202 በ20/07/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበችዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በቢቡኝ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁን አመልካች ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር።ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ በ26/2/1999 ዓ.ም በተደረገዉ ዉል ተከሳሽ 8 ሜትር በ 12 ሜትር የሆነዉ ቦታና ቤት በብር 1,800.00 ሸጠዉልኝ በቦታዉ ላይ 37 ቆርቆሮ ቤት ከሰራሁኝ በኂላ ስመ ሀብቱን አዛዉርልኝ ካርታና ፕላን ላሰራበት ሲላት ፈቃደኛ ካለመሆንዋም በላይ በስሟ ካርታና ፕላን አሰርታ ከይዞታዋ ጋር ስላከተተች ቤቱን የገዛሁበትን ብር 1,800.00 ዉል ላፈረሰችበት ብር 5,000.00፣ 37 ቅጠል ቆርቆሮ ለማሰራት ያወጣሁትን ወጪ በአጠቃላይ ብር 27,198 /ሀያ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ስምነት/ እንዲትከፍለኝ በማለት ከሷል።

ይህን ክስ በተመለከተ ተከሳሽ ባቀረበችዉ መልስ በተባለዉ ዉል ቤቱንና ቦታዉን አልሸጥኩም፣ በ26/2/1999 ዓ.ም በተጻፈ ዉል 5 ሜትር በ 5 ሜትር ባዶ ቦታ በብር 1,800.00 ሽጩለት በዉሉ ቀን ብር 50.00 ሰጥቶኝ ቀሪዉን ዉሉ በቀበሌ ሲጸድቅ ሊሰጠኝ ተስማምተን ነገር ግን ባዶ ቦታ አይሸጥም ስለተባለ ብሩን መልሸለታለሁ እኔ ለቅሶ በሄድኩበት በሌለሁበት 32 ቆርቆሮ በጉልበት ባልሸጥኩለት ቦታ ሁሉ ቤት ሰርቷል፣ ባዶ ቦታ አይሸጥም፣ ቤቱን ለመስራት የተባለዉን ወጪ አያወጣም፣ ስለዚህ ቤቱን በራሱ ወጪ አፍርሶ እንዲያነሳ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት በሰጠዉ ዉሳኔ የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ ባዶ ቦታ ላይ ስለሆነ የሚጸና የቤት ሽያጭ ዉል የለም፣ ዉሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል፣ ከሳሽ በተከሳሽ ቦታ ላይ 33 ቆርቆሮ የሰራዉ ተከሳሽ እያወቀች ቢሆንም ከሳሽ ቤቱን አፍርሰዉ ከሚያነሳ በቀር ግምቱንም ሆነ ቤቱ የተሰራበትን ወጪ ለመክፈል የሚትገደድበት የሕግ አግባብ የለም፤ ነገር ግን ከሳሽ ቤቱን አፍርሶ ለመዉሰድ የጠየቀዉ ዳኝነት ስለሌለ ታልፏል፣ በዚህ በሕገ ወጥ ዉል ምክንያት ከሳሽ ለተከሳሽ የከፈላት ብር 1,800.0 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲትከፍለዉ በማለት ወስኗል፡፡ የምስራቅ ጎጀም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሥር ዉሳኔ አንጽቷል፡፡

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሽያጭ ዉሉ ሕገ ወጥ ስለሆነ ተጠሪ ለአመልካች ብር 1,800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ እንድትመልስ መባሉ በአግባቡ ነዉ፣ የሥር ፍ/ቤት ዉሉ ሕገ ወጥ ቢሆንም መኖሩን እስካመነበት ድረስ አመልካች ቤቱን ለመሥራት ያወጣዉን ወጪ ተጠሪ ልትከፍለዉ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ፣ አመልካች ቤቱን ለመሥራት ያወጣዉን ወጪ ተጠሪ ልትከፍለዉ ይገባል፣ የወጪዉን መጠን ግን የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን በማለት ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ16/09/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡--የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር የፈጸምነዉ ረቂቅ ዉል ሲሆን የሽያጭ ዉሉ ባዶ ቦታ የሚመለከት በመሆኑ በወቅቱም ዉሉን ለማዞር ስንጠይቅ የባዶ ቦታ ሽያጭ ዉል አይዞርም በመባላችን ረቂቅ ዉሉ ቀሪ ወይም ፈራሽ ያደረግነዉ ሆኖ ሳለ ቤቱንም ያለ እኔ ፈቃድ የሰራዉ መሆኑን ምስክሮች ከማረጋገጣቸዉም በላይ የቀበሌዉ ዋና አስተዳደሪ በችሎት ቀርቦ ያስረዳ በመሆኑ መክፈል የሚገባዉ ስለረቂቅ ዉሉ የተባልኩትን ገንዘብ ብቻ እንጂ ያለ እኔ ፈቃድ ከሳሽ ስለሰራዉ ቤት ግምት ለመክፈል የምገደድበት ምክንያት የለም፣ ቤቱ የተሰራበትም ተቃዉሜአለሁ ስለዚህ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል በማስረጃ ተመልሶ እንዲጣራልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ዉሉ ሕገ ወጥ እንደሆነ እና ቤቱ የተሰራዉ በሌለሁበት ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር ታልፎ ተጠሪ ቤቱን ለመስራት ያወጡት ወጪ አመልካች እንዲከፍሉ የመባሉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ቢታዘዝም ተጠሪ መጥሪያ ተቀብለዉ ባለመቅረባቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች እና ተጠሪ በ26/2/1999 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ዉል ቦታና ቤት እንደሚመለከት ቢገለጽም፣ የሥር ፍ/ቤት ባደረገዉ ማጣራት ግራ ቀኛቸዉ የተሻሻጡት ባዶ ቦታ ብቻ መሆኑን ባቀረበዉ ማስረጃ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ግራ ቀኛቸዉ የተሻሻጡት ባዶ ቦታ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የሚጸና የቤት ሽያጭ ዉል እንደሌለ እና ዉሉ ሕገ ወጥ መሆኑን ድምዳሜ ላይ በመድረስ ወስኗል፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 /3/ መሰረት ‹‹የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነዉ፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ

ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ፡፡ በማለት ደንግጓታል፡፡ ይህን ድንጋጌ ተግባራዊ ለማድረግ ከወጡት ዝርዝር ሕጎች መካከል የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝን እንደገና ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 272/1994 እና ይህን አዋጅ የሻረ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ እነዚህ እና ሌሎች ዝርዝር ሕጎችን ማየት እንደሚቻለዉ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት በሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት ተከትሎ ስልጣን ያለዉን አካል ጠይቆ ከማግኘት ዉጭ በሽያጭ ገዝቶ መያዝ እንደማይቻል ያስገነዝባሉ፡፡ የከተማ ቦታ በሽያጭ ዉል ተሸጦ ከሆነ ዉሉ ሕገ መንግስቱንም ሆነ ዝርዝር ሕጎቹን የሚጥስ ስለሆነ ሕገ ወጥና ፈራሽ ዉል ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን ተጠሪ ባዶ ቦታ ከአመልካች ገዝቶ ቤት የሰራ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዉሳኔዎቻቸዉ እንዳመለከቱት ይህ ዉል ሕገ ወጥ እና ፈረሽ ዉል ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ግራ ቀኛቸዉ ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1815 ማየት ይቻላል፡፡ ግራ ቀኛቸዉ ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ሲባል ግን የባለይዞታነት መብት ያለዉን ሰዉ/አካል ላይ እዳ በመጫን መሬቱን ሊያጣዉ የሚችል የገንዘብ ክፍያ ሊጣልበት አይገባም፡፡ በመሆኑም ይህ ዉል ሕገ ወጥ በመሆኑ እስከፈረሰ ድረስ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ልትከፍለዉ የሚገባት ብር 1,800 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ ብቻ ሊሆን ይገባል እንጂ የአሁን ተጠሪ በሕገ ወጥ ዉል በያዘዉ ቦታ ላይ የሰራዉን ቤት ለማሰራት ያወጣዉን ወጪ አመልካች የምትከፍልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ በአመልካች ቦታ ላይ የሰራዉን ቤት በራሱ ወጪ በማፍረስ ቦታዉን ለተጠሪ ለማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ግራ ቀኛቸዉ ከተስማሙ የአሁን አመልካች የቤቱን ግምት ለተጠሪ ከፍለዉ ቤቱን ለመዉሰድ ይህ ዉሳኔ የሚያግዳቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኛቸዉ መካከል የተደረገዉ ዉል ሕገ ወጥ ስለሆነ አመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ ብር 1,800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ ለተጠሪ እንድትመልስ ያለዉ ተገቢ ቢሆንም ተጠሪ በአመልካች ቦታ ላይ ቤት ለመስራት ያወጣዉን ወጪ እንድትከፍል በማለት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ቦታ ላይ ቤት ለመስራት ያወጣዉን ወጪ የመክፈል ኃላፊነት አለባት በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ የአሁን ተጠሪ በራሱ ወጪ ቤቱን ከአመልካች ቦታ ላይ አፈርሶ በማንሳት ቦታዉን ለአመልካች ሊለቅ ይገባል፡፡ አመልካች ቤቱን ለመስራት ተጠሪ ያወጣዉን ወጪ ለመክፈል አይገደዱም ብለናል፡፡ ነገር ግን ግራ ቀኛቸዉ ከተስማሙ እና የአሁን አመልካች ከፈለጉ የቤቱን ግምት ለተጠሪ ከፍለዉ ቤቱን ለመዉሰድ ይችላሉ ብለናል፡፡
3. የቢቡኝ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.07213 በ17/3/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.0120127 በ7/4/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
4. የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች በዉል ምክንያት ከተጠሪ የተቀበሉትን ብር 1,800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ ለተጠሪ እንዲመልሱ በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
5. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይደረስ፡፡ ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. በ8/10/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

# ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ.138479

የካቲት 26 ቀን 2010

ዓ.ም.

ዳኞች- ዳኜ መላኩ

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካች - ወ/ሮ ሸዋዬ ገ/እግዚአብሔር - ጠበቃ ወይንሸት መንግስቱ ቀረቡ

ተጠሪ - ወ/ሮ ብርሃኔ ፀአዱ - ጠበቃ ቅድስት የበቃ- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

1. አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 20 ቀበሌ 38 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 426 የሆነ ቤት ያላቸው ሲሆን ባለቤቴ ሟች አቶ ኃይለ ስልጣን ፀአዱ በህይወት በነበሩበት ወቅት በራስህ ጉልበትና ገንዘብ ቤት ሰርተህ በመኖሪያነት ተገልገልበት በማለት ውክልና ጭምር ሰጥተውት በቤታቸው ግቢ ውስጥ ተጠሪ ከልለው በሰጡት ቦታ ላይ ግምቱ ብር 10,000.00 (አስር ሺ.ህ) የሆነ ከእንጨትና ጭቃ የተሰራ አንድ ክፍል ቤት ከነመፀዳጃው ሰርተዋል፤ የሟችን ሞት ተከትሎ ተከሳሽ ቤቱን እየተገለገሉበት ሲሆን በዚሁ ቤት ውስጥ የነበሩ ግምታቸው ብር 11,766.00 (አስራ አንድ ሺ.ህ ሰባት መቶ ስድሳ ስድስት) የሆኑ የተለያዩ ንብረቶች ይዘው ስለከለከሉኝ

ንብረቶቹን በአይነት ያስረክቡኝ ወይም ግምቱን እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2. ተጠሪ በሰጡት መልስ የቤት ቁጥር 426 የሆነው ቤት በተጠሪ እና በባለቤታቸው ሻምበል አረዳ በኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት በ1965 ዓ.ም የተሰራ ሲሆን ከዚያ ወዲህ በግቢው ውስጥ የተሰራ ቤት የለም፤ የአመልካች ባለቤት በተጠሪ ግቢ ቦታ ተሰጥቶት የሰራው ቤት የለም፤ ሟች የተጠሪ ወንድም በመሆኑ በእንግድነት መጥቶ ሲኖር ነበር፤ በመታመሙ ምክንያት ተጠሪ ሳስታምመው ቆይቶ ከዚህ አለም በሞት የተለየ ሲሆን አመልካች ለቅሶ ከመምጣት ውጪ አላስታመሙም፤ የቤት ቁሳቁስ በማለት ዘርዝረው ያቀረቡት አንድም ዕቃ የለም፤ በአጠቃላይ ክሱ አላግባብ ለመበልፀግ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

3. ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸውን እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ከሳሽ ምስክር በቀጠሮ ቀን አቅርበው ባለማሰማታቸው መብታቸው የታለፈ ሲሆን የተከሳሽ ምስክሮች ቀርበው እንደመልሳቸው ማስረዳታቸውን፤ ምስክር ከተሰማ በኋላ የአመልካች ጠበቃ በዕለቱ ሌላ ቦታ ቀጠሮ ስለነበረኝ ምስክሮችን ፍርድ ቤቱ አስቀርቦ ይስማልኝ በማለት ቢጠይቁም በመጀመሪያ ምስክር ለመስማት ሲቀጠር ግራ ቀኙ በተገኙበት መታዘዙን መዝገቡ የሚያሳይ በመሆኑና ከሳሽ ሆነ ጠበቃቸው በቀጠሮው ምስክር እንደሚሰማ እያወቁ ሌላ ቦታ ቀጠሮ ተደርቦ ቢሆን እንኳ ቢያንስ ጠበቃው ከቀጠሮ ቀን በፊት ይህንን ለችሎቱ ማሳወቅ ሲገባቸው ካለማሳወቃቸውም በላይ ለምስክሮች መጥሪያ ስለማድረሳቸው እንኳ አልተረጋገጠም፤ በመሆኑም ከሳሽ በራሳቸው ችልተኝነት ምስክር አላሰሙም፤ በሰነድ ረገድም ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ ስለሆነም ክሱ በተከሳሽ የተካደ በመሆኑና ከሳሽም በሰነድም ይሁን በሰው ማስረጃ እንደክሱ ያላስረዱ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

4. አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 3/2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አመልካች ጠበቃቸው

ባለመገኘታቸው ብቻ ምስክር የማሰማት መብታቸው ታልፎ ክሱን አላስረዱም ተብሎ የመወሰኑን አግባብ ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መስከረም 23/2010 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ለምስክሮች የተጻፈውን መጥሪያ እንኳን ሳይወስዱ እርሳቸውም ሆነ ጠበቃቸው በቀጠሮው እለት ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በመቅረታቸው በሥነ ሥርዓት ህጉ መሰረት ምስክር የማሰማት መብታቸው የታለፈው በህጉ አግባብ በመሆኑ የሚነቀፍበት አንዳችም ምክንያት ካለመኖሩም በላይ ይህን የታለፈ መብታቸውን ለማስነሳት የሚያበቃ በቂ ምክንያት ያላቀረቡ በመሆኑ ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

5. ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ እና በሰበር የተደረገውን ክርክር ሲሆን በበኩላችን በሥር ፍርድ ቤቶች በተላለፈው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

6. ክርክሩ በሚመራበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 199(1) ሥር እንደተደነገገው ለቀጠሮ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት ሆኖ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ የመሰለውን ውሳኔ መስጠት እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

7. ከተያዘው ጉዳይ መገንዘብ እንደሚቻለው የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውደቅ በማድረግ የወሰኑት አመልካች ሆኑ ጠበቃቸው በቀጠሮው ምስክር እንደሚሰማ እያወቁ ባለመቅረባቸውና ጠበቃው ሌላ ቦታ ቀጠሮ ተደርቦባቸው ቢሆን እንኳ ቢያንስ ከቀጠሮ ቀን በፊት ይህን ለፍርድ ቤቱ ካለማሳወቃቸውም በላይ ለምስክሮች መጥሪያ ማድረሳቸው እንኳ አልተረጋገጠም፤ በመሆኑም ከሳሽ በራሳቸው ቸልተኝነት ምስክር አቅርበው ያላስረዱ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል ነው፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ መብታቸው የታለፈው ከህግ ውጪ ነው ሊባል የሚችልበት በህግ የተደገፈ ምክንያት አላቀረቡም፡፡

8. ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልኩ የደረሱበት መደምደሚያ እና ያሳለፉት ውሳኔ ክርክሩ የሚመራበትን የሥነ ሥርዓት ህግ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የተከተሉት የክርክር አመራር ሥርዓት የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 15286 ጥር 20/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በከፍተኛው ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 166927 ህዳር 6/2009 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 133708

ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ፀጋይ አስማማው

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ጣይቱ ደያሳ

2. ወ/ሮ ዘነቡ ደያሳ

3. አቶ አሸናፊ ደያሳ

4. ወ/ሮ ዘር ደያሳ

5. ወ/ሮ ሸዋዬ ለገሰ

6. ወ/ሮ ዲባቤ ለገሰ — ጠበቃ ጸጋዬ ፈይሳ -ቀረቡ (ለ1–10)

7. ወ/ሮ እመቤት ለገሰ

8. አቶ ካሳ ለገሰ

9. አቶ መስፍን ረጋሳ

10. አቶ ደገፉ ረጋሳ

11. አቶ ሽፈራው ለገሰ

ተጠሪ፡- አቶ ጉደታ ዲያሳ -ጠበቃ በሬሳ በየነ- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በረክ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ የሟች እናታችን የወ/ሮ ሎሚታ ጉደታ በቀን 22/11/2006 ዓም በውርስ አጣሪዎች የተጣራ የውርስ ንብረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 17 በመዘርዘር በፍ/ብ/ህ/ቁ.996 መሰረት ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው የጠየቁትን ዳኝነት በመቃወም ተጠሪው የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ በቀን 24/02/2007 ዓ.ም አቅርበዋል፤ በዚህ ማመልከቻቸውም አመልካቾች በአቤቱታቸው ከተራ ቁጥር 7 እስከ 10 እንዲረጋገጥላቸው የጠየቁት የባህር ዛፍ፤ የሳር እና የእርሻ መሬት የውርስ ሳይሆን የግሌ በመሆኑ ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ የአሁን ተጠሪ የስር ጣልቃ ገብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.43 መሰረት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ሲል ብይን ሰጥተዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት ብይን በመቃወም ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ብይን በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ሲል በውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 29 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ

በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ጥር 8 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የአመልካቾች ጥያቄ ተጠሪ የሟች የውርስ ንብረት ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲጣራ በግልፅ ተስማምቶ ውክልና ሰጥቶ በሚጣራው የውርስ ፋይል ተሳታፊ ሆኖ እያለ ቀድሞ የሰጠው ስምምነት ፀፅቶት ውርሱ ሊጣራ አይገባም በይርጋ ይታገዳል በማለት በጣልቃ ገብነት መቀወሚያ በማንሳትና መከራከሩን ከክርክሩ እየታየ ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41፣43 ድንጋጌዎች በመጥቀስ ተጠሪ ጣልቃ ይግባ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ በወካይና ተወካይ መካከል ያለው ግንኙነት በቅን ልቦና የተመሰረተ መሆን እንዳለበት እና ተወካዩም የወካዩን ጉዳይ ልክ እንደራሱ ጉዳይ የወካዩን ጥቅም በማስቀደም መስራት እንዳለበት የውክልና ህግ ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካቾች ይህንን የውክልና ስልጣን መከታ በማድረግ የተሰጣቸውን የውክልና ስልጣን በመተላለፍ የእናታችን የውርስ ሀብት ብቻ ሳይሆን በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የተጠሪን የግል ንብረት እና ይዞታ ጭምረው ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው ስህተት ነው፤ የሰጠሁት የውክልና ስልጣን በሌላ ጉዳይ ላይ ሁኖ እያለ ከፍላጎቴና ፍቃዴ ውጭ እንዲሁም በግል ንብረቴ ላይ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 ውጭ ጣልቃ ገብቼ ተከራክሬ መብቴን የማስከብርበት ሌላ አመራጭ የለም፤ ስለዚህ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚሁ ረገድ የሰጠው ውሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁን ተጠሪ የሟች የውርስ ንብረት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግ ከአሁን አመልካቾች ውስጥ ለወ/ሮ ዘርፌ ደያሳ እና ለአቶ ደገፋ ረጋሳ የውርስ መብታቸውን ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲታወቅላቸው የውክልና ስልጣን በመስጠት መሰማማታቸው፤በዚሁ መሰረት ውርስ ንብረት አጣርተው ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው፤ የውርስ ማጣራት በሂደት እያለ የአሁን ተጠሪ በስር 3ኛ አመልካች የነበሩት የውርሱ ማጣራት በይርጋ መታገድ አለበት፤ንብረቴ በውርሱ ውስጥ

ተጨምሯል የሚሉ ምክንቶች በመዘርዘር በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር መጠየቃቸው ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ የሟች የውርስ ንብረት ለማጣራት አመልካቾችና ተጠሪ ጭምር ተስማምተው አጣርተው ለፍርድ ቤት ማቅረባቸውን ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ አልተስማማሁም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የፍትሀብሔር ህጉ የሟች ውርስ የማጣራት ስልጣን ያላቸውን ግለሰቦች በቅደም ተከተል የሚዘረዝር ሲሆን እነርሱም፡-ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ ሆኖ ውርሱን እንዲያጣራ የሾመው ሰው ካለ በመጀመሪያ የውርስ አጣሪ እንደሆነ የፍትሀብሔር ህጉ 948/1/ የሚደነግግ ሲሆን፣ ሟች በውርስ አጣሪነት በኑዛዜ የሾመው ሰው ከሌለ ጠቅላላ የኑዛዜ ተቀባይ የሆነው ሰው የሟችን ውርስ የማጣራት ስልጣን እንዳለው የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር አንቀጽ 948 ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ሟች በኑዛዜ የመረጠው የውርስ አጣሪ ወይም ጠቅላላ የኑዛዜ ተቀባይ የሌለ በሆነ ጊዜ ሁሉ የሟች ያለኑዛዜ ወራሾች ያላንዳች ፎርማሊቲ የውርስ አጣሪነት ስልጣን እንዳላቸው በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 947 ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካቾች እና ተጠሪ የሟች ያለ ኑዛዜ ወራሾች በመሆናቸው የውርስ አጣሪነት ስልጣን እንዳለቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት ነጥብ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ ለፍርድ ቤት በቀረበው ሪፖርት ላይ ያላቸውን አስተያየት በመቀበል በውርሱ ማጣራት ሂደት በአግባቡ አልተጣራም የሚል መቃወሚያ ካለም ፍርድ ቤቱ በህጉ መሰረት አጣርቶ ሪፖረቱን ሊያሻሽለው ወይም ሊያፀናው ይችላል፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ የውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ በተመለከተ ሪፖርቱን በመደገፍ ወይም በመቃወም የሚቀርበው አስተያየት ተቀብሎና መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ የግድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 መሰረት ተጠሪ በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ ለመከራካር ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፤ፍርድ ቤቱም ሊቀበለው አይገባም፡፡ ምክንያቱም በአንድ ክስ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ላይ ባሉበት ጊዜ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም 3ኛ ወገን ከፍርድ ውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ መከራከር እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41/1/ ላይ የተደነገገ በመሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በዚሁ ጉዳይ 3ኛ ወገን አይደለም፡፡ ስለዚህ ለተያዘው ጉዳይ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41፤43 አግባብነት ያላቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ ከይርጋ ውጭ በሌሎች ነጥቦች ረገድ የውርስ

ማጣራቱን ሂደት እና ውጤቱን በተመለከተ አስተያየት መስጠት እና ፍ/ቤቱም ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ሊወስን ይገባል፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የሚች የውርስ ንብረት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግ ከአመልካቾች ጋር የተስማማ በመሆኑ የውርስ ማጣራት በይርጋ ይታገዳል በማለት የሚያቀርበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች በገዳዩ የሰጡት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ስጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 240200 መስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 24107 ህዳር 1 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በመሻር የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 227678 ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም እና የበረክ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.12792 ታህሳስ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. ተጠሪ በክርክሩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41/43 መሰረት ጣልቃ ይግባ በማለት የሰጡት ውሳኔ ክፍል በመሻር ፤በውጤት ደረጃ ተጠሪ የሚች ውርስ ንብረት ማጣራት በይርጋ ይታገዳል የሚለውን መቃወሚያ ውጭ ያለውን አስተያየት እንዲያቀርብ መፍቀዳቸው በአግባቡ በመሆኑ አጽንተነዋል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡የ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

የሰ/መ/ቁ.138717

የካቲት 28 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡1.ፀጋዬ አስማማዉ

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርክቲ ግደይ - ጠበቃ አበባ ዘበነ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1.አቶ ሽምሱ ኑሪ } 1ኛ ተጠሪ ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ፈዲላ እስማኤል

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የብድር ዉል የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.185781 በ23/05/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ሆነው ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበችዉ ክስ ተከሳሾች በ16/11/1999 ዓ.ም በተደረገዉ የብድር ዉል ብር 300,000 የተበደሩ ሲሆን በ10/2/2000 ዓ.ም ይህን የብድር ገንዘብ ካልከፈሉ በመያዣነት ያስያዙትን ቤት ስም ሀብት ወደ ከሳሽ ለማስተላለፍ ግዴታ ገብቷል፤ ከሳሽ የቤቱን እዳ ለመንግስት ብር 37,080.40 በተከሳሽ ስም የተከፈለ በመሆኑ፣ የዉስጥ ሁለት በሮችን ለማሰራት ብር 10,000 ያወጣሁ ስለሆነ፣ የቤቱ የመከላከያ ብረት ለማሰራት ብር 2,500 እና ለባለሙያ ብር 1,500 ከፍያለሁ፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች ይህን ቤት ስመ ሀብት ወደ ከሳሽ እንዲያዛዉሩልኝ ይህ ካልሆነ ገንዘቡን ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ፣ በዉሉ መሰረት ግዴታቸዉን ባለመፈጸማቸዉ ገደብ ብር 20,000 እንዲከፍሉኝ በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ የሥር ተከሳሾች ባቀረቡት መልስ የብድር ዉሉን በተመለከተ ተገቢ ነዉ ያሉትን ክርክር በማቅረብ፣ ከሳሽ ለባንክ ከፍያለዉ በማለት እንዲተካላቸዉ /እንዲከፈላቸዉ/ ያቀረቡትን ጥያቄ በሚመለከት ለባንክ የተከፈለዉን ቀሪ እዳ ብር 37,080.40 ለሁለት በሮች ለመከላከያ ብረት የወጣዉ ወጪ በጊዜዉ የነበረዉን ተመጣጣኝ ዋጋ ብንከፍል ተቃዉሞ የሌለን በመሆኑ በዚህ መሰረት ቢወሰን እንስማማለን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሾች የተበደሩትን ብር 300,000 ለከሳሽ እንዲከፍሉ፤ ከሳሽ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 14 ሚኪሊላንድ ሳይት የሕንጻ የቤት ቁጥር 22 የቤት ቁጥር 843 ለተከሳሾች ሊያስረክቡ ይገባል፣ ለቤቱ አወጣሁ ያሉትን ወጪ በዳኝነት ዉስጥ ስላልጠየቁ ታልፏል በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች መጋቢት 4 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች በመያዣነት የተያዘዉን ቤት በተመለከተ የመንግስት እዳ ብር 37,080.40 እና ቤቱም ወጪ ለበር ብር 10,000 ለመከላከያ ብረት ብር 2,500 ለባለሙያ ብር 1,500 ያወጣነዉን ወጪ እንዲከፈለኝ ጠይቄ እያለሁ፣ ተጠሪዎችም ባቀረቡት መልስ ይህን እዳ እና ወጪዎችን ሳይክዱና ታምኖ እያለ፣ ፍ/ቤቱ ይህን የታመነዉን ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242 መሰረት ወዲያዉኑ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ወይም ከዋናዉ ፍርድ ጋር ሊወስንልኝ ሲገባዉ ዳኝነት አልተጠየቀበትም በማለት በማለፍ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ ይህ ገንዘብ ከወለድ ጋር ታስቦ እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የአሁን አመልካች ለባንክ የከፈሉትን እዳ እና ለቤቱ ያወጡትን ወጪዎች ተጠሪዎች የቤቱን ሰነዶች ሲያስረክቡ እንደሚከፍሉ እንደማይቃወሙ፣ ወጪዎችን በተመለከተ ግምቱ የተጋነነ ስለሆነ በነበረዉ የገበያ ዋጋ ተገምቶ ብንከፍል አንቃወምም ብለዉ እያለ በክስ የዳኝነት ክፍል ስላልተጠቀሰ ብቻ ዳኝነት ሳይሰጥበት ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት መስከረም 23 ቀን

2010 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ እንዲሆንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ በብድር ዉል መነሻነት የያዙትን ቤት በተመለከተ ለባንክ የተከፈለ እዳ ብር 37,080.40 እና ለቤቱ ያጣሁት ወጪ 4,000 /አራት ሺህ/ እንደከፈሉ በክሱ ዝርዝር ዉስጥ የገለጹ ቢሆንም በዳኝነት ክፍል ሳይጠቅሱ መቅረታቸዉን መገንዘብ ተችሏል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ይህን ክስ በተመለከተ ባቀረቡት መልስ ለባንክ ተከፍሏል የተባለዉን ገንዘብ የካዱት ነገር የለም እንዲሁም ቤቱ ላይ ለተሰሩት ስራዎች የወጣዉን ወጪ በተመለከተ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተገምቶ ቢከፍሉ የማይቃወሙ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን ተጠሪዎች ለባንክ የተከፈለዉን ገንዘብ እና ቤቱ ላይ የወጣዉን ወጪ በተመለከተ አምነዉ የተከራከሩ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህን የግራ ቀኛቸዉን ክርክር በሕግ አግባብ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡

በመሰረቱ ከሳሽ በሚያቀርበዉ የክስ ማመልከቻ ላይ በተለይ ወይም በምትክ ወይም በተለዋዋጭ የሚጠይቀዉን ዳኝነት በግልጽ መጥቀስ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.224 ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም ከሳሽ የሚጠይቀዉ ዳኝነት ጠቅላላ እንደሆነ የክሱን ጭብጥና የማስረጃዉን አካባቢ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ትክክለኛ መስሎ የታየዉን ፍርድ መስጠት እንደሚችል በዚህ ድንጋጌ ሥር ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልስ ወይም በማናቸዉም በሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ወይም በቃል ክርክር ወቅት የእምነት ቃሉን የሰጠ እንደሆነ፣ ሌላኛዉ ተከራካሪ ወገን በዚህ እምነት መሰረት ዉሳኔ እንዲሰጠዉ መጠየቅ እንደሚችል እና ፍ/ቤትም ሌላ በማስረጃ የሚረጋገጥ ነገር ቢኖርም እንኳን በታመነዉና

ዉሳኔ እንዲሰጥበት በተጠየቀዉ ጉዳይ ብቻ ፍርድ መስጠት እንደሚገባዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242 ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች በብድር ዉል ምክንያት የያዙትን ቤት በተመለከተ ለባንክ የከፈሉትን ገንዘብ እና ከቤቱ ጋር በተያያዘ ለተሰሩት ሥራዎች ያወጡትን ወጪዎች በክሳቸዉ ዝርዝር ዉስጥ ገልጸዋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች የሚመልሱበት ሁኔታ መኖሩን እስከተገነዘበ ድረስ አመልካች ከቤቱ ጋር በተያያዘ አዉጥቻለሁ፣ ከፍያለሁ በማለት በክስ ማመልከቻ ላይ እስከጠየቁ ድረስ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ይህ ገንዘብ እንዲከፈላቸዉ በዳኝነት ክፍል ዉስጥ አልጠየቁም የሚል ከሆነ ስለጉዳይ በሕግ አግባብ ግልጽ እንዲያደርጉ ማድረግ የሚከለክለዉ ነገር አልነበረም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስና የቃል ክርክር አመልካች የጠየቀችዉን ይህን ገንዘብ የካዱት ነገር የለም፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ከዚህ ቤት ጋር በተያያዘ ለባንክ የተከፈለዉን እዳ እና ለቤቱ የወጣዉን ወጪ አምነዉ እና ለመክፈልም ፈቃደኛ እንደሆኑ ገልጸዉ እስከተከራከሩ ድረስ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የህግ ድንጋጌ በእምነት ቃላቸዉ አግባብ ዉሳኔ መስጠት ይገባቸዉ ነበር፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች እምነት መሰረት ይህን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍሉ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ በክሳቸዉ የዳኝነት ክፍል ዉስጥ ይህ ገንዘብ እንዲከፈላቸዉ አልጠየቁም በሚል ምክንያት ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ማረም ሲገባዉ ሳያርመዉ የሥር ዉሳኔ በማጽናት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>**ዉ ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.61912 በ3/2/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.185781 በ23/5/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. የአሁን አመልካች በብድር ዉል ምክንያት የያዙትን ቤት በተመለከተ ለባንክ የከፈሉትን እና ለቤቱ ያወጡትን ወጪ በድምሩ ብር 41,080.40 /አርባ አንድ ሺህ ሰማንያ ከአርባ ሳንቲም/ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ የአሁን ተጠሪዎች ይህን ገንዘብ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች በዚህ ገንዘብ መጠን የዳኝነት ክፍያ ያልከፈሉ እንደሆነ ባለዉ የዳኝነት ክፍያ ታሪፍ ደንብ መሰረት ሊያከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በብድር ዉል ምክንያት የያዙትን ቤት ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ እና ተጠሪዎች ደግሞ በብድር ዉሉ መሰረት የተበደሩትን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍሏቸዉ በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፣ ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ማ/**

የሰ.መ.ቁ.131832

ታህሳስ 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1.ዳኜ መላኩ

2. ተኽሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ መረሳ አማረ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1.ቄስ ሃይለ ገብረ } የቀረበ የለም

2. መቶ አለቃ ካልሃዩ ተስፋይ

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የጎጆ መዉጫ ይዞታና ቤትን የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.83091 በ19/09/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በተክዓ ቀበሌ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ የአሁን አመልካች የመቃወም አመልካች፣የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ የመቃወም ተጠሪዎች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበዉ ክስ መነሻነት የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የጎጆ መዉጫ ይዞታ ለአሁን 2ኛ ተጠሪ እንዲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የተሰራዉን ቤት ቆርቆሮዉን እና እንጨቱን አፍርሰዉ አንስተዉ እንዲወስዱ በማለት ወስኗል፡፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን፣ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ጉዳዩን በማየት በሰጠዉ ብይን አመልካች ያቀረቡት የመቃወሚያ ማመልከቻ የብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ/ ግምት ያለዉ የጎጆ መዉጫ ስለሆነ ኮሚቴዉ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት ማመልከቻዉን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለእምባ ኣላጀ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ይህን የጎጆ መዉጫ ክርክር ለማየት ስልጣን አለዉ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 መልሶለታል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች የይግባኝ ማመልከቻ ለማይጨዉ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች አሁንም የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱ ይህ ጉዳይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አሁን የቀረበዉ አቤቱታ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ የብር 200000 ግምት ያለዉን ንብረት ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን ሳይኖረዉ የተሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ የሥር የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፤የሥር ፍ/ቤቶች ተገምተዉ ያልቀረበዉን ንብረት በመጀመሪያ ያየዉ ፍ/ቤት ስልጣን አለዉ በማለት የመወሰናቸዉ አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪዎች የየራሳቸዉን መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡትም መልስ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግ በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ያቀረቡት የመቃወሚያ ማመልከቻ በአሁን ተጠሪዎች መካከል ሲካሄድ ቆይቶ የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል በማለት ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ይህን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻን ተቀብሎ የማየት እና የቀደመዉን ዉሳኔ መለወጥ የሚችለዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 ሥር እንደተመለከተዉ ራሱ ፍርዱን የሰጠዉ አካል ነዉ፡፡ በዚህ ጉዳይም የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ለክርክር

ምክንያት የሆነዉን የጎጆ መዉጫ እና ቤት በተመለከተ ዉሳኔ የሰጠ አካል እስከሆነ ድረስ ይህን የሕግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ፣ አመልካች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተከትሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.360 /2/ መሰረት የቀደመዉን ዉሳኔ የማጽደቅ ወይም የማሻሻል ወይም የመለወጥ ወይም የመሰረዝ ስልጣን አለዉ፡፡ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴዉ በዚህ አግባብ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ የሚያጸድቀዉ ወይም የሚያሻሽለዉ ወይም የሚለዉጠዉ ወይም የሚያሰርዘዉ የአሁን አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀብሎ ጉዳዩን ያየ እንደሆነ ብቻ ነዉ፡፡ ኮሚቴዉ አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ከጅምሩ ዉድቅ የሚያደርግ እንደሆነ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ ምንም ሳይባል እንዳለ ስለሚሆን ከላይ የተመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎችን ዓላማ የሚቃረን ይሆናል፡፡ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻዉን ተቀብሎ ግራ ቀኛቸዉን ከአከራከራቸዉ በኋላ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ የሚያጸድቅበት ወይም የሚያሻሽልበት ወይም የሚለዉጥበት በሕግ በተመለከተዉ አግባብ ሲሆን፣ ይህን የሚያደርገዉ በስልጣን ወይም በሌላ ሕጋዊ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ኮሚቴዉ አመልካች ያቀረቡትን የመቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎ አስቀድሞ የሰጠዉ ዉሳኔ ምን መሆን አለበት በሚለዉ ነጥብ ላይ ዉሳኔ ሊሰጥበት ይገባል እንጂ ከጅምሩ ማመልከቻዉን ለመቀበል ስልጣን የለኝም በማለት አስቀድሞ ስለሰጠዉ ዉሳኔ ምንም ሳይል መተዉ አግባብ አይደለም፡፡ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ሁኔታ በመገንዘብ የቀበሌዉን መሬት ዳኝነት ኮሚቴ አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ የማየት ስልጣን አለዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነበር፡፡ በመሆኑም የሥር የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን የወረዳዉ ዉሳኔ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የሥር የሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.83091 በ19/09/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰ.መ.ቁ.130410

ታህሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች**፡...1.ዳኜ መላኩ

2. ተኽሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

**አመልካች፡-**.....አቶ ሱፍያን አቡበከር ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-**.....1.አቶ ክፍሉ ጋሼ የቀረበ የለም

2. ወ/ሮ ዘዉዴ መኩሪያ

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.233491 22/9/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በአደኣ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች 1ኛ የመቃወም ተጠሪ እና የአሁን ተጠሪዎች የመቃወም አመልካቾች፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነዉ የቢሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አጀንሲ 2ኛ የመቃወም ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች የቢሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አጀንሲ ላይ ባቀረበዉ ክስ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ከሳሽ እና ተከሳሽን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን 9936 ካ.ሜ የሆነዉን ቦታ ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲያስረክብ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህን ዉሳኔ ተከትሎ የመቃወም አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ባቀረቡት አቤቱታ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ የ1ኛ የመቃወም ተጠሪ የአቶ ሱፊያን

አቡበከር ሳይሆን የእኛ ነዉ፣ ይዞታዉ ከእጃችን ወጥቶ አያዉቅም፣ በዚህ ጉዳይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.163687 በ11/2/2006 ዓ.ም ዉሳኔ የሰጠ በመሆኑ 1ኛ የመቃወም ተጠሪ በተሰረዘ ካርታ መክሰስ መብት የለዉም፣ ስለዚህ የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻርልን በማለት ጠየቋል፡፡

በዚህ የመቃወም ማመልከቻ ላይ 1ኛ የመቃወም ተጠሪ አቶ ሱፊያን አቡበከር ባቀረበዉ መልስ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ በሕግ አግባብ የተሰጠኝ ነዉ፣ ካርታ አልተሰረዘም፣ ይዞታዉ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም ግብር እየከፈልኩኝ ስጠቀምበት ነበር፣ የመቃወም አመልካቾች መብት ሳይኖራቸዉ ነዉ ይህን መሬት ወጥተዉ ያረሱት በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ የመቃወም ተጠሪ የብሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አጀንሲ ባቀረበዉ መልስ ከዚህ በፊት የ1ኛ ተጠሪ ካርታ መሰረዙ ተረጋግጦ ከይዞታዉ መብት እንደሌለዉ ዉሳኔ የተሰጠ በመሆኑ የ1ኛ ተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የአደኣ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ በተመለከተ ለ1ኛ የመቃወም ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ ያልተሰረዘ መሆኑን ማህደሩ ያረጋግጣል፣ የመቃወም አመልካቾች በይዞታዉ ላይ ባለመብት ቢሆኑም መሬታቸዉን ለሌላ ሰዉ አሳልፈዉ የሰጠዉን አካል ከሶ ከሚጠይቁ በስተቀር 1ኛ የመቃወም ተጠሪ በሕገ ወጥ መንገድ ይዟል የሚያስብል ስላልሆነ፣ ከዚህ በፊት የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚያፈርስ ምክንያት ስለሌለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ.360/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሥር የመቃወም አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ከዚህ በፊት ይህ ችሎት በመ.ቁ.163687 በ11/2/2006 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለ1ኛ ተጠሪ አቶ ሱፊያን አቡበከር ካርታ ቀሪ ሆኖ የተሰረዘ መሆኑን፣ ይዞታዉ በእጁ ሳይኖር ግብር መክፈሉ ብቻ ባለመብት እንደማያደርገዉ እና አቶ ሱፊያን በዚህ ይዞታ ላይ መብት የለዉም በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ዉሳኔ ሰጥቶ

እያለ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ ድጋሚ አጣርተዉ ዉሳኔ መስጠታቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ3/5/2009 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ ብሾፍቱ ከተማ በሕግ አግባብ የተሰጠኝ ካርታም ተሰጥቶኝ እና ከ1983 ዓ.ም ስጠቀምበት የነበረ ሆኖ ሳለ፣ ለአመልካች የተሰጠ ካርታ ያልተሰረዘ መሆኑን ተረጋግጦ እያለ፣ በዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ዉሳኔ ተሰጥቷል የተባለዉ እና አሁን የቀረበዉ ክርክር የተለያዩ ጭብጦችና ተከራካሪ ወገኖች በመሆኑ አስቀድሞ ዉሳኔ ተሰጥቷል የሚያስብል ነገር በሌለበት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነዉ በማለት ዉሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪ በ5/7/2009 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ በዚህ ጉዳይ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት የሌለዉ በመሆኑ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ከዚህ ቀደም ይህን ይዞታ በተመለከተ የአሁን ተጠሪዎችን ጨምሮ በአራት ሰዎች ላይ ክስ አቅርበዉ ሲከራከሩ ከቆዩ በኂላ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.163687 በ11/2/2006 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለአሁን አመልካች የተሰጠዉ ካርታ የተሰረዘ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የቀረበ ማስረጃ እንደሚያረጋግጥ በማመልከት፣ ይዞታዉም በአመልካች እጅ ሳይገባ እስከ 2004 ዓ.ም ግብር መክፈሉ

ባለመብት እንደማያደርገዉ እና አመልካች በተሰረዘ ካርታ ይዞታዉን በተመለከተ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የአሁን አመልካች ከዚህ ዉሳኔ በኋላ ባቀረበዉ አዲስ ክስ ካርታዉ እንዳልተሰረዘ እና የብሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ይህን ይዞታ እንዲያስረክበዉ ዳኝነት በመጠየቁ፣ ኤጀንሲዉ የአመልካች ክስ ተቀባይነት እንደሌለዉ በመግለጽ ቢከራከርም፣ የሥር ፍ/ቤት ለአመልካች የተሰጠ ካርታ እንዳልተሰረዘ እና ኤጀንሲዉ መሬቱን እንዲያስረክብ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ይህን ዉሳኔ በመቃወም የመቃወሚያ ማመልከቻ አቅርበዉ ቢከረከሩም፤ የሥር ወረዳ ፍ/ቤት እና ከፍተኛ ፍ/ቤት አስቀድመዉ ካርታዉ እንደተሰረዘ እና ለክርክር ምክንያት በሆነዉ ይዞታ ላይ ዉሳኔ ተሰጥቷል በማለት ያቀረበዉን መቃወሚያ በማለፍ ዉሳኔ መስጠታቸዉን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ሁኔታ በመገንዘብ የአሁን አመልካች ከዚህ ቀደም ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል መወሰኑን የሥር ዉሳኔ ያሳያል፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ችሎት ጉዳዩን እንደመረመረዉ የአሁን አመልካች ከዚህ ቀደም የአሁን ተጠሪዎችን ጭምሮ በአራት ሰዎች ላይ ክስ አቅርበዉ ዉሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 /1/ መሰረት ድጋሚ አዲስ ክስ የሚያቀርብበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የአሁን አመልካች ካርታዉ እንደተሰረዘ እና በዚህ ካርታ ይዞታዉን ለመጠየቅ መብት እንደሌለዉ ዉሳኔ ተሰጥቶ እያለ ተከራካሪ ወገን በመቀየር የብሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አጀንሲ ላይ ክስ ስላቀረበ ብቻ የክርክሩ ጭብጥና ተከራካሪ ወገን ስለሚለያይ የዚህን ድንጋጌ መስፈርት አያሟላም፣ ከዚህ ቀደም ዉሳኔ ተሰጥቷል የሚያስብል አይደለም በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ክስ ከዚህ ቀደም ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ስለሆነ አዲስ ክስ ለማቅረብ አይችልም፡፡

ሲጠቃለል የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ክስ ከዚህ በፊት ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በመሻር አመልካች ያቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ

ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 233491 22/9/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስላልሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

*ሩ/ለ*

የሰ/መ/ቁ. 137831

ህዳር 28 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ለተብርሃን ያይንሽት - የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ የማነ በየነ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የክርክሩ ምክንያት የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ተጠሪ የነበሩ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ደግሞ አመልካች ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ የግል እና የጋራ ንብረቶች ናቸው ያሉዋቸውን የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን፣ የባንክ ገንዘብ እንዲሁም የኮንደሚኒየም ቤት ቁጠባ በተመለከተ አመልካች ተጠሪን ሳያገቡ የተመዘገቡ በመሆኑ የሥር አመልካች/የአሁን ተጠሪ/ የግል ንብረታቸው መሆኑን ገልጸው ቤቱም ያልደረሳቸው በመሆኑ መካፈል አይችሉም በማለት ውሳኔ እንዲሰጥበት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች /የሥር ተጠሪ/ በሰጡት መልስ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን በተመለከተ የግልና የጋራ ንብረቶች ናቸው ያሉዋቸውን በዝርዝር በማቅረብ እነዚህ ንብረቶች እንዲሁም በወጋገን ባንክ ያለው ገንዘብ እኩል እንዲካፈል፣ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ አመልካች /የአሁን ተጠሪ/ በልጁ ስም በ40/60 የኮንደሚኒየም ቤት

የቆጠበውን ገንዘብ ሊካፈል ይገባል፣ ከ1997 ዓ/ም ጀምሮ በአመልካች ስም የተጠራቀመውን ገንዘብ ልንካፈል ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተለያዩ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡለት ካደረገ በኃላ የግልና የጋራ ንብረቶች ናቸው ባላቸው የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች፣ ወጋገን ባንክ ያለው ገንዘብ ላይ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የኮንደሚኒየም ቤት በተመለከተ አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ የፈጸሙት ጳጉሜ 2 ቀን 2002 ዓ/ም ሲሆን አመልካች /የአሁን ተጠሪ/ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘብ መቆጠብ የጀመሩት እ.ኤ.አ በ20/6/2013 ነው፡፡ ይህም ጊዜ ሲታይ አመልካች ለኮንደሚኒየም ቤት የቆጠቡት ገንዘብ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ እንዳሉ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦሌ ቡልቡላ ቅርንጫፍ ከቆጠቡት ገንዘብ ከፊሉን ብር 7,227.23 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም/ ለተጠሪ ይክፈሉ፡፡ የ40/60 ኮንደሚኒየም ቤት በተመለከተ የአሁን አመልካች /የሥር ተጠሪ/ በማስረጃ ስላላስረዱ ታልፏል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪ የግል ንብረቶች ናቸው ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ፣ ከወጋገን ባንክ የአሁን ተጠሪ ጋብቻ ከመፍረሱ በፊት ያወጡትን 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ሳይወስን ያለፈው ያለአግባብ ነው፣ በልጅ ቀለብ ውሳኔ ላይ እንዲሁም የኮንደሚኒየም ቤት ምዝገባ የተደረገውና ቁጠባ የተጀመረው በጋብቻ ውስጥ በመሆኑና የኮንደሚኒየም ቤቱ ከጋብቻ ፍቺ ውሳኔ በኃላ የደረሰ ቢሆንም የንብረት ክፍፍል ጉዳይ በክርክር ላይ እያለ የደረሰ በመሆኑ ቤቱን በጋራ መካፈል ሲገባን የተቆጠበውን ገንዘብ ድርሻ የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ያለአግባብ ነው በማለት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የቤት ቁሳቁሶች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት፣ ከወጋገን ባንክ የአሁን ተጠሪ ያወጡትን ገንዘብ በተመለከተ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ባለማስረዳታቸው ግማሽ ብር 50,000 /አምሳ ሺህ ብር/ ለአሁን አመልካች እንዲከፍሉ፣ የልጅ ቀለብ ከአንድ ሺህ ብር ወደ ሁለት ሺህ ብር ከፍ በማድረግ እንዲሁም የኮንደሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ምዝገባ የተደረገው ግራ ቀኙ ጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን፣ ለቤቱ ገንዘብ የተቆጠበውም በትዳር

ውስጥ እያሉ በመሆኑ የአሁን ተጠሪ ከፍቺ ውሳኔ በኃላ ለኮንደሚኒየም ቤቱ የከፈሉትን ገንዘብ ግማሽ አመልካች መልሰው /ከፍለው/ ቤቱ የጋራ ሊሆን ይገባል ሲል የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ ከውሳኔዎቹ መካከል በባንክ ገንዘብ እና በኮንደሚነየም ቤት ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የአሁን ተጠሪ ከባንክ ያወጡትን ገንዘብ ግማሽ ለአሁን አመልካች እንዲከፍሉ የተባለውን የውሳኔ ክፍል አጽንቶ የኮንደሚኒየም ቤቱን በተመለከተ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልስ ሲሰጡ የተጠራቀመው ገንዘብ ድርሻ እንዲሰጠኝ በማለት የጠየቁ በመሆናቸው ከጠየቁት ዳኝነት ውጪ ቤቱን እንዲካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኮንደሚኒየም ቤት ላይ የሰጠው ውሳኔ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተፈጽመውብኛል ያሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን በጠበቃቸው በኩል አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ የኮንደሚኒየም ቤት ላይ ግልጽ የሆነ ክርክር አድርገው እያለ የሥር ፍርድ ቤት ያልተጠየቀ ዳኝነት የማለቱ እና ኮንደሚኒየም ቤቱ ምዝገባ ወቅት ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ የነበሩና ሲቆጥቡ ቆይተው የግራ ቀኙ ጋብቻ ፍቺ ተወስኖ የንብረት ክፍፍል ሳይደረግ የወጣ የኮንደሚኒየም እጣ በተመለከተ የኮንደሚኒየም ቤቱ የተጠሪ የመባሉ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል ግንቦት 15 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የአመልካች ጠበቃም ሰኔ 5 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን አመልካች የኮንደሚኒየም ቤት ድርሻ እንዲወሰንላቸው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ያላነሱትን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነው ባልተጠየቀ ዳኝነት ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሻረውን በተመለከተ የአሁን ተጠሪ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በራሳቸው ይህንን አንስተው ተከራክረውበታል ወይስ ፍርድ ቤቱ በራሱ አንስቶ ነው ውሳኔ የሰጠው ? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የአሁን ተጠሪ ኮንደሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ከጋብቻ በፊት መመዝገባቸውን፣ ቤቱም ያልደረሳቸው መሆኑን ገልጸው በንብረት ክፍፍል ግን ሊካተት የማይችል የግል ንብረት ነው በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው የዳኝነት ጥያቄያቸው ላይ አንስተዋል፡፡ የአህኑ አመልካች መልሳቸውን በጽሁፍ የመስጠት መብታቸው በሥር ፍርድ ቤት የታለፈባቸው ቢሆንም በቃል ክርክር ጊዜ የኮንደሚኒየም ቤቱ በጋብቻ ውስጥ በአሁን ተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑንና የቁጠባ ገንዘብ መከፈል የጀመረውም በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን ገልጸው የተጠራቀመው ገንዘብ ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ለኮንደሚኒየም ቤት ምዝገባ የተመዘገቡት ግራ ቀኙ ከተጋቡ በኃላ በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦሌ ቡልቡላ ቅርንጫፍ በአሁን ተጠሪ ስም በተከፈተው ሂሳብ ቁጥር መቆጠብ የተጀመረውም ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን ገልጾ ከተጠራቀመው ብር 14,454.46 /አስራ አራት ሺህ አራት መቶ አምሳ አራት ብር ከአርባ ስድስት ሳንቲም/ ውስጥ ለአሁን አመልካች ብር 7,227.23 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም/ የአሁን ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በይግባኝ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሄዱበትም የኮንደሚኒየም ቤት ምዝገባ የተደረገው እና ገንዘብ መቆጠብ የተጀመረው በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን ገልጸው የኮንደሚኒየም ቤት ለአሁን ተጠሪ የደረሳቸው ምንም እንኳን የፍቺው ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ቢሆንም እጣ የወጣው በንብረት ክርክር ላይ እያሉ በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል በማለት ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ለውሳኔው መሠረት ያደረገው ይህንን ነጥብ እንደሆነ የውሳኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡

የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለማሻሻል ምክንያት ያደረገው አመልካች የኮንደሚኒየም ቤቱን ሊካፈል ይገባል የሚል ዳኝነት በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስላላነሱ የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ ውሳኔ ያላገኘውን ፍሬ ነገር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ለዚህ ሰበር ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ እንዲሁም በመልስ መልሳቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተጠሪው አመልካች የኮንደኒየም ቤት ያካፍለኝ ብላ በሥር ፍርድ ቤት አልጠየቀችም የሚል በይግባኝ ቅሬታው አላቀረበም፣ የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዚህ ዓይነት ቅሬታ በጽሁፍም በቃልም ያከራከረው ነገር የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ በተጠሪ /በሥር ይግባኝ ባይ/ በኩል በይግባኝ ቅሬታ ላይ ያልተነሳውን አንስቶ መወሰኑ የሥነ ሥርዓት ህጉን ድንጋጌ የተከተለ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይህን የቅሬታ ነጥብ እውነታ ለማረጋገጥ ይህ ችሎት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍ/ይ/መ/ቁ 130707 የሆነውን አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ /የሥር ይግባኝ ባይ / ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ ከመልስ ሰጪዋ /ከአሁን ተጠሪ / ጋር ከፍቺ በኃላ በተደረገ የንብረት ክፍፍል ከጋብቻ በፊት በይግባኝ ባይ በተደረገ የኮንደሚኒየም ቤት ምዝገባ፣ ከጋብቻ መፍረስ በኃላ በወጣልኝ እጣ በተፈጸመ ክፍያ ምክንያት የተገኘን የኮንደሚኒየም ቤት እንዲሁም ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ከአስተዳደር አካል በተሰጠው ትዕዛዝ ምክንያት መልሶ ምዝገባ መደረግን ብቻ ምክንያት በማድረግ የኮንደሚኒየም ቤት የጋራ ነው ተብሎ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ መወሰኑ አግባብ ስላልሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ  የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዳሩ ፀንቶ በነበረበት ወቅት ከተቆጠበው ገንዘብ ላይ ድርሻዋን እንድትወስድ በማለት የወሰነውን የውሳኔ ክፍል በማጽደቅ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አሻሽሎ እንዲወስንልኝ እጠይቃለሁ የሚል እንደሆነ የክርክሩ ሂደት እንዲሁም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በግልጽ ያሳያል፡፡

የአሁን ተጠሪ በጠቅላይ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በኮንደሚኒየም ቤቱ ላይ ብቸኛ ባለመብት ያደርገኛል በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያው ነጥብ በ1997 ዓ/ም መመዝገባቸውን ሲሆን ሁለተኛው ሰኔ 4 ቀን 2006 ዓ/ም ጋብቻ ፈርሶ ሚያዚያ ወር 2007 ዓ/ም እጣ ወጥቶላቸው ውል መዋዋላቸውን ነው፡፡

ከላይ የተመለከተውን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የነበረውን የአሁን ተጠሪን ክርክር ስንመለከት ክርክር ያስነሳውን የኮንደሚኒየም ቤት የአሁን አመልካች ይገባኛል ወይም ድርሻ ይሰጠኝ የሚል ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያላነሱትን የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል የሚል ቅሬታ በይግባኝ ማመልከቻም ሆነ በቃል ክርክር ወቅት የተነሳ ነገር አልነበረም፡፡ የሥር ይግባኝ ባይ /የአሁን ተጠሪ/ በይግባኛቸው ያላነሱትን አዲስ ነገር የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በራሱ አንስቶ መወሰን ይችላል ወይ? የሚለውን አግባብነት ካለው የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌ አንጻር መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተለይ ካልፈቀደ በቀር ይግባኝ ባዩ በይግባኝ ማመልከቻው ላይ ዘርዝሮ ያልገለጸውን አዲስ ነገር በማንሳት ወይም መሠረት በማድረግ ለመከራከር አይችልም ሲል የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 328 /2/ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማመልከቻው ተዘርዝሮ ከተገለጸው ወይም ክርክር ከተነሳበት ውጭ በሆነ ነገር ፍርድ መስጠት እንደማይችል የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 328 /3/ በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ከላይ እንደተገለጸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በይግባኝ ማመልከቻ ላይ ዘርዝረው ያልገለጹትን መሠረት በማድረግ አመልካች የኮንደሚኒየም ቤት ይገባኛል ሲሉ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልጠየቁትን ዳኝነት መሠረት በማድረግ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም ሲል የደረሰው ድምዳሜ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1.የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.130707 ታኅሳስ 12 ቀን 2009 ዓ/ም ግራ ቀኙን የሚያከራክረውን የኮንደሚኒየም ቤት በተመለከተ የሠጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2.የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ሌላው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

3.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 168169 ሚያዚያ 26 ቀን 2008 ዓ/ም ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

4.በቁሉ ዲምቱ ቁጥር 2 ሳይት ብሎክ 362 የሚገኘውና ቁጥሩ 36216 የሆነው በተጠሪ ስም የተመዘገበው የኮንደሚኒም ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ስለሆነም ቤቱን ግራ ቀኙ በዓይነት እኩል እንዲካፈሉ፣ በዓይነት እኩል ለመካፈል የማይቻል ከሆነና ግራ ቀኙ ከተስማሙ የቤቱን ዋጋ አንደኛው ወገን የሌላኛውን ወገን ድርሻ በገንዘብ በመክፈል ቤቱን እንዲያስቀር፣ በዚህ ካልተስማሙ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡

5.የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

6.የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

7.መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰ.መ.ቁ.131498

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1.ዳኜ መላኩ

2. ሪታ ቶለሳ

3. ተኽሊት ይመሰል

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. አብዩ ካሳሁን

አመልካች፡- አቶ መሳይ ቦጋለ - ተወካይ ወ/ሮ አይናለም በቀለ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይናለም አለሙ - ጠበቃ ፋሲል ይነሱ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የብድር ዉልን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.176598 በ14/11/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁን አመልካች ተከሳሽ ሆኖ ተከራክሯል፡፡ ከሳሽ ባቀረበችዉ ክስ በከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል በ18/1/2003 ዓ.ም በተደረገ የገንዘብ ብድር ዉል ተከሳሽ ብር 400,000 /አራት መቶ ሺህ/ ከከሳሽ ተበድረዉ በዉሉ መሰረት ስላልከፈለ ይህን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለኝ በማለት በተፋጠነ ሥነሥርዓት ክስ አቅርቧል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ ተከሳሽ ቀርበዉ የመከላከያ መልስ እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ማመልከቻ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ሳይቀበለዉ አልፎታል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ በብድር ብር 400,000 /አራት መቶ ሺህ/ ከከሳሽ የወሰደ መሆኑን የቀረበዉ የገንዘብ ብድር ዉል ሰነድ የሚያስረዳ በመሆኑ ተከሳሽ በዉሉ መሰረት የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለሆነ ከሳሽ ደግሞ በዉሉ መሰረት እንዲፈጸምላቸዉ የመጠየቅ መብት ስላላቸዉ ተከሳሽ ይህን በብድር የወሰደዉን ገንዘብ ለከሳሽ እንዲከፍል ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ሐምሌ 9 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- የአሁን ተጠሪ ላቀረቡት ክስ አመልካች ማስፈቀጃ በማቅረብ ወደ ክርክር እንድገባ ያቀረብኳቸዉ ምክንያቶች የብድር ዉሉ በይርጋ የሚታገድ ነዉ፣ ዉሉ ፈራሽ ነዉ፣ ብድሩ ሕገ ወጥ የአራጣ ብድር ዉል ስለሆነ ፈራሽ ነዉ፣ የብድር ዉሉ የኮንዶሚኒያም ቤት ሽያጭ ዉል ተቀጽላ እና ጥገኛ /መተማመኛ/ ዉል ነዉ፣ አመልካች በ1997 ዓ.ም የደረሰኝን ባለ ሁለት ክፍል መኝታ ያለዉ የኮንዶሚኒየም ቤት ለተጠሪ በመሸጥ ዉክልና ሰጥቼ ለዚህ መተማመኛ እንዲሆን የብድር ዉል በማስመሰል የተፈረመ እንደሆነ በመግለጽ ያቀረብኩት ሲሆን የሥር ፍ/ቤት ማስፈቀጃዉን ሳይቀበል እና መልስ እና ማስረጃዬን ሳይሰማኝ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር፣በዚህ ጉዳይ አመልካች በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት ለቀረበበት ክስ መከላከያ ለማቅረብ ያቀረበዉ ማስፈቀጃ በሥር ፍ/ቤት ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት፣ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘዉ መሰረት መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--አመልካች ለቀረበባቸዉ ክስ ሊያስተባብልላቸዉ የሚችል ማስፈቀጃ በሥር ፍ/ቤት ባላቀረቡበት በሀሰት አቅርቤያለሁ በማለት ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ

በማጽናት በቂ ኪሳራ እንዲወስንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋገዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት ክስ አመልካች በ18/1/2003 ዓ.ም በተደረገ የገንዘብ ብድር ዉል መሰረት ብር 400,000 ተበድረዉ ስላልከፈሉ ገንዘቡን ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ በተፈጠነ ሥነ ሥርዓት ክስ ማቅረባቸዉ ተመልክተናል፡፡ የአሁን አመልካች በበኩሉ ለዚህ ክስ የመከላከያ መልስ ማቅረብ እንዲችል እንዲፈቀድለት የማስፈቀጃ ማመልከቻ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን የሥር ዉሳኔ ያሳያል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበዉን የማስፈቀጃ ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ አመልካች በቀረበዉ ክስ መሰረት በብድር ዉሉ መሰረት የወሰደዉን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል የወሰነ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንጻር ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት መሰረት የቀረበ ነዉ በሚል ምክንያት የአመልካች ማስፈቀጃ ተቀባይነት ማጣቱ የሕጉን ዓላማ ያገናዘበ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የፍትሐ ብሔር ክርክር የሚመራበት ሂደት በፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ላይ ተመልክቷል፡፡ የሥነሥርዓት ሕጉ የክርክሮችን ባህር ከግንዛቤ በማስገባት የክስና የመልስ አቀራረብ ሂደቱን በሚያመላክት የተቀረጸ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት የፍትሓ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ በአምስተኛ መጽሐፍ ልዩ ስነሥርዓት ምዕራፍ 1 በአጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ላይ ስለሚፈጸም ሥነ ሥርዓት ከአንቀጽ 284--292 ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ ሥርዓት የሚቀርብ ክርክር የሕግ አዉጭዉን ሃሳብ የሚያሳካ ነዉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ነገር ግን የእነዚህን ድንጋጌዎች መስፈርት የማያሟሉ ክሶች በዚህ ሥርዓት የሚቀርቡ ከሆነ እና በተከሳሽ በኩል የሚቀርበዉን የመከራከርና የመከላከል መብቱን የሚያሳጡ ከሆነ በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉን የመሰማት መብት የሚነፍግ ይሆናል፡፡ በአጭር ሁኔታ የሚወሰኑ

ክርክሮች መመራት ያለባቸዉ በዚህ ምዕራፍ በተደነገገዉ አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም በአጭር ሁኔታ የሚወሰኑ ክርክሮች ወይም በተፋጠነ ሥነሥርዓት የሚቀርብ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.284 የተመለከተዉን ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟላ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ ሥር እንደተመለከተዉ ከሳሽ ከተከሳሽ ላይ የሚጠይቀዉ ሂሳብ ወይም ጥሬ ገንዘብ ከነወለዱ ወይም ያለወለድ ወይም ልኩ ተወስኖ የታወቀ ሲሆን ክሱም የተመሰረተዉ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ምክንያቶች ላይ በሆነ ጊዜ ፡- /ሀ/ በዉል መሰረት በግልጽ በተደረገ ዉል ወይም በሐዋላ ወረቀት ወይም በገንዘብ አለብኝ ሰነድ ወይም በቼክ ወይም ተራ የሆነ የባለዕዳነትን በሚገልጽ ዉል በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ አግባብ የሚቀርብ ክስ የተፋጠነ ሥነሥርዓት የሚል አርዕስት ተሰጥቶና በቃለ መሓለ ተደግፎ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዚህን ድንጋጌ መስፈርት የሚያሟላ ክስ ሊቀርብ የሚገባዉ በዚህ በአጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ወይም በተፋጠነ ሥነሥርዓት እንደሆነ የሚያከራክር አይሆንም፡፡

በዚህ ድንጋጌ አግባብ የሚቀርብ ክስ ደግሞ የተከሳሽ የመከራከርና የመከላከል መብት ሙሉ ለሙሉ ለመንፈግ ታስቦ የተቀረጸ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.285 ይዘትና ዓላማ እንደሚያመለክተዉ ተከሳሽ ቀርቦ መከላከያ እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ለፍ/ቤት ማመልከት እንደሚችል ነዉ፡፡ በዚህ መልክ የመከላከያ መልስ እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ማመልከቻ ያላቀረበ እንደሆነ ግን ከሳሽ የጠየቀዉን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል እንደሚወሰንበት ያስገነዝባል፡፡ ተከሳሽ ቀርቦ እንዲከላከል እንዲፈቀድለት የሚያመለክተዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.286 ሥር በተመለከተዉ አግባብ ሊሆን እንደሚገባዉ ነዉ፡፡ ተከሳሽ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበዉ ማመልከቻ በቃለ መሓለ ተደግፎ መቅረብ እንዳለበት ነዉ፡፡ ፍ/ቤቱ የቀረበዉን መሓላ ቃሉን ተቀብሎ ሊመረምር እንደሚችልና የቀረበዉ የመሐላ ቃልና ማመልከቻዉ ለከሳሽ እንዲደርሰዉ ማድረግ እንደሚገባዉ ይደነግጋል፡፡ ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ለመከላከል ማስፈቀጃ ማመልከቻ እና መሐላ ቃል የተቀበለዉ እንደሆነ ተከሳሽ ሙሉ ክርክሩን እንዲያቀርብ የሚደረግ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ማስፈቀጃ ያልተቀበለ እንደሆነ ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.287 መሰረት ወዲያዉኑ ለከሳሽ ፍርድ መስጠት እንደሚገባዉ ማየት ይቻላል፡፡ ይህ የተፋጠነ ሥነሥርዓት የክርክር አመራር

የሰዎችን የመከላከል የመሰማት የመደመጥ ሕገ መንግስታዊ መብትን በሚደፈጥጥ መልኩ መተርጎም እና ሥራ ላይ መዋል እንደማይገባዉ የሚያከራክር አይደለም፡፡
በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር የብድር ዉሉ የተደረገዉ በማስመሰል ነዉ፣ በመካከላችን የኮንዶሚኒያም ቤት ሽያጭ ዉል በሕግ በተከለከለዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ በመደረጉ ለተጠሪ መተማመኛ እንዲሆናቸዉ ይህን የብድር ዉል ፈረምኩኝ እንጂ የተበደርኩት ገንዘብ የለም የሚል ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ለተጠሪ የኮንዶሚኒያም ቤት በመሸጥ ገንዘብ ከመቀበሌ ዉጭ በዚህ የብድር ዉል ምንም ዓይነት ገንዘብ አልተቀበልኩም በማለት በመከራከር ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን አመልካች እና ተጠሪ መካከል የኮንዶሚኒያም ቤት ሽያጭ ዉል ተደርጓል ወይስ አልተደረገም? ይህ የብድር ዉል ከኮንዶሚኒያም ቤት ሽያጭ ዉል ጋር ግንኙነት አለዉ ወይስ የለዉም? ሁለት ዉሎች አሉ ወይስ የሉም? የዉሎቹ ቁርኝት ወይም ግንኙነት ምንድን ነዉ? የሚሉት ነጥቦች ከግራ ቀኛቸዉ በሚቀርበዉ ክርክርና ማስረጃ መመርመር የሚገባቸዉ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የመከላከያ ክርክሩን እንዲያቀርብ ሊፈቅዱለት የሚገባቸዉ የሚያመለክት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ መሰረት አመልካች የመከላከያ መልስ እንዲያቀርብ በመፍቀድ ሙሉ የመከላከያ ክርክሩን እንዲያቀርብ በማድረግ ተገቢዉን ማጣሪያ በማድረግ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ አመልካች ያቀረበዉን የመከላከያ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.234216 በ28/6/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.176598 በ14/11/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ መደበኛ የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ

የአሁን አመልካች የመከላከያ መልስ እና ክርክሩን እንዲያቀርብ በማድረግ፣ በሕጉ አግባብ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 /1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

5. ነሐሴ 11 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

የሰበር መ/ቁ 135590

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ፋንታሁን ተፈሪ - ጠበቃ ብርሃኑ ከፍያለው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አበባ ገ/ማርያም - ጠበቆች ጉሣዬ ጉርሙና አለማየሁ ለገሠ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጊዚያዊ እግድ ትዕዛዝ ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን እየተከራከሩ ሲሆን ለአሁኑ አቤቱታ መነሻ የሆነውን የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ የቀረበው በአሁኑ አመልካች ጠያቂነት ነው፡፡ ዋናው ክርክር የጋብቻ ውጤት የሆነውን ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ሁኖ ግራ ቀኙ አሉን የሚሏቸውን ንብረቶችን አይነታቸውንና ብዛታቸውን ዘርዝረው የክፍፍል ጥያቄውን አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በግራ ቀኙ የንብረት ክፍፍል ላይ ግራ ቀኙ በሕጉ አግባብ እንዲከራከሩ ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የግራ ቀኙን የጋራና የግል ንብረት ስለመሆናቸው ግራ ቀኙ የተማመኑባቸውን ንብረቶች በመለየት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 በሚደነግገው አግባብ በእምነታቸው መሰረት ከፊል ዳኝነት ሰጥቷል፡፡ ግራ ቀኙ በተካካዱባቸው ሌሎች ንብረቶች ላይ ግን ክርክሩ እንዲቀጥል አድርጓል፡፡ በግራ ቀኙ እምነት መሰረት ከፊል ፍርድ ያረፈባቸው ንብረቶችም አንድ G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት፣ አንድ ፒካፕ መኪናና አልጋ ሲሆኑ እነዚህ ንብረቶች በሕጉ አግባብ እንዲከፋፈሉም ተብሎ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት G+1 የሆነ መኖሪያ

ቤት በሐራጅ የተሸጠ ሲሆን የአሁኗ ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ጥር 09 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በሌሎች ንብረቶች ላይ በግራ ቀኙ መካከል የሚካሄደው ክርክር ውጤት ለተጠሪ የሚያስገኝላቸው ጥቅምና መብት ያለ መሆኑን ጠቅሰው የአመልካች ድርሻ የሆነው የቤቱ ሽያጭ ገንዘብ ለአመልካች ሳይከፈል ተከብሮ እንዲቆይላቸው ዳኝነት ጠይቀው የአሁኑ አመልካችም ድርሻቸው ሊታገድ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት ከተሸጠበት ገንዘብ ውስጥ ለአመልካች የሚደርሳቸው ገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 መሰረት ተከብሮ እንዲቆይ የሚደረግበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በመሻር ገንዘቡ ለጊዜው ተከብሮ እንዲቆይ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ፍርድ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሃብት ስለመሆኑ ግራ ቀኙ ተማምነው በሕጉ አግባብ እንዲሸጥ ከተደረገ በኃላ የአመልካች ድርሻ ታግዶ እንዲቆይ የሚደረግበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትዕዛዝ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ መሰረታዊ ይዘቱ፡- ግራ ቀኙ የጋራ ስለመሆኑ ተማምነው

በሀራጅ ከተሸጠው ቤት ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ የአመልካች ድርሻ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር የሚል ሆኖ አገኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ የጋብቻ ውጤት በሆነው ንብረት ላይ ክርክር ሲያደርጉ አከራካሪው እግድ የተሰጠበት ገንዘብ የተገኘው የግራ ቀኙ መሆኑ አካራካሪ ያልሆነው ቤት በሐራጅ ተሸጦ መሆኑን፣ ግራ ቀኙ በሌሎች ንብረቶች ላይ ክርክር ሲያደርጉ ቆይተው የሥር ፍርድ ቤት በ5/5/2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውሳኔ በመስጠት መዝገቡን የዘጋው መሆኑን፣ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ድርሻ የሆነው ገንዘብ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በማለት ዳኝነት የሰጠውም ተጠሪ ከአመልካች የሚፈልጉት ገንዘብ ካለ ለአፈጻጸም እንዲያመቻቸው በሚል ሆኖ እግዱ ተግባራዊ የሚሆነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት የገንዘብ ጥያቄ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ መሆኑን በመ/ቁጥር 17440 መጋቢት 01 ቀን 2008 ዓ./ም የሰጠው ውሳኔ የተፈፃሚነት ክፍል በግልጽ የሚያሳይ መሆኑን፣ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች በተጠሪ መካከል የነበረውን የገንዘብ ክርክር ተመልክቶ እልባት መስጠቱን በመ/ቁጥር 198855 ጥር 05 ቀን 2009 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ እንደሚያሳይ አመልካች ገልፀው ለአቀረቡት የሠበር ክርክር በተጠሪ የቀረበ ግልጽ ማስተባበያ የሌለ መሆኑን ተጠሪ ለዚህ ችሎት የሰጡት የመልስ ማመልከቻ የሚያሳይ መሆኑን፣ የሥር ፍርድ ቤት በገንዘብ ክርክሩ ላይ እልባት የሰጠ ከመሆኑም በላይ በዚህ ውሳኔ በባንኮቹ ውስጥ ይገኛል ተብሎ ከተረጋገጠውና ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ ከተገለጸው ከብር 303,401.06(ሶስት መቶ ሶስት ሺህ አራት መቶ አንድ ብር ከዜሮ ስድስት ሳንቲም) ውጪ ተጠሪ ከአመልካች የሚፈልጉት ገንዘብ ስለመኖሩ የማያሳይ መሆኑን፣ ተጠሪም ከአመልካች የሚፈልጉት ገንዘብ በባንኮች ውስጥ ይገኛል ከተባለው ውጪ ስለመሆኑ በሰበር አቤቱታቸው ካለመግለጻቸውም በተጨማሪ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው የገንዘብ ክርክር ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸውና በሕጉ አግባብ ለበላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆኑን ጠቅሰው ያቀረቡት ክርክር የሌለ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ዕግድ የሚሰጠው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንብረት የሚጠፋ፣ የሚበላሽ፤ ተከሳሹ ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት፣ ለመሸጥ ወይም በሌላ ዘንድ በተሰጠ ውሳኔ ንብረቱን ያለአግባብ አዛውሮ ለመስጠት ወይም ለመሸጥ ያቀደ፣ መሆኑ ወይም

የባለመብቱ ጥቅም ለመጉዳት ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት የሚደረግ እንቅስቃሴ መኖሩን ፍርድ ቤቱ ከተገነዘበ አስፈላጊውን ትዕዛዝ የሚሰጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 154 (1) መረዳት ይቻላል፡፡ የድንጋጌው መሰረታዊ ዓላማም ዳኝነት እንዲሰጥለት የጠየቀ ወገን በፍርዱ ሂደት ረቺነቱ ቢረጋገጥለት የተሰጠውን ፍርድ ለማስፈፀም ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርለት ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ከአመልካች ላይ የሚፈልጉት ገንዘብ ክርክር ተደርጎ እልባት ያገኘ ሲሆን የተጠሪ መብት ያለበት ስለመሆኑ የተረጋገጠው ጥሬ ገንዘብም በባንኮች ያለ መሆኑን በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 198855 በ05/05/2009 ዓ/ም የተሰጠው የውሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡ አከራካሪውን እግድ የሰጠው ፍርድ ቤት እግዱ ተግባራዊ እንዲሆን ትእዛዝ የሰጠውም ይኼው የገንዘብ ክርክር በስር ፍርድ ቤት ታይቶ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

በመሆኑም የእግዱ ትዕዛዝ በባህርይው ጊዜያዊ ከመሆኑም በላይ እግዱ እንዲቆይ ምክንያት የሆነው ክርክርም እልባት ያገኘ በመሆኑ G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት ተሽጦ የተገኘው የአመልካች ድርሻ ገንዘብ ተከብሮ የሚቆይበት ሕጋዊ ምክንያት ቀሪ የሆነ መሆኑን አሁን ካለው የግራ ቀኙ የክርክር ሂደትና ደረጃ ተገንዝበናል፡፡ ሲጠቃለልም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች እግዱን የሰጡበት አግባብ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 መሰረታዊ አላማ የሚነቀፍበት አግባብ ያልነበረ ቢሆንም አሁን ክርክሩ ከደረሰበት ደረጃና ከእግዱ ባህርይ አንጻር ሲታይ እግዱ የሚቆይበት አግባብ የሌለ በመሆኑ በተለወጠ ምክንያት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ማረም ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 174440 መጋቢት 01 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 126988 ጥቅምት 02 ቀን 2009 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት ተሽጦ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ የአመልካች ድርሻ ታግዶ የሚቆይበት ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡ ሆኖም ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ በሠጠው ውሣኔ በስርዓቱ መሠረት

የሚያቀርቡት ቅሬታ ካለ የእግድ ጥያቄውን ከማቅረቡ  ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡

3. የዚህ ችሎት ክርክር ያስከተለው ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

የሰ/መ/ቁጥር---136901

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካቾች:-** 1ኛ. ሕጻን ቤተልሄም ሰለሞን ሞግዚት ወ/ሮ አዜብ እንግዳ

2ኛ. ሕጻን ቃለአብ ሰለሞን ሞግዚት አዜብ እንግዳ

**ተጠሪዎች:-** 1ኛ. አቶ ጌታቸዉ ገ/መስቀል

2ኛ. ወ/ሮ ንግስት ሃይሉ

3ኛ. ወ/ሮ ትርሐስ ሃይሉ

} ጠበቃ ሀብታም ስብሀቱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

አመልካቾች በትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዕርቅ ጉዳዩን ለመጨረስ ጠይቀዉ የተጠሪዎች ወንድም ወደ ዉጭ በመሄዱ ዛሬ ነገ ይመጣል እያሉ ሊሰበሰቡ ስላልቻሉ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት የዘጋዉ መዝገብ ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ ይታይልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ለተጠሪዎች እንዲደርሳቸዉ ተደርጎ በሰጡት መልስ ጉዳዩን በእርቅ እጨርሳለሁ ብለዉ በእርቅ መጨረስ ካልተቻለ ይህንኑ ለፍ/ቤቱ በቀጠሮ እለት ቀርቦ በማስረዳት ጉዳዩ እንዲቀጥል መጠየቅ ሲገባቸዉ የአመልካቾች ጠበቃ ባለመቅረቡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ከተዘጋም ሁለት ዓመት ከ6 ወር

ሆኖታል፡፡ መዝገቡ የተዘጋዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69 ሆነ 73 ለዉጥ የሌለዉ በመሆኑ መዝገቡ ሊንቀሳቀስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት ከሳሾች ጉዳዩን በዕርቅ ለመጨረስ ከሄዱ በኃላ ባለመቅረባቸዉ መዝገቡ መዘጋቱ ተገቢ ሲሆን መዝገቡ ከተዘጋ ከ2 ዓመት ከ6 ወር በኃላ የሚከፈትበት አግባብ የለም፤ በቀጠሮ ቀን እርቁን አልጨረስንም ቀጠሮ ይሰጠን ብለዉ መጠየቅ እየተገባቸዉ ይህን አላደረጉም በማለት የአመልካቾችን መዝገብ ይንቀሳቀስልን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተዉ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገቡን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሰጠዉ ብይን በቀን 06/10/2005 ዓ.ም መዝገቡን የዘጋዉ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በቀን 22/12/2005 ዓ.ም ብይኑን በመሻር ወደ ፍሬ ጉዳዩ ገብቶ እንዲያከራክር ወስኖ መልሶለታል፡፡ ከዚያም መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ጠይቀን በቀን 11/02/2006 ዓ.ም ለቀን 28/02/2006 ዓ.ም ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ሳይቀርቡ በሽማግሌ እንድንጨርስ ጊዜ ይሰጠን ስላሉ እኛም ለፍ/ቤቱ ይህን አሳዉቀን ሄደናል፡፡ ፍ/ቤቱ ራሱ በቀን 23/03/2006 ዓ.ም ቀጠሮ ግራቀኙ ሳንቀርብ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት ዘግቶታል፡፡ ግራቀኛችን ጉዳዩን በእርቅ እንጨርሳለን ብለን ያቀረብነዉ በሌለንበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 69 መሠረት ለጊዜዉ መዝጋት ሲገባዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዝጋቱ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት ግራቀኛችን በማናዉቀዉ እኛ ተስማምተን እንመጣለን ብለን የሄድነዉ በማስመሰል 2 ዓመት ከ6 ወር ሆኖታል መዝገቡ ሊንቀሳቀስ አይገባም ማለቱ አግባብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የተጠሪዎች ወንድም ወደ ዉጪ አገር በመሄዱ እየጠበቅን ቆይተን እያለ መዝገቡ የተዘጋዉ በምን ምክንያት መሆኑን ሳናዉቅ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዘጋቱ አግባብ ስላልሆነ የስር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ ከፍ/ቤት የሄዱ ቢሆኑም የተከሳሽ ወገን በተለያየ ምክንያት ለእርቁ ዝግጁ ባለመሆናቸዉ የአሁኑ አመልካቾች ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስ ሲያመለክቱ ከ1 ወር በላይ ጊዜዉ ያለፈ ስለሆነ የተዘጋዉ መዝገብ ሊንቀሳቀስ አይገባም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 69-73 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ካላቸዉ ሕጎች መሠረት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በመቀባበል ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪዎች መልስ ይዘት፡- የስር ፍ/ቤት አመልካቾች ጉዳዩ በእርቅ ባያልቅም ለ23/03/2006 ዓ.ም በሰጠዉ ቀጠሮ መቅረብ ሲገባቸዉ ባለመቅረባቸዉ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.73 መሠረት መዝጋቱም ሆነ ይንቀሳቀስልን አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74(2) መሰረት በአንድ ወር ዉስጥ የቀረበ ባለመሆኑ ዉድቅ መደረጉ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ ስለሆነም ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጉትን የጽሁፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይን እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡
ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለዉ ጉዳዩ በክርክር ሂደት ላይ እያለ የአሁን አመልካቾች ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ በተጠሪዎች መጠየቃቸዉን ለፍ/ቤቱ በማስታወቃቸዉ ፍ/ቤቱ ቀጠሮ ለሕዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም ለዉጧል፡፡ በዚህ ቀጠሮ ግራቀኙ ባለመቅረባቸዉ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መዝገቡን መዝጋቱን ገልጾ ተመላሽ አድርጓል፡፡ ከ2 ዓመት ከ6 ወር በኂላ ግንቦት 17 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የተዘጋዉ መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸዉ መጠየቃቸዉን ተገንዝበናል፡፡ አመልካቾች ለሕዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም ቀጠሮ የተያዘዉ ግራቀኞችን በሌለንበት ነዉ የሚለዉ ክርክር ለቀጣይ 2 ዓመት ከ6 ወር ጉዳዩን ያልተከታተሉ በመሆናቸዉ የሚያመጣዉ ለዉጥ የለም፡፡ አመልካቾች መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69 መሠረት ሊዘጋ እየተገባዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት መዘጋቱ ስህተት ነዉ በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ በተመለከተ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት የተዘጋዉ ሐምሌ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠዉ

ብይን ሳይሆን 2 ዓመት ከ6 ወር በፊት ሕዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበዉ ቅሬታ በዚህ መዝገብ ሊታይ አይችልም፡፡

በመሠረቱ አንድ ከሳሽ የሆነ ወገን በአንድ ሰዉ ላይ ክስ ከመሠረተ በኃላ በመጀመሪያዉ ቀጠሮ ይሁን ክርክር ላይ ባለበት ወቅት በተሰጠ ቀጠሮ ቀጠሮን አክብሮ በራሱ ወይም ወክሎት ሊከራከር የሚችል ሰዉ አለመቅረብ ዋጋ እንደሚያስከፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጋችን ስለተከራካሪ ወገኖች መቅረብና አለመቅረብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 69 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች፣ ስለቀጠሮ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.197 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንዲሁም ክስን መተዉ አስመልክቶ ከተደነገጉ ጥብቅ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 275 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት አንድ ጉዳይ በማንኛዉም የክርክር ደረጃ ላይ በሚገኝበት ወቅት ተከራካሪ ወገኖች በእርቅ ወይም በግልግል ስምምነት የመጨረስ መብት ያላቸዉ ቢሆንም ክሱን ከሳሽ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 279(1) መሠረት ፍርድ ቤትን ሳያስፈቅድ ያቀረበዉን ክስ የተወ ከሳሽ ኪሳራ እንዲከፍል ሊወሰንበት ከመቻሉም በላይ በተወዉ ክስ አዲስ ክስ መመስረት እንደማይችል በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች በክርክር ላይ ያለዉን ጉዳያቸዉን በእርቅ ለመጨረስ ቀጠሮ እንዲለወጥላቸዉ ጠይቀዉ ተለዉጦላቸዉ በተሰጠዉ ቀጠሮ ቀርበዉ የደረሱበትን ደረጃ ለፍ/ቤቱ አላሳወቁም፡፡ ከዚህ አልፎ ለ2 ዓመት ከ6 ወር ጉዳያቸዉን አልተከታተሉም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ በቀጠሮ ዕለት ላለመቅረባቸዉ ያቀረቡት ምክንያት ምንም ይሁን ከ2 ዓመት ከ6 ወር በኃላ የተዘጋዉን መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸዉ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የተዘጋዉ መዝገብ 2 ዓመት ከ6 ወር በኃላ የሚንቀሳቀስበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት የተዘጋዉ መዝገብ አይንቀሳቀስም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ብይን የስነ ስርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች አላማ የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ በአብላጫ ድምጽ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል በማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1631 ሐምሌ 01 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 88251 ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ባለመቻሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

## የሐሳብ ልዩነት

ስሜ በተ.ቁ 5 ላይ የተገለጸው ዳኛ አብላጫው ድምጽ አመልካቾች በክርክር ላይ ያለውን ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ ቀጠሮ እንዲለወጥላቸው ጠይቀው ተለውጦላቸው በተሰጠው ቀጠሮ ቀርበው የደረሱበትን ደረጃ ለፍ/ቤቱ ያላሳወቁ እና ለሁለት ዓመት ከሥድሥት ወር ጉዳያቸውን ያልተከታተሉ በመሆኑ በቀጠሮ ዕለት ላለመቅረባቸው ያቀረቡት ምክንያት ምንም ይሁን ከሁለት ዓመት ከሽድሥት ወር በኋላ የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸው የሚያደርጉበት የሕግ አግባብ የለም በማለት በደረሰበት መደምደሚያ ስላልተሥማማሁ በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡ በሐሳብ ለመለየት ያስቻሉኝን ምክንያቶችም እንደሚከተለው አስፍሬአለሁ፡፡

የሥር ፍ/ቤት አመልካቾች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69/2 ግራቀኙ ባለመቅረባቸው የሚዘጋ መዝገብ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 ከሳሽ ባለመቅረቡ በሚዘጋ መዝገብ መካከል ያለው ልዩነት ሁለቱም በሚዘጋበት ጊዜ ስላልነበሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መዘጋቱ ትክክል አይደለም የሚባልበት ምክንያት የለም፤ከሳሽ በቀጠሮው ዕለት ካልተገኘ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት ሊዘጋ ግድ ነው፤ከሳሽ በዕርቅ ለመጨረስ ቀጠሮ ከተሰጠ በኋላ በቀጠሮ ዕለት ቀርቦ ለማስረዳት ስላልቻለ በቀጠሮ አልተገኘም ተብሎ መዘጋቱ ስህተት የለውም፤ጉዳዩ ለሽማግሌ ከተመራ በኋላ ሽማግሌዎች የተከሳሾች ወንድም ወደ ውጪ ስለሄዱ እና ሽማግሌዎች ሊሰበሰቡ ስላልቻሉ ነው በማለት

ያቀረቡት ምክንያትም ከዓመታት በኋላ ቆይተው መዝገቡን ለማንቀሳቀስ የሚያስችላቸው ምክንያት አይደለም በማለት ነው፡፡

በእርግጥ የፍትሐብሔር ክርክር በጥብቅ ሥነ-ሥርዓት የሚመራ ስለመሆኑ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከቁጥር 65-78 ስለተከራካሪዎች መቅረብ እና ሳይቀርቡ መቅረት አስመልክቶ ስለሚያስከትለው ውጤት ከተደነገጉት ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ እነኚህ ጥብቅ የሆኑ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ  ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚገባውም ጉዳዩን የሚመራው ፍ/ቤት እንደየጉዳዩ አግባብነት ተገቢውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ በማድረግ ጉዳዩን መምራት ሲችል እንደሆነ ድንጋጌዎቹ ራሣቸው አመላካች ናቸው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ የሚከራከሩበትን ጉዳይ በዕርቅ ለመጨረስ አስበው የሥር መዝገብ የግራቀኙን የዕርቅ ሥምምነት ለመጠባበቅ መዝገቡን ቀጥሮት  የነበረ እና በዕለቱ ግራቀኙ ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዝገቡን የዘጋው መሆኑ አላከራከረም፡፡ ፍ/ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት ከዘጋው በኋላ አመልካቾች መዝገቡ ተንቀሳቅሶ ጉዳያችን ይታይልን በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ፍ/ቤቱ ውድቅ ማድረግ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ከመታየቱ በፊት ከመነሻውም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተገቢውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ በማድረግ መዝገቡን ዘግቷል? ወይስ አልዘጋም? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊያገኝ ይገባል፡፡

ግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍ/ቤቱ መዝገቡን እንደሚዘጋው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69/2/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተዘጋ መዝገብ ውጤትም መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ከሳሹ ተገቢውን ዳኝነት እና ኪሣራ ከፍሎ መዝገቡን እንደገና ከማስከፈት እንደማያግደው ወይም ከሳሹ በዕለቱ ሳይቀርብ የቀረው በበቂ ምክንያት  እንደሆነ ዳኝነት እና ኪሣራ ሳይከፍል መዝገቡ እንዲከፈት ማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ ከዚሁ ሕግ ቁጥር 71 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት አንድ መዝገብ ሊዘጋ የሚችለው ክርክሩ እንዲሰማ በተያዘው ቀነ-ቀጠሮ ከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ እና ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ የካደ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት መዝገብ የተዘጋበት ከሳሽ ለክሱ መነሻ የነበረውን ነገር መሠረት በማድረግ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል በሥነ-ሥርዓት

ሕጉ በቁጥር 74/1 ላይ ተደንግጓል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 279/1/ ከሣሽ ከፍ/ቤቱ ፈቃድ ሳይቀበል ክሱን የተወ እንደሆነ ያለፈቃድ በተወው ክስ ሌላ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 እና 279/1/ መሠረት የሚዘጋው መዝገብ ከሳሹን ለክሱ መነሻ የነበረውን ነገር መሠረት በማድረግ እስከወዲያኛው ክስ እንዳያቀርብ የማድረግ ውጤት ያለው ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69/2 መሠረት የሚዘጋው መዝገብ ደግሞ ከሳሹ ተገቢውን ዳኝነት እና ኪሣራ ከፍሎ መዝገቡን እንደገና ከማስከፈት የማያግደው በመሆኑ ፍ/ቤቶች የተከራካሪ ወገኖችን አለመቅረብ መሠረት በማድረግ በተከራካሪ ወገኖች ላይ የተለያየ ውጤት የሚያስከትሉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት መዝገብ ሲዘጉ ተገቢውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መዝገቡ ከተዘጋ በኋላም ተከራካሪ ወገኖች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ የሚያቀርቡት አቤቱታም ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ከመነሻውም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተገቢውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ በማድረግ መዝገቡን የዘጋው በሆነ ጊዜ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 37 ማንኛውም ሠው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም በሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከመነሻውም ቢሆን መዝገቡ ለእርቅ በተቀጠረበት ሁኔታ ግራቀኙ አልቀረቡም በማለት ለጉዳዩ አግባብነት በሌለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዝገቡ በተዘጋበት ሁኔታ የበታች ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ዜጎች በሕገመንግሥቱ የተረጋገጠላቸውን ፍትሕ የማግኘት መብት የማሳጣት ውጤት ያለው ሆኖ ስላገኘሁት አብላጫው ድምጽ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ከደረሰበት መደምደሚያ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁ. 139138

ህዳር 20 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋዬ አስማማው

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ኃይሉ ሂንጌ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አመርቲ ነሼ የፊንጫኣ ሀይል ማመንጫ ፕሮጀክት ነገረ ፈጅ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የክርክሩ መነሻ በጉዳት ካሳ ክርክር ላይ ተሳታፊ ለመሆን የቀረበ ነው፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የአሁን አመልካችን ጨምሮ አራት ከሳሾች የአሁን ተጠሪ ይዞታቸውን ለኤሌክትሪክ ማመንጫ ስለወሰደባቸው የንብረት ጉዳት ካሳ እንዲከፍል ክስ አቅርበው ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 14442 በቀን 28/6/2006 ዓም የሰጠውን ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሥር ከሳሾች መካከል የአሁኑን አመልካች ጨምሮ ሶስቱ ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት አቅርበው ሲፀናባቸው ከይግባኝ ባዮች መካከል አቶ አመንቴ ደበሎ እና አቶ በላይ በየነ የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሲያቀርቡ የአሁን አመልካች ተሳታፊ አልነበሩም፡፡ የተጠቀሱት ሁለቱ አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በሰበር መዝገብ ቁጥር 111629 የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሊጣሩ የሚገባቸውን ነጥቦችን በመለየት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት ለሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ መልሶታል፡፡

ጉዳዩ ከተመለሰ በኃላ የአሁኑ አመልካች በነጥብ የተመለሰው ጉዳይ እሳቸውንም የሚመለከት በመሆኑ ወደ ክርክሩ ለመግባት ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ሲያመለክቱ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ የተሻረው ሁለቱን ከሳሾች በሚመለከት በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ አመልካችን አይመለከታቸውም ሲል ትዕዛዘ ሰጥቷል፡፡

ይህን ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት አቅርበው ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመውብኛል ያሏቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ የአሁን አመልካች ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን በተጠሪ ላይ የካሳ ጥያቄ አቅርበው እስከ መጨረሻ ድረስ ተከራክረው ክርክራቸው ተቀባይነት በማጣቱ ከነሱ ጋር ተከራካሪ የነበሩ ሰዎች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበው በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት ተገቢው ማጣራት ተደርጎ እንዲወሰን በመመለሱ የአሁን አመልካች በተመለሰው ነጥብ መሠረት ለመከራከር የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ለማጣራት ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብለናል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ተጠሪን በአድራሻ ለውጥ ምክንያት ለማግኘት ያለመቻላቸውን ገልጸው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ በጠየቁት መሠረት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ባለመቅረቡ ምክንያት መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አስቀድሞ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ደርሶ በነጥብ በተመለሰው ጉዳይ የአሁኑን አመልካችን ጨምሮ አራት ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው እያንዳንዳቸው የሚገባቸውን የንብረት ጉዳት ካሳ ግምት በማቅረብ በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.14442 በሆነው ተከራክረዋል፡፡ ክስ ያቀረቡት በአንድ መዝገብ፣በአንድ ዓይነት ጉዳይ፣ በአንድ ላይ ነው፡፡ ይህም የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት

ህግ ቁጥር 35 ድንጋጌን የተከተለ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ክስ አቅርበው ከተፈረደባቸው ሰዎች መካከል አንዱ ይግባኝ አቅርቦ ውሳኔው ከተሻረ ወይም ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ ይግባኝ ያልጠየቀው ሰው የፍርዱ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 331 በአንድ ክርክር ውስጥ የከሳሾች ወይም የተከሳሾች ብዛት ከአንድ በላይ ሲሆንና ክርክሩም ከሳሾችን ወይም ተከሳሾችን በአንድ ዓይነት መልክ የሚመለከታቸው ሲሆን ከሳሾቹ ወይም ከተከሳሾቹ አንዱ በጠቅላላው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደነገሩ አከባቢ ፍርዱን በማሻሻል ወይም በመለወጥ ያሻሻለው ወይም የለወጠው ወይም ያጸናው ፍርድ ይግባኙን ባላቀረቡት ከሳሾች ወይም ተከሳሾች ላይም ይፀናባቸዋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 35 ላይ የተደነገጉትን ዝርዝር ነገሮችን ባሟላ መልኩ በአንድነት ሆነው ክስ ያቀረቡ ከሳሾች ከውሳኔ መልስ በይግባኝ ደረጃም በቀረበው ጉዳዩ ከከሳሾቹ መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የሚሰጠው ውሳኔ ሌሎችንም እንደሚያካትት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸው የአሁኑን አመልካች ጨምሮ አራት ከሳሾች ክስ መስርተው በአንድ መዝገብ የተከራከሩ ናቸው፡፡ ጉዳዩ ንብረት ካሳን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እያንዳንዱ ከሳሽ ለራሱ የሚገባውን የካሳ መጠን ገምቶ ማቅረብ ማለት ግን ለየብቻው ክስ አቅርቧል ሊያስብል አይችልም፡፡ የሆሮ ጉድሮ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ሲያደርግ በትዕዛዙ ላይ የገለጸው ምንም እንኳን ከሳሾቹ በአንድ ላይ ክስ ቢያቀርቡም እያንዳንዳቸው የካሳውን መጠን ለይተው ያቀረቡ ስለሆነ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በነጥብ በተመለሰው ጉዳይ አመልካች ሊከራከሩ አይችሉም የሚል ሲሆን ይህም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 35 እና 331 ድንጋጌን መንፈስና ዓላማ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.14442 በቀን 07/10/2008 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.209044 በቀን 13/04/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ወደ ክርክሩ ውስጥ ገብተው ለመከራከር ያቀረቡት አቤቱታ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 331 ድንጋጌን የተከተለ በመሆኑ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 111629 ላይ የሚጣሩ ነጥቦች ተይዘው በተመለሱት መሠረት በመ/ቁ. 14442 በሆነው ላይ የአመልካች ክርክር ቀጥሎ ፍርድ ቤቱ አከራክሮ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በተመለሰው መሠረት የሁለቱ ከሳሾች ክርክር ውሳኔ አግኝቶ ከሆነም የአመልካች ክርክር በዚያው መዝገብ ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ ይገባል ብለናል፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይደረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 139942

ቀን 27/03/2010 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘይባ ሳኒ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ለይላ ዘይኑ ተወካይ ዴቻሳ ጉርሙ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ተገቢውን ለመስራት ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቤት ክርክር የሚመለከት ሲሆን የጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ በኮ/መ/ቁ. 63738 ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የስር ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ አስተዳደር ዓለምገና ቀበሌ 02 ውስጥ ስፋቱ 395.7 ካሬ ሜትር በሆነው ይዞታ ላይ ቤት ሰርተው ተጠሪ በነበራቸው ጊዜያዊ ችግር በቤቱ እንዲኖሩ ተፈቅዶላቸው የነበረ ቢሆንም ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰን መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
2. የአሁኑ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ጉዳዩ የበኩላቸውን መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም ቤቱ የራሳቸው እንጂ የአሁኑ ተጠሪ አለመሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡
3. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የተጠሪ ነው ከሚል መደምደሚያ የደረሰ ሲሆን

በዚህም አመልካች ቤቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህ ውሳኔ በመቃወም ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከህግ ውጭ ውድቅ ስለ መደረጉ በፍሬ ጉዳዩም ቤቱ የአመልካች እንጂ የተጠሪ አለመሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ በስር ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በህጉ አግባብ አይደለም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በዚህ አግባብ አቤቱታ የቀረበለት አጣሪ ችሎትም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ በአደራ መስጠታቸው ባልተጠረጋገጠበት ሁኔታ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ማጣራት ይቻላል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም የበኩላቸውን መልስ ያቀረቡ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል ፡፡

4. የጉዳዩ አመጠጥ ከላይ የተገለጸው አጭር ይዘት ያለው ሲሆን እኛም ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ከላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመረነው የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያሻው ዓቢይ ነጥብ በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠው ፍርድና ትዕዛዝ ተገቢነት ከመመርመራችን በፊት ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታይቶ ፍርድ መሰጠቱ ከስረ ነገር ስልጣን አንጻር በህጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን መታየት ያለበት ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት የሚቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ የሚገኘው ኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 02 ውስጥ ነው፡፡ አመልካችም ነዋሪነታቸው ኦሮሚያ ክልል ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት መልስ ጉዳዩ የፌዴራል ሆኖ በውክልና በኦሮሚያ ክልል ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚታይ ቢሆንም ውክልና ሰጪው በጉዳዩ ላይ ስልጣን የለውም ማለት ስላልሆነ ከዚህ አንጻር የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን ተመልክተናል፡፡

5. በመሠረቱ የስረ ነገር ስልጣን ጥያቄ በየትኛውም የክርክር ደረጃ የሚነሳ ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 9 እና 231 (1) (ለ) እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ መሆኑ አለመሆኑን ለመለየት

አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ ከመሆኑ በተጨማሪ አመልካች እና ተጠሪ የኦሮሚያና አዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ስለመሆናቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በይፋ ባልተቋቋባቸው ክልሎች የፌዴራል ጉዳይ በውክልና የሚታይ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የስረ ነገር ስልጣኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ በመሆኑ መታየት ያለበት በኦሮሚያ ክልል ንብረቱ የሚገኝበት የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ስለመሆኑ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(4) ያስገነዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይሁን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ሲገባቸው ይህንን በማለፍ ግራ ቀኙን በማከራከር ፍርድና ትዕዛዝ መስጠታቸው በህጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 63738 በ29/11/2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 185671 በ29/06/2009 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡ ይሁንና የአሁኑ ተጠሪ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸው ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት በ2/08/2009 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

የሰ/መ/ቁ 135254

የካቲት 29 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡- አልማው ወሌ**

**ሙስጠፋ አህመድ**

**አብርሃ መሰለ**

**ፈይሳ ወርቁ**

**ጻውሎስ ኦርሺሶ**

አመልካች፡- አቶ ይስሃቅ ተክለ ፃዲቅ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ሃረገወይን አሸኔ

2. አቶ ጌጡ አሸኔ

3. ወ/ሮ ወይንሸት ተክሌ

**መዝገቡን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 10 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታቸው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99270 የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 172878 ነሀሴ 30 ቀን 2008 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት የአቀረቡት አቤቱታ በዚህ ችሎት ታይቶ እንዲወሰን በሰበር አጣሪ ችሎቱ ስለተወሰነ ነው፡፡የሕጉ ጥያቄም በአንድ የፍትሃብሔር ክርክር ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ጣልቃ በገባ ተከራካሪ ወገን ላይ በክርክሩ ከሳሽ የሆነው ወገን ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ለማንሳት የሚችልበት የሕግ አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ሚያዚያ 19 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፉት ማመልከቻ ሲሆን የማመልከቻቸው ይዘትም ወላጅ አባታቸው መምሬ ተክለፃዲቅ ወ/ዳዊት እና ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ ፀዳለ ታደሰ ተሰማ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 190 በሆነ ቤት ውስጥ ሲኖሩ ወላጅ አባታቸው ጥር 22 ቀን 1996 ዓ/ም፣ ወላጅ እናታቸው ደግሞ ግንቦት 21 ቀን 1995 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን ገልፀው የወላጆቻው የውርስ ሃብት በመረጧቸው አጣሪ እንዲጣራላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ሌላ ተጠሪ ሰይመው ያልነበሩ ቢሆኑም የአሁኑ ተጠሪዎች ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተዋል፡፡ ውርሱ እንዲጣራ ከተደረገ በኂላም ሪፖርቱ በ28/03/2008 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን በዚህ ጊዜም አመልካች ተጠሪዎች ወራሾች ነን በማለት መቅረባቸው በይርጋ የታገደ ነው የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በዚህ መልኩ የቀረበውን የአመልካችን መቃወሚያ መርምሮ አመልካች በራሳቸው አመልካችነት ውርሱ እንዲጣራ ጠይቀው የውርስ አጣሪው በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ወራሾችን ከለየ በኂላ ይርጋ ማንሳታቸው የህግ አግባብ የሌለው መሆኑን፣ ይርጋውን ማንሳት ይችላሉ ቢባል እንኳን የውርስ አጣሪው ይቋቋም የሚል ጥያቄ ሲቀርብ መሆን አለበት የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፤ የሚች ወራሾች እነማን እንደሆኑ በመለየት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት አሻሽሎ አፅድቆታል፡፡

አመልካች የአነሱት የይርጋ ክርክር ውድቅ በመደረጉ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪዎች አውራሾቻቸው ከሞቱ ከአስር አመታት በኂላ አመልካች ባቀረቡት የውርስ ንብረት ክፍፍል መዝገብ ላይ የሚቾች ወራሾች ነን በማለት የአቀረቡት የክፍፍል ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት አመልካች የአቀረቡት መቃወሚያ በበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ የተደረገው ከሕግ ውጪ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጎም ተጠሪዎች ቀርበው ከአመልካች ጋር በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ ማድረጋቸው ሕጋዊ መሰረት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷአል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች የሟች አባታቸው አቶ ተክለጻዲቅ ወ/ዳዊት እና የሟች እናታቸው ወ/ሮ ፀዳለ ታደሰ ወራሽ መሆናቸው የተረጋገጠ መሆኑን፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ ጸዳለ ታደሰ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን፣ 3ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ተክለጻዲዲቅ ወ/ዳዊት የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን በአመልካች ያልተካደ ከመሆኑም በላይ የወራሽነት ማስረጃ ቀርቦ መረጋገጡን፣ ተጠሪዎች ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ መብትና ጥቅም ባለው ወገን ተቃውሞ ቀርቦበት ያልተሰረዘ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም የበታች ፍርድ ቤቶች የአሁኑ አመልካች የሟቾች የውርስ ሃብት በፍርድ ቤት ትእዛዝ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ሃብቱ ተጣርቶ ብቸኛ የሟቾች ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ የውርስ ሃብቱ በስማቸው እንዲዛወር አመልካች በመሆን ክስ ከማቅረባቸው ውጪ ተጠሪዎች የአመልካችን ክስ በመቃወም በተከሳሽነት ጣልቃ ገብተው ለመከራከር አቤቱታ ከማቅረብ ውጪ የሟቾች ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸውም ሆነ የውርስ ሃብት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው ከሳሽ በመሆን ክስ ያለማቅረባቸውን በአቢይ ምክንያትነት ይዘው አመልካች የክስ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ የይርጋ መከራከሪያ በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ውድቅ ማድረጋቸውን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና ተካፋይ ያልሆነበት ክርክር የሚሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ወገን አቤቱታውን ለማቅረብ መብት እንደአለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39፣ 40 እና 41 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች የተዘረጋው የጣልቃ ገብነት ስርዓት በአንድ በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር ውስጥ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ያልተሰየሙ ሰዎች ለክሱ ምክንያት በሆነው ነገር ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን በማስረዳት ፍርድ ቤቱ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ገብተው ተካፋይ እንዲሆኑ እንዲፈቀድላቸው ዳኝነት የሚጠይቁበትን አግባብ የሚያሳይ

ስርዓት ነው፡፡ ድንጋጌዎቹ ጣልቃ ገብ የሆኑት ወገኖች የሚያቀርቡት አቤቱታ ክስ ከቀረበበት ምክንያት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለው መሆን ያለበት ሲሆን በሚሰጠው ፍርድ ወይም ውሳኔ መብታቸው በቀጥታ የሚነካ መሆኑ መረጋገጥ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ መብት፤ ጥቅማቸውን ወይም ግዴታቸው የሚነካባቸው ወገኖች የግድ ተሳታፊ መሆን እንደሚገባቸው የፍትሃብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 40 (2) ስር ያስቀመጠበት አቢይ ምክንያትም አንድን የክስ ምክንያት የሚመለከቱ የክርክር ነጥቦች ሁሉ በማያዳግም ሁኔታ ዳኝነት እንዲያገኙ ለማድረግ ታስቦ ስለመሆኑ ይታመናል፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ደግሞ የክሱ ማመልከቻ መሻሻል እንደአለበትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 40(3) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ እንደዚህ አይነት የክርክር አመራር መከተል ደግሞ የይርጋ ጥያቄውንም ሆነ ሌሎች ክርክሮችን በሕጉ አግባብ በመምራት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት የሚያስችልና የፍትሃብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ አላማዎችንም የሚያሳካ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ አንድ ክርክር ታይቶ የፍርድ ውሳኔ ቢያርፍ የሚሰጠው ውሳኔ መብቴን፤ጥቅሜን ወይም ግዴታን የሚነካ ነው በማለት ወደ ክርክሩ ለመግባት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ለመሆን በቂ የክስ ምክንያት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 40(3) አግባብ ክሱ እንዲሻሻል በማድረግ ስርዓቱን ጠብቆ የሚቀርበውን ማናቸውንም ክርክር አግባብነት ካለው መሰረታዊና ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ዳኝነት መስጠት የዳኝነት አካሉ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የጣልቃ ገብነት አቤቱታ አቅራቢዎች በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት ሲሰየሙ ይርጋን ለማንሳት የሚችሉበትና የማይችሉበት አግባብ ያለ መሆኑን ከላይ የተመለከቱት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የውርስ ንብረቱን ለብቻው ለመውሰድ ጥያቄ ያቀረበ ወገን በሌሎች መብት አለን በሚሉ ወገኖች የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ቀርቦበት የዳኝነት ጥያቄው ተቀባይነት እንዳያገኝ መፍትሔ ሲጠየቁ ዳኝነት ሰጪው አካል በጣልቃ ገብነት ጊዜ የይርጋ ክርክር ሊነሳ የሚችልበት አግባብን መሰረት በማድረግ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥ እንደሚችል የሚያሳዩ እንጂ ይርጋ ሁሉጊዜ መነሳት የአለበት በተከሳሽነት በተሰየሙ ሰዎች ብቻ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርሱ አይደሉም፡፡ እንደየክርክሩ ይዘትና አቀራረብ እንዲሁም የዳኝነት ጥያቄው ውጤት

የሚያስከትለውን የመብት አድማስ እየታዬ ከሳሽ የሆነ ወገን ተከሳሽ፣ ተከሳሽ ደግሞ ከሳሽ በሚል ዘንግ ተመድቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባው ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ሊስተናገድ የሚችል አይደለም የተባለው ይርጋ መቃወሚያ የሚነሳው በተከሳሽ በመሆኑና ተጠሪዎችም የጠየቁት ዳኝነት የውርስ ሃብት እንዲሰጣቸው የሚል ይዘት የለውም በሚል ከሳሽ በነበሩት ባሁኑ አመልካች የሚነሳበት አግባብ የለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ መብታቸውን፤ ጥቅማቸውን የሚነካ መሆኑን ጠቅሰው ወደ ክርክሩ ለመግባት የሚያስችላቸው የክስ ምክንያት ያላቸው መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረና በስር ፍርድ ቤቶችም የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን ጥያቄያቸውም አመልካች የሚቐችን የውርስ ንብረት ብቻቸውን ለመጠቀም የሚያስችላቸው መብት የለም በማለት በሕጉ አግባብ አግኝተናል በሚሉት የወራሽነት ማስረጃ መሰረት ድርሻቸው እንዲጠበቅላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህ የተጠሪዎች ጥያቄ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያልቀረበ መሆኑን አመልካች ገልጸው መከራከራቸው ደግሞ ክርክሩ የውርስ እንደመሆኑ መጠን አመልካችን እንደተከሳሽ ተጠሪዎችን ደግሞ እንደከሳሽ የሚያስቆጥራቸው ነው የሚል ትርጉም ከሚያሰጥ በስተቀር ሌላ የተከራካሪ ወገኖች ዘንግን የሚፈጥር አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ከተጠሪዎች የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ጠቅላላ ይዘት እና መጨረሻ ላይ በፍርድ ቤቱ እንዲረጋገጥላቸው ከጠየቁት የዳኝነት ጥያቄ አንጻር እንዲሁም የክርክሩ ባህርይም የውርስ ንብረት ድርሻ ጋር ተያይዞ የተነሳ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተጠሪዎችና አመልካች የተከራካሪነት ቦታ እንደተለዋወጡ በመቁጠር የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት አድርጎ በመሰረታዊ ሕጉ የተደገፈ መሆን ያለመሆኑን በመመርመርና አስፈላጊ ከሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 245 (1) አግባብ በማስረጃ አጣርቶ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆን ያለመሆኑ ላይ ብይን መስጠት ሲገባቸው አመልካች በከሳሽነት ዘንግ መቅረባቸውን ብቻ መሰረት በማድረግ የይርጋ መቃወሚያቸውን ሊያነሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. አመልካች ይርጋን ማንሳት አይችሉም ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99270 የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 172878 ነሐሴ 30 ቀን 2008 ዓ/ም የጸናው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎች ጣልቃ ሲገቡ ይርጋ ለማንሳት የሚከለክላቸው ሕግ የለም ብለናል፡፡ በዚህም መሰረት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99270 ቀጥሎ በአመልካች የይርጋ ጥያቄ ላይ አስፈላጊ ሲሆን ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ተገቢ ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ ጸዳለ ታደሰ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን፣ 3ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ተክለጻዲዲቅ ወ/ዳዊት የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተያዘው ድምዳሜ በዚህ ውሳኔ አልተነካም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 138340

**ህዳር 19 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መለሰ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

**አመልካች**:- 1. ሶፍያን ከማሎ
2. አማና ከማሎ
3. አሚኖ ከማሎ
4. ጃቢር ከማሎ
5. ሐይቃ ከማሎ
6. ሙስሊም ካመሎ

(1–6) ወኪል ወ/ሮ ሰዲያ አብድሮ -ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ጀሚላ ቃሲም -ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ ::**

**ፍርድ**

ጉዳዩ ከውርስ ጋር ተያይዞ የቀረበን ክርክርን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህንን የሰበር አቤቱታ አመልካቾች ያቀረቡት በሱዴ ወረዳ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00669 በ28/07/2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00437 በ3/12/2008 ዓ/ም የጸናውን ውሳኔ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 519/2008 በ28/04/2009 ዓ/ም ሽሮ ተጠሪ 2.1589 ሄክታር የገጠር እርሻ መሬት ለአመልካቾች ሊለቁ አይገባም በማለት በመወሰኑና ይኼው የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 255157 በ21/06/2009 ዓ/ም ትእዛዝ በመሰጠቱ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የአቤቱታቸው መሰረታዊ ይዘትም፡- የወላጅ አባታቸውን የሟች አቶ ከማሎ ሀምዳ የውርስ ንብረት የሆነውን የገጠር እርሻ መሬትና ባህርዛፍ እንዲካፈሉ ክስ መስርተው የሟቹ ሚስቶች በሆኑት ባሁኗ ተጠሪና የአመልካቾች ወላጅ እናት እጅ ያለው ይዞታ መኖሩ ተረጋግጦ ተጠሪ ያላግባብ የያዙትን ይዞታና ባህርዛፍ እንዲያካፍሉ በወረዳውና

በዞኑ የሸሪያ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሻረው ተጠሪ ተገቢውን ክርክርና ማስረጃ ባላቀረቡት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ የአመልካቾችን የውርስ ንብረት እንካፈል ጥያቄ በዝምታ ያለፈ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉም ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎል፡፡

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 34(5) እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግት ህገ መንግስት በአንቀጽ 35(5) ስር የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሀይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን በሕገ መንግስቱ ክልከላ እንዳልተደረገበት በግልጽ ከማስቀመጡም በላይ ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን ያሳያል፡፡ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብትም ምንጩ ይኼው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ሲሆን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 54/1994 መሰረት ተደራጅተዋል፡፡ በዚሁ አዋጅም ስልጣናቸው ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ በአዋጁ የክርክሩን የአመራር ሥርዓት ካልሆነ በስተቀር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሥረ ነገር ሥልጣናቸው ሥር የሆኑ ጉዳዮች የሚቀርብላቸውን አቤቱታና ክርክር የሚወስኑት የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 53/94 በአንቀፅ 6(1) ስር በግልፅ የተደነገገ ሲሆን አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፈቃድ የሰጠ መሆኑም ሊረጋገጥ ይገባል፡፡በመሆኑም የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 53/1994 አግባብ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ የሚገባ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 6 ድንጋጌና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሆነ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))፣ 80(3(ለ)) እና አዋጅ ቁጥር 53/94 እና አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6 ጣምራ ንባብ መሰረት ስነ ስርዓታዊ የሆነ የህግ ጥያቄን ብቻ ለማየት ስልጣን እንዳላቸው ግንዛቤ በመውሰድ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ሕጎችን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን መመርመር እንጂ ከዚህ ውጪ መደበኛ ሕጎችን መሰረት አድርገው በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሊመረምሩ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡

እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 53/94 ከተዘረጋው ስርዓት አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ስርዓት ህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን መርምረነዋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተጠሪ 2.1589 ካ/ሜትር ይዘው እንዲቀሩ ውሳኔ የሰጠው አመልካቾች በወላጅ እናታቸው በኩል ተጠሪ ይዞታውንና ባህርዛፉን እንዲለቁላቸው የመሰረቱትን ክስ የበታች የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ተጠሪ ይዞታውን እንዲለቁ መወሰናቸው ተገቢውን የፍሬ ነገር ማጣራትና የሸሪዓ ሕግ መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ስለመሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ መረዳት ችለናል፡፡

አመልካቾች በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለመዳኘት ፍቃደኛ ሳይሆኑ የተሰጠ ውሳኔ ስለመሆኑ ገልጸው ያቀረቡት ቅሬታ የሌለ ሲሆን አጥብቀው የሚከራከሩት ተጠሪ የያዙትን ይዞታ እንድንካፈል አልተወሰነም በሚል ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካቾች ተጠሪ የያዙትን ይዞታ በሚች ከማሎ ሀምዳ ወራሽነታቸው ከተጠሪ ጋር ልንካፈል ይገባል በሚል የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን በራሱ አጣርቶ የአመልካቾች ወላጅ እናት የሆኑት ወ/ሮ ዛዲያ አብድሮ 6.77 ሄክታር ይዘው ያሉ መሆኑን፣ ይህን ይዞታ ይዘውም የአሁኑ አመልካቾችን ወክለው ተጠሪ የያዙትን 2.1589 ሄክታር ጭምር ለመውሰድ ዳኝነት መጠየቃቸው በጉዳዩ ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሸሪዓ ሕግ አንጻር ተገቢ ያለመሆኑን በመገንዘብ ተጠሪ የያዙትን ይዞታ ሊለቁ አይገባም በማለት ዳኝነት መስጠቱን የውሳኔ ግልባጭ የሚያሳይ በመሆኑና ይህም ውሳኔ ከሸሪዓ ሕግ አንጻር ታይቶ ከመሰጠቱም በተጨማሪ የአመልካቾች ወላጅ እናትም ከተጠሪ ይዞታ የበለጠ ይዞታ ይዘው እንደሚገኙና አመልካቾችም ከወላጅ እናታቸው ስር ያሉ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሕግ ተለይቶ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተጠሪ ይዞታውን የሚለቁበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን በማስረጃ አጣርቶና ጉዳዩን በሐይማኖት ስርዓት መዝኖ ይዞታውን ተጠሪ ሊለቁ የሚችሉበት ሐይማኖታዊ ምክንያት የሌለ

መሆኑን ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ይሔው ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣኑ የደረሰበት መደምደሚያ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ የሚመዘንበት አግባብ የሌለ መሆኑን በኢ.ፌዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10፣ እንዲሁም በክልሉ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 53/94 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ከእነዚህ የሕግ ማዕቀፎች አንጻር ስናየው ደግሞ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ክርክሩ ሲመሩ በስነ ስርዓት ሕግ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካቾች የክፍፍል ጥያቄአችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሆኗል በማለት ያቀረቡት ክርክር የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አጣርቶና በሐይማኖቱ ስርዓት አግባብ ውድቅ ያደረገውን ያላገናዘበ እና የአመልካቾች ቅሬታ መሰረታዊ ይዘቱ በሐይማኖት ስርዓት ላይ ተመርስቶ የተሠጠውን ውሳኔ በመደበኛው ሕግ እንዲታይ የሚጠይቅ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ በማድረግ በሰጠው ውሳኔና ይህንኑ ውሳኔ ባፀናው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህትት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 519/2008 በ28/4/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 255157 በ21/06/2009 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.chilot.me

የሰ/መ/ቁ.138062

ህዳር 26 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች - ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካች - የሰቆጣ ከተማ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ዓ/ህ ሙሉ ባዩለኝ ቀረቡ

ተጠሪ - ወ/ሮ አድና ምህረቱ ጠ/ነቀዓጥበብ ገ/ሚካኤል ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በአማራ ብ/ክ/መንግስት በሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- ተከሳሽ የከሳሽ መ/ቤት የሆነን በሰቆጣ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኝ ኮንደሚኒየም የጋራ መኖሪያ ቤት ቁጥር B 13 R7 ባለሁለት መኝታ ቤት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኙና ሳይሰጣቸው በራሳቸው ከጥር ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ ንብረታቸውን አስገብተው ቤቱን ይዘው ስለሚገኙ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ ባቀረቡት መቃወሚያ በዚሁ ጉዳይ በመ/ቁጥር 0105706 በሁከት ይወገድልኝ ከሶኝ ተከራክረን ፍርድ ቤቱ ሁከት አለመፍጠሬንና በህጋዊ መንገድ በቤቱ መቀመጤንና የሚፈለገውን ክፍያ እየከፈልኩ ለመሆኔ አረጋግጦ የፈጠርኩት ሁከት የሌለ ስለመሆኑ ተወስኖልኝ እያለ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ድጋሚ እንደአዲስ ከሳሽ ጭብጡን ሳይቀይር የክሱን ርዕስ ብቻ በመቀየር ይዞታ ይረጋገጥልኝ በሚል ሰበብ ከቤቱ ለማስወጣት ያቀረበው የሃሰት ክስ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 5 እና 244(ለ) መሰረት በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ነው ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ግራቀችን ያከራከረ ሲሆን ከሳሽ በመቃወሚያው ላይ ባቀረበው ክርክር በመጀመሪያው ክስ ተከሳሾች ሁለት የነበሩ መሆኑንና በአሁኑ ክስ ግን ተከሳሽ አንድ ሰው ብቻ መሆናቸውን፤ የክርክሩ ፍሬ ነገርም

የመጀመሪያው የሁከት ይወገድልኝ ሲሆን የአሁኑ ግን ይዞታ ይለቀቅልኝ የሚል መሆኑን፤ የሚያዙት ጭብጦችም በመጀመሪያው ሁከት አለ የለም የሚል ሲሆን በአሁኑ ደግሞ ተከሳሽ ይዞታውን ይለቃሉ አይለቁም የሚል በመሆኑ የተለያዩ መሆናቸውን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ተከሳሽ በበኩላቸው በመጀመሪያው ክስ ሁለት ተከሳሾች ቢኖሩም ከእሳቸው ውጪ ሌላዋ ተከሳሽ አለመከራከራቸውንና ውሳኔም እንዳልተሰጠባቸው፤ የክርክሩም ይዘት በጭራሽ ልዩነት የሌለውና ዝርዝር ክሱ ተመሳሳይ መሆኑን፤ በመጀመሪያው ክስ ፍርድ ቤቱ አከራክሮ የሰጠው ውሳኔ ሁከት አለ የለም የሚለው ብቻ ሳይሆን የቤት ኪራይ ግንኙነት ስለመኖሩ ጭምር አከራክሮ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን በማንሳት መቃወሚያቸውን አጠናክረዋል፡፡

የመቃወሚያ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የመጀመሪያው ክስ ላይ ሁለት ተከሳሾች የነበሩ መሆኑና የአሁኑ ክስ ደግሞ በተጠሪ ላይ ብቻ መሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው ከሚለው የመከራከሪያ ሃሳብ ጋር ፍፁም ግንኙነት የሌለው መሆኑን፤ የሥረ ነገር ክርክሩ እና የተያዘው ጭብጥ ሲታይ የከሳሽ የዳኝነት ጥያቄ በፊተኛው ክስም ሆነ በአሁኑ ክስ የቤቱ ይዞታ እንዲለቀቅለት ስለመሆኑ ሁለቱንም የክስ ዝርዝር ይዘቶች አይቶ መረዳት እንደሚቻል፤ በአጠቃላይ በመጀመሪያው ክስ ከሳሽ በሁከት ይወገድልኝ ሽፋን ክስ ያቀረበ ቢሆንም ተከሳሽ የቤት ኪራይ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሁከት ሊባል እንደማይገባና በኪራይ ግንኙነት ምክንያት የያዙት ይዞታ ህጋዊ ውጤት ያለው መሆኑ ተረጋግጦ ፍርድ ተሰጥቶበት ያደረ ጉዳይ በመሆኑ በድጋሚ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5፣ 244(ለ) እና 245 መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ብይን በመቃወም ቅሬታውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 8/2009 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር ማመልከቻ በሥር ፍርድ ቤቶች የተላለፈው ብይን እና ትዕዛዝ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው እንዲባል እና ተጠሪ በህገወጥ መንገድ የያዙትን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ሀምሌ 11/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱ ውስጥ የገባሁት አመልካች እንደሚለው በህገወጥ መንገድ ሳይሆን እንደማንኛውም የከተማ አስተዳደሩ ሰራተኛ በከተማ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት በነበረው አሰራር መሰረት

ቤት እንዲሰጠኝ ወረፋ ከያዝኩ በኋላ መሆኑና በየወሩ የቤቱን ኪራይ እየከፈልኩ መሆኑ አመልካች እራሱ በፍርድ ቤት ያመነውና የማይክደው ከመሆኑ በተጨማሪ በሥር ፍርድ ቤት ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ከዚህ ቀደም ሁከት ይወገድልኝ በማለት ባቀረበው ክስ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ አንድ አይነት ጭብጥ የተያዘበትና አንድ አይነት ክርክር ነው ተብሎ ክሱ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው እንዲባል ጠይቀዋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይን እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

የፍትሃብሄር ስነ ስርዓት ህጉ ክርክሮች መቋጫ ይኖራቸው ዘንድ ከዘረጋው ሥርዓት አንዱ በአንቀፅ 5 ሥር የተደነገገው የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮችን የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር እንደተደነገገው አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ያለባቸው ሁኔታዎች ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ይመለከታል፡፡ ከሕጉ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው ፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5፣ 244(2(ለ)) እና 245(2) ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች ሁከት ይወገድልኝ በሚል አከራካሪው ቤት እንዲለቀቅለት አስቀድሞ ባቀረበው ክስ መሰረት በግራቀኙ መካከል ክርክር ተደርጎ አመልካች ከተጠሪ ጋር የቤት ኪራይ ግንኙነት ያለው መሆኑ

በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ሁከት ፈጥረዋል ሊባል እንደማይገባና በኪራይ ግንኙነት ምክንያት የያዙት ይዞታ ህጋዊ ውጤት ያለው መሆኑ ተረጋግጦ ፍርድ ተሰጥቶበት ያደረ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ ወስኗል፡፡

ስለሆነም አመልካች ሁከቱ ተወግዶ ቤቱ እንዲለቀቅለት ክስ አቅርቦ የተጠሪ ይዞታ ህጋዊ መሆኑ ዳኝነት ከተሰጠበት በኋላ ይዞታ ይለቀቅልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ዳኝነት በተሰጠበት ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌዎች አንፃር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች በቀደመው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው በየደረጃው በይግባኝ እና በሰበር ስርዓት አቤቱታ ከሚያቀርብ በቀር በዚያው ጉዳይ ድጋሚ ዳኝነት መጠየቁ ህጉን የተከተለ አይደለም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት በድጋሚ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5፣ 244(ለ) እና 245 መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ያሳለፈው ብይንና በየደረጃው ቅሬታ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ቅሬታውን አለመቀበላቸው ህጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሰቆጣ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 01-05940 ሰኔ 6 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን፣ የዋግኽምራ ብሄረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 01-02548 ሀምሌ 27 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ፣ እንዲሁም የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 03-15514 ታህሳስ 10/2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ሁከት ተወግዶ ይዞታ እንዲለቀቅለት ክስ አቅርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በድጋሚ ይዞታ ይለቀቅልኝ በሚል ክስ የመሰረተበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት የለውም መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

የሰ.መ.ቁ.137401

የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች:...1.ዳኜ መላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች:-......ወ/ሮ ጀምላ ጀብር ⟶ ተወካይ ሽፊቃ ሁሴን ቀርበዋል

ተጠሪ:-............አቶ ሶፊያ ጅማ ⟶ የቀረበ የለም።

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የንብረት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.253490 በ05/04/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ።

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ ፣በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት ሚማ ሚስጠፋ፣ሩማና ጅማ፣አሊማ ጅማ፣መሀመድ ጅማ እና ናስር ሁሴን 2ኛ-6ኛ ተከሳሾች ሆነው ሲከራከሩ ነበር። ከሳሽ ባቀረበችዉ ክስ በተከሳሾች አክስት ግቢ ዉስጥ በነበረዉ ክፍት መሬት ላይ ሰርቪስ ቤት እና ከ1-22 የተዘረዘሩትን አትክልቶች ያለማሁት ቢሆንም አሁን ይዞታዉን ለወራሾች እንዲተላለፍ ዉሳኔ ስለተሰጠ ግምቱን ብር 908800 እንዲከፍሉኝ በማለት ከሳለች።

በዚህ ክስ ላይ ከ1ኛ-5ኛ ተከሳሾች ባቀረቡት መልስ ይህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ በመሆኑ እና አትክልቱን እርሷ ስላልተከለች የንብረት ግምት እንዲከፈለኝ በማለት ያቀረበችዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል። 6ኛ ተከሳሽ በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ የከሳሽ ክስ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሾች የቤት እና የአትክልት ግምት በአጠቃላይ ብር 104180 ለከሳሽ እንዲከፍሉ፣ ሰርቪስ ቤቱ እና አትክልቶቹ የዉርስ ንብረት ሆኖ ተከሳሾች እንዲከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

የሥር 1ኛ-5ኛ ተከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ባዮች ከዚህ ቀደም የአክስታቸዉ ይዞታ 800 ካ.ሜ የሆነዉን በዉርስ ለመከፋፈል በፍ/ቤት ክስ ባቀረቡ ጊዜ መልስ ሰጭ /የሥር ከሳሽ/ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብታ ስትከራከር በይዞታዉ ላይ ስለሰራችዉ ቤት ሲሆን በዚህ መሰረት የቤቱ ግምት እንዲከፈላት እና ቤቱ ወደ ዉርስ ተቀላቅሎ እንዲከፋፈሉ የተወሰኑ በመሆኑ፣ መልስ ሰጭ ከዚህ ዉሳኔ በኋላ እንደአዲስ የአትክልቶች ግምት እንዲከፈለኝ በማለት ክስ ያቀረበች በመሆኑ ይህ ደግሞ ዳኝነት በአንድ ቦታ አጠቃላ መጠየቅ ሲገባት ከፋፍላ የጠየቀች በመሆኑ፣ የሥር ፍ/ቤት የሰርቪስ ቤት ግምት ይግባኝ ባዮች እንዲከፍሏት በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ቢሆንም የአትክልቶችን ግምት እንዲከፍሏት የሰጠዉ ዉሳኔ ግን ያለአግባብ ነዉ፣ ይግባኝ ባዮች የአትክልቶችን ግምት ለመልስ ሰጭ መክፈል የለባቸዉም በማለት ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበዉን ቅሬታ ዉድቅ በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ21/5/2009 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ከዚህ ቀደም በነበረዉ ክርክር ወራሾች ከዉርስ ንብረት ቀላቅለዉ የጠየቁት አንድ ትልቅ መኖሪያ ቤት ብቻ ነዉ እንጂ የተለያዩ አትክልቶችን ጨምረዉ ባልጠየቁበት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ ተጠሪዎች የጠየቁትን መብት ለመቃወም ወደ ክርክሩ የገባሁት ሆኖ እያለ በክርክሩ ዉስጥ ያልነበረዉን የተለያዩ አትክልቶችን በተመለከተ በዛን ጊዜ መጠየቅ ነበረባት አሁን መጠየቅ አትችልም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የአሁን አመልካች በቀድሞ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብተሽ ሲትከራከሪ የአትክልት ግምት

አልጠየቅሽም በማለት ክሷ ዉድቅ ሲደረግ በቀድሞ ክስ አትክልቶች በተመለከተ ክርክር ስለመኖሩ አለመኖሩን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ4/8/2009 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ጨምሮ የሥር ተከሳሾች በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት የአክስታቸዉን የወ/ሮ ሀዋ ኡስማን በ800 ካ.ሜ ይዞታ ዉስጥ የሚገኘዉን ንብረት እና ይዞታ ለመከፋፈል ዳኝነት ጠይቀዉ የነበሩ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በበኩሏ በዚህ ይዞታ ዉስጥ የሰራችዉን መኖሪያ ቤት በተመለከተ መብቷን ለማስከበር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብታ እንደተከራከረች የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ጉዳይ ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ወራሾች የቤቱን ግምት ለአመልካች ከፍሏት ቤቱን ወደ ዉርስ ንብረት ተቀላቅሎ እንዲከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበችዉ ክርክር በቀደመዉ ክርክር የሥር ተከሳሾች ስለ ቤት እንጂ ስለአትክልት ዳኝነት ስላልጠየቁ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ሲገባ ስለአትክልት የማነሳበት ሁኔታ የለም የሚል ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ጣልቃ ለመግባት አቤቱታ ሲታቀርብ አትክልቶች አለኝ ብላ የጠየቀችዉ ነገር የለም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በ800 ካ.ሜ ይዞታ ዉስጥ የሚገኘዉን የዉርስ ንብረትና ይዞታዉን እንዲትለቅ ዉሳኔ የሰጠ ስለሆነ ለመጠየቅ መብት የላትም የሚል ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ የአሁን ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ለመከፋፈል በክሳቸዉ ዝርዝር ስለማቅረባቸዉ የገለጸዉ ነገር የለም፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች በቀደመዉ ክርክር ጣልቃ ገብታ ስትከራከር አትክልቶችን መጠየቅ ነበረባት ከማለት ዉጭ የሥር ተከሳሾች አትክልቶችን ለመከፋፈል ዝርዝር ማቅረባቸዉን በዉሳኔዉ ያመለከታዉ ነገር የለም፡፡ ይህን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር በሕግ አግባብ ማየቱ ተገቢ ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 እንደሚደነግገዉ ባንድ ክስ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለዉ ክርክር ያገባኛል ወይም መብቴን ይነካል የሚለዉ ሶስተኛ ወገን ፍርድ ወይም ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጣልቃ ገብ ሆኖ ለመከራከር እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ሶስተኛ ወገን በሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረገዉ ክርክር ያገባኛል ወይም መብቴን ይነካል በማለት ወደ ክርክሩ መግባት የሚችለዉ ተከራካሪ ወገኖቹ በግልጽ ዳኝነት ጠይቀዉ የሚከራከሩበት ንብረት፣ ጥቅም፣ ወይም መብት ላይ ነዉ፡፡ ባንድ ክስ በሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረገዉ ክርክር በግልጽ ዳኝነት ያልተጠየቀበትን ንብረት፣ ጥቅም፣ ወይም መብት በተመለከተ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጣልቃ ገብቶ መብት ማስከበር የሚቻልበት ሁኔታ የለም፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር ከሳሾች የአክስታቸዉን 800 ካ.ሜ የሆነዉን ይዞታና ንብረት ለመከፋፈል ዳኝነት መጠየቃቸዉን እንጂ አሁን ለክርክር ምክንያት የሆኑትን የተለያዩ አትክልቶችን ለመከፋፈል በግልጽ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ የሥር ተከሳሾች በቀድሞዉ ክስ እነዚህ አትክልቶች ለመከፋፈል በግልጽ ዳኝነት ካልጠየቁ ደግሞ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብተው ሲትከራከር መብቷን ለማስከበር የሚጠይቀዉ ነገር አይኖርም፡፡ አመልካች ጣልቃ ገብ እንጂ ከሳሽ እስካልሆነች በቀድሞ ክርክር እነዚህን አትክልቶች በተመለከተ በግልጽ ዳኝነት እስካልተጠየቀ ድረስ መብቷን ለማስከበር የምትጠይቀዉ ነገር የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር አመልካች በ800 ካ.ሜ ዉስጥ የሚገኘዉን ንብረትና ይዞታ ላይ መብት የላትም ተብሎ ተወስኗል ይባል እንጂ ክርክሩ የይዞታ ሳይሆን የአትክልት በመሆኑ አመልካች በአትክልቶች ላይ መብት የላትም ተብሎ በግልጽ ዉሳኔ እስካልተሰጠ ድረስ በአትክልቶች ላይ ዉሳኔ ተሰጥቷል ሊባል አይችልም፡፡ በደፈናዉ ንብረት ተብሎ ዉሳኔ ተሰጥቶም ከሆነ በትርጉም አትክልቶችን ያጠቃልላል ተብሎ በመተርጎም አመልካች መብት የላትም ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች ጣልቃ ገብ ነበረች እንጂ ቀጥታ ክስ ያላቀረበች በመሆንዋ እና ለክርክር ምክንያት በሆኑት አትክልቶች በተመለከተ በግልጽ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ከዚህ ቀደም በነበረዉ ክርክር መብቷን አጠቃልላ መጠየቅ ነበረባት አሁን እንደአዲስ ከፋፍላ መጠየቅ የለባትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.216

እና 218 መሰረት ክሷ ተቀባይነት የለዉም ማለት ከፍ ሲል የተመለከተዉን የሕግ ድንጋጌ የሚቃረን ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በቀደመዉ ክርክር ጣልቃ ገብ እንጂ ቀጥታ ክስ ያቀረበች ወገን ባልሆነችበት እና ለክርክር ምክንያት በሆኑት አትክልቶች በተመለከተ በቀደመዉ ክርክር ግልጽ ዳኝነት ባልተጠየቀበት አመልካችዋ ከዚህ በፊት መብቷን አጠቃላይ መጠየቅ ነበረባት አሁን ከፋፍላ ያቀረበችዉ ተቀባይነት የለዉም በማለት ክሷን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.207855 በ15/3/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.253490 በ5/4/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ እንደተመለከተዉ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን የተለያዩ አትክልቶችን በተመለከተ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች የቤት ግምት ለአመልካች ተከፍሎ ቤቱ ወደ ዉርስ ንብረት ተቀላቅሎ ወራሾች እንዲከፋፈሉት በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. በ29/6/2009 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

የሰ/መ/ቁጥር 129534

ቀን 24/01/2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ረታ ቶሎሳ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- የሊቦ ከምከም ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት - ዓ/ህግ አበበ ሙሉ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ ወ/ሮ እናትነሽ ዘለቀ ጠበቃ በላይ መሸሻ ቀረቡ

2ኛ አቶ አበባው ክብረት

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የግንባታ ውል የሚመለከት ክርክር ሲሆን የጀመረው በአ/ብ/ክ/መ የሊቦ ከምከም ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመዝገብ ቁጥር 6118656 ባቀረበው መነሻ ነው ፡፡ አመልካች ባቀረበው ክስም ከ1ኛ ተጠሪ በተደረገው የግንባታ ውል ስምምነት ጤና ጣቢያ ለመስራት በብር 459,779.81 /አራት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ዘጠኝ 81/100 ግዴታ ገብተው 1ኛ ተጠሪ ለስራ ማስጀመሪያ ቅድመ ክፍያ ብር 137,931.50 የወሰዱ ቢሆንም ሥራውን በ10 ቀን አልጀመሩም ፡፡ 2ኛ ተጠሪም ሥራውን ለመስራት ውክልና የወሰዱ ቢሆንም በ10 ቀን ውስጥ ምንም ዕቃ አላስቀመጡም ፡፡ በመሆኑም ውሉ እንዲሰረዝ በቅድመ ክፍያ የተወሰደውን ገንዘብ እንዲመልሱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው ፡፡
2. የስር ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ 2ኛ ተጠሪ ሊከሰሱ እንደማይገባ የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ የሚሰረዝበት ህጋዊ

ምክንያት አይኖርም ፤ውሉ ላይ የተጠቀሰው ሥራ እና ሳይት ፕላኑ ላይ የተቀመጠው ሥራ መሰረታዊ ልዩነት ያለው ስለመሆኑ የሚፈጀው ገንዘብና ጊዜ ልዩነት የሚያመጣ በመሆኑ ውሉ እንዲሻሻል በመጠየቅ በቅድሚያ ክፍያ መልክ የወሰደው ገንዘብ ግን የሚመለስበት አግባብ እንደሌለ በመጥቀስ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል ፡፡

3. በዚህ መልክ ክርክሩ ያቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር ከመረመረ እና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነው ያለው ጭብጥ ከመሰረተ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ቅድመ ክፍያ የግንባታው አጠቃላይ ዋጋ 30% መቀበሉን የስራ ዝርዝር እና ሳይት ፕላኑ የማይጣጣም ስለመሆኑ ፤የስራ ዝርዝሩ OPd የሚል ሲሆን ፕላኑ ላይ ደግሞ IPd የሚል ስለመሆኑ፤ ይህ ደግሞ የዋጋ ልዩነት እንደሚያስከትል አመልካች ተጠሪዎችን ማስገደድ የሚችለው ፕላኑ በማስተካከል ወይም የሚያስፈልገው ወጪ በባለሙያ አስገምቶ በማስተካከል ብቻ ስለመሆኑ ፤ አመልካች ውሉ በማቋረጡ የሚከፈለው ኪሳራ ካለ ተጠሪዎች የመጠየቅ መብት እንደላቸው በመግለጽ ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል ፡፡የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመቀጠልም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም ፡፡ አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም የአሁኑ ሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን የአቤቱታው መሰረታዊ ይዘት ሲታይም ፡- የስር ፍርድ ቤቶች ግራቀኙ ያደረጉት ውል አይፈርስም በማለት የቅድመ ክፍያው እጣ ፋንታ ሳይወስኑ ማለፋቸው ተገቢ አለመሆኑን ፤1ኛ ተጠሪ ልዩነት እንዳለው እያወቁ ወደ ውል የገቡ በመሆኑ ውሉ ተሻሽሎ መቀጠል አለበት ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ግንባታ ሳይጀመር የቀረው በአሁኑ አመልካች ምክንያት ነው የሚባል ቢሆን ተጠሪ በቅድሚያ የወሰዱት የውለታውን ገንዘብ 30% እንዲመልሱ የተጠየቀው ዳኝነት የመታለፉ አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ማጣራት ይቻላል ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ይቅረብ ተብሏል ፡፡ ተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ባቀረቡት የጽሑፍ መልስ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል ፡፡ አመልካች አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቧል ፡፡

4. የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከትነው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበትን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል ፡፡

5. እንደመረመረነውም አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የግንባታ ውል ስምምነት በማድረግ ቅድመ ክፍያ 30% ወይም ብር 137,931.50 የወሰዱ ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም ። አመልካች ባቀረበው ክስ ያደረጉት ውል ተሰረዞ በቅድመ ክፍያ የተወሰደው ገንዘብ እንዲመለስለት ጠይቋል ። 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ ተሻሽሎ የፕሮጀክቱ ገንዘብ ተጨምሮ ሥራውን ከሚቀጥል በቀር በቅድመ ክፍያ መልክ የወሰደው ገንዘብ ለመመለስ የሚገደድበት አግባብ አለመኖሩን በመግለጽ ተከራክሯል ። ጉዳዩን ያጣራው የስር ፍርድ ቤት በግንባታ ውሉ ያለው የስራ ዝርዝር እና ሳይት ፕላኑ የማይጣጣም ስለመሆኑ ሥራውን ተጨማሪ ውጪ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሥራውን መቀጠል የሚችለው ፕላኑ በማስተካከል የሚያስፈልገው ወጪ በባለሙያ አስገምቶ በማስተካከል ብቻ ስለመሆኑ በመግለጽ ክሱን ውድቅ ማድረጉን መዝገቡ ያሳያል ። ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች የቅድመ ክፍያ 30% ከከፈለ በኋላ ከተጠሪዎች ጋር በተነሳው አለመግባባት ሥራውን አለመሰራቱን ነው ። የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ ውድቅ በማድረግ የወሰነ ቢሆንም በቅድመ ክፍያ ተወሰደ የተባለው ገንዘብ በተመለከተ ግን ያለው ነገር የለም ። አመልካች እና ተጠሪዎች ያደረጉት የግንባታ ውል ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሰረት የማይፈጸም ከሆነ ሊኖር የሚችለው ህጋዊ ውጤት ከፍ/ሕ/ቁ 1815 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ማየቱ ተገቢ ይሆናል ። በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ውል የተሰረዘ ወይም የፈረሰ ከሆነ ግራቀኙ ውሉታ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ እንደሚገባ በግልጽ ተመልክቷል።

6. አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው ውል ባህሪ ሲታይም አስተዳደራዊ ውል ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል። በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የተደረገው የጤና ጣቢያ ግንባታ ውል ከመሆኑ አንፃር የአስተዳደር አካሉ ውለታ የማፍረስ መብት ያለው ስለመሆኑ ተጠሪም ውሉ በመፍረሱ ምክንያት ጉዳት ያደረሰበት ቢሆን ካሳ የመጠየቅ መብት እንዳለው የፍ/ሕ/ቁ 3180 እና 3181 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት ያስገነዝቡናል ። በመሆኑም የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው የግንባታ ውል በተፈጠረው አለመግባባት የማይቀጥል ስለመሆኑ ግልጽ በሆነበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት በቅድመ ክፍያ የተወሰደውን ገንዘብ በተመለከተ ምንም ሳይል ማለፉ በሕጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም። በሌላ በኩል አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው ውል አስተዳደራዊ ውል ከመሆኑ አንፃር መንግስት ውሉን የመሰረዝ መብት አለው። የአሁኑ ተጠሪዎች የደረሰባቸው ጉዳት ካለ ካሳ ከሚጠይቁ በቀር መንግስት ውል እንዲያሻሽል

የማስገደድ ወይም በቅድመ ክፍያ የተወሰደውን ገንዘብ ያለመመለስ መብት የላቸውም ብለናል ፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ የቅድሚያ ክፍያ ይመለስልኝ የሚል ሆኖ ሳለ እና ውሉም የሚቀጥልበት የህግ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው የፍ/ሕ/ቁ 1815 ፤ 3180 እና 3181 ያላገናዘበ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል ፡፡

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ጎንደር መስተዳደር የሊቦ ከምከም ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0118656 በ16/02/2008 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52825 በ01/04/2008 ዓ.ም የሰጠው ብይን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ 55983 በ08/09/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል ፡፡
2. የአሁኑ ተጠሪዎች ከአመልካች በቅድመ ክፍያ የወሰዱት ከፕሮጀክቱ አጠቃላይ ዋጋ 30% ወይም ብር 137,931.50 /አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አንድ ከሀምሳ ሳንቲም / ሊመለሱ ይገባል በማለት ወስነናል ፡፡
3. ተጠሪዎች ከውሉ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የደረሰባቸው ኪሳራ ካለ በሕጉ አግባብ ክስ አቅርበው የመጠየቅ መብታቸው ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል ፡፡
4. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል ፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 128746

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ፀጋየ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-ሻምበል መሐመድ ብርሃን ረዳ -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ዘምዘም መኮንን-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58200 በ06/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142615 በ06/07/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

በንብረት ክፍያ ክርክሩ ፍርድ ካረፈባቸው ንብረቶች መካከል ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው ራዕይ 2001 ሁለገብ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ግራ ቀኙ በአመልካች ስም ያላቸው ድርሻ ነው፡፡በዚህ ማህበር ውስጥ በአመልካች ስም ያለው ድርሻ ተጣርቶ ክፍፍል እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ያቀረቡት ተጠሪዋ ሲሆኑ አመልካቹም የአባልነት ድርሻው የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት መሆኑን አምነው መልስ በመስጠታቸው ፍርድ ቤቱ አመልካች ያላቸው ድርሻ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ከማህበሩ በጽሁፍ የተሰጠውን ምላሽ መሰረት አድርጎ

አመልካች በማህበሩ ውስጥ እንዳላቸው ከተረጋገጠው ብር 174,412.65 (አንድ መቶ ሰባ አራት ሺህ አራት መቶ አስራ ሁለት ከስድሳ አምስት ሳንቲም) ውስጥ ግማሹ የተጠሪዋ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ እና አመልካች በማህበሩ ውስጥ ያላቸው ድርሻ መጠን በድጋሚ ተጣርቶ እንዲቀርብ ሁለት ጊዜ ትዕዛዝ ሰጥቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከተከናወነው ኦዲት ውስጥ በ23/05/2008 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ የተላከለትን ሁለተኛ የኦዲት ሪፖርት መርምሮ በዚህኛው የኦዲት ሪፖርት ላይ የተገለጸው አመልካች ከማህበሩ ያገኙት ድርሻ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ከተገለጸው መጠን በላይ ሆኖ መገኘቱን በምክንያትነት ይዞ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በተከናወነው ኦዲት መሰረት የቀረበው ሪፖርት ማህበሩ ባለዕዳ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ ሳለ አመልካች ከማህበሩ ገንዘብ እንዳገኙ ተቆጥሮ ከተጠሪዋ ጋር እኩል ይከፋፈሉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ክርክሩ የተስተናገደበትን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ጭምር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ በመቀበል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካቹ በማህበሩ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ወይም ከማህበሩ ያገኙትን ትርፍ በተመለከተ ኦዲቱ በድጋሚ ተከናውኖ ሪፖርት እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ኦዲቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ተከናውኖ በ16/10/2007 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ ሰባት ገጽ የኦዲት ሪፖርት የተላከተ መሆኑን፣በዚህ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው አመልካች በ02/11/2007ዓ.ም.፣ተጠሪዋ ደግሞ በ29/10/2007 ዓ.ም. የተጻፈ አስተያየት ማቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን አስተያየት በተለይ ደግሞ በተጠሪዋ የቀረበውን የተቃውሞ አስተያየት መሰረት

በማድረግ ኦዲቱ አሁንም በድጋሚ ተከናውኖ ሪፖርት እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ኦዲቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ተከናውኖ በ23/05/2008 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ ሶስት ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና ስምንት ገጽ ደጋፊ ሰነድ የተላከት መሆኑን፣በዚህ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው አመልካች በ01/06/2008 ዓ.ም.፣ተጠሪዎም በተመሳሳይ ቀን በ01/06/2008 ዓ.ም. የተጻፈ አስተያየት ማቅረባቸውን፣በተጠሪዋ በኩል የቀረበው አስተያየት ሪፖርቱ ግልጽነት የሌለው በመሆኑ ቢቻል ቀደም ሲል በስር ፍርድ ቤት በቀረበው የኦዲት ሪፖርት መሰረት ውሳኔ እንዲሰጣቸው፣ካልሆነም እንደገና እንዲጣራ እንዲደረግ የሚጠይቅ መሆኑን እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሪፖርቱን እና የግራ ቀኙን አስተያየት ከመረመረ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ያጸናው በመጨረሻ በቀረበው ሪፖርት መሰረት አመልካች ከማህበሩ ያገኙት ድርሻ በስር ፍርድ ቤት በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ ከተገለጸው መጠን በላይ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡

እንደሚታወቀው ማንኛውም ፍርድ ቤት ባለጉዳዮችን ማከራከር የሚገባው የተለያዩበት የሕግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ምን እንደሆነ አረጋግጦ ለጉዳዩ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ ስለመሆኑ፣የነገር ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነውን የሕግ ወይም የነገር አግባብ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የካደ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ፣ፍርድ ቤቱ ጭብጥን ለመመስረት የሚችለውም ከግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሰረት በሚደረግ ምርመራ በተከራካሪ ወገኖች የሚሰጠውን መልስ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የጭብጥ አመሰራረትን በሚደነግጉ ከቁጥር 246 እስከ 248 በተመለከቱት የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በክርክሩ የተያዘው ጭብጥ ምን እንደሆነ እና12010 ጭብጡ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተወሰነበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ የፍርድ አጻጻፍን በሚመለከተው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 182 (1) ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ስም በማህበሩ ውስጥ ያለው ድርሻ የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት መሆኑ በአመልካቹ የታመነ ሲሆን እያከራከረ ያለው በማህበሩ ውስጥ አመልካች ያላቸው ድርሻ ምን ያህል ነው? ማህበሩ ለአባላቱ ያስገኘው ትርፍ አለ ወይስ የለም?

አለ ከተባለ አመልካች ከማህበሩ ያገኙት ወይም ማግኘት የሚገባቸው ወይም የተካፈሉት ድርሻ ምን ያህል ነው? የሚሉ እና ተያያዥ ጥያቄዎች ናቸው፡፡እነዚህ ጥያቄዎች ደግሞ በባህሪያቸው ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም ብቻውን የሚፈታቸው ሳይሆኑ የኦዲት ባለሙያ እገዛ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ፍርድ ቤቶች ሂሳብ የማጣራት ስራ በምትክ ዳኞች ወይም በልዩ አዋቂዎች /ኤክስፐርቶች/ ተከናውኖ ውጤቱ እንዲቀርብላቸው ትዕዛዝ መስጠት የሚችሉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 133 እስከ 136 ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን ሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች ኦዲቱን በተመለከተ የተለያየ ትዕዛዝ ሲሰጡ የነበረውም በዚሁ ስርዓት መሰረት ነው፡፡በዚህ አግባብ በጽሁፍ ተዘጋጅተው በቀረቡት የኦዲት ሪፖርቶች ላይ ገልጽ ያልሆኑትን ወይም አሻሚ መስለው የታዩ ነጥቦችን ማጣራቱ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 133 (3) በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት የኦዲት ስራውን አከናውነው ሪፖርቱን ያቀረቡ ልዩ አዋቂዎችን ምስክርነት መስማት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ኦዲቱ በድጋሚ ተከናውኖ ሪፖርት እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ኦዲቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ተከናውኖ በ23/05/2008 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ የተላከው ሶስት ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና ስምንት ገጽ ደጋፊ ሰነድ ማህበሩ በአንድ በኩል በኪሳራ ላይ እንደነበረ እና በሌላ በኩል ደግሞ ትርፋማ እንደነበረ የሚያመላክት አሻሚ ይዘት ያለው መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ይህም የኦዲት ሪፖርቱ ግልጽነት የሌለው ነው በማለት ተጠሪዋ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሪፖርቱ ላይ የሰጡት አስተያየት ተገቢነት የነበረው መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 133 (3) ድንጋጌ መሰረት በሪፖርቱ ላይ የሚያሻማ በሚመስል አገላለጽ የሰፈረውን ሀሳብ ይዘት እንዲያስረዱ ፍርድ ቤቱ ስማቸው በሪፖርቱ ላይ የተጠቀሰውን የሂሳብ ባለሙያዎች አስቀርቦ መስማት ይጠበቅበት ነበር፡፡ ኦዲቱን ያከናወኑ ኦዲተሮች በሪፖርቱ ላይ የሚያሻማ በሚመስል ሁኔታ የሰፈረውን ሀሳብ ለይተው እንዲያስረዱ ባልተደረገበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች የኦዲት ሪፖርቱን እራሳቸው በተረዱት አግባብ ተርጉመው የሚሰጡት ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ነው ሊባል የሚችል ካለመሆኑም በላይ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚያስችልም አይደለም፡፡በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ጉዳዩ ወደ

ፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ ኦዲቱን ያከናወኑት ባለሙያዎች ቀርበው ስለሪፖርቱ አጠቃላይ ይዘት ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ከተደረገ በኃላ ተገቢው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 58200 በ06/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142615 በ06/07/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ራዕይ 2001 ሁለገብ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ግራ ቀኙ በአመልካች ስም ያላቸውን ድርሻ በተመለከተ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. ቁጥሩ 142615 የሆነውን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ አስቀርቦ ራዕይ 2001 ሁለገብ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ግራ ቀኙ በአመልካች ስም ያላቸውን ድርሻ በተመለከተ ኦዲቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ተከናውኖ በ23/05/2008 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ የተላከውን ሶስት ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና ስምንት ገጽ ደጋፊ ሰነድ እንዲሁም በዚሁ የኦዲት ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ የሰጡትን አስተያየት ከመዝገቡ ውስጥ ከተመለከተ በኃላ በሪፖርቱ መጨረሻ ላይ ስማቸው የተጠቀሰውን ሶስት ኦዲተሮች፣እነዚህ ኦዲተሮች በቂ በሆነ ሕጋዊ ምክንያት ሊገኙ እንደማይችሉ የሚረጋገጥ ከሆነም ስለጉዳዩ ሊያስረዱ የሚችሉ ሌሎች ኦዲተሮችን ከዚያው ተቋም አስቀርቦ ስለሪፖርቱ አጠቃላይ ይዘት ምስክርነታቸውን ከሰማ በኃላ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንደ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡

4. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት ከተመለከተው ውጪ ያለው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. በዚህ መዝገብ በ14/03/2009 ዓ.ም. እና በ27/07/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 131950

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች ፡- ወ/ሮ የሺመቤት ገ/ፃዲቅ - ጠበቃ ተፈሪ ከበደ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ፋንታዬ ሽጉልቱ - ተወካይ ወ/ሮ ንጋቷ ባየህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍቺ እና የንብረት ክፍፍል ስምምነት መነሻ አለአግባብ የተወሰደ ነው የተባለን ንብረት ለማስመለስ ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በባሶና ወራና ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 08006 በ27/03/2008 ዓ.ም. የተሰጠው እና በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0119440 በ13/05/2008 ዓ.ም. ተሻሽሎ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 030-7079 02/10/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-አቶ ደምሴ ባየህ የተባሉ የተጠሪዋ ልጅ እና አመልካቿ ከሃያ ዓመታት በላይ በጋብቻ ተሳስረው ከቆዩ በኃላ በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት መነሻ የፍቺ እና የንብረት ክፍፍል ስምምነት አድርገው ይኸው ስምምነት በወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07651 በ08/09/2007 ዓ.ም.የተመዘገበ እና

ንብረቶቹንም የተከፋፈሉ መሆኑን፣ከዚህ በኃላ የንብረት ክፍፍል ስምምነቱ የተደረገው ተጋቢዎቹ በጋራ ባፈሩት ንብረት ላይ ሳይሆን በእኔ ንብረት ላይ ነው በማለት የአሁኗ ተጠሪ በ24/09/2007 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኗ አመልካች እና 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት የተጠሪዋ ልጅ /የአመልካቿ የቀድሞ ባለቤት/ ላይ የንብረት ያስረክቡኝ ክስ ማቅረባቸውን፣አመልካቿ ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው፣ስምምነቱ እንዲፈርስ ባልተደረገበት ሁኔታ አዲስ ክስ ሊቀርብ አይገባውም፣ የንብረት ክፍፍሉ ሲደረግ ተጠሪዋ በቦታው እያሉ ባልተቃወሙበት ሁኔታ አዲስ ክስ ማቅረባቸው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦችን ካስቀደሙ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ በፍርድ ቤት በጸደቀው ስምምነት መሰረት ክፍፍል የተደረገባቸው ንብረቶች በጋብቻው ውስጥ የተፈሩ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተከራከሩ መሆኑን፣የስር 2ኛ ተከሳሽን በተመለከተ በእጃቸው የነበረውን 0.5 ጥማድ የእርሻ ይዞታ መልሰውልኛል በማለት ተጠሪዋ ክሱ እንዲቋረጥ ያደረጉ መሆኑን፣ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦቹን በብይን አልፎ በተጠሪዋ እና በአመልካቿ መካከል ክሱን እና የግራ ቀኙን እንዲሁም የማጣሪያ ምስክሮችን ከሰማ እና ከወረዳው መሬት እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ክርክር ያስነሳው 0.5 ጥማድ የእርሻ መሬት የተጠሪዋ ልጅ እና አመልካቿ በመጋዞ ሲጠቀሙበት እንደነበረ የተገለጸ ቢሆንም የይዞታ ባለመብትነቱ ግን የተጠሪዋ እንደሆነ ከሚመከተው አካል በቀረበ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና ክፍፍል የተደረገባቸው ከብቶች እና የተለያዩ እህሎችም የተጠሪዋ እንደሆነ መረጋገጡን ገልጾ አመልካቿ በክፍፍሉ የወሰዷቸውን ከብቶች እና በውሳኔው ላይ መጠናቸው እና ዓይነታቸው በዝርዝር የተገለጸውን የተለያዩ እህሎች ለተጠሪዋ እንዲመልሱ ውሳኔ መስጠቱን፣ይግባኙን የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ክፍፍል የተደረገባቸው ከብቶች እና የተለያዩ እህሎች የተጠሪዋ ስለመሆናቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን አሻሽሎ ከብቶቹን እና እህሎቹን አመልካቿ የመመለስ ግዴታ የለባቸውም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን እና በክልሉ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ የጸናውም ይኸው ውሳኔ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቿ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ለ24 ዓመታት ሲጠቀሙበት የኖሩትን የእርሻ መሬት የስር 2ኛ ተከሳሽ ያገኙት ከእናታቸው ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቿን መብት የማሳጣታቸውን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባው ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቿ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡት ከብቶቹን እና እህሎቹን ይመልሱ መባሉን በመቃወም ብቻ ሳይሆን በ0.5 ጥማድ መሬት ላይ መብት የላቸውም መባሉን በመቃወም ጭምር ስለመሆኑ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ የገለጹ ሲሆን መሬቱ ጭምር የይግባኝ ምክንያት የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪዋም በሰበር መልሳቸው ላይ ገልጸዋል፡፡ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 339 ድንጋጌ መሰረት ይግባኙ በተሰማበት ጊዜም ግራ ቀኙ በመሬት ይገባኛል ጉዳይ ላይ ጭምር የተከራከሩ መሆኑን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ያመለክታል፡፡ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክርክሩን የሰማው በመሬት ይገባኛል ጉዳይ ላይ ጭምር ቢሆንም በመጨረሻ ግን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በሌሎች ነጥቦች ረገድ ሲያሻሽል በመሬት ይገባኛል ክርክሩ ረገድ ግን ውሳኔ ሳይሰጥ በዚህ ረገድ በአመልካቿ የቀረበውን ቅሬታ በዝምታ አልፎታል፡፡በመሰረቱ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ የመጀመሪያውን ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ያሻሻለው ወይም የለወጠው እንደሆነ በትችቱ ላይ ለይግባኝ ባዩ የሚገባውን ዳኝነት ዘርዝሮ መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 182 (1) ድንጋጌ ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኝ በተባለበት ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ የሰፈረው ማስረጃ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግምት በቂ ሆኖ ሲገኝ የነገሩን ጭብጥ በማሻሻል ወይም በመለወጥ ተገቢ መስሎ የታየውን የመጨረሻ ፍርድ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ እና ይግባኝ የተባለበት ፍርድ ቤት ፍርዱን የሰጠው በሌላ ምክንያት ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመዝገቡ ላይ በተረዳው

መሰረት ጭብጡን ለውጦ ከመፍረድ የማይታገድ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 242 ስር ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም አመልካቿ የይግባኝ ቅሬታ ባቀረቡበት የ0.5 ጥማድ መሬት ክፍያ ጥያቄ ላይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እንደሰማ ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ሊያሳርፍበት ሲገባው በዝምታ ማለፉ ስነ ስርዓታዊ ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በእርግጥ በአንድ ክርክር እና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ የታለፈ እንደሆነ የተጠየቀው ዳኝነት እንደተከለከለ የሚቆጠር ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 5 (3) ድንጋጌ ስር ተመልክቶአል፡፡ይህ ማለት ግን በቀድሞ ክርክር ጊዜ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት በዝምታ የታለፈ ጉዳይ በሌላ ጊዜ የክስ እና የክርክር ምክንያት ሊሆን አይችልም ማለት እንጂ በተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ ፍርድ ቤቶች በዝምታ ማለፍ ይችላሉ ማለት አይደለም፡፡ይህ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዝምታ የታለፈው የዳኝነት ጥያቄ ተገቢ ፍሬ ነገሮችን ማጣራትን እና ማስረጃ መመዘንን ጭምር የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩ ወደ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተመልሶ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት ከሚደረግ በቀር በዚህ ሰበር ደረጃ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በባሶና ወራና ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 08006 በ27/03/2008 ዓ.ም. የተሰጠው እና በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0119440 በ13/05/2008 ዓ.ም. ተሻሽሎ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 030-7079 02/10/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካቿ የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡበትን የ0.5 ጥማድ መሬት ክፍያ ጥያቄ ጉዳይ በዝምታ በማለፍ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ የጸናው የውሳኔ ክፍል ተሽሮአል፡፡

3. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሰውን የይግባኝ ቅሬታ ነጥብ በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለባሶና ወራና ወረዳ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት ከተጠቀሰው ውጪ ያለው የውሳኔው ክፍል አልተነካም፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# ወንጀል

የሰበር መዝገብ ቁጥር 127484

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ በቀለ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤሕግ- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

የአሁን ተጠሪ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና 676/1 በመተላለፍ በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ማሕበር ሥብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ደብረመድሐኒት መድሐኔዓለም ቤተክርስትያን ሒሳብ ሹም ሆኖ ሲሰራ ከመጋቢት 2004 ዓ.ም እስከ ሕዳር 2005 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ ሀላፊነቱን ወደጎን በመተው የሂሳብ አሰራር እና ደንብ ከሚፈቅደው ውጪ ብር 689,688.34 / ሥድሥት መቶ ሠማንያ ዘጠኝ ሺህ ሥድሥት መቶ ሠማንያ ሥምንት ብር ከሠላሣ አራት ሣንቲም / ከሥር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነት በማጉደል ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበበትን ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪን ምስክሮች ከሰማ በኂላ አመልካች ሊከላከል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675/1 መሠረት ነው በማለት ብይን ከሰጠ በኂላ የአመልካችን መከላከያ

ምስክሮች ሰምቶ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675/1/ መሠረት ጥፋተኛ ነው በማለት በአንድ አመት ከሥምንት ወር ቀላል እሥራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች የኦዲት ምርመራው በሚከናወንበት ወቅት በሐገር አቀፍ ምርጫ በምርጫ አስፈጻሚነት ሥራ ላይ የነበሩ መሆኑ፤ የፍትሕ ሚኒስቴርም አመልካች ኦዲቱ በተሰራበት ወቅት በሐገራዊ የምርጫ ማስፈጸም ሥራ ላይ የነበሩ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች በተገኙበት የኦዲት ሥራው ተከናውኖ ውጤቱ እንዲገለጽለት ለአዲስአበባ ፖሊስ ኮሚሽን የልዩ ልዩ ወንጀል ምርመር ዲቪዝዮን ማዘዙን እና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ተሰባስበው አመልካች በተገኙበት ድጋሚ ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ እንዲገለጽለት ቤተክርስቲያንዋን ማዘዙን፤የኢትዮጲያ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤትም ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ምርጫ ጽ/ቤት አመልካች ከሕዳር 27/2005 ዓ.ም እስከ የካቲት 11/2005 ዓ.ም በመራጮች እና እጩዎች ምዝገባ እንዲሁም ከመጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ ግንቦት 02 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በወረዳ 06 ምርጫ ጽ/ቤት አስተባባሪነት ቅዳሜ እና እሁድን የበአል ቀናትን ጨምሮ ሲሰሩ ቆይተው ከግንቦት 12/2005 ጀምሮ ወደ መደበኛ ስራቸው መመለሳቸውን ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ከጻፈው ደብዳቤ መገንዘብ ተችሏል፤በኦዲቱ ሥራ ገንዘብ ያዥ፤የሂሳብ ሹም እና የውስጥ ተቆጣጣሪ አስፈላጊዎች መሆናቸው የኦዲት ሪፖርቱ ያስገነዝባል፤አመልካች ሂሳብ ሹም በመሆናቸው ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ ቢሆኑም አዲቱ ሲሰራ አልነበሩም፤ሒሳቡን የሠሩት ባለሙያዎች የኦዲት ሥራው አስፈላጊ የሆኑ ገቢ እና ወጪ የሂሳብ ሰነዶች ባልተገኙበት የተከናወነ ስለመሆኑ በሂሳብ ስራው ሂደት ያጋጠሙን ችግሮች ናቸው በማለት ዘርዝረዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች የተከሰሱበትን የእምነት ማጉዳል ወንጀል ለማረጋገጥ ዓይነተኛ ማስረጃ ሆኖ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት ውጤት የአመልካችን ጥፋት ሊያሳይ አይችልም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ለክሱ መነሻ የሆነው የኦዲት ሥራ ግራ ቀኙ በተገኙበት  እና በሚያቀርቡት ማስረጃ በገለልተኛ ሂሳብ አዋቂ በድጋሚ ተሰርቶ ሊቀረብ ይገባል፤የሥር ፍ/ቤት የኦዲት ሥራው ድጋሚ ተመርመረሮ የተገኘው ውጤት ከቀረበለት በኋላ የመሰለውን እንዲወስን በማለት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ከሻረ በኋላ አመልካችን በነጻ ማሰናበት ሲገባው ቀደም ሲል ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ጉዳዩን በድጋሚ እንዲያይ በማለት ጉዳዩን በመመለስ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ አስቀርቦ ግራቀችን ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ስለተገኘ ተሽሯል በማለት ከወሰነ በኋላ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2ለ ውጪ በሆነ ሁኔታ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ የግራቀኙ ማሥረጃ ተሰምቶ እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ  በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ በግልጽ የሚደነግግ ባይሆንም ከአጠቃላይ የይግባኝ ዓላማ እና ግብ አንጻር ሊታይ የሚገባው ከመሆኑም በላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወስን ትዕዛዝ ከመስጠት የሚያግደው ነገር የለም በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት  ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የፍ/ቤቶች ዋነኛ ሚና እውነትን አፈላልጎ ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠት እንደሆነ ከወንጀል ህጉ እና ከወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ይዘት  መገንዘብ ይቻላል፡፡ እውነትን ለማፈላለግ እና እውነቱ ላይ ለመድረስም ፍ/ቤቶች በሕገመንግሥቱ የተሰጣቸውን ሕገመንግሥታዊ ተልዕኮ በአግባቡ በመወጣት ክርክሩን መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለው ወይም ጥፋተኛ አይደለም ተብሎ በነጻ ሊለቀቅ የሚችለው ጥፋተኛ ሊያደርገው ወይም ነጻ ሊያስለቅቀው የሚችል ተገቢ የሆነ ማሥረጃ ሲቀርብበት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የኦዲት ሪፖርቱ ግራቀኙ በተገኙበት ድጋሚ ተሰርቶ ውጤቱ ከቀረበ በኂላ ሊወሰን ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው አመልካች የኦዲት ምርመራው በሚከናወንበት ወቅት በሐገር አቀፍ ምርጫ በምርጫ አስፈጻሚነት ሥራ ላይ የነበሩ በመሆናቸው ነው፤አመልካች ሂሳብ ሹም በመሆናቸው ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ ናቸው፤አመልካች ባልተገኙበት የተከናወነው የኦዲት ሥራ የአመልካችን ጥፋት ሊያሳይ አይችልም በማለት እንደሆነ ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ዓቃቤሕግ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚያስችለውን በቂ ማሥረጃ ካላቀረበ ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በነጻ ሊያሰናብተው የሚገባ ቢሆንም በአመልካች በኩል የቀረበው  የኦዲት ሪፖርት በአመልካች ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችል በቂ ማሥረጃ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የቀረበው የኦዲት ሪፖርት አመልካችን ጥፋተኛ ለማስባል በቂ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው የኦዲት ሪፖርቱ አመልካች ባልተገኙበት የተሰራ እና አመልካች ሒሳብ ሹም በመሆናቸው ምክንያት ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ መሆናቸውን አምኖ ግራቀኙ በተገኙበት እና ግራቀኙ በሚያቀርቡት ማስረጃ የኦዲት ሥራው በገለልተኛ የሒሳብ ባለሙያ ተሰርቶ በሚቀርበው ውጤት መሠረት  ሊወሰን ይገባል በማለት ነው፡፡ ይህ መደምደሚያም አመልካች ባልተገኙበት በተሰራው የኦዲት ሪፖርት መሠረት አመልካች ጥፋተኛ እንዳይባሉ በሌላ በኩል ተጠሪ ክስ ለማስረዳት ያቀረበው የኦዲት ሪፖርት አመልካች ባልተገኙበት የተሰራ ነው ስለተባለ ብቻ አመልካችን ከወዲሁ በነጻ እንዳይለቀቁ የሚያደርግ እና እውነትን አፈላልጎ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ እና የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያሻው ዋነኛ ነጥብ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካችን ጥፋተኛ ለማስባል ዓይነተኛ ማስረጃ ሆኖ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት አመልካች ባልተገኙበት የተሰራ ስለሆነ አመልካች ባልተገኙበት የተሰራው የኦዲት ሪፖርት አመልካችን ጥፋተኛ ሊያስብል አይችልም ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በኂላ ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት  መመለስ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ነው፡፡

የወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 143 ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም ማስረጃ መጥራት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት በአግባቡ ያልተጣሩ ነጥቦች ሲገኙ እና ለትክክለኛ

ፍትሕ አሰጣጥ ሲባል  መጣራት ያላባቸው ሆነው ሲገኙ ተገቢ የሆነውን ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩ እንዲጣራ ማድረግ የሚችልበትን ሥርዓት የሚደነግግ ነው፡፡

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጥፋተኛ ነው በተባለበት ውሳኔ እና በቅጣቱ ይግባኝ በተባለ ጊዜ ጥፋተኛ ነው የተባለበትን ውሳኔ  እና ቅጣቱን ሰርዞ ተከሳሹን በነጻ ለመልቀቅ ወይም ፍርዱን ለውጦ ወይም ሳይለውጥ ቅጣቱን ያጸናል፤ይጨምራል ወይም ይቀንሳል በማለት ይደነግጋል፡፡ይህ ድንጋጌ ፍርድን መለወጥ፤ቅጣትን ማጽናት፤ መጨመር፤መቀነስ እንዲሁም ፍርድን ሰርዞ ተከሳሹን በነጻ እስከመልቀቅ ድረስ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሥልጣን የሰጠ ድንጋጌ እስከሆነ ድረስ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተከሳሽ ላይ የቀረበው ማሥረጃ ተገቢ በሆነ ምክንየት ድጋሚ ሊጣራ ይገባል ብሎ ሲያምንበት በድጋሚ ተጣርቶ እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት እንዳይመለስ የሚያደርገው ነው ተብሎ ሊተረጎም አይገባም፡፡ በእርግጥ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 143 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የኦዲት ሪፖርቱ ግራቀኙ በተገኙበት በገለልተኛ የሒሳብ ባለሙያ ተሰርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኂላ ራሡ ለመወሰን የሚችል ቢሆንም ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቢወሰን የግራቀኙ የይግባኝ መብት የሚጣብብ በመሆኑ ጉዳዩን ለሥር ፍ/ቤት በመመለስ በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘነበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 001028 መጋቢት 12 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 141663

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች፡-** ሻለቃ አለማየሁ ወንጀሎ ለኰ - ጠበቃ አይረሳም ሸንቁጤ

**ተጠሪ፡-** የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16522 ጥር 18 ቀን 2008 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ብይን የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 124937 በቀን 22/02/2009 ዓ.ም በመሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ነው፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 676/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ በኢ.ፌ.ድ.ሪ የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ውስጥ ከግንቦት 8 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በአልባሳት ዋና ግምጃ ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት በማሰብ በሥራው ምክንያት ከመስሪያ ቤቱ ከተረከባቸው የ15 ዓመት የሽልማት ሜዳሊያዎች ውስጥ የሰኔ ወር

ግምጃ ቤት ቆጠራ ሰኔ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ሲካሄድ 300 ሜዳሊያ የአንዱ ዋጋ ብር 2425.49 ጠቅላላ ብር 727647 ለራሱ ያደረገ/ የወሰደ/ ያስወሰደ/ የሰወረ በመሆኑ ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ የቀረበው ክስ ከደረሰው በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም ፤አመልካች የኢፌዲሪ የመከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ሠራዊት አባል ነኝ በአዋጅ 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ መሠረት በሠራዊቱ አባላት መካከል የሚፈፀም የግድያ የድብደባ ወንጀል ወይም የሠራዊቱ አባላት በሚንስትሩ ንብረት ላይ በሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች የማየት ሥልጣን የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው፣ ይህ ከታለፈም ጉድለቱ የተከሰተው ተቀጥሬ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ወስጥ በተደረገ ቆጠራ ነው፤ ምስክሮች ሌላ ተጠርጣሪ እንዳለ እያስረዱ ነበር ስለሆነም የሙያ ሥራን በአግባቡ አለመምራት ነው ክሱ ሊቀርብብኝ የሚገባው ፡፡ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በመቃሚያው ላይ በሰጠው መልስ አመልካች የተከሰሰበት ወንጀል በቀጥታ ከውትድርና ሥራቸው ጋር የሚገናኝ ሳይሆን የህዝብና የመንግስት ንብረት አጉድሏል ተብሎ ነው ይህ የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በሌላ ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ ሌላ ተጠርጣሪ እያለ የቀረበ ነው የተባለው ወደፊት የሚነሳ እንጂ መቃወሚያ የሚሆን አይደለም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም መርምሮ በአዋጅ 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ በተመለከተው መሠረት የሠራዊቱ አባላት በሚኒስቴሩ ንብረቶች ላይ በሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎችን ስለሚል እና ከሙስና ወንጀሎች በቀር የሚል ሀረግ ስለሌለ፣ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ከወንጀል ህግ በኋላ የወጣና በቀዳሚነት ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ እና ልዩ ህግ በህጉ ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ፣ እና አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል ከመሆኑም ባሻገር ፋውንዴሽኑ ራሱን በቻለ ደንብ የተቋቋመ ቢሆንም ሠራተኞቹ ወታደሮች መሆናቸው ዓላማውም የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት ሥራ በተቀላጠፈ ማስተናገድ ተጠሪነቱም ንብረቱም /ኒሻኑም/ የመከላከያ ሚ/ር በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ አነስተኛው ድምጽ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው ብሏል፡፡

ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ራሱን የቻለ ተቋም ነው አይደለም የሚለው በቅድሚያ መርምሮ በደንብ ቁጥር 179/2002 አንቀጽ 2/3/ መሠረት በህጉ የሰውነት አካል የተሠጠው ራሱን የቻለ ተቋም መሆኑን በአንቀጽ 8 እና ተከታዮቹ በቦርድ የሚተዳደር አባላቱን ከሠራዊቱ አባላት በተጨማሪ ሌሎች ሰዎችን የሚያሳትፍ ራሱን የቻለ በራሱ በጀት የሚተዳደር ተቋም እና በራሱ መክሰስና መከሰስ የሚችል ነው፣ ተጠሪነቱ ለመከላከያ ሚኒስቴር ይሁን እንጂ በሚንስቴር በጀት የሚተዳደር ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለቀደሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ሳይሆን በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ሽሯል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ መሠረት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው፤ አመልካች በመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን አገልግሎት የምሰጠው በሠራዊት አባልነት በመመደብ በመሆኑ የተቋሙን ህጋዊ ሠውነት እና የአመልካችን ልዩ መብት ያላገናዘበ ስለሆነ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ የሚል ሲሆን አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን አግባብነት ከደንብ ቁጥር 179/2002 አንቀጽ 3፣6፣7፣13/ለ/ ጋር ለማገናዘብ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዞ በሰጠው መልሱ አመልካች ተቀጥረው የሚሰሩት በመከላከያ ፋውንዴሽን ሲሆን ይህም ራሱን ችሎ የተቋቋመ የህግ ሠውነት ያለው ተቋም ነው፤ ሠራተኞችም የፋውንዴሽኑ እንጂ የመከላከያ ሚኒስቴር አይደለም፣ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች የተቋቋሙት ወታራዊ ይዘት ያላቸው ነው ፡ አመልካች የፈፀሙት ሲቪል ጉዳይ ነው ስለሆነም ጉዳዩ ወታራዊ ይዘት ያለው ባለመሆኑ ስልጣኑ የመደበኛ ፍርድ ቤት ነው ብሏል፡፡ አልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘወ ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት የሚያስገነዝበው አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል እና የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን የአልባሳት ዋና ግምጃ ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት በሥራው ምክንያት ፈጽሞታል ተብሎ የቀረበበትን የከባድ የእምነት ማጉደል ሙስና ወንጀል ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት የመዳኘነት ሥልጣን መኖር አለመኖርን የሚመለከት ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 79 የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው የሚለውን በዚሁ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ወሰን ከሚያመለክተው ጋር አገናዝበን ማየት እንደሚቻለው ማንኛውም ጉዳይ ያለ ገደብ በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነው፡፡ በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 የተቀመጠው የሥልጣን ክፍፍል ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል እና ጉዳዩንም አይቶ ለመወሰን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ለሌላ የዳኝነት ሠጪ አካል ያልተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህንኑ በፍርዱ ሊያልቅ የሚችለውን ጉዳይ ለማየትና ለመወሰን ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው መደበኛ ፍርድ ቤቶች መሆናቸውን ነው፡፡ ስለሆነም መደበኛ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል መሆኑ ላይ ብቻ ሳይወሰኑ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 መሠረት ይኸው ጉዳይ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ቀርቦ የሚታይ መሆን አለመሆኑን በቀጥታ የመመርመር ግዴታ አለባቸው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ክሱ በመደበኛነት የቀረበለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በወ/ህ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ130/2/ መሠረት በቀረበለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ይህንን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለ/ መሠረት ለቀዳሚ ወታራዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም የሚል መቅረቡን እና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የተለያየ ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ነው፡፡ ስለሆነም በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለ/ መሠረት ተሰጥቷል አልተሰጠም የሚለውን መርምረናል፣ የአዋጁ አንቀጽ 38 የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ሥልጣንን የሚዘረዝር ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ በሠራዊቱ አባላት መካከል በሚፈፀም የግድያ ወይም የድብደባ ወንጀል ወይም የሠራዊቱ አባላት በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ በሚፈጽማቸው ማናቸውም ወንጀሎች የዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋል በዚሁ ድንጋጌ

መሠረት በስር ፍ/ቤት የክርክርም ምክንያት የሆነው የሠራዊቱ አባላት በሚኒስትር ንብረት ላይ የሚፈጽሚቸው ማናቸውም ወንጀሎች የሚለውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል ሲሆን የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሞበታል የተባለው በመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በመሆኑ በመከላከያ ሚኒስቴር ንብረት ላይ ተፈጽሟል ለማለት የሁለቱን አካላት አንድነትና ልዩነት ካቋቋማቸው ድንጋጌዎች ተመልክተናል፡፡

የኢ.ፌ.ድ.ሪ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ.316/2008 አንቀጽ 9/1/ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የተቋቋመ እና ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የሆነ የመንግስት አስፈጻሚ አካል ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ላይ … በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ በሚፈፀሙ ማናቸውም ወንጀል ሲል በዚህ የሀገር መከላከያ ሚኒስትር ንብረት ላይ የሚፈፀም ማናቸውም ወንጀሎችን ነው፡፡ በሌላ በኩል የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በመንግስት በጀት ሊሟሉ የማይችሉት የመከላከያ ሠራዊት አባላትን ፍላጐት የሚያረኩና የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽሉ አገልግሎቶች በማቅረብ የተለያዩ ድጋፎችን የማድረግ ዓላማ ይዞ በደንብ ቁጥር 179/2002 የተቋቋመ የህግ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡ ከዓላማው አንጻር ተጠሪነቱ ለሀገር መከላከያ የሚኒስቴር መሆኑ፣ በአባልነትም ከተሰናበቱ የሠራዊቱ አባላትና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተጨማሪ የመከላከያ ሠራዊት አባላት መኖር ፋውንዴሽኑን ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ የተፈጸመ አያደርገውም፡፡ ይህም የሚያስገነዝበው የተለያዩ ህጋዊ ሠውነት ያላቸው አካላት መሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም የሠራዊቱ አባላት በፋውንዴሽኑ ንብረት ላይ የሚፈጽማቸው ማናቸውም ወንጀሎች በሚኒስቴር ላይ እንደተፈፀመ ወንጀሎች የሚገመቱ አለመሆናቸውን ነው፡፡

በሌላ በኩልም ወታደራዊ የፍትህ አካላት በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 28 መቋቋም መሠረታዊ ዓላማ ከሥራው ልዩ ባህሪ አንጻር ወታደራዊ የሆነ የወንጀል ድርጊቶችን በተለይም በቁጥር 38 የተመለከቱትን የመከላከል ፤የመመርመር ፤የመክሰስ፤ ውሳኔ የመስጠትና የማስፈፀም ነው፡፡ ስለሆነም በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ የሠራዊቱ አባል በሚኒስትሩ ንብረት ላይ የተፈፀመ ተብሎ የሚወሰዱ አይደለም፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ድርጊቱ ተፈጽሟል

በተባለበት ጊዜ በሥራ ላይ በነበረው የተሻሻለው የፀረ-ሙስና የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 7/1/ መሠረት ጉዳዩን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

በአጠቃላይ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ተጠሪ ያቀረበውን ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ክስ የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት የስር ፍ/ቤት በአብላጫ ድምጽ የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16555 ጥር 18 ቀን 2008 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ብይን በመሻር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ/ቁ 124937 በቀን 22/02/2009 ዓ.ም የሰው ፍርድ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

የሰ/መ/ቁጥር 141978

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች፡- የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ - ሙሉተስፋ ከበደ**

**ተጠሪ፡- እዮኤል ተስፋዬ የሺጥላ - አልቀረቡም**

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 114261 በቀን 22/02/09 የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 183790 በቀን 13/06/2009 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በዐቃቤ ህግ አማካኝነት የቀረበን ክስ ስለማንሳትና ከክርክር ውጭ ስለመሆን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ሁለት የወንጀል ክስ ያቀረበ ሲሆን ይኸውም የወንጀል ህግ ቁጥር 559/2/ እና 575 /2/ /ሀ/ የተመለከተውን ተላልፎ በዋናው መንገድ ለሚጓዝ ተሽከርካሪ ቅድሚያ በመከልከልና ያለጥንቃቄ ሲያሽከረክር

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-06155 ኢ.ት የሆነ መኪና የኋላ ግራ ጐን የገጨና አቅጣጫ እንዲስትና ከድንጋይ ጋር ተጋጭቶ በውስጡ የነበሩት የግል ተበዳይ አብነት ጐሹ በመኪናው አካል ተመትቶ የአንገት የቀኝ እግር እና የአካል ጡንቻዎች ላይ የህመም ስሜት እንዲሰማ ያደረገ እና እርዳታ ሳያደርግ በሌላ መኪና ገብቶ ያመለጠ በመሆኑ በቸልተኝነት ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰና በአደጋ ላይ የሚገኝ ሰውን አለመርዳት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ የቀረበው ክስ ደርሶት እምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ከግል ተበዳይ ጋር የታረቀ መሆኑን የገለፀ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህንኑ ገልጾ በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በወንጀል ህግ ሥ/ሥርዓት ቁ 151/2/ መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሳይቀበል መዝገቡን ዘግቶቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በተጠሪ ላይ የቀረበው የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ በወንጀል ህግ 212 መሠረት በግል አቤቱታ የማይቀርብና በወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት በእርቅ ሊነሳ የማይችል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን ያቋረጠው መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ የቀረበ ክስ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት በእርቅ በመጨረስ የሚቋረጥ መሆኑን ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ታዞ በሰጠው መልሱ በወቅቱ እኔም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኝ እራሴን ለማዳን ወደ ህክምና ተቋም ሄጃለሁ ሆነ ብዬ ሰውን ላለመርዳት አልሄድኩም ብሎ ክሱን በመካድ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪም ዕርቁን የማይቃወም መሆኑን እና የሚያቀርቡት ማስረጃ እንደሌለ በመግለጽ ፍ/ቤቱ ክሱን አቋርጧል እንጂ የግል አቤቱታ ነው በማለት አይደለም፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልኝ ብሏል፡፡ አመልካች በሰጠው የመልስ መልስም ሁለቱም ክሱ የተቋረጠው በእርቅ እንጂ አመልካች ማስረጃ ባለማቅረቡ ወይም እንደክሱ ባለማስረዳቱ አይደለም የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/3/ የተመለከተውን ተቃውሞ አላነሳንም እንጂ በሁለተኛው ክስ ላይ ተቃውሞ ገልፀናል፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ክሱን ማቋረጡ ተገቢ አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነው በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶችንና የሚቀርቡበትን አግባብ የሚመለከት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ ከቀረበው ጭብጥ አንጻር የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ሀ/ በወንጀል ህግ ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት ከተበዳዩ ጋር በዕርቅ በመጨረስ ክሱ የሚቋረጥ ስለመሆኑ አለመሆኑ ምላሽ የሚሰጥ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የወንጀል ህግ ግብ ስለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የሀገሪቱን መንግስት የህዝቦችን የነዋሪዎቹን ሰላም ደህንነት ሥርዓት መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ መንግስት በህዝብ ስም ሆኖ ለዜጐች ተወክሎ የወንጀል ጉዳይን እንዲከታተልና ክሶ እንዲያስቀጣ ኃላፊነት ሊወድቅበት የቻለውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም የጠቅላላውን ህዝብ ሰላምና ፀጥታ የሚያደፈርሱ ከተጐጂው ሠው ጥቅም በላይ አልፈው የሌሎችን ጥቅም የማይነኩ አሉ፡፡ በእርግጥ በጠቅላላው ተበዳይ ቢስማማም ባይስማማም የወንጀል ክስን መከታተል የመንግስት ኃላፊነት ቢሆንም በእነደዚህ ባሉ ነገሮች የተጐዳው ሠው ጉዳዩን ክሶ በፍርድ እንዲታይለት ፈቃደኛ መሆኑ በእርግጥ ካላሳየ በቀር መንግስት ይህንን ግዳጁን አያከናውንም፡፡

የወንጀል ህጉ ክስ በቀረበ ጊዜ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች የሚገልጽ የተጠናቀቀ ዝርዝር አይገልጽም ፡፡የወንጀል ህግ አንቀጽ 212 ቢሆንም በጠቅላላው መልክ ነው በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ውስጥም የሚገኙ ድንጋጌዎች "ማናቸውም … የግል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ …. ይቀጣል" ሲል ያዛሉ፡፡ እነዚህን አንቀጾች በመተላለፍ ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ በግል አቤቱታ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት ሰው በቀር በሌላ በማንም ሠው የክስ ጉዳይ ሊንቀሳቀስ አይችልም፡፡ የግል ከሳሹ የክሱን ማመልከቻ ካዘጋጀ በኂላ የክሱ ጉዳይ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 150-153 በተገለፀው መሠረት ይመራል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በአመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት ክሶች 1ኛ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/2/ እና 2ኛ የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ በግል ተበዳይ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ አማኻኝነት የሚቀርቡ ወይም እንዲቀርቡ የታዘዙ ክሶች አይደሉም፡፡ ክሱም በስር ፍርድ ቤት የቀረበው በአመልካች /በመንግስት/ በዐቃቤ ህግ ነው፡፡ ክሱን የሚመራው

በወ/ህ/ሥ/ሥ /ቁ 132-135 ፣ 185፣196፣117፣ 94-98፣ 123-131 እና 136-149 በተመለከቱት መሠረት ይሆናል፡፡

ስለሆነም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን የወንጀል ክስ የግል ተበዳይ ክሱን ትቷል በማለት በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 151/3/ መሠረት በግል አቤት ባይ የቀረበ ክስ በሚመራበት ሥነ ሥርዓት የወንጀል ክሱን ያቋረጠው የወንጀል ህግን ግብ እና በዓቃቤ ህግ ስለሚቀርቡ የወንጀል ክስ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ክስ አመራር ያልተከተለ በመሆኑ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንን ሳያርም ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 114261 በቀን 22/02/09 የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 183750 በቀን 13/06/2009 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች የቀረበውን ክስ ተጠሪን አስቀርቦ የወንጀል ክሱን በመስማት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /መ/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የሰ/መ/ቁ 137545

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ አሸብር መለስ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 626/4/ሀ በመተላለፍ ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ጾታ ካላት ዕድሜዋ አሥራ ሥምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም በማሰብ በቀን 10/08/07 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 12፡30 ሲሆን በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 ክልል ልዩ ቦታው ላምበረት አካባቢ የቤት ሠራተኛ የሆነችው እና እድሜዋ ከ15/16 ዓመት የሚገመተውን የግል ተበዳይ ዓይናለም አየነው ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት የፈጸመ በመሆኑ ዕድሜያቸው አሥራ ሦስት ዓመት በሆነ እና አሥራ ሥምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረሥጋ ድፍረት በደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ለአመልካች ክሱ ተነቦለት መቃወሚያ አቅርቦ መቃወሚያው በብይን ውድቅ ከተደረገ በኋላ የእምነት ክሕደት ቃሉን ሲጠየቅ ድርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ

በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የተጠሪ ምስክሮች እንዲሰሙ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የተጠሪ ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡

የተጠሪ 1ኛ ምስክር የሆነችው የግል ተበዳይ ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል በአመልካች ቤት በቤት ሰራተኛነት የተቀጠረች መሆኑን፤አመልካች ጠዋት ሚስቱ ወደ ሥራ ስትወጣ ቀኑን በማታስታውሰው ዕለት አመልካች የግብረሥጋ ግንኙነት የፈጸመባት መሆኑን፤ድርጊቱን የፈጸመችው በፍላጎት መሆኑን፤አመልካች የወርአበባ መምጫ ጊዜዋን የሚያውቅ እና የሚቆጣጠር መሆኑን፤ከአመልካች ቤት ከወጣች በኂላ ሌላ ሰው ቤት የገባች መሆኑን፤ለአመልካች ስልክ ደውላ አርግዣለሁ ስትለው የሰደባት እና አላውቅልሽም ብሎ ስልኩን የዘጋው መሆኑን፤በአመልካች ቤት ያስቀጠረቻት ትዝታ የተባለች ግለሰብ መሆንዋን፤ድርጊቱ እንደተፈጸመ ለማንም ያልተናገረች መሆኑን፤ድርጊቱ ከተፈጸመ ከተወሰነ ቀን በኂላ ከቤቱ የወጣች እና ወደ ትዝታ ቤት የሔደች መሆኑን፤ትዝታ ሰው ቤት ካስቀጠረቻት በኂላ አርግዣለሁ ብላ ለአመልካች ስልክ ስትደውልለት ሲሰድባት ለትዝታ አርግዣለሁ ብላ የነገረቻት መሆኑን፤አርግዣለሁ ያለችው ገንዘቧን ስለከለከላት ተናዳ መሆኑን፤የአመልካች ባለቤት ደውላ የጠየቀቻት እና ሁሉንም ነገር የነገረቻት መሆኑን፤የአመልካች ባለቤት ጋንዲ ሆስፒታል ወስዳ ያስመረመረቻት መሆኑን በመግለጽ መሥክራለች፡፡

የተጠሪ 2ኛ ምስክር ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል የግል ተበዳይ አመልካች ደፍሮኛል ስትላት ማመን ስላቃታት ስልክ ደውይለት ያለቻት መሆኑን፤የግል ተበዳይ ለአመልካች አርግዣለሁ ብላ ስልክ ስትደውልለት የሰደባት መሆኑን፤የአመልካች ባለቤት ስለድርጊቱ ለማወቅ የግል ተበዳይ መመርመር አለባት በማለት ስልክ የደወለችላት መሆኑን፤ከአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን የግል ተበዳይን ሆስፒታል ወስደው ያስመረመሯት መሆኑን በመግለጽ መስክራለች፡፡ የግል ተበዳይ በ25/10/07 ዓ.ም የተመረመረች እና በክብረንጽሕና መገለጫ አካሏ ላይ የቆየ የክብረንጽህና መገርሰስ መኖሩን እና ሌላ አካላዊ ጉዳት ያልተገኘባት መሆኑን የሚያሳይ ከጋንዲ መታሠቢያ ሆስፒታል የቀረበው የሕክምና ማስረጃ እና የግል ተበዳይ ዕድሜ ከ15-16 ዓመት መሆኑን የሚያሳይ ከዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል የተጻፈ የሕክምና ማሥረጃም ቀርቧል፡፡

ፍ/ቤቱ ተጠሪ ባቀረበው የሰው ምስክር እና የሰነድ ማሥረጃ እንደክሱ አስረድቷል በማለት አመልካች እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ 1ኛ የአመልካች መከላከያ ምስክር ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል አመልካች ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ሰዓት በቤት ውስጥ ያልነበረ መሆኑን፤የግል ተበዳይ ለአመልካች ሥልክ ደውላ አርግዣለሁ ያለች መሆኑን  እና እውነት መሆን አለመሆኑን  ለማረጋገጥ ጋንዲ ሆስፒታል ወስደው ያስመረመረቻት መሆኑን በመግለጽ መስክራለች፡፡

2ኛ የአመልካች መከላከያ ምሥክር የግል ተበዳይ ስትሆን ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምሰክርነት ቃል በአመልካች ቤት ተቀጥራ ስትሰራ የነበረ እና ሌላ ሰው ቤት ለመስራት ብላ ከአመልካች ቤት በፍላጎትዋ የለቀቀች መሆኑን፤ከአመልካች ቤት ከለቀቀች በኋላ የተቀጠረችበት ቤት ባለቤት አስቀድሞ ስትሰሪበት የነበረው  ቤት አሰሪዎች ገንዘብሽን ከፍለውሻል ወይ ብላ ስትጠይቃት ገንዘቤን አልሰጡኝም ስትላት ገንዘብሽን እንዲሰጡሽ ክሰሽው አስፈራሪያቸው ስላለቻት ክሱን የመሰረተች መሆኑን እንጂ ከአመልካች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽማ የማታውቅ መሆኑን፤አመልካችን ያለአግባብ በመክሰሷ የጸጸታት መሆኑን፤በዚህም ምክንያት አመልካችንና ባለቤቱን ይቅርታ የጠየቀቻቸው መሆኑን እና ክሱን እንደምታነሳ የነገረቻቸው መሆኑን፤ይቅርታ ጠይቂ ብሎ የነገራት ወይም የመከራት ሰው የሌለ መሆኑን፤በራሷ ተነሳሽነት ይቅርታ የጠየቀች መሆኑን እና በዚህም ምክንያት ከአመልካች ወይም ከባለቤቱ የተከፈላት ገንዘብ የሌለ መሆኑን በመግለጽ መሥክራለች፡፡

የአመልካች 3ኛ መከላከያ ምስክርነት ቃል  ለፍ/ቤቱ በሰጠው የምሥክርነት ቃል ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ዕለት አመልካች ቤት ምሳ ተጠርተው ሄደው እንደነበረ እና ተበዳይ በወቅቱ ጤናማ እንደነበረች እና ሰኔ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ልጁን ሲያስመርቅ አመልካችን እና ባለቤቱን ጠርቷቸው ተበዳይ ለአመልካች ስልክ ደውላ ደፍሮኛል ብየ እከስሃለሁ ያለችው መሆኑን በመግለጽ መሥክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ በግራቀኙ የቀረቡትን ማሥረጃዎች ከመረመረ በኋላ አመልካች የግል ተበዳይን በመከላከያ ምሥክርነት አቅርቦ ያሰማ ቢሆንም የግል ተበዳይ የአመልካች መከላከያ ምሥክር ሆና በሰጠችው ቃል አመልካችን እንድከሰው የገፋፉችኝ አመልካችን የማታውቅ እና ከግል ተበዳይ ጋርም ዝምድና የሌላት እና አንድ ሣምንት ብቻ የሠራችባት አሰሪ ነች ያለች በመሆኑ በምንም ሁኔታ ሊሆን የሚችል አይደለም፤ምስክሯ አመልካች አንዴ ደፍሮኛል ሌላ ጊዜ ደግሞ

አልደፈረኝም በማለት የሰጠችው ቃል እምነት የሚጣልበት አይደለም፣የአመልካች ምስክሮች ቃልም እርስ በእርስ የሚደጋገፍ አይደለም በማለት አመልካች በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ነው ብሎ በሦስት ዓመት ከሠባት ወር ቀላል እሥራት እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-የግል ተበዳይ የአመልካች የመከላከያ ምስክር ሆና ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምሥክርነት ቃል አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ድርጊት አልፈጸመብኝም የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽሞብኛል ያልኩት ገንዘቤን ስለከለከለኝ እና አሠሪዬ አመልካች ገንዘብሽን እንዲሰጥሽ ክሰሽው ስላለችኝ ነው በማለት በመሰከረችበት ሁኔታ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የግል ተበዳይ በአመልካች የመከላከያ ምሥክርነት ቀርባ ከአመልካች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት አልፈጸምንም፣የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽመናል ብዬ የከሰስኩት የሰራሁበትን ደመወዜን እንዲከፍለኝ ነው በማለት በመሰከረችበት ሁኔታ አመልካች ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡ የግል ተበዳይ የተጠሪ ምስክር ሆነ በመቅረብ አመልካች በክሱ በተገለጸው ሁኔታ ድርጊቱን የፈጸመባት ስለመሆኑ የመሰከረች ቢሆንም የአመልካች መከላከያ ምስክር ሆና ስትቀርብ ከአመልካች ቤት በፍላጎትዋ የለቀቀች መሆኑን፣አመልካች በክሱ የተገለጸውን ድርጊት ፈጽሟል ያለችው ከአመልካች ቤት ከለቀቀች በኋላ የተቀጠረችበት ቤት አሰሪ አመልካች ገንዘብሽን እንዲሰጥሽ ክሰሽው አስፈራሪያቸው ስላለቻች እንጂ ከአመልካች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽማ የማታውቅ መሆኑን፣አመልካችን ያለአግባብ በመክሰሷ የጸጸታት መሆኑን፣አመልካችንና ባለቤቱን ይቅርታ የጠየቀቻቸው መሆኑን እና በዚህም ምክንያት ከአመልካች ወይም ከባለቤቱ የተከፈላት ገንዘብ የሌለ መሆኑን በመግለጽ መሥክራለች፡፡

ተከሳሽ በቀረበበት ማሥረጃ መሠረት  የተመሰከረበት እንደሆነ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል ብይን የሚሰጥ መሆኑ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/1 መሠረት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች በቀረበበት ማስረጃ መሠረት የተመሰከረበት ሆኖ ስላገኘው አመልካች እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም የግል ተበዳይ የአመልካች መከላከያ ምሥክር ሆና ቀርባ አመልካች ድርጊቱን ያልፈጸመባት መሆኑን፤ድርጊቱ ተፈጽሞብኛል ያለችው ገንዘብዋን ስላልከፈላት ተናዳ እና አሰሪዋ ክሰሽው ስላለቻት መሆኑን፤በዚህም ምክንያት ተጸጽታ አመልካችን እና ባለቤቱን ይቅርታ የጠየቀቻቸው መሆኑን እና ይህንንም በማድረግዋ ከአመልካች ወይም ከባለቤቱ የተከፈላት ገንዘብ የሌለ መሆኑን በማያሻማ ቃል ለፍ/ቤቱ ገልጻለች፡፡ ከዚህም በላይ የግል ተበዳይ የዓቃቤሕግ ቀጥተኛ ምስክር በመሆን ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል አርግዠለሁ ያለችው አመልካች ገንዘቧን ስለከለከላት ተናዳ መሆኑን በመግለጽ የሰጠችው የምስክርነት ቃል የአመልካች መከላከያ ምስክር በመሆን ከሰጠችው የምስክርነት ቃል ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የግል ተበዳይ  ከመነሻውም ቢሆን አመልካች የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽሞብኛል በማለት የሰጠችው የምሰክርነት ቃል ሐሰት እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡

በአጠቃላይ የተጠሪ ቀጥተኛ ምስክር የሆነችው የግል ተበዳይ ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል አመልካች ድርጊቱን አልፈጸመብኝም፤አመልካች የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽሞብኛል ያልኩት ገንዘቤን ስለከለከለኝ ነው፤ ይህንንም በማድረጌ ስለተጸጸትኩ አመልካችን እና ባለቤቱን ይቅርታ ጠይቄያቸዋለሁ፤ይህንንም በማድረጌ የተከፈለኝ ገንዘብ የለም በማለት የመሰከረች በመሆኑ እና ተጠሪ የግል ተበዳይ የአመልካች የመከላከያ ምስክር በመሆን የሰጠችው የምሥክርነት ቃል ተደልላ ወይም ጥቅም አግኝታ የሰጠችው ቃል መሆኑን  ያላረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የተጠሪን ማስረጃ የጉዳዩ ባለቤት በሆነችው የግል ተበዳይ በበቂ ሁኔታ አስተባብሏል፡፡ አመልካች የቀረበበትን ክስ እስካስተባበለ ድረስ ፍ/ቤቱ  በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149/2 መሠረት አመልካችን በነጻ መልቀቅ ይገባዋል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች የጉዳዩ ባለቤት የሆነችውን የግል ተበዳይ በመከላከያ ምስክርነት አቅርቦ የቀረበበትን ክስ በበቂ ሁኔታ ባስተባበለበት ሁኔታ አመልካችን ጥፋተኛ በማለት በሦስት ዓመት ከሰባት ወር ቀላል እሥራት ሊቀጣ ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በአብላጫ ድምጽ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 230341 ሕዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሕዳር 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 188723 ጥር 23 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ/2 መሠረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ ቀጥተኛ ምስክር የሆነችው የግል ተበዳይ አመልካች ድርጊቱን እንዳልፈጸመ በመግለጽ የአመልካች መከላከያ ምሥክር በመሆን የመሠከረች በመሆኑ አመልካች የቀረበበትን ክስ ተከላክሏል በማለት አመልካች በነጻ እንዲሰናበት በአብላጫ ድምጽ ወስነናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

-የሚመለከተው ማረሚያ ቤት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የተሻረ መሆኑ አውቆ አመልካችን ከእሥር እንዲፈታው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

-የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ 230341 የሆነው መዝገብ ወደመጣበት ይመለስ፡፡

**-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>**የልዩነት ሃሳብ**</u>

ስማችን በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተመለከተው ዳኞች በአብላጫው ድምፅ ከሰጠው ውሳኔ በሚከተለው ምክንያት በሃሳብ ተለይተናል፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበው ክስ ሲታይ፡- አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 626/4//ሀ/ በመተላለፍ ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ጾታ ካላት ዕድሜዋ አሥራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም በማሰብ በቀን 10/08/07 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 12፡30 ሲሆን በየካ ክፍለከተማ ቀበሌ 16/17 ክልል ልዩ ቦታው ላምበረት አካባቢ የቤት ሠራተኛ የሆነችው እና እድሜዋ ከ15/16 ዓመት የሚገመተውን የግል ተበዳይ ዓይናለም አየነው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ በመሆኑ ዕድሜአቸው

አሥራ ሦስት ዓመት በሆነ እና አሥራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው።

አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ድርጊቱን አለመፈፀሙና ጥፋተኛ አለመሆኑ ገልፆ የተከራከረ ቢሆንም በወቅቱ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በቀረበበት ክስ የወንጀል ህግ አንቀፅ 626/4/ሀ ጥፋተኛ በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሰው የቀረቡት የዓ/ህግ ምስክሮች በአመልካች በቤት ሰራተኛነት ተቀጥራ ስትሰራ የነበረችው ተበዳይ አይናለም አየነው አመልካች ጠዋት ሚስቱ ወደ ሥራ ስትወጣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመባት መሆኑን፤ድርጊቱን የፈጸመችው በፍላጎት መሆኑን፤የግል ተበዳይ በሌላ ጊዜ ለአመልካች ስልክ ደውላ አርግዣለሁ ስትለው የሰደባት እና አላውቅልሽም ብሎ ስልኩን የዘጋው መሆኑን፤2ኛ የዓ/ህግ ምስክር ደግሞ ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል የግል ተበዳይ አመልካች ደፍሮኛል በማለት ከነገረቻት በኋላ ስልክ ደውይለት ያለቻት መሆኑን፤የግል ተበዳይ ለአመልካች አርግዣለሁ ብላ ስልክ ስትደውልለት የሰደባት መሆኑን መስክራለች፣ በተጨማሪ የግል ተበዳይ ጋንዲ መታሠቢያ ሆስፒታል በመሄድ የተመረመረች ሲሆን በክብረንጽሕና መገለጫ አካሏ ላይ የቆየ የክብረንጽህና መገርሰስ መኖሩን እና ሌላ አካላዊ ጉዳት ያልተገኘባት መሆኑን ፣እንዲሁም የግል ተበዳይ ዕድሜ ከ15-16 ዓመት መሆኑን የሚያሳይ ከዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል የተጻፈ የሕክምና ማስረጃ በመቅረቡና በቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ስለመሆኑ መዝገቡ ያመለክታል።

አመልካች የተከሰሱት የወንጀል ህግ አንቀፅ 626/4/ሀ በመሆኑ ይኸው የወንጀል ህግ አንቀፅ 626/4/ሀ/ “ ማንም ሰው ተቃራኒ ፆታ ካላት ፣ዕድሜዋ አሥራ ሦስት ዓመት በላይ ሆኖ አሥራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ይህችው ልጅ እንዲህ አይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈፅም ያደረገ እንደሆነ …“ ስለመሆኑ ተደንግጓል:: ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የግል ተበዳይ አካለመጠን ያልደረሰች እድሜዋ ከ16 አመት በታች ሆና በአመልካች ቁጥጥር ስር የቤት ሰራተኛ የነበረች በመሆንዋ ከክርክሩ ይዘት ለመረዳት ችለናል። ስለሆነም አመልካች ፈፅሞታል የተባለው ወንጀል የግል ተበዳይ ፍቃድ መኖሩ ተበዳይ አካለመጠን ያልደረሰች ስለሆነች ፍቃደኛ ነበረች ተብሎ አመልካች ከጥፋተኝነት ሊድን የሚችልበት

የሕግ ምክንያት ሊኖር ካለመቻሉም በላይ የነበራቸው የአሰሪና የቤት ሠራተኛ ግንኙነት ተበዳይን በተጽዕኖው ስር ያዋላት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው ፡፡

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤት አመልካች ድርጊቱን ፈፀመ በማለት ድምዳሜ የደረሱት አመልካች ድርጊቱን ስለመፈፀሙ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እና የፅሁፍ ማስረጃዎች በሚገባ ተረጋግጧል ፤አመልካች በመከላከያ ማስረጃው አልተደገፋም በሚል ምክንያት ነው፡፡አመልካች ከሚከራከርባቸው ነጥቦች ውስጥ የአመልካችን የድርጊት ፈጻሚነት በተገቢው መንገድ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ያለማስደገፋንና የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የማስተባበላቸው ሁኔታን በተለይ የግል ተበዳይ መከላከያ ምስክር ሆና አልተደፈርኩም በማለት መስክራለች በማለት ሲሆን፤ የበታች ፍርድ ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ስር የተመለከተውን የማስረጃ ምዘና መርህ ተከትለው የግል ተበዳይ አካለ መጠን ያልደረሰችና መጀመሪያ የዓ/ህግ ምስክር በመሆን ቀርባ መደፈርዋ በተመለከተ የሰጠችው የምስክርነት ቃል በቀረበው የሃኪም ማስረጃም ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑ ተአማኒነት ያለው መጀመሪያ የሰጠችው የምስክርነት ቃል ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ባላቸው ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ተጠቅመው ማስረጃውን መዝነው አመልካችን ጥፋተኛ ያደረጉ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳየን እና በአመልካችና ተበዳይ የነበረው ግንኙነትም የአሰሪና የቤት ሠራተኛ መሆን በራሱ ግምት ውስጥ አስገብቶ ተመዝኖ የተስጠ በመሆኑ ተገቢና ህጋዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ከዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለውም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎቸ ተመዝነው መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም አብላጫው ድምፅ አመልካች በነፃ እንዲሰናበት እንደ ምክንያትነት የገለፁት የተከሳሽ 2ኛ መከላከያ ምስክር በመሆን የቀረቡት የግል ተበዳይ በዓ/ህግ ምስክር ሆና የሰጠችው ምስክርነት በመቀየር አመልካችን የከሰስኩት የሰራሁበት ገንዘብ ስላልሰጠኝ እንጂ ከአመልካች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም በማለት በመመስከርዋ የዓ/ህግ ምስክር ሆና የሰጠችው ምስክርነት ቃል ተአማኒነት የለውም በማለት መሆኑ ውሳኔው ያመለክታል እዚህ ላይ መታየት ያለበት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘን ጉዳይ ማረም የሚችለው በውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች

ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ይህ ሰበር ችሎት ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 41526 እና ሌሎች  በርካታ መዛግብት የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ በየትኛውም ፍርድ ቤት፤ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትንም ጨምሮ የሚያስገድድ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2 መሰረት አስገዳጅነት ያለው ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም የግል ተበዳይ በአመልካች ላይ ክስ መስርታ የከሳሽነት ቃል ከሰጠች በኋላ ፍርድ ቤት ቀርባም መደፈርዋን አረጋግጣ እያለ ፤መጀመሪያ የሰጠችው የምስክርነት ቃል ቀይራለች እና ተአማኒነት ያለው በኋላ የተሰጠው ምስክርነት ነው በማለት በአብላጫው ድምፅ መወሰኑ የግል ተበዳይ አካለመጠን ያልደረሰች ከመሆኑዋና የአመልካች የቤት ሠራተኛ ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በሃኪም ማስረጃም ጭምር የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ፣የዓ/ህግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ መመዘን እንዳለበት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35697 የሰጠው ትርጉም ያላገናዘበና የስር ፍርድ ቤቶች ባላቸው ማስረጃ የመመዘን ስልጣን አመልካች ወንጀል መፈፀሙ በሰውና በሃኪም ማስረጃ ተረጋግጧል አመልካች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በመከላከያ ማሰረጃው አላስተባበለም በማለት የገለጸዉ ሲታይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁ.25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር ይህን በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር ከመቀበል ዉጭ ድጋሚ ለማጣራት የሚያስችለዉ የህግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለድርጊቱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተወሰነው ወንጀሉ መሰራቱ ወይም መፈጸሙና ተሰራ ወይም ተፈጸመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በአመልካች በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑና ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4) እና 626(4(ሀ))  ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያሟላ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ጥፋተኛ በማለት የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት አብላጫው ድምፅ ከሰጠው ውሳኔ በሃሳብ ተለይተናል ፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

የሰበር መ/ቁ/127505

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች ፡- አበራ ዋቅጅራ

ተጠሪ ፡- የቤ/ጉ/ክልል ፍትህ ቢሮ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የወንጀል ክርክር የሚመለከት ነዉ ፡፡ተጠሪ አመልካች ላይ ያቀረበዉ ክስ ይዘት የወንጀል ህግ አንቀጽ 27/1 እና 539/1/ሀ ተላልፎ በ09/02/07 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ላይ በወንበራ ወረዳ ገሳንገሳ ቀበሌ አቶ ፍቃዱ አድማሱ መጠጥ ቤት ዉስጥ ምንም ምክንያት ሳይኖረዉ ከተቀመጠበት ተነስቶ የግል ተበዳይ አቶ በየነ ቡባ መቀመጫዉ ላይ በካራ ሁለት ጊዜ የወጋዉ ስለሆነ ከባድ የግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ሲሆን አመልካች ክዶ በመከራከሩ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኝ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች የዓቃቤ ህግ ማስረጃ ማስተባበል አልቻለም በማለት በተከሰሰበት አንቀጽ ጥፋተኛነትና 16 ዓመት ከ6ወር ጽኑ እስራት ቅጣት ወስኖበታል አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ፍ/ቤቱም አከራክሮ ድርጊቱ የተፈጸመዉ በመጠጥ ቤት በተነሳ ድንገተኛ ፀብ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ አንቀጹን ወደ 27/1/ እና 540 በመለወጥ ቅጣቱንም ወደ 10 ዓመት ጽኑ እስራት አሻሽሎ ፍርድ ሰጥቷል ፡፡

አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም ፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮ የግል ተበዳይ ላይ ደረሰ ከተባለዉ ጉዳት አንጻር አመልካች በወ/ህግ አንቀጽ 27/1/እና 540 ስር ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል ፡፡ለተጠሪ የፍ/ቤት መጥሪያ በፖስታ ቤት በኩል የተላከለት ቢሆንም መልስ አልሰጠም ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አኳያ ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡

ከመዝገቡ መርምረን እንደተገነዘብነዉ ድርጊቱ የተፈጸመዉ በመጠጥ ቤት በተነሳ ድንገተኛ ፀብ ሲሆን ዐቃቤህግ አመልካች በካራ የተበዳይ መቀመጫ ላይ ሁለት ቦታ ወግቶታል ሲል አመልካች ደግሞ በፀቡ ምክንያት ተያይዘዉ ሲወድቁ ተበዳይ አረቄ መጠጫ መለኪያ ሲባሪ ላይ ወድቆ የተወጋ እንጂ አመልካች ስለት ነገር በእጁ እንዳልነበር በመከላከያ ምስክር አስረድቻለሁ በማለት ቢከራከርም የስር ፍ/ቤቶች አልተቀበሉም ስለሆነም አመልካች የግል ተበዳይን በስለት ነገር መቀመጫዉ ላይ ሁለት ጊዜ ወግቶ ጉዳት ማድረሱ ማስረጃ የመመርመርና ፍሬነገር የማጣራት ስልጣን በህግ የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል ፡፡በዚህ ችሎት እልባት የሚሻዉ ነጥብ የአመልካች ድርጊት የወ/ህጉን አንቀጽ 540 ያቋቁማል መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ላይ ነዉ ፡፡

በወ/ህግ አንቀጽ 540 ስር አንድ ሰዉ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ፈጽሟል ተብሎ የሚቀጣዉ የድርጊቱ አፈጻጸም በወ/ህጉ አንቀጽ 539 ወይም 541 ስር የተመለከተዉን ፍሬነገር የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ ነዉ ፡፡ ስለዚህም የተፈጸመዉ ድርጊት የወ/ህጉን አንቀጽ 539 ሳይሆን 540 ያቋቁማል በማለት ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት ሊመረመር የቀረበ ነዉ ፡፡ድርጊቱ የተፈጸመዉ ሰዉን መግደል ሀሳብ ኖሮት ነገር ግን ዉጤት ሳያገኝ ቢቀርም በመደቡ ጥፋተኛ ተብሎ እንደሚቀጣ የወ/ህጉ አንቀጽ 27/1/እና/3/ ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የፈጸመዉ ድርጊት ተበዳይን መግደል ሀሳብ ኖሮት በሙከራ የቀረ ነዉን የሚለዉን ስንመረምር የግል ተበዳይ የተወጋዉ መቀመጫዉ ላይ መሆኑና የጉዳቱ መጠንም 2 በ2 ሳ.ሜ እና 2 በ5ሳ.ሜ እንደሆነ በማስረጃ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል ፡፡

በመሰረቱ የወንጀል አድራጊዉ የሀሳብ ክፍል የሚታወቀዉ ከወንጀሉ አፈጻጸም ጠቅላላ ሁኔታዎች እንደሆነ ልብ ይለዋል ፡፡አመልካች ስለት ነገር ተጠቅሟል እስከተባለ ድረስ የግል ተበዳይን መግደል አስቦ ቢሆን ኖሮ ስስ ብልቶቹ ላይ እንዳይወጋዉ ያላስቻለዉ ነገር ስለመኖሩ አልተረጋገጠም ፡፡ አመልካች በመጠጥ ቤት በተነሳ ፀብ መነሻ ከግል ተበዳይ ጋር ተያይዘዉ በወደቁበት ሁኔታ የግል ተበዳይ መቀመጫ ላይ መዉጋቱና የደረሰዉም የአካል ጉዳት መሆኑ ሲታይ አመልካች ተበዳይን የመግደል ሀሳብ ነበረዉ የሚለዉን የሀሳብ ክፍል ግምት ወይም ድምዳሜ ለመድረስ የሚያስችል ሆኖ አላገኘንም ፡፡ይልቁንም አመልካች ሆነ ብሎ ስለት ነገር ተጠቀሞ የግል ተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬነገር በመሆኑ በወ/ህጉ አንቀጽ 555/1/ የሚያሟላ ድርጊት ሆኖ አግኝተናል ፡፡ በዚህ አግባብ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በአንቀጽ 27/1/እና 540 ስር ያስተላለፈዉን የጥፋተኛነት ዉሳኔ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 113/2/ መሰረት ለዉጠን አመልካች የግል ተበዳይ ላይ ላደረሰዉ ከባድ አካል ጉዳት በወ/ህጉ አንቀጽ 555/1/ስር ጥፋተኛ ነዉ ብለናል ፡፡ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ደንጋጌ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት  በወጣዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ /2/2006 ደረጃና እርከን የወጣለት ስለሆነ በዚሁ መሰረት በድርጊቱ ከባድ የአካል ጉዳት መድረሱ ስለተረጋገጠ ደረጃ1 እርከን 16 ላይ ይመደባል ፡፡ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስለመኖሩ በፍርዱ አልተመለከተም ፡፡ በአመልካች በኩል ተቀባይነት ያገኘዉ 4 የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስለመኖሩ በስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ተገልጸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት 4 እርከን ሲቀነስ እርከን 12 ላይ ያርፋል ፡፡ እርከን 12 ላይ የተመለከተዉ የእስራት ቅጣት ፈቅደ ስልጣን ከ2 አመት እስከ 2 ዓመት ከ6ወር ሲሆን አመልካች በዚህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም የታሰረዉ ታሳቢ ተደርጎ የእርከኑ ጣሪያ 2 አመት ከ6ወር እስራት እንዲቀጣ ፈርደናል ፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩ ተወስኗል ፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1ኛ/ የቤ/ጉ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/06525 በ22/10/07 ዓ.ም የሰጠዉ የጥፋተኛነትና የቅጣት ዉሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/06674 በ19/02/08 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 195/2/ለ/2 መሰረት ተሻሽሎ ተወስኗል  ፡፡

2ኛ/ አመልካች ለፈጸመዉ ድርጊት በወ/ህግ አንቀጽ 555/1/ስር ጥፋተኛ ነዉ ብለናል፡፡ቅጣቱም በዚህ ጉዳይ የታሰረዉ ታስቦለት በሁለት አመት ከስድስት ወር /2፡6/ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል ፡፡

3ኛ/ መተከል ዞን ማረሚያ ቤት በዚህ ፍ/ቤት ተሻሽሎ በተወሰነዉ መሰረት እንዲያስፈጽም ዉሳኔ ግልባጭ ይተላለፍለት ብለናል ፡፡ ለአመልካቹም ዉሳኔ ግልባጭ በማ/ቤት በኩል ይድረሰዉ ፡፡ይጻፍ ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰ/መቁ-134549

ቀን-መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች**፡- አቶ አበበ ተፈራ አለሙ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ አመልካች ላይ ቀርበዉ የነበሩት ሁለት ክሶች ሲሆኑ የ1ኛ ክስ ይዘት፡- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(3) ላይ የተመለከተዉን በመተላለፍ የሙያ ግዴታዉን በመተላለፍ ሟች አያን ገቦቤን ወደ ተከራየበት ቤት በመዉሰድ በባለሙያ ብቻ የሚሰጠዉ ዲያዜፖም እና ትራማ ዶ የሚባሉትን አደንዛዥ መድሃኒቶችን እራሱ በመርፌ በመዉጋት ብልቷን ከሰፋት በኃላ በተወጋችዉ መድሃኒት የተነሳ የመተንፈስ ችግር ተከስቶ የሞተች በመሆኑ በፈጸመዉ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ የ2ኛ ክስ ይዘት ደግሞ በወንጀል ሕግ ቁጥር 566(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ላይ በተገለጸዉ ጊዜና ቦታ የሟች አያን ገቦቤን ብልት የሰፋ በመሆኑ የሴት ልጅ ብልት የመስፋት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ጥፋተኝነቱን በማረጋገጥ አፈጻጸሙን በዝርዝር ሲያስረዳ ሚያዚያ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ማታ ከሟች ጋር አብረን አድረናል፡፡ ቀን ሥራዬን አጠናቅቄ ለመዉጣት ስል ሟች ቀደሞ የፍቅር ጓደኛዬ ስለነበረች በመማጸን እጮኛዬ ከዉጭ ይመጣል፤ በባህሉ ብልቴን ተሰፍቶ ካላገኘኝ ለቤተሰቤም ለእኔም ዉርደት ይሆንብኛል፤ አግብቶኝ ዉጭ ሀገር የመሄድ አጋጣሚዉ ያመልጠኛል በማለቷ ለድርጊቱ የሚያስፈልጉ ቁሶችን በመያዝ ወደ ቤት ሄጃለሁ፡፡ የአክስቴ ቤት ገብተን ክፍል ተሰጥቶን አድረናል፡፡ ከዚያም ጧት ላይ ብልቷን ሰፍቼ ካጠናቀቅኩ በኃላ ሟች ሕይወቷ አልፏል፡፡ ስለሆነም ጥፋተኛ ነኝ በማለቱ የስር ፍ/ቤት አመልካች በሰጠዉ የእምነት ቃል መሠረት የወንጀል ሕግ ቁጥር 543(3) እና 566(1) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ አመልካች በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዉሳኔዉ ቅር ተሰኝቶ ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህንኑ ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ድርጊቱን ስፈጽም ሁለት የወንጀል ድርጊቶችን ለመፈጸም አቅጄ የፈጸምኩት የወንጀል ድርጊት አይደለም፡፡ ሟችን ብልቷን ስሰፋ የሕመም ስሜት እንዳይሰማት በክሱ ላይ የተገለጹትን መድሃኒቶችን ልሰጣት ችያለሁ፡፡ በወ/ሕ/ቁ 61(1) በአንድ መብት ላይ የሚደረግ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቱም በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊዉ ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸዉ በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም በማለት ደንግጓል፡፡ ስለሆነም በአንድ የወንጀል ማድረግ ቸልተኝነት የተፈጸመ በመሆኑ ድርጊቶቹም በአንድ የወንጀል ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ያቀረብኩትን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉም ሆነ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ዉሳኔዉን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ በአንድ ክስ ተጠቃልሎ ስህተቱ ይታረምልኝ፡፡

የስር ፍ/ቤት የ1ኛ ክስ ደረጃና እርከን ሲያወጣ ደረጃ 2 እርከን 25 ስር ያሳረፈዉ ማደንዘዣ መድሃኒት መስጠት እና ህክምናዉን ለመስጠት ባልተፈቀደ የግል መኖሪያ ቤት በማድረጉ ሁለት የድንጋጌዉ ፍሬ ነገሮች ተሟልተዋል በማለት ነዉ፡፡ እነዚህ ፍሬ

ነገሮች እንደሁለት የሚወሰዱ ሳይሆን በድንጋጌዉ ስር ግልጽ የሆነ ደንብን በመተላለፍ የሚለዉን ፍሬ ነገር ብቻ የሚያሟሉ በመሆናቸዉ እንደ አንድ የሚወሰዱ ናቸዉ፡፡ ስለሆነም በደረጃ 1 እርከን 21 ስር የሚያርፍ ይሆናል፡፡ 2ኛ ክስ በ1ኛ ክስ የሚጠቃለል ከመሆኑም በላይ ደረጃዉን መካከለኛ ማለቱ ተገቢ አይደለም፡፡ በስር ፍ/ቤት ካቀረብኳቸዉ 6 ማቅለያ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱን ብቻ በመተዉ አምስቱን የወሰደ ቢሆንም 4 እርከን ብቻ መቀነሱ ተገቢ ባለመሆኑ 5 እርከን ተቀንሶ ቅጣቱ ሊቀነስልኝ እና ሊገደብልኝ ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የአመልካች ሃሳብ በሰጣት የማደንዘዣ መድሃኒት ስትደነዝዝ ብልቷን መስፋት ከሆነ ድርጊቱ ሞት ያስከተለ ቢሆንም በድርጊት እና ሃሳብ አንጻር በሁለቱም የሕግ አንቀጾች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቀባበል ክርክር ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ያቀረበዉ መልስ ይዘት፡- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 60(ለ) መሠረት በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የሕግ ድንጋጌዎችን ያደረገ እንደሆነ ክሱ በተደራራቢነት መቅረብ እንዳለበት ሕጉ ይደነግጋል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ድንጋጌዎችን ወይም በአንድ ድርጊት ልዩ ልዩ ግዙፋዊ ዉጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን ያደረገ በመሆኑ በ1ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 543/3/ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል እና በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 566/1/ የሴትን ብልት መስፋት ወንጀል መከሰሱም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ መወሰኑ አግባብና ሕግን መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ የ10 ዓመት ጽኑ እስራት የተሻሻለዉን ቅጣት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊጸና ይገባል የሚል ነዉ፡፡ አመልካች አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች የሟችን ብልት ለመስፋት የማደንዘዣ መድሃኒት በመስጠት በመስፋት ላይ እያለ በመድሃኒቱ የተነሳ መተንፈስ ተስኗት ሕይወቷ ማለፉ በአመልካች በራሱ የእምነት ቃል የተረጋገጠ በመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ግራቀኙን ያከራከረዉ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በጭብጥነት

የተያዘዉ አመልካች በወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኛነት ሰዉ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ በተባለበት ሁኔታ በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 566(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ የሴት ልጅ ብልት በመስፋት ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በወ/ሕ/አንቀጽ 61(1) በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊዉ ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸዉ በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም በማለት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ የምንገዘበዉ በአንድ የወንጀል የማድረግ ሃሳብ ወይም ቸልተኝነት የተፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት በሕግ በተጠበቀ አንድ መብት ላይ በሚሆንበት ጊዜ እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር መሸፈን እስከቻሉ ድረስ ፈጻሚዉ የሚቀጣዉ ድርጊቶቹ በሚሸፈኑበት በአንድ ድንጋጌ ስር እንጂ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች አለመሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በአንድ ወንጀል በማድረግ ሃሳብ የፈጸመዉ ወይም በሟች ላይ የፈጸመዉ የሴት ብልት መስፋት የወንጀል ድርጊት ለሟች ሞት ምክንያት ሆኗል፡፡ የሟች ሕይወት ባያልፍ ኖሮ አመልካች የወ/ሕ/አንቀጽ 566(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ በሴት ብልት በመስፋት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በተቀጣ ነበር፡፡ ሆኖም ድርጊቱ በሟች አካል ላይ ስቃይና ጉዳት ከማድረስ አልፎ ለሟች ሕይወት ማለፍ ምክንያት ሆኗል፡፡ የሟች ሕይወት ማለፍ ትልቁ ወንጀል በመሆኑ በዉስጡ በሟች አካል ላይ የሚደርሰዉን ስቃይና ጉዳት አጠቃልሎ የሚይዝ በመሆኑ አመልካች የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ተላልፎ በሟች ላይ በቸልተኝነት ግድያ ፈጽሟል ተብሎ ክስ ቀርቦበት እስከተቀጣ ድረስ በትንሹ ወንጀል የወ/ሕ/አንቀጽ 566(1) የተመለከተዉን ተላልፏል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀል የሚቀጣበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡ የዚህ ማጠናከሪያዉ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የሴት ብልት መስፋቱ የጤና ችግር ወይም የአካል ጉዳት አስከትሎ እንደሆነ ቅጣቱ ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ጽኑ እስራት ሊደርስ እንደሚችል ሲደነገግ ነገር ግን የደረሰዉ ጉዳት ወይም ዉጤት ከዚህ በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ተፈጻሚ የሚደረገዉ ትልቁን ወይም ከባዱን ቅጣት የያዘዉ

መሆኑን ያስገነዝበናል እንጂ በተደራራቢ ወንጀል በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች ይቀጣል አይልም፡፡ በዚሁ መሠረት በ1ኛ ክስ የተጠቀሰዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ከ5 ዓመት እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ትልቁን ቅጣት የያዘና በሟች ላይ የተፈጸመዉን ድርጊትና ዉጤት በሙሉ የሚሸፈንበት ከመሆኑም በላይ አመልካች የተከሰሰበትና የተከራከረበት ጭምር በመሆኑ ጥፋተኛ መባል የሚገባዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ብቻ መሆን ሲገባዉ በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 566(1) የተመለከተዉን ተላልፏል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀል መቀጣቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የተላለፈዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተሻሽሎ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ብቻ ጥፋተኛ ሊባል ይገባል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ በተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ደረጃ የወጣለት በመሆኑና የወንጀል ማቋቋሚያ ዉስጥ ግልጽ ደንብና መመሪያ በመተላለፍ የተፈጸመ በመሆኑ የተሟላዉ አንድ የአንቀጹ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት ደረጃ አንድ በእስራት ቅጣት እርከን 21 በገንዘብ መቀጮ እርከን 6 ላይ ያርፋል፡፡ በስር ፍ/ቤት የገንዘብ መቀጮ ያልተወሰነና ቅሬታ ያልቀረበበት በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ የእስራት ቅጣቱን በተመለከተ በስር ፍ/ቤት የተያዙለትን አራት የቅጣት ማቅለያዎችን እንዳለ ወስደን አራት እርከን ሲቀነስለት እርከን 17 ላይ ያርፋል፡፡ እርከን 17 ፍቅድ ስልጣኑ ከ3 ዓመት ከ3 ወር እስከ 3 ዓመት ከ11 ወር የሚያስቀጣ በመሆኑ አመልካች ለፈጸመዉ አድራጎት ይመጥናል ባልነዉ በ3 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት ሊቀጣ ይገባል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካች ላይ የተሰጠዉ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10692 ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ 126459 ጥቅምት 23

ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. በስር ፍ/ቤት አመልካች የወ/ሕ/ አንቀጽ 543(3) እና 566(1) የተመለከተዉን ተላልፏል ተብሎ የተሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ እና የ10 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ተሻሽሎ አመልካች የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኛ ነዉ ተብሎ በ3 (ሦስት) ዓመት ከ6(ስድስት) ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ዉሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይተላለፍ፡፡ እንዲሁም ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

የሰበር መ/ቁ/141677

ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች ፡ያዕቆብ አብዱ -

ተጠሪ ፡የደቡብ ክልል አቃቤ ህግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል ፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ አመልካች የወ/ህግ አንቀጽ 27/1/ እና 540 ተላልፎ ተራ የሆነ ሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በ12 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ ቤት የሰጠዉ ፍርድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ችሎት በማጽናታቸዉ ዉሳኔዉ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል እንዲታረም ስላመለከተ ነዉ ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በወ/ህግ 541 ተከሶ እያለ በወ/ህግ 540 ጥፋተኛ መባሉና እና ድርጊቱ በሙከራ ቀርቶ እያለ በወ/ህጉ አንቀጽ 27/3/ መሰረት ቅጣት ያልቀለለበት አግባብ ለመመርመር እንዲቻል ዓቃቤ ህግ መልስ እንዲሰጥ ታዟል፡፡ የፍ/ቤቱ መጥሪያ ለዓቃቤ ህግ በፖስታ ቤት በኩል የተላከለት ቢሆንም ቀርቦ መልስ አልሰጠም ፡፡ በዚሁ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎ መዝገቡ ተመርምሯል ፡፡

በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉ አንደኛ ጭብጥ አመልካች በወ/ህግ አንቀጽ 541 ተከሶ እያለ በአንቀጽ 540 ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲሆን በእኛ በኩል መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነዉ ዐቃቤ ህግ መጀመሪያ ክስ ያቀረበዉ በአንቀጽ 541 ቢሆንም በክርክር ሂደት ክሱን በማሻሻል በወ/ህግ አንቀጽ 27/1/ 540 ስር የለወጠ ስለመሆኑ ስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ይዘት ያስረዳል ፡፡ፍ/ቤቱም ተሻሽሎ በቀረበዉ አንቀጽ መሰረት የጥፋተኝነት ዉሳኔ ሰጥቷል ፡፡ ስለሆነም አንቀጹን ወደ 540 የለወጠዉ ፍርድ ቤቱ ሳይሆን ከሳሽ ዓቃቤ ህግ ስለሆነ ሰበር አጣሪ ችሎት የስር ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ከአንቀጽ 541 ወደ 540 ማለትም ከቀላል ወደ ከባዱ አንቀጽ የለወጠ መስሎት በዚህ ነጥብ ላይ ጭብጥ መያዙ ፍርዱን ባለማገናዘብ እንደሆነ ማየት ችለናል ፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ክሱ ከተሻሻለ በኋላ በከበደዉ አንቀጽ ስር የመከራከር መብቱ ባልተጠበቀበት ሁኔታ የጥፋተኝነት ፍርድ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በማለት ነዉ ፡፡ ስለዚህም ክስ ከተሻሻለ በኋላ ፍ/ቤቱ የተከተለዉ የክርክር አመራር ስርዓት አግባብነት ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ክስ ሊሻሻል የሚችልባቸዉ ምክንያቶች በወ/መ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ118 እና 119 ስር የተመለከቱ ሲሆን የክሱ መሻሻል የሚያስከትለዉ ዉጤት በዚሁ ድንጋጌ አንቀጽ 120 እና 121 ላይ ተመልክቷል ፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ ክስ ተሻሽሎ ከቀረበ በኋላ ለተከሳሹ ተነቦለት የክሱ መሰማት የሚቀጥል መሆኑን እና ምስክሮችም በዚህ አግባብ እንደገና እንዲሰሙ መደረግ የሚችልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ነዉ ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ዓቃቤ ህግ የወ/ህግ አንቀጽ 27/1/ እና 541 ጠቅሶ ክስ አቅርቦ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቃል ከተሰማ በኃላ ዓቃቤ ህግ ክሱን በማሻሻል ወደ አንቀጽ 27/1/ እና 540 ለዉጦ ያቀረበ ሲሆን ጉዳዩን የያዘዉ ፍ/ቤት የተከሳሽን የመሰማት መብት ሳይጠብቅ ቀደም ሲል በተሰማዉ ክርክርና የዓቃቤ ህግ ማስረጃ መሰረት ተከሳሽ /አመልካች / ተሻሽሎ በቀረበበት ክስ ድንጋጌ እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል ፡፡አመልካች ቀደም ሲል የተከሰሰዉ በቀላል ግድያ ሙከራ ወንጀል ሲሆን ተሻሽሎ የቀረበዉ ክስ ደግሞ ተራ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል በመሆኑ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ የሚጣልበት ቅጣት ከባድ ከመሆኑ አንጻር የተከሳሹ መሰረታዊ መብት ላይ የሚኖረዉ አሉታዊ ተጽእኖ ጋር ተመዛዝኖ በስነስርዓት ህጉ የተጠበቀለት የመሰማት መብት በጥብቅ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ መረዳት አዳጋች አይደለም፡፡ ከዚህ

መሰረታዊ መብት አንጻር  የፍርድ ቤቱ የክርክር አመራር በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/119/2/ ፤120 እና 121 ድንጋጌዎች በአግባቡ ያላገናዘበ እንደሆነ መረዳት ተችሏል ። ስለሆነም ክሱ ተሻሽሎ ለዚያዉም ወደ ከባድ አንቀጽ ተለዉጦ ቀርቦ እያለ ክሱ እንደገና እንዲሰማ መደረግ እንዳለበት የተደነገገዉን ስርዓት ሳይጠብቅ  ክርክሩን በመምራት የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል ። የበላይ ፍ/ቤቶች ይህንኑ ተገንዝበዉ ሳያርሙ ማጽናታቸዉ ግልጽ ግድፈት ስለሆነ ለታረም ይገባል ብለናል።

ሁለተኛዉ ጭብጥ ድርጊቱ በሙከራ ደረጃ የቀረ ከመሆኑ አኳያ በወ/ህጉ አንቀጽ 27/3/ መሰረት ቅጣት እንዲቀልለት አለመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነዉ። ነገር ግን ክርክሩ በአንደኛዉ ጭብጥ እልባት ያገኘ ስለሆነ መመርመር አስፈላጊ ባለመሆኑ ታልፏል በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል ።

<u>**ዉ ሳ ኔ**</u>

1ኛ /የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 5224 በ16/02/09 ዓ.ም አመልካች የወ/ህግ እንቀጽ 27/1/ እና 540  ስር የተመለከተዉን ተላልፎ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል በማለት በ12 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/04047 የሰጠዉ ትእዛዝ እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/04781 የሰጠዉ ትእዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ 195/2/ለ/2 / መሰረት ተሽሯል ።

2ኛ/ዓቃቤ ህግ አሻሽሎ ባቀረበዉ ክስ ላይ የአመልካችን እምነት ክህደት ቃል ከመቀበል ጀምሮ በወ/መ/ ስ/ስ ህግ አንቀጽ 119/2/ ፤120 እና 121 በተደነገገዉ አግባብ ክርክሩን በማየት ተገቢዉን ፍርድ እንዲሰጥ ብለን መዝገቡን በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/ 195/2/ሀ መሰረት ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል ።ይጻፍ ።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 127313

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የአ/ብ/ክ/መ/ፍ/ቢሮ ዓ/ህግ- አብርሃም በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አንዱአለም ገናነው መላኩ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የጉዳዩን አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች በስር ደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ መነሻ ያደረገ ሲሆን የቀረበው ክስ ይዘት ተከሳሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 555(1(ለ)) በመተላለፍ የሰው አካል ላይ ጉዳት ማደረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ክስ ቀርቦበታል፡፡ የሥር ተከሳሽ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ የሰዉ ምስክሮች በመስማትና በመመርመር ተከሳሽ ስለተመሰከረባቸው እንዲከላከሉ ብይን በሰጠዉ መሰረት ተከሳሽ መከላከያ ምስክሮች አስቀርቦ እንዲያሰማ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ የተከሳሽ መከላከያ ምስክር ለመስማት ተደጋጋሚ ቀጠሮ የተሰጠ ሲሆን ተከሳሽ መከላከያ ምስክሩ

በሚሰማበት ቀን ቀጠሮ መከላከያ ምስክሩን ይዞ ባለመቅረቡ አመልካች ተከሳሽ መከላከያ የማቅረብ መብቱ ታልፎ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይለት ለፍርድ ቤት አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 161 መሰረት በሌለበት ጉዳዩ ሊታይ የሚቻል አይደለም በማለት ፖሊስ ተከሳሽ ካለበት ቦታ አፈላልጎ እንዲያቀርብ ትእዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው አቅርቦ አቤቱታውን ባለመቀበል ሰርዘውታል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን  የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው እንዲያቀርቡ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበው ቅሬታ የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በመሆን የቀረበበት ክስ የወ/ህ/ቁጥር 555(1(ለ)) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ሲሆን ተጠሪ ችሎት ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲሰጥ ክዶ የተከራከረ መሆኑ የከሳሽ ዓ/ህግ ምስክሮች ሲሰሙ ችሎት ቀርቦ የተከራከረ እና እንዲከላከል ተነግሮት በተደጋጋሚ ቀጠሮ መከላከያ ማስረጃውን ይዞ ያልቀረበ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ፡፡አሁን ለቀረበው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ እንዲከላከል ትእዛዝ ተሰጥቶና አውቆ መከላከያ ምስክሩን ይዞ ባለመቅረቡ የመከላከል መብቱ ታልፎ ውሳኔ እንዲሰጥ የቀረበው የአመልካች አቤቱታ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ አይደለም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የወንጀል ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ወንጀሉን ያልፈፀመ መሆኑን በመግለፅ የተከራከረ መሆኑ፣ተጠሪ ባለበት አመልካች ማስረጃዎቹን ያሰማ መሆኑንና ተጠሪም የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት እንዲከላከል ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሲሰጥ በችሎት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ይህም ተጠሪ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የአመልካችን ምስክሮች ቃል የመመርመርና የመጠየቅ መብቱ ሙሉ በሙሉ በተከበረበት ሁኔታ ተጠሪ በህገ መንግስት የተጠበቀለት የመከላከል መብት ፍርድ ቤት ቀርቦ ማሰማትና መጠቀም ሲገባው በራሱ ፍቃድ የተወው መሆኑ ከክርክሩ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

በመርህ ደረጃ የወንጀል የክርክር ሂደት ተከሳሾች ባሉበት እንደሚደረግ በልዩ ሁኔታ ደግሞ የፈጸሙት ወንጀል ቀርበው መከራከር የማይፈልጉና ከፍትህ ስርዓቱ የሸሹ ግለሰቦች በፍትህ ስርዓቱ መጠየቅ ያለባቸው በመሆኑ በሌሉበት ነገሩ ሊሰማ እንደሚችል ከወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 161(1) እና (2(ሀ) ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ንባብ የምንረዳው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም አንድን ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ለማየት እንዲችል ተከሳሹ በቀጠሮ ቀን ያለ በቂ ምክንያት መቅረቡ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑ የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ ለመስማት ትዕዛዝ ከሰጠ ጥሪው ተደራሽ በሆነ አግባብ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡ በወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162 እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ የሚያስተላለፈው ጥሪ ተከሳሹ ስለተጠረጠረበት ጉዳይ ዝርዝር መግለጫ የያዘ እና ጥሪውም በጋዜጣ እንዲወጣ መታዘዝ እንዳለበት ከድንጋጌው ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ፍ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘም የመጥሪያ ማስታወቂያው በሌላ መንገድ ማስተላለፍ እንደሚችል የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ያሳያል፡፡በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ክሱ በሚሰማበትና የከሳሽ ዓ/ህግ ምስክሮች በሚሰሙበት ጊዜ ችሎት ቀርቦ የተከራከረ በመሆኑ እና በተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ አውቆ መከላከያ ማስረጃ ለመስማት ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ በያዘበት ቀን ሳይገኝ መቅረቱ ጉዳዩ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (4) በወንጀል የተከሰሰው የዓቃቤ ህግ ማስረጃ ሲሰማ በመገኘት የዓቃቤ ህግን ምስክሮች የመጠየቅና የመመርመር መብቱን በአግባቡ ከተጠቀመና የመከላከያ ምስክሮችንና ማስረጃ እንዲያቀርብ የተሰጠውን መብት በራሱ ፍላጎት ካልተጠቀመ እና የመከላከል መብቱን ካልተጠቀመ ዳኞች የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን ፍርድ ከመስጠት የሚገድባቸው ባለመሆኑ በህጉ ለተከሳሽ ከተሰጠው የመደመጥ መብት አንፃር ተከሳሹ መብቱ በራሱ ፍላጎት ባለመጠቀሙ ጉዳዩ ተከሳሹ በሌለበት እንደሚታይ ጉዳይ ሊታይ የሚችል ባለመሆኑ ፍርድ ቤቶች የቀረበውን ጉዳይ መርምረውና መዝነው ውሳኔ

ከመስጠት የሚገድባቸው ጉዳይ አይሆንም፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ (የስር ተከሳሽ) መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ እንዲከላከል ተፈቅዶለት ቀጠሮውን አክብሮ ባልቀረበበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳይ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 161 ጋር በማያያዝ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ አይደለም በማለት ውሳኔ መስጠታቸው፣ አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት በ(default procedure) ታየ የሚባለው መቼ ነው? ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክስ ስለሚታይበት ሁኔታ የሚደነግጉት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነስርዓት ሕግ ቁጥር 161 እስከ 164 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት ትርጉምና ተፈፃሚነትና ውጤት እንደዚሁም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በሌለበት ታይቶ ከሚሰጥ ፍርድ ለእንዴት አይነት ጉዳይ ነው የሚለውን የህገመንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 4 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጡት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ በመሆኑ የክርክሩ ሂደት በአግባቡ የተመራና የተሟላ ሁኖ አልተገኘም፡፡ የክርክሩ ሂደት በአግባቡ ያለመመራትና የተሟላ ፍሬ ነገር እንዲኖር ያለማድረግ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የማይፈቅደው በመሆኑ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብ/ክ/መንግስት የደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁጥር 01362 ታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ./ቁጥር 0215307 ታህሳስ 29 ቀን 2008 ዓ/ም ያፀናው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 54349 መጋቢት 01 ቀን 2008 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 195(2)(ለ)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የክርክሩ ሙሉ ሂደት ተከታትሎ ለተከሰሰበት ወንጀል እንዲከላከል ትእዛዝ መሰጠቱን አውቆ የጠፋ ስለሆነ ይህ ጉዳይ በሌለበት ሊባል የሚችል ስላልሆነ ፍርድ

ቤቱ ተጠሪ የመከላከል መብቱን ለመጠቀም እንዳልፈለገ ቆጥሮ ተገቢውን እንዲወስን ለክልሉ ደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት ተመልሶለታል፡፡ይፃፍ፡፡

3. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

የሰ/መ/ቁ. 137672

ሕዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ**

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

**አመልካች፡-** ብርሃነ ሀለፎም ገ/መድህን-ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ሙናቸው

**ተጠሪ፡-** የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቢ ህግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 164774 በቀን 18/02/2009 ዓ.ም ፍርድ እና በቀን 01/03/2009 ዓ.ም የቅጣት ውሳኔ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 124288 ጥር 10 ቀን 2009 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ገንዘብ ማከማቸት የሙስና ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክሱ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 419/1//ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከመስከረም 1982 ጀምሮ በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ተቀጥሮ ሲያገለግል በፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ከህዳር 1/1996-ሰኔ 30/1997 በብር 595 ደመወዝ መረጃ አገልግሎት ውስጥ በክለርክነት፣ ከሰኔ 1/1999-ነሐሴ 30/1999 በብር 1145 ደመወዝ በተ.እ.ታ. መምሪያ የግብር ከፋዮች

ምዝገባ ውስጥ ሱፐርቫይዘርነት፣ ከሰኔ 1/2006-ሐምሌ 2/2006 በብር 7284 ደመወዝ በኢ/ገ/ጉ/ባለስልጣን የአጠቃላይ ቅሬታ አስተናጋጅ ቡድን አስተባባሪ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት በመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ወይም ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ህጋዊ ገቢ ጋር በማይመጣጠን ሁኔታ በባለቤቱ ወ/ሮ አይናለም ጌታቸው ስም የተመዘገበ በአ.አ ኮልፌ ቀ/ክ/ከ ቀበሌ 02/03 የቤት ቁጥር 2244 የካቲት 26/2000 ዓ.ም በብር 275000 የተገዙ፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ቆሬ ኮንደሚኒየም የቤት ቁጥር ቢ51/54003 ሐምሌ 9/2004 ዓ.ም በብር 125000 የተገዛ እና ከ10/03/2005 ጀምሮ የካፍቴሪያ አገልግሎት የሚሰጥ በባለቤቱ ስም የተመዘገበ ንግድ ፈቃድ፣ በአመልካች ስም የዳሽን ባንክ ሂሳብ ቁጥር 5001503553001 እስከ ሐምሌ 13 ቀን 2004 የነበረ ብር 65733.19፣ በባለቤቱ ወ/ሮ አይናለም ጌታቸው ዳሽን ባንክ ሂሳብ ቁጥር 5001503552001 እስከ ሐምሌ 13 ቀን 2004 የነበረ ብር 63294.28 ያለአግባብ ያከማቹ በመሆኑ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ማከማቸት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች የቀረበበትን ክስ በመካዱ በተጠሪ የቀረውን የሰነድ ማስረጃዎች ፍርድ ቤቱ ከመረመረ በኋላ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በሰጠው ብይን በአመልካች 6 የሰው የመከላከያና የጽሁፍ ማስረጃዎች የቀረቡ መሆኑን ገልጾ ፍርድ ቤቱ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በአመልካች እና በባለቤቱ ስም ተመዝግበው የሚገኙት ንብረት እና ገንዘብ የአመልካች ገቢ ተብሎ ከተገለፁት በላይ መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን፤ የአመልካች አንደኛ ምስክር በብድር ለአመልካች ሁለት ጊዜ ሠጥቻለው ያሉትን በተመለከተ የመጀመሪያውን በ1999 ተሰጠ የተባለውን 84000 ውድቅ በማድረግ ሁለተኛው በ2004 ዓ.ም የተሰጠውን ብር 50000 የብድር ውሉ ያረጋግጣል በማለት ተቀብሎታል፡ ሁለት የአመልካች ወንድሞችና መከላከያ ምስክሮች የአባታቸው የውርስ ድርሻ ተሸጦ ብር 80000 ለአመልካች ቤት መግዢያ የሰጡት መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፡ በሌላ በኩል 4ኛ 5ኛ እና 6ኛ ምስክር በተመለከተም አመልካች በግል ያስተምር የነበረ መሆኑን ገቢው እንደማይታወቅ፤ ዕቁብ ብር 22000 እና 11000 የደረሰው ስለመሆኑ የገለፁ መሆኑን ገልጾ አመልካች የመንግስት ሥራ ከጀመረበት 1982-1999 የነበረው አጠቃላይ የደመወዝ ገቢ ብር 66162 የነበረና በአመልካች ባለቤት ስም ቤት የገዛው በብር 275000 በመሆኑ ይህንን ለመግዛት የሚያስችል ገቢ የለውም

በልዩነት የተገኘው ብር 208838፣ አመልካች ጥቅምት 3/2003 ድረስ ያለው ጥቅል ገቢ ብር 109260 ተሽከርካሪ ከገዛበት በልዩነት የተገኘ ብር 62740 እና ሐምሌ 9/2004 የተገዛውን ቤት ጋር ገቢውና በብድር የተገኘው ሲነፃፀር ንብረቱን ለማፍራት የሚችልበት ነው፣ በባንክ ያለው ገንዘብ በወቅቱ ከነበረው ገቢ ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ብር 51063.47 አመልካች አላስረዳም በአጠቃላይ አመልካች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ ተገኝቷል ከተባለው ውስጥ ብር 322641.47 የሆነውን ብቻ ምንጩን ህጋዊ አመጣጡን ያላስረዳ ስለሆነ በቀረበበት ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 419/1//ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው ብሎ በአንድ ዓመት ከሁለት ወር እስራት እና በብር 5000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ እና ብር 322641.47 ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡት ይግባኝ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳይቀበል የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቶታል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የኮንደሚኒየም ቤት የተገዛበትን ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተከፈለው ከቤትና ከባንክ ገንዘብ ሲሆን እንደተለያዩ ንብረት አድርጐ ወስዷል፣ የቀረበውን ክስ በመከላከያ ማስረጃዬ አስተባብያለሁ፣ የመከላከያ ምስክር የሰጠኝ ብድር አንዱን ተቀብሎ ሌላውን ውድቅ ያደረገበት ምክንያት ተገቢ አይደለም፣ የአባቴን የውርስ ድርሻ ወንድሞቼ የሰጡኝ ስለመሆኑ ማረጋገጣቸው መተሳሰብና መፋቀር እንጂ ሀብትን አያመለክትም ፤አመልካች በግል የማስተምር እና የምነግድ መሆኑ ባለቤቴም ከመጋባታችን በፊት ጀምሮ ነጋዴ መሆንዋ መጠኑ ባለመታወቁ መታለፍ የለባትም፣ የደረሰኝ ዕቁብ አልተያዘም፣ ለቤቱ መግዢያ ይኸው መዋሉን ገልጩ አልተያዘም የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ብር 84000 ሳይዝ ብር 50000 ብቻ የያዘበት እና 2ኛ ምስክር የአመልካች ወንድምን እህት የሰጡትን ፍ/ቤቱ ውድቅ ያደረገበትን አግባብ ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት በሰጠው መልሱ የአመልካች አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሳይሆን የማስረጃ ምዘናን የሚጠይቅ ነው፡ ተቀባይነት የለውም፣ የገንዘብ ብድሩን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ተገቢውን ማጣራት አድርጐ የወሰነው ነው፡፡ የመከላከል ምስሮችም የተጠና ሊሆን የሚችል እንጂ አልተከላከለውም፣ ሁለት ጊዜ የታሰበ የለም፣ የሚሉ ዝርዝር መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለዚህ ሰበር ምክንያት ከሆነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለዚህ ሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች የመንግስት ሠራተኛ በመሆን ያገኘውን ገቢ መሠረት በማድረግ አፍርቶታል የተባለውን ገንዘብ እና ንብረት የብር 322641.47 ልዩነት ያለው በመሆኑ ተመጣጣኝ አይደለም ምንጩንም ማስረዳት አልቻለም በማለት በተሰጠው ውሳኔ ላይ በማስረጃ ምዘና ወቅት በብድር ያገኘው ብር 84000 እና የውርስ ንብረት ከወንድሞቹ የተላለፈለትን ብር 80000 ውድቅ የተረገበትን አግባብ ለመመርመር ያስቀርባል መባሉን ነው፡፡

ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 ንዑስ አንቀጽ 1//ሀ/ እና /ለ/ ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻለው ዐቃቤ ሕግ የመንግስት ሠራተኛ የሆነው ወይም የነበረው ሰው ያገኝ የነበረውና የሚያገኘው ገቢ ምን ያህል እንደሆነና የመንግስት ሠራተኛው በራሱ ስምም ሆነ በቤተሰቡ ስም ከሕጋዊ ገቢው ውጪ ይዞት የሚገኘውን የገንዘብና የንብረት ግምት የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግልፅ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የመንግስት ሠራተኛ የነበረው ሰው ከነበረውና ከሚያገኘው ገቢ በላይ ይዞት የተገኘው ገንዘብ ወይም ሀብት ትክክለኛው ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ ፣ "... የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት እንደገባ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር" ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ በመገኘቱ ጥፋተኛ ተብለው በሕጉ የተደነገገው ቅጣት ሊጣልባቸው እንደሚችል በመግለፅ ይደነግጋሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳው ዐቃቤ ሕግ በግልፅ ከሚታወቀው ሕጋዊ ገቢ በላይ ነው በማለት በክሱ የተገለፀውንና በማስረጃ ያረጋገጠውን ሀብት ትክክለኛ ምንጭ የማስረዳት ግዴታ / Burden of Proof/ በተከሳሾች ላይ የሚወድቅ መሆኑን ነው፡፡ የተከሳሾች የማስረዳት ግዴታም ዐቃቤ ሕግ በክሱ ከገለፀውና በማስረጃ ካረጋገጠው ውጭ ተከሳሽ ሌላ ገቢ የሚያገኝበት ስራ ወይም የገቢ ምንጭ ያለው መሆኑን ብቻ ለፍርድ ቤቱ በማሳየት የሚወሰን ሳይሆን፣ በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ከተረጋገጠው ገቢ ውጭ በእጁ እንደተገኘ የተረጋገጠው ገንዘብና ሀብት ትክክለኛ ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት

ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ ድንገጌ አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻር አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆነው ካገኙት ህጋዊ ገቢ /ደመወዝ/ በተጨማሪ ያስቀርባል ሲባል የተያዙትን ከመከላከያ ምስክራቸው በብድር አግኝቼዋለሁ ያሉትን ብር 84000 እና እህት እና ወንድማቸው የአባታቸውን ድርሻ ብር 80000 ሰጥተውኛል ያሉት የስር ፍርድ ቤት ቢቀበላቸው በልዩነት ከገቢያቸው በላይ ለሆነው የገንዘቡን ምንጭ አላስረዱም ብሎ ጥፋተኛ ካለበት ብር 322641.47 አንጻር የሚያስተባብል አይደለም፡፡ በዋናነት ግን የስር ፍርድ እነዚህን በብድርና በስጦታ ተገኙ የተባሉትን የገንንዘብ ምንጮች ውድቅ ያደረገው በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ መሆኑ ሲሆን ይህ በፍሬ ጉዳይ ላይ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን በመመዘን በደረሰበት ድምዳሜ ላይ የቀረበው አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ውሳኔ

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 164774 በቀን 18/02/2009 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በ01/03/2009 የቅጣት ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 124288 በቀን 10/05/2009 ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

የሰበር መዝገብ ቁጥር 122595

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የገ/ጉ/ባለስልጣን ዓ/ህግ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ አቶ ፋሲል ጥላሁን

2ኛ አቶ ካሊድ ሳቢት

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የኮንትሮባንድ ወንጀልን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 10870 በ30/3/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ 1ኛ ና 2ኛ ተከሳሽ ሆነው ሲከራከሩ የነበር ሲሆን፣ከሳሽ ባቀረበዉ 1ኛ ክስ፡-በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን በመተላለፍ ተከሳሾች እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት ምንም ዓይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና በሞዴል 270 በቁጥር 876593 ተመዝግቦ ወደ መንግስት መጋዘን የገባው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-020775 ሐረር ሚኒባስ የሆነ ተሽከርካሪ ቀረጥ ተከፍሎበት የገባ መኪና ለማስመሰል የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና ሞተር ቁጥሩ 5L21455255 ከሌላ መኪና ተቆርጦ የተለጠፈውን በቀን 10/08/05 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 አከባቢ በፌዴራል ፖሊስ

አካላት ክትትል በሃረር ከተማ ቀበሌ 14 በመያዙ 1ኛ ተከሳሽ የህገወጥ መኪና ባለቤት እና 2ኛ ተከሳሽ ለህገወጥ መኪናው የ1ኛ ተከሳሽ ወኪል ሆነው ህገወጥ እቃ ይዘው በመገኘታቸው ተከሷል፡፡ 2ኛ ክስ በ2ኛ ና 3ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ሲሆን የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ በመተላለፍ ተከሳሾች እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው የካቲት 30 ቀን 2005 ዓ/ም ምንም አይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና ከላይ በ1ኛ ክስ ላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ በ2ኛ ተከሳሽ ወኪልነት ለ3ኛ ተከሳሽ የሸጠለት በመሆኑ ተከሳሾች የኮንትሮባንድ እቃ የተገበያዩ በመሆናቸው በኮንትሮባንድ ወንጀል ተከሷል፣ 3ኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ የተመለከተ ሲሆን የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ ተከሳሽ በ1ኛ ክስ ለተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ ካስገባ በኋላ ተገቢዉን ቀረጥና ታክስ ለመንግስት እንዳይከፈል ለማድረግ በማሰብ በፋጢማ መሃመድ ያሲን ስም ተመዝግቦ በህጋዊ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገባውን ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 በመጠቀም በራሱ ስም ሊብሬ አውጥቶ ሲገለገልበት በቀን 10/08/05 ዓ/ም በቁጥጥር ስር በመዋሉ ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ቀርበው ክሱ ደርሷቸው ተቃውሞ እንደሌላቸው ገልፀው፣ በሰጡት የእምነት ክህደት ቃል ደርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር ተከሳሾች በቀረበባቸው ሁሉም ክሶች እንዲከላከሉ ባዘዘዉ መሰረት ተከሳሾች የፅሁፍ ማስረጃና የሰዉ መከላከያ ምስክሮችንም አቅርበው አሰምቷል፡፡ በመቀጠል ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች እና የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃዎችን በሕጉ አግባብ ከመዘነ በኋለ በሰጠዉ ዉሳኔ በክስ የተመለከተዉ ተሽከርካሪ በሕገ ወጥ መንገድ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈጸምበት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ከዉጭ አገር ወደ አገር ዉስጥ መግባቱ እና ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት እንደተከፈለ በማስመሰል ሰነድ የተዘጋጀ መሆኑም አልተረጋገጠም ተከሳሾች በሚገባ ተከላክለዋል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ18/05/2008 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ተጠሪዎች በቀረበባቸው ክስ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና የሞተር ቁጥር 5L21455255 የሆነ ተሽከርካሪ እነዚህ ቁጥሮች ለተሽከርካሪው በፋብሪካ የተሰጡት ቁጥሮች ሳይሆኑ በህጋዊ መንገድ በዲክለራሲዮን ቁጥር C-1828/2010 በፋጡማ መሃመድ ያሲን ስም ወደ ሃገር ውስጥ የገባው ህጋዊ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 ሲሆን ለሌላ መኪና ተቆርጦ የተመታ መሆኑ ለተያዘው መኪና እንደ ሻንሲ ቁጥር አገልግሏል ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ተሽከርካሪዎች ሻንሲና ሞተር ቁጥር ወደ ሃሰት ተለውጧል የሰሌዳ ቁጥር ከኮድ 3-17811 ኦሮ ወደ ሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-02075 ሐረ. ሲቀየር አካላዊ ሻንሲ ቁጥርና ሞተር ቁጥሩ ከሰነዱ ጋር አልተመሳከረም ይህ ስለመሆኑ በቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የሥር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104 /3፣ ሀ/ለ/ መኪናዉ እንዲወረስ ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸው ይህንን ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪዎች ቀርበው በፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው አመልካች የወንጀሉን ድርጊት ተጠሪዎች ፈጽመዋል በሚል ያቀረበው ክስ ዋናው ድርጊት 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው ውክልናን መሠረት በማድረግ እያወቁ ወይም ማወቅ እየተገባቸው በክሱ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በመተባበር የፈፀሙ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዛፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2/ በግልጽ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ ማሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ

ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀጽ 24፣57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በቀረበው ክስ ላይ የተገለፀው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ በህጋዊ መንገድ በዲክለራሲዮን ቁጥር C-1828/2010 በፋጡማ መሃመድ ያሲን ስም ወደ ሃገር ውስጥ የገባው ህጋዊ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 ሲሆን ይህ አሁን በቁጥጥር ስር ከዋለው መኪና ተቆርጦ የተመታ ነው በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የባለሞያ ማስረጃ እንደተገለፀው በሰሌዳ ቁጥር 3-02075 ሐረ የሆነ ሚኒባስ ተሽከርካሪ ላይ የተገኘው መረጃ በተሽከርካሪው ጋቢና በር ስር (በተሳፋሪ በኩል ) የተገኘው የቻንሲ ቁጥር ሆን ተብሎ ለማጭበርበር ተቆርጦ በሌላ የተቀየረ መሆኑ በግልፅ ማረጋገጡ ተለጥፎ የተገኘው የቻንሲ ቁጥር LH172-1039214 መሆኑ እንዲሁም በተሽከርካሪው ሞተር ላይ የተገኘው የሞተር ቁጥር መጀመሪያ በነበረው ቁጥር ላይ በድጋሚ የተመታ መሆኑ በሞተር ላይ የተገኘው ቁጥር 5L-21455255 ስለ ተሽከርካሪው መረጃ የሚሰጥ ፕሌት (ስለ መኪናው ቀለም ፤ሞዴል፣የምርት ዘመን ፣የሞተር ጉልበት ) በሌላ መቀየሩን በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የመኪና ሞተር እና የሻንሺ ቁጥር አስመስሎ የተመታ እና መረጃ የሚሰጥ ፕሌትም የተቀየረ ሲሆን አሁን በአካል የተመረመረው ተሽከርካሪ ግን ከላይ የተገለፀው ከሌላ መኪና የተመታ መሆኑ በባለሙያ በመመርመር ተረጋግጧል የሚል በመሆኑ ተጠቃሹ አካል ከጻፋቸው ደብዳቤዎች ይዘት የመኪናው ሞተር እና ሻንሲ ቁጥር ተመሳስሎ የተሰራ እና የተመታ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለሆነም እነዚህ የሻንሲ ቁጥር መለወጥ እና የሞተር ቁጥር መምታት፤ አድራጎቶች ተጠሪዎች ሆነ ብለው ወይም ማወቅ እየተገባቸው ድርጊቱን የፈጸሙትና ውጤቱንም የራሳቸው ያደረጉ መሆኑንን የሚያስገነዝብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለተሽከርካሪዎች መለያ፤መመርመሪያ እና መመዝገቢያ የወጣው አዋጅ ቁጥር 681/2002 ቁጥር 7/1 (ለ) እና (ሐ) የተሽከርካሪን ዝርዝር መግለጫ ለመመዝገብ እና የባለንብረት መታወቂያ ለመስጠት የሞተር ቁጥሩ እና የሻንሲ ቁጥር ሊመዘገብ እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ የአዋጁ ቁጥር 42/5 እና 48/2/ሐ ማንኛውም ሰው አግባብነት ያለው አካል ሳይፈቅድ የተሽከርካሪውን የሞተር ቁጥር የሻንሲ ቁጥር እና መሰል መረጃዎች መቀየር እንደማይቻል እና በወንጀል እንደሚያስጠይቅ ይደነግጋል፡፡

በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የተሽከርካሪው ሞተር ቁጥር እና ሻንሲ ቁጥር የተመታ እና ተመሣሥሎ የተሰራ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬነገር ከመሆኑም በላይ ተጠሪ የመኪናው ሞተር ቁጥር እና ሻንሲ ቁጥር የተመታው አግባብነት ያለው አካል ፈቅዶላቸው መሆኑን መኪናው በጨረታ ሲገዙትም አሁን ባለበት ሁኔታ የሚመለከተው አካል አውቆት ስለመሆኑ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ፈጽመዋቸዋል በማለት በማስረጃ ያረጋገጣቸው ፍሬ ነገሮች ሁለቱም ተጠሪዎች የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና  የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን በመተላለፍ  እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት  ምንም ዓይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና በሞዴል 270 በቁጥር 876593 ተመዝግቦ ወደ መንግስት መጋዘን የገባው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-020775 ሐረር ሚኒባስ የሆነ ተሽከርካሪ ቀረጥ ተከፍሎበት የገባ መኪና ለማስመሰል የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና ሞተር ቁጥሩ 5L21455255 ከሌላ መኪና ተቆርጦ የተለጠፈውን በቀን 10/08/05 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 አካባቢ ሲገለገሉ በፌዴራል ፖሊስ አካላት ክትትል በሃረር ከተማ ቀበሌ 14 በመያዙ 1ኛ ተከሳሽ የህገወጥ መኪና ባለቤት እና 2ኛ ተከሳሽ ለህገወጥ መኪናው የ1ኛ ተከሳሽ ወኪል ሆነው ህገወጥ እቃ ይዘው በመገኘታቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን የኮንትሮባንድ ወንጀል የፈፀሙ መሆኑን የተረጋገጠበት በመሆኑ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡ ሁለተኛው ክስም በተመለከተ ፣ 2ኛ ተጠሪ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ በመተላለፍ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ምንም አይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና ከላይ በ1ኛ ክስ ላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ ሚያዝያ ወር  2005 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-17811  ተሽከርካሪ እንዲያስተዳድር የተሰጠውን ውክልና መሰረት በማድረግ ለ3ኛ ተከሳሽ የሸጠለት በመሆኑ ተከሳሾች የኮንትሮባንድ እቃ የተገበያዩ  መሆኑ በኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጧል ፣  እንዲሁም  1ኛ ተጠሪ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ ተከሳሽ በ1ኛ ክስ ለተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ ካስገባ በኋላ ተገቢዉን ቀረጥና ታክስ ለመንግስት እንዳይከፈል ለማድረግ በማሰብ በፋጢማ መሃመድ ያሲን ስም ተመዝግቦ በህጋዊ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገባውን ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214

በመጠቀም በራሱ ስም ሊብሬ አውጥቶ ሲገለገልበት በቀን 10/08/05 ዓ/ም በቁጥጥር ስር በመዋሉ በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በመገንዘብ መወሰን ሲገባቸው ይህንን ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ፡፡ሌላው መታየት ያለበት በዐ/ሕግ ክስ የተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 104/3/ /ሀ/ በሚደነግገዉ አግባብ መኪናዉ በመንግስት ከመወረስ ሊድን የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ የተያዘ መኪና ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ መኪናዉ ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰዉ ሊመለስ የሚችለዉ መኪናዉ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ አጥጋቢ ማስረጃ ያልቀረበ እንደሆነ ነዉ፡፡ አሁን አከራካሪ የሆነው መኪና የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ በበቂና አጥጋቢ ማስረጃ እስከተረጋገጠ ድረስ መኪናዉ እንዲወረስ ከሚደረግ በስተቀር ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰዉ የሚመለስበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ለክርክር የሆነዉ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት መሆኑን እስከተረጋገጠ ድረስ መኪናዉ ሊወረስ ይገባል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ተሽከርካሪ የተጭበረበረ ስለመሆኑ በባለሞያ የቀረበው ማስረጃ ሳይመለከቱ ተሽከርካሪው ሕጋዊ መሆኑ ተከላክለዋል በማለት ተጠሪዎች ነፃ እንዲለቀቁ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1 .የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 48692 በቀን 28/04/2007 ዓ.ም.እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10870 በቀን 30/03/2008 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2 .1ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) / ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ

፣እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) / ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ የተመለከተውን በመተላለፋ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

3 .የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈጸመበትን ከላይ የተገለጸውን በኤግዚቢትነት የተያዘው ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-02075 ሐረ. በሚል የሚታወቀው ተጠሪዎች ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104/1/ መሠረት ለመንግስት እንዲወረስ ታዟል፡፡ አመልካች ተከታትሎ ያስፈጸም፡፡

4/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ የቅጣት ሀሳብ ከተቀበለና ከአከራከረ በኂላ ከሕጉ እና ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንጻር በመመርመር በተጠሪዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጥ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1/ የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪዎች፡-1ኛ አቶ ፋሲል ጥላሁን እና 2ኛ አቶ ካሊድ ሳቢት ከተገኙበት ቦታ ይዞ ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት እንዲያቀርበው ታዟል፡፡ይጻፍ ፡፡

2/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት መ/ቁ 48692 በመጣበት አካኂን በፍ/ቤቱ ሬጅስትራር አማካኝነት ተመላሽ ይሁን ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች አለበት፡፡

ቅ/ሀ

የሰ/መ/ቁጥር 139107

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

**አመልካች:-** የጉለሌ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ - ኢንስፔክተር የትምወርቅ ጋሻው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ምርመራ ሂደት የተጠረርጣሪን የባንክ ሂሳብ መረጃ የማግኘት ፈቃድን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠርጣሪ አቶ መኮንን በላይ ላይ ለጀመረዉ የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ምርመራ ሥራ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተጠርጣሪዉን የባንክ ሂሳብ መረጃ እንዲሰጠዉ እንዲታዘዝለት ለስር ፍ/ቤት ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ጥያቄዉን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 3(3) መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ በወንጀል ምርመራ ወቅት ባንክ ማዘዝ የሚችል ስለሆነና ስልጣኑም የጠቅላይ ዐ/ሕግ በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ በዐ/ሕግ በኩል ሊስተናገድ ስለሚችል ጥያቄዉን አልተቀበልኩም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም አመልካች ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ የአዋጅ ቁጥር 943 አንቀጽ 6(3/ሀ) ለፖሊስ የተሰጠ ወንጀል የመመርመር ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሚል ቃል ያለዉና ለፖሊስ

ራሱን በቻለ አዋጅ ስልጣኑ ተለይቶ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ ተገቢ አይደለም በማለት ትዕዛዙን በመሻር ሲወስን፤ ፖሊስ እንዲሰጠዉ የጠየቀዉን ትዕዛዝ አስፈላጊነት በተመለከተ ፖሊስ ስንቅ የሌለዉ ቼክ ቀርቦለት፤ ባንኩ የቼኩ ባለቤት ቼኩ ተሰርቆብኛል በማለት ያስታወቀዉ መሆኑን በገለጸበት ሁኔታ ፖሊስ ባንክ የሚገኝ ማስረጃ የሚፈልግበት ምክንያት ግልጽ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡ አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በፌዴራል ፖሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/04 መሠረት ወንጀል የመመርመር ስልጣን ለፖሊስ የተሰጠ ሲሆን እንደሚደርሰን ጥቆማ እና የወንጀሉ ክብደት በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 እና በአዋጅ ቁጥር 592/2000 መሰረት የግለሰቦች የባንክ መረጃ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንደሚገኝ ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ማስረጃ የማግኘት ያለን መሆኑን ቢያረጋግጥም የወንጀል ምርመራዉ ተጠርጣሪዉ ለባንኩ ጠፍቶብኛል ብሎ ካስታወቀዉ ቼክ ጋር የተያያዘ በመሆኑ እየታወቀ የማስረጃዉ አስፈላጊነት ግልጽ አይደለም በማለት አቤቱታችን ዉድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለሆነም የተጀመረዉን ምርመራ ማጠናቀቅ እንዲቻል ቼኩ በወጣበትና ለባንክ ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ በተጠርጣሪዉ የባንክ ሂሳብ በቂ ስንቅ ወይም ገንዘብ መኖር አለመኖሩ እንዲረጋገጥ እንዲታዘዝልን፤ በተጠርጣሪዉ ፊርማ ላይ የፎረንሲክ ምርመራ ማድረግ በማስፈለጉ ከዚህን ቀደም ተጠርጣሪዉ የፈረመባቸዉ ከ5 እስከ 7 የሚሆኑ ቼኮች እንዲሰጡ እንዲታዝ እና ተጠርጣሪዉ ፊርማ የሌለዉ ቼክ ጠፍቶብኛል ብሎ ያመለከተበት ደብዳቤ እንዲሰጠን ትዕዛዝ ይሰጥልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማዉጣት ወንጀል ተፈጽሟል በሚል በግል ተበዳይ በኩል አቤቱታ ቀርቦ ፖሊስ ለምርመራ ይጠቁምኛል ያላቸዉን ሰነዶች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሰጠዉ ማዘዣ ከፍ/ቤት ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት ማስረጃዉ የሚፈለግበት አግባብ ግልጽ አይደለም በሚል የአመልካች ማዘዣ ጥያቄ ዉድቅ ያደረገበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 22(2-ሠ)፣ ከአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 28(4-ሠ)፣ ከአዋጅ ቁጥር 720/04 አንቀጽ 6 እና አግባብነት ካላቸዉ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ድንጋጌዎች መሠረት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች በፌዴራል ፖሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 6 ወንጀልን የመርመር ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑና ለምርመራ የሚያስፈልገዉን የግለሰብ የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ መረጃ ማግኘት የሚችለዉ ስለባንክ ስራ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 28(4/ሠ) መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሆኑ በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ ፖሊስ ለምርመራዉ አስፈላጊ የሆነ የተጠርጣሪ የባንክ መረጃ ሲኖር ጥያቄዉን ለፍ/ቤት አቅርቦ አስፈላጊነቱ ሲታመን ፍ/ቤት ለባንክ መረጃ እንዲሰጥ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተጠርጣሪዉን የባንክ መረጃዉን የሚመለከተዉ ባንክ እንዲሰጠዉ የፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ያቀረበዉ ምክንያት በቂ አይደለም በማለት ጥያቄዉን ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ስንቅ ሳይኖር ቼክ የማዉጣት ወንጀል በተጠረጠረዉ አቶ መኮንን በላይ በጀመረዉ ምርመራ ምክንያት ምንም እንኳ ቼኩ ለባንክ ቀርቦ ክፍያ ሳይፈጸም ተመላሽ የተደረገ መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ተጠርጣሪዉ አስቀድሞ ቼኩ የተሰረቀ በመሆኑ ክፍያ እንዳይፈጸምበት ለባንኩ ማስታወቁን ባንኩ በመግለጹ ቼኩ የተሰረቀ ነዉ ወይስ በተጠርጣሪዉ ተፈርሞ የተሰጠ ነዉ የሚለዉን እዉነታ ለማጣራትና ምርመራዉን ለማጠናቀቅ የተጠርጣሪን የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ፣ ቀድሞ የፈረማቸዉን የፊርማ ናሙናዎች ማግኘቱ ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች ያለፍ/ቤት ትዕዛዝና ለተፈቀደላቸዉ ሰዎች ካልሆነ በቀር ለማንም ሰዉ ተላልፎ የማይሰጡ በሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸዉ መረጃዎች በመሆናቸዉ ፖሊስ በፍ/ቤት ትዕዛዝ መረጃዎችን ካላገኘ በስተቀር በተጠርጣሪዉ ላይ የጀመረዉን ምርመራ ሊያጠናቅቅ አይችልም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተጠርጣሪዉን የባንክ መረጃ የሚፈልግበት አግባብ ግልጽ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበል መቅረቱ የወንጀል ምርመራዉን ልዩ ባህሪ፣ በአዋጅ ቁጥር 720/04 አንቀጽ 6 ለአመልካች የተሰጠዉን ወንጀል የመመርመር ስልጣንና በአዋጅ ቁጥር 592/00 አንቀጽ 28(4/ሠ) መሠረት የተጠርጣሪዉ የባንክ ሂሳብ መረጃ የሚገኝበትን አግባብ ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

ሌላዉ ይህ ሰበር ችሎት ለባንክ ትዕዛዝ ይስጥልን የሚለዉን የአመልካች ጥያቄን በተመለከተ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት ለዚህ ችሎት የተሰጠዉ ስልጣን የመጨረሻ በሆነ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ በቀጥታ ለባንክ ትዕዛዝ በመስጠትና መረጃዉ መሰጠቱን በመከታተል የሚያስፈጽምበት አግባብ ባለመኖሩ የተፈጸመዉን የሕግ ስህተት በማረም ትዕዛዙ በስር ፍ/ቤት በኩል እንዲሰጥና አፈጻጸሙን አስመልክቶ ክትትል እንዲደረግበት ለስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መመለሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 003839 የካቲት 03 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57579 የሰጠዉን ትዕዛዝ መሻሩ በአግባቡ ነዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በተጠርጣሪዉ ላይ የጀመረውን ምርመራ ለማጠናቀቅ ቼኩ በወጣበት የባንክ ሂሳብ ጋር የተያያዙና በአመልካች የተጠየቁ መረጃዎችን ማግኘት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ አመልካች መረጃዎችን ማግኘት እንዲችል በስር ፍ/ቤት ተገቢዉ ትዕዛዝ ሊሰጥበት ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ አመልካች በተጠርጣሪ ላይ እያካሄደ ላለዉ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ የማዉጣት ወንጀል ምርመራ የጠየቃቸዉን መረጃዎች ማግኘት እንዲችል ትዕዛዝ ለሚመለከተዉ ባንክ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ይመለስለት ተብሎ ተወስኗል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 146727

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
እንዳሻው አዳነ
ሃይሉ ነጋሽ
እትመት አሡፋ

አመልካች፡- አቶ አክሊሉ አፈወርቅ ጠበቃ ናትናኤል ተክሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 08 ቀን 2009 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት በመ.ቁ 144037 ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሠበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡ የአሁን አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ሥድሥት ተከሳሾችን ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪን ማሥረጃዎች ከሰማ በኋላ ተከሳሾች በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ፈቅዷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ለአመልካች እና ለሥር ተከሳሾች የሰጠውን የዋስትና መብት በመሻር ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከታተሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 በዋስትና ጉዳይ ላይ ከአንድ ጊዜ በላይ ይግባኝ እንደማይኖር የተደነገገ በመሆኑ አመልካች አቤቱታውን ለሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ከማሳረም ውጪ ሁለተኛ ይግባኝ ሊያቀርብ አይችልም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ከመነሻውም ቢሆን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዋስትና መብቱ ያልተከለከለ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 ሁለተኛ ይግባኝ አይፈቅድም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን የዋስትና መብት የሻረው ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ሆኖ ሳለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዋስትና ጉዳይ ላይ ሁለት ጊዜ ይግባኝ ማለት አይቻልም በማለት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ወድቅ ማድረጉ የሰጠው ውሳኔ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ጥቅምት 02 ቀን 2010 ዓ/ም በሰጠው መልስ በሥር ፍ/ቤት የአመልካች የይግባኝ መብት መታለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ሥሕተቱ ቢታረም ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልጿል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል።የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9/2 የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ሥልጣን እንዳለው ይደነግጋል።

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75 (1)እና(2) በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የቀረበውን ማመልከቻ ፍ/ቤቱ ያልተቀበለው እንደሆነ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚቻል እና በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የሌለው መሆኑን ይደነግጋል። ሆኖም በድንጋጌው ርዕስ ላይ እንደተገለጸው የዚህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ጠይቆ ባልተፈቀደ ጊዜ እንጂ የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት ጠብቆ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት በመጠበቅ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በሰጠው ውሳኔ ላይ ተከሳሽ ይግባኝ እንዳያቀርብ ተፈጻሚ የሚሆን አይደለም። በወንጀል ሥነ ስርዓት ሕጉ ቁጥር 75 (2) ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ

የለውም በማለት የተደነገገው ድንጋጌ ተከሳሹ በበታች ፍ/ቤት የተፈቀደለት የዋስትና መብት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተሻረበት ጊዜም የተከሳሹ ይግባኝ የማቅረብ መብት እንደሚከለክል አድርጎ መተርጎም የዜጎችን ይግባኝ የማቅረብ መሠረታዊ መብት የማጣበብ ውጤት ያለው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት የሻረው ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት በመሆኑ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9/2 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 ሁለተኛ ይግባኝ አይፈቅድም በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገመንግሥቱ ዕውቅና ያገኘውን የአመልካችን ይግባኝ የማለት መብት ያጣበበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 144037 ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 194317 ሠኔ 05 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ድጋሚ ይግባኝ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

**-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

የሰ/መ/ቁ. 135787

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች፡-**አበባየሁ ሳሙኤል -ጠበቃ ዮሴፍ ኪሮስ

**ተጠሪ፡-**የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ -አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 23604 በቀን 01/06/2008፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 237785 በቀን 17/09/2008 እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 249149 በቀን 8/02/2009 በሰጠው ትእዛዝ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ውንብድናና ከባድ ሰው መግደል ወንጀል የቅጣት ውሳኔ የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካችና ሌሎች 5 ሰዎች ላይ ሁለት የተሻሻለ የወንጀል ክሶችን ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ /ሀ/ እና 671/1/ /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ካልተያዘው አቡሽ ተከተል ጋር በመሆን አመልካች የግል ተበዳይ ሚች ዶ/ር ቢንያም ማሞ መጽሀፍ ለማዘጋጀት ያዘጋጀውን ጽሁፍ ለመውሰድ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር በመምከርና 2ኛ ተከሳሽ

ገንዘብ ከተከፈለው ጽሁፉን በእጁ እንደሚያስገባለትና አመልካች የሚከፍል መሆኑን ተስማምተው 2ኛ ተከሳሽም ይህንኑ ከ3ኛ-5ኛ እና ካልተያዘው አቡሽ ተከተል ጋር ተመካክረው 5ኛ ተከሳሽ ሜሮን አየለ ከሟች ጋር ተቀራርባ በሚፈልጉት ጊዜ እንድትጠራው ተስማምተው በ20/12/2006 ሟችን ጠርታ እስከ ሌሊት 6፡00 ሰዓት አብረው ቆይተው ከ2ኛ-4ኛ ያሉ ተከሳሾችና አቡሽ ተከተል በጉልበት ይዘውት ባንተ ላይ የምንፈጽመውን ለፖሊስ ከተናገርክ እንገድልሃለን በማለት የሞት አደጋ የሚያደርሱ መሆኑን በማስጠንቀቅ ሞባይል፣ ጃኬት፣ ጫማ፣ ፍላሽ ሟች መድሐፍ ለማሳተም በእጁ የያዘው ጽሁፍ ሶፍት ኮፒ የወሰዱ በመሆኑ ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል እና 2ኛው ክስ ደግሞ ከ1ኛ -6ኛ ተከሳሾች የወንጀል ህግን አንቀጽ 32/1/ /ሀ// /ለ/ እና 539 /1/ /ሀ/ /ለ/ /ሐ/ በመተላለፍ ከላይ በ1ኛው ክሱ የገለፀውን ከፈፀሙ በኋላ ሟችን ለመግደል አስበው ከአቡሽ ተከተል ጋር በመሆን ሟች ለማሳተም ያዘጋጀውን ጽሁፍ ሶፍት ኮፒ 2ኛ ተከሳሽ ለአመልካች /1ኛ ተከሳሽ/ ከሰጠ በኋላ አመልካች ሟች በህይወት ሳለ በዚህ ጽሁፍ መጠቀም ስለማይቻል ሟችን መግደል አለባችሁ ብሎ ሲገልጽ ገንዘብ እንደሚጨምር ከተስማሙ በኋላ ለ2ኛ ተከሳሽ ብር 30000/ሰላሳ ሺህ/ ለ4ኛ ተከሳሽ ብር 15000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ ለ5ኛ ተከሳሽ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ 3ኛ ተከሳሽ እና አቡሽ ተከተል የወሰዱት ገንዘብ የማይታወቅ ከወሰዱ በኋላ 5ኛ ተከሳሽ ሟችን ሻሸመኔ ከተማ ቀበሌ 03 ልዩ ቦታው ሻሌት ከተባለ ሆቴል በስልክ ቀጥራው ሲመጣ ሌሊት ከ2፡00-3፡00 ሰዓት ከ2-4ኛ ያልተያዘው አቡሽ ተከተል ወደ ሆቴል ሲገባ አፍነው መኪናው ውስጥ በመወርወር ከወሰዱት በኋላ ለስድስት ቀን ሌሊት ሌሊት ሻሸመኔ ከተማ መልካ ኦዳ አና ለገጉጌቱ በተባለ ቦታ በመውሰድ በፕላስቲክ አፉን በማሸግ እግርና እጁን በማሰር በዘግናኝ ሁኔታ የተያዩ ጉዳቶች ካደረሱበት በኋላ የጐን አጥንት መሰበር፣ የግራ ሳንባ እና ኩላሊት መሰንጠቅ በአሰቃቂ ሁኔታ በ30/12/2006 ከገደሉት በኋላ እሬሳውን በመኪና ጭነው አርሲ ነገሌ ወረዳ ዳኮ ሆራ ቀሎ በተባለ ቀበሌ ውስጥ ሌሊት 5፡00-8፡00 ሰዓት የጣሉት በመሆኑ በአሰቃቂ ሁኔታ የግድያ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች የቀረበበትን የወንጀል ክስ አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ የተከራከረ ቢሆንም አምስተኛ ተከሳሽ የነበረችው የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሟን አምና በሰጠችው ቃል መሠረት በቀረበው ክስ መሠረት ጥፋተኛ በማለት የእድሜ ልክ ጽኑ

እስራት የቅጣት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በተቀሩት ተከሳሾች ላይ 5 የተጠሪ ምስክሮችን፣ የ5ኛ ተከሳሽ የሰጠችው የእምነት ቃል፣ ሐናን ጌታቸው በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት የሰጠችው የምስክርነት ቃል፣ ሟች የተጣለበትን ቦታ የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ አንድ የቪዲዮ ሲዲ፣ የሟች ሲም ካርድ ከ5ኛ ተከሳሽ የተወሰደ፤ከዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የተጻፈ የሟች የህክምና ምስክር ወረቀት የቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ እንዲከላከሉ አመልካችን ጨምሮ በሰጠው ብይን መሠረት አመልካች የተከሳሽነት ቃሉንና የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ያሰማ እና በፖሊስ ምርመራ የተጣራ መዝገብ እና 5ኛ ተከሳሽ በፍ/ቤት ቀርባ የሰጠችው ቃል፣ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር የስልክ ልውውጥ ስለማድረጌ ከኢትዮ ቴሌኮም ማስረጃ ማቅረብ እና ከአድማስ ገጽ ስነጽሁፍ ማህበር የተጻፈ ማስረጃ አቅርቧል ፍርድ ቤቱም በአመልካች ላይ የቀረበውን ክስ እና በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ የቀረበበትን ሁለቱንም ክስ አልተከላከለም በማለት ጥፋተኛ ነው በማለት ቅጣትን በተመለከተ የአመልካች የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ሁኔታ የወ/ህ/አንቀጽ 539/1/ የሚፈልገውን ሁሉ በመተላለፍ ከዚህ በፊት ጥሩ ሥነ ምግባር የሌላቸው ተከሳሾች ጋር በመሆን ትእዛዝ በመስጠት እና በመፈፀም ተቀራራቢ በሆኑ ጊዜያት ከባድ ዝርፊያ እና ከባድ ግድያ ወንጀል መፈፀሙ ያለፈ የህይወት ታሪኩ መልካም ነው ተብሎ በማቅለያነት ታሳቢ የሚደረግ አይደለም ፤ቤተሰብ አለው በማለት የቀረበው በህጉ በግልጽ ያልተቀመጠና ማስረጃ ያልቀረበበት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በሞት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አጽንተዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህንን በመቃወም መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም ጥፋተኛ የተባለባቸው ሁለት ድርጊቶች በአንድ የወንጀል ህግ ድንጋጌ የሚጠቃለሉ ናቸው፣ የመከላከያ ምስክሮች በሚገባ ቀርበው ሳይመረመሩ የተሰጠ ውሳኔ ነው ፤የማስረጃ ምዘና መሠረታዊ መርሆዎች አልተከተሉም ቅጣትን በተመለከተም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ቅጣት ሊቀልልኝ ይገባ ነበር የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በአመልካች የቀድሞ

የወንጀል ሪከርድ በሌለበት እና ከቅጣት አወሳሰን መመሪያም የቅጣት ውሳኔ ያልተሰጠ መሆኑን መሠረት በማድረግ ከወ/ህ/አንቀጽ 117 አንጻር ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት በሰጠው መልስ የወ/ህ/ አንቀጽ 82/1/ /ሀ/ መሠረት የወንጀል ድርጊቱ በዕውቀት ማነስ ባለማወቅ በየዋህነት ከተፈፀመ የወንጀል ሪከርድ ባልቀረበ ጊዜ በማቅለያነት የሚያዝ እንጂ እንደአመልካች የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመው በዕውቀት ማነስ ሳይሆን የዕውቀት ሥራን ለራስ ለማድረግ ለማሳተም ዕውቅና ለማግኘት በማሰብ እና የተማረ በመሆኑ ቅጣቱ ሊቀልለት አይገባም፣ አመልካች ሁለት የወንጀል ድርጊቶችን አከታትሎ የፈፀመ በመሆን ግምት ውስጥ ገብቶ የተሰጠ የቅጣት ውሳኔ በመሆኑ የተፈፀመ መሠረታዊ ስህተት የለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልኝ ብሏል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ምክንያት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ /ሀ/ እና 671/1//ሀ/ በግብረአበርነት ከባድ የውንብድና የተመለከተውን በመተላለፍ እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ እና 539/1/ /ሀ//ለ//ሐ/ በግብረአበርነት ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከባድ የውንብድና ወንጀል ካስፈፀመ በኋላ ከባድ የግድያ ወንጀል እንዲፈጽም ትእዛዝ አስተላልፎ በማስፈፀም የአመልካች ጠበቃ ያቀረበው የወንጀል ሪከርድ የሌለበት መሆን ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች ያልተቀበለው መሆኑን እና የቤተሰብ አስተዳደሪነት በተመለከተ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑና ለፍርድ ቤቱ የተተወ ነው በማለት ውድቅ በማድረግ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ 2/2006 መሠረት ምንም ማቅለያ ሳይዝ በሞት እንዲቀጣ መወሰኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ

ነው፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቀቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችን የአሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን ነው፡፡ በዚህም አፈጻጸም አወሳሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የወጣ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በቅጣት መመሪያ ውስጥ የተቀመጠው የቅጣት አወሳሰን ሥርዓትም ስለቅጣት አወሳሰን በህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ዓቢይ ነጥብ ቅጣቶችን በመጣልና እርምጃዎችን በመውሠድ ረገድ ዳኞች አመዛዝነው የመወሠን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ዳኞች አጥፊውን በተመለከተ ከግምት ውስጥ ሊያስገቧቸው የሚገባቸው በርካታ የአጥፊ ሁኔታዎች ቢኖሩም የቅጣት አወሳሰናቸው መሠረት የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን /degree of individual guilt/ ስለመሆኑ የአንቀጽ 88/2/ ድንጋጌ ይዘትና አቀራረፅ ያስረዳል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በሁለት ግዘፍነት ባላቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ሲሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1//ሀ/ እና 671/1/ /ሀ/ እና /ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የውንብድና ወንጀል በመፈፀም ሲሆን ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1//ሀ/ 539 /ሀ/ /ለ/ /ሐ/ የተመለከተውን ተላልፎ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል በመፈፀም ደግሞ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጡ ወንጀሎች

ናቸው፡፡ ሁለቱም የወንጀል ድርጊቶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ደረጃ እና እርከን የወጣላቸው ናቸው፤ የመጀመሪያውን ክስ በተመለከተ አመልካች በ2ኛው ክስ የተመለከተውን የውንብድና ወንጀል ከፈፀመ በኋላ በዚሁ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ከሟች ዶ/ር ቢኒያም ማሞ የወሰደው ጽሁፍ ለማሳተም የግሉን ስብዕና ለማሳደግ ጥቅም ለማግኘት የሟች መገደል አስፈላጊ ነው በሚል አስነዋሪ የአፍቅሮተ ንዋይ ስሜት ከ2ኛ-5ኛ ተከሳሾች የነበሩትን የውንብድና ቡድን በመጠቀም ከሟች የዕውቀት ብርሃን የተገኘውን ጥበብ /ጽሁፍ/ በውንብድና ተግባር የወሰደውን የአዕምሮ የፈጠራ ውጤት እንዳይገለጽ ለማድረግ የፈፀመው መሆኑ የወንጀሉ ደረጃ 2 እርከን 39 ላይ የሚያርፍ ሲሆን ሁለተኛው ክስ በተመለከተ የወንጀል ድርጊቱ ከባድነት እና አፈጻጸሙ ከላይ የተመለከተው በመሆኑና በመጀመሪያ ክስ ዕድሜ ልክ ወይም ሞት የሚያስቀጣ በመሆኑ ሁለተኛው ክስ ላይ የተመለከተው አጠቃሎ የሚይዝ ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 184/1/ /ሀ/ /ለ/ በተመለከተው መሠረት መነሻ ቅጣት እርከን 39 ላይ የሚያርፍ ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም ሆኖም አመልካች ላይ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ የሌለው መሆኑን በቅጣት ማቅለያነት ቀርቦ ፍርድ ቤቱ አመልካች ተቀራራቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ከባድ የዝርፊያ ወንጀል እና ከባድ ግድያ እንዲፈጽም በማድረግ ጥሩ ፀባይ ያለው ነው ብሎ ለመገመት የሚያስችል አይደለም ብሎ አመልካችን በሞት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ በተደነገገው ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይገባ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 15 ስር በኃይለ ቃል የደነገገው ጉዳይ ነው፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ ከባድ ወንጀል መፈጽሙ በተረጋገጠበት ሰው ላይ የሞት ቅጣት ማስተላለፍ የሚፈቀድ መሆኑን ሕገ መንግስቱ አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል የሞት ቅጣት ሊተላለፍ የሚገባበት አግባብ የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 117 ስር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር አንደ ድንጋጌ መሰረት የሞት ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ፍጻሜ ያገኘ ሆኖ እጅግ በጣም ከባድ በመሆኑና ወንጀለኛውም በተለይ አደገኛ በመሆኑ ለወንጀሉ ቅጣት እንዲሆን በሕጉ በግልጽ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ እንዲሁም

ወንጀለኛው ቅጣትን የሚያቀልለት ምክንያት በታጣ ጊዜ እድሜው ቢያንስ አስራ ስምንት አመት የሞላው ሆኖ ሲገኝ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባለባቸው የወንጀል ድርጊቶች የተፈፀሙት የአሁን አመልካች የሆነው የስር 1ኛ ተከሳሽ የሟችን ዶ/ር ቢኒያም ማሞን መጽሃፍ ለማዘጋጀት ያዘጋጀውን ጽሁፍ በከባድ የውንብድና ቡድን ተግባር ለመውሰድ እና የዚህን ጹሁፍ ባለቤት ለመሆን የእውቀቱን አመንጪ መግደል ለሌላኛው ወንጀል ከለላ እንዲሆን ታስቦ የተፈፀመ በመሆኑ በዚህ አይነት ሁኔታ በወንጀል ህግ አክብዶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመበት ሟች ሆነ አመልካች የሀገሪቱ ሀብት እና በዩኒቨርስቲ መምህራን የሚቀርፁ ባለሙያዎች ሆነው በመልካም ባህሪያቸው ለህብረተሰቡ አርአያ ተደርገው የሚወሰዱ ሆነው ፍፁም ወራዳ በሆነ ተግባር መፈፀሙ የአመልካችን አደገኛ ባህሪይ የሚያመለክት ሲሆን በአመልካች የቀረበው የቀደመ የወንጀል ሪከርድ አለመኖር በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላገኘ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መሆኑን ከውሳኔ ይዘት እና ከወንጀል ህግ አንቀፅ 117 አንጻር የወንጀል ድርጊቶቹ አፈጻጸም ከባድነት በተለይም የአመልካችን አደገኛነት መሠረት ያደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአጠቃላይ በአመልካች ላይ የተወሰነው የሞት ቅጣት የወንጀል ሕጉን መሠረታዊ ግብና ዓላማ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን ከአመልካች የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ጋር የተገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1/ በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 23604 በቀን 01/06/2008፣ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 237785 በቀን 17/09/2008 እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 249149 በቀን 08/02/2009 የሰጠው ትእዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ አመልካች በሞት እንዲቀጡ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ የሞት ቅጣቱ ተፈጻሚነት የሚኖረው በወንጀል ህግ አንቀጽ 117/2/ መሠረት በሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር ከፀና በኋላ ይሆናል ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

*መ/ይ*

የሰበር መዝገብ ቁጥር 137262

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካቾች፡- 1. ወጣት ሀይላይ ወ/ገብርኤል

2. ወጣት ወ/ገርግስ ሐጎስ } የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ጉዳይ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ ፍ/ቤት በአክሱም ምድብ ችሎት ነው፡፡ ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው የተሻሻለ ክስ ይዘት አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 ድንጋጌን በመተላለፍ ሚያዝያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት አባሪ ተባባሪ በመሆን በአክሱም ከተማ በማፅበል ቀበሌ ቀጠና 4 በተባለ ቦታ የግል ተበዳይ ወ/ት ሐጎሳ ሀይሉን በመምታት በተለያየ የሰውነት አካሏ ላይ 1 × 1 ሳ.ሜ፤ በጭንቅላትዋ ላይ 2 × 1 ሳ.ሜ፤በምላሷ ላይ 2 × 2 ሳ.ሜ ጉዳት ካደረሱባት እና ራሷን እንድትስት ካደረጉ በኋላ ለብሳው የነበረውን ልብስ በመቅደድ አውልቀው እርቃንዋን በማድረግ 1ኛ አመልካች ክብረንጽህናዋን በመድፈሩ፤2ኛ አመልካችም ተባብሮ ክብረንጽሕናዋን በመድፈር ቀጥቅጠው ራሷን እንድትስት በማድረግ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካቾች ክሱ ተነቦላቸው መቃወሚያ የሌላቸው መሆኑን ከገለጹ በኋላ የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው የተከራከሩ በመሆኑ የተጠሪ ማስረጃዎች ተሰምተዋል፡፡

1ኛ የተጠሪ ምስክር የግል ተበዳይ ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል አመልካቾች በዕለቱ በሐሙስ ገበያ በኩል ወደ ቤታቸው አብረው እንሂድ ያልዋት መሆኑን፣ምሽት ነው አልሔድም ስትላቸው ሞባይል እናበራለን ያልዋት መሆኑን፣2ኛ አመልካች ወደኋላ ቀርቶ ስለነበር 1ኛ አመልካች እንጠብቀው ያላት መሆኑን፣ብርሃን ያለበት ቦታ እንጠብቀው ብትለውም ልብስሽን አውልቂ ያላት መሆኑን፣እንደማትፈልግ በመግለጽ ተው ብትለውም ደጋግሞ አፍንጫዋን በመምታት እያንዳንዱ የለበሰችውን ልብስ ቀዶ የጣለው ፓንት ሳይቀር የወረወረ መሆኑን፣ለሕይወትሽ ሳሳሽላት ሲላት የመጣ ይምጣ ለሕይወቴ አልሳሳም ያለችው መሆኑን፣እንዳልገልሽ ሲላት ግደለኝ ስትለው እንዳታይ በማለት በድንጋይ ዓይኗን ጭንቅላትዋን አንገትዋን እጇን የመታት መሆኑን፣ድንግልናዋን የደፈረ እና ማሕጸኗ የተሰነጠቀ መሆኑን፣ሁለተኛ አመልካችም መጥቶ የደፈራት መሆኑን፣በምላጭ፣በሚስማር ወይም በቢላዋ መሆኑን ባልለየችው ሁኔታ እንደእባብ ሲቀጠቅጧት ያደሩ መሆኑን፣ባሕር ውስጥ እንክትሻለን ያልዋት መሆኑን፣በጀርባዋ ወድቃ እያለ በእግራቸው ሆድዋን ረግጠው ከእግርዋ እስከ ጸጉርዋ ድርስ የሸኑባት መሆኑን፣ምራቃቸውን ከተፉባት በኋላ ሞታለች አልሞተችም እያሉ ሹራብ ሸፍነዋት የሄዱ መሆኑን፣በረሃ ላይ ራቁትዋን ያደረች መሆኑን፣ከፍላጎትዋ ውጪ አስገድደው የእርቅ ውል ያስፈረሟት መሆኑን፣ በደረሰባት አደጋ ምክንያት ሆድዋን የሚቆርጣት፣ የሚነፋት ፣የሚያቃጥላት ፣የሚያዞራት፣ የሚሞቃት እና የሚያስቃያት መሆኑን በመግለጽ መስክራለች ፡፡

ሁለተኛ የተጠሪ ምስክር ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል ሚያዝያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ከሌሊቱ በ 6፡00 ሰዓት በራቸው የተንኳኳ መሆኑን፣ማነው ሲሉ የግል ተበዳይ ክፈችልኝ ያለቻቸው እና ፈርተው ያልከፈቱላት መሆኑን፣ጠዋት በሩን ሲከፍቱ የግል ተበዳይ ራቁትዋን በር ሥር ቁጭ ብላ ያገኟት መሆኑን፣ሰውነትዋ ተመትቶ የነበረ እና 1ኛ አመልካች መትቶኝ ነው ያለቻቸው መሆኑን፣ልብሶቿ ተቀዳድው ሜዳ ላይ ተጥለው የተገኙ መሆኑን እና ለቤተሰቦቿ ስልክ የደወሉ መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፡፡

3ኛ የተጠሪ ምስክር ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል በእለቱ ስልክ ተደውሎላቸው መጥተው የግል ተበዳይን ሕክምና ቦታ የወሰዷት መሆኑን፣የተመታችበትን አካባቢ ያዩ እና ልብሶቿ ተቀዳደው ተጥለው ከባድ ጉዳት ደርሶባት የነበረ እና አመልካቾች መቱኝ ብላ የነገረቻቸው መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፡፡ 4ኛ ምስክር በሰጡት የምስክርነት

ቃል አመልካቾች በእለቱ ከግል ተበዳይ ጋር የግል ተበዳይ ተመታሁ ባለችበት አካባቢ ሲሄዱ ያይዋቸው መሆኑን በመግለጽ መስክሯል፡፡ 5ኛ ምስክርም በሰጡት የምሥክርነት ቃል በእለቱ አመልካቾችን ያዩ እና የግል ተበዳይ መቱኝ ብላ የነገረቻቸው መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፡፡ በግል ተበዳይ ላይ አዲስ የሆነ የክብረንጽሕና መገርሰስ እንደደረሰባት፤ማሕጸንዋ እንደተሰነጠቀ እና እንደተሰፋ ፤በተለያየ አካሏ ላይ ጉዳት እንደደረሰ የሚያሳይ የተለያየ የሰነድ ማስረጃም ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ተጠሪ እንደክሱ አስረድቷል በማለት አመልካቾች በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ እንዲከላከሉ በማለት በሰጠው ብይን መሠረት አመልካቾች ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ቦታ ላይ እንዳልነበሩ የሚያስረዱ መከላከያ ምሥክሮችን በማቅረብ አሰምተዋል፤የሰነድ ማሥረጃዎችም አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙ ለመሆኑ በሚገባ ስለተመሰከረባቸው እና ባቀረቡት መከላከያ ማሥረጃ ክሱን ስላላስተባበሉ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የቅጣት ውሳኔን በተመለከተም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ቅጣቱን በማስላት የወንጀሉን ደረጃ ደረጃ ሐ እርከን የቅጣት መነሻ እርከን 38 በመያዝ ፤ተጠሪ ድርጊቱ በጭካኔ ስለተፈጸመ በማክበጃነት ይያዝልን በማለት ያቀረበውን የቅጣት ማክበጃ ባለመቀበል፤ተጠሪ ድርጊቱ በጨለማ የተፈጸመ ስለሆነ በማክበጃነት ይያዝ በማለት ያቀረበውን ማክበጃ በመቀበል ወደ እርከን 39 በማሳረፍ፤አመልካቾች ድርጊቱን በሥምምነት የፈጸሙት ስለሆነ በቅጣት ማክበጃነት ሊያዝ የሚገባው ቢሆንም ከእርከን 39 በላይ የሚወጣ በመሆኑ ማክበድ አይቻልም በማለት፤አመልካቾች የወንጀል ሪከርድ የለባቸውም የሚለውን በቅጣት ማቅለያነት በመያዝ፤አመልካቾች የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነን ከተበዳይ ጋር ታርቀናል በማለት ያቀረቡትን የቅጣት ማቅለያ ባለመቀበል አመልካቾች በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- በግል ተበዳይ ላይ ከባድ የሆነ የአካል እና የአእምሮ ጉዳት ወይም ሞት ባልደረሰበት ሁኔታ የተከሰስንበት የሕግ አንቀጽ መቀየሩ፤የተጠሪ ማሥረጃዎች በአግባቡ ባላስረዱበት ሁኔታ እና አመልካቾች ክሱን በተከላከልንበት ሁኔታ የበታች ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠታቸው እና የወንጀል ሪከርድ የሌለን እና ወጣቶች ሆነን ሳለ በቅጣት ማቅለያነት ሳይያዝ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች የተከሰሱት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 620/2/መ የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል በሚል ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 በመለወጥ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ፤ተፈጸመ ከተባለው የወንጀል ድርጊት በሁለቱ ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከተው የቅጣት መጠን እንዲሁም ከወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡ በሰበር አጣሪው እንዲጣራ የተያዘው ነጥብ አመልካቾች የተከሰሱት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 620/2/መ የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል በሚል ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 በመለወጥ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ፤ተፈጸመ ከተባለው የወንጀል ድርጊት በሁለቱ ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከተው የቅጣት መጠን እንዲሁም ከወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል የሚል ቢሆንም ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው ክስ አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 ድንጋጌን ተላልፈው ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ ያቀረበባቸው በመሆኑ የሰበር አጣሪው አመልካቾች የተከሰሱት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/2/መ መሠረት ሆኖ ሳለ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/3 ጥፋተኛ መባላቸው ከወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር በማለት የያዘውን ማጣሪያ ነጥብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በሌላ በኩል የበታች ፍ/ቤቶች አመልካቾችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/3 መሠረት ጥፋተኛ የማለታቸውን አግባብነት እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 ድንጋጌ አስገድዶ መድፈሩ ከባድ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ቅጣቱ የዕድሜ ልክ እሥራት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ በበታች ፍ/ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬነገር የግል ተበዳይ የተደበደበች ቢሆንም በዚሁ ድንጋጌ በተጠቀሰው ሁኔታ በግል ተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ወይም ሞት የደረሰባት መሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው ፍሬነገር አያሳይም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች በግል ተበዳይ ላይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/3 በተመለከተው መሠረት ጉዳት እንደደረሰባት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካቾችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/3 መሠረት ጥፋተኛ ናቸው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙት ሁለት ሆነው በጭካኔ እና የግል ተበዳይን በማሰቃየት መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማሥረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/መ አስገድዶ መድፈሩ የተፈጸመው በጭካኔ ወይም በማሰቃየት ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ወንዶች ሕብረት ሲሆን ወንጀል ፈጻሚው ቅጣቱ ከአምስት አመት እስከ ሀያ አመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት እንደሚቀጣ ይደነግጋል፡፡ አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙት ሁለት ሆነው በጭካኔ እና የግል ተበዳይን በማሰቃየት መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካቾች የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113/2 መሠረት በመቀየር አመልካቾች ጥፋተኛ መባል ያለባቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/መ መሠረት ነው ብለናል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1 የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የዚሁ ሕግ አንቀጽ 87 እና 88 ድንጋጌም ቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች ሕጉ ሊደርስበት ያሰበበትን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መንፈስ መሠረት መፈጸም እንዳለባቸው እና ሰብአዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈጸም እንደሚኖርባቸው፤ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወሰነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የሀሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን ይደነግጋል፡፡ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 4/9 መመሪያው በወንጀል ሕጉ ስለቅጣት አወሳሰን ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥሞ መተርጎም እንደሚገባው ይደነግጋል፡፡

አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/መ ድንጋጌ ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ሲሆን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ደረጃ እና እርከን የወጣለት ነው፡፡ አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙት የግል ተበዳይን አልባሳት በሙሉ በመቀዳደድ፤በድንጋይ የተለያዩ አካላትዋን ደጋግመው በመምታት፤ድርጊቱን እንዳታይ በድንጋይ ዓይኗን ጭንቅላትዋን አንገትዋን እጇን በመታት በመሆኑ እና ድንግልናዋን ከደፈሩ በኋላም እንደአባብ ሲቀጠቅጧት ያደሩ እና በጀርባዋ ወድቃ እያለ በእግራቸው ሆድዋን ረግጠው ከእግርዋ እስከ ጸጉርዋ ድርስ የሸኑባት፤ምራቃቸውን የተፉባት በመሆኑ የአመልካቾች ድርጊት አፈጻጸም አጸያፊ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ለወንጀሉ በወጣው ደረጃ መሠረት ሊወከል የማይችል እና ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት ቢወሰን የወንጀል ሕጉን የቅጣት ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 27/1 መሠረት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ሊወሰን ይገባል ብለናል፡፡ አመልካቾች

አጸያፊ በሆነ ሁኔታ የግል ተበዳይን አልባሳት በመቀዳደድ እና የተለያዩ የሰውነት ክፍሏን በድንጋይ በመምታት አካላትዋን በመርገጥ ድርጊቱን የፈጸሙ እና ድርጊቱን ከፈጸሙ በኋላም በግል ተበዳይ ላይ ምራቃቸውን በመትፋት እና ሽንታቸውን በመሽናት ጥለዋት የሔዱ በመሆኑ አመልካቾች በሀያ ዓመት ጽኑ እሥራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ ፍ/ቤት በአክሱም ምድብ ችሎት በመ.ቁ 20654 ግንቦት 17 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 86242 ሐምሌ 28 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 88489 ታሕሣሥ 19 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/መ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. የበታች ፍ/ቤቶች በአመልካቾች ላይ ያስተላለፉትን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካቾች በሀያ ዓመት ጽኑ እሥራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

**ትዕዛዝ**

-የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡

-በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት እንዲደርሰው ታዟል፡፡

-በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 27/2 መሠረት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ታዟል፡፡

**-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

# አሠሪ ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁ. 143334

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

**አመልካች**፡- ዋኢል አብዱጌት አብዱላዚዝ ፕላስቲክ ፋብሪካ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡-

1. አበራ አመዩ
2. ስሜነሽ ወርቁ
3. ብርሃኑ ዳበሳ
4. በቀለ መገርሳ

(1–4) ቀረቡ

5. ዘሜ አባራያ- ወኪል አያደር መሃመድቀረቡ
6. ጥሩ በሬቻ - ወኪል ደጀኔ መርጋ ቀረቡ
7. እቴነሽ ዳኜ - ወኪል አስናቁ ዳኜ ቀረቡ
8. አበበች በቀለ - አልቀረቡም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች ከሌሎች ሶስት ግለሰቦች ጋር በመሆን በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰበታ አዋስ ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ መልስ ሲሰጥ የተጠሪዎች የስራ ውል የተቋረጠው ድርጅቱ ከውጪ አገር የሚመጣ ጥሬ እቃ በውጭ ምንዛሬ ጋር ተያይዞ ማቅረብ ባለመቻሉ ፋብሪካው ለዘለቄታው ስራ በማቆሙ ስለሆነ የተጠየቀው ክፍያ ሊከፈል እንደማይገባና ለተጠሪዎችም መከፈል የሚገባውን ክፍያ ከፍሎ ያሰናበታቸው በመሆኑ የቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ተገቢ ነው ያለውን ዳኝነት ሰጥቶ የነበረ ሲሆን ጉዳዩ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በይግባኝ ከታየ በኋላ የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ ዳግም እንዲሰማ በማለት በመለሰለት አግባብ ማስረጃዎችን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት ድርጅቱ ከስሮ ለዘለቄታው በመዘጋቱ ምክንያት ስለመሆኑ አመልካች ድርጅት አላስረዳም በማለት ደምድሞ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን ለተጠሪዎች እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኃላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ተጠሪዎችን ያሰናበታቸው በመክሰሩ ምክንያት በመሆኑ ስንብቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24(4) አግባብ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች መክሰሩን በማናቸውም ማስረጃ የሚያረጋግጥ ቢሆን እንኳን በመክሰር ምክንያት ስራውን የሚዘጋ መሆኑን ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ስንብቱን ማከናወኑ ሕጋዊ ሊያደርገው አይችልም በማለት ስንብቱን ህገ ወጥ ነው በማለት የደመደመ ሲሆን ክፍያዎችን በተመለከተ ግን አመልካች ለተጠሪዎች የከፈላቸው የክፍያ አይነቶችና መጠናቸው በስር ፍርድ ቤት ተጣርተው እንዲወሰኑ በማለት በዚህ ረገድ ያለውን ነጥብ ብቻ ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ በቅሬታውም አመልካች ድርጅት የተዘጋው በጥሬ እቃ አቅርቦት እጥረት ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለና ማስጠንቀቂያም በቃል የሰጠ ሆኖ እያለ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተወሰነው ያላግባብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮም የተጠሪዎች የስራ ስንብት ህገ ወጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎችም ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ስንብቱ ህገ ወጥ የተባለበትን አግባብ እንደሚከለተው መርምሮታል፡፡

አመልካች ድርጅት ከውጭ ምንዛሬ ጋር ተያይዞ በተከሰተው የጥሬ እቃ አቅርቦት እጥረትና በኪሳራ ምክንያት ለዘለቄታው ስለመዘጋቱ አመልካች ጠቅሶ የሚከራከር ቢሆን ተጠሪዎች ይህ የአመልካች ክርክር በሕጋዊ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ የተዘጋው በጥሬ ዕቃ አቅርቦትና በኪሳራ ስለመሆኑ ማስረዳት የሚቻለው በሰነድ ማስረጃ መሆን ያለመሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግልፅና በሕግ የተደገፈ ምክንያት ሳይጠቅስ ስንብቱን ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አመልካች ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ መስጠት ሕጋዊ ግዴታ እያለበት ይህንኑ ግዴታ ያለመወጣቱ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደረገዋል በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም የመክሰር ወይም የውጭ ምንዛሬ እጥረት በማጋጠሙ ከውጭ አገር የሚገባ የፋብሪካ ጥሬ ዕቃ እጥረት መኖር በማናቸውም የማስረጃ አይነት ሊረጋገጡ የሚችሉ ናቸው ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ የማይቻል ሲሆን በዚህ ረገድ ለሚቀርቡ ክርክሮች መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች በሕጉ አግባብ ስልጣን በተሰጣቸው አካላት የሚሰጡና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው መሆን ያለባቸው መሆኑን ከማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን መርሆዎች እንዲሁም ስለመክሰርም ሆነ ስለ ውጭ ምንዛሬ አግባብነት ባላቸው በሌሎች ሕጎች የተዘረጉትን ስርዓቶች በመመርመር የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ ያስፈረው የምክንያት ክፍልና አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው የሰበር ክርክር ሕጋዊ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ማስጠንቀቅያ የሚያስፈልገው መሆን ያለመሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 28(2(ሀ)) ድንጋጌ ከአለው አንድነትና ልዩነት አንፃር ተመልክተናል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/2/ሀ/ ሰራተኞች የተሰማሩባቸውን ስራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘለቄታው የሚያስቀም የሰራተኛ ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ በአሰሪው ወይም አሰሪውን በሚመለከቱ ምክንያቶች ሲከሰት የስራ ውሉ በማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ እንደሚችል ይገልፃል፡፡ ድንጋጌው ምክንያቶች ከአሰሪው ጋር የተያያዙ መሆናቸውንና የድርጅቱ ስራ በከፊል ብቻ ሳይሆን በሙሉ ለዘለቄታው ሲቆም ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ እንደሚገባው የሚያስገነዝብ መሆኑን የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ ከአዋጁ አንቀፅ 24(4) ድንጋጌ አቀራረጽ፣ ይዘትና መንፈስ ጋር አዳምረን በምንመለከትበት ጊዜ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ድርጅት በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው መዘጋት የሥራ ውልን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለማቋረጥ የሚያስችል ሲሆን ለዚህም መረጋገጥ ያለበት መሰረታዊው ነጥብ የአሰሪው ድርጅት ለዘለቄታው መዘጋት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24(4) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ለዘለቄታው መዘጋቱ አልተረጋገጠም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪዎች የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ያለመስጠቱን አምኖ ማስጠንቀቂያው በቃል መሰጠቱ ስንብቱን ሕጋዊ ያደርጋል በማለት ያቀረበው ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 34 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ድርጅቱ በዘለቄታው ስለመዘጋቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ባላቀረበበት ሁኔታ እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት ከአዋጅ ቁጥር 24(4) ድንጋጌ አንጻር የሚያቀርበው ክርክር የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሆኖ ስለአገኘን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ ከውጤት አኳያ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 253316 ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

# ትዕዛዝ

ሰኔ 20 ቀን2009 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰ/መ/ቁ.126667

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

**አመልካች፡-** ኤልያስ ባርና ሬስቶራንት - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ ምርትነሽ አጥናፉ - የቀረበ የለም

2. ወ/ሪት ፌቨን ተክሌ- ተሰርዘዋል፡፡

3. ወ/ሪት ራሄል ገ/ሚካኤል -ታልፏል

4. ወ/ሪት ቆንጂት ብርሃኑ - ታልፏል

5. ወ/ሪት ዓይናለም አገዘው -ታልፏል

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪ እና ሰራተኛ የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሆኖ በአሁኑ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች እና ባሁኑ አመልካች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ከተባለ በኋላ ክፍያ ለዘገዩበት የሁለት ወር ደመወዝ ለእነዚህ ተጠሪዎች እንዲከፍል፣ 4ኛ ተጠሪ ደግሞ ከሕግ ውጪ ተሰናብተዋል ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ

ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሽ በመሆን ነው፡፡ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ዋና ይዘቱ፡-በአመልካች ድርጅት በተለያዩ ጊዜያትና የተለያዩ የሥራ መደብ ለመስራት ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ወደ አልሆነ ሱስና ተግባር ተጠሪዎች እንዲገቡ፤ ከአመልካች ደንበኞች ጋር ተገቢ ያልሆነ ደርጊት እንዲፈፅሙ አመልካች ድርጅት ትዕዛዝ አስተላልፎ ተጠሪዎች ሊቀበሉና ድርጊቶችን ሊፈፅሙ ፈቃደኛ ሊሆኑ ባለመቻላቸው ምክንያት ያለምንም ጥፋትና ማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ተጠሪዎች ለህግና ለሞራል ተቃራኒ የሆኑና ያልተገቡ ድርጊቶችን ተጠሪዎች ከአመልካች ደንበኞች ጋር እንዲፈፅሙ ያለማድረጉንና ይልቁንም 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች እንዲሰናበቱ የተደረጉት የደረሠኝ ማጭበርበርና ደንበኞችን የማታለል እንዲሁም በሚሰሩት ስራ የገንዘብ ጉድለት ያሳዩ በመሆናቸው ምክንያት ስለመሆኑ፣ 4ኛ ተጠሪ ከማጭበርበርና ከማታለል ተግባራት በተጨማሪ ያልሆነ ምክንያት በማቅረብና በመስጠት በተደጋጋሚ ከስራ የሚቀሩና ማስረጃ የማያቀርቡ በመሆኑ ምክንያት ስለመሆኑ፣ 5ኛ ተጠሪ ደግሞ ከአምስት ተከተታይ የሥራ ቀናት በላይ ቀርተው በቂ ምክንያት ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው ምክንያት ስለመሆኑ አመልካች በማረጋገጥ ከስራ እንዲወጡ ማድረጉን ዘርዝሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች አመልካች ድርጅት ተጠሪዎችን ወደ አልሆነ ሱስና ተግባር ሲገፋፋቸውና ተጠሪዎች ለመፈጸም ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ሲገልፁ እንደአሰናበታቸው የገለፁ ቢሆንም አመልካች ድርጅት ይህንን ስለማድረጉ ተጠሪዎች በማስረጃዎቻቸው ያላስረዱ መሆኑን፣ ይልቁንም 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በስራ ላይ የማጭበርበርና የማታለል ተግባር መፈፀማቸውን አመልካች ድርጅት በማስረጃዎቹ ማስረዳቱን፣ 5ኛ ተጠሪ ደግሞ ያለበቂ ምክንያት ከአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት በላይ ከስራ መቅረታቸውን አመልካች ማስረዳቱን ገልጾ አመልካች ድርጅት ከ1ኛ፣ 2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ጋር የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው በማለት የደመደመ ሲሆን 4ኛ ተጠሪን ግን ከሕግ ውጪ ስራ ላይ መቅረታቸውን ወይም በስራ ላይ የማጭበርበርና የማታለል ተግባር የፈጸሙ ስለመሆኑ አመልካች ያላስረዳ መሆኑን ጠቅሶ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሷል፡፡ ውጤቱን በተመለከተ ለ4ኛ ተጠሪ ስራ ሰርተው ያልተከፈላቸው ብር 800.00 የሚያዚያ ወር

2007 ደመወዝ፣ የሁለት ቀን ደመወዝ ለአመት እረፍት፣ የአንድ ወር ደመወዝ ለማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ 67.00(ስልሳ ሰባት ብር) የአገልግሎት ክፍያ፣የስድስት ወር ደመወዝ ካሳ እንዲከፈላቸውና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው፣ ለ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም ለእያንዳንዳቸው ብር 800.00(ስምንት መቶ ብር) የሚያዚያ ወር ደመወዝ፣ ለ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች የሁለት ቀን ደመወዝ ለአመት እረፍት፣ ለ3ኛ ተጠሪ የአምስት ቀን ደመወዝ ለአመት እረፍት፣ለ5ኛ ተጠሪ ደግሞ የአስር ቀን ደመወዝ ለአመት እረፍት እንዲከፈላቸውና የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ስራ ሰርተው ያልተከፈላቸው የሚያዚያ ወር 2007 ደመወዝ በመዘግዬቱ ምክንያትም አመልካች ለእያንዳንዳቸው ተጠሪዎች የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍላቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የደመወዝ ክፍያ ለዘየበት የሁለት ወር ደመወዝ ለተጠሪዎች እንዲከፈል፣ 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ ደግሞ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዟል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ክሊራንስ ባላስጨረሱበት ሁኔታ የዘገየ ክፍያ አለ ተብሎ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ያለግባብ መሆኑን፣ 4ኛ ተጠሪም ለሙከራ የተቀጠሩ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚቻል ሆኖ እያለ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው፣ 5ኛ ተጠሪም ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት የተቆረጠባቸው ደመወዝ ዘግይቷል ተብሎ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎቸው ክሊራንስ ሳይጨርሱ የዘገየ ክፍያ አለ ተብሎ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የመወሰኑን አግባብነት እና የ4ኛ ተጠሪ ስንብትም የሙከራ ጊዜአቸውን ያልጨረሱ ሆኖ እያለ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን፣ 5ኛ ተጠሪም ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት የተቆረጠባቸው ደመወዝ ዘገይቶአል በሚል ምክንያት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የመወሰኑነ ተገቢነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን 1ኛ፣3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ቀርበው ከአመልካች ጋር የጽሑፍ ልውውጥ ያጠናቀቀ ሲሆን 2ኛ

ተጠሪን በተመለከተ ግን አመልካች መጥሪያውን ስለማድረሱ ለማረጋገጥ ባለመቻሉ ምክንያት በእኚህ ተጠሪ ላይ አመልካች ያቀረበው የሠበር አቤቱታ በ14/11/2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚጠይቁ አበይት ነጥቦች፡-

1. የአሁኑ አመልካች ለ1ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የሚያዚያ ወር 2007 ዓ/ም ደመወዝ ዘግይቷል በማለት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው በማለት መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣
2. የ4ኛ ተጠሪ ስንብት ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተያያዥ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በተወሰነው የውሳኔ ክፍል የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ? ወይስ የለም? የሚሉት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

<u>**የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u>በአመልካችና በ1ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች መካከል የተመሰረተው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ሲሆን ይህ የውሳኔ ክፍል በሕጉ አግባብ ስለመለወጡ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ በአመልካችና በ1ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች መካከል እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እያከራከረ ያለው ጉዳይ የሚያዚያ ወር 2007 ዓ/ም ደመወዝ በወቅቱ አልተከፈለም ተብሎ አመልካች ለተጠሪዎች የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈል የመወሰኑ አግባብነት ነው፡፡ አመልካች ለእነዚህ ተጠሪዎች የሚያዚያ ወር ደመወዝ በወቅቱ ያለመክፈሉን አምኖ ይህ ክፍያ ለመዘገየቱ ምክንያት ነው በማለት ክፍያው ለዘገየበት ክፍያ የሚከፈል ክፍያ የለም በማለት መከላከያ የሚያቀርበው ተጠሪዎቹ የተረከቡትን የሆቴሉን ሂሳብ አወራርደውና ያለባቸውን እዳ ከፍለው ደመወዛቸውን እንዲወስዱ ተፈቅዶላቸው ግዴታቸውን አልፈጸሙም የሚል ምክንያት ነው፡፡ተጠሪዎች በዚህ ሰበር ደረጃ ባቀረቡት ክርክር አመልካች ድርጅት ከስራ ሲያሰናብታቸው የግል ልብሳቸውን እንኳን ለመውሰድ ያልቻሉና በጥበቃም እንዳይገቡ የተደረጉ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 መሰረት የስራ ውል ሲቋረጥ የሰራተኛው ደመወዝና ከደመወዙ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት ቀናት ውስጥ መከፈል እንዳለባቸው የተመለከተ ሲሆን፣ የክፍያው ጊዜ ሊዘገይ የሚችለው ሰራተኛው ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት ለማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ሂሳብ ለማወራረድ የራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየ እንደሆነ በሕጉ ተደንግጓል፡፡ ሰራተኛው ስለጠየቀው ክፍያ አለመግባባት የተፈጠረ እንደሆነ አሰሪው በአንቀጽ 36 በተመለከተው ሰባት ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ ያመነውን ያህል ሊከፍለው እንደሚገባ በአዋጁ አንቀጽ 37 ሥር ተመልክቷል፡፡ ክፍያው ከአሰሪው ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር በአዋጁ አንቀጽ 36 ከተመለከተው የመክፈያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተፈፀመ አሰሪው ክፍያውን ላዘገየበት ጊዜ እስከ ሶስት ወር ለመድረስ የሚችል ደመወዙን ለሰራተኛው እንዲከፍለው ዳኞች ሊወስኑ እንደሚችሉ በአዋጁ አንቀጽ 38 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህ ችሎትም በመዝገብ ቁጥር 44405 ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ አሰሪው ሰራተኛውን ያላስረከበው ንብረት አለ ወይም አጉድሏል በሚል ምክንያት ሰራተኛው በሚጠይቃቸው ክፍያዎች ሊጠይቅ አይችልም የሚል የአሰሪው ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲል ወስኗል፡፡ ከላይ በሕጉ የተመለከተው የስራ ውል ሲቋረጥ ከደመወዙ የተያያዙ ክፍያዎች በሰባት ቀናት መከፈል ያለባቸው ስለመሆኑ ነው፡፡ ክፍያው ሊዘገይ የሚችለው ሰራተኛው ያላስረከበው ንብረት ካለ ወይም ሂሳብ በማወራረድ ላይ ሰራተኛው በራሱ ጥፋት ካዘገየው ለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ 1ኛ፣3ኛ እና5ኛ ተጠሪዎች ለአመልካች የምንከፍለው ዕዳም ሆነ የሚመልሱት ንብረት የለብኝም የሚል መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካች 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በስራ ላይ እያሉ የማጭበርበርና የማታለል ተግባር በመፈፀማቸው ከስራ መሰናበታቸውን አስረድቷል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች ደምዳሜ ከመያዙ ውጪ ከእነዚህ ተጠሪዎችም ሆነ ከ5ኛ ተጠሪ የሚፈልገው ዕዳ ያለው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ከሶ ያስፈረደባቸውና መጠኑንም በትክክል የተለየ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ማስረጃዎች ያለመረጋገጡን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ 5ኛ ተጠሪ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በመቅረታቸው ከስራ ስለመባረራቸው ከመረጋገጡ ውጪ የሚያዚያ ወር 2007 አስራ ሶስት ቀናት ደመወዝ በሕጉ አግባብ ከስራ በመቅረታቸው የተቆረጠ እና ዘግይቷል ሊባል የማይችል መሆኑን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ተጠሪዋ ደመወዝ

ተቀጥተው እያለ ከስራም ተሰናብተዋል የሚለው ክርክርም አንድ ላይ የማይሄድ በመሆኑ ለእኚህ ተጠሪ የዘገየ ደመወዝ ስለሌለ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የለም ብሎ ለመደምደም የሚቻልበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡ በአጠቃላይ የዘገየ ክፍያ አለ ተብሎ አመልካች የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍል በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም፡፡

<u>**ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u> አንድ ሠራተኛ ሊመደብበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑና አለመሆኑን ለመመዘን ለሙከራ ጊዜ ሊቀጥር እንደሚችል፤ይህ የግራ ቀኙ ስምምነትም በጽሑፍ መደረግ እንዳለበት፤ የሙከራ ጊዜውም ከ45 ተከታታይ ቀናት መብለጥ እንደሌለበት ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(1) ፣(2) እና (3) አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ የሙከራ ጊዜ ቅጥር ሲፈፀም ሰራተኛው በግልጽ ሊያውቀው የሚገባው ጉዳይ ሲሆን የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ስምምነት ከተደረሰም ስምምነቱ በጽሑፍ ሁኖ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ የተደረገ የሙከራ ጊዜ ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ አሰሪው ሰራተኛውን ለተቀጠረበት የሥራ መደብ ተስማሚ አለመሆኑን ካላመነበት የቅጥር ውሉን ያለምንም ማስጠንቀቂያ የማቋረጥ መብት ሕጉ የሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አሰሪው ይህንኑ በሕጉ የተቀመጠውን መብቱን ሊጠቀም የሚችለው አሰሪው ሰራተኛውን ለሙከራ ጊዜ ለመቅጠር ወስኖ ሰራተኛውም ይህንኑ በግልጽ አውቆትና ተገንዝቦት በፅሑፍ ያሰፈሩት ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ ብቻ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች 4ኛ ተጠሪን የሙከራ ጊዜ ከማለቁ በፊት ስለማባረሩ ገልጾ ቢከራከረም ለሙከራ ጊዜ የቀረጠራቸው ስለመሆኑና በዚህ ረገድም ተጠሪ የሚያውቁት ውል መኖሩን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች አላረጋገጡም፡፡ ስለሆነም አመልካች 4ኛ ተጠሪ ለሙከራ የተቀጠሩ በመሆኑ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የማቋረጥ መብት አለኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 11(3) ስር የተቀመጠውን ድንጋጌ ሙሉ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ 4ኛ ተጠሪ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚያስችል ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆኑ አመልካች ገልጾ ያቀረበው ክርክርም በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የሥር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ክፍያ ለዘገዩት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈልም ሆነ ስለ 4ኛ ተጠሪ ስንብት ሕገ ወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36፣ 38 እንዲሁም አንቀፅ 11(3) ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ከክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡበት ፍሬ ነገሮች ጋር ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበትን የሕግ አግባብ ስለሌለ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት  አልተፈጸም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 99812 በ10/05/2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.172555 በ20/07/2008 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. የዚህ ችሎት ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

በ24/08/08 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ቅ/ሀ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 151474

መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-ቦሰት የሕጻናትና ቤተሰብ በጎ አድራጎት ድርጅት ጠበቃ ዴሬሳ በዳዳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዓለም ሽመልስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/1996 “ን” መሰረት አድርጎ የተነሳ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምስራቅ ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የቅነሳ እርምጃው የተወሰደው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28፣29 (3) እና 42 የተመለከተውን ስርዓት ተከትሎ አለመሆኑ እና ድርጅቱ በ2002 ዓ.ም. ባወጣው የሰው ኃይል መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የመስሪያ ቤቱ ቦርድ ሳያጸድቀው መሆኑ ስለተረጋገጠ እርምጃው ሕገወጥ ነው፣ ሕገወጥ ስንብት የሚያስከትላቸውን እና ተያያዥ ክፍያዎችን አመልካች ለተጠሪዋ ሊከፍል ይገባል በማለት በመዝገብ ቁጥር 867/01/2008 በ29/07/2009 ዓ.ም.የሰጠው እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 258827 በ21/02/2010 ዓ.ም.እና በመዝገብ ቁጥር 273765 በ16/04/2010 ዓ.ም. በተመሳሳይ

ሁኔታ በፍርድ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የመታየቱን አግባብነት፣ቅነሳው የተከናወነው ሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም መሰረት በማድረግ ሆኖ ሳለ ስንብቱ ሕገወጥ ነው የመባሉን አግባነት፣የህክምና ወጪ ከኢንሹራንስ ድርጅት ለተጠሪዋ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት እና ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው እያለ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት እንዲከፈል የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29 (3) እንዲሁም የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ ከሆነው አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ (2) (ሰ) እና በመዝገብ ቁጥር 98676 ከተሰጠው የሰበር ችሎት ገዥ ውሳኔ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. የቅነሳ እርምጃው የተከናወነው አግባብነት ባላቸው የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት አድርጎ አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
3. ያልተከፈለው የሕክምና ወጪ ታስቦ አመልካች ለተጠሪዋ ሊከፍል ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
4. ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው እያለ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ (2) (ሰ) ድንጋጌን እና በዚህ ረገድ የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ የሚጻረር ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር በመዝገቡ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 377 1996 "ን" መሰረት አድርገው የሚነሱ የስራ ክርክር ጉዳዮች የሚታዩት እንደየጉዳዩ ዓይነት በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታዩት በአዋጁ አንቀጽ 138 (1) ስር ከፊደል (ሀ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩት እና ሌሎች ተመሳሳይ የግል የስራ ክርክር ጉዳዮች መሆናቸውን እና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ የሚታዩት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 142 (1) ከፊደል (ለ) እስከ (ሽ) የተዘረዘሩት እና ሌሎች ተመሳሳይ የወል የስራ ክርክር ጉዳዮች መሆናቸውን የተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 147 (1) (ሀ) ድንጋጌ ያመለክታሉ።በሁለቱ ድንጋጌዎች ስር ከተመለከቱት የግል እና የወል የስራ ክርክር ዓይነቶች አንዳንዶቹ በስያሜም ሆነ በይዘት የመመሳሰል ባህርይ ያላቸው በመሆኑ የትኛው ክርክር በግል፣የትኛው ደግሞ በወል የስራ ክርክር ስር እንደሚወድቅ መለየቱ በተግባር ሲያስቸግር ይታያል።ከዚህም በመነሳት እና አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የግል የስራ ክርክርን ከወል የስራ ክርክር ለመለየት ስለሚያስችሉ መስፈርቶች በመዘርዘር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ.18180 በ29/11/1997 ዓ.ም. እና በሌሎችም በርካታ መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው።በዚህ አስገዳጅ የህግ ትርጉምም ሕጉ የስራ ክርክር ጉዳዮችን የወል ወይም የግል ብሎ ለመለየት የተከራካሪ ሰራተኞችን ቁጥር እንደመስፈርት መወሰድ እንዳለበት የማያመለክት መሆኑ፣አንድ የስራ ክርክር የወል ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑ፣አንድን የስራ ክርክር ጉዳይ የግል የስራ ክርክር የሚያደርገው ደግሞ ጉዳዩ ከግል አልፎ በጋራ መብት ላይ የሚያስከትለው ውጤት የሌለ በሆነ ጊዜ መሆኑ እና መሰል ጉዳዮች በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡

በሌላ በኩል በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር ከሚወድቁ ጉዳዮች አንዱ የሰራተኞች ቅነሳ ጉዳይ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142 (1) (ሽ) እና አንቀጽ 147 (1) (ሀ) ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል።ይህ ማለት ግን ከቅነሳ ጋር የተያያዘ ማናቸውም ጉዳይ በቦርዱ የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም።በቦርዱ የስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ

ነው ለማለት የሚቻለው ከላይ በተጠቀሰው የሰበር ገዥ ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ የወል ባህርይ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዋ ለክሳቸው ምክንያት ካደረጓቸው ነጥቦች አንዱ ተጠሪዋ በሕመም ፈቃድ እና ቀጥሎም በወሊድ ፈቃድ ምክንያት በስራ ላይ ሳልነበሩበት ጊዜ የስራ አፈጻጸማቸውን ሞልቶ ለቅነሳው መሰረት በማድረግ አመልካች ድርጅት የዘረጋው የቅነሳ ስርዓት ተገቢነት የለውም የሚል መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ይህ ደግሞ የድርጅቱ ሰራተኞች በተለያዩ ምክንያቶች በስራ ገበታ ላይ ባልነበሩበት ጊዜ በሌላ አነጋገር ስራ ባልሰሩበት ጊዜ የስራ አፈጻጸማቸውን በመሙላት አመልካች ድርጅት ለቅነሳ ተግባር ሊጠቀምበት ይችላል ወይም አይችልም? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ጉዳዩ በቀረበለት አካል በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የሚሰጠው ውሳኔ በተጠሪዋ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በሌሎችም ሰራተኞች መብት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ክርክሩ የወል ባህርይ እንዲኖረው የሚያደርግ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ በቦርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር የማይወድቅበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡በመሆኑም ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ድርጅት የቅነሳ እርምጃውን የወሰድኩት የ30% በ70% ቀመር በትክክል ተገባራዊ እንዳደርግ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ኤጀንሲ በተሰጠኝ መመሪያ መሰረት ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም ይህንን የክርክር ነጥብ በማስረጃ ማስደገፍ ያልቻለ መሆኑ፣የቅነሳ እርምጃው የተከናወነውም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29 (3) የተመለከቱትን ግልጽ መስፈርቶች መሰረት በማድረግ አለመሆኑ፣ይልቁንም ተጠሪዋን ከስራ ያሰናበተው በሕመም ምክንያት ለረዥም ጊዜ በስራ ላይ ያልነበሩ መሆኑን በስንብት ደብዳቤው ላይ በመግለጽ መሆኑ፣በተጠሪዋ ላይ የስንብት እርምጃ የወሰደውም ተጠሪዋ ስራ ላይ ባልነበሩበት ጊዜ የተሞላላቸውን የስራ አፈጻጸም ውጤት ጭምር በመጠቀም መሆኑ በቦርዱ የተረጋገጡ እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ያገኙ ፍሬ ነገሮች መሆናቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካቹም በዚህ ረገድ በሰበር አቤቱታው ላይ ያቀረበው የማስተባበያ

ክርክር የለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የወሰደው እርምጃ ሕጋዊ ሊሆን አይችልም፡፡በመሆኑም የቅነሳ እርምጃው የተከናወነው አግባብነት ባላቸው የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት አድርጎ አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ለተጠሪዋ እና ለቤተሰባቸው አባላት የህክምና ወጪ አመልካች በጥቅል የገባውን የመድን ሽፋን ብር 7,000 /ሰባት ሺህ/ ተጠሪዋ እና የቤተሰባቸው አባላት ተጠቅመው ያጠናቀቁ ስለመሆኑ የመድን ሽፋን ከሰጠው ድርጅት በተጻፈ ደብዳቤ ተረጋግጦ እያለ አመልካች ለተጠሪዋ ተጨማሪ የህክምና ወጪ እንዲተካ ውሳኔ የተሰጠው አለአግባብ ነው በማለት ሲሆን ቦርዱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ሳይቀበሉ የቀሩት በግራ ቀኙ መካከል ባለው ውል መሰረት አመልካች የብር 7,000 /ሰባት ሺህ/ የህክምና ወጪ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ለተጠሪዋ እና ለቤተሰባቸው አባላት በጥቅል ሳይሆን በነፍስ ወከፍ ነው በማለት ነው፡፡አመልካች የመድን ሽፋን ከገባበት የገንዘብ መጠን ብር 7000 /ሰባት ሺህ/ ውስጥ ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ለተጠሪዋ በግል የብር 4,236 /አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት/ የህክምና ወጪ የተተካላቸው መሆኑ እና ቀሪው ብር 2,764 /ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ አራት/ የህክምና ወጪ የተተካው ደግሞ ለተጠሪዋ የቤተሰብ አባላት መሆኑ በተጠሪዋም ያልተካደ ሲሆን በቦርዱ ውሳኔ መሰረት አመልካች ለተጠሪ መተካት የሚጠበቅበት የህክምና ወጪ ብር 2,764 /ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ አራት/ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካች በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት ውስጥ ለተጠሪዋ እና ለቤተሰባቸው አባላት በጥቅል ሳይሆን በነፍስ ወከፍ የብር 7,000 /ሰባት ሺህ/ የህክምና ወጪ የመሸፈን ግዴታ የተጣለበት በየትኛው ደንብ እና ድንጋጌ መሰረት እንደሆነ ለይተው በመጥቀስ ተጠሪዋ በሰበር መልሳቸው ላቀረቡት ክርክር አመልካቹ በመልስ መልሱ የሰጠው ማስተባበያ የለም፡፡አመልካች ድርጅት ለተጠሪዋ እና ለቤተሰባቸው አባላት በጥቅል የብር 7,000 /ሰባት ሺህ/ የመድን ሽፋን መግባቱ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል መሰረት ያደረገ ካልሆነ ደግሞ ልዩነቱን እራሱ የመሸፈን የውል ግዴታ ይኖርበታል፡፡በመሆኑም ያልተከፈለው የሕክምና ወጪ ታስቦ አመልካች ለተጠሪዋ ሊከፍል ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

አራተኛውን እና የመጨረሻውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆናቸው ተረጋግጦ እያለ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ  አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ (2) (ሰ) ድንጋጌን እና በዚህ ረገድ የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በማለት ነው፡፡እንደተባለው የስራ ውሉ በሕገ ወጥ መንገድ የተቋረጠበት ሰራተኛ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 39 ( 1) (ለ) በተመለከተው መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ካላቸው ሰራተኞች ወስጥ የሚካተት ቢሆንም የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ በተደራቢነት የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንደማይኖረው የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 494/1998 በአንቀጽ 2 (ሰ) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት  ሰበር ችሎት አግባብነት ያላቸውን የሁለቱን አዋጆች ድንጋጌዎች አገናዝቦ በመተርጎም የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የማይኖረው ስለመሆኑ ቀደም ሲል በቀረቡ ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ በመዝገብ ቁጥር 35197፣37048 እና በሌሎችም መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆናቸው ያልተካደ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ እና የሰበር ገዥ ውሳኔ መሰረት የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የማግኘት መብት የማይኖረው መሆኑን ተቀብለው ነገር ግን ለተጠሪዋ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈል የወሰኑት አመልካች ድርጅት ለተጠሪዋ በጻፈው የስንብት ደብዳቤ ላይ ከፕሮቪደንት ፈንድ በተጨማሪ  የስራ ስንብት ክፍያ እንደሚከፈላቸው የገለጸ መሆኑን መሰረት በማድረግ እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ውሳኔው አዋጁን እና የሰበር ገዥ ውሳኔን የሚጻረር ነው በሚል በጥቅሉ ከመከራከር በቀር የስንብት ደብዳቤው አነጋገር እና ይዘት ከላይ የተገለጸው ስላለመሆኑ አመልካች በሰበር ደረጃ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር የለም፡፡

አመልካች በአስረጂነት ጠቅሶ የሚከራከርባቸው የአዋጁ ድንጋጌ እና የሰበር ገዥ ውሳኔዎች ደግሞ አሰሪው የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ለሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የመክፈል ግዴታ እንደሌለበት የሚያመለክቱ ከመሆናቸው በቀር አሰሪው በራሱ ፍላጎት የስራ ስንብት ክፍያውን በተደራቢነት እንዳይከፍል የሚከለክሉ

አይደሉም፡፡አመልካች የስንብት ክፍያው በተደራቢነት እንደሚከፈል ክርክር ከመጀመሩ በፊት በስንብት ደብዳቤው ላይ በግልጽ ፈቅዶ እያለ ተጠሪዋ ክስ ካቀረቡ በኃላ የስራ ስንብት ክፍያው ሊከፈል የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ ያቀረበው ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር የስራ ስንብት ክፍያው እንዲከፈል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ከላይ የተጠቀሰውን አዋጅ እና የሰበር ገዥ ውሳኔ የሚጻረር ነው በማለት በደፈናው የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው እያለ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ (2) (ሰ) ድንጋጌን እና በዚህ ረገድ የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ የሚጻረር ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር በመዝገቡ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ በመዝገብ ቁጥር 867/01/2008 በ29/07/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 258827 በ21/02/2010 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 273765 በ16/04/2010 ዓ.ም. በተመሳሳይ ሁኔታ በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በምስራቅ ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ በመዝገብ ቁጥር Mr/290/01/2009/3 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ26/04/2010 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡
3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁ. 132280

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ/ም

**ዳኞች**:- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ሰናይት አድነው

**አመልካች**:- 1. አቶ አስቻለው አስማማው }የቀረበ የለም

2. አቶ አሸናፊ ሲርባሞ

**ተጠሪ**:- የደቡብ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች በሀዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ሕዳር 24 ቀን 2008 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ:- ከተጠሪ ጋር ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ የመሰረቱትን የስራ ግኙነት አመልካቾች ከጳጉሜ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ በጡረታ በመገለላቸው ምክንያት የተቋረጠ ቢሆንም ለጡረታ መብታቸው የተያዘላቸው የአገልግሎት ዘመን ከሐምሌ ወር 1988 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ ያለው ብቻ መሆኑን ገልፀው ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም ድረስ በተጠሪ ድርጅት ለአገለገሉበት ጊዜ የስራ ስንብት ካሳ ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካቾች ጋር የተደረገው የስራ ውል የተቋረጠው እድሜአቸው ለጡረታ ደርሶ መሆኑንና አመልካቾችም በጡረታ የወጡና የመብቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሰራተኞች መሆናቸውን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች በጡረታ የተገለሉና የጡረታ መብት ተጠቃሚ ሁነው እያለ ከ1969 ዓ/ም

ጀምሮ እስከ ሐምሌ 1988 ዓ/ም ድረስ ለአገለገሉበት ጊዜ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ሕጋዊ አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል:: የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ ለበርካታ አመታት አግልግሎት የሰጡ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለና ለዘላቂ የጡረታ መብት የተያዘው አገልግሎታቸውም ከሐምሌ 1988 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ብቻ ሁኖ እያለ አመልካቾች ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሀምሌ 30 ቀን 1988 ዓ/ም ድረስ ለዘላቂ ጡረታ ላልተያዘላቸው ጊዜ ያቀረቡት የስራ ስንብት ክፍያ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በጡረታ የወጡ ሰራተኞች መሆናቸውን፣ ከተጠሪ ጋር ያደረጉት የስራ ውልም ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም ድረስ የኮንትራት የስራ ውል በመሆኑ ይኼው ጊዜ ለጡረታ መብት አከባበር እንዲያዝላቸው ስልጣን ለአለው አካል አቅርበው ተቀባይነት ያጡና በስርዓቱም መሰረት በይግባኝ ወይም በሰበር ያልተለወጠ መሆኑን፣ ከሐምሌ ወር 1988 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2007 ዓ/ም መጨረሻ ያለው ጊዜ ለጡረታ መብታቸው ተይዞላቸው ከጳጉሜ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ ከተጠሪ መስሪያ ቤት በጡረታ በመገለል የጡረታ መብትም ወዲያውኑ ተጠቃሚ የሆኑ መሆናቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ የስራ ውል ከህግ ውጪ መቋረጡ ከሚያስከትላቸው ሕጋዊ ውጤቶች አንዱ የሥራ ስንብት ክፍያ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር

377/96 አንቀጽ 43 (4) ከተቀመጠው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ የስራ ውል በሕግ አግባብ ከተቋረጠ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከሕጉ ቅርጽና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር ያልተካደው ወይም የተረጋገጠው አመልካቾች ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም ድረስ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የሥራ ውል ግንኙነት በኮንትራት ላይ የተመሰረተ መሆኑና ይህ ጊዜ ለጡረታ መብት አከባበር ለአመልካቾች እንዲያዝላቸው ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ አመልካቾች አቅርበው አገልግሎታቸው ለጡረታ አይያዝላቸውም ተብሎ ውሳኔ ማግኘቱንና በበላይ የዳኝነት አካልም ያለመለወጡን ነው፡፡ አመልካቾች የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄውን ያቀረቡት በጡረታ ተገልለው የመብቱ ተጠቃሚነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ስለመሆኑም ያልተካደ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ የክፍያ ጥያቄውን ከሥር ጀምሮ ሲቃወም የመጣውም አመልካቾች መደበኛ የጡረታ ዕድሜ የደረሱና የጡረታ አበልም የሚከፈላቸው ናቸው፣ ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ደግሞ የኮንትራት ውል የነበረበት ከመሆኑም በላይ ተጠሪው ሕጋዊ ሰውነቱን ያላገኘበት ጊዜ ነው በማለት ነው፡፡

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 "ን" ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ.494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ እና /ሸ/ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 39 እንደተደነገገው የሥራ ስንበት ክፍያ የሚከፈለው ሠራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ከሆነ እንደዚሁም ሥራውን ሲለቅ መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ያልደረሰ ሲሆን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ሥራቸውን የጡረታ መውጫ እድሜያቸው ደርሶ መብቱም ተከብሮላቸው በሕግ አግባብ የተሰናበቱ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 43 (4) እና ከማሻሻያ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ እና /ሸ/ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካቾች ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም የአገለገሉት ጊዜ የኮንትራት ጊዜ ነው ተብሎ ለጡረታ መብት ሊያዝላቸው አይገባም በሚል ዳኝነት በተሰጠበትና አመልካቾች የጡረታ መብት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ መደበኛ የጡረታ ዕድሜም ደርሰው የመብቱ ተጠቃሚ መሆናቸው ጭምር በተረጋገጠበት አግባብ ለጡረታ መብት ላልተያዘላቸው ጊዜ የሥራ ስንብት ካሳ ሊከፈለን ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን ነው፡፡  በመሆኑም አመልካቾች

የስራ ስንብት ክፍያ የሚያገኙበት የሕግ አግባብ የለም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02989 ታህሳስ 08 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19216 የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 67526 በ04/12/08 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 1988 ላለው ጊዜ የስራ ስንብት ካሳ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 136571

መስከረም 29 ቀን 2010ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- እድገት ተስፋ ሁለገብ ሽ/ኃ/የተ/የህ/ሥ/ማህበር - የስራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ታመነ መኮንን ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቦዬ ለሜሳ/ባለቤታቸው አቶ ሐይሉ አስፋውና ወራሾች እነ አሉላ ሀይሉ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሥር ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ጋር ከሐምሌ 28 ቀን 1978 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 11 ቀን 2008 ዓ.ም በተለያዩ የስራ መደቦች 1,300.00/አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ እየተከፈላቸው ሲሰሩ እንደነበረ ነገር ግን አመልካች ከሚሰሩበት የነበረ የስራ መደብ ሳይፈልጉ በማንሳት ፤ምክንያቱ ሳይነገራቸው፤የውድድር ስርዓት ሳያደርጉ፤የተመደቡት የስራ መደብ ለማታ ስራ የማይመችና ሞያቸው ወዳልሆነ የስራ መደብ የስራ ዝውውር ደብዳቤ የሚገልፅ ደብዳቤ የደረሳቸው መሆኑን፤በዚሁ ምክንያት

ዝውውሩ ላይ ቅሬታ አቅርበው እያሉ አመልካች የስራ ውሉ ያለአግባብ ስላቆረጠብኝ የካሳ፤የስራ ስንብት ክፍያ፤ ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ዝውውሩን ያደረገበት ምክንያት ተጠሪ የተዛወሩበት የስራ መደብ ላይ ለረጅም አመታት የሰሩበት እንደሆነ እስከ ምሽቱ 4:00 ሰዓት የሚያሰራው የመዝናኛ ክበቡ የስራ ባህሪ መሆኑን ፤የተጠሪ ዋናው ምክንያታቸው ትምህርት ስለምማር አይመቸኝም የሚል መሆኑን፤ስራ እየሰሩ ምላሽ መጠበቅ ሲችሉ ከ14/03/08 ዓ.ም እስከ 11/04/08 ዓ.ም ስራ ትተው ቤታቸው መቀመጣቸው ትክክል እንዳልሆነ ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄም ጡረታ የሚዋጣላቸው በመሆኑ ሊከፈላቸው እንደማይገባ በመግለፅ የመከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ተጠሪ የተመደቡት በሙያቸው መሆኑን፣ የተመደቡት የስራ መደብ ለህይወታቸው አስጊ አለመሆኑን፤ተጠሪ ወደተመደቡበት ስራ ሄደው አለመስራታቸው፤በትምህርት ምክንያት ዝውውሩን የሚቃወሙ ስለመሆኑ እንደማያሳይ፤ ተጠሪ ቅሬታ አቅርበው ከስራ መቅረታቸው፣ ከስራ የቀሩበት በበቂ ምክንያት ነው የሚያስብል አለመሆኑን በምክንያትነት ጠቅሶ ተጠሪ ከ5 ተከታታይ ቀናት በላይ ከስራ መቅረታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ለ/ መሰረት ስንብቱን ህጋዊ ያደርገዋል፤በተጠሪ የተጠየቁት ክፍያዎች የህግ ድጋፍ የሌላቸው ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት እንዲሰሩ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን፤ተጠሪ ላቀረቡት ቅሬታ ምላሽ ጠብቅ ሲባሉ ወደስራ ገበታቸው ያልገቡት ተጠሪ ላይ ጫና በሚያሳድር ሁኔታና መብታቸውን ባላከበረ መልኩ በመሆኑ ከስራ ገበታቸው ያለበቂ ምክንያት ቀርተዋል አያሰኝም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ስንብቱ ህገወጥ ነው፤ ስለሆነም የህገወጥ ስንብት ውጤት ክፍያዎቹ በተመለከተ የግራ ቀኙን ማስረጃ በማየት ውሳኔ እንዲሰጥበት ለስር ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 12 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው

አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሐምሌ 21 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ መስጠት መብታቸው በመታለፉ የቀረበ የመልስ መልስ የለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከግራ ቀኙ ክርክርና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ነጥብ በጉዳዩ ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ይሰሩበት ከነበረው የስራ መደብ ወደሌላ የስራ መደብ የተዛወሩ መሆናቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ እንደደረሳቸው ስራው በምሽት የሚሰራ በመሆኑ ለህይወታቸው አስጊ እንደሆነና ሌሎች ምክንያቶች በመግለፅ እንዲስተካከል አቤቱታ አቅርበው ምላሽ በመጠባበቅ እያሉ ከ5 በላይ ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ ቀርተዋል በማለት አመልካች የስራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን ከውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በመሰረቱ የስራ ውል ሊቋረጥ የሚችልባቸው መንገዶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 23 ስር ተመልክቷል፡፡ አንደኛው መንገድ በአሰሪው አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ እንደሁኔታው በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊደረግ የሚችል ሆኖ የምክንያቶቹ ዝርዝር እና አፈፃፀሙ ከአንቀፅ 26 እስከ 30 ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በሕብረት ስምምነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይም በአሰሪው አነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 27/1/ተ/ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በአዋጁ በተደነገጉ ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚፈፀም የስራ ውል ማቋረጥ ህጋዊ የስራ ማቋረጥ ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረጉ የስራ ውል ማቋረጥ ህገወጥ መሆኑን ከአንቀጽ 42 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአመልካችና ተጠሪ መካከል የተደረገው የስራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት መብትና ግዴታ ያቋቁማል፡፡ በህጉ አንቀጽ 12 የአሰሪው ግዴታ በአንቀጽ 13 ደግሞ የሰራተኛው በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ህገወጥ ድርጊት የተባሉት

የአሰሪና ሰራተኛ ቅደም ተከተል በአንቀጽ 14/1/ እና 14/2/ በዝርዝር ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ የአሰሪው ግዴታ ከተገለፁት ከስራው ጋር በተያያዘ የሰራተኛውን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች ሁሉ የመውሰድና እነዚሁንም እርምጃዎችን በሚመለከት ረገድ አግባብ ባላቸው ባለስልጣኖች የሚሰጡትን ደረጃዎች መመሪያዎች የመከተል በአሰሪው ላይ የተጣለ ግዴታ ነው፡፡ በሌላ በኩል አሰሪውና ሰራተኛው ህገወጥ ድርጊት ተብለው ከተገለፁት ውስጥ በህጉ አንቀጽ 14/1/ሠ/ በአሰሪው ሰራተኛውን በህይወቱ ላይ አደጋ ሊያደርስበት በሚችል አኳኋን እንዲሰራ ማድረግ ህገወጥ ድርጊት መሆኑን የተመለከተ ነው፡፡ አሰሪው ግዴታው ካልፈፀመና ህገ ወጥ ድርጊት መፈፀሙ ከተረጋገጠ ሰራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ማቋረጥ በቂ ምክንያት ይሆናል በማለት በአንቀጽ 32/1/ለ ይደነግጋል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ ደግሞ ሰራተኛው በአዋጁ መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን ከአሰሪው የማግኘት መብት አለው፡፡ ስለሆነም ከላይ እንደተጠቀሰው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች አድራጎት የተጠሪን ህይወት ለአደጋ ያጋለጠ ስለመሆኑ አረጋግጧል፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ የሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 117169 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2/1/ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍ/ቤትን የማስገደድ ኃይል ያለውን ህግ ትርጉም ስጥቷል፡፡

ለዚህም አመልካች ዝውውሩን ተግባራዊ ያደረገው ትራንስፖርት አገልግሎት የማሟላት ግዴታውን ሳይወጣ ስለመሆኑ በማረጋገጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57101 መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 173539 ታህሳስ 14 ቀን 2009 ዓ/ም በመሻር የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ከዚህ ፍርድ ቤት ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮ/ቀ/ ምድብ ችሎት በመ/ቁ.74378 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**አ/ጕ**

ሰ/መ/ቁ.140677

ህዳር 22 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ ጌቱ ጠበቃ ተፈሪ ፅጌ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት አ/ማ ሰራተኛ ማሕበር የቀረበ የለም ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሥር ከሳሽ የአሁን አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በአስተዳደር ሙያ ስራ ተቀጥረው በወር 1712.00 /አንድ ሺህ ሰባት መቶ አስራ ሁለት ብር/ እየተከፈላቸው ኤ/አ/16/5/2014 ጀምሮ በካምቲን አስተዳደር ኃላፊ የስራ መደብ ተቀጥረው ሲሰሩ ፈቃድ እንዲወጡ ተደርጎ ከ04/04/16–13/04/16 በፈቃድ ቆይተው ሲመለሱ በብትድ/ሠ/መማ/ካ/04/07/16 በተፃፈ ደብዳቤ ከ14/04/16 ጀምሮ የስራ ውሉ ከህግ ውጭ እንዲቋርጥ በማድረጉ የስራ ስንብት ክፍያ፤የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፤የካሳ ክፍያ፤የዓመት እረፍት የመሳሰሉት አመልካች እንዲከፍል ተብሎ እንዲወሰንላቸው ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበው ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም

በቀረበው መቃወሚያ መሰረት አመልካች የስሪ መሪ በመሆናቸውን የቀረበው ክስ በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት ብይን ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሚያዚያ 13 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በታዘዘው መሰረት ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከግራ ቀኙን ክርክርና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ነጥብ አመልካች የስራ መሪ ናቸው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

የአመልካች ጥያቄ በተጠሪ ድርጅት በአስተዳደር ስራ ከመቀጠር በስተቀር አንድ የአስተዳደር ኃላፊ መስራት ያለበትን እንደ ሰራተኛ መቅጠር፣ማሰናበት እድገት መስጠት መቅጣት ስራዎችን ማከናውን የሚያስችል ስልጣን ባልተሰጠበት ሁኔታ ስራ መሪ የሚያስብል ምክንያት ባለመኖሩ አመልካች በአስተዳደር ስራ መደብ በመስራቱ ብቻ የስራ መሪ አያሰኝም፣በስር ፍርድ ቤቶች የስራ መሪ ነህ ለማለት የቻሉት በቀን 4/4/14 ለወ/ሮ እታገኝ እንድሪስ የጻፍኩትን መነሻ እንደሆነ በብይኑ ላይ ገልጸ አስቀምጦታል፣ ነገር ግን የዚህ ዓይነት ሌላ የአስተዳደር ስራ እንዲሰራ ተጠሪ ባላስረዳበት በዚህች ድብዳቤ መነሻ ብቻ የስራ መሪ ነህ በማለት የተሰጠ ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ የአመልካች ቅጥር ደብዳቤ የስራ መሪ መሆኑን ያስረዳል፣ እንዲሁም የአስተዳደር ኃላፊ፣ የክበቡ ዋና መሪ ፣የሰራተኞች አስተዳዳሪ

ቀጣሪም፣ አሰናባችም፣ ማስጠንቀቂያ ሰጪም የክበቡ የምግብ ዝግጅትና መሪ፤ በአጠቃላይ ለክበቡ ከአሁን አመልካች በቀር የመጨረሻ ባለስልጣን የለም ፣ መሪውና አስተዳዳሪው አመልካች በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ሐ/ መሰረት ውሳኔ መስጠታቸው ባግባቡ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሠረቱ የሥራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደ የድርጅቱ የስራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣት የማስፈፀም ከነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚሁን ሣይጨምር ሠራተኛን የመቆጣጠር የማዛወር፣ የማገድ፣ ለማሰናበት የመመደብ ወይም የስነ-ስርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወስን ግለሰብ ስለመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ቁ. 377/96 3/2/ /ሐ/ ስር እና በማሻሻያ አዋጁ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ /ሐ/ ሥር ተመልክቷል፡፡

አመልካች በአስተዳደር ሙያ ስራ የተቀጠሩ ስለመሆናቸውና ለወ/ሮ እታገኝ እንድሪስ ማስጠንቃቂያ መፃፋቸውን ሳይክዱ በአዋጁ እንደተመለከተው የስራ መሪ ተግባራትን ስለማከናወናቸው በተጠሪ የቀረበ ማስረጃ የለም፤ለአንድ ሰራተኛ ማስጠንቀቂያ በመጻፉ ብቻ የስራ መሪ አያሰኝም ከማለት ውጭ ክበቡን የሚያስተዳድረው፣ ሰራተኞች የሚቀጥረው፤ የሚያሰናብተው የማን እንደሆነ ፤የስራ ግንኙነታቸው ከማን እንደሆነ ፤እና ስለ ክበቡ አደረጃጀት /መዋቅር/ የገለጹት ነገር የለም፡፡ የአስተዳደር ኃላፊ፣ የክበቡ ዋና መሪ፣ የሰራተኞች አስተዳዳሪ ቀጣሪም፣ አሰናባችም፣ ማስጠንቀቂያ ሰጪም፣ የክበቡ የምግብ ዝግጅትና መሪ፣ በአጠቃላይ ለክበቡ ከአሁን አመልካች በቀር የመጨረሻ ባለስልጣን የለም፣ መሪውና አስተዳዳሪው አመልካች መሆናቸው ተገልፆ በተጠሪ ለቀረበው ክርክርም አመልካች ግልፅ የሆነ ማስተባበያ በመልስ መልሳቸው ያላቀረቡ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ለአንድ ሰራተኛ ማስጠንቀቂያ በመጻፉ ብቻውን የስራ መሪ ተብሎ ይገመታል በማለት የያዙት ምክንያት ለጉዳዩ በቂ ባይሆንም አመልካች የስራ መሪ ስለሆኑ ጉዳያቸው በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ ግን

ከላይ ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61790 ሰኔ 15 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 173709 ጥር 16 ቀን 2009 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 140461

መስከረም 29 ቀን 2010ዓ.ም

**ዳኞች፡**

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሡናይት አድነው

**አመልካች፡** አቶ ንጉሴ ዘርይሁን **-ቀረቡ**

**ተጠሪ፡** የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን **-ወኪል አልቀረቡም**

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

**ጉዳዩ፡** የስራ ክርክርን ይመለከታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 044/09 ጥር 30 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 138065 መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይህንኑ ፍርድ በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

በመዝገቡ ከተያያዙት የውሳኔ ግልባጮች መረዳት እንደሚቻለው የአሁኑ ተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ከድሲፕሊን ኮሚቴው የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተመልክተው አመልካች ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ ባልታወቀ ምክንያት በስራ ገበታ ላይ አልተገኙም በማለት ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው እንዲቋረጥ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ቅሬታውም በአጭሩ ከተጠሪ ፍቃድ ወስጄ እረፍት ላይ እያለሁ የጫማ ኢንፌክሽን እና የቁርጭምጭሚት ውልቃት ደርሶብኝ በህክምና ላይ መሆኔን አሳውቂ ተጠሪም እስከ ህዳር 30 ቀን 2007ዓ.ም ድረስ ደመወዝ

የከፈለኝ እና በህመሜም ምክንያት የመ/ቤቱን ማስታወቂያ መከታተል የማልችል መሆኔ እየታወቀ ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሌ እንዲቋረጥ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ቢያዘውም ባለመቅረቡ የመከራከር መብቱ ታልፎ የይግባኝ ባይን ክርክር ሰምቶ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የስራ ስንብት ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምሮ አመልካች ከደረሰባቸው የጫማ ኢንፌክሽን እና የቁርጭምጭሚት ውልቃት አዳማ ሆስፒታል ታክመው ከህዳር 3/2007 እስከ ሚያዝያ 30/2007ዓ.ም ድረስ በህክምና ፍቃድ ላይ የነበሩ መሆናቸው፣ ሰኔ 2 ቀን 2007ዓ.ም ቁርጭምጭሚታቸው በብሎን ታስሮ እስከ ታህሳስ 6 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ በህክምና ክትትል ላይ የነበሩ መሆኑን፣ ነሀሴ 10 ቀን 2008ዓ.ም በተጻፈ አመልካች የስኳር ታማሚ እና በሶዶ ሆስፒታል ለ3ኛ ጊዜ ቀዶ ህክምና የተደረገላቸው እና በአዳማ ሆስፒታል በክትትል ላይ የሚገኙ መሆናቸውን እና መጋቢት 1ቀን 2008ዓ.ም እና ሚያዝያ 3ቀን 2008ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ከደረሰባቸው የጤና መታወክ የተሻላቸው መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ወደ ስራ እንዲያሰማራቸው ለተጠሪ የጠየቁበት ደብዳቤ እና ተጠሪ ሰኔ 2ቀን 2007ዓ.ም የጻፈላቸው የስንብት ደብዳቤ ግንቦት 23/2008ዓ.ም የደረሳቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የስራ ውል ለማቋረጥ ምክንያት ያደረገው አመልካች በስራ ገበታቸው አልተገኙም በማለት ታህሳስ 27/2007 እና ጥር 7/2007 ተደጋጋሚ ማስታወቂያ በማውጣት ሰኔ 2/2007 ዓ.ም በተጻፈ ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሉ መቋረጡን የገለጸበት ደብዳቤ ግንቦት 23/2008ዓ.ም እንዲደርሳቸው በማድረግ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት አትቶ እና የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 42/5ን ጠቅሶ አመልካች በህክምና ላይ የነበሩ መሆናቸውን ለተጠሪ እንደገለጹ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 42(3) መሰረት ለመጀመሪያዎቹ 3 ወራት ከሙሉ ደሞዝ ጋር፣ ለቀጣዩ 3 ወራት ከግማሽ ደሞዝ ጋር፣ ለመጨረሻዎቹ 2 ወራት ያለ ደሞዝ ተጠሪ ፍቃድ መስጠት ያለበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከስራ ገበታቸው ከቀሩበት ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ 8 ወር ሲቆጠር እስከ ነሀሴ 16 ቀን 2007ዓ.ም ድረስ ተጠሪ አመልካችን የመጠበቅ ግዴታ ነበረበት በማለት ደምድሞ ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ አመልካች በነበራቸው የህክምና ፍቃድ

ምክንያት ለመጀመሪያዎቹ 3ወራት እና ቀጥሎ ላሉት 3 ወራት በአዋጁ መሰረት ክፍያ እንዲፈጽም፣ አመልካች የጠየቁት የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ላልተሰራ ጊዜ የሚከፈል አይደለም በማለት ውድቅ በማድረግ አመልካች ወደስራ ልመለስ ጥያቄንም በተመለከተ አመልካች ወደስራ ልመለስ በማለት ጥያቄ ያቀረቡት መጋቢት 1/2008ዓ.ም ሲሆን በአዋጁ መሰረት የአመልካች የስራ ውል ከሚቋረጥበት ነሀሴ 17/2007ዓ.ም በኃላ በመሆኑ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጠ፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሚያዝያ 10/2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት ባልጠየቀው ዳኝነት አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የኔን አቤቱታ ብቻ መርምሮ መወሰን ሲገባው ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

ቅሬታቸው ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ውሳኔው እንዲፀና በመጠየቅ መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የጽሁፍ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ክርክሩ በተመራበት ሥርዓትም ሆነ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ስለመኖር አለመኖሩ መርምረናል፡፡

የአመልካች ቀዳሚ ቅሬታ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት የኔን ክርክር ብቻ መርምሮ መወሰን ሲገባው ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሲሆን አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ማጣራት አድረጎ የወሰነ በመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም እንዲባል ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ የድሲፒሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳቡን ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርበው ተገቢውን ማጣራት አድርጎ የምርመራውን ሙሉ ይዘት የሚያመልክት የምርመራ ሪፖርት በማዘጋጀት ስለመሆኑና፤ የምርመራው ውጤት የተከሳሹን ጥፋተኝነት የሚያረጋግጥ ከሆነ የውሳኔ ሃሳቡ ሊወሰድ የሚገባውን የቅጣት እርምጃ

ማመልከት እንደሚኖርበት፤ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች የዲስፕሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ለመደንገግ ከወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 77/1994 አንቀፅ 19 እና 49 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም በስር አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ክርክር ተጠሪ ቀርቦ ያልተከራከረ ቢሆንም አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚመረምረው የዲሲፕሊን ኮሚቴው ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር አንጻር የሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን እና ያለመሆን ጋር በማገናዘብ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 347 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ተጠሪ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ቀርቦ ባይከራከርም ለዲሲፕሊን ኮሚቴው ክስ አቅርቦ ያስወሰነው እሱ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ክርክር በኮሚቴው ውሳኔ ላይ ተያይዞ እንደሚገኝ አጠያያቂ ካለመሆኑም በተጨማሪ ይህንን አስመልክቶ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት በተመለከተ የፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 42(5) መሰረት ሰራተኛው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት እስካላጋጠመው ድረስ መታመሙን ለመ/ቤቱ ማሳወቅ እንዳለበት፣ በዚህ መልኩ መታመሙን ላሳወቀ የሙከራ ጊዜውን ለጨረሰ ሰራተኛ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 42(2) መሰረት ህመሙ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ባሉ ተከታታይ 12 ወር ውስጥ ለ8 ወራት ፍቃድ ሊሰጥ እንደሚገባ እና በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3)ላይም ለመጀመሪው የ3ወር ጊዜ ከሙሉ ደሞዝ ጋር ለሚቀጥለው 3 ወር ጊዜ ከግማሽ ደሞዝ ጋር ለተከታዩ 2 ወር ያለደሞዝ ፍቃድ ሊሰጥ እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 79(1) ላይ በዚህ ጊዜ ውስጥ ወደ ስራ ለመመለስ ያልቻለ ሰራተኛ በህመም ምክንያት የስራ ውሉ ሊቋረጥ እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በህመም ምክንያት ስራ ለመግባት ያለመቻላቸውን ለመ/ቤቱ ካሳወቁበት ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ ህጉ እስሚፈቅደው 8ወር ጊዜ ድረስ በደሞዝ እና ያለደሞዝ ፍቃድ ሊሰጣቸው የሚገባ በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያልተከፈላቸው ደሞዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ከወሰነ በኃላ የአመልካች ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄያቸው የቀረበው መጋቢት 1 ቀን 2008ዓ.ም ሲሆን የ8 ወር ጊዜው የሚያበቃው ነሀሴ 16 ቀን 2007ዓ.ም በመሆኑ ጊዜው ካለፈ በኃላ ያቀረቡት ወደስራ ልመለስ አቤቱታ በህጉ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሰኔ እና ይህንን ውሳኔ በትእዛዝ በማጽናት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ነጥብ ሳይኖር ይህ ችሎት የአመልካችን ቅሬታ የሚቀበልበትን መሰረታዊ ምክንያት አላገኘም፡፡

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ይግባኙን በመሰረዝ የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 044/2009 ጥር 30 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 138065 መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ጊዜው ካለፈ በኃላ ያቀረቡት ወደ ስራ ልመለስ አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ በተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

የሰ.መ.ቁጥር 150947

ቀን 12/7/2010 ዓ/ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች - ሚሮና ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠበቃ ታደሰ ገመቹ ቀርቧል

ተጠሪ - ጫልቱ ዓለሙ፣ መሰረት አበራ፣ ብርቱካን ነገዎ እና አልማዝ አበበ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ሚሮና ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ ታህሳስ 16 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273118 ታህሳስ 2 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤት ከሳሾችና ተከሳሽ የተስማማንበት የምርት መጠን ከሳሾች መስራት አንደሚችሉና ሌሎችም ሰራተኞች እየሰሩ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ሳለ ተጠሪዎች ለመስራት እምቢተኛ በመሆናቸው የተሰናበቱ መሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ሆኖ ሳለ ህገወጥ ስንብት ነው ሲል መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በከሳሾች ያልቀረበውን ክርክር ራሳቸው በማንሳት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.182 ድንጋጌ ውጪ ነው፡፡ ከሳሾች እንዲሰሩ የተፈለገው ምርት መጠን በ3 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ብቻ የሚሰሩት ሆኖ እያለ ከአቅማቸው

በላይ ነው ተብሎ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 61(1) ውጪ መወሰኑ አለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር ከሳሽ የአሁን ተጠሪዎች ጫልቱ ዓለሙ፣ መሰረት አበራ፣ ብርቱካን ነገዎ እና አልማዝ አበበ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ. የበረክ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ሚሮና ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከሳሾች ካለጥፋታችን ጥር 29 ቀን 2009 ዓ/ም ከዚህ በፊት ሰርተን የማናውቀውን ከአቅማችን በላይ እንድንሰራ ሲነገረን ከአቅማችን በላይ ነው ስላልን ከስራ ያሰናበተን በመሆኑ ሊከፈለን የሚገቡ ክፍያዎችን ይከፈለን ሲሉ ክስ መስርተዋል፡፡ ተከሳሽም ከሳሾች ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1ረ) መሰረት ስራ ለመስራት ችሎታ እያላቸው የስራው ውጤት በብዛትና በጥራት ላይ ከተስማማነው በታች በመስራታቸው ካለማስጠንቀቅያ ተሰናብተዋል፡፡ ከሳሾች እንደ ድርጅቱ እቅድ የቦልጋም ምርት 8 ዙር ከሬሜላ 11 ዙር እንዲያመርቱ ተስማምተን ሲሰሩ ቆይተው በኂላ አንሰራም በማለታቸው ካለማስጠንቀቅያ መሰናበታቸው ህጋዊ ስንብት በመሆኑ ክሳቸው ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የስር በኦሮሚያ ብ/ክ/መ. የበረክ ወረዳ ፍ/ቤት አራት መዝገቦች የመ/ቁጥር 27507፣ 27548፣ 27506 እና 27509 በአንድ በማጣመር የመረመረ መሆኑን ገልጾ በመ/ቁጥር 27509 ላይ ሰኔ 8 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ ከሳሾች ቦልጋም 8 ዙር ከረሜላ 11 ዙር ሲያመርቱ ቆይተው አንሰራም በማለታቸው ምርት ቀንሶብናል ቢልም ከ2000 ዓ/ም እስከ 2006 ዓ/ም ባሉት ጊዜያት ከ4 እስከ 7 ዙር ምርት ስያመርቱ እንደነበር የተረጋገጠ እንጂ ምርት እየቀነሰ የመጣ አይደለም፡፡ ተከሳሽ ምርት ለመጨመር ከፈለገ ማሽንና ሰራተኛ በመጨመር እንጂ ባለው ሰራተኛ ከአቅም በላይ በማሰራት አይደለም፡፡ ተከሳሽ ከሳሾችን ከአቅማችን በላይ ነው ስላሉ ብቻ ሳያረጋግጥ ከስራ ማሰናበቱ ህገወጥ ነው፡፡ ለከሳሾች ሊከፍል ይገባል ያለውን በማስላት እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ ከሳሽ የአሁን አመልካች ለፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ የፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 29694 አከራክሮ መስከረም 25 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ አሰሪው ማምረት ያለበት ምርት ኮታ ማውጣት፣ ለማምረት የሚያግዙ ዘመናዊ መሳሪያዎችን ማመቻቸት ብቻ ሳይሆን ከሚፈለገው ምርት ጥራትና መጠን በታች የሚሰራ ሰው ካለ የተለያዩ

ስልጠና በመስጠት ምርታማነት መጨመር እያለበት ሌሎች ቡድን ስላመረቱ ብቻ ከሳሾችም ማምረት አለባቸው በሚል ከከሳሾች የቀረበውን ሀሳብ ባለመቀበል ከሳሾችን ከስራ ማሰናበቱ ህገወጥ የስራ ስንብት ነው መባሉ ባግባቡ ሲሆን ከሳሾች ሁሉም የጡረታ ዋስትና ተጠቃሚ መሆናቸው ተረጋግጦና ከሳሾችም ያልካዱ ሆኖ እያለ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ስህተት ነው ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ክፍያውን አስተካክሎ ወስኗል፡፡ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን አቅርቦ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273118 አከራክሮ ታህሳስ 2 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ከሳሾች ተከሳሽ እንደሚለው 8 ዙር ቦልጋም እና 11 ዙር ከረሜላ ሰርተው እንደማያውቁ እየተከራከሩ ሲሆን በስር ፍ/ቤትም የተሰሙት የግራ ቀኙ ምስክሮች ይህንኑ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ከሳሾችን ከአቅማቸው በታች ሰርተዋል በማለት ከስራ ማሰናበቱ ማስረጃ ያልተደገፈና የህግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት አይደለም ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ ተጠሪዎች በመደበኛ የስራ ሰዓታቸው ምርቱን በማሳደግ እንዲሰሩ በአመልካች የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ከአቅማችን በላይ ነው በማለት ለመስራት ፍቃደኛ አለመሆናቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የወሰኑበት አግባብ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 13(2) እና 27(1) አንጻር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ጥር 4 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት ያቀረብነውን ክስ በማስረጃ አጣርቶ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት ተተርጉሞ የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ ስህተት ያለበት አይደለም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ጥር 24 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር

መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ተጠሪዎች እንዲሰሩ የሚፈልገውን 8 ዙር ቦልጋም እና 11 ዙር ከረሜላ መጠንና ጥራት ምርት ካሁን በፊት ተጠሪዎች አምርተው እንደማያውቁ እንድያውም የምርት መጠኑን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉ የመጡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪዎች ይህን 8 ዙር ቦልጋም እና 11 ዙር ከረሜላ መጠንና ጥራት ምርት ማምረት ስለመቻላቸው በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ሰራተኞች በሙሉ እውቀታቸውና ብቃታቸው ሰርተውም እኩል የምርት ጥራትና መጠን ያመርታሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ አንደኛው ሰራተኛ ባመረተው ምርት መጠንና ጥራት መነሻነት ሌላውን ከአቅም በታች ሰርቷል ለማለት በቂ መሰፈርት አይሆንም ፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከአቅማቸው በታች መስራታቸው ባለማረጋገጡና ባላቸው እውቀትና ብቃት እያመረቱ ካለው ምርት በላይ እንዲያመርቱ በመጠየቃቸው እንዲያመርቱ የተጠየቁትን ምርት ለማምረት የሚቸገሩ መሆኑን በማሳወቃቸው የአሁን አመልካች ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑ ህገወጥ የስራ ስንብት እንደሆነ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273118 ታህሳስ 2 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ታህሳስ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የበረህ ወረዳ ፍ/ቤት የአፈጻጸም መ/ቁጥር 28532 የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የስር ፍ/ቤት እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሳቸው ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

# የንግድ ሕግ

የሰ/መ/ቁ. 139385

መጋቢት 12 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ መዋዕል ትኩዕ መርሻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ ነገረፈጅ ፌቨን ቢኒያም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ከአክሲዮን ሽያጭ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ነው፡፡ የአሁን አመልካች /የሥር ከሳሽ/ ሰኔ 3 ቀን 2007 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ማኀበር /ለአሁን ተጠሪ/ አክሲዮን የመግዛት ፍላጎት እንዳላቸው አሳውቀው ተከሳሹም አክሲዮኖቹን ለመሸጥ የሚፈልግ አለ መጥተው መግዛት ይችላሉ በማለት ባደረገላቸው ጥሪ መሠረት ጥር 12 ቀን 2006 ዓ/ም የማኀበሩ አባል ከሆኑት ከአቶ ሰባጋዲስ ስዩም 3949 አክሲዮኖችን በመግዛት ብር 120,904.80 /አንድ መቶ ሃያ ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም/ መክፈላቸውን፣ አቶ ሰባጋዲስ ስዩም እና ከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ ባዘጋጀው የማዘዋወሪያ የውል ሰነድ ላይ ተፈራርመው ተከሳሽም በራሱ ማኀተም በማጽደቅ ዝውውሩን መመዝገቡን ገልጸው ተከሳሽ ማኀበር በ2006 ዓ/ም ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያከፋፈለውን ትርፍ ጨምሮ ሰርተፊኬት ላይ አስፍሮ እንዲሰጣቸው በቃልም ሆነ በጽሁፍ ቢጠይቁም ይህንን ለመፈጸም ፈቃደኛ ስላልሆነ

ተከሳሽ በአክሲዮን ማዘዋወሪያ የውል ሰነድ ላይ በራሱ ማኅተም ያጸደቀው የአክሲዮን ሽያጭ ከገዙዋቸው ግለሰብ በማስተላለፍ ወይም ከሚሸጣቸው አክሲዮኖች ላይ በመቀነስ መዝግቦ ሰርተፊኬት እንዲሰጣቸው ወይም አክሲዮኑን ለመግዛት ያወጡትን ገንዘብ ማግኘት ከነበረባቸው ትርፍ ክፍያ ጋር ብር 173,022.22 /አንድ መቶ ሰባ ሶስት ሺህ ሃያ ሁለት ብር ከሃያ ሁለት ሳንቲም/ ከነወለዱ እንዲከፍላቸው፣ ወጪና ኪሳራን እንዲተካ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ /የሥር ተከሳሽ/ ሰኔ 25 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ከሳሽ ያቀረቡት ማስረጃ የአክሲዮን ማስተላለፊያ ጥያቄ የሚቀርብበት ማመልከቻ ነው፣ ተከሳሽ ማኅበር የአክሲዮን ዝውውሩን አልመዘገበም፣ ለከሳሽም የሰጠው ማረጋገጫ የለም፣ ተከሳሽ ማኅበር በህጉ መሠረት ለመመዝገብ እና ለጠቅላላ ጉባዔ ለማቅረብ ሲያጣራ የሻጩ አክሲዮኖች ከሳሽ አክሲዮኖቹን ከመግዛታቸው በፊት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የታገደ በመሆኑ ዝውውሩ ሊፈጸም አልቻለም፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት 1ኛ/ ተከሳሽ ማኅበር ለከሳሽ ለ3949 አክሲዮኖች የአክሲዮን ሠርቲፊኬት ለከሳሽ ሊሰጥ ይገባል ወይስ አይገባም? 2ኛ/ የአክሲዮን ሠርተፊኬቱን የመስጠት ኃላፊነት የለበትም የሚባል ቢሆን ከሳሽ የጠየቁትን ክፍያ ተከሳሽ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሯል፡፡ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ጥር 12 ቀን 2006 ዓ/ም የተደረገው የአክሲዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፊያ ማመልከቻ ሠነድ ነው፡፡ በዚህ ሰነድ (መ) እና (ሠ) ሥር ዝውውሩን ያፀደቀው አካል ዝውውሩን ተቀብሎ የመዘገበው ሰው ስም እና ፊርማ ያረፈ፣ የተከሳሽ ማኅበር ማኅተም ያረፈበት ቢሆንም ይህ ሰነድ ግን በንግድ ህግ ቁጥር 331 /1/ እና 341 /2/ ሥር በአዛዥ ሁኔታ የተቀመጠውን በባለአክሲዮኖች መዝገብ የመመዝገብ ግዴታን የሚተካ ወይም ቀሪ የሚያደርግ አይደለም፡፤ በማመልከቻ ሰነዱ ላይ ዝውውሩ ፀድቋል ወይም ተመዝግቧል መባሉ ብቻውን ተከሳሽ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ከሳሽን በመመዝገብ ባለአክሲዮን አድርጓል የሚያስብል አይደለም፡፡ እነዚህ ተሸጡ የተባሉት አክሲዮኖችም ከሽያጭ ውሉ በፊት እንዳይሸጡ የእግድ ትዕዛዝ ከተሰጠባቸው ተከሳሽ ይህን ሁኔታ በመተላለፍ በአክሲዮኖች መዝገብ ዝውውሩን

መመዝገብ ግዴታ አለበት ሊባል አይችልም፡፤ ከሳሽ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ካልተመዘገቡ ደግሞ ተከሳሽ የአክሲዮን ሰርተፊኬት እንዲሰጥ የሚገደድበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ተከሳሽ የራሱን አክሲዮኖች ለመሸጥ ባልተስማማበት ሁኔታም ሌላ አክሲዮን በምትኩ እንዲሰጥ የሚጠየቅበትም ሆነ የሚገደድበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ከሳሽ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም በማለት ወስኗል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከሳሽ አክሲዮኖቹን ለመግዛት ገንዘቡን የከፈሉት ለአቶ ሰባጋዲስ ስዩም ሲሆን እነዚህ ክፍያ የተፈጸመባቸው አክሲዮኖች የእግድ ትዕዛዝ ያለባቸው በመሆኑ ዝውውሩ ሊፈጸም አልቻለም፣ ይህ ከሆነ ደግሞ ክፍያውን እንዲከፍል መጠየቅ የሚቻለው ክፍያውን የወሰደውን አካል እንጂ ተከሳሽ ባለአክሲዮኑ በህጉ በተሰጠው መብት መሠረት አክሲዮኖችን ለመሸጥ በመጠየቁ ሁኔታዎቹን ስላመቻቸ ብቻ  ክፍያውን ባልተቀበለበት ሁኔታ የሌላውን ሰው ኃላፊነት የሚወስድበት አግባብ የለም፣ ከዚህ በተጨማሪ የትርፍ ክፍያ ተከሳሽ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ባለአክሲዮን መሆኑ ለተረጋገጠ ሰው እንጂ እንዲሁም የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ እንዲከፍል ሊጠይቅ አይችልም፡፡ በመሆኑም ከሳሽ የጠየቁትን ክፍያ ተከሳሽ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ ሊከፍል አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈጽሞብኛል ያሉዋቸውን ቅሬታ ነጥቦችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪዎች አክሲዮኖች ለአመልካች ሊሸጡ የቻሉት ተጠሪ ባደረገው ጥሪ መነሻ ከመሆኑ አንጻር የሥር ፍርድ ቤቶች አክሲዮኖቹ እገዳ የነበረባቸው ናቸው በማለት ተጠሪን ከኃላፊነት ነፃ ማድረጋቸው መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ነሐሴ 1 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን የአመልካች ጠበቃም ጥቅምት 13 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን 1ኛ/ አመልካች ለገዙባቸው አክሲዮኖች ተጠሪ ሠርተፊኬት ሊሰጥ ይገባል ወይስ አይገባም? 2ኛ/ ሠርቲፊኬት ሊሰጥ አይገባም የሚባል ከሆነ አመልካች የከፈሉትን ገንዘብ ከነወለዱ ተጠሪ ሊመልስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉ ጭብጦች ተይዘው ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ተጠሪ ባደረገው ጥሪ መሠረት የአቶ ስባጋዲስ ስዩም አክሲዮን ድርሻ መግዛታቸውን ሲከራከሩ ተጠሪ ደግሞ በግለሰቦች የተያዙ የአክሲዮን ድርሻዎችን በተመለከተ ባለአክሲዮኖች መሸጥ በሚፈልጉበት በራሳቸው የሚያመጡትን የገዢ ማመልከቻ ተቀብሎ እና መርምሮ ለአጽዳቂ አካል ከማስተላለፍ ውጪ ገዢ እና ሻጭ የማገናኘትም ሆነ የማደራደር ሥራ እንደማይሰራ፣ ብሔራዊ ባንክ የሰነዶችና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የሚያጣራውን የምዝገባ ሥርዓት ተጠሪ ባንክ በውክልና እንዲሰራ በመመሪያ በሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት ተጠሪ ባንክም አቶ ስባጋዲስ ስዩም ከተባሉት የባንክ ባለአክሲዮን እና የአሁን አመልካች ተስማምተው በተጠሪ ጽ/ቤት በመቅረብ የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ ቅጽ ሞልተው ለተጠሪ ባንክ ሲያቀርቡ የተቀበለ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ይህንን መከራከሪያ ብሔራዊ ባንክ ለባንኮች ታኅሳስ 20 ቀን 2001 ዓ/ም በቁጥር ሱዳ/ባሱመ/382/08 ካስተላለፈው መመሪያ አንጻር ተመልክተናል፡፡

በዚህ መመሪያ በግልጽ እንደተቀመጠው የተጠሪ የሥራ ድርሻ የሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት የሚያከናውነውን የማጣራት ሥራ በውክልና ማከናወን ነው፡፡ በመመሪያው የአክሲዮን ዝውውርን በተመለከተ በቁጥር 3 ሥር ከንዑስ ቁጥር 3.1.እስከ ንዑስ ቁጥር 3.6 የተቀመጠው ማናቸውም የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻዎች ለተጠሪ ባንክ በሚቀርቡበት ወቅት በተለይም በተራ ቁጥር 3.2 ላይ እንደተገለጸው የአክሲዮን ማኅበራቱ የአክሲዮን ዝውውር ጥያቄውን ተቀብለው በንግድ መዝገብ ላይ ከመመዝገባቸው እና ለ3ኛ ወገን ከማሳወቃቸው በፊት ማጣራት የሚገባቸውን ቅድመ

ሁኔታዎችን ማጣራት እና ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአሁን አመልካች እና በአቶ ስባጋዲስ ስዩም መካከል ጥር 12 ቀን 2006 ዓ/ም የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ ተፈርሞ ለአሁን ተጠሪ ባንክ ሲቀርብለት ሰነዱን ፈርሞ እና ማኅተም አድርጎ መቀበሉን ተጠሪ አይክድም፡፡ ተያይዞ ከቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ እንደተመለከተነው የቀረበውን የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻን መሠረት በማድረግ ባንኩ ማጣሪያ ሲያደርግ የአክሲዮን ዝውውር እንዲደረግ የቀረበው የአቶ ስባጋዲስ ስዩም የአክሲዮን ድርሻ በ2004 ዓ/ም ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተሰጠ እግድ ትዕዛዝ የታገደ መሆኑን ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም ይህንን ለአመልካች ያሳወቀ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ይህንን የአሁን አመልካችም ክደው አልተከራከሩም፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአክሲዮን ባለቤትነት የማጽደቅ ሥልጣን የጠቅላላ ጉባኤው እንጂ የተጠሪ ባንክ እንዳልሆነ በህግ የተደነገገ ነው፡፡ የአክሲዮን ባለቤትነት የሚመዘገበውም በጠቅላላ ጉባኤው ከፀደቀ በኃላ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተፈጸመ ስለመሆኑም አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ የአመልካች መከራከሪያ መሠረት የሚያደርገው የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻውን ተጠሪ ተቀብሎ በራሱ ፊርማና ማኅተም አረጋግጧል የሚል ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር በተመለከተ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው አመልካችና አቶ ስባጋዲስ ሥዩም ተፈራርመው ያቀረቡት የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ የተጠሪ ባንክ አክሲዮን ማህበር ማኅተም ያረፈበት ቢሆንም ይህ ሰነድ ግን በንግድ ህግ ቁጥር 331 /1/ እና 341 /2/ ሥር በአዛዥ ሁኔታ የተቀመጠውን በባለአክሲዮኖች መዝገብ የመመዝገብ ግዴታን የሚተካ ወይም ቀሪ የሚያደርግ አይደለም፡፤ በአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ ሰነዱ ላይ ዝውውሩ ፀድቋል ወይም ተመዝግቧል መባሉ ብቻውን ተጠሪ በባለአክሲዮኖች መዝገብ አመልካችን በመመዝገብ ባለአክሲዮን አድርጓል የሚያስብል አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ለአመልካች የአክሲዮን ባለቤትነት ሠርተፊኬት ለመስጠት የሚገደድበት ህጋዊ ሁኔታ የለም በማለት በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከላይ በአንደኛው ጭብጥ በዝርዝር እንደተገለጸው በተጠሪ አክሲዮን ማኅበር ውስጥ ባለድርሻ የሆኑት አቶ ስባጋዲስ ስዩም እና አመልካች ተፈራርመው ያቀረቡትን የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻን ተጠሪ ሲያጣራ ከኢትዮጵያ

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተጻፈው እግድ ምክንያት አክሲዮኑ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ የማይችል በመሆኑ የማጣራት ሂደቱን ባለማለፉ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ባልተወሰነበትና ባልፀደቀበት፣ በንግድ ህጉ መሠረት ምዝገባ ባልተደረገበት እንዲሁም ክርክር የቀረበበት ገንዘብ ለተጠሪ ባንክ ስለመሰጠቱ ወይም ገቢ ስለመደረጉ ማረጋገጫ ባልቀረበበት አመልካች የጠየቁትን ክፍያ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ ሊከፍል አይገባም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የወሰነውን ውሳኔ ስንመለከተው የሚነቀፍበት ምክንያት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለልም የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ በዝርዝር የተገለጹትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ በማጤን የሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ.228396 በ13/4/2008 ዓ/ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.176245 ጥር 1 ቀን 2009 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ 348 /1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች የአክሲዮን ምስክር ወረቀት ሊሰጥ አይገባም፤ አመልካች የጠየቁትን ክፍያ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰበር መዝገብ ቁጥር 127352

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡-

1. አቶ ታደሰ አይችሉህም
2. አቶ ደሳለኝ አስራደ
3. አቶ ንጉሴ አማረ
4. አቶ መስፍን በጋሻው

} የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-አቶ ዘውዴ ታደሰ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአክሲዮን ማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄን አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካቾቹ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18932 በ09/06/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67288 በ13/08/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪው በ19/04/2008 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ እንደቀደም ተከተላቸው 1ኛ፣2ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች በነበሩት የአሁኖቹ አመልካቾች እና የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ

ባልተደረጉት አቶ አባስ መሐመድ እና አቶ ገደፋው ጌጡ በተባሉ የስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረቡት ከሳሽ እና ተከሳሾች በጋራ በመሆን የትምህርት ተቋማትን የማቋቋም ዓላማ ያለው አክታ ጠቅላላ ንግድ አክሲዮን ማህበር በመስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ማቋቋማቸውን፣በዚሁ መሰረትም ማህበሩ አክታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍቶ በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ መሆኑን፣ማህበሩን በስራ አኪያጅነት የሚመሩትም ከሳሽ መሆናቸውን፣በማህበሩ እንቅስቃሴ ላይ ለመወያየት ከሳሽ በተደጋጋሚ ስብሰባ ቢጠሩም ተከሳሾቹ ለመገኘት ፈቃደኛች ሳይሆኑ መቅረታቸውን እና በትምህርት ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ ምክንያት ከሳሽ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው በነበረበት ጊዜ እንኳ ተከሳሾቹ ስለጉዳዩ ቀርበው ያልጠየቁ መሆኑን እና እነዚህ ሁኔታዎችም  በንግድ ሕጉ መሰረት ማህበሩን ለማፍረስ በቂ ምክንያት መሆናቸውን በመግለጽ ማህበሩ እንዲፈርስ እና አስተዳዳሪ ተሾሞለት ሂሳቡ እንዲጣራ እንዲደረግ እንዲወሰንላቸው በመጠየቅ ነው።

የስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች በ10/05/2008 ዓ.ም.በሰጡት መልስ የከሳሹ ጥያቄ የእነርሱም ጥያቄ በመሆኑ በክሱ መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለጹ ሲሆን የአሁኖቹ አመልካቾች በበኩላቸው በ17/05/2008 ዓ.ም. በሰጡት መልስ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው በማህበሩ ላይ እንጂ በእኛ በአባላቱ ላይ አይደለም፣ከሳሽ በተከሳሾቹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የላቸውም የሚሉ የመቃወሚያ ነጥቦችን ካስቀደሙ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ስብሰባ የመጥራት ስልጣን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንጂ የከሳሹ አለመሆኑን፣ከሳሹ ስብሰባ ለመጥራት የሚያስችል ስልጣን ነበራቸው ቢባል እንኳ በሕጉ አግባብ ያከናወኑት ጥሪ አለመኖሩን፣የስብሰባ አለመደረግም ሆነ በቁጥጥር ስር ሲውል አልጠየቃችሁኝም በማለት ከሳሹ በክሱ የጠቀሷቸው ምክንያቶች በንግድ ሕጉ መሰረት አንድን ማህበር ለማፍረስ የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች አለመሆናቸውን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል።

ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦችን በብይን አልፎ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ክሱን ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አክሲዮን ማህበሩ ከተመሰረተበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተካሄዶ እንደማያውቅ በተከሳሾቹ ያልተካደ መሆኑን፣እነዚህ ምክንያቶች ደግሞ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ14፣በንግድ ሕግ ቁጥር 217

(2)፣218 (2) እና 495 (3) መሰረት ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች መሆናቸውን፣3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾችም በክሱ መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለጹ መሆኑን በዝርዝር አስፍሮ አክሲዮን ማህበሩ ትምህርት ቤት ከሚዘጋበት ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲፈርስ፣አስተዳዳሪ እንዲሾም እና ንብረቱ እንዲጣራ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡በአሁኖቹ አመልካቾች ጠያቂነት ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በፍርድ ያጸናው ይህንኑ ውሳኔ ሲሆን አመልካቾቹ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አክሲዮን ማህበሩ ባልተከሰሰበት የማህበሩ አባላት ተከሰው ማህበሩ እንዲፈርስ የመወሰኑን አግባብነት ከንግድ ሕግ ቁጥር 495 ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለመመርመር እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪው በ19/04/2008 ዓ.ም.ባቀረቡት ክስ ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችል ነው በማለት የጠቀሷቸው ምክንያቶች ተጠሪው በማህበሩ ስራ አስኪያጅነታቸው ባደረጉት ጥሪ መሰረት የማህበሩ አባላት በስብሰባ ለመገኘት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀርተዋል፣ ከማህበሩ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ተጠሪው በስራ አስኪያጅነታቸው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው በነበረበት ጊዜ የማህበሩ አባላት ቀርበው ስለጉዳዩ አልጠየቁም፣ዋስትና ለመግባትም ፈቃደኛነታቸውን አልገለጹም የሚሉ መሆናቸውን፣ማህበሩ ከተመሰረተበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተከናውኖ አያውቅም የሚሉት ምክንያቶች በተጠሪው በኩል የቀረቡት በክስ ማመልከቻው ላይ ተገልጸው ሳይሆን ክሱ በተሰማበት ጊዜ በተደረገ ክርክር መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤቶችም ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች ናቸው በማለት የተቀበሉት ክሱ በተሰማበት ጊዜ በተጠሪው በኩል የቀረቡትን ምክንያቶች መሆኑን፣ማህበሩ ከተመሰተረበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የተደረገ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አለመኖሩ በአመልካቾቹ ያልተካደ መሆኑን

እና ይሁን እንጂ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ማህበሩ ያቋቋመው ትምህርት ቤት የስራ እንቅስቃሴ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በሆኑት ተጠሪ አማካይነት ሲከናወን የቆየ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የንግድ ሕጉ በአንድ በኩል ለሁሉም ዓይነት የንግድ ማህበራት ተፈፃሚነት ያላቸውን የማፍረሻ ምክንያት ያካተተ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ ዓይነት ንግድ ማህበር ካለው የተለየ ባህሪ አንጻር ለየማህበሩ ተፈጻሚ የሚሆኑ ተጨማሪ የማፍረሻ ምክንያቶችን አካቶ ይዞአል፡፡በንግድ ሕጉ ስለ ንግዱ ማህበራት በጠቅላላው በሚናገረው ክፍል ከሚገኙት ቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች በተጨማሪ የአክሲዮን ማህበራት የሚፈርሱባቸው ምክንያቶች በንግድ ሕጉ በቁጥር 495 (1) ስር ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡እነርሱም፡-

(ሀ) በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማኅበሩ እንዲቀጥል ካልተወሰነ በቀር በመመስረቻ ጽሁፍ የተወሰነው ጊዜ ሲደርስ፣

(ለ) ማህበሩ የተቋቋበት ስራ ሲያልቅ፣

(ሐ) በነገሩ መጥፋት ወይም የማህበሩ ጉዳይ (ዓላማ) ሊደረስበት የማይቻል ሲሆን፣

(መ) አስቀድሞ እንዲፈርሱ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ፈቅዶ ሲወስን፣

(ሠ) ከማህበረተኞቹ አንዱ ባቀረበው በቂ ምክንያት ማህበሩ እንዲፈርስ ፍርድ ቤቱ ሲያዝ

(ረ) በቁጥር 311 የተደነገጉት ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው አክሲዮኖቹ ሁሉ በአንድ ማህበረተኛ እጅ ሲጠቃለሉ፣

(ሰ) የኪሳራ ክስ ሲጀመር እና

(ሸ) ከማህበሩ ዋና ገንዘብ ሶስቱ ሩብ ሲጠፋየሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው ካቀረቡት ክስ አንጻር ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ለጉዳዩ አግባብነት ያለው “ከማህበረተኞቹ አንዱ ባቀረበው በቂ ምክንያት ማህበሩ እንዲፈርስ ፍርድ ቤቱ ሲያዝ” በሚል የተገለጸው ምክንያት ነው፡፡ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ አክሲዮን

ማህበሩ ባልተከሰሰበት የማህበሩ አባላት ተከሰው ማህበሩ እንዲፈርስ የመወሰኑን አግባብነት ከንግድ ሕግ ቁጥር 495 ድንጋጌ አንጻር ለማጣራት የሚል ነው።አንድ ማህበር እንዲፈርስ ክስ በሚቀርብበት ጊዜ እንደየክርክሩ ባህርይ እና እንደየአስፈላጊነቱ ማህበሩ የክርክሩ ተካፋይ መደረግ እንደሚገባው የሚታመን ቢሆንም ቁጥር 495 ድንጋጌ የማህበሩን የክርክር ተካፋይ መደረግ ጉዳይ አስመልክቶ የሚገልጸው ነገር የለም።በመሆኑም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባው ማህበሩ ከተመሰረተበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የተደረገ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አለመኖሩ የአክሲዮን ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያስችል በቂ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ዓቢይ ነጥብ ነው።ከድንጋጌው አነጋገር እንደሚታየው ከማህበርተኞቹ አንዱ ባቀረበው በቂ ምክንያት ማህበሩ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈርስ እንደሚችል ከመገለጹ በቀር በቂ ምክንያት ተብለው የሚወሰዱትን ሁኔታዎች ድንጋጌው ለይቶ አያመለክትም።በመሆኑም ማህበሩ እንዲፈርስ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ነው በሚል ከማህበረተኞቹ በአንዱ የሚቀርበው ምክንያት በርግጥም በቂ መሆን አለመሆኑ በፍርድ ቤቶች በአግባቡ ሊጤን ይገባል።

በመሰረቱ የንግድ ማህበራት ለአባላቱ ትርፍ ከማስገኘት ዓላማ ባሻገር በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ገንቢ ሚና የሚጫወቱ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።የሕግ ጥበቃም አላቸው።በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የአክሲዮን ማህበር በትምህርት ዘርፍ የተሰማራ መሆኑ እና ትምህርት ቤት በማቋቋም ወደ እንቅስቃሴ የገባ መሆኑም ተረጋግጦአል።ይህም የማህበሩ ሕልውና ጉዳይ በተቀጣሪ ሰራተኞች፣በተማሪዎች እና በአካባቢው የትምህርት እንቅስቃሴ ላይ ጭምር በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ተጽዕኖ የሚኖረው መሆኑን የሚያመለክት ነው።በመሆኑም የማህበሩ መፍረስ አለመፍረስ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ በቀረበ ጊዜ እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ከግምት መግባት የሚገባቸው መሆኑን እና ማህበሩ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚገባው ተከሰተ የተባለውን ችግር ማህበሩ እንዲፈርስ በመወሰን ካልሆነ በስተቀር በሌላ የሕግ አግባብ መፍታት ወይም ማስወገድ እንደማይቻል ሲረጋገጥ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ማህበሩ ከተመሰተረበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የተደረገ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አለመኖሩ

የተረጋገጠ ቢሆንም ማህበሩ ያቋቋመው ትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ግን ስራ አስኪያጁ መደበኛ ባልሆነ መንገድም ቢሆን ከማህበሩ አባላት ጋር በሚያደርጉት ውይይት እየተከናወነ የነበረ መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡ ተጠሪውም በክስ ማመልከቻቸው ስብሰባ ጠርቼ አባላቱ አልተገኙም ከማለት በቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ጠይቀው የነበረ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ጠይቀው ነገር ግን ስብሰባ የመጥራት ስልጣን ያለው የማህበሩ አካል ስብሰባውን ለመጥራት ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ይህ መሆኑ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲከናወን ጥያቄ አቅርቦ ለማስወሰን የሚያስችል ከሚሆን በቀር በቀጥታ ማህበሩ እንዲፈርስ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው አይደለም፡፡ የሀዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርዱ ለይ በጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁጥር 495 (3) ስር የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች የተረጋገጡ ስለመሆኑም መዝገቡ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም ማህበሩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አለመደረግ ጉዳይ በሌላ የሕግ አግባብ ሊፈታ የሚችል ችግር ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤቶች በቀጥታ አክሲዮን ማህበሩን ለማፍረስ እንደሚያስችል በቂ ምክንያት ተወስዶ ማህበሩ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የንግድ ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ እና ማህበሩ የተቋቋበትን ዓላማ እንዲሁም የማህበሩ መፍረስ የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ውጤቶች ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18932 በ09/06/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67288 በ13/08/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሮአል፡፡

2. ማህበሩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ወይም የማህበሩ የጠቅላላ ጉባኤ አለመደረግ በሌላ የሕግ አግባብ ሊፈታ የሚችል ችግር እንጂ በቀጥታ ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪውም ሆኑ የማህበሩ ሌላ አባል የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ወይም የማህበሩ የጠቅላላ ጉባኤ በፍርድ ኃይል እንዲከናወን ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
5. በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18932 የተያዘው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ01/10/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አበለት

መ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 136030

ህዳር 20 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ምስራ መሐመድ፤ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.አቶ አብደላ፤ አሜ ቀረቡ

2 አቶ ፋሃሚ መሐመድ፣ በሌሉበት የታየ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የክርክሩ ምክንያት የአካል ጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ በሆኑበት በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የ1ኛ ተከሳሽ /የአሁን 1ኛ ተጠሪ/ የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 32057 ኦሮ የሆነ በ2ኛ ተከሳሽ /በአሁን 2ኛ ተጠሪ/ ይሽከረከር የነበረ አይሱዙ መኪና በቀን 22/07/2007 ዓ/ም ከተፈቀደለት በላይ በፍጥነት በማሽከርከር ላይ እያለ ከግድግዳ ጋር በመጋጨት ድንጋይ ተፈናጥሮ የቀኝ አይኔ ላይ ጉዳት ስላደረሰብኝ የጉዳት ካሳ እና የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ በድምሩ ብር 71,100.00 /ሰባ አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር/ ተከሳሾች የአሁኖቹ ተጠሪዎች/ እንዲከፍሉ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ /የሥር 1ኛ ተከሳሽ/ መኪናዬ የጭነት እንጂ የህዝብ አይደለም፣ ከሳሽ /የአሁን አመልካች/ በመኪናዬ አልተሳፈረችም በማለት ከተከራከሩ በኃላ መኪናው የሶስተኛ ወገን የኢንሹራንስ ሽፋን ስላለው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጣልቃ እንዲገባ

ጠይቀው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ መኪናው የሶስተኛ ወገን የኢንሹራንስ ሽፋን የሌለው መሆኑን በመግለጹና የሥር 1ኛ ተከሳሽም ማስረጃ ባለማቅረባቸው መድን ከክርክሩ እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን የአሁን 2ኛ ተጠሪም /የሥር 2ኛ ተከሳሽም/ ከሳሽን መጫናቸውን አምነው ጉዳት ግን እሳቸው በሚያሽከረክሩት መኪና እንዳልደረሰ ክደው በመከራከር ኃላፊነት የለብንም ብለዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎች /ተከሳሾች/ ኃላፊነት አለባቸው ብሎዋል፡፡ የጉዳት ካሳን በተመለከተ ግን አመልካች በማስረጃ አላስረዱም በማለት አልፎባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ወጪዎችን በተመለከተ ለህክምና፣ ለትራንስፖርት እንደዚሁም ለተለያዩ ነገሮች ከሳሽ /አመልካች/ ታወጣለች ተብሎ የተገመተ ብር 5,519.00 /አምስት ሺህ አምስት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር/፣ ክስ ለማዘጋጀት፣ ለኮፒ እና ለትርጉም በክርክሩ ምክንያት ታወጣለች ተብሎ የተገመተ ብር 3,500.00 /ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር/፣ ለሞራል ካሳ ብር 1000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 10,019.00 /አሥር ሺህ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ይክፈሉ፡፡ የዳኝነት ክፍያ በተወሰነው ገንዘብ ታሪፍ ልክ ተከሳሾች/ተጠሪዎች/ ለከሳሽ /ለአመልካች/ እንዲከፍሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምሥራቅ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ቀጥለውም አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተዘግቶባቸዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመውብኛል ያሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት አስመልክቶ አግባብነት ያለው ህግ የትኛው ነው? የንግድ ህጉ ነው የሚባል ከሆነም የስሌቱ መጠን ከደረሰው ጉዳት አንጻር ከህጉ ቁጥር 598 (2) አኳያ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ይቅርብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 1ኛ ተጠሪ ቀርበው ግንቦት 7 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ለመቀበል እምቢተኛ ሆነዋል ተብሎ ቃለ መኀላ ስለቀረበ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ ለ1ኛ ተጠሪ መልስ አመልካች በቀን 05/10/2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ መኪና ላይ አልተሳፈሩም በማለት 1ኛ ተጠሪ ክደው ቢከራከሩም በወቅቱ መኪናውን ያሽከረክሩ የነበሩት 2ኛ ተጠሪ አመልካች በመኪናው ላይ ስለመሳፈራቸው አምነው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግራ ቀኙ ምስክሮችም አመልካች በ2ኛ ተጠሪ አማካይነት ይሽከረከር በነበረው በ1ኛ ተጠሪ መኪና ላይ ስለመሳፈራቸው ፣አመልካች በመኪና ላይ እንዳሉ ድንጋይ ዓይኔን መታኝ እያሉ ሲጮኹ እንደነበረ ከአመልካች ጋር አብረው ተሳፍረው ሲጓዙ የነበሩ ምስክሮች መመስከራቸውን ተያይዞ ከቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከድሬ ጮራ ሆስፒታል በቁጥር g/268424 በቀን 19/05/2008 ዓ/ም የተጻፈ የጽሁፍ ማስረጃ የአመልካች የቀኝ ዓይን ብሌን ቦታውን ለቋል፣በቋሚነት 48% ጉዳት ደርሶባታል ሲል ይገልጻል፡፡

የምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ በአመልካች ዓይን ላይ ስለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎችን ኃላፊ አድርጎዋቸዋል፡፡ ለወደፊት የታጣ ገቢ በማለት አመልካች የጠየቁትን ዳኝነት  በተመለከተ ግን ከሳሽ ሥራቸው ምን እንደሆነ፣ እንደዚሁም ጤነኛ ሳሉ በወር ሲያገኙ የነበረው ገቢ ምን ያህል እንደሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ እና የተገለጸ ነገር የለም፡፡ እንደዚሁም ይህ በዓይናቸው ላይ የደረሰው ጉዳት ለወደፊት ሠርተው የሚያገኙትን ገቢ የሚከለክላቸው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነገር የለም በማለት በዚህ በኩል የተጠየቀውን ዳኝነት ውድቅ በማድረግ አልፎባቸዋል፡፡ ለተለያዩ ወጪዎች እና ሞራል ካሳ በድምሩ ብር 10,019.00 /አሥር ሺህ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን የአመልካች ቅሬታ መሠረት የሚያደርገውም የጉዳት ካሳ ሳይወሰን በመታለፉ ምክንያት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ

መሆን አለመሆኑን ከደረሰው ጉዳት እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር መመልከት ተገቢ ነው፡፡

በመሠረቱ ከላይ እንደተገለጸው በአመልካች ዓይን ላይ ጉዳት ስለመድረሱ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎችም ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ተደርገዋል፡፡ ይህ ኃላፊነት ሊታይ የሚገባው ደግሞ በንግድ ህጉ ስለ አጓዡ እና ተጓዡ በተደነገገው ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካች ለመኪናው የትራንስፖርት ክፍያ ከፍለው ሲጓዙ በነበረበት ወቅት ድንጋይ ተፈናጥሮ በዓይናቸው ላይ ጉዳት በማድረሱ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የንግድ ህጉን መሠረት ያደረገና በውል ላይ የተመሰረተ ግንኙት በግራ ቀኙ መካከል ተመስርቷል ማለት ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 561 የማጓጓዝ ውል ማለት አጓጓዥ ዋጋ በመቀበል ሰውን፣ ጓዝንና እቃዎችን የተወሰነ ስፍራ ለማድረስ ግዴታ የገባበት ስምምነት ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የንግድ ህጉ አንቀጽ 595 ደግሞ  አጓዡ ለመንገደኞች ያለበትን ኃላፊነት ያስቀምጣል፡፡ አጓዡ ከኃላፊነት የሚድንባቸው ምክንያቶች በአንቀጽ 596 ላይ የተቀመጡ ሲሆን የአጓዡ ኃላፊነት ከተረጋገጠ በአንቀጽ 599 ላይ የተመለከተው ልዩ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር የንግድ ህግ አንቀጽ 597 /1/ ላይ የተጎዳው ማንኛውም ዓይነት መንገደኛ ቢሆንም አጓዡ በአላፊነት ለአንድ መንገደኛ የሚከፍለው ገንዘብ መጠን ከ40,000.00 ብር /ከአርባ ሺህ ብር/ ሊበልጥ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ዓይን ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎች ኃላፊ መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ በንግድ ህጉ አንቀጽ 561 መሠረት በተመሰረተው በውል ግዴታ፣ በአንቀጽ 595 መሠረት በአጓዡነት ግዴታ መሠረት በአንቀጽ 597 /1/ ላይ የተደነገገውን ገንዘብ መጠን የመክፈል ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ የምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን አመልካች ሥራቸው ምን እንደሆነ፣ ጤነኛ ሳሉ በወር ሲያገኙ የነበረው ገቢ ምን ያህል እንደሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ እና የተገለጸ ነገር የለም፡፡ እንደዚሁም ይህ በዓይናቸው ላይ የደረሰው ጉዳት ለወደፊት ሠርተው የሚያገኙትን ገቢ የሚከለክላቸው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነገር የለም በማለት የደረሰው ድምዳሜ ከላይ የተመለከቱትን የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ባለመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ቀጥሎ ያሉት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይህንን ሳያርሙ ማለፋቸው ሲታይ የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤኑ በአመልካች ዓይን ላይ ለደረሰው ጉዳት ከሳ ሊከፈል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.50296 በቀን 01/07/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 243965 በቀን 23/9/2008 ዓ/ም እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.248800 በቀን 29/2/2009 ዓ/ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች ዓይን ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. ለልዩ ልዩ ወጪዎች እና ለሞራል ካሳ በድምሩ ብር 10,019.00 /አሥር ሺህ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በንግድ ህግ አንቀጽ 561፣ 595 እና 597 /1/ መሠረት 40,000.00 /አርባ ሺህ/ ብር ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
5. ዳኝነት በተወሰነው ታርፍ ልክ ተጠሪዎች ይክፈሉ ብለናል፡፡
6. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

   መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# ከውል ውጪ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 134240

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ፍቃዱ በለጠ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አለሚቱ አድራሮ

2. ህፃን አማኑኤል ታምሩ

3. ህፃን ክብራለም ታምሩ ሞግዚት ወ/ሮ አለሚቱ አድራሮ } የቀረበ የለም

4. ወ/ሮ አሙሬ መሾ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች በአመልካችና 2ኛ ተከሳሽ በነበረው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ላይ ያቀረቡት ክስ የአመልካች ንብረት የሆነው የሴ.ቁ 3-75918 ሲኖትራክ የጭነት መኪና በ03/05/2008 ዓ.ም ከጋምቤላ ወደ ቴፒ አሸዋ ጭኖ በመጓዝ ላይ እያለ በደቡብ ክልል ሸካ ዞን የኪ ወረዳ እርምጫ ቀበሌ ልዩ

ስሙ ጫቲ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ሲደርስ መንገድ ስቶ አቶ ታምሩ ገሊቶ መኖሪያ ቤት ላይ በመውጣት የ1ኛ ተጠሪ ልጅ የሆነውን ተሻለ ታምሩ የተባለውን ሌሊት በተኛበት ገጭቶ የገደለ በመሆኑ ይህ ሟች በግብርናና ንግድ ስራ ተሰማርቶ በሚያገኘው ገቢ ይጦራችን ስለነበረ በመሞቱ ምክንያት የተቋጠረውን ገቢ ለ1ኛ ተጠሪ ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር)፤ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 80,000.00 (ሰማንያ ሺህ ብር) በድምሩ 160,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ ብር) እንዲሁም ወላጅ አባታቸው አቶ ታምሩ ገሊቶም በ40 ዓመት እድሜያቸው በዚህ አደጋ ስለሞቱና ይጦራቸው ስለነበረ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ትምህርታቸውን እስከሚጨርሱ ብር 108,000.00 ( አንድ መቶ ስምንት ሺህ ብር) እና 118,800.0 (አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ብር) ለሁለቱ እንዲከፍሉ፤ 4ኛ ተጠሪ የሟች የአቶ ታምሩ ገሊቶ ወላጅ እናት የሆኑት ሟች ልጃቸው ለመጦሪና ለቀለብ ይሰጣቸው የነበረው ስለተቋረጠ ብር 51,000.00 (ሃምሳ አንድ ሺህ ብር) እሱ በመሞቱ የሞራል ካሳ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) እና ለቀብር ማስፈፀሚያ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) በድምሩ ብር 499,800.00 (አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ብር) 2ኛ ተከሳሽ የጉዳት አድራሹ መኪና ባለቤት ከኢንሹራንስ ሽፋን ሰጭ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር ሆነው ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአመልካችና 2ኛ ተከሳሽ ከነበረው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ተከሳሾቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ተጠሪዎች በርትዕ ብር 236,000.00 (ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ብር) ሊከፈላቸው ይገባል፤ከዚህ ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ ብር) ይክፈለው ቀሪ ብር 196,000.00 ( አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር) አመልካች እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህንን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በትእዛዝ ሰርዞቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ህዳር 15 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ

ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ጥር 2 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች ጥያቄ የጉዳት ካሳ መጠን የስር ፍርድ ቤቶች በርትዕ መወሰናቸው እንዲሁም የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ወንድማቸው ተሻለ ታምሩ ላይ በአመልካች መኪና በደረሰው የሞት ጉዳት ምክንያት የተቋረጠውን የመጦሪያ ቀለብ የመጠየቅ መብት ሳይኖራቸው አመልካች የጉዳት ካሳ እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095/1/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ  የሚጥስ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪዎች በኩል ደግሞ በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው ከፍተኛ የሆነ የመጦሪያና የቀለብ ገቢ በርትዕ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ህግን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ ተጠሪ ልጃቸው ተሻለ ታመሩ ፤2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አባታቸው ታምሩ ገሊቶ እና ወንድማቸው ተሻለ ታምሩ በአመልካች መኪና ጉዳት ደርሶባቸው ህይወታቸው በማለፉ ምክንያት መጦሪያና የቀለብ ገቢ እንዲከፈላቸው የጠየቁ መሆናቸው፤የ4ኛ ተጠሪ ጥያቄ ደግሞ የሟች አቶ ታምሩ ገሊቶ ወላጅ እናት በመሆናቸው ካሳ የጠየቁ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በተመለከተ አከራካሪ አይደለም እንዲሁም ሟቾች በህይወት እያሉ በእርሻ ስራ፤በንብ ማነብና በንግድ ተሰማርተው ቤተሰቦቻቸው ያስተዳድሩ የነበሩ መሆናቸውና የተቋረጠ ቀለብና መጦሪያ መኖሩን ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪዎች ለደረሰባቸው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከተረጋገጠ የጉዳት ካሳ የመክፈል ግዴታ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የካሳ መጠን ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታ መኖሩን ፍርድ ቤቱ ከተገነዘበ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2102 ድንጋጌ መሰረት በርትዕ መወሰን እንደሚቻል በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ አመልካች የካሳ መጠን አወሳሰን በተመለከተ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አጥብቀው

የሚከራከሩበት ነጥብ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በወንድማቸው ሞት ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2095/1/ መሰረት መብት ሳይኖራቸው እንዲከፈላቸው የተሰጠ ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ በተጎጂው ላይ ከደረሰው የሞት አደጋ የተነሳ በራሳቸው ስም ሆነው በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ የሚችሉት የተጎጂው ባል ወይም ሚስት፣ወይም ወላጆቹና ልጆቹ እንደሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2095/1/ ይደነግጋል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው መሰረት ያደረጉት አባታቸው አቶ ታምሩ ገሊቶ እና ወንድማቸው አቶ ተሻለ ታምሩ በአመልካች መኪና ጉዳት ደርሶባቸው በመሞታቸው ምክንያት ለተቋረጠባቸው መጦሪያና ቀለብ ገቢ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ ወንድማቸው በመሞቱ ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ የሚያስችል መብት ሳይኖራቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ እያለ በአባታቸውና ወንድማቸው ሞት ምክንያት የተቋረጠባቸው መጦሪያና ቀለብ ገቢ አመልካች እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች የተቋረጠባቸው መጦሪያና ቀለብ ገቢ መኖሩን በማረጋገጥ የጉዳት ካሳ መጠን በርትዕ መሰረት በማድረግ መወሰናቸው በአግባቡ ሆኖ ነገር ግን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በወንድማቸው ሞት ምክንያት የጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት ሳይኖራቸው ይህን ሳይለይ የተሰጠ ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12143 መስከረም 20 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04428 ጥቅምት 22 ቀን 2009ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአባታቸው ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ካልሆነ በስተቀር በወንድማቸው ላይ ከደረሰው የሞት አደጋ የተነሳ በራሳቸው ስም ሆነው በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ አይችሉም ብለናል፡፡

3. ስለሆነም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሟቾች አባታቸውና ወንድማቸው በመሞታቸው ምክንያት የተቋረጠባቸውን የቀለብና የመጠሪያ እንዲሁም የትምህርትና የህክምና ወጪ በርትዕ እያንዳንዳቸው ብር 80,000.00/ሰማንያ ሺህ ብር/ እንዲከፈላቸው የተሰጠ ውሳኔ ክፍል በማሻሻል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባው ለእያንዳንዳቸው ብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ በማለት ወስነናል፡፡
4. ተጠሪዎች ሊከፈላቸው ከሚገባ የሞት ጉዳት ካሳ፤የሞራል ካሳ እና ለቀብር ማስፈፀሚያ በድምሩ ብር 156,000.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ ብር/ ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር/ እንዲከፍል ቀሪው ብር 116,000.00 (አንድ መቶ አስራ ስድስት ሺህ ብር) አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል ወስኗል፡፡
5. ከዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 20 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት በመ/ቁ.12143 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

የሰ/መ/ቁ. 137918

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን -ዓቃቤ አቶ ዐቢይ ተሃድሶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የዳሽን ባንክ አክሲዮን ማኅበር -ነ/ፈጅ አቶ አስራት አድማሱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የክርክሩ ምክንያት የካሳ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበረ ሲሆን የክሱም ይዘት፡- ተከሳሽ /የአሁኑ አመልካች/ አውጥቶ ለነበረው የግንባታ ሥራ ጨረታ አፈጻጸም ተጫራቹ ለሚያስይዘው የዋስትና ገንዘብ አመልካች በጻፈው ደብዳቤ ከዳሽን ባንክ የሚቀርብ ማንኛውም ዓይነት ዋስትና ተቀባይነት የለውም በማለት መግለጹ እና ይህንንም ለተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማሳወቁ የተጠሪን መልካም ስም ያጠፋ በመሆኑና ባንኩም የደንበኝነት ቅድሚያ ክፍያ እንዲሁም የመልካም ሥራ አፈጻጸም ፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ብር 417,117.71 /አራት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰባ አንድ ሳንቲም/ እንዲከፍልና ለፈጸመው ህገ ወጥ ድርጊት ማስተባበያ እንዲሰጥ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ የተጠሪን /የከሳሽን/ ስም አንስተን ሳይሆን ለህንፃው ተቋራጭ የቅበላ ደብዳቤ በገለጽንበት ወቅት ዋስትናን ማስያዝ በተመለከተ ከዳሽን ባንክ ጋር ካለን የፍርድ ቤት ክርክር አንጻር የማንቀበል መሆኑን ከመግለጽ ውጪ የከሳሽን ስም አላጠፋንም፣ ስም ሳይጠፋ መልካም ስሜ ጠፍቷል በማለት ያቀረበው ክስ በመሆኑ መብትና ጥቅም የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካቀረበ በኃላ በአማራጭ በሰጠው መልስ ከባንኩ ጋር ፍርድ ቤት ክርክር ስላለን ኮንትራክተሩ ጨረታ በማሸነፉ የአሸናፊነቱን የሚገልጽ ዝርዝር ደብዳቤ ላይ ከዳሽን ባንክ የሚቀርብ የመልካም ሥራ ዋስትናን በተመለከተ የማንቀበል መሆኑን ገልጸናል፡፡ በግልባጭ እንዲያውቁት የተደረጉትም መ/ቤቶች ቢሆኑ ካለን የሥራ ግንኙነት በብድር የተገኘ ገንዘብ በመሆኑ ስለጨረታ አሸናፊ እንዲያውቁት የተጻፈ ደብዳቤ ከመሆኑ ባሻገር የስም ማጥፋት ተግባር ያልፈጸምን ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩን  የሰማው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የሥር ተከሳሽን / የአሁኑን አመልካችን/ ጥፋተኛ በማድረግ ከሳሽ /ተጠሪ/ የጠየቀውን ብር 417,117.71 /አራት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰባ አንድ ሳንቲም/ 9% ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል እና ወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብቱን በመጠበቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህን ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኑ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ሰርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ እንዲሁም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሞብኛል ያላቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡ አጣሪው የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ቀደም ሲል ከተጠሪ ባንክ ጋር ክስ ስለነበረን ጉዳዩም በፍርድ ቤት እየታየ ባለበት ሁኔታ ከዳሽን ባንክ የሚቀርበውን ዋስትና አንቀበልም ማለቱ ስም ማጥፋት ነው የተባለበት አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል አዟል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ሚያዚያ 12 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን አመልካቹም በቀን 26/09/2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ተመርምሯል፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ባለው ደብዳቤ ላይ የአሁኑ አመልካች **"የቅበላ ደብዳቤ"** በሚል ርዕስ ሥር **"ማሳሰቢያ"** በማለት ከተጠሪ ባንክ ማንኛውንም ዓይነት ዋስትና አንቀበልም በማለት ስለመጻፉ በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ይህ የተጻፈው መልእክት የተጠሪን መልካም ስም ያጠፋ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሊታይ ይገባል፡፡

ደብዳቤው የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴን ሌሎች ሰዎች እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ማንኛውም ምክንያታዊ ሰው ከደብዳቤው ሊረዳ የሚችለው ባንኩ በሥራው፣በሙያውና በሚሰጠው አገልግሎት ብቃት እና ታማኝነት እንደሌለው ነው፡፡ አመልካች የባንኩን ዋስትና የማይቀበልበትን ምክንያት አብራርቶ ቢጽፍ ኖሮ ምክንያቱ ግልጽ ሊሆንና የሚያነቡም ሰዎች ሊረዱ ይችሉ ነበር፡፡ ነገር ግን ደብዳቤው በጥቅሉ የባንኩን ዋስትና አንቀበልም በማለቱ ለተለያየ ጥርጣሬ የሚጋብዝ፣ ከባንኩ ጋር ደንበኝነት ለመፍጠር የሚፈልጉ ቢኖሩ እንኳን ባንኩን እንዲጠራጠሩ የሚደርግ፣ የተጠሪ ድርጅት ሥራ እንዲቀዘቅዝና የተቋቋመለትን ዓላማ እንዳይወጣ መሰናክል የሚፈጥር እንደሆነ ለመገንዘብ ያስችላል፡፡ ደብዳቤው ለተጠሪ ብቻ ተጽፎ የቀረ ሳይሆን ለተለያዩ አካላት ግልባጭ የተደረገ ነው፡፡ ይህ ደብዳቤ የደረሳቸው አካላት ከባንኩ ጋር የውል ግንኙነት ለማድረግ ቢፈልጉ የተላለፈው መልእክት ከፍተኛ ጥያቄን የሚፈጥርባቸው እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ አመልካች ይህን ደብዳቤ ሲጽፍ ግልባጭ ያደረገው ከአመልካች ጋር የሥራ ግንኙነት ያላቸው አካላት በመሆናቸው ነው በማለት ቢከራከርም በተጠሪ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት በአግባቡ ማጤን ሲገባው ሳያጤን የጻፈው ደብዳቤ በመሆኑ በዚህ አኳኋን ሊስተባበል የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ደብዳቤውን የጻፈው ከተጠሪ ጋር በፍርድ ቤት ክርክር ስላለ ነው ይበል እንጂ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው የተጻፈው ደብዳቤ ይህንን አይገልጽም፡፡ ይህን

በተመለከተ ተጠሪ ለዚህ ችሎት በሰጠው መልስ በአመልካች እና ጣና ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር መካከል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች የውል ጥሰት ፈጽሟል በሚል ባቀረበው ክስ በአመልካች ስም ተጠሪ ዘንድ ያለው የዋስትና ገንዘብ እንዳይከፈል እግድ እንዲሰጥለት ባንኩን 2ኛ ተከሳሽ አድርጎ ያቀረበ ክስ መሆኑን፣ ጉዳዩን ሲያይ የነበረው ፍርድ ቤት ክስ ከመስማቱ እና ክርክር ከመደረጉ በፊት በባንኩ ዘንድ ያለን ገንዘብ ለማሳገድ ካስፈለገ የእግድ አቤቱታ ከማቅረብ በቀር ባንኩን ተከሳሽ አድርጎ ማቅረቡ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ነው በሚል ከክሱ ከኪሳራ ጋር አሰናብቶናል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካች ይህንን መከራከሪያ በመልስ መልሱ በአግባቡ አላስተባበለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ከተጠሪ ጋር ክርክር ስለነበረን የጻፍኩት ደብዳቤ ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ማስተባበያ ተገቢ አይደለም፡፡

በመሠረቱ የባንክ ሥራ ከፋይናንስ እንቅስቃሴ እና ለደንበኞቹ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር እጅጉን የተቆራኘ በመሆኑ በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ያለው መልካም ስም የህልውናው መሠረት ነው፡፡ ህጉም ለዚህ መልካም ስም ጥበቃ ያደርጋል፡፡ ይህን መልካም ስም የሚያጎድፍ ተግባር መፈጸም ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ ይህም በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 2109 ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከላይ በግልጽ እንደተመለከተው አመልካች የጻፈው ደብዳቤ የተጠሪን መልካም ስም የሚነካ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህን ተመልክቶ አመልካችን ኃላፊ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡

በሌላ በኩል ካሳን በተመለከተ ተጠሪም በዚህ ደብዳቤ ምክንያት የደንበኝነት ቅድሚያ ክፍያ እንዲሁም የመልካም ሥራ አፈጻጸም ፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ብር 417,117.71 /አራት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰባ አንድ ሳንቲም/ እንዳጣ ገልጾ አመልካቸ እንዲከፍል ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶችም ተጠሪ የጠየቀውን ብር አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን በአመልካች ላይ የደረሰውን ትክክለኛ ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ የማያስችል በሆነበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት የተጠየቀውን ብር እንዳለ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ካሳው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 2102 መሠረት ሊወሰን የሚገባው በርትዕ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ

መልክ አይቶ ያለመወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ካሳው ሊሰላ የሚገባው በርትዕ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1.የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 227957 በቀን 02/02/09 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.180632 በቀን 04/05/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2.አመልካች ለተጠሪ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 2102 መሠረት በርትዕ ብር 50,000.00 /አምሳ ሺህ ብር/ ካሳ ሊከፍል ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡

የዚህ ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻሉ፡፡

3.የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡:

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 137589

ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡-በደሴ ከተማ የአራዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት -ዓ/ሕግ ሙላት መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.ወ/ሮ ዘይነባ ሰይድ -የቀረበ የለም

2.አቶ ቴዎድሮስ ፍቅሩ---የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አለአግባብ የተከፈለ ነው የተባለን ገንዘብ ለማስመለስ ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12630 በ08/11/2007 ዓ.ም.የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ አመልካችን ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ለክሱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ በማድረግ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22278 በ13/03/2008 ዓ.ም.የሰጠው እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01-03707 በ28/11/2008 ዓ.ም. በፍርድ፣እንዲሁም በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-15588 በ05/05/2009 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት በደሴ ከተማ በአራዳ ክፍለ ከተማ በቁጥር A-462 የተመዘገበ ቤት ከወ/ሮ ዘሀቡ ሁሴን ገዝተው ውሉን 1ኛ ተከሳሽ ለነበረው የአሁኑ አመልካች ሲያቀርቡ ቤቱ በባለሙያ በብር 276,644.50 በመገመቱ ለስም መዛወሪያ መክፈል የሚገባቸው ብር 13,832.20 ሆኖ ሳለ የአመልካች ሰራተኛ የሆነው የስር 2ኛ ተከሳሽ /የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ/ በማታለል ቁጥር 244271 በሆነው ደረሰኝ ላይ ብር 23,832.20 ጽፎ በመቀበል በፊደል ግን ብር 13,832.20 በሚል ሞልቶ የሰጣቸው መሆኑን እና በዚሁ አግባብ የስም ዝውውሩ የተፈጸመ መሆኑን ገልጸው አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ያለአግባብ የተቀበሉትን ገንዘብ ብር 10,000 በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሏቸው በመጠየቅ ነው፡፡2ኛ ተጠሪ ስላልቀረቡ ጉዳዩ የተሰማው በሌሉበት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በበኩሉ ቀርቦ 2ኛ ተጠሪ በፈጸሙት ድርጊት በዲሲፕሊን ከስራ የተሰናበቱ መሆኑን እና ገንዘቡ ለ2ኛ ተጠሪ የግል ጥቅም የዋለ እንጂ ለአመልካች ገቢ ያልተደረገ መሆኑን ገልጾ በአመልካቹ ላይ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ድርጊቱ የተፈጸመው በሰራተኛው ጥፋት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (3) እና 2127 መሰረት አመልካች ኃላፊነት የለበትም በማለት የተጠየቀውን ገንዘብ 2ኛ ተጠሪ ብቻ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ውሳኔ አሻሽሎ አመልካችን ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ለክሱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ለማድረግ የቻለው 2ኛ ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመው ስራውን በማከናወን ሂደት ውስጥ በመሆኑ አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) መሰረት ኃላፊነት አለበት በሚል ምክንያት ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተጨማሪ ማጣራት ካደረገ በኃላ ይህንን ውሳኔ ሊያጸና የቻለው የክፍለ ከተማው የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና የስራ ሂደት በ02/06/2007 ዓ.ም. ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና ስራ ሂደቱ በፃፈው ደብዳቤ ለስም መዛወሪያ በ1ኛ ተጠሪ ስም ብር 23,832.20 ገቢ እንደተደረገ ያረጋገጠ ስለመሆኑ በተደረገው ተጨማሪ ማጣራት በመረጋገጡ አመልካቹ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) መሰረት ኃላፊነት አለበት መባሉ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ነው፡፡

በክልሉ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ይኸው ውሳኔ ሲሆን አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ የመደረጉን አግባብነት ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) እና 2127 (1)

እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 82154 ከተሰጠው የሰበር ገዥ ውሳኔ አንጻር ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ የ2ኛ ተጠሪ መልስ የመስጠት መብት ታልፎ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው እና ጉዳዩም ለሰበር ክርክር ያስቀርባል የተባለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) እና 2127 (1) እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 82154 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በማድረግ ነው፡፡ተጠቃሹ ገዥ ውሳኔ የመንግስት ሰራተኞች ናቸው የተባሉት ግለሰቦች ወደ ጉዳዩ ገብተው እንዲከራከሩ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነቱ የመንግስት ነው ወይስ የሰራተኞቹ ነው? ወይስ የሁለቱም ወገኖች ነው? የሚሉ ነጥቦች ተለይተው ውሳኔ እንዲያርፍባቸው በነጥብ የተመለሰን ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡በተጠቃሹ መዝገብ የመንግስት ተቋም ከነበረው አመልካች የቀረበው ክርክር ይዘትም የአመልካች ድርጅት ሰራተኞች ዕቃ አቅራቢ ከነበረው ተዋዋይ ወገን ጋር በመተባበር ለፈጸሙት ተግባር መንግስት ኃላፊ ሊሆን አይገባውም የሚል ይዘት ያለው መሆኑን በውሳኔው ላይ የሰፈረው የክርክሩ ይዘት ያመለክታል፡፡በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ የማይገባቸውን ክፍያ የፈጸሙት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር እና አመልካችን ለመጉዳት በማሰብ ስለመሆኑ በአመልካቹ በኩል የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡በሰበር ደረጃም በዚህ ረገድ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ከዚህም በተጨማሪ በተያዘው ጉዳይ ተፈጸመ በተባለው ድርጊት ጉዳቱ የደረሰው በ1ኛ ተጠሪ ላይ እንጂ በመንግስት ላይ አይደለም፡፡በመሆኑም በሁለቱ ጉዳዮች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መለያየት አንጻር ገዥ ውሳኔው ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት የሚኖረው አይደለም፡፡በሌላ በኩል የክፍለ ከተማው የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና የስራ ሂደት በ02/06/2007 ዓ.ም. ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና ስራ ሂደቱ በፃፈው ደብዳቤ ለስም መዛወሪያ በ1ኛ ተጠሪ ስም ብር 23,832.20 ገቢ እንደተደረገ ያረጋገጠ ስለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍርዱ ላይ አስፍሯል፡፡ አመልካች ይህ ደብዳቤ ሊጻፍ የቻለው 2ኛ ተጠሪ በሰጡት መረጃ መነሻ ነው የሚል ይዘት ያለው ክርክር ያቀረበ ቢሆንም በመሰረቱ

የመንግስት ተቋማት ሰራተኞቻቸውን የመቆጣጠር እና የመከታተል ግዴታ ያለባቸው መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።ይህን ሳይፈጽሙ ቀርተው በተገልጋዮች ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ጉዳዩ አይመለከተንም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም።አመልካች ከገንዘብ ጋር በተያያዘ የስራ መደብ ላይ ይሰሩ የነበሩት 2ኛ ተጠሪ ዋስ ለሚፈጽሙት ጥፋት ዋስ እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባው ነበር በማለት 1ኛ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ላቀረቡት ክርክርም አመልካቹ በመልስ መልሱ ላይ የሰጠው ግልጽ ማስተባበያ የለም።በመሰረቱ ሊከፍል የማይገባውን ነገር የከፈለ ሰው እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2164 ስር ተመልክቷል። አመልካቹ ገንዘቡን የሚከፍል ከሆነም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በሕጉ አግባብ መስርቶት የነበረውን የቅጥር ግንኙነት መሰረት አድርጎ በመጨረሻ ከ2ኛ ተጠሪ ማስተካት የሚችል ከመሆኑ በቀር ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ መሆን አይገባኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ጉዳይን የሚመለከት ነው ከሚባል በቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል።

## ው ሳ ኔ

1. በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12630 በ08/11/2007 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ አመልካችን ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ለክሱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ በማድረግ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22278 በ13/03/2008 ዓ.ም. የሰጠው እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01-03707 በ28/11/2008 ዓ.ም. በፍርድ፣ እንዲሁም በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-15588 በ05/05/2009 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል።
2. በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12630 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ09/06/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።

3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 132017

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1. አቶ ማቲያስ ወልደየስ

2. አቶ ሙሉሸዋ ጥላሁን } ጠበቃ ገለታ ደገፉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ መላኩ መኬ ማዶ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-79472 አ.አ ሚኒባስ መኪናቸው ጥቅምት 5 ቀን 2006 ዓ.ም በ1ኛ አመልካች ይሽከረከር የነበረውና በ2ኛ አመልካች እና በስር 3ኛ ተከሳሽ የሆነው ኖህ የደረቅ ጭነት አ.ማ ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-27047 ኢት የተሳቢ ቁጥር 03-03870 ኢት የሆነው መኪና ላይ የተጫነው ኮንቴይነር በመልስ ሰጪ መኪና ላይ ወድቆ ከባድ ጉዳት በማድረሱ የስር ከሳሽ መኪናው የደረሰበት ጉዳት ለማስገመት ያወጣውን ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) አደጋው የደረሰበት የሰሌዳ ቁጥር 03-79472 አ.አ የሆነውን ሊጠገን

የማይችል በመሆኑ የመኪናው ከአደጋው በፊት የገበያ ዋጋው ብር 300,000.00 (ሶስት መቶ ሺህ ብር) ጉዳት የደረሰበት መኪና የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን ይህ መኪና በአማካይ በቀን ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) የሚያስገባ በመሆኑ ጉዳቱ ከደረሰበት ከጥቅምት 5 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ክስ እስከቀረበበት ሕዳር 10 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ለ35 ቀናት ያጣውን ብር 10,500.00 (አስር ሺህ አምስት መቶ ብር)፤ ከህዳር 11 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የስር ከሳሽ ያጣውን ጥቅም የቀን ገቢ ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) በዚህ ክስ ምክንያት የወጣውን ወጪ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ለቀረበው ክስ የሰጡት መልስ በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት መድረሱን አምነው 1ኛ አመልካች አደጋ የደረሰበት መኪና ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ጥገና ተደርጎለት ወደነበረበት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲመለስ እና ተጠሪ ያጣውን የእለት ገቢ እንዲያገኝ ተጠሪን ከአፍሪካ ኢንሹራንስ ጋር በማገናኘት መኪናው ከአደጋ በፊት ወደነበረበት እንዲመለስ የተለያዩ በመኪና ጥገና ላይ የተሰማሩ እና በአደጋ ገማች ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን በማወዳደር የአፍሪካ ኢንሹራንስ በ87,000.00 (ሰማንያ ሰባት ሺህ ብር) ሊጠገን እንደሚችል ካረጋገጠ በኋላ መኪናው እንዲጠገን ተጠሪን ቢጠይቅም ፍቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ መኪናው በወቅቱ ሳይጠገን ቀርቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ መኪናው ጠቅላላ የወደመ በማስመሰል ያቀረበው የመኪናው ጠቅላላ ዋጋ ተጠሪ መኪናው ተጠግኖ ወደነበረበት በመመለስ ያገኝ የነበረውን የእለት ገቢ በተጠሪ እምቢተኝነት በመቅረቱ ተጠያቂ አይደለንም፤ተጠሪ አደጋው የደረሰበት መኪና ተጠግኖ ወደነበረበት እንደሚመለስ በአፍሪካ ኢንሹራንስ ከተረጋገጠ በኋላ በሌላ ድርጅት አስገምቻለሁ ይከፈለኝ በማለት ያቀረበው ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ተጠሪ አለአግባብ ለመበልጸግ ሊጠገን የሚችል መኪና አስቁሞ ያቀረበው ክስ በመሆኑ በክሱ ምክንያት ያወጣውን የዳኝነት፤የጠበቃ አበልና የተለያዩ ወጭዎችን የማንጠየቅ ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልንና ከወጪ ኪሳራችን ጋር እንዲወሰንልን በማለት አፍሪካ ኢንሹራንስ ጣልቃ እንዲገባ ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአፍሪካ ኢንሹራንስ ጣልቃ እንዲገባ ካደረገ በኋላ ግራ ቀኙ በማከራከርና የስር ከሳሽን ክስ በመስማት ጥር 8 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት አደጋ የደረሰበት መኪና ሊጠገን እንደሚችል በመረጋገጡ ተሽከርካሪውን ለማስጠገን ብር 112,183.00 (አንድ መቶ አስራ

ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት ብር) የተገመተበትን ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ተጠሪ ያጣውን የእለት ገቢ ከጥቅምት 10 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ የአንድ ቀን ሰርቪስ ቀን በመቀነስ ብር 131,200.00 (አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) ተጠሪ የወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብቱን በመጠበቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኂላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ነሐሴ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎቸ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ጥር 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች ደንበኛ የሆነው የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ ተሽከርካሪው አስፈላጊ ጥገና ተደርጎለት ከአደጋ በፊት ወደነበረበት እንዲመለስ ያደረገው ጥረት በተጠሪ እምቢተኝነት ምክንያት አለመሳካቱን ገልፀው እየተከራከሩ እያለ ይህ ሳይጣራ አመልካቾች የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍሉ በስር ፍርድ ቤት የተወሰነው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት መድረሱን አምነው 1ኛ አመልካች አደጋ የደረሰበት መኪና ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ጥገና ተደርጎለት ወደነበረበት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲመለስ እና ተጠሪ ያጣውን የእለት ገቢ እንዲያገኝ ተጠሪን ከአፍሪካ ኢንሹራንስ ጋር በማገኛኘት መኪናው ከአደጋ በፊት

ወደነበረበት እንዲመለስ የተለያዩ በመኪና ጥገና ላይ የተሰማሩ እና በአደጋ ገማች ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን በማወዳደር የአፍሪካ ኢንሹራንስ በ87,000.00 (ሰማንያ ሰባት ሺህ ብር) ሊጠገን እንደሚችል ካረጋገጠ በኋላ መኪናው እንዲጠገን ተጠሪን ቢጠይቅም ፍቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ መኪናው በወቅቱ ሳይጠገን ቀርቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ መኪናው ተጠግኖ ወደነበረበት በመመለስ ያገኝ የነበረውን የእለት ገቢ በተጠሪ እምቢተኝነት በመቅረቱ ተጠያቂ አይደለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሥር ፍርድ ቤት በጣልቃገብነት ተከራካሪ የነበረው አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጉዳቱ እንደደረሰ መኪናው ተጠግኖ ወደነበረበት ለመመለስ ያደረገው ጥረት በተጠሪ ተቀባይነት እንዳላገኘ ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ይህንን የሚያስተባብል ክርክርና ማስረጃ ከሥርም ሆነ ከዚያ በኋላ በተደረገው ክርክር ያላቀረበ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ይህንን ገንዘብ በቅንነት በመቀበል ቀረብኝ የሚሉትን ገንዘብ ከአመልካቾች መጠየቅ የሚችሉበት እድል ነበራቸው፡፡ በተበዳይ ላይ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈለው ካሣ ለቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ አኳኋን ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ ከአመልካች ጋር ያለውን የመድን ውል መሠረት በማድረግ እንዲቀበሉት የጠየቃቸውን ብር 87,000(ሰማንያ ሰባት ሺህ ብር) በቅንነት ቢቀበል ገቢ በመቋረጡ ምክንያት የደረሰባቸውን ኪሣራ ሊያስቀሩት ወይም ሊቀንሱት የሚችሉበት አቅም ይፈጥርላቸው ነበር፡፡ ሌላ ሰው ኃላፊ በሆነበት ድርጊት ወይም አደጋ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱን ለማስቀረት ወይም የጉዳቱን መጠን ቀላል ለማድረግ ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 2 ተበዳዩ በማስተዋል ቢሠራ ኖሮ የደረሰበትን ጉዳት ሊያግደው ወይም ሊያቀለው የሚችል ሲሆን በደረሰበት ጉዳት መጠን በሙሉ ካሣ ለመጠየቅ አይችልም በማለት በግልፅ ደንግጎታል፡፡ ተጠሪ በግጭቱ ጉዳት የደረሰበት መኪና በወቅቱ ተጠግኖ ወደ ስራ ቢመለስ በአደጋው ምክንያት ያቋረጠባቸውን የገቢ መጠን ለመቀነስ እየቻሉ ለማስጠገን እንቢተኛ ለመሆናቸው ምክንያት ኪሣራውን ለማስቀረት ወይም ሊያቀሉት እንዳልቻሉ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ ምክንያት የተቋረጠው ገቢ መጠን መጨመር የተጠሪ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2098 /1/ መሰረት በከፊል ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በመኪናው መውደም ምክንያት የተቋረጠባቸውን የገቢ መጠን ለመቀነስ ወይም ለማቅለል የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው

መሠረት በቅን ልቦናና በአስተዋይነት ያደረጉት እንቅስቃሴ የሌለ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያልሰጡ በመሆኑ ውሳኔያቸው በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና ሊሻሻል የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35023 ጥር 8 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 166426 ግንቦት 22 ቀን 2008 ዓ/ም በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሻሏል፡፡
2. በተጠሪ መኪና ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ለተቋረጠው ገቢ አመልካቾች ሙሉ ሐላፊነት የለባቸውም፤ተጠሪው ከፊል ሃላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡
3. የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ መኪናቸው ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ተጠሪ ለተቋረጠባቸው ገቢ ብር 131,400 (አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ አራት መቶ ብር) አመልካቾች እንዲከፍሉ በማለት የሰጡትን ውሣኔ አሻሽለን አመልካቾች የተቋረጠ ገቢ ብር 65,700(ስልሳ አመስት ሺህ ሰባት መቶ ብር) 9% ወለድ ጋር የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡ ተሽከርካሪውን ለማስጠገን ብር 112,183.00 (አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት ብር) 9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ፤የተገመተበትን ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ፤የስር ጣልቃ ገብ አፍሪካ ኢንሹራንስ ለተጠሪ ከሚከፈለው ገንዘብ ውስጥ ብር 90,781.30 (ዘጠና ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ አንድ ብር ከሰላሳ ሳንቲም) እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ እንዲሁም ተጠሪ የወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብቱን በመጠበቅ የተሰጠ ውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.chilot.me

# ቤተሠብ

የሰ/መ/ቁ. 134836

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አባተ ሀይሉ -ጠበቃ አዲስ ለገሰ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. አቶ አስረስ ረታ
2. አቶ ኑርዬ ሰማው
3. አቶ የሽምቢ ሰማው
4. አቶ ሀይሉ ከበደ
} የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ብ/ክ/መ/ ሰሜን ወሎ ዞን ራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ከ1-3 ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተጠሪዎች አሻሽለው ባቀረቡት ክስ እነዚህ ተጠሪዎች የሚች ዘሙ ሰማው ወንድምና እህት መሆናችን በመዝገብ ቁጥር 01027488 በህጋዊ መንገድ ወራሽነታችንን አረጋግጠናል፡፡ ሚች ዘሙ ሰማው ከመሞቷ በፊት ከ4ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ነበሩ፤ የንብረት አስተዳደራቸውንም አስመልክቶ በየግላቸው ይዘው ሲኖሩ ከቆዩ በኂላ በቀን

20/03/2006 ዓ.ም ለአመልካች በ108 ካ/ሜ ቦታ ውስጥ ያለው የግል መኖሪያ ቤቷን በኑዛዜ ካስተላለፈች በኋላ 4ኛ ተጠሪ ጋር ንብረታቸውን የጋራ ለማድረግ ተስማምተው ቆቦ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት በቀን 30/05/2006 ዓ.ም ማስረጃ ያወጡ ሲሆን በኑዛዜ ለማንም ያልተሰጠውንና በቆቦ ከተማ 01 ቀበሌ በክሱ በአዋሳኝ የተገለፀው 253 ካ/ሜ ቦታ በጋራ የሰሩትን አሜሪካን ሞድ ቤት ጓዳና ሳሎን ያለው እና አንድ ሰርቪስ በብሎኬት የተሰራ ግምቱ ብር 500,000.00/አምስት መቶ ሺህ ብር/ የሚያወጣው ድርሻ 126.5 ካ/ሜ ከፍሎ እንዲሰጠን እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን 4ኛ ተጠሪም ለአቤቱታው የሰጡት መልስ ክርክር የተነሰበት ንብረት ያረፈበት የመኖሪያ ቤት ከእናቱ እሚሆይ ሙሽራ አባይ በውርስ ያገኘው እና አሜሪካ ሞድ የተባለው ቤትንም ከሚች ጋር ከመጋባቱ በፊት በግሉ የሰራው መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን የአሁን አመልካች በበኩሉ በክርክር ጣልቃ እንዲገባ ጠይቆ ተፈቅዶለት አከራካሪው ቤት 4ኛ ተጠሪ እና ሚች ዘሙ ሰማው በወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት በመቅረብ በ20/03/2006 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ያስተላለፉልኝ በመሆኑ በውርስ ሊጠየቁት የማይገባ ፤ኑዛዜውም በህግ በተደነገገው ኑዛዜ በተሰጠበት አይነት ግልፅ ተግባር ያልተሻረ መሆኑን በመግለፅ ያቀረቡት የሚች ንብረት ያለኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ኑዛዜው ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ ስለአደረጉት እና በተዘዋዋሪ መንገድ ተሽሯል በማለት የፍ/ብ/ህ/ቁ.858 እና 900/1/ በመጥቀስ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቦታና ቤት ለተጠሪዎች ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ከ1-3 ተራ ቁጥር

የተጠቀሱ ተጠሪዎች ሚያዚያ 2 ቀን 2009ዓ.ም፤4ኛ ተጠሪ መጋቢት 28 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ የአመልካች ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው በብዙ ሰዎች የተደረገ ስለሆነ እና በተዘዋዋሪ መንገድ የተሻረ ስለሆነ የሟች ድርሻ ቤትና ቦታ ከ1ኛ-3ኛ ያሉ ተጠሪዎች በውርስ ሊተላለፍ የሚገባው ነው በሚል የሰጡት ውሳኔ መስረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ ክርክር ከተነሰባት ቤትና ቦታ ውስጥ የሟች ድርሻ የሆነው ለአመልካች በኑዛዜ የተላለፈ ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል የሚል ሲሆን ከ1ኛ-3ኛ ያሉ ተጠሪዎች ደግሞ ለአሁን አመልካችና ወንድሙ በቀን 20/03/2006 ዓ.ም ኑዛዜ ሲያደርጉ በየግል ንብረታቸው በተለየ ሰነድ መናዘዝ ሲኖርባቸው ነገር ግን ሟች ዘሙ ሰማው የግል ንብረት ላይ 4ኛ ተጠሪ በኑዛዜ ሰነድ ላይ በጋራ ኑዛዜ አድርጎ በመገኘቱ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርገው መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔው የተሰጠው በዚህ ረገድ ሆኖ ሳለ አመልካች ግን ከኑዛዜው ውጭ ለአገልግሎት ጽ/ቤት የየግል ንብረታቸውን በስምምነት የጋራ ማድረጋቸው እና ካርታ እና ፕላን ማውጣቸው በዝምታ እንደተሻረ አድርገው ማቅረባቸው ፍፁም ከስር ፍርድ ቤቶች ጭብጥ እና ውሳኔ ጋር የማይገናኝ  በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ሙሉ በሙሉ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የ4ኛ ተጠሪ መልስ ለልጆቻቸው የተደረገው ኑዛዜ ሊሻር አይገባም በማለት የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተገቢ በመሆኑ በመግለፅ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው ለክርክር ምክንያት የሆነው  ሟች ዘሙ ሰማው ከ4ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት የነበሩ መሆናቸው፤የንብረት አስተዳደራቸውን በተመለከተ በየግላቸው ይዘው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ ሟች የግል ንብረቷን አስመልክቶ በቀን 20/03/2006 ዓ.ም ለአመልካች በ108 ካ/ሜ ውስጥ ያላትን የግል መኖሪያ ቤቷን ከ4ኛ ተጠሪ ጋር በኑዛዜ ከአስተላለፈች በኋላ ከ4ኛ ተጠሪ /የስር ተከሳሽ/ ንብረታቸውን አስመልክቶ የጋራ ማድረግ እንዳለባቸው ተስማምተው በቆቦ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት በኩል በቀን 30/05/2006 ዓ.ም ማስረጃ ያስወጡ መሆናቸው ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና

ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሰረቱ ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ የግል ጠባይ ያለው መሆኑን በፍ/ብ/ህ/ቁ.857 ስር ተደንግጓል፤የሚች ጥብቅ የሆነ እራሱ የሚፈፀመው ስራ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.858 ስር ብዙ ሰዎች አንድ በሆነ ጽሁፍ ማናዘዝ የማይቻል መሆኑን ተመልክቷል፡፡ ይህንንም ከፍ/ብ/ህ/ቁ.880 እና ተከታዮቹ ጭምር ተንፀባርቋል፤ አሁን በተያዘው ጉዳይ ሟች ዘሙ ሰማው እና 4ኛ ተጠሪ ለአመልካችና ለወንድሙ በአንድ የኑዛዜ ጽሁፍ ላይ በጋራ ተናዘዋል፤ይህ ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነው ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ ሟች ብቻውን እራሱ የሚፈፅመው በመሆኑ በጋራ መናዘዝ በፍ/ብ/ህ/ቁ.858 የተደነገገ በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ ነው፡፡ ስለሆነም  የስር ፍርድ ቤቶችም ኑዛዜው በቀን 20/03/2006 ዓ.ም የተደረገው ኑዛዜ ህጋዊነትን አስመልክቶ በሟች ዘሙ ሰማው የግል ንብረት ላይ 4ኛ ተጠሪ የሆነው በግል ንብረቷ ላይ በአንድ የኑዛዜ ሰነድ ላይ ተናዘዘው መገኘታቸው እና ከፍ/ብ/ህ/ቁ.858፤857 እና 880 እና ተከታዩ ድንጋጌዎች አንፃር በመመርመር ሟች ዘሙ ሰማው እና 4ኛ ተጠሪ ለአመልካች እና ለወንድሙ በአንድ የኑዛዜ ፅሁፍ የግል ንብረቷን በአንድ ላይ ተናዘው በመገኘታቸው የስር ፍርድ ቤቶች ኑዛዜውን ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ መስጠታቸው የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት የሌለበት በመሆኑ አመልካች ክርክር ከተነሰባት ቤትና ቦታ ውስጥ የሚች ድርሻ የሆነው ለአመልካች በኑዛዜ የተላለፈ ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል ስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0107811 መጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ/ም እና በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17313 ሚያዚያ 17 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-14318 ጥቅምት 29 ቀን 2009 ዓ/ም በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ከዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 8 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0127811 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰበር መ/ቁ/138286

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች ፡ 1ኛ. ጫሉሜ ሙለታ - ቀረቡ

2ኛ. ሶበቄ ሙለታ - ቀረቡ

ተጠሪ፡ ጫለሺ ቀልበሳ - ወ/ድንቁጣ ጉተማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የገጠር መሬት ይዞታ የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የከሳሾች (አመልካቾች) ክስ ይዘት ባጭሩ የአመልካቾች አባት እና እናት ይዞታ የነበረ የገጠር መሬት የተጠሪ ባለቤት ሟች ቀጄል ሙለታ ከመሞቱ በፊት ከአመልካቾች እናት ጋር በጋራ ይዞ ሲጠቀም የቆየዉን ወንድማቸው ከሞተ በኂላ ተጠሪ ምንም መብት ሳይኖራት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ለብቻዋ እየተጠቀመች ስለሆነ ስፋቱ 1.5 ሄክታር የሆነ የገጠር መሬት እንድትለቅ እንዲወስን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የተጠሪ መልስ ባጭሩ የአመልካቾች አባት ከሞቱ 17 ዓመት በላይ መሆኑን እናታቸውም ከሞቱ 10 ዐመት በላይ ስለሆነው የአመልካቾች ክስ በይርጋ ሊቋረጥ እንደሚገባ ይህም ቢታለፍ የአመልካቾች አባት እና እናት ይህንኑ ይዞታቸውን በስጦታ ለተጠሪ ባል ለሟች ቀጄላ ሙለታ አስተላልፈው በዚህ ይዞታ ባልና ሚስት እስከ 2004 ዓ.ም. በጋራ ሲጠቀሙ ቆይተው የተጠሪ ባል

ሲሞት በዚህ ይዞታ ላይ ተጠሪ በስሟ የይዞታ ማረጋገጫ አግኝታበት የያዘችው በመሆኑ አመልካቾች መብት የላቸውም በማለት ክሱ ውድቅ  እንዲደረግ ተከራክራለች ፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው የአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ይዞታው መሠረቱ የአመልካቾች አባት እና እናት ስለሆነና ሚስት (ተጠሪ) ባሏን መውረስ ስለማትችል ይዞታውን ለአመልካቾች ትልቀቅ ሌላውን የጋራ (የባልና ሚስት) ንብረት መካፈል ትችላለች ሲል ውሳኔ ሠጥቷል ፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝታ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበች ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ መሬቱ የአመልካች አባት እና እናት መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ ለተጠሪ ባል ስጦታ ስለመደረጉ ማስረጃ አልቀረበም ሲል የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በከፊል በማሻሻል ሚስት ከባለቤቷ ጋር ስትጠቀም ስለ ቆየች ከዚህ ይዞታ ላይ 1/8 ይገባታል ሲል ወሰኗል፡፡

ተጠሪ ሁለተኛ ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረቧ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ክርክር የተነሳበት ይዞታ በ1983ዓ.ም የአመልካቾች አባት እና እናት ለተጠሪ ባል በስጦታ ማስተላለፋቸዉ ፤ በ1996 ዓ.ም የተጠሪ ባል መሬቱን በስሙ አስለክቶ ማስረጃ ማግኘቱንና የተጠሪ ባል ከሞተ በኂላ ይዞታው በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣት መሆኑን በማስረጃ መረጋገጡን ጠቅሶ ይዞታው የተጠሪና የሟች ባለቤቷ ቀጄላ ሙለታ ሆኗል ሲል የኦሮሚያ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 9 እና በደንብ ቁጥር 151/05 አንቀጽ 10 መሠረት ተጠሪ ባለመብት ስለሆነች መሬቱን ልታካፍልም ሆነ ልትለቅ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡ አመልካቾች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም ፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር ቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ መሬት የአመልካቾች ወላጆች ይዞታ የነበረ እና አመልካቾች ሲጠቀሙበት የነበረ ስለመሆኑ የወረዳው መሬት እና አካበቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ምላሽ በሰጠበት ሁኔታ የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት አመልካቾች ሟች ወንድማቸውን ለመውረስ  ያቀረቡት ጥያቄ የለም ወንድማቸውን

ለመውረስ የሚያስችል የሕግ መሠረት የለም ማለቱ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ተጠሪ መልስ እንድትሰጥ ተደርጓል ፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት ባጭሩ የአመልካቾች እና የተጠሪ ባል የአባት እና የእናታቸውን ይዞታ በ1999 ዓ. ም ድርሻ ድርሻቸውን የተከፋፈሉ መሆኑን ፤ አመልካቾች የሟች ወንድማቸው ድርሻ የሆነ የውርስ ንብረት ለመካፈል ዳኝነት አለመጠየቃቸውን እና የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማስረጃ መዝኖ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የለውም በማለት ተከራክራለች ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተመለከተ ሲሆን እኛም አቤቱታ በቀረበበት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስሕተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ መርመረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለዉ አመልካቾች ክስ ያቀረቡት የአባት እናታቸዉ ይዞታ የሆነ እርሻ መሬት ተጠሪ መብት ሳይኖራት ስለያዘች እንድትለቅ እንዲወሰንላቸዉ ነዉ፡፡ተጠሪ በበኩሏ ይህንን መሬት የአመልካቾች አባት እና እናት በስጦታ ለባለቤቷ በመስጠታቸዉ ከባሏ ጋር በስማቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ አዉጥተዉ ሲጠቀሙ እንደነበር እና ባለቤቷ ከሞተም በኋላ በስሟ ደብተር ተሰጥቷት እየተጠቀመች መሆኗን ጠቅሳ ተከራክራለች፡፡ ይህንን የፍሬነገር ክርክር በማስረጃ የማጣራትና የመመርመር ሥልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች የተለያየ ድምዳሜ ላይ የደረሱ ሲሆን ፍሬነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመርመር ረገድ የመጨረሻ ስልጣን የተሰጠዉ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክርክር የቀረበበትን ይዞታ የአመልካቾች አባት እና እናት ለተጠሪ ባል በስጦታ ሰጥተዉ ተጠሪ እና ባሏ ለረዥም ዓመታት ሲጠቀሙ መቆየታቸዉን አረጋግጧል፡፡

ስለሆነም አከራካሪዉ ይዞታ ሥረ-መሰረቱ የአመልካቾች አባት እና እናት መሆኑ በአስተዳደር አካል ቢገለጽም ለተጠሪ ባል በስጦታ መተላለፉን የስር ፍ/ቤት በማስረጃ አረጋግጧል ፡፡በዚህ አኳኋን ባልና ሚስት ሲጠቀሙበት የኖሩትን ይዞታ ባል ማለትም የአመልካቾች ወንድም ስለሞተ ተጠሪ የመዉረስ መብት የላትም ሲሉ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር አግባብነት ባለዉ የመሬት አጠቃቀም አዋጅ ሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት መሰረት ተቀባይነት ያለዉ አይደለም ፡፡በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት

ከተረጋገጡት የሴቶች የእኩልነት መብት አንዱ መሬትን በመጠቀም ፤በማስተላለፍ፤በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ የሚደነግገዉ አንቀፅ 35(7) ነዉ ፡፡ ይህንኑ ሕገ መንግስታዊ መብት ለማስፈጸም የወጣዉ የኦሮምያ የገጠር መሬት አዋጅ ቁ/130/99 አንቀጽ 6(13) እና ደንብ ቁ/ 151/05 አንቀጽ 15 ይዘት እንደሚያስገነዝበን ባልና ሚስት በጋራ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ ጋብቻቸዉ በአንደኛዉ ተጋቢ ሞት ምክንያት ሲቋረጥ በህይወት ያለዉ ተጋቢ በሌላ ሕጋዊ ምክንያት መብቱ ካልተቋረጠ በስተቀር ይዞታዉ በስሙ ተመዝግቦ ደብተር እንደሚሰጠዉና በዚህ ይዞታ መጠቀም መብቱ እንደሚቀጥል ነዉ ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ቀደም ሲል ይዞታዉ ለተጠሪ ባል በስጦታ ተላልፎ በተጠሪና በባለቤቷ ስም ተመዝግቦ በጋራ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ የተጠሪ ባል ሲሞት ከ2000ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ ተጠሪ እየተጠቀመችበት ስለመሆኑ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማስረጃ አረጋግጦ ተጠሪ መሬቱን ልትለቅ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘንም ፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ወስነናል ፡፡

## ዉሳኔ

1-የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/239515 ላይ በ 02/10/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/248943 በ27/03/2009ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ/348(1) መሰረት ጸንቷል ፡፡

2-ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጕ

የሰ.መ.ቁ.131677

ጥቅምት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች**:..1. ዳኜ መላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

**አመልካች**፡- የወ/ሮ ጌጤ ካሳ ወራሾች ወ/ሮ ኤፌሶን ወልዴ እና ወ/ሮ አምሳለ ከተማ ወ/ሮ፤ ወ/ሮ

ኤፌሶን ወልዴ ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ**፡-.የኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ መሬትና አስተዳደር ጽ/ቤት ዐ/ህግ ሰይፈ ስላሴ ገሪማ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.127492 በ16/10/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች እና በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት ወ/ሮ ጸዳለ ካሳ እና ወ/ሮ ገነት ካሳ የመቃወም ተጠሪዎች፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ የመቃወም አመልካች ሆነው ሲከራከሩ ነበር፡፡ የአሁን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ባቀረበዉ አቤቱታ የመቃወም ተጠሪዎች የግራ ቀኛቸዉ አባት የሻለቃ ካሳ ሃይሉ በወረዳ 24 ቀበሌ 09 የቤት ቁጥር 622 ስፋቱ 942 ካ.ሜ ይዞታ በተመለከተ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ሳይኖራቸዉ ባለይዞታ አይደሉም፣ ይዞታዉ ሊስተናገድ የሚገባዉ በነባር ይዞታ ሆኖ ሳለ የመቃወም ተጠሪዎች በግልግል ዳኝነት ባደረጉት ስምምነት ይዞታዉን ሶስት ቦታ ተካፍለዉ በ29/10/1993 ዓ.ም ፍ/ቤቱ ስምምነቱን አጽንቷል፡፡ ስለዚህ ይህ ዉሳኔ እንዲሻርልን፣ እስከ 500 ካ.ሜ

በነባር ይዞታ እንዲወስዱ እና ቀሪዉን 434 ካ.ሜ ይዞታ ግን በሊዝ አዋጅ መሰረት ሊወስዱ ይገባል ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

የመቃወም ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ በታዘዘዉ መሰረት 1ኛ የመ/ተጠሪ /የአሁን አመልካች/ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ቤትና ቦታ የአባታችን ንብረት ሲሆን በአባታችን ስም ግብር እየገበርን፣ ካርታ ለመዉሰድ ጥያቄ አቅርበን እየተጠባበቅን እንገኛለን፡፡ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 6 /3/ መሰረት አዋጁ በዉርስ በሚተላለፍ ንብረት ላይ ተፈጻሚነት የለዉም፣ስለዚህ የቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መልስ ባለማቅረባቸዉ መብታቸዉ ታልፏል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በሰጠዉ ዉሳኔ የመ/ተጠሪዎች የንብረት ክፍፍል ስምምነት ያደረጉት በ1993 ዓ.ም ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህን ስምምነት ያጸደቀዉ በ1993 ዓ.ም በመሆኑ፣ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 በአንቀጽ 6 መሰረት በዉርስ በሚተላለፍ ይዞታ ወይም ቤት ላይ ተፈጻሚነት ስለሌለዉ በፍ/ቤት የግልግል ዳኞች ስምምነትን ያጸደቀዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.360 /2/ መሰረት ጸንቷል በማለት ወስኗል፡፡

የሥር የመቃወም አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን መልስ ሰጭዎች በስምምነት የተከፋፈሉት የዉርስ ሀብት የተባለዉ ይዞታ የሰነድ አልባ በመሆኑ የሰነድ አልባ ይዞታዎች ስርዓት ሊከተል ስለሚገባ ይዞታዉ በስምምነቱ መሰረት ሊካፈል የሚችል መሆን አለመሆኑ በባለሙያ ማጣራት አለበት በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ለሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በይግባኝ በማየት የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡--ወላጅ አባታችን ይህን መኖሪያ ቤትና ቦታ በ1952 በዉል ገዝተዉ ቤቶችን ሰርተዉ በ1962 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸዉ አመልካችና የሥር የመ/ተጠሪዎች ወራሽነታችንን አረጋግጠን የቤቱና ቦታዉ ባለሀብት ሆነናል፡፡ ይህን ቤትና ቦታ ለመከፋፈል በእርቅ ስምምነት ለመጨረስ ተስማምተን በዚህ መሰረት ስምምነት አድርገን ፍ/ቤቱም ስምምነቱ ከሕግና ሞራል የማይቃረን መሆኑን በማረጋገጥ ስምምነቱን በማጽደቅ ክርክሩ ተቋጭቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004

እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡት መመሪያዎች ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት በባለሙያ እንዲጣራ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲሻርልን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልኝ ወጪዎችን ተጠሪ እንዲተካልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ አቤቱታ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘዉ መሰረት የአሁን ተጠሪ ህዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ያስነሳዉ ይዞታን በተመለከተ የባለሙያ አስተያየት በመቀበል ዉሳኔ እንዲሰጥበት ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ በአግባቡ ስለሆነ እንዲጸናልን ኪሳራ እንዲከፈልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ በተመለከተ የክፍፍል ስምምነቱ ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑን በባለሙያ ሊጣራ ይገባል የመባሉን አግባብነት እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአመልካች ወላጅ አባትና አዉራሽ የሆኑት ሻለቃ ካሳ ሃይሉ ለረጅም አመታት ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ቤትና ቦታ ይዘዉ ሲኖሩበት እንደነበር እና የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንደሌላቸዉ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ሻለቃ ካሳ ሃይሉ ይህን ቤትና ቦታ በተመለከተ የይዞታ ምስክር ወረቀት ባይኖራቸዉም ይዞታዉ የዉርስ ሀብት ስለመሆኑ ሌሎች ሰነድ ማስረጃዎች መቅረባቸዉን እና ይዞታዉም ሰነድ አልባ እንደሆነ የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ሻለቃ ካሳ መሞታቸዉን ተከትሎ የአሁን አመልካች እና በዚህ ችሎት ባለዉ ክርክር ተካፋይ ያልሆኑት ወራሾች ወራሽነታቸዉን በማረጋገጥ ይህን የዉርስ ሀብት የሆነዉን ቤትና ይዞታ በ1993 ዓ.ም በእርቅ ስምምነት ተከፋፍለዉ ይህን ስምምነታቸዉን ደግሞ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበዉ ፍ/ቤቱም ስምምነቱን በሕጉ አግባብ በማየት ማጽደቁን የሥር ዉሳኔ የሚያመለክተዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ እንግዲህ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ የፍርድ መቃወም አቤቱታ አመልካችና ሌሎች ወራሾች በስምምነት የመንግስትን ይዞታ ስለተከፋፈሉ በነባር ይዞታ አግባብ እና በሊዝ አዋጁ መሰረት እንዲፈጸም ዳኝነት መጠየቁን ክርክሩ ያሳያል፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት በዚህ ጉዳይ የሊዝ አዋጁ ተፈጻሚነት የለዉም የሚል ነዉ፡፡ ስለሆነም

በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና ይህን አዋጅ ተከትለዉ የወጡት መመሪያዎች ተፈጻሚነት አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? ይህን አዋጅ መነሻ በማድረግ ይዞታዉ በባለሙያ ሊጣራ ይገባል መባሉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች ናቸዉ፡፡

በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች እና ሌሎች ወራሾች የወላጅ አባታቸዉ ሻለቃ ካሳ ሃይሉ ወራሾች መሆናቸዉን፣ ይህን ቤትና ይዞታ በእርቅ ስምምነት በ1993 ዓ.ም ተካፍለዉ ስምምቱም በዛሁ ዓመት በፍ/ቤት የጸደቀ መሆኑን እና ይዞታዉም በነባር ይዞታ አግባብ የሚታይ እንደመሆኑ መጠን የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 6 /3/ መሰረት ተፈፃሚነት ያለዉ ሆኖ አይገኝም፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 /1/ ሥር እንደተመለከተዉ ማንኛዉም ሰዉ የከተማ መሬትን በአዋጁ ከተደነገገዉ የሊዝ ሥርዓት ዉጪ መያዝ እንደማይችል ደንግጎታል፡፡ እንዲሁም ነባር ይዞታዎች ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 6 መሰረት ወደ ሊዝ ስሪት የሚቀየሩበትን ሁኔታዎች በዝርዝር ደንግጎ እናገኛለን፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አዋጅ ቁጥር 6 /3/ ሥር እንደተመለከተዉ በነባር ይዞታ ላይ ያረፈዉ ንብረት ባለቤትነት በዉርስ አግባብ የሚተላለፍ እንደሆነ በአዋጁ የተመለከተዉ የሊዝ ስሪት ተፈጻሚነት እንደማይኖረዉ በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ በነባር ይዞታ ላይ ያረፈዉ ንብረት በዉርስ የሚተላለፍ እንደሆነ ወደ ሊዝ ሥሪት ማስገባቱ ከአዋጁ ዓላማ ጋር የማይሄድና አዋጁ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ እንደማይገባዉ ነዉ፡፡ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም አዋጁን ተከትለዉ የወጡት መመሪያዎች ደግሞ ከአዋጁ ሊቃረኑ ይችላሉ ተብሎም ስለማይገመት፣ በነባር ይዞታ ላይ ያረፈዉ ንብረት ባለቤትነት በዉርስ አግባብ ሲተላለፍ መመሪያዎቹም ተፈጻሚነት ሊኖራቸዉ አይችልም፡፡

በዚህ ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወራሾች ያቀረቡትን የእርቅ ስምምነት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.277 /1/ በሚደነግገዉ አግባብ ሕግንና ሞራልን የማይቃወም መሆኑን በማረጋገጥ በማጽደቅ ከመዝገቡ እንዲያያዝ ያደርጋል ተብሎ ይገመታል፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር በዚህ ድንጋጌ አግባብ አለመፈጸሙን የሚያረጋግጥ ነገር ስለማቅረቡ መዝገቡ አያመለክትም፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ተፈጻሚነት የሌለዉ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች ነባር ይዞታዎች ወደ ሊዝ ስሪት የሚገቡበትን ሂደት በመጥቀስ ይዞታዉ በስምምነት ሊካፈል የሚችል መሆን አለመሆኑን በባለሙያ ሊጣራ

ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ የአዋጁን ዓላማና የተፈጻሚነት ወሰን ያላገናዘብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለአሁን አመልካች እና ለሌሎች ወራሾች የተላለፈዉ በነባር ይዞታ ላይ ያረፈዉ የዉርስ ንብረት በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 721/2004 ተፈጻሚነት የሌለዉ ሆኖ ሳለ በዚህ አዋጅ መሰረት የዉርስ ሀብቱ ያረፈበት ይዞታ በስምምነት የሚካፈል መሆን አለመሆኑን ባለሙያ እንዲያጣራ በማለት የሰጡት ዉሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.165672 በ5/7/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.127492 በ16/10/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.37664 በ3/2/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

የሰ/መ/ቁ. 132518

ቀን መስከረም 22/2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ተኽሉ አስፍሃ

| | |
|---|---|
| 2ኛ. ሃለቃ ደስታ ሃ/ስላሴ | 7ኛ. ወ/ሮ ዮዲት ግርማይ |
| 3ኛ. አቶ ገ/ትንሳኤ ጸሃዬ | 8ኛ. አቶ ገ/መድህን አባይ |
| 4ኛ. አቶ ልብሰ ማሪያም አሳይ | 9ኛ. አቶ ሃይላይ ገ/አምላክ |
| 5ኛ. ወ/ሮ ንግስቲ ገብሩ | 10ኛ. አቶ ወ/ገሪማ ገ/መድህን |
| 6ኛ. አቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/አረጋዊ | 11ኛ. ቁስ እቡይ ገ/እግዚአብሔር |

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ስብሃቱ ገ/መስቀል
2ኛ. ወ/ሮ ብርሃን ገ/ማሪያም } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾችን ጨምሮ 17 ሰዎች የፍርድ ባለመብቶች፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ሲሆኑ 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳው ባለቤትና የመቃወም አመልካች ነበሩ፡፡ የፍርድ ባለመብቶች በተለያዩ መዝገብ በ 1ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረዱትን

ፍርድ ለማስፈጸም የባለእዳውን ንብረት ጠቁመው በመቀሌ ከተማ በቀዳማዊ ወያኔ የሚገኙ 1ኛ/ በምስራቅ ገበያ፣ በሰሜን ታደሰ ኪዳኑ፣ በምእራብ መንገድ፣ በደቡብ ኣጽበሃ የሚዋሰን በ 32 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤትና ቦታ፣ 2ኛ/ በምስራቅ ግደይ ገ/መድህን፣ በሰሜን ታደሰ ኪዳኑ፣ በምእራብ ኣርያ መለሰ፣ በደቡብ መንገድ የሚዋሰን በ 311.75 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤትና ቦታ በፍርድ ባለእዳው ስም የሚታወቅ መኖሩን ገልጸው ስላቀረቡ ለአፈጻጸሙ እንዲውሉ ተገምተው እንዲቀርቡ በስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪ ከፍርድ ባለእዳው ጋር ከ 1967 ዓ.ም ጀምሮ በትዳር የኖሩና ለአፈጻጸም ተገምተው እንዲቀርቡ የተባሉ ንብረቶች በጋራ ያፈሯቸው መሆኑን ገልጸው አመልካቾች ያስፈረዱት በፍርድ ባለእዳው ላይ በመሆኑ ንብረቶቹ የሚሸጡ ከሆነ መብታቸው የሚነካ በመሆኑ በድርሻቸው ላይ የተሰጠው ትእዛዝ እንዲነሳላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የፍርድ ባለመብቶች ለመቃወሚያው በሰጡት መልስ ተጠሪዎች በትዳር በነበሩበት ወቅት 1ኛ ተጠሪ የገቡት እዳ እንደባልና ሚስት እዳ የሚታሰብ በመሆኑ ከባል ወይም ከሚስት የግል እና የጋራ ንብረት ሊጠየቅ እንደሚችል በንግድ ሕግ አንቀጽ 19 ተደንግጎ የሚገኝ በመሆኑና ተቃዋሚ ነጋዴ በመሆናቸው እንዲሁም ከደደቢት ብድር ተቋም ተጠሪዎች በጋራ ተበድረው ስለነበር የጋራ እዳቸው ነው፡፡ በተጨማሪም 1ኛ ተጠሪ ከስር 7ኛ የአፈጻጸም ከሳሽ የወሰዱት በቼክ የንግድ ፈቃድ ከመመለሱ በፊት ስለሆነ ያቀረቡት ተቃውሞ ውድቅ ተደርጎ አፈጻጸሙ ይቀጥልልን በማለት ተከራከሩ፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር መርምሮ የንግድ ፈቃድ ከመመለሱ በፊት ቼክ ቆርጫለሁ የሚለው ብቻውን እዳውን የጋራ እዳ ስለማያደርገው እዳው ለትዳር ጥቅም መዋሉ በማስረጃ የተደገፈ ነገር ባለመኖሩ 2ኛ ተጠሪ በቤትና ቦታዎቹ ላይ ያላቸው ግማሽ ድርሻ በዓይነት ወይም በገንዘብ ግምት ይገባቸዋል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የአፈጻጸም ትእዛዙን በመቃወም ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ያደረገ ተቃውሞ ሲቀርብ በአፈጻጸም በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት መብት አለኝ የሚል ተቃውሞ አለው ወይስ የለውም ተብሎ የሚታዘዝበት እንጂ እዳ የጋራ ነው የግል ተብሎ በማጣራት

የሚወሰንበት ስላልሆነ ንብረቶቹን ተጠሪዎች በጋብቻ ውስጥ በጋራ ያፈሯቸው መሆኑ ባልተካደበት እና በ 2ኛ ተጠሪ ላይ ባልተፈረደበት ሁኔታ ድርሻቸው ለአፈጻጸሙ የሚያዝበት አግባብ የለም በማለት በውጤት ደረጃ የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- ለአፈጻጸም ክርክሩ መሰረት የሆነው እዳ ቼክን መሰረት ያደረገ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ነጋዴነታቸው ተረጋግጦ ቼክ ተሰጥቷቸው በንግድ ስራ ተሰማርተው የቆዩ ነጋዴ ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጋቢዎች በትዳር እያሉ የመጣ እዳ የባልና ሚስት የጋራ እዳ ለመሆኑ በንግድ ሕግ አንቀጽ 19 ተመልክቷል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ራሳቸው ነጋዴ በመሆናቸው እዳው የሚመለከታቸው በመሆኑ እንዳለ ሆኖ በጋራ ጥቅም ላይ አለመዋሉም የማስረዳቱ ሸክም የራሳቸው ሆኖ እያለ ይህንን አላስረዱም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በትግራይ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 90/2/ መሰረት 2ኛ ተጠሪ ባለቤታቸው እዳ የገቡ ለመሆናቸው ቀደም ብለው ያወቁ እንደነበርና ለባለገንዘቦችም ቤቶችን ትወስዳላችሁ ሲሉ እንደቆዩ እየታወቀ ይህንን ባወቁ በ 6 ወር ጊዜ ውስጥ ግዴታው ውድቅ እንዲደረግላቸው ጠይቀው አላስፈረሱም፡፡ ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ ነጋዴ እንደነበሩና ያለ ንግድ ፈቃድ ቼክ ከባንክ እንደማይሰጥ እየታወቀ ንግድ ቢሮውም ሆነ ባንኮቹ ሳይጠየቁ፣ እንደዚሁም 2ኛ ተጠሪ እዳውን ለጋራ ጥቅም አለመዋሉን ሳያስረዱና ተቃውሞ አቅርበው ባላስፈረሱበት ሁኔታ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይሻርልን የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ ቼክ የተሰጠው ተጠሪዎች ባልና ሚስት መሆናቸው ተረጋግጦ ሳለ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪም በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ መሆኑ በታወቀበት ሁኔታ እዳው የጋራ አይደለም የተባለበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ መልስ ባለማቅረቡ መብቱ ታልፎ 2ኛ ተጠሪ እና አመልካቾች መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ እንዲቀባበሉ በማድረግ ክርክር ተደርጓል፡፡

የ 2ኛ ተጠሪ የሰበር መልስ ይዘት፡- አመልካቾች በቼክ ምክንያት ክስ ያቀረቡትና ያስፈረዱት በ 1ኛ ተጠሪ ላይ ሲሆን ሁሉም ቼኮች ደግሞ በ 1ኛ ተጠሪ ስም ከባንክ የወጡ ቼኮች እንጂ በ 2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገቡ ቼኮች አይደሉም፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 19 መሰረት ተበዳሪው ነጋዴ መሆን እንደሚገባው እና ነጋዴ ያልሆነ ባል ወይም ሚስት የሚበደረው ብድር ግን በዚህ የሕግ ድንጋጌ የማይሸፈን በመሆኑ ነጋዴ ያልሆነው ባል የወሰደው ብድር ነጋዴ ለሆነችው ሚስት ይመለከታታል ማለት አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከንግድ ውጭ ብቻቸውን የቆረጡት ቼክ 2ኛ ተጠሪ አያውቁትም የሚል እንደመሆኑ መጠን እና 1ኛ ተጠሪ ቼኩን ሲቆርጡ 2ኛ ተጠሪ ሚስት ከመሆናቸው ውጭ ስለቼኮቹ የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከንግድ እንቅስቃሴ ውጭ በስማቸው የያዙት ቼክ በ 2ኛ ተጠሪ የንግድ ልውውጥ የተቆረጡ ቼኮች ናቸው የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ፤ እንዲሁም ቼኮቹ በንግድ ልውውጥ ምክንያት የተሰጡ መሆኑ ባልተረጋገጠበት በ 2ኛ ተጠሪ ድርሻ ለአፈጻጸም ሊውል ስለማይገባ አመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግ የሚል ነው፡፡ አመልካቾች አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው 1ኛ ተጠሪ በሰጣቸው ቼኮች መነሻነት የአሁን አመልካቾች በ 1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው በተለያየ መዝገብ አስፈርደዋል፡፡ አመልካቾች ለአፈጻጸሙ እንዲውሉ የጠየቋቸው ክርክር ያስነሱ ንብረቶች በ 1ኛ ተጠሪ ስም የሚገኙ ቢሆንም ከ 2ኛ ተጠሪ ጋር በትዳር ውስጥ በነበሩበት ወቅት ያፈሯቸው የጋራ ንብረቶች በመሆናቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት እዳው የተጠሪዎች የጋራ እዳ አይደለም በማለት ውሳኔ የሰጠው ምንም እንኳ እዳው ከቼክ መስጠት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ቼኮቹ በ 1ኛ ተጠሪ የተሰጡት 2ኛ ተጠሪ የንግድ ፈቃዳቸውን ከመለሱ በኂላ በመሆኑ የጋራ እዳ ነው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ ነው፡፡ ሆኖም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ያጸናው እዳው የጋራ እዳ አይደለም በማለት ሳይሆን ክስ ቀርቦ የተወሰነበት 1ኛ ተጠሪ ላይ ብቻ በመሆኑና 2ኛ

ተጠሪ ባልተከሰሱበትና ባለእዳ ናቸው ተብሎ ሳይፈረድባቸው በአፈጻጸም ሊገደዱና ድርሻቸው ለአፈጻጸም ሊውል አይገባም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ በጋብቻ በተሳሰሩ ባልና ሚስት መካከል ከአንዱ ጋር የውል ግዴታ የገባ ሰው በዋናው ክርክር ሁለቱን አጣምሮ ሊከስ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ተዋዋይ በሆነው ተጋቢ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የተጋቢዎች የጋራ እዳ ነው ወይስ የተወሰነበት ተጋቢ የግል እዳ ነው የሚለው ክርክር ሊነሳ የሚችለው በአፈጻጸም ወቅት እንጂ ሌላኛው ተጋቢ ሊከሰስም ሆነ ሊፈረድበት አይችልም፡፡ ይህ ለመሆኑም ከዚህን ቀደም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 22891 በማናቸውም ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት ያለው ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ ክርክር ባስነሱ ንብረቶች ላይ ያላቸው ድርሻ ለአፈጻጸም ይውላል ወይስ አይውልም ለማለት በቅድሚያ በአፈጻጸም መዝገቡ እየተፈጸመ ያለው እዳ የጋራ እዳ ነው ወይስ የ 1ኛ ተጠሪ የግል እዳ ነው? የሚለው ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እዳው የጋራ ነው ወይስ የግል የሚለው ክርክር በአፈጻጸም ወቅት ሊነሳ አይችልም በማለት 2ኛ ተጠሪ ሳይፈረድባቸው ድርሻቸው ለአፈጻጸም አይውልም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስ በ 1ኛ ተጠሪ ላይ የተወሰነው የገንዘብ እዳ የጋራ እዳ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በተመለከተ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የጋራ እዳ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ የ 2ኛ ተጠሪ ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል አይገባም በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በዚህ ድምዳሜ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራካሪ በሆነው የፍሬ ነገር ጭብጥ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ አልሰጠበትም፡፡ ይህ ሰበር ችሎት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10/2/ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ እዳው የተጠሪዎች የጋራ እዳ ነው ወይስ የ 1ኛ ተጠሪ የግል እዳ የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ ማስረጃ መዝኖ የሚያረጋግጥበት የሕግ አግባብ ካለመኖሩም በላይ የአመልካቾችን የይግባኝ መብት የሚያጣብብ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መመለሱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እዳው የጋራ ነው ወይስ የግል የሚለው ክርክር በአፈጻጸም ወቅት ሊነሳ አይችልም፤ 2ኛ ተጠሪ ሳይፈረድባቸው ድርሻቸው ለአፈጻጸም አይውልም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ እዳው የተጠሪዎች የጋራ እዳ ነው? ወይስ አይደለም? እንዲሁም በአፈጻጸም ክርክር ባስነሱ ንብረቶች ላይ 2ኛ ተጠሪ ያላቸው ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል የሚገባው መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ ግራቀኙ ያቀረቧቸውን ክርክሮችና ማስረጃዎች በመመዘን የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ለይግባኝ ሰሚው ችሎት መመለሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 64323 ሰኔ 04 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ፣ በክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 85286 ሐምሌ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሃተታው በተገለጸው አግባብ አመልካቾች በ 2ኛ ተጠሪ ላይ ያስወሰኑት የገንዘብ እዳ የተጠሪዎች የጋራ እዳ ነው ወይስ የ 1ኛ ተጠሪ የግል እዳ? በሚለው ጭብጥ ላይ ግራቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ክርክር ባስነሱ ንብረቶች ላይ 2ኛ ተጠሪ ያላቸው ድርሻ ለአፈጻጸሙ መዋል መቻል አለመቻሉን አስመልክቶ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት ይመለስለት ተብሏል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 141527

ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች**፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች፡-** አቶ እለፋቸው ታምሩ አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እመቤት ተሾመ አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል አስመልክቶ የቀረበን አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ሲደረግ የነበረውን የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በተመለከተ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት አፈጻጸሙን ለመራው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ የይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት በላከው ምላሽ ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የሚችል መሆኑን ገልጾ ክፍፍሉ ሲፈጸም ለግራቀኙ በደረሰው ንብረት የሐብት ማጋደል ስለሚኖርበት ግራቀኙ ልዩነቱን በማካካስ የሚፈጽሙት ነገር ካለ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ መጥሪያ የተላከላቸው ቢሆንም የፍርድ ባለመብት ሃሳባቸውን ይዘው ቀርበው የፍርድ ባለእዳ ሀሳባቸውን ያላቀረቡ በመሆኑ አፈጻጸሙ በምን መንገድ መቀጠል እንዳለበት ፍ/ቤቱ ትእዛዝ እንዲሰጥበት በማለት ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራቀኙ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ በዋናው ውሳኔ ላይ የግራቀኙ የጋራ ንብረት ናቸው በማለት ፍርድ ያረፈባቸው ቤቶች ግራቀኙ ከተቻለ በዓይነት እንዲካፈሉት፣በዓይነት መካፈል ካልተቻለ ክፍፍሉን በተመለከተ በውሳኔው ላይ በተቀመጠው አማራጭ መሠረት እንዲካፈሉት በማለት የተሰጠ ውሳኔ ነው፣በፍርድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ቤቶቹ እኩል መካፈል እንደማይችሉ ተገልጿል፣የሐብት ማጋደል ባለበት ሁኔታ ግራቀኙ እንዲካፈሉ ለማድረግ የግራቀኙን ሥምምነት ይጠይቃል፣ግራቀኙ በሰጡት አስተያየት ሥምምነት የሌላቸው መሆኑን የገለጹ በመሆኑ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በውሳኔው ላይ በቀጣይ በተቀመጡት አማራጮች መሠረት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍ/ቤት አፈጻጸሙ በፍርዱ በተቀመጡት ሌሎች አማራጮች መሠረት እንዲፈጸም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ፍርዱ እንዳይፈጸም እና ዋጋ አልባ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፤የሚመለከተው አካል ፍርድ ያረፈባቸው ቤቶች ከዋናው ቤት ተነጥለው መሸጥ እንደማይችሉ፤ይዞታው ለሁለት እኩል ሲካፈል ለግራቀኙ ከ150 ካ.ሜ ያነሰ ቦታ ሊደርሳቸው ስለማይችል በዓይነት እኩል ማካፈል እንደማይቻል ያረጋገጠ በመሆኑ በፍርዱ በተቀመጡት ሌሎች አማራጮች መሠረት ፍርዱ ሊፈጸም አይችልም፤ፍ/ቤቱ ፍርዱን ለማስፈጸም ተስማሚ ነው የሚለውን ትዕዛዝ በመስጠት ፍርዱን ማስፈጸም ስላለበት ጉዳዩን በአግባቡ ካጣራ በኋላ ቤቶቹ የየራሣቸው የሆኑ ሁለት መግቢያ እና መውጫ በሮች ስሏሏቸው ግራቀኙ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / ተካፍለው እንዲገለገሉባቸው ከማድረግ ውጪ ፍርዱ የሚፈጸምበት ሌላ አማራጭ ስለሌለ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / ክፍፍሉ እንዲፈጸም በማለት ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በሌላ አማራጭ መሠረት ፍርዱ ይፈጸም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የበታች ፍ/ቤቶች አከራካሪ የሆነው ቤት ሊካፈልም ሆነ ሊሸጥ የማይችል ነው፤ሊካፈል የሚችለው በተነጻጻሪ ካርታ ነው በማለት ባለሙያ አስተያየት በሰጠበት ሁኔታ በሌላ አማራጭ ይፈጸም በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 91(1)እና(2) እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሐብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሐብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል፤እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል በማለት ይደነግጋል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች የሐብት ማጋደል ባለበት ሁኔታ ቤቱን

በዓይነት ለማካፈል የግራቀኙ ሥምምነት ያስፈልጋል፤ግራቀኙ ስምምነታቸውን ባልሰጡበት ሁኔታ በዓይነት ማካፈል የማይቻል በመሆኑ በውሳኔው በቀጣይ በተቀመጠው የክፍፍል አማራጭ መሠረት ውሳኔው ሊፈጸም ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ ቢሆንም የሚመለከተው አካል ቦታው በዓይነት ሲካፈል እያንዳንዳቸው 150 ካ.ሜ ማግኘት አለባቸው ሁለቱም ሠዎች የየራሣቸው መግቢያ እና መውጫ መንገድ ስላላቸው ሰዎቹ የሚሥማሙ ከሆነ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / መገልገል የሚችሉ መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ ተጠሪ መጠለያ እና ቀለብ ለመንፈግ የቀረበ ነው ከማለት በቀር ክፍፍሉ በተነጻጻሪ ካርታ ቢፈጸም የሚያመጣባቸው ጉዳት መኖሩን በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ቤቶቹ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / መከፋፈል እንሚችሉ በሚመለከተው አካል እስከተገለጸ ድረስ በቤተሰብ ሕጉ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በተቻለ መጠን ባልና ሚስት ንብረታቸውን በዓይነት የመካፈል መብታቸውን ባስጠበቀ መንገድ ሊፈጸም ይገባዋል የሚለውን የክፍፍል መርህ ባስጠበቀ መልኩ በዚሁ ቤቶቹ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / እንዲከፋፈሉ በዚሁ አግባብ ክፍፍሉ ሲደረግ የበለጠ ይዞታ የደረሰው ወገን ለሌላው ወገን ግምቱን እንዲከፍል በማድረግ ማስፈጸም ሲገባው በፍርዱ በተቀመጠው ሌላ አማራጭ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም በማለት መወሰኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 117839 ሕዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 193470 ሚያዝያ 18 ቀን 2009 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው በተገለጸው መሠረት አፈጻጸሙን እንዲቀጥል ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

-የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ 117839 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡

-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

የሰ/መ/ቁ. 136872

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ህፃን እስጢፋኖስ ኃይሉ ሞግዚት ወ/ሮ ብርቱካን ተረፈ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሽቱ ቦንገን-ጠበቃ ነገደ ለማ -ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በ21/11/2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ሟች አቶ ኃይሌ ተረፈ ውርስ እንዲጣራ አመልክተው ተጠሪ ባሉበት ወርሱ እንዲጣራ በማድረግ ግራ ቀኙ ሪፖርቱን አስመልክተው አስተያየት ከሰጡ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ሪፖርቱን መዝግቦታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 101 የሆነው የንግድ ኮንቴነር ሱቅና ከሱቁ የተገኘው የኪራይ ገንዘብ የሟችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ስለሆነ ተጠሪ ግማሽ ድርሻ አላት በማለት

የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 18 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 101 የሆነው የንግድ ኮንቴነር ሱቅ ላይ ተጠሪ ግማሽ ድርሻ አላት ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁን ተጠሪና ሟች ባልና ሚስት እንደነበሩና ጋብቻቸውም የተፈፀመው በ2001 ዓ.ም እንደሆነ፣ሟች አቶ ኃይሌ ተረፈ የንግድ ፍቃድ የተሰጣቸው ከጥር 5 ቀን 1998 ዓ.ም አንስቶ እንደሆነ፣ ለክርክር ምክንያት የሆነው ኮንቴነሩን/የንግድ ቤቱን/ በኪራይ ያገኙት ግን ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን የጉለሌ ክ/ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት የንግድ ምዝገባ ፍቃድ እና ግብይት ዋና ስራ ሂደት በ28/06/2008 ዓ.ም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በላከው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ለክርክር ምክንያት ሆነው የኮንቴነር ሱቁ በጋብቻ ውስጥ መንግስት በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋም አደራጅቶ የሰጣቸው መሆኑን ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ኮንቴነር ሱቁ /ንግድ ቤቱ/ ከጋብቻ በፊት የተገኘ የሟች የግል ንብረት በመሆኑ ኮንቴነር ሱቁና የኪራይ ገንዘብ ግማሹ የተጠሪ ድርሻ

መባሉ አግባብ አይደለም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች የኮንቴነር ሱቁ እና ከሱቁ ኪራይ የተገኘው ገንዘብ የተጠሪና የሟች የጋራ ሀብት በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46454 ሰኔ 22 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 170166 ሐምሌ 25 ቀን 2008 ዓ/ም በውሳኔ የተሻሻለው እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁጥር 132640 ታህሳስ 28 ቀን 2009 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ከዚህ ፍርድ ቤት ጥር 29 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት በመ/ቁ. 28805 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰበር መ.ቁ. 126411

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ/ም

**ዳኞች**፡- አልማዉ ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

**አመልካች**፡- አቶ ተስፋጊዮርጊስ አዳነ -ጠበቃ ኤልያስ መሐመድ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አሰፉ ግርማ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረዉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ፣ ወ/ሮ አለም መንግስተአብ ደግሞ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ከአሁኑ አመልካች ጋር እንደባልና ሚስት በመሆን አብረን የኖርን ስለሆነ ንብረት ሊያካፍለኝ ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካች ከተጠሪ ጋር በሕግ ጥበቃ በሚደረግለት ግንኙነት ውስጥ ያልነበሩና በጋራ ያፈሩት ንብረትም የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ሕጋዊ ሚስት ነኝ ያሉት ግለሰብም ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ጥያቄ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ፈቅዶላቸው ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አመልካች ከሁለቱም ሴቶች ጋር እንደባልና ሚስት የኖሩ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም የተሻለ ያስረዱና መጀመሪያ ከአመልካች ጋር መኖር የጀመሩት የአሁን ተጠሪ ናቸው በማለት አመልካችና ተጠሪ ንብረቱን እኩል ከተካፈሉ በኃላ የአሁኑ አመልካች

ከድርሻቸው ለስር ጣልቃ ገብ እንዲያካፍሏቸው ጣልቃ ገቢ መጠየቅ ይችላሉ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካችና የስር ጣልቃ ገብ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ እና በስር ፍርድ ቤት የተሰሙትን የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሚ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ከአሁኗ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት መኖር የጀመሩት ከ1996 ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ ተጠሪ በምስክሮቻቸው ማስረዳታቸውን፣ አመልካች ከስር ጣልቃ ገብ ጋር እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር የጀመሩት ደግሞ ከ1995 ዓ/ም ጀምሮ በማስረጃ ተነግሯል ወደሚል ድምዳሜ ደርሶ የስር ፍርድ ቤት ሁለቱንም ሚስቶች ናቸው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተገቢ ቢሆንም በንብረት መብት ረገድ ቅድሚያ ደረጃ ሊሰጣቸው የሚገባው ግን የአሁኗ ተጠሪ ሳይሆኑ ለስር ጣልቃ ገብ ሁኖ እያለ ይኼው መታለፉ ያላግባብ ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማሻሻል የጣውላ ቤት ድርጅትና 46 ካ/ሜትር የማህበር ቤት የአሁኑ አመልካችና የስር ጣልቃ ገብ የጋራ ሃብት ሁኖ ሊከፈል እንደሚገባ፣ ከአሁኑ አመልካች ድርሻ ግማሹን ማለትም ከጠቅላላ ንብረቱ ¼ኛው ለአሁኗ ተጠሪ እንዲያካፍሉ፣ ክፍፍሉም በአይነት ወይም ግምቱን በመክፈል ሊከናወን ይገባል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ሲያከራክር ቆይቶ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት በተሠጠው ውሳኔ ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ በወሰነበት አግባብ ድጋሚ ይግባኝ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል ምክንያት ወደ ፍሬ ነገሩ ሳይገባ የአመልካች ይግባኝ መዝገብ ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አጣሪ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከተጠሪ ጋር በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ግንኙነት ውስጥ የነበሩ ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ ሳይረጋገጥና አመልካች ከ1988 ዓ/ም ጀምሮ ከሌላ ሴት ጋር በሕጋዊ ግንኙነት ያሉ መሆኑ የሚያሳዩ ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይታዩ መታለፋቸውን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ከ1996 እስከ 2004 ዓ/ም እንደባልና

ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ነበር በማለት የሰጡት ውሳኔ እንዲሻር ቅድሚያ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑንና በአማራጭ ደግሞ ብር 75,000.00 ተጠሪ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ከንብረቱ ¼ኛ እንዲወስዱ የሚያደርግ የክፍፍል ውሳኔ መሰጠቱ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰዉ ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከተጠሪ ጋር በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ግንኙነት የለኝም፣ በስር ፍርድ ቤቶች መታየት የነበረባቸው ውሳኔዎች በማስረጃነት አልታዩም፣ የተጠሪ ምስክሮች ዘመዶቻቸው ሆነው በሐሰት የሠጡት የምስክርነት ቃል የማስረጃነት ዋጋ መሰጠቱ ያላግባብ ነው የሚሉ ነጥቦችን በማንሳት ስለመሆኑ ከሰበር አቤቱታቸው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የማስረጃ አሰማም ላይ ቅሬታ አድሮባቸው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠሪን ምስክሮች እንደገና የሰማ ሲሆን የተጠሪ ምስክሮችም በስር ፍርድ ቤት የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመድገም አመልካች እና ተጠሪ እንደባልና ሚስት ሁነው ከ1995 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2004 ዓ/ም ድረስ አብረው የቆዩ መሆኑን፣ ከ1991 እስከ 1995 ዓ/ም መጀመሪያ ድረስ በፍቅር ጓደኝነት የቆዩ መሆኑን ማስረዳታቸውን፣ ምንም እንኳን የአሁኑ አመልካች የስር ጣልቃ ገብን ሚስቴ ናት በማለትና ንብረቶችን ደግሞ የሌላ ሚስቴና የግሌ ልጅ በሰጠችኝ ብር የተገዙ ናቸው የሚል ክርክር ቢያቀርቡም በስር ፍርድ ቤት የተሰሙት የአመልካች ምስክሮች ግን አመልካችና የስር ጣልቃ ገብ ባልና ሚስት እንደሆኑ፣ ጋብቻ ግን ሲፈጸም አለማወቃቸውን፣ የስር ጣልቃ ገብም አራት ልጆችን ወልደው ከአሁኑ አመልካች ጋር አብረው እንደሚኖሩ ያስረዱ መሆናቸውን፣ እነዚህ የአመልካች ምስክሮች አመልካች ከተጠሪ ጋር ግንኙነት የላቸውም በማለት ያላስረዱና ስለንብረቱም ያስረዱት ነገር ያለመኖሩን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት

የደመደመ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ድምዳሜ የተያዘው ደግሞ ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲል የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሚ በመስማት ፍሬ ነገሩን በሚገባ ከአጣራና በጉዳዩ በሕጉ አግባብ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ከመዘነ በኋላ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ድምዳሜ ደግሞ ከስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ጋር ተመሳሳይ ከመሆኑም በላይ በሕጉ አግባብ የተቆጠሩትንና የተሰሙትን ማስረጃዎችን በመመዘን የተያዘ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሊለወጠው የሚችለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ለዚህ ችሎት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረምን እንጂ የፍሬ ነገር ማጣራት ስህተት ወይም የማስረጃ ምዘና ስህተትን የሚመለከተውን ጉዳይ አይደለምና፡፡ በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ ጋር ሕጉ ጥበቃ በሚያደርገው ግንኙነት ውስጥ አልነበርኩም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ አይችልም በማለት አልፈነዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖርን ግንኙነት ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃ ግንኙነቱን የማሳየት ብቃት ያለው መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ከአረጋገጡ ሕጉ ግንኙነቱን ጥበቃ የሚያደርግለት መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 109፣110፣113፣ 117 እና ከሌሎች ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር በሕጉ ጥበቃ ሊደረግ የሚገባው ግንኙነት ስላለመኖሩ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀፅ 117 (4) ድንጋጌ አግባብ የማስረዳት ግዴታቸውን ያልተወጡ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ንብረቶቹ የግላቸው ስለመሆኑም በአዋጁ አንቀፅ 114 እና 97 ድንጋጌዎች መሰረት የማስረዳት ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ ባቀረቡት ክርክር ድርሻቸው ¼ኛ እንዲሆን በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ግልጽ የሆነ ቅሬታ ያላቀረቡና ክፍፍሉም የእኩልነት መርህን ወይም የእያንዳንዱ ተጋቢ በንብረቱ ላይ የነበረውን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት መኪናውን ነበረበት በማለት ያቀረቡት ክርክር ካለመኖሩም በላይ በሰበር አቤቱታቸው መጨረሻ ላይ የጠየቁት ዋናም ሆነ አማራጭ

የዳኝነት ጥያቄ መጠንም በዚህ ረገድ የሚጠቅሰው ግልጽ የሆነ የዳኝነት ጥያቄ የሌለ በመሆኑ የሠበር አጣሪው ስለንብረት ክፍፍሉ የያዘውን ጭብጥ ተገቢነት ያልነበረው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠው የግራ ቀኙ ክርክር በአግባቡ ተሰምቶና ፍሬ ነገሩም በሚገባ ተጣርቶ የግራ ቀኙን የማስረጃ ማቅረብና የማስረዳት ግዴታቸውን ባገናዘበ መልኩ ከመሆኑ ውጪ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻልበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በአማራ ክልል በጎንደር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0228 ጥር 29 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁጥር 01-16605 በ27/07/2007 ዓ/ም ተሻሽሎ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር አጣሪ ችሎት በመ.ቁ 03-56035 መጋቢት 01 ቀን 2008ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ከአሁኗ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት መኖር የጀመሩት ጊዜ በ1996 ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ ተጠሪ በምስክሮቻቸው አስረድተዋል፣ ከአሁኑ አመልካች ድርሻ ግማሹን ማለትም ከጠቅላላ ንብረቱ ¼ኛውን ለአሁኗ ተጠሪ እንዲያካፍሉ፣ ክፍፍሉም በአይነት ወይም ግምቱን በመክፈል ሊከናወን ይገባል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለ

መ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 137853

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ በለጠ ነጋሽ-ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እጅጋየሁ ላቀው-ጠበቃ ጎሳዬ ነጋሽ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የህግ አሳዳጊዬ የሆኑት ወ/ሮ በለጤ ግዛው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቷ ሟች አሳዳጊዬ በህይወት ዘመንዋ ያፈራችውን የግል ቤትዋን እና የገጠር እርሻ መሬት ከአሁንዋ ተጠሪ ከአሳዳጊዬ ልጅ ጋር እኩል እንድንካፈል እንዲውሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ለአቤቱታው በሰጡት መልስ የሟች ንብረትም ይሁን ይዞታ ሁሉም በስጦታ ውል አግኝቻለሁ፤አመልካችም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የጉዲፈቻ ውሉ ስላልፀደቀ የመውረስ መብት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪን መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ የሟች ሀብትና የገጠር ይዞታ ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም በፊንፊኔ ዙሪያ ለኦሮሚያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ በሟችና በአመልካች መካከል በ1996 ዓ.ም የተደረገው የጉዲፈቻ ውል በኦሮሚያ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 እና 83/1996 መሰረት እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ሰው የጉዲፈቻ ውል ሲደረግም ሆነ ፍርድ ቤት ሲያፀድቅ እድሜው 27 አመት እንደሆነ የውል ሰነድ ራሱ ያሳያል፤ ይህ ደግሞ ለህግ ተቃራኒ በመሆኑ አንድም መብት መስጠት አይችልም በማለት ፀድቋል የተባለው የጉዲፈቻ ውል ውድቅ በማድረግ አመልካች ከገጠር መሬት ይዞታ ውጭ ያለው የሟች ንብረት መውረስ አይችልም፤በሌላ በኩል የገጠር መሬትን አስመልክቶ የሟች ቤተሰብ ከሆነ የመውረስ መብት ያለው ስለሆነ ይህ ደግሞ በማስረጃ ከተጣራ በኋላ እንዲወሰን ጉዳዩን ለወረዳ ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡

የአሁን አመልካች የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 8 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 20 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ጉዳይ ወራሽነቱን ያረጋገጠበት መዝገብ ሳይሻር የውርስ ሀብት ለመጠየቅ ባስከፈተው መዝገብ ወራሽነት በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው ሚችና አመልካች በ1996 ዓ.ም የጉዲፈቻ ስምምነት ማድረጋቸው፤ስምምነቱም ለፍርድ ቤት ቀርቦ በመ/ቁ.498/96 ስምምነቱ ህጋዊ መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን፤ይህ ውሳኔ መቃወሚያ ቀርቦበት ያልተሻረ መሆኑን ከክርክሩ ሂደትና ከስር መዝገብ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ የአመልካች ጥያቄ የጉዲፈቻ ውሳኔ ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት የተወሰነ በውርስ አቤቱታ በተከፈተ መዝገብ እንደማስረጃ የቀረበውን ሰነድ መቃወም አትችልም፤የጉዲፈቻ ውሳኔ ስህተት ቢኖረው እንኳን በተወሰነበት መዝገብ ላይ መቃወሚያ ማቅረብ የምትችልበት እንጂ በዚሁ የውርስ ፋይል ላይ ማቅረብ የማይገባውን በመቀበል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ ደግሞ አመልካች በተሻረና ለጉዲፈቻነት በህግ በተቀመጠው ከ18 ዓመት እድሜ በላይ በ27 ዓመቱ የተደረገን የጉዲፈቻ ውል መነሻ በማድረግ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት ድረስ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ህግን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ እዚህ ሊታይ የሚገባው ነጥብ የጉዲፈቻ ውል ውሳኔ ፀንቶ ባለበት ሁኔታና ሳይሻር በውርስ ንብረት ክፍፍል በተጠየቀበት በሌላ መዝገብ የመታየቱ ጉዳይ ነው፡፡ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለ አንቀጽ 202 መሰረት ከ18 ዓመት እድሜ በላይ የጉዲፈቻ ልጅ መሆን እንደማይችል ይደነግጋል፡ አመልካችም እድሜው 27 ዓመት የነበረ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ሚች ወ/ሮ በለጤ ግዛው አመልካችን የጉዲፈቻ ውል ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ፤.ይህ ውሳኔ መብቴን ይነካል የሚል ወገን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41፤358 በክርክሩ ገብቶ መቃወም ወይም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን መቃወሚያ በማቅረብ መጀመሪያ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝ ማድረግ እየተቻለ አመልካች ወራሽነቱን በማረጋገጥ የሚች ንብረት ድርሻውን በጠየቀበት መዝገብ ላይ የጉዲፈቻ ውል አስመልክቶ የተሰጠ ውሳኔ ላይ ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በፍርድ ቤት የፀደቀ /የተሰጠ/ ውሳኔው ሳይሰረዝ የተሻረበት አግባብ ስነስርዓት ህጉን ያልተከተለ በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል ስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36014 ጥር 14 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 24227 ህዳር 14 ቀን 2008 ዓ/ም በመሻር የሰጠው ውሳኔ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 227747 የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ/ም እና በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 242197 ህዳር 3 ቀን 2009 ዓ/ም በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የሚች ወ/ሮ በለጤ ግዛው የጉዲፈቻ ልጅ ስላልሆነ ሊወርስ አይችልም በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል በመሻር በሱሉልታ ወረዳ ጎርፎ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ መኖሪያ ቤት የመውረስ መብት ስላለው ከተጠሪ ጋር እኩል ሊካፈሉ ይገባል ብለን ወስነናል፡፡
3. የስር ፍርድ ቤቶች በገጠር እርሻ መሬት ይዞታ በተመለከተ የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት የመ/ቁ.36014 የሆነውን በማንቀሳቀስ የገጠር መሬት አዋጅ በሚያዘው መሰረት የግራ ቀኙ ማስረጃ እንደገና በማጣራት ውሳኔ እንዲሰጥበት የተመለሰው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 133736

ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም.

**ዳኞች---ዳኜ መላኩ**

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች፡**-1ኛ አቶ መዚድ ተስፋዬ አህመድ

2ኛ አቶ መርዙቅ ተስፋዬ አህመድ ጠ/ወልደሰስላሴ ብርቱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡**- ወ/ሮ ዘይነባ ለካ ሱሩር ጠ/መሀዲ ሁሴን ቀረበ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ከሣሽ አመልካቾች ሆነው ተከሣሽ ተጠሪ በመሆን በኪራይ ውል መነሻነት ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረው ክስ የሚያመለክተው በቂ/ክ/ከ/ወረዳ 18 ቁጥሩ 063/መ/ ተመዝግቦ የሚያታወቀውን የፋብሪካ ውጤቶች የህንጻ መሳሪያ ንግድ ድርጅት የከሣሾች እህት ከሆነችው ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዩ በወር ብር 5,000/አምስት ሺ ብር/ ከሚያዝያ 03/2003 ጀምሮ ተከሣሾች መከራየታቸውን ሆኖም ከሚያዝያ 03/2004 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጥቅምት 02/2005 ዓ.ም.ድረስ የአንድ ዓመት ኪራይ ብር 60000.00 /ስድሣ ሺ ብር/ አልከፈሉም፡፡ በተጨማሪም ጥቅምት 03ቀን 2005 ዓ.ም.እስከ ጥር 23/2005 ዓ.ም. ድረስ ያለውንም ኪራይ ብር 18,333.33 አልከፈሉም፡፡ ተከሣሽ እንዲከፍሉ

ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ለመክፈል ፈቃደኛ አይደሉም ስለሆነም በድምሩ 78,333.33 / ሰባ ስምንት ሺ ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር ከሰላሳ ሶስት ሣንቲም/ ከወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከጥቅምት 03/2004 ጀምሮ ያለውን የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ሲሆን ክሱን ያቀረቡት 6 ወር ካለፈው በኋላ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የንግድ ቤቱ የከተማው አስተዳደር ንብረት ስለሆነ መቅረብ ያለበት በከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤት ነው፣ ከሣሾች ቤት አላከራዩንም ያከራዩን እህታቸው በመሆናቸው ቤቱ ለአሁን ተከሣሽ ይገባል በማለት አስተዳደሩ የወሰነው በአግባቡ በሚል እንጂ የኪራይ ውል አለ ብሎ አልወሰነም ስለሆነም የኪራይ ገንዘብ ለመጠየቅ የሚያስችል ውል ስለሌላቸው ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ግራ ቀኙን በቃል አከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ከወሰነ በኋላ ቀሪውን መቃወሚያ አስመልክቶ ተከሣሽ ኪራዩን የተከራየሁት ከከሣሾች እህት ወ/ሮ አሰለፈች እንጂ ከከሣሾች አይደለም በሚል የተከራከሩ ሲሆን የኪራይ ውሉ ላይ ወ/ሮ አሰለፈች በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ድርጅት ለተከሣሽ አከራይቻለሁ የሚል ተገልጿል እንጂ ከሣሾችን በመጨመር ወይም ሞግዚትና አስተዳዳሪ መሆናቸውን በመግለጽ የተፈፀመ ባለመሆኑ ከሣሾች ይህን ውል መሠረት በማድረግ ክስ ያቀረቡት የመክሰስ መብት ሳይኖራቸው ነው በማለት በብይን መዝገቡን መዝጋቱን የመ/ቁ/ 22834 የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው የብይን ግልባጭ ያሣያል፡፡

አመልካቾች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢሉም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 177126 ሐምሌ 26 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ይግባኝ ቅሬታውን በትዕዛዝ ውድቅ ማድረጉን ተመልክተናል፡፡

አመልካቾች በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ፡- አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት የኪራይ ገንዘብን አስመልክቶ ባቀረቡት ክስ ላይ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑን፣

ምክንያቱም የንግድ ቤቱ የተከራይነት መብት የመጣው ከአመልካቾች ወላጆች ከአቶ ተስፋዬ አህመድ ናጂ እና ከወ/ሮ በላይነሽ ምሩሪ እንደሆነ የኪራይ ውሉ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡

የወራሽነት ማስረጃንም አቅርበዋል፣ የአውራሻቸውን መብት እና ግዴታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 826/2/ መሠረት ለወራሾች ተላልፏል፡፡ አመልካቾች አካለ መጠን ባላደረሱበት ጊዜ እህታቸው ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዬ አካለመጠን ላላደረሱት ልጆች ሞግዚት ለመሆናቸው ሐምሌ 30 ቀን 1995 ዓ.ም. በመ/ቁ/ 1904/95 የተሰጠ ውሣኔን በማቅረብ ተረጋግጧል፡፡ ወ/ሮ አሰለፈች በውርስ የመጣውን ክርክር ያስነሳውን የንግድ ድርጅት ከቂ/ክ/ከ/ወ/8 ጋር ሲዋዋሉ እነ አሰለፈች ተስፋዬ በማለት የተከራዩ መሆኑን ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ተጠሪ ወራሽና ሞግዚት ከሆኑት ከወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዬ በተከራዩት የንግድ ቤት ላይ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ በአ.አ.ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት ቂ/ክ/ከ/ ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 07615 እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሁለት መዛግብት ተጣምረው በተሰጠው ፍርድ ቁጥሩ 063/መ/ ያሁን አመልካቾች ወላጆች አቶ ተስፋዬ አህመድና ወ/ሮ በላይነሽ ምሩሪ በጋብቻ እያሉ ለንግድ አገልግሎት በጋራ ተከራይተውት የነበረ መሆኑን የይግባኝ ባይ ወላጆች ሲሞቱ የተከራይነቱ መብት በሕይወት ላሉት ልጆቻቸው የተላለፈ መሆኑን፣ አመልካቾች አቅመ አዳም ባለመድረሳቸው እነ አሰለፈች ተስፋዬ በሚል እህታቸው ያደረጉት የኪራይ ውል ሌሎችንም የሚጭምር በመሆኑ መብት ያላቸው መሆኑን ስለሚያሳይ ስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምላቸው በጠበቃቸው አማካይነት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በሚል ጭብጥ ይዞ በመላኩ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡ አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪ ደርሷቸው መልስ እንዲያቀርቡ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው ሲሆን ሚያዝያ 12 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበው ተያይዟል፡፡ ይዘቱም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ብቻ እንደተመለከትነው ፡- በወ/ሮ አሰለፈች በስሟ ላደረገችው የኪራይ ውል አመልካች እንዴት ከእኔ ጋር የቤት ኪራይ ውል አለኝ በማለት እንደሚችል ያላስረዳና ሊያስረዳም ስለማይችል የሰበር ችሎቱ ውሣኔውም ቢሆን ቤቱ ለአመልካች ይገባል ከማለት በቀር በእኔ እና በአመልካች መካከል ውል ማቋቋም ስለማይችል የአመልካችን

ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ አግባብ ነው በማለት አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበው አቤቱታ አጠቃላይ ክርክር እና አግባብነት ያለውን የህግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የኪራይ ገንዘብ ይከፈለን የሚል ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የኪራይ ውል ማድረጋቸውን ገልፀው ነገር ግን ከአመልካቾች ጋር ሣይሆን ከእህታቸው ጋር የተዋዋልኩ እና ውሉም እነሱን ስለማይገልጽ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም ተብሎ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በተከሣሽ ላይ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላችሁም በማለት በብይን ክሱን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ማጽናቱን ተመልክተናል፡፡

የአመልካቾች ጥያቄ በአጣሪው ከተያዘው ጭብጥ አኳያ ስንመለከተው ክርክር የተነሳበት የንግድ ድርጅት ከአመልካቾች ወላጆች መብቱ በውርስ የተላለፈላቸው ሲሆን በጊዜው ህጋዊ ተግባር ለመፈፀም አመልካቾች አቅመ አዳም ያልደረሱ በመሆኑ ወራሽነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በእህታቸው ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዬ አማካይነት ከአስተዳደሩ ጋር የኪራይ ውል በንግድ ቤቱ ላይ "እነ ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዬ" በሚል የተዋዋሉ በመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ወ/ሮ አሰለፈች የአመልካቾች ሞግዚት እና ወራሽም መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ ክርክር ባስነሳው የንግድ ቤት ላይ ያላቸው መብት ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል ሲሆን ለሌላ ሰው ንብረቱን በሚያከራዩበት ጊዜ ይህንን የሞግዚትነት ሥልጣን ተላብሰው እንጂ በራሳቸው ሙሉ ስልጣን ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ግለሰቧ በዛ የንግድ ቤት ላይ ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል ድርሻ ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡

በዚህ ክርክር ባስነሳው የንግድ ቤት ላይ በስር ፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ ክርክር ተደርጐበት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የነበረ እና በሠ/መ/ቁ/ 84037 በሆነው መዝገብ ላይ ግንቦት 19/2005 ዓ.ም. ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡

በዚህ የሰበር መዝገብ ላይ ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ በሰጠው ማጠቃለያ ውሣኔ የንግድ ቤቱን የአመልካቾች ሞግዚት ለሌላ 3ኛ ወገን አሳልፈው ያከራዩት መሆኑን እና በመመሪያውም

ያለአስተዳደሩ እውቅና አሳልፈው ማከራየታቸው የተከራይነት መብቱን ወደ ተከራየው ሰው የሚያዛውር በመሆኑ ወ/ሮ አሰለፈች ይህንን በውርስ ለወራሾች የተላለፈላቸውን ንግድ ቤት ያለአስተዳደሩ እውቅና ማከራየታቸው በራሳቸው በኩል ያለውን የተከራይነት መብት የሚያቋርጥባቸው እንጂ የሌሎች በሞግዚትነት የሚያስተዳድሯቸውን ወራሾች መብት የሚነካ መሆን እንደሌለበት በመግለጽ ፣ በሰበር መዝገቡ ላይ አመልካች በዚህ በያዝነው መዝገብ ደግሞ ተጠሪ የሆኑት ግለሰብ በመመሪያው መሠረት ንግድ ቤቱን ከአስተዳደሩ በቀጥታ በራሷ ስም ለመከራየት እንደመብት ጥያቄ ለማቅረብ የማያስችላት ሁኔታ አይኖርም ስለሆነም አስተዳደሩ የሌሎች ወራሾችን የተከራይነት መብት ሊያስቀጥል በሚያስችል መልኩ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰዱ በአግባቡ ነው በማለት በስር የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ማጽናቱን የውሣኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ወ/ሮ አሰለፈች በስማቸው በሞግዚትነት የሚያስተዳድሯቸው ወራሾችን ንብረት ለተጠሪ አከራይተው እንኳን ቢሆን የተከራይ አከራይ መመሪያ ወ/ሮ አሰለፈችን ከሚመለከት በስተቀር ሌሎች ወራሾችን የሚመለከት እንደማይሆን እና ከአስተዳደሩ ጋር ሌሎች ወራሾች የመከራየት መብታቸው የሚቀጥል መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ወ/ሮ አሰለፈች ያከራዩት ንብረት በግላቸው መብት ያገኙበት ሣይሆን የሌሎችንም የሚጭምር በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

በዚህ ረገድ አመልካቾች በውርስ ባገኙት መብት መነሻነት የኪራይ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍሉ የጠየቁ በመሆኑ ክርክር ባስነሳው የንግድ ቤት የኪራይ ውል መነሻነት ክስ በተጠሪ ላይ ለማቅረብ የሚያበቃ መብትና ጥቅም ያላቸው በመሆኑ መብትና ጥቅም የላችሁም በማለት የስር ፍርድ ቤት በብይን መዝገቡን መዝጋቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንን ስህተት ሳያርም ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ሊሻር የሚገባው ነው ብለን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/22834 በ18/6/08 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 177126 በ26/11/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት

የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ አመልካቾች ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም አላቸው ብለናል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በብይን የዘጋውን መ/ቁ/ 22834 በማንቀሳቀስ  አመልካቾች ያልተከፈለን የኪራይ ገንዘብ ተጠሪ ሊከፍሉን ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክስ ከተጠሪ ጋር በሞግዚትነታቸው መነሻነት የኪራይ ውል የፈፀሙትን ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዬን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 41 መሠረት ወደ ክርክር እንዲገቡ በመጥራት በፍሬ ነገር ላይ በማከራከር ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 341/1/ መሠረት አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን እንዲወስን መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

የሰ/መ/ቁ. 130284

ጥቅምት 30 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

አብርሃመሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1.አቶ ክንፈ ሐጎስ
2. ቄስ ወረደ ሐጎስ
3. ወ/ሮ ለተብርሃን ገ/ሂወት
ከጠበቃቸው ሃይለ ገብረማርያም ጋር ቀረቧል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዛፉ ሐጎስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በትግራይ ብ/ክ/መ/ በመቐለ ከተማ በዓይደር ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካቾች ለተጠሪ ተቃዋሚ ሆነው

ባቀረቡበት የውርስ ማጣራት መቃወሚያቸው ውድቅ በማድረግ ያቀረቡት ውርስ ማጣራት ፀድቆ የወንድማቸው የወራሽነት ማስረጃ የተሰጣቸው መሆኑ በመግለፅ ወንድማቸው አቶ ዮሴፍ ሐጎስ በህይወት እያለ በመቐለ ከተማ ዓይደር ክፍለ ከተማ ቀበሌ ሰርፀ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ስፋቱ 250 ካ/ሜ ግምቱ ብር 300,000.00 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ የሆነው ከተጠሪ ትዳር ከመመስረታቸው በፊት የተፈራ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ የወራሾች ስለሆነ ተጠሪ ከዚህ ቤትና ቦታ እንዲወጡና ሌላ የውርስ ዕቃ ድርሻ እንዲያስረክቡን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ ለክሱ የሰጡት መልስ ከ1989 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ እንደ ባልና ሚስት ሆነን አንድ ላይ እየኖርን ቆይተን በህዳር 1996 ዓ.ም እስከ እለተ ሞታቸው 2005 ዓ.ም ከአቶ ዮሴፍ ሐጎስ ጋር በጋብቻ ስለነበርን በኤርትራ የሚኖሩ ክብሮም ዮሴፍና ዘካሪያስ ዮሴፍ የተባሉ የሟች ልጆች በሟች የሚታወቁ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዲያካፍሉኝ ለመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቤ፤ፍርድ ቤቱም አጣርቶ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤትና ቦታ ሆነ ሌላ የሟች ሀብት ግማሹ ለተጠሪ ግማሹ ደግሞ ለሟች ወራሾች እንዲሆን ወስኗል፡፡ የሟች ልጆች እያሉ አመልካቾች ወራሾች ሊሆኑ ስለማይችሉ ለመክሰስ መብት የሌላቸውና ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገሩ የሰጡት መልስ ደግሞ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤትና ቦታ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት እንጂ የሟች የግል ንብረት አይደለም፤ በሽምግልናም የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የቀረበው ክስ ውድቅ በማድረግ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉ ተብሎ እንዲወሰንላቸው የመከላከያ መልሳቸው አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም በመጀመሪያ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ዘግቶት እንደነበረ ነገር ግን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣንህ ነው በማለት በነጥብ ከተመለሰ በኂላ መቃወሚያዎቹ በብይን ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኂላ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤትና ቦታ በከፍተኛ መቐለ ከተማ  ፍርድ ቤት ግማሹ የሟች አቶ ዮሴፍ ልጆች ቀሪው ግማሽ ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን ተወስኖ በዚሁ ውሳኔ መሰረት በስማቸው የተመዘገበ በመሆኑና የከፍተኛ ፍርድ ውሳኔ እስካልተሻረ ድረስ አመልካቾች ሟች ልጆች የለውም በማለት ያቀረቡት ክርክርና የጠየቁት ዳኝነት አይገባቸውም ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለመቐለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም አመልካቾች የሟች ወራሾች መሆናቸው የሚያረጋግጥ የፍርድ ቤት ውሳኔ ቅጂ ስላቀረቡ ተጠሪ በዚሁ የውርስ ማጣራት መቃወሚያ አቅርበው ውድቅ መደረጉ፤በመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ክብሮም ዮሴፍ እና ዘካሪያስ ዮሴፍ ራሳቸው ወይም በወኪላቸው ዳኝነት ጠይቀው ወይም ተከራክረው ሳይሆን ተጠሪ ራሳቸው በይዞታቸው ለሚገኘው ንብረት እነዚህ የሟች ልጆች ባለእኩል ናቸው በሚል በእነርሱ ላይ ክስ መስርተው በሌሉበት የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ አመልካቾች ነን ብለው ቢያረጋግጡም በቀጥታ ወራሾች አለን ብለው የቀረበ ተቃውሞ ስለሌለ ክብሮምና ዘካሪያስ ቀጥታ ወራሾች መሆናቸው ያቀረቡት የውርስ ማስረጃ ሆነ ክርክር ስለሌለ ህጋዊ ወራሾች ናቸው ለማለት ስለማይቻል፤አመልካቾች ግን የፍርድ ቤት የውርስ ማስረጃ ስላቀረቡ ወራሾች የማይሆኑበት ህጋዊ ምክንያት የለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤትና ቦታ ግማሹ አመልካቾች በወራሽነታቸው፤ ግማሹ ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የሟች 1ኛ ደረጃ ወራሾች የሆኑ የሟች ልጆች መኖራቸው የፍርድ ቤት ውሳኔና አፈፃፀም ትእዛዝ ተረጋግጦ እያለ ፤ይህ የፍርድ ቤት ውሳኔና ትእዛዝ ደግሞ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ባልተቀየረበት 1ኛ ደረጃ ወራሾች እንደሌሉ ታስቦ የሟች ሀብት ድርሻ ለ2ኛ ደረጃ ለሆኑ ወራሾች እንዲሆን የተሰጠ ውሳኔ ህጋዊነት ስሌለው ሊሻር ይገባል በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ሰኔ 10 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 9 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመርመርነውም የአመልካቾች ጥያቄ በአመልካቾችና በተጠሪ መካካል ሲካሄድ የቆየው የውርስ ማጣራት ሂደት የፍ/ብ/ህ/ቁ.826 በሚያዘው መሰረት የውርስ ማጣራቱ ሂደት ሟች ይኖሩበት በነበረው ስፍራ ስልጣኑ በሚፈቅድለት የዓይደር ወረዳ ፍርድ ቤት እንጂ በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ ተደርጎ ውሳኔ ያገኝ መባሉ፤ተጠሪ ወራሽ ናቸው ለተባሉት እናት አይደሉም ሞግዚትነትም ሆነ የውክልና ስልጣን የላቸውም በማለትያቀረብነው መቃወሚያ ግምት ውስጥ ሳይገባ ወራሽነቱ እንዲፀድቅ መደረጉ፤የዚህ ውርስ ተጠቃሚዎች ናቸው የተባሉት ከነአካቴው ያልተወለዱና በአካልም የሌሉ ሆን ተብሎ ተጠሪ ንብረቱን ያለ ጠያቂ ለብቻ ለማስቀረት በተንኮል የፈጠሩት ዘዴ ሆኖ እያለና ተጠሪም የልጆቹ መወለድና በሕይወት መኖር በተጨባጭ ባላረጋገጡበት እንዲያውም ወራሾች ናቸው የተባሉት በአካል ቀርበው ውርስ ባልጠየቁበት የፀደቀ በመሆኑ እና ሟች ወንድማችን ያለ አመልካቾች ሌላ ወራሽ የሌለው መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝና ሰበር ችሎቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ የሟች ልጆች እያሉ ወንድሞች ወራሾች ሊሆኑ ስለማይገባ የስር ፍርድ ቤቶች የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁን ተጠሪ ሟች ልጆች ላይ ባቀረቡት ክስ ጉዳዩን በሌሉበት ታይቶ ልጆች የሟች አባታቸው ወራሽ ናቸው በማለት ውሳኔ መስጠቱ ግልፅ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአሁን አመልካቾች የወንድማቸው ሟች አቶ ዮሴፍ ሐጎስ ወራሾች መሆናቸው በፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ እዚህ ሊታይ የሚገባው ነጥብ የወራሽነት ሰርተፊኬት በፍርድ ቤት ከተሰጠ በኋላ እውነተኛ የሟች ወራሽ ነኝ በማለት መቃወሚያ ሊቀርብበት የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በፍ/ህ/ቁ 996 (1) ወራሽ የሆነ ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑንና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመላክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፍርድ ቤት ማመልከት የሚችል ሲሆን የተሰጠው የወራሽነት ምስክር ወረቀትም በፍ/ህ/ቁ/998(1) በተመለከተው

ሁኔታ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በፍ/ህ/ቁ/999 በተደነገገው መሰረት አንድ ሰው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ ያደረገ እንደሆነ እውነተኛው ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት የወራሽነት ጥያቄ ክስ ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ የውርስ ሰርተፊኬት አንድ ሰው የራሱን ወራሽነት ለማስረዳት የሚወስደው ማስረጃ እንጂ ሌሎች ወራሾች አለመኖራቸውን የሚሳይ ሰነድ አይደለም፡፡ በግራ ቀኙ የሟች ወራሾች መሆናቸው በማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከማስረጃነት በዘለለ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ በሚያዘው መሰረት ከሌሎች ሰዎች ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ ያገኝና በፍርድ ያለቀ መቃወሚያ የማይቀርብበት ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ስለሆነም ትክክለኛ የሟች ወራሽ ማነው? የሚለውን ጭብጥ ተገቢውን ማጣራት ከተደረገበት በኋላ ነው እውነተኛ ወራሽ መለየት የሚቻለው፡፡ ስለዚህ ወራሾች የተባሉትን ግራ ቀኙ ባሉበት የሟች እውነተኛ ወራሽ ማን ነው? የሚለውን ጭብጥ ማጣራት ሳይደረግበት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 77320 ጥር 18 ቀን 2008 ዓ/ም የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 17334 ሰኔ 24 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በመሻር የዓይደር ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 4884 የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በትግራይ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበርሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 83740 ሚያዝያ 4 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የስር ፍርደ ቤቶች የአሁን ተጠሪ ግማሽ ድርሻ እንዲያገኙ የሰጡት ውሳኔ ክፍል በማፅናት፣የሟች አቶ ዮሴፍ ሐጎስ ድርሻ አመልካቾች ሊወርሱ አይገባም፣የልጆቹ ድርሻ ነው በማለት የተሰጠ ውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
3. የዓይደር ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የሟች ድርሻ ለመውረስ ትክክለኛ ወራሽ ማስረጃ የያዘ ማንነው ወይም የሟች እውነተኛ ወራሽ ማን ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ፣የሟች ልጆች የተባሉት ስነስርዓት ህጉ መሰረት

ጥሪ ተደርጎላቸው ባሉበት ተገቢው ማጣራት አድርጎ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

የሰ/መ/ቁ. 137869

ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ቦንሲቱ ዱፌራ - ተወካይ አቶ ዓለማየሁ ዱፌራ -ቀረቡ ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ታምሪ ረጋሳ - ተወካይ አቶ ጋረደ አርጋሳ ቀረቡ ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የክርክሩ ምክንያት ውርስ ይገባኛል የሚል ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ በወሊሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆኑ አመልካች ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክርክሩ መነሻ በአጭሩ የአሁኗ አመልካችና የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት ብርቄ ዱፌራ የሟች ባለቤቴ ልጆች ሆነው ንብረትና ይዞታ ከውርስ በማያያዝ የሚስትነት ድርሻዬን ሳያካፍሉኝ ስለያዙ እንዲለቁልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ከሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ያቀረቡት መልስ የቀረበው የጋብቻ ውል አባታችን የፈረመ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኝ ክርክር አዳምጦ የሰው ማስረጃም ሰምቶ ከሳሽ የተከሳሾች ሟች አባት ሚስት ስለሆኑ የከሳሽን ድርሻ ይልቀቁላቸው በማለት ወስኖአል፡፡

ይህንን ውሳኔ በመቃወም የሥር 1ኛ ተከሳሽ /የአሁኗ አመልካች /ይግባኝ ወስደው የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሳሽ ያቀረቡት የጋብቻ ውል በተከሳሽዋ በኩል የአባታችን ፊርማ አይደለም ተብሎ ተክዶ እያለ በሰነድ ምርመራ ላቦራቶሪ በኩል

ሳይለይ የተሰጠው ውሳኔ ጉድለት አለው በማለት የሚች ውል ፊርማ የተካደው ተመርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በነጥብ ተመልሷል፡፡

የወሊሶ ወረዳ ፍርድ ቤት የጋብቻ ውሉን ለኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ከላከ በኃላ የውሉ አርጂናል እንዲቀርብ በፖሊስ በኩል በመጠየቁ የሥር ከሳሽ /የአሁኗ ተጠሪ/ አርጂናሉን /ዋናውን/ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ያለው ኮፒ መሆኑን በመግለጻቸው ከሳሽ ለማቅረብ ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን ተገንዝበን የቀረበው ክስ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ከሳሽ /ተጠሪ/ የሚች ዱፌራ ሰርቤሳ ሚስት አይደለችም ብለን የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርገናል፣ሌላ ግንኙነት ካላቸው በንብረትና በይዞታ ጉዳይ ላይ ያሉዋቸውን መብት ከሳሽ ለማቅረብ  ይህ ውሳኔ አያግድም በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ምዕራብ  ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን  ካከራከረ በኃላ ጋብቻን ማረጋገጥ የሚቻለው በጋብቻ ወረቀት ሲሆን የጋብቻ ወረቀት ማስረጃ በሌለ ጊዜ ግን የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ጋብቻ መኖርን ለማስረዳት እንደሚቻል የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው አንቀጽ 93 /1/ ይደነግጋል፡፡ በይግባኝ ባይ /በአሁኗ ተጠሪ/ እና በተቃዋሚዎች አባት መካከል ጋብቻ መኖሩን ግራ ቀኝ ማስረጃዎች በሥር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ቀርበው መስክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ሚች ለአሁኗ ተጠሪ ሚስቴ ነች ብለው ሲፈርሙላቸው ማየታቸውን በተጨማሪ ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም በአሁኗ ተጠሪ እና በሚች ዱፌራ ሰርቤሳ መካከል ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ ጋብቻ መኖሩ ስለተረጋገጠ የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ የባለቤትነት ድርሻቸውን እንዲለቁላቸው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻር ወስኗል፡፡ የአሁኗ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ ካከራከረ በኃላ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ በመቀጠልም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከከፍተኛ ፍርድ ቤት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጡትን ውሳኔ ለማስቀየር ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሞውብኛል ያሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ ተጠሪ ከሟች ጋር በጋራ ያፈሩት ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በተመለከተ ግራ ቀኙ ባልተከራከሩበትና ምንም ማስረጃ ቀርቦ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ የሚስትነት ድርሻዋን እኩል ትካፈል ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በተወካያቸው በኩል በቀን 13/08/2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ የሰጡ ሲሆን የአመልካች ተወካይም በቀን 18/9/2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን በውሳኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ክርክሩ አስቀድሞ እስከ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት ድረስ ደርሶ የጋብቻ ውል ተጣርቶ እንዲወሰን የተመለሰ ሲሆን የወረዳ ፍርድ ቤትም የጋብቻ ውሉ ኮፒ ስለሆነ ኦርጂናሉ ካልቀረበ የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ፊርማውን ለመመርመር ያለመቻሉን ገልጾ ተጠሪ ኦርጂናል ውል እስካላቀረቡ ድረስ ተጠሪ የሟች ዱፌራ ሰርቤሳ ሚስት አይደሉም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ክርክር ላይ ትኩረት የተሰጠው ሚስትነት ክርክር ላይ እንጂ በንብረት ክርክር ላይ አይደለም፡፡ የንብረት ክርክር የሚደረገው የሚስትነት ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ እንጂ አስቀድሞ ሊሆን አይችልም፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ሚስት አይደሉም የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ በመሆኑ ስለ ንብረት ጉዳይ ያነሳውም ሆነ በውሳኔው ላይ ያሰፈረው ነገር የለም፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን የተጠሪ ሚስትነት በሁኔታ ተረጋግጧል ካለ በኃላ ንብረትን በተመለከተ ውሳኔ አሳርፎበታል፡፡ ይህ አካሄድ ግራ ቀኙን ክርክር እና የክልሉን የቤተሰብ ህግ ድንጋጌን የተከተለ ነው ወይ? የሚለውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪ ሚስት ናቸው ቢባል እንኳን ተጠሪ ከአመልካች አባታቸው ጋር ያላፈሩት የአባታቸው ግል ንብረታቸው በመሆኑ ተጠሪ አይመለከታቸውም በማለት ያቀረብነው ክርክር በአግባቡ ሳይጣራ ለተጠሪ ንብረት ይገባቸዋል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ይከራከራሉ። ከላይ እንደተገለጸው ይህ ክርክር በወረዳ ፍርድ ቤት የተነሳ ቢሆንም ከሚስትነት ክርክር ውጪ ንብረትን በተመለከተ ያልተጣራና ውሳኔ ያላረፈበት ነው። የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው የባልና ሚስት ሀብት እንዴት እንደሚጣራ በአንቀጽ 112 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ አስቀምጧል። በአንቀጽ 112 (1) መሠረት ባልና ሚስቱ የጋብቻቸው መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው መሠረት ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተመለከተው የጋብቻ ውል ወይም ሌላ ስምምነት የሌለ ወይም በህግ ፊት የማይፀና ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የባልና ሚስት ሀብት የሚጣራው በአንቀጽ 113 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት እንደሆነ የድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ያመለክታል።

በያዝነው ጉዳዩ በተጠሪ እና በሟች ባለቤታቸው አቶ ዱፌራ ሰርቤሳ /በአመልካች አባት/ መካከል ንብረትን በተመለከተ በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍቺም ሆነ በሞት ምክንያት ሲፈርስ ንብረት የሚጣራበትን ሁኔታ በውል ወይም በስምምነት ለይተው ባላስቀመጡበት ሁኔታ አመልካች የሟች አባታችን የግል ንብረት ነው በማለት የሚከራከሩበት ንብረት ሳይጣራ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ የጠየቁት ንብረት ይገባቸዋል ሲል የወሰነው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል።

በመጨረሻም በግራ ቀኙ መካከል የተነሳውን የንብረት ይገባኛል ጥያቄ በተመለከተ ሊጣራ የሚገባው በኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው በአንቀጽ 113 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ነው በማለት ይህ ችሎት ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

በሌላ በኩል አመልካች ከተጠሪ ሚስትነት ጋር አያይዘው ያነሱትን ቅሬታ ነጥብ በተመለከተ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ የሚስትነት ሁኔታ በክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው አንቀጽ

93 /1/ መሠረት የጋብቻ ጽሁፍ ባይኖርም ተጠሪ በሌላ አሳማኝ ማስረጃ ስላረጋገጡ ሚስት ናቸው ሲል የደረሰውን ድምዳሜ ይህ ችሎትም የሚስማማበት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ያሉት ፍርድ ቤቶች ንብረትን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ በማግኘታችን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 35947 በቀን 24/6/2008 ዓ/ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 239363 በቀን 09/10/2008 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አጣሪ በመ/ቁ. 249031 በቀን 15/3/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. በተጠሪ እና በሟች ባለቤታቸው አቶ ዱፌራ ሰርቤሳ መካከል ጋብቻ ነበረ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. ከላይ በፍርዱ ላይ በግልጽ እንደተገለጸው ክርክር የተነሳባቸው ንብረቶች በአግባቡ ሳይጣሩ የተጠሪ ሚስትነት ድርሻ ይገባቸዋል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. ተጠሪ እና ባለቤታቸው ሟች አቶ ዱፌራ ሰርቤሳ በጋራ ያፈሩት ንብረቶች መኖር ያለመኖራቸውን፣ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ማን እንዳፈራቸው? ከጋብቻ በፊት ወይም ከጋብቻ በኃላ የተፈሩ መሆን ያለመሆናቸውን እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮችን በክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው አንቀጽ 113 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የወሊሶ ወረዳ ፍርድ ቤት አጣርቶ እንዲወስን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መልሰናል፡፡
5. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 135902

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፦

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሡናይት አድነው

**አመልካች:-** ወ/ሮ መስከረም ጫካ- የቀረበ የለም ከተባለ በኂላ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፦** 1.አቶ አክሊሉ ሽፈራው -ከማረሚያ ቤት ቀረቡ

2.ወ/ሮ ካኦሬ ከተማ- የቀረበ የለም ከተባለ በኂላ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ ::**

**ፍርድ**

**ጉዳዩ፦** የባልና ሚስት ፍቺን ተከትሎ የቀረበ የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ነው። ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በ1ኛተጠሪ ላይ ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ ሲሆን ተጠሪ ደብድቦ ጉዳት ስላደረሰብኝ በማረሚያ ቤት የሚገኝ በመሆኑ የጋራ ንብረታችንን ልንካፈል ስላልቻልን በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ 09 ቀበሌ የቤት ቁጥሩ አዲስ የሆነ ከጋብቻችን በፊት ለምልክት የሚሆን ጅምር ቤት የነበረው በጋብቻችን ወቅት ፈርሶ 4 ክፍል ሰርቪስ ቤት የሰራን ስለሆነ እና በጋራ ያፈራነው የቤት ቁሳቁስ ስላለን እንድንካፈል ይወሰንልኝ በተጨማሪም ተከሳሽ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈጸሙ ለጋብቻው መፍረስ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ጋብቻው እንዲፈርስ በመጠየቁ ደብድቦ ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰብኝ ስለሆነ

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 84 መሰረት የጉዳት ካሳ ብር 50,000.00 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሆኑት የስር ተከሳሽ የሰጡት መልስ ከከሳሽ ጋር ጋብቻ ስንፈጽም የነበረን የጋብቻ ውል የጋራ ሀብታችንን የሚያስረዳልን ነው፤ የክርክሩን ቤት ከሳሽን ከማግባቴ በፊት የሰራሁት የግል ንብረቴ ነው፣ የካሳ ጥያቄውን በተመለከተ በማስረጃ ያልተደገፈ እና በምን ስሌት እንደተሰላም ስለማይታወቅ ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ሲሆን የአሁን 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃ ገብ ክርክር ከተከሳሽ ጋር በ1988 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመን በኦሮሚያ ክልል የነበረንን ቤት ሸጠን አሁን ክርክር የተነሳበትን ቤት በሰኔ ወር 2002 ዓ.ም ገዝተን ሳለ እኔ የተከሳሽን አባት ለማስታመም ገጠር በሄድኩበት ከሳሽ እና ተከሳሽ በዚህ ቤት አብረው የኖሩበት ቢሆንም ምንም አይነት መሻሻል ያልተደረገበት እና ቤቱንም እኔ እና ተከሳሽ በትዳር እያለን ያፈራነው ስለሆነ የቤቱ ግማሽ ድርሻ እንዳገኝ ይወሰንልኝ በማለት የጣልቃ ገብ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የቤቱ ቁሳቁስ ክርክር ያልቀረበበት ስለሆነ ከሳሽ እና ተከሳሽ እንዲካፈሉ ሲወስን የክርክሩን ቤት በተመለከተ ከሳሽ እና ተከሳሽ በባህላዊ ጋብቻ ሲጋቡ በሀብትሽ በሀብቴ በ80 ውል የተጋቡ መሆናቸውን የሚገልጽ የጋብቻ ውል የቀረበ ስለሆነ፤ የክርክሩን ቤት ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ከመጋባታቸው በፊት ተከሳሽ እና ጣልቃ ገብ በትዳር እያሉ የገዙት መሆኑን እና ከሳሽ እና ተከሳሽ አብረው ሲኖሩበት ቤቱ ላይ የተለያየ እድሳት የተደረገበት መሆኑም ጭምር በምስክሮች ተረጋግጧል በማለት አትቶ ቤቱ የታደሰበትን ወጪ በተመለከተ ከሳሽ ከተከሳሽ ባለቤታቸው ጋር አብረው ሲኖሩ የተጠቀሙበት ግምት ቤቱ ከታደሰበት ወጪ የሚያንስ አይሆንም፤ ስለሆነም አለ የተባለው የእድሳት ወጪ የሚቻቻል ነው ብሎ ቤቱን በተመለከተ ግራ ቀኙ እንዲከፋፈሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የካሳ ጥያቄውን በተመለከተ በዚህ መዝገብ የሚታየው የጋብቻ ፍቺ ውጤት በሆነው የጋራ እና የግል ንብረት ላይ በመሆኑ የካሳ ጉዳይ ባለመሆኑ ሊወሰን አይገባም ተብሎ ታልፏል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ የክርክሩን ቤት የእድሳት ወጪ በተመለከተ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ እና ተከሳሽ በቤቱ

ሲኖሩ ከተጠቀሙበት ጥቅም ጋር ይቻቻል በማለት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ለቤቱ እድሳት እና ለማሻሻያ ስራው የወጣው ወጪ በባለሙያ ተገምቶ ግማሹን 1ኛ መልስ ሰጭ ለይግባኝ ባይ እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መልሶ ልኮለታል፡፡

የአሁን አመልካች ለዚህ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት በነዚህ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም የክርክሩ ቤት የኔ እና የ1ኛ ተጠሪ እንጂ 2ኛ ተጠሪን የሚመለከት ባልሆነበት ለ3 እንድንካፈል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እና ያቀረብኩትን የካሳ ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ሳይወስኑ ማለፋቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የፈጸሙ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎትም መዝገቡን መርምሮ ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሁፍ መልስ እና የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤቶች ካቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሰበር አጣሪው ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረነዋል፡፡

የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ የክርክሩን ቤት በተመለከተ የኔ እና የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ቤቱ ግን የአሁን አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት የተሰራ መሆኑን በማመን አመልካች በሰጡት ቃል የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ይህንን ቤት በሀብትሽ በሀብቴ የባህላዊ የጋብቻ ውል የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት እንዳደረጉት እና በጋብቻቸው ጊዜም በክርክሩ ቤት ላይ ተጨማሪ ስራ መስራታቸው እና አመልካች እና 1ኛ ተጠሪም ከመጋባታቸው በፊት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በጋብቻ የነበሩ መሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ተደርጎ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡

በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ በነበሩበት ጊዜ የተፈራ ንብረት መሆኑ በመረጋገጡ፣ በፌደራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62(1) መሰረት

ባል እና ሚስት በጋብቻቸው ጊዜ የተፈራ ንብረት የ1ኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው እስካለተብለ ድረስ የጋራቸው እንደሆነ የሚገመት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ንብረቱ በተጠሪዎች ጋብቻ ጊዜ የተፈራ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት እንደሆነ በህጉ የሚገመት ሲሆን በ1ኛ ተጠሪ በኩል የክርክሩ ቤት የግል ንብረቴ ነው በማለት ተቃራኒ ክርክር ያልቀረበ ስለሆነ፣ አመልካችም በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 42(1) ተጋቢዎች ንብረታቸውን በተመለከተ በጋብቻ ውል መወሰን እንደሚችሉ በተደነገገው መሰረት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የጋብቻ ውል መነሻነት እና ከጋብቻቸው በኃላ በቤቱ ላይ በሰሩት ተጨማሪ ስራ የቤቱ የጋራ ባለሀብትነትን ይመሰርታሉ፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በክርክሩ ቤት ላይ የባለቤትነት መብት ያላቸው መሆኑ በፍሬ ነገርም ሆነ በህግ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን ክፍፍሉን በተመለከተ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በነበራቸው ጋብቻ ላይ ህግ የሚከለክለውን በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈጸም አመልካችን ያገቡ እና አመልካችም 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ትዳር እንዳላቸው ሳያውቁ ያገቧቸው እና 2ኛ ተጠሪም 1ኛ ተጠሪ ባለቤታቸው ሌላ ትዳር መመስረታቸውን ሳያውቁ በላያቸው ላይ አመልካችን ያገቡባቸው ከመሆኑ አንጻር በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወስኖ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊሻሻል ይገባል ብለናል፡፡ ሌላው እና በአመልካች የቀረበውን የጉዳት ካሳ ጥያቄን በተመለከተ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎቱ የባልና ሚስት ፍቺን ተከትሎ የሚመጣ የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት በመሆኑ የጉዳት ካሳ ጥያቄውን በዚህ ችሎት መወሰን አይቻልም በማለት ሳይወስን ማለፉ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ምንም ሳይወስን ማለፉ የጉዳት ካሳው ጥያቄ ከጋብቻ ፍቺው ጋር ተያይዞ የቀረበ እና ጉዳቱም የደረሰው ከፍቺው ጋር ተያይዞ መሆኑን አመልካች በስር ክርክራቸውም እያነሱት የቤተሰብ ህጉም ይህንኑ የካሳ ክፍያ ሊወሰን እንደሚገባ ደንግጎት እያለ እና አመልካችም ይህንኑ የቤተሰብ ህግ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ ጠቅሰው አቅርበው እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በክርክሩ ላይ ተገቢውን ሳይወስኑ የሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40986 ጥር 19 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 176260 ጥቅምት 30 ቀን 2009 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. በአጠቃላይ የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ የክርክሩን ቤት ግምት 25 ፐርሰንት ለአሁን 1ኛ ተጠሪ ሆኖ የተቀረውን 75 ፐርሰንት አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ እኩል ይካፈሉ ብለናል፡፡

3. የጉዳት ካሳ ጥያቄውን በተመለከተ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራክሮ እና በማስረጃ አጣርቶ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል ይፃፍ፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5. የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# ግብር

የሰ/መ/ቁ. 138837

ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች:- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ /ዶ/ር/

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች-----1ኛ አቶ ብሩክ ገ/ሥላሴ ቀረቡ

2ኛ አቶ ገ/ህይወት በርሄ አልቀረቡም

ተጠሪ-----------አቶ ዳዊት ተሰማ ቡታ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በመኪና ሽያጭ ውል መነሻነት የታጣ ጥቅም ሊከፈለኝ ይገባል በሚል በአሁን አመልካቾች ከሣሽነት በተጠሪ ተከሣሽነት በስር የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀረበው ክስ የተሰጠው ውሣኔ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ በመሻሩ መነሻነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረው ክስ እንደሚያስረዳው በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል የመኪና ሽያጭ ውል ተፈጽሞ የነበረ ሲሆን፣ የሠ.ቁ. 03-02-50764 ኢት የሆነውን ትራክተር የጭነት ተሽከርካሪን ለንግድ ሥራ አገልግሎት የሚውል በብር 1,700,000.00/ አንድ ሚሊዩን ሰባት መቶ ሺ ብር/ በ19/04/2006 ዓ.ም. በተፃፈ ውል

ሽያጭ መፈፀማቸውን እና ከዚህ ገንዘብ ላይ ብር 500,000.00/ አምስት መቶ ሺ ብር/ ወዲያው ከፍለው መኪናውን መረከባቸውን፣ ቀሪ ገንዘቡን ስመ ንብረቱ ሲዛወር ሊከፍሉ መስማማታቸውን፣ መኪናው ከውጭ ሲገባ ቀረጥ ያልተከፈለበት በመሆኑ ለሥራ ሳይሰማራ መቆየቱን ገልፀው በ27/2/2007 ዓ.ም. የተፃፈ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን፣ ሆኖም ቀድመው አድርገውት የነበረውን ውል በመተው በ9/7/2007 ዓ.ም. ሌላ ውል መስማማታቸውን፣ የውሉም ይዘት ተሽከርካሪው ከተገዛበት ዋጋ ውስጥ አሁንም በውሉ ዕለት 850,000.00 ወዲያውኑ ከፍለው ከሣሽ ከዳሽን ባንክ ተሽከርካሪውን በዋስትና አስይዘው የተበደረውን ገንዘብ 500,000.00 ዕዳ ነፃ አድርገው ብር 140,000.00 በቼክ ቁጥር 3425633 በሆነ በቀን 09/07/2008 የተፃፈ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ እንዲወስድ የሰጡት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የቀረጥ ገቢ ዕዳ ብር 200,000.00 መሆኑን ተከሣሽ የነገሯቸው በመሆኑ ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ እንዲቆርጡ መስማማታቸውን፣ ሆኖም ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲጠይቁ 200,000.00 ሣይሆን ብር 489,000.00 /አራት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ብር/ መሆኑ መገለፁን፣ በመሆኑም ብር 132,000.00/ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ ብር/ ከተስማሙት ልዩነት የፈጠረ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ ከፍለው ስም እንዲያዛውሩ ቢጠይቋቸው ሊፈጽሙላቸው ያልቻሉ በመሆኑ በመኪናው ተጠቅመው ሊያገኙ የሚገባቸውን ጥቅም ያሳጧቸው በመሆኑ፣ ተሽከርካሪው በቀን ብር 6,000.00፣ በወር 180,000.00 የሚያስገባ በመሆኑ ገቢው በ8 ወር ተባዝቶ ብር 1,440,000.00/ አንድ ሚሊዩን አራት መቶ አርባ ሺ ብር/ ያጣነውን ገቢ እና ውሉን በማፍረሱ ምክንያት 20,000.00/ ሃያ ሺ ብር/ መቀጮ ጨምረው በድምሩ ብር 1,490,000.00/ አንድ ሚሊዩን አራት መቶ ዘጠና ሺ ብር/ እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ክስ ማቅረባቸውን ተመልክተናል፡፡

ተከሣሽም ባቀረቡት መልስ መኪናውን የሸጥኩት ከቀረጥ ነፃ ለኢቨስትመንት ያስገባሁት መሆኑን ነግሬ የቀረጡን ሊከፍሉ ተስማምተን ነው፡፡ እንድረዳቸው ጠይቀውኝ ሌላ ውል ተዋውለናል፡፡ ከመኪናው ዋጋ ላይ ብር 210,000.00/ ሁለት መቶ አስር ሺ ብር/ ቀንሼላቸው ተዋውለናል፡፡ ስለሆነም ክሱ ተገቢ አይደለም፡፡ የታጣውን ጥቅም መጠን በተመለከተም ተሽከርካሪው ከ9/7/2007 ዓ.ም. እረፍት እና ሰርቪስ ሳያስፈልግ እና ዕቃ ለመጫን እና ለማውረድ የሚቆምባቸው ቀናቶች ሳይታሰቡ በቀጣይነት የቀን ገቢ ብር

6,000.00 ይገኛል በማለት የጠየቁት ገቢ እና በውሉ መሠረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ያልተወጡት ከሣሾች ሆነው እያለ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የጠየቁት ቅጣት ብር 20,000.00 የሕግ መሠረት ስለሌለው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በቃል ማከራከሩን እና የቀን ገቢውን ለማወቅም ተመሳሳይ ሥራ ከሚሰሩ ድርጅቶች በመጠየቅ እና በማስቀረብ ተከሣሽም አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ መዝገቡን መመርመሩን፣ ከተደረገው ክርክር እና ከቀረበው ማስረጃ በመነሳትም ለደረሰው ጉዳት ተከሣሽ ኃላፊ መሆኑን እና ጉዳቱም መካስ ያለበት በመሆኑ ከሣሾች ያጡትን ገቢ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በማስላት እና ከተጠየቀው በመቀነስ ብር 132,000.00/ አንድ ሚሊዩን ሶስት መቶ ሃያ ሺ ብር / የ8 ወር ገቢ ተከሣሽ እንዲከፍል መወሰኑን ወደፊት ስም እስኪዛወር ድረስ የሚታሰብ መሆኑን በመግልጽ መወሰኑን የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 226982 ሰኔ 28 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው የውሣኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

የስር ተከሣሽ/ ተጠሪ/ ይግባኝ ብለው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና ጉዳዩን መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል በሕግ በተከለከለ ነገር ላይ የተፈፀመ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1678/ለ/ እና 1716/1/ መሠረት ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ በውሉ የተመከተው ግዴታ በአግባቡ አልተፈፀመም በሚል ምክንያት ይ/ባይ በውሉ መሠረት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 231/1/ሀ/ መሠረት የክስ ምክንያት የሌለው መሆኑን ገልፆ ነገር ግን ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ለመመለስ የሚያቀርቡትን ክስ የውሣኔው ግልባጭ የማያግድ መሆኑን በመግለጽ እና የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር መዝገቡን መዝጋቱን የመ/ቁ/ 131429 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይህን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመቃወም እና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አመልካቾች የካቲት 05 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ሙሉ የክርክሩን ይዘት በመግለጽ ሊታረም ይገባዋል ሲሉ ያቀረቡት የህግ ስህተት የሚያመለክተው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 130 ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ ሀገር ለኢንቨስትመንት የገባ ዕቃ

ሊሸጥ ሊለወጥ ወይም ለ3ኛ ወገን መተላለፍ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ መተላለፍ የሚችልበትን አግባብ ደግሞ ዕቃው ሲሸጥ ያለበትን ቀረጥ በመክፈል እንደሆነ ደንግጓል፡፡ በአመልካቾች እና በተጠሪ መሃከል የተደረገው ውል ደግሞ ውል የተደረገበት ተሽከርካሪ ላይ ያለው ቀረጥ ብር 210,000.00 ብቻ ነው ወክላችሁኝ ቀረጡን ክፈሉ ብለው ከሽያጩ ብር ላይ ቆርጠን ተክተናቸው ልንከፍል ስንንቀሳቀስ ዕዳው ከተጠቀሰው በላይ 130,000.00 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ አከራካሪ ጭብጥ የነበረው በውሉ ላይ ከተገለጸው በላይ የሆነው የቀረጥ ብር ማን ይክፈል ቀረጡ ባለመከፈሉ ተሽከርካሪው በመቆሙ የታጣ ገቢ መክፈል የማን ግዴታ ነው የሚል ነው፡፡ አዋጁ የሚያስቀምጠው ከቀረጥ ነፃ የገባን ዕቃ መሸጥ ከተፈለገ ቀረጡን ቅድሚያ ከፍሎ ነፃ ማድረግ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ነው እንዲባልልን የሚሉ እና ሰፊ የይታረምልን ጥያቄን አንስተዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል በህግ የተለከለከ ነው በሚል የከሳሾች/አመልካቾች/ የስር ክስ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ሊመረመር ይገባል በማለት በማስቀረቡ ሊቀርብ ችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት የቀረበው አቤቱታ እና የማስቀረቢያ ነጥቡ ለተጠሪ እንዲደርስ እና የመከላከያ መልስ እንደያቀርቡ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው ሲሆን ተጠሪም ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበው ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ አጠቃላይ ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በግራ ቀኙ መካከል ሁለት ጊዜ የሽያጭ ውል ክርክር ባስነሳው ተሽከርካሪ ላይ የተፈፀመ መሆኑ ያለማከራከሩን እና የመጀመሪያውን ውል ሁለተኛው ውል መተካቱን አመልካቾችም መኪና ከተጠሪ ተረክበውም ሙሉ ገንዘብ ባይሆንም ክፍያ መፈፀማቸውን ፣ የተሸጠው መኪና ግን ለኢንቨስትመንት የገባና ቀረጥ ያልተከፈለበት የነበረ መሆኑ አላከራከራቸውም፡፡ነገር ግን መታየት የሚገባው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ውል ለማድረግ በተፈቀደ ነገር ላይ የተደረገ

ነው ወይንስ አይደለም የሚለውን ሲሆን፣ ይህን አስመልክቶ ከተነሳው ክርክር ጋር አግባብነት ያለው ድንጋጌ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 30/1/ እንደሚደነግገው ከቀረጥ ነፃ የገባን ተሽከርካሪ መሸጥን የሚከለክል ባይሆንም ነገር ግን መሸጥ ከተፈለገ ቀረጡን ከፍሎ ነፃ ካደረገ በኋላ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል ግን የሽያጭ ውሉ የተደረገው ቀረጥ ሳይከፈልበት በፊት ውሉ የተደረገ እና ቀረጥ ያልተከፈለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ደግሞ የቀድሞውን የሽያጭ ውል በሌላ ውል በመተካት ቀረጥ እንዲከፈልበት የተዋዋሉ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ከክርክሩ መረዳት ይቻላል፡፡

የህጉ አላማ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር የሚገቡ ንብረቶች አንድን አላማ ለማሳካት ሲባል እንጂ እንደተፈለገ ሊሸጡ ሊለወጡ ወይም ለ3ኛ ወገን እንደማንኛውም ንብረት ሊተላለፉ የማይችሉ መሆናቸውን በማሰብ ሲሆን ይህን ለመቆጣጠር እና መንግሥትም ይህ ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር የገባ ዕቃ ለታሰበለት አላማ ሳይውል ሲቀር በቀረጥ ነፃ መብት የሚጠቀመው ሰው ፣ወይንም የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዛ ንብረት ላይ ያለውን የቀረጥ ነፃ መብት በመጠቀም ለሌላ እንዳያስተላልፍ ሊቆጣጠርበት እና ቀረጡን ማስከፈልና ገቢውን መሰብሰብ ተገቢ መሆኑን በመረዳት ከማንኛውም ዝውውር በፊት ቀረጡ እንዲከፈል አስገዳጅ ሁኔታን ማስቀመጡን እንረዳለን፡፡

ከዚህ ይህ ድንጋጌ ከተቀረፀበት አላማ አንፃር ስንመለከተው ከቀረጥ ነፃ መብትን በመጠቀም ወደ አገር የገባን ዕቃ ወደ ሌላ ማስተላለፍ ከተፈለገ ቀድሞ ቀረጡን በመክፈል ነፃ ማድረግን የሚጠይቅ በመሆኑ ይህ ሳይደረግ ወደሌላ ማስተላለፍ ግን በራሱ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ጥብቅ ክልከላ የተደረገበት መሆኑን ከድንጋጌው መረዳት የሚቻል በመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል በህግ ክልከላ በተደረገበት ነገር ላይ የተፀመ ነው በማለት የቀረበውን ክርክር የስር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ የሚነቀፍ እና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያበቃ ሕጋዊ ምክንያት ባለመገኘቱ ሊፀና የሚገባው ነው ብለን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 131429 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ የተፈፀመበት መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
4. መዝገቱ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

የሰበር መ/ቁ 131900

ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ

እንዳሻው አዳነ

እትመት አሠፋ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ዋዝሞ ዋሲራ

አመልካች፡- የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ኃይለመለኮት አበበ

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር

- ጠበቃ ቢኒያም ተርፋ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28 መሠረት በተሰጠው የኪሣራ ማሸጋገር መብት መሠረት የኪሣራ ማካካሻ ከተደረገ በኋላ ቀሪው የትርፍ ግብር ብር 847,134.47 /ሥምንት መቶ አርባ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሠላሣ አራት ብር ከአርባ ሰባት ሳንቲም/ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ገቢ ከተደረገ በኋላ ተጠሪ የስም እና የካፒታል ለውጥ አድርጓል ከሚል መነሻነት አመልካች መሥሪያ ቤት የኪሳራ ማካካሻ አልቀበልም ማለቱ ተገቢ ስላልሆነ ሊሻር ይገባል በማለት ያቀረበውን ቅሬታ የተመለከተው የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የተጠሪ ስም እና የካፒታል መጠን የተቀየረው ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ እና አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1 መሠረት በአንድ የግብር ዘመን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ በዚያው የግብር ዘመን ውስጥ በሚቀጥሉት የግብር ዘመናት ከተገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ

ላይ የሚካካስ ይሆናል በማለት የደነገገ በመሆኑ ተጠሪ ኪሳራው ሊካካስለት ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የተጠሪ የስም እና የካፒታል ለውጥ የተደረገው የ2004 ዓ.ም የግብር ዘመን በተዘጋ በሁለተኛው ቀን ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም ነው፤እንደ ተጠሪ ዓይነቱ ድርጅት የካፒታል መጠን ከ25% በላይ ለማሣደግ ውስብስብ ሂደቶችን የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ ተጠሪ የበጀት ዘመኑ ከተዘጋ ከአንድ ቀን በኋላ የካፒታል ለውጡን ያደረገ መሆኑ እና ድርጅቱ ቀደም ባሉት ዘመናት ለደረሰበት ኪሣራ ማካካሻ ሲደረግለት የነበረ መሆኑ ሲታይ ተጠሪ ግብርን ለማስቀረት የኪሳራ ማካካሻ ለማግኘት ከቅን ልቦና ውጪ አስቦ የፈጸመው መሆኑን የሚያሳይ ነው፤በመሆኑም ተጠሪ ግብርን ለማስቀረት ከቅን ልቦና ውጪ በመንቀሳቀስ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ ከአንድ ቀን በኋላ ለውጡን ያደረጉ ቢሆኑ ለውጡ የተደረገው በ2004 ዓ.ም እንደሆነ ስለሚቆጠር በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/2 መሠረት ቀደም ሲል ለነበሩት ዓመታት የተሰጠው የኪሣራ ማካካሻ መብት የተቋረጥ ነው በማለት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ቸሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የተጠሪ ሥም እና ካፒታል የተለወጠው ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም በ2005 ዓ.ም በጀት ዘመን በመሆኑ፤የኪሣራ ማካካሻ በማድረግ ሂሳቡን የዘጋው ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በመሆኑ እና የኪሳራ ማካካሻ ካደረገ በኋላ ያገኘው ትርፍ ለአመልካች የከፈለ በመሆኑ ከ2005 ዓ.ም በፊት ላለው ዕዳ ሊጠየቅ አይችልም በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ከመንግሥት ወደ ግል ባለቤትነት በሽያጭ ሲዘዋወር በአቶ አካሉ ገለታ በብር 18,600,000 /አሥራ ሥምንት ሚልየን ሥድሥት መቶ ሺህ ብር/ ተገዝቶ በዚሁ

ሥሙ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ቆይቶ ሠኔ 26 ቀን 2004 ዓ.ም በተፈረመ እና ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም በውልና ማስረጃ በጸደቀ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ቀደም ሲል ፋብሪካው የተገዛበት ገንዘብ እና በወ/ሮ መሠለች ኪዳኔ በተዋጣ ብር 15,600,000 / አሥራ አምሥት ሚልየን ሥድስት መቶ ሺህ ብር / በድምሩ ብር 34,200,000 / ሠላሳ አራት ሚልዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር / በሆነ ካፒታል የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ሀላፊነቱ የግል ማሕበር በሚል የተቋቋመ በመሆኑ ቀደም ሲል የነበረውን ፋብሪካ የካፒታል ባለቤትነት ድምጽ የመሥጠት መብት በዋጋ ወይም በቁጥር ከ25% በላይ ለውጦታል፡፡ የ2004 ዓ.ም የግብር ዘመን ግብር የሚከፈለው ከሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም እሥከ ጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በመሆኑ ተጠሪ የ2002 ዓ.ም የ2004 ዓ.ም የግብር ዘመን ሲከፍል ኪሳራውን ያሸጋገረበት ጊዜ ተጠሪ በካፒታል ከ25% በላይ በተለወጠበት ጊዜ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/2 የካፒታል ባለቤትነት ወይም ድምጽ የመሥጠት መብት ከ25% በላይ ከተለወጠ ድርጅቱ በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉት የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት የኪሣራ ማሸጋገር መብቱ እንደሚቋረጥ በግልጽ የደነገገ ሆኖ ሳለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ ሥም እና ካፒታል የተለወጠው ከ2001 እሥከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት የግብር ዘመናት ግብር ከፍሎ አጠናቆ ከዘጋ በኂላ ነው በማለት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የተጠሪ የኪሣራ ማሸጋገር መብት የተቋረጠ መሆን አለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28 (1) እና (2) ድንጋጌ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/2 ሕጉ ባስቀመጠው መሥፈርት እና መጠን በግብር ዘመኑ ውስጥ ለውጥ ቢደረግ በግብር ዘመኑም ሆነ ቀደም ባሉት ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት ኪሣራ የማሸጋገር መብቱ ይቋረጣል የሚለው ድንጋጌ ለውጡ የተደረገው በግብር ዘመኑ ውስጥ መሆን እንዳለበት በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በኢትዮጲያ ሕግ የግብር ዘመን የሚባለው ከሐምሌ 01 ቀን እስከ ሠኔ 30 ቀን ድረስ ነው፡፡ በሕግም ሆነ በአፈጻጸም እንደሚታየው የግብር መክፈያ ወቅት የግብር ዘመኑ አልቆ የቀጣዩ የግብር ዘመን መጀመሪያ ወር ላይ በመሆኑ በ2004 የግብር

ዘመን ለተሰራ ሥራ ግብርን አስታውቆ የሚከፈለው በ2005 ዓ.ም የግብር ዘመን መጀመሪያ ወራት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 28/2 መሠረት የኪሣራ ማሸጋገር መብት ሊቋረጥ የሚችለው የ2005 ዓ.ም የግብር ዘመን ለመክፈል ስንቀርብ እንጂ የ2004 ዓ.ም ግብር ለመክፈል ስንቀርብ አይደለም በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ የካፒታል መጠኑን ከ25% በላይ በማሳደግ የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚል የተቀየረ መሆኑን ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የተለያዩ ውሳኔዎችን ሊሰጡ የቻሉት የተጠሪ የካፒታል መጠኑ ከ25% በላይ ያደገው በ2004 ዓ.ም ወይም በ2005 ዓ.ም የበጀት ዓመት ነው ከሚል መነሻነት ቢሆንም ምላሽ የሚያስፈልገው ዋነኛ ጭብጥ በአዋጁ አንቀጽ 28 ላይ የተሰጠው ኪሳራን የማሸጋገር መብት በመብቱ ተጠቃሚ የሆነው ኩባንያ አስቀድሞ ከነበረበት ኪሣራ በመውጣት የካፒታል ባለቤትነት መብቱ ወይም ድምጽ የመስጠት መብቱ ከ25% በላይ ባደገ ጊዜ ቀሪ ሊደረግ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ በአዋጁ የተሰጠው የኪሣራ ማሸጋገር መብት ኩባንያዎች ኪሣራ ውስጥ በገቡ ጊዜ ከገቡበት ኪሣራ እንዲወጡ ለማበረታታት እና በገበያው ተወዳዳሪ በመሆን ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ስለመሆኑ ከኪሣራ ማሸጋገር መብት ዓላማ እና ከግብር አዋጁ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ኩባንያው በኪሣራ ማሸጋገር መብት ተጠቃሚ ከሆነ በኋላ ከነበረበት ኪሣራ በመውጣት የካፒታል ባለቤትነት መብቱ ወይም ድምጽ የመስጠት መብቱ ከ25% በላይ ያደገ ለመሆኑ በተጨባጭ ከተረጋገጠ አስቀድሞ አግኝቶት የነበረው የኪሣራ ማሸጋገር መብት ቀሪ ሊሆን ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡ ለዚህ መሠረታዊ ነጥብ ምላሽ ለመሥጠት በአዋጁ የኪሣራ ማሸጋገር መብት አስመልክቶ የተቀመጠውን ድንጋጌ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1 በአንድ የግብር ዘመን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ በዚያው የግብር ዘመን ውስጥ የታየው ኪሣራ በሚቀጥሉት ሦስት የግብር ዘመናት ከተገኘው ግብር የሚፈጸመው በመጀመሪያ ያጋጠመውን ኪሣራ በኋላ ካጋጠመው ኪሳራ አስቀድሞ በማካካስ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌም በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ የአንድ ኩባንያ የካፒታል ባለቤትነት ወይም ድምጽ የመሥጠት መብት በዋጋ ወይም በቁጥር ከ25% በላይ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተለወጠ እንደሆነ ኩባንያው በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉ የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት የንኡስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ያቋርጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ኩባንያው በደረሰበት ችግር ምክንያት ከገበያ እንዳይወጣ እና ተወዳዳሪ መሆን እንዲችል ተሰጥቶት የነበረው የኪሣራ ማሸጋገር መብት የካፒታል ባለቤትነት ወይም ድምጽ የመሥጠት መብት በዋጋ ወይም በቁጥር ከ25% በላይ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተለወጠ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ኩባንያው አስቀድሞ ከነበረበት ኪሣራ ወጥቶ በተጨባጭ ያደገ መሆኑ የሚገመት በመሆኑ በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉት የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት አስቀድሞ ተሰጥቶት የነበረው ኪሣራ የማካካስ መብት የሚቋረጥ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለውጡ የተደረገው በ2004 ዓ.ም የግብር ዘመን ስላልሆነ አስቀድሞ ያገኘሁት ኪሳራ የማካካስ መብት ሊቋረጥ አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የኪሳራ መብት ዓላማን ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው ለውጡ የተደረገው በ2005 ዓ.ም የግብር ዓመት ስለሆነ የተጠሪ የኪሳራ ማካካሻ መብት ሊቋረጥ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 124463 ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 166408 ጥር 12 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡

3. ግራቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 139334

ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የኢ/ገ/ጉ/ባለስልጣን

ተጠሪ፡- ሻንዶንግ ሃይወይ ኢንጂነሪንግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር የቀረበው ጉዳይ በአሁኑ አመልካች ተወስኖ የተሰጣቸው የግብር መጠን ላይ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረቡትን ጥያቄ መነሻ ያደረገ ክርክር ነው፡፡ ተጠሪ ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ያቀረቡት ቅሬታ ይዘት፡- በሱር ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዋና ተቋራጭነት በሚገነባው የሚሌ ጭፍራ አለወሃ የመንገድ ስራ ማሻሻል 2ኛ ፕሮጀክት በንኡስ ስራ ተቋራጭነት በሰሩበት ጊዜ ዋናው የስራ ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ አገልግሎት የሚውል ግብአት እያቀረበ ስራው ከተሰራ በኋላ በውሉ መሠረት ከንኡስ ስራ ተቋራጭ ገንዘብ እየተቀነሰ የተከፈለ በመሆኑ እንዲሁም የባንክ አገልግሎት ክፍያ በዋናው ስራ ተቋራጭ የተከፈለ ቢሆንም ከንኡስ ስራ ተቋራጭ እንዲቀነስ የውል ስምምነት ባደረጉት መሰረት የተከፈለ በመሆኑ የአሁኑ ተጠሪ ግብር እንዲከፍል የተጠየቀበት ገቢ ለማግኘት ያወጡት ውጭ ሆኖ ሊያዝ ሲገባ ይህ ሳይያዝ የተወሰነ ግብር በመሆኑ ፍትሃዊ አይደለም በማለት

ውሳኔው ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰው አመልካች አላግባብ የጠየቃቸውን ክፍያ ጉባኤው ውድቅ እንዲያደርግላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የፌዴራሉ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጥ ካደረገ በኂላ በግራ ቀኙ መካከል የቀረበው ክርክርና ማስረጃ በመመርመር በሰጠው ውሳኔ በተጠሪ በኩል የጥሬ እቃ ክፍያ በሱር ኮንስትራክሽን ተቀንሶ ለመቅረቱ የክፍያ ሰርትፊኬት የቀረበ በመሆኑ እንዲሁም በተጠሪ እና በሱር ኮንስትራክሽን መካከል በተደረገው የውል ስምምነት ለባንክ አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ በይግባኝ ባይ የሚሸፈን በመሆኑና ገንዘቡ በሱር ኮንስትራክሽን ስም መከፈሉን የባንክ አሰራር ስለሆነ የግብአት ዋጋና የባንክ አገልግሎት ክፍያ ወጭ ዋና ስራ ተቋራጭ በሆነው በሱር ኮንስትራክሽን በወጭ አለመያዙ ተረጋግጦ ለአሁኑ ይግባኝ ባይ በወጭ ተይዞለት ግብሩ እንደገና ሊሰላ እንደሚገባ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ለግንባታ እቃ አቅርቦት ወጣ የተባለው ብር 34,371,218.06 እና ለባንክ አገልግሎት ክፍያ ወጣ የተባለው ብር 564,480.00 ለተጠሪ በወጪነት ሊያዝ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በመሻር የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡እንደመረመርነው በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብም ተጠሪ በወጪነት እንዲያዝለት ያቀረበው ደረሰኝ በሌላ አካል የተመዘገበ በሆነበት ሁኔታ ወጪ ለማረጋገጥ በሌላ አካል የተመዘገበ ደረሰኝ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ ከግብር አዋጁ መርህ አንፃር በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ

ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከክርክሩ ሂደት ለመረዳት እንደቻልነው ተጠሪ እንዲከፍል የተጠየቀውን የንግድ ትርፍ ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ የ2011 እ.ኤ.አ. የግብር ዘመን መሆኑ ተጠሪ በዚሁ የግብር ዘመን ወጪ ማድረጉን በመግለፅ ያቀረበውን የሲሚንቶ፣የነዳጅ፤ሌሎች የግንባታ እቃ ወጪዎች ብር 34,371,218.06 (ሰላሳ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰባ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ስምንት ከስድስት ሳንቲም) እና ለባንክ አገልግሎት የተፈፀመን ክፍያ ወጪ ብር 564,480 (አምስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ብር) በወጪነት እንዲያዝለት ጠይቆ አመልካች ውድቅ በማድረጉ መነሻ ያደረገ ክርክር ነው ፡፡

ግብር ከፋዩ ወጪዎችን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ እንደሚደረግ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 20 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ግብር ከፋዩ ወጪውን ለማስረዳት ማረጋገጫ ማቅረብ እንዳለበት አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በወጪነት እንዲያዝለት እየጠየቀ ያለው በ2011 እ.ኤ.አ. የግብር ዘመን ወጪ አድርጌያለሁ በማለት፤ ማድረጉን ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረበውን የሲሚንቶ፣የነዳጅ፤ሌሎች የግንባታ እቃ ወጪዎች ብር 34,371,218.06 (ሰላሳ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰባ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ስምንት ከስድስት ሳንቲም) እና ለባንክ አገልግሎት የተፈፀመን ክፍያ ወጪ ብር 564,480 (አምስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ብር) አጠቃላይ በተጠሪ ስም ወጪ ተደርገው የቀረቡ ሳይሆን ዋና ተቋራጭ በሆነው በሱር ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወጪ የተደረገ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 20 ስር እንደተደነገገው ወጪ አውጥቻለሁ የሚል አካል ወጪውን ማስረዳት የሚችለው በሚያቀርበው ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የግዢ ደረሰኝ ማለት የሻጭና የገዢ ሙሉ ስም፣ የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር፣ተከታታይ ደረሰኝ ቁጥር፣የተሸጠው እቃ ወይም አገልግሎት አይነትና የታክሱ መጠን፣የሽያጩ ወይም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ መያዝ ያለበት ስለመሆኑ ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 22(2) እና ደረሰኝ አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 28/2001 አንቀፅ 4(1) ጣምራ ንባብ መረዳት

ይቻላል፡፡ስለሆነም ግብር ከፋዩ ለንግድ ስራው ያወጣውን ወጪ ማረጋገጥ አለበት ሲባል ይህንን ለማረጋገጥ የሚቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ ደግሞ ወጪ አውጥቻለሁ በሚለው አካል ስም መሆን እንዳለበት ከተጠቀሰው ድንጋጌ እና ከማስረጃ መርህ አንፃር ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም በሱር ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም ወጪ የተደረገ የሲሚንቶ፣የነዳጅ፤ሌሎች የግንባታ እቃ ወጪዎች እንዲሁም ለባንክ አገልግሎት ክፍያ ተጠሪ ገቢ ለማግኘት ያወጡት ወጭ ሆኖ ሊያዝ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ከገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌ ውጪ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 129915 የካቲት 10 ቀን 2009 ዓ/ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 163541 ሰኔ 01 ቀን 2009 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

# አፈፃፀም

የሰበር መዝገብ ቁጥር 136092

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ሙሉአለም ግዛው ወልዴ -ጠበቃ መሀመድኑር አበደሰረም -ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ ዙፋን ዘለቀ - ተልማ አቻሜ -ቀረቡ

2ኛ መስፍን አስፋው

3ኛ አልማዝ አስፋው

4ኛ ቱቱ አስፋው

5ኛ ሶስና አስፋው

(2ኛ–5ኛ) ጠበቃ አማረ ጋሳ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ፍርድ ለማስፈፀም የተደረገው ሀራጅ የተመለከቱ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍርድ ባለመብት አቤቱታ አቅራቢነት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመሀብት ወ/ሮ አመለወርቅ ኢየሱስ ወራሽ ወ/ሮ ዙፋን ዘለቀ ሲሆኑ የፍርድ ባለዕዳዎች ደግሞ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ ለአፈፃፀም አቤቱታ መነሻ የሆነው ክርክር የተነሳበት ቤት በ15/05/07 ዓ/ም በተደረገ ሀራጅ ሽያጭ አቶ እንግዳወርቅ አታክልቲ ብር 22,500,000,00 ዋጋ በመስጠት አሸናፊ ቢሆኑም ገንዘቡን ገቢ ስላላደረጉ በድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ መደረጉንና በዚሁ በ29/08/07 ዓ/ም

በተደረገው ጨረታ ላይ ለቀደመው ጨረታ የተጫራቾች ብዛት በ16 ቀንሶ 5 ብቻ መቅረባቸውን እነዚህም ተጫራቾች እውነተኛና በቂ አለመሆናቸውን ገልፀው ጨረታው እንዲዛወር ሲጠይቁ በፅሁፍ ያቅርቡ ተብለው በመፃፍ ላይ እያሉ ከሌላ የመ/ቤቱ ሰራተኛ ጋር በመነጋገር አሸናፊ ለሆኑ አቶ ሙሉአለም ግዛው በብር 10,350,000 ( አስር ሚሊዮን ሶስት መቶ አምሳ ሺህ) እንዲሸጥ ተደርጓል፡፡ሁለተኛ ጨረታ አካሄድ ላይ ቅሬታ አቅርቤ በፅሁፍ እያደረግኩ እያለ አጫራቹ ሃሳባቸው በመቀየር ሀራጁ በጥድፍያና በተነንኮል እንዲካሄድ ያደረጉ ስለሆነ ጨረታው ፈርሶ ሌላ ጨረታ ይደረግልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡የጨረታው አሸናፊ በበኩላቸው ጨረታውን ስርአቱን አሟልቶ የበለጠ ዋጋ አቅርቤ አሸናፊ ሆኛለሁ የማጭበርበር ተግባር አልተፈፀመም በማለት ተከራክረዋል ፡፡ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙ ካከራከረ እና ምስክሮች ከሰማ በኋላ የጨረታ ሽያጭ አካሄድ ስርአትን በጉልህ ሁኔታ በጣሰና ነፃ ውድድር ባልነበረበት ውጤትን ለመፍጠር በሚያስችል ሁኔታ የቀድሞ የተጫራቾች መግባባት በሚታይበት የተደረገ ሽያጭ ሊፀና የሚገባ ባለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 445 መሰረት ጉድለት ያለበት ሽያጭ ስለሆነ በ29/08/07ዓ/ም የተደረገው አቶ ሙሉአለም ግዛው አሸናፊ የሆኑበት በአፈ/መ/ቁ. 16046 የተከናወነው ሀራጅ ሊፈርስ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ግራቀኙ አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ቅሬታው ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ብይንና ትዕዛዝ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር ቅሬታ ዋና ትኩረት፡- በፍርድ አፈፃፀም የማይንቀሳቀስ ንብረት ጨረታ ሽያጭ የሚፈርሰው በጨረታ ስርአቱ ላይ ግዙፍ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይም የማታለል ተግባር መኖሩ ከተረጋገጠ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ የጨረታው ሽያጭ እንዲፈርስ ያመለከቱት በጨረታው ጉዳት ደረሰብኝ ብለው ሳይሆን ቤቱ በ2ኛው ጨረታ ከተሰጠው ባነሰዋጋ የሚል በመሆኑ በህጉ አግባብ የተደረገው ጨረታ እንዲሰረዝ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው የስር ፍረድቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓአል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በአግባቡ መሆኑ በመዘርዝር የሥር ፍርድ ቤት ብይን ይሁን ትዕዛዝ ስሕተት የለውም ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙ በሰበር ችሎት ያደረጉት የጽሑፍ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ብይን እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚያስፈልገው ጭብጥ የሥር ፍርድ ቤቶች ጨረታው እንዲሰረዝ የሰጡት ብይን እና ትዕዛዝ በሕጉ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከሥር የክርክር ሂደት መረዳት የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሁነውን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 የቤት ቁጥር 750 የሆነውን ቤት በ15/05/07 ዓ/ም በተደረገ ሀራጅ ሽያጭ አቶ እንግዳወርቅ አታክልቲ ብር 22,500,000,00 ዋጋ በመስጠት አሸናፊ ቢሆኑም ገንዘቡን ገቢ ስላላደረጉ በድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ መደረጉንና በዚሁ በ29/08/07 ዓ/ም በተደረገው ጨረታ ላይ ለቀደመው ጨረታ የተጫራቾች ብዛት መቀነሱ የጨረታው ተሳታፊዎችም እየተጠቃቀሱና እየተጠባበቁ ጨረታውን ማደረጋቸው በተደረገው የማጭበርበር ተግባር ምክንያት ቤቱ በመጀመሪያ ጨረታ ከተጠቀሰው ዋጋ ግማሽ በታች አሸናፊ መሆኑ በምስክሮች መረጋገጡ ከስር ፍርድ ቤቶች መዝገብ ለመረዳት ችለናል፡፡

በመሰረቱ በሀራጅ በተሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተፈጸመ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ወይም ማጭበርበር ወይም ማታለል ድርጊት ካለ አቤቱታ የሚቀርብበት ሥርዓት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 445 ሥር ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተደረገው ጨረታ ግዙፍ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይም የማታለል ድርጊት መኖሩ አልተረጋገጠም በማለት አጥብቀው የሚከራከሩ ቢሆንም በሀራጅ አካሄድና ሽያጩ የተፈጸመበት ሥርዓት ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይም የማታለልና ማጭበርበር ድርጊት ስለመፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ድምዳሜ ላይ የደረሰና ይህ ምክንያት ደግሞ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 445 እንደተመለከተው ጨረታው ለማፍረስ በቂ ምክንያት በመሆኑ ሲታይ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የሕግ መሠረት

ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 62246 በ25/04/2008 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 176451 በ20/03/2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ጥር 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/ሀ

የሰ/መ/ቁ/ - 131084

**ቀን** - 25/04/2010

ዳኞች፡- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ጌታቸዉ ይርገቡስ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-

1. በላይ ናማጋ፡ በሌለበት
2. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ነ/ፈ ፍርድ አወቅ አክሊሉ
3. አቶ በርሁን የማነ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበዉን ክስ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ ወ/ሮ መቅደስ አበበ የፍርድ ባለ መብት በመሆን ባቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ምክንያት ቁጥሩ 150 የሆነዉ ቤት በዕዳዉ ምክንያት እንዲሸጥ በተወሰነዉ መሠረት ተሸጦ ገንዘቡ ገቢ ከተደረገ በኋላ፣ ቁጥራቸዉ 149 እና 151 የሆኑ ቤቶች ቁጥሩ 150 ከሆነዉ ቤት ጋር የተያያዙ ቢሆኑም የተለያዩ መሆናቸዉን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸዉ ተጠሪዎች ተመሳጥረዉ የቤ/ቁ/ 149 እና 151 የሆኑትን ቤቶች 3ኛ ተጠሪ እንዲረከብ ያደረጉ በመሆኑ ቤቶቹን ከዳቦ ማሽን ጭምር ተጠሪዎች እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ቀርበዉ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን፣ 1ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ፍርድን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠዉ እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አካል እንጂ እራሱን የቻለ የህግ ሰዉነት የተሰጠዉ ተቋም አለመሆኑን ገልፆ ሊከሰስ እንደማይገባዉ የተከራከረ ሲሆን፤ 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ቁጥሩ 150 የሆነዉን ቤት ተረክቦ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ አወጥቶበት ለ8 ዓመታት በእጁ አድርጎ የነበረ መሆኑን፣ አመልካች ቁጥሩ 151 የሆነዉ ቤት የግል ቤቱ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ዉድቅ ሆኖ እንዲወሰንለት በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ በግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ፤ 1ኛ ተጠሪ ዳኛ ሆነዉ ጉዳዩን ሲያዩ በነበረበት ወቅት ለፈጸሙት ተግባር በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2138(ሐ) መሠረት ክስ ሊቀርብባቸዉ የማይገባ መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪም ፍርድ ለማስፈጸም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስር የተደራጀ አካል እንጂ እራሱን የቻለ የህግ ሰዉነት ያለዉ ባለመሆኑ ሊከሰስ አይገባም በማለት በሁለቱ ላይ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ያደረገ ሲሆን፤ ቁጥሩ 150 የሆነዉ ቤት ቁጥሩ 151 ከሆነዉ ቤት በተናጥል የሚገኝ መሆኑ እና ይዞታዉ የማን እንደሆነ የሚያሳይ የሰነድ ማረጋገጫ ማስረጃ አለማግኘቱን ገልፆ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ የይዞታ አስተዳደር እና የሽግግር ጊዜ አገልግሎት የላከለትን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያለዉ መሆኑን አላረጋገጠም በሚል ምክንያት 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ የቀረበዉንም ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 28/11/08 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፤ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች እንዲቀርቡ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ተጠሪዎችን አንድ ላይ አጣምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ክስ ለማቅረብ መሰረት ያደረገዉ ከወ/ሮ መቅደስ አበበ ጋር በነበራቸዉ ክርክር የፍርድ ባለ ዕዳ በመሆን በቀረበባቸዉ የአፈፃፀም ክስ 1ኛ ተጠሪ በወቅቱ ዳኛ በመሆን በአፈፃፀም መዝገብ ላይ በሰጠዉ ትዕዛዝ፣ 2ኛ ተጠሪ ፍርዱን በማስፈጸም ሂደት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት 3ኛ ተጠሪ እንዲረከብ በማድረጉ እና 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በመጀመሪያ በአፈፃፀም እንዲሸጥ ሳይወሰን ቁጥራቸዉ 149 እና 151 የሆኑትን ቤቶች መረከቡ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ አመልካች መብቴ ተጥሷል በሚል ላቀረበዉ ክስ ምክንያቱ ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በተጠሪዎች የተፈጸመ ተግባር መሆኑን ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከመነሻዉም ተቀባይነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻ ጭብጥ ይሆናል፡፡

በመሠረቱ በሌላ ሰዉ በተፈጸመ ድርጊት ምክንያት መብቱ የተጣሰበት ሰዉ መብቱን ለማስከበር አቤቱታዉን ስልጣን ላለዉ አካል የማቅረብ መብት ያለዉ ሲሆን፤ የሚቀርበዉም አቤቱታ የጉዳዩን ዓይነትና መሠረታዊ ባህርይ መሠረት በማድረግ በህግ የተዘረጋዉን ስርዓት ተከትሎ መሆን እንደሚገባዉ እሙን ነዉ፡፡ ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ አመልካች ክሱን ለማቅረብ በምክንያትነት የጠቀሰዉ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት በተጠሪዎች በተፈጸሙት ተግባራት ምክንያት መብቱ መጎዳቱን ነዉ፡፡ ለተያዘዉ ጭብጥ እልባት ለመስጠት ይቻል ዘንድም በአፈፃፀም ምክንያት የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሚያዝበትን እና የሚሸጥበትን ስርዓት በተመለከተ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በቅድሚያ ማየቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ፍርድን ለማስፈጸም ሲባል ንብረት ስለሚያዝበት፣ ስለሚሸጥበት ስርዓት እና ዉጤቱ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ሕጉ ከአንቀጽ 404 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት መረዳት የሚቻለዉም፤ ሂደቱ የሚመራዉ የአፈፃፀም መዝገቡን በያዘ ፍርድ ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱም በአፈፃፀም ምክንያት ንብረት

የሚሸጥበትን ሁኔታ እና ስርዓቱን በመከታተል እና እንደየአግባብነታቸዉ በስነ ስርዓት ሕጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ሂደቱን በመምራት የፍርድ ባለዕዳ፣ የፍርድ ባለ መብትን እና የገዥዉን መብቶች ባገናዘበ መልኩ የሽያጩ ሂደት መከናወኑን የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡ ይህ ሂደትም የተሸጠዉ ንብረት በርግጥም እንዲሸጥ የተወሰነ ንብረት መሆን አለመሆኑ፣ ሂደቱ በህጉ የተመለከቱትን ስርዓቶች የተከተለ መሆን አለመሆኑ፤ ከሂደቱ ጋር በተያያዘ ከፍርድ ባለ መብት፣ ከፍርድ ባለ ዕዳ፣ ከገዥዉ እንዲሁም ከንብረቱ ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም አለኝ ከሚል 3ኛ ወገን የሚቀርበዉን ተቃዉሞ መርምሮ ዉሳኔ መስጠትን ሁሉ የሚያካትት ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

በእርግጥ ከሽያጭ ሂደት ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤቱ ወይም በፍርድ አስፈፃሚዉ አካል በሚፈጸም ስህተት/ጥፋት ምክንያት የፍርድ ባለ መብት ወይም የፍርድ ባለ ዕዳ እንዲሁም የገዥዉ መብት ሊጎዳ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ይሁንና እነዚህ ስህተቶች የሚቃኑት በስነ ስርዓት ህጉ መሠረት አፈፃፀሙን በያዘዉ ፍርድ ቤት በመሆኑ፣ ሽያጩ በሚደረግበት ሂደት ወይም ከዉጤቱ ጋር በተያያዘ ስህተት (ጥፋት) በመፈጸሙ ምክንያት መብቴ ተጎድቷል የሚል ወገን የሚኖረዉ የህግ መፍትሔ ይህ እንዲስተካከልለት ጥያቄዉን አፈፃፀሙን ለያዘዉ ፍርድ ቤት ማቅረብ ነዉ፡፡

በመሆኑም አፈፃፀሙን የያዘዉ ፍርድ ቤት በዕዳ ምክንያት እንዲሸጥ ከተወሰነዉ ቁጥሩ 150 ከሆነዉ ቤት ሌላ አመልካች ለክርክሩ መነሻ ያደረጋቸዉ ሁለቱ ቤቶች ያላግባብ እንዲሸጡ በፍርድ ቤቱ ሌላ ትዕዛዝ መሰጠቱ ወይም ከተሸጠዉ ንብረት ዉጪ ሌላ ተጨምሮበት 3ኛ ተጠሪ ያላግባብ እንዲረከብ ተደርጎ ከሆነ እና በዚህ ምክንያት መብቱ የተነካ መሆኑን ካመነበት አፈፃፀሙን ለያዘዉ ፍርድ ቤት አቤቱታዉን ማቅረብ አሊያም አፈፃፀሙን በያዘዉ ፍርድ ቤት የተፈጸመዉ ስህተት እንዲታረም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ መብቱን ማስከበር ነበረበት፡፡ ይሁንና ይህን ሳያደርግ የአፈፃፀም መዝገቡ ተዘግቶ ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት የተጎዳዉን መብቱን ለማስከበር በአዲስ መልክ ያቀረበዉ ክስ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 231(1-ሀ) መሠረት ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት

በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/174646 በቀን 01/09/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 45369 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

# ልዩ ልዩ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 78629

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአቶ ካሣ አበበ ወራሽ አቶ ሰለሞን ካሣ; ከጠበቃ አስናቀ ስፍራ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አያልነሽ ባይለየኝ ጠበቃ ሰለሞን ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር በሌላ ሰው ሃብት አላግባብ መበልፀግ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የስር ተከሣሽ (የአሁኑ ተጠሪ አውራሽ) አቶ ካሣ አበበ ገዳሙ ንብረትነቱ የከሣሽ የሆነ የሰ.ቁ. 3-16729 የሆነ የጭነት ተሽከርካሪ ወስደው ባለመመለሣቸው ቀደም ሲል በመ.ቁ. 03016 በተደረገ ክርክር ተከሣሽ ተሽከርካሪውን እንዲመልሱና እስከ 12/11/92 ዓ.ም ላለው ጊዜ ከተሽከርካሪው ያገኙትን ጥቅም ብር 366,000 ለከሣሽ እንዲከፍሉ መወሰኑን በውሣኔው መሠረት ከሣሽ መኪናውን በ01/10/98 ዓ.ም መረከባቸውን የተከሣሹን ንብረት በአፈፃፀም አሸጠው ብር 497,000 በእጃቸው መግባቱን ከዚህ ገንዘብ ላይ ከልዩ ልዩ ወጭ ጋር ተከሣሽ የሚከፍሉትን ገንዘብ ብር 413,580 ሲቀነስ ብር 83,470 በትርፍነት በእጃቸው የሚገኝ መሆኑንና በቀድሞው ክስ እና ውሣኔ

ውስጥ ያልካተተውን የመኪናውን የገቢ ጥቅም በክስ መጠየቅ እንደሚችሉ በቀድሞው ውሣኔ ላይ መብት የተጠበቀላቸው መሆኑን በዝርዝር የሚገልጽ ሆኖ ተሸከርካሪው የሚያስገኘው ወርሀዊ የተጣራ ገቢ ብር 3000 (ሶስት ሺህ) መሆኑ በቀድሞው ክርክር ጊዜ በማስረጃ በተረጋገጠው መሠረት ከ30/10/92 ዓ.ም እስከ 01/10/98 ዓ.ም ድረስ ላለው የ71 ወር ጊዜ ብር 213,000 (ሁለት መቶ አስራ ሶስት ሺህ) የሚመጣ በመሆኑ በትርፍ በእጃው የሚገኘው የተከሣሽ ገንዘብ ተቀናሽ ተደርጐ ተከሣሽ ብር 129,530 (አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሰላሣ) እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሣሽ በበኩላቸው ክሱ በፍ.ህ.ቁ. 2143(1) መሠረት በሁለት አመት ይርጋ እንደሚታገድ እና ክስ የማቅረብ መብት የሚመነጨው ከሕግ እንጂ ከፍ/ቤቱ ውሣኔ እንዳልሆነ በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በአማራጭም በፍሬ ነገሩ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ከውሉ ውጭ ኃላፊነት ክስን አስመልክቶ በፍ/ህ/ቁ. 2143(1) የተደነገገው የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ አላግባብ መበልፀግ አስመልክቶ በሚቀርብ ክስ ጉዳዩ ተፈፃሚነት እንደሌለው ከፍ/ህ/ቁ. 2143(3) ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ከሰጠ በኃላ በቀጣይ ቀጠሮዎችም የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ከ12/11/92 ዓ.ም ጀምሮ ከሣሽ መኪናውን እስከተረከቡበት 01/10/98 ዓ.ም ድረስ ያለው ገቢ በወር በብር 3000 /ሶስት ሺህ/ ተሰልቶ በትርፍነት በከሣሽ እጅ የሚገኘው ገንዘብ ተቀናሽ ከተደረገ በኃላ ቀሪውን ብር 129,530 (አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሰላሣ) ከወለድና ልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍሉ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአሁኑ አመልካች ያቀረቡለትን ይግባኝ ዘግቶ አሰናብቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ እና ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ ሊሻሩ ይገባል በማለት ሲሆን ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ይርጋውንም ሆነ ፍሬ ነገሩን አስመልክቶ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ

የሕግ ስህተት ያለበት ነው ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት የይርጋ ጉዳይን በተመለከተ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት በፍ.ሕ.ቁ. 2143 (1) ሥር የተደነገገው የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት እንደሚኖረው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በመ.ቁ. 34406 በ07/08/2000 ዓ.ም የትርጉም አስገዳጅነት ያለው ውሣኔ ሰጥቶ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን ውሣኔ ወደ ጐን በመተው በፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) የተመለከተው የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ለክርክር በቀረበው ጉዳይ ተፈጸሚነት የለውም ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መሆኑ እና ተጠሪው የሚከራከሩት ደግሞ በፍ.ሕ.ቁ. 2143(1) የተመለከተው የይርጋ ዘመን ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

እኛም አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ ለሚቀርቡ ክሶች አግባብነት ሊኖረው የሚገባውን የይርጋ ዘመን ለመለየት ያስችለን ዘንድ የግራ ቀኙን ክርክር እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 34406 የሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የፍ.ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ማየቱን ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሠረት የፍ.ሕ.ቁ. 2143

በን.ቁ (1) "ሥር ተበዳዩ ክስ ማቅረብ የሚችለው ካሣ የሚጠይቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2 አመት ድረስ ነው" በማለት

በን.ቁ (2) "ሥር ስለሆነም ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት የበለጠ እንደሆነ የካሣው ጉዳይ ክስ የይርጋ ዘመን ልክ በዚሁ መሠረት ይሆናል" በማለት እና

በን.ቁ.(3) ስር ደግሞ "ተበዳዩ የራሱ የሆኑትን ነገሮች የሚጠይቅበትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በተነገሩት ድንጋጌዎች መሠረት የሚከራከርበት መብቱ የተጠበቀ ነው" በማለት ድንግጉ ይገኛል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 34406 የሰጠው ውሣኔ ደግሞ "……. ያለአግባብ ስለመበልፀግ የሚናገረው ምእራፍ የካሣ ጥያቄ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ አይናገርም" ነገር ግን አለአግባብ ስለመበልፀግና ከውል ውጭ

ስለሚደርስ ኃላፊነት የሚናገሩት ድንጋጌዎች በአንድ አንቀጽ ውስጥ ተካተው መገኘታቸው እንዲሁም ያለአግባብ መበልፀግም ከውል ውጪ የሚደርስ ኃላፊነት በመሆኑ ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት ስር የተመለከተው የይርጋ ዘመን በተመሣሣይ አላግባብ መበልፀግን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል…" የሚል ነው፡፡

በሰበር ችሎቱ ውሣኔ ውስጥ እንደተገለፀው ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃለፊነት እና አላግባብ ስለመበልፀግ የሚናገሩት ድንጋጌዎች የሚገኙት በአንድ አንቀጽ ስር ነው፡፡ ይሁን እንጂ በፍ.ብሔር ሕጋችን ውስጥ የተለያየ የይርጋ ዘመንን የሚያቋቁሙ ድንጋጌዎች በአንድ አንቀጽ ውስጥ ተካትተው የሚገኙባቸው አጋጣሚዎች በመኖራቸው ድንጋጌዎቹ የሚገኙት በአንድ አንቀጽ ስር የመሆኑ ጉዳይ ብቻውን ተፈፀሚነት ሊደርግባቸው የሚገባው የይርጋ ዘመን ተመሣሣይ መሆን አለበት ወደሚል ድምዳሜ መድረስ የሚያስችል አይሆንም፡፡

ከውል ውጪ የሚደርስ ኃለፊነት እና አላግባብ መበልፀግን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በአንድ አንቀጽ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረገው የሚጋሯቸዋው ተመሣሣይ ባህሪያት ስላሏቸው እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይርጋን በተመለከተ ግን የፍ.ሕ.ቁ. 2143(3) ጉዳዩን በተለየ ሁኔታ እና በግልጽ የደነገገ በመሆኑ በፍ.ሕ.ቁ. 2143(1) የተመለከተው የሁለት አመት የይርጋ ዘመን አላግባብ መበልፀግ አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ጉዳይ ተፈፃሚነት እንዳማይኖረው ተገንዝበናል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ አላግባብ ስለመበልፀግ የሚቀርቡ ክስችን አስመልክቶ በፍ.ሕጉ የተመለከተ የይርጋ ዘመን አለ ወይስ የለም ካለ ምን ያህል ወይም ስንት ነው የሚል ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ መታየት የሚገባቸው አላግባብ በመበልፀግን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ሲሆኑ ከእነርሱ መካከል ይርጋን የሚመለከት ድንጋጌ የለም፡፡ ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ የሚገዛው የሕግ ክፍል ይርጋን አስመልክቶ በተለይ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ በሌለ ጊዜ በፍ.ሕ.ቁ. 1677(1) የተመለከተውን መርህ በመከተል ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባው በፍ.ሕ.ቁ. 1845 የተመለከተው የአስር አመት የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት

ቀደም ሲል በመ.ቁ. 31748 በ28/06/2000 ዓ.ም የትርጉም አስገዳጅነት ያለው ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔ ሰጥቶ የነበረ መሆኑን ቀደም ሲል ተገልጾአል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው፤ ሆኖም የሰበር ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሣሣይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ እንደሚችል የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅን እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ስር ተደንግጓል፡፡ እኛም ይህንኑ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በዚህ መዝገብ የተያዘውን ክርክር ጨምሮ አላግባብ በመልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የአስር አመት የይርጋ ዘመን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም ከላይ በዝርዝር በተገለፁት ምክንያቶች በፍ.ሕ.ቁ. 2143(1) የተመለከተው የይርጋ ዘመን አላግባብ መልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በፍሬ ጉዳይ ረገድ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ አመልካች የተጠሪ ንብረት በሆነ ተሽከርካሪ ገቢ አላግባብ የበለፀጉ መሆኑ እና የተሽከርካሪው የወር የተጣራ ገቢ በቀድሚው ክርክር ጊዜ ተረጋግጦ ውሣኔ አርፎበታል፡፡ ተሽከርካሪው በመሐል በሌላ ግለሰብ እጅ ገብቶ ነበረ በማለት አመልካች ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንደገለፀው ግለሰቡን በክስ መጠየቅ የሚችሉ ከመሆኑ ውጪ ጉዳዩ በተጠሪ መብት ላይ ለውጥ ማስከተል የሚችል አይደለም፡፡

በዚህም ሁኔታ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለውን ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፍ.ሕ.ቁ. 2143(1) በተመለከተው የይርጋ ዘመን አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 184727 በ24/10/03 የሰጠው ብይን እና ፍሬ ነገሩን አስመልክቶ በዚህ በመ.ቁ. 184727 በ17/04/04 የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 118043 በ27/07/04 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት ስለሚኖረው የይርጋ ዘመን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ችሎት በመቁ. 34406 ሰጥቶት የነበረው የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሠረት በመለወጥ አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ዘመን አስር አመት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በሰበር ደረጃ ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሠባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ.መ.ቁ.128035

ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡1.ዳኜ መላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-.....ምስኪ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር-ጠበቃ አቶ አለሙ ገበየሁ ቀርበዋል

ተጠሪ፡-..........ቤካስ ኬሚካልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር -ነ/ፈጅ አቶ አድነው ደቻሳ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.120677 በ28/7/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሲሆን፣ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ተጠሪ የፈሳሽና ክሬም ዲተርጀንቶችንና ሳሙናዎችን በማምረት ለ18 ዓመታት ሲሸጥ የቆየ ሲሆን፤ተጠሪ ከሚያመርተዉና ብራይት ቤክስ ከሚለዉ ምርት ጋር ተመሳሳይ በሆነ ቢጫ ቀለም ባለዉ ጀሪካንና ቤስት ብራይት ብሎ አምርቶ ለገበያ እያቀረበ ስለሆነ ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 8 መሰረት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር በመፈጸም የተጠሪን ጥቅም በመጉዳቱ፣አመልካች በፈጸመዉ ድርጊት የገንዘብ ቅጣት እንዲወሰንበት፣አመልካች ብራይት ቤካስ ጋር ከሚመሳሰለዉ ቤስት ብራይት በቢጫ ቀለም ጀሪካን ምስል መጠቀሙ ሕገ ወጥ ነዉ እንዲባልልን ፣አመልካች በማምረት በገበያ ላይ የተሰራጩት ምርቶች እንዲሰበሰቡ እና በዚህ ክርክር የወጣዉ ወጪና ኪሳራ እንዲጠበቅልን በማለት ከሷል፡፡

የአሁን አመልካች ባቀረበዉ መልስ ተጠሪ የብራይት ቤካስ እና የቢጫ ጀሪካን ንግድ ምልክት ባለቤት ነኝ ማለቱ ሕጋዊ አይደለም፣ብራይት የሚለዉ ቃል ገላጭና የጋራ መጠቀሚያ እንጂ በአንድ ግለሰብ በብቸኝነት በንግድ ምልክትነት ሊመዘገብ የሚገባ አይደለም፤ በጀሪካን ላይ ያለዉ የቢጫ ቀለም የንግድ ምልክት ባለቤት ነኝ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም ፤ለተጠሪ የተሰጠዉ የጀሪካን ቀለም ዓይነት ቢጫና አረንጓዴ እንጂ በሙሉ ቢጫ ቀለም አይደለም፣ ተጠሪ የንግድ ምልክት መብት አለዉ ቢባል እንኳን የአመልካችና የተጠሪ የንግድ ምልክቶች ፍጹም የተለያዩ ናቸዉ፣ሁለቱም የንግድ ምልክቶች የተለያዩ ስለሆኑ ሸማቾቹን የሚያደናግር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኂላ የዳኝነት ችሎቱ ጉዳዩን በመመርመር የሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች የግራቀኛቸዉ የምርት ማሸጊያ ጀሪካን ዲዛይኖች እና የቀለም ዉህድ ሸማቾችን የሚያደናግርና ተጽዕኖ የሚፈጥር፣የማይለያዩ እና ተመሳሳይነታቸዉ የሚጎላ በመሆኑ በንግድ ዉድድርና ሸማቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር አንቀጽ 8 /2፣ሀ/ ሥር ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ነዉ፤አመልካች ሸማቾችን የሚያደናግር እና ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር መፈጸሙ ስለተረጋገጠ በአዋጁ አንቀጽ 32 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ እና አስተዳደራዊ ቅጣት መወሰን ተገቢ ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ምርት ለገበያ ማቅረብ እንዲያቆም፣ አመልካች በፈጸመዉ ያልተገባ የንግድ ዉድድር በአዋጁ አንቀጽ 42 /3/ መሰረት ምርቱን አምርቶ ወደ ገበያ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በሰራባቸዉ አጠቃላይ ጊዜያት ዉስጥ ከሽያጭ ገቢ 5% እንዲቀጣ በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል የንግድ ዉድድር የሸማቾች ጥያቄ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር አለ ለማለት የሚያስችል ነገር ስለሌለ የሥር ዉሳኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጥበቃ የተደረገለት ቤስት በረኪና ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ብራይት ቤካስ የሚል ነዉ፣ አመልካች ግን ይህን የንግድ ምልክት በመተዉ ቤስት ብራይት በማለት ከተጠሪ ጋር ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ዉስጥ በመግባት ሸማቹን ሕዝብ የማደናገር ተግባር መፈጸሙ የተረጋገጠ ስለሆነ የይግባኝ ሰሚ

አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ስምንት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡--የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ድርጊት በሌለበት እና በዚህ ረገድ ዐ/ሕግ ክስ ባላቀረበበት በቅጣት መልክ ከሽያጭ ገቢዉ 5% እንዲቀጣ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሮ የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፤የሥር ፍ/ቤት የካሳ መጠን ሳይጣራ 5% ካሳ ይከፈል ያለበት አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘዉ መሰረት ታህሳስ 13 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ ስምንት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ጽ/ቤት ጥበቃ የተሰጠዉ የንግድ ምልክት ‹‹ቤስት በረኪና›› እንደሆነ፣ ለተጠሪ የተሰጠዉ የንግድ ምልክት ደግሞ ‹‹ብራይት ቤካስ›› የሚል እንደሆነ የሥር ዉሳኔ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪ ስልጣን ባለዉ አካል ይህን ‹‹ብራይት ቤካስ›› /BRIGHT BEKAS/ የሚለዉ የንግድ ምልክት ጥበቃ የተሰጠዉ ሲሆን አመልካች ግን ስልጣን ባለዉ ሳያስመዘግብ ወይም ስልጣን ባለዉ ዘንድ ባላስመዘገበ ‹‹ቤስት ብራይት›› /BEST BRIGHT/ የሚል ምልክት በመጠቀም ምርቶቹን ለገበያ ማቅረቡ ተገቢ ያልሆነ የንግድ

ዉድድር መፈጸሙን እና ሸማቹን ማህበረሰብ የሚያደናግር እንደሆነ በሥር የዳኝነት አካላት የቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ እንደሚያረጋግጥ የሥር ዉሳኔ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ምርቶቹን በማሸግ ለገበያ የሚያቀርብባቸዉ የጀሪካን ዲዛይኖች እና የቀለም ዉህድ በቀላሉ የማይለያይ እና ተመሳሳይነታቸዉ የሚጎላ በመሆናቸዉ ሸማቾችን የሚያደናግርና ተጽዕኖ የሚፈጥር ይህ ደግሞ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር መፈጸሙን የሚያረጋግጥ እንደሆነ በሥር የዳኝነት አካል የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ስለሆነም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የአሁን አመልካች የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 8 በመተላለፍ በተጠሪ ላይ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ተግባር መፈጸሙን የሥር የዳኝነት አካላት በማረጋገጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 መሰረት ተገቢ እርምጃ ሊወሰንበት እንደሚገባ አረጋግጧል፡፡ ይህ ችሎት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን የመጨረሻ ዉሳኔዎችን ከማረም ባለፈ ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ስለሌለዉ፣ በዚህ ምክንያት የሥር የዳኝነት አካላት ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር መቀበል አስፈላጊ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች ሸማቾችን የሚያደናግር እና ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ተግባር በተጠሪ ላይ መፈጸሙን በሥር የዳኝነት አካላት የተረጋገጠዉን ይህ ችሎትም ተቀብሎታል፡፡ ስለዚህ ይህ ችሎት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበዉን ቅሬታ አልተቀበለዉም፡፡

ሌላዉ መታየት ያለበት ጉዳይ የሥር የዳኝነት አካላት የአሁን አመልካች የአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 8 /2፣ ሀ/ በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር መፈጸሙን ያረጋገጡ ቢሆንም አስተዳደራዊ ቅጣት መወሰናቸዉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የአሁን አመልካች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር መፈጸሙ ተረጋግጧል በማለት በአዋጁ አንቀጽ 42 /3/ መሰረት ምርቱን አምርቶ ለገበያ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሽያጭ ገቢዉ 5% እንዲቀጣ መወሰኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን በይግባኝ በማየት ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ይህን የሥር የዳኝነት አካል የዉሳኔ ክፍል ሳያርም ማጽናቱን የሥር ዉሳኔ ያመለክታል፡፡ በዚህ ረገድ የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 37 መሰረት ክስ የማቅረብ ስልጣን ያለዉ አካል ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በባለስልጣኑ የዳኝነት ችሎት አስተዳደራዊ

እርምጃ እንዲወስድና አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲጣል ክስ ሊያቀርብ የሚችለዉ የባለስልጣኑ ዓቃቤ ሕግ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ የአስተዳደራዊ ቅጣትን ለማስቀጣት ክስ ማቅረብ ያለበት ዐቃቤ ሕግ ነዉ እንጂ የአሁን ተጠሪ ዳኝነት የሚጠይቅበት እና በዚህም ጥያቄ መነሻነት በአመልካች ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚወሰንበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ የባለስልጣኑ ዐ/ሕግ ያቀረበዉ ክስ በሌለበት አመልካች ለፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ተግባር አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲወሰንበት በሕግ ስልጣን የተሰጠዉ ተገቢ የሆነ አካል ክስ ባላቀረበበት ከላይ የተጠቀሱት የዳኝነት አካላት የተጠሪን ጥያቄ ተቀበለዉ አስተዳደራዊ ቅጣት መወሰናቸዉ ከአዋጁ ዓላማ ዉጭ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት በመ.ቁ.00041 በ7/1/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.120677 በ28/7/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የንግድ ዉድድር የሸማቾች ጥያቄ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት በመ.ቁ.00007 በ17/3/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
3. የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ከሽያጭ ገቢዉ 5% አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲቀጣ የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ነገር ግን እነዚህ የዳኝነት አካላት የወሰኑት ሌላዉ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉ ይቻሉ፡፡
6. በ2/9/2009 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**የሰ/መ/ቁ/** - 136245

**ቀን** - 23/05/2010

**ዳኞች፡-** ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች፡-** በደሌ ቢራ አ/ማህበር ነ/ፈጅ ወንድወሰን ክፍሉ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ገብረመዲህን ገ/ሕይወት አልቀሩቡም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍርድ**

ክርክሩ የተጀመረዉ በ ኢሉአባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ ከአመልካች ጋር ባደረጉት ቢራ የማከፋፈል ዉል መሠረት ተጠሪ ቁጥራቸዉ 7461491 እና 716,1487 የሆኑትን ቼኮች አስይዞ ባዶ ጠርሙሶችን በመዉሰድ ሲሰራ የነበረ ሲሆን በኋላ ላይ ብር 1,036,840.00 ጥሬ ገንዘብ አስይዞ አመልካችም በቼኮቹ ምትክ ብሩን ተቀብሎ ሁለቱን ቼኮች መልሶ የሰጠዉ መሆኑን፣ ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠሪ ስራዉን አቋርጦ የተረከባቸዉን ጠርሙሶች ለአመልካች የመለሰ ሲሆን፣ አመልካች በማስያዣነት ከወሰደዉ ገንዘብ ዉስጥ ብር 783,840.00 የከፈለዉ ሲሆን ቀሪዉን 253,000.00 ብር ግን ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ አላደረገም በሚል የከለከለዉ በመሆኑ ይሄዉ ገንዘብ ከ14/11/2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 15 ወለድ ጋር እንዲከፈለዉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ፡፡

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ መልስ፤ ተጠሪ በብር 1,036,840.00 ለሚገመት የገንዘብ መጠን ሁለት ቼኮችን አስይዞ ጠርሙሶቹን ከወሰደ በኋላ ቁጥሩ 7461487 ለሆነ ቼክ በጥሬ ገንዘብ ብር 783840 ገቢ ያደረገ ሲሆን፣ ቁጥሩ 7461491 ለሆነዉ ቼክ ብር 253,000.00 ገንዘቡን ገቢ ሳያደርግ በስህተት ገቢ እንደተደረገ ተቆጥሮ ሁለቱም ቼኮች የተመለሱለት መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ ደረሰኝ ማቅረብ ያለበት መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ግራ ቀኝ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ፤ ተጠሪ የሚጠበቅበትን ገንዘብ ብር 1036840.00 በመክፈሉ ምክንያት ቀደም ሲል አስይዞ የነበረዉ ሁለቱ ቼኮች ከምስጋና ጋር የተመለሱለት መሆኑን፣ አመልካች ገንዘቡ ገቢ መደረጉን ገልፆ ሁለቱን ቼኮች ለተጠሪ መመለሱ የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን እና ይህም ማስረጃ በፍ/ሕጉ አንቀጽ 2020 መሰረት በቂ መሆኑን ጠቅሶ አመልካች ለተጠሪ በክሱ የተመለከተዉን ብር 253,000.00 ከ14/11/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ተጠሪ ገንዘቡን ካስያዘ በኋላ ቼኩን መልሶ ሊወስድ የቻለበት አግባብ ዋስትና እንጂ ዕዳን የማይመለከት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ ከአንቀጽ 2018-2025 ያሉት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሌላቸዉ መሆኑን፣ በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ በፃፈዉ ደብዳቤ በቼክ ቁጥር 746191 የተመለከተዉ ገንዘብ ሳይከፈል በስህተት እንደተከፈለ ተቆጥሮ ለተጠሪ የተመለሰለት መሆኑን እና ተጠሪ ደረሰኝ ካቀረበ በድጋሚ የሚታይለት መሆኑን የገለጸለት መሆኑን እና በርግጥም ተጠሪ ከፍሎ ቢሆን ኖሮ በባንክ እስቴትመንት ላይ ሊገኝ እንደሚችል በመግለጽ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 03/05/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃዉ አማካይነት ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ብር 253,000.00 ገቢ ሳያደርጉ ቼኩ በስህተት የተመለሰላቸዉ መሆኑ እና በአመልካች ሲኒየር አካዉንታንት የተጠሪ አካዉንት ተፈትሾ ተጠሪ ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉ ተረጋግጦ እያለ አመልካች ገንዘቡን እንዲከፍል የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በመግለጽ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኝ እንዲከራከሩ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ ተጠሪ ለብር 1,036,840.00 ቼክ አስይዞ ጠርሙሶቹን መዉሰዱን፣ ከዚህ ዉስጥ አመልካች ለተጠሪ ብር 783840.00 የከፈለዉ በመሆኑ ላይ ግራ ቀኝ ክርክር የላቸዉም፡፡ ተጠሪ ለጠርሙስ መያዣ በሰጣቸዉ ሁለት ቼኮች ላይ የተመለከተዉን ብር 1,036,840.00 በጥሬ ገንዘብ ለአመልካች መክፈሉን ገልፆ አመልካች ቼኮቹን ስመልስ ለተጠሪ በፃፈዉ ደብዳቤ ያረጋገጠ ስለመሆኑም ተገንዝበናል፤ አመልካችም ይህን አምኗል፡፡ አመልካች ለተጠሪ ሊመልስ ከሚገባዉ ገንዘብ ብር 253,000.00 ላለመክፈል በዋናነት የሚከራከረዉ ይህ ገንዘብ ገቢ ሳይሆን ገቢ እንደተደረገ ተደርጎ በደብዳቤዉ የተገለጸ እና ቼኩም በስህተት የተመለሰ መሆኑን፣ በስህተት የተከፈለ ስለመሆኑም በሌላ ጊዜ በተፃፈ ደብዳቤ ለተጠሪ መግለጹን ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ገንዘብ የተከፈለ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ወይም ደብዳቤ ሰነዱን ባዘጋጀዉ ወይም ደብዳቤዉን በፃፈዉ ሰዉ ላይ ማስረጃ እንደሚሆን በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2018(1) ስር ከተደነገገዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ህጉ ይህን ድንጋጌ በዚህ መልኩ ሲያስቀምጥም አንድ ሰዉ ገንዘብ መከፈሉን በተመለከተ የሚሰጠዉ የሰነድ ማስረጃ ወይም ደብዳቤ በርግጥም ገንዘቡ መከፈሉን አረጋግጦ ነዉ በሚል ሃሳብ እንደሆነ ይታመናል፡፡ አመልካች ቼኩ ለተጠሪ የተመለሰዉ እንዲሁም ደብዳቤዉም የተፃፈዉ ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ሳያደርግ መሆኑን እና ይህም ስህተት መሆኑን በኋላ ለተጠሪ በፃፈዉ ደብዳቤ የገለጸለት መሆኑን በመግለጽ ይከራከራል፤ ይሁንና በስር ፍርድ ቤት በሰጠዉ መልስ

ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ አድርጎ ከሆነ ይህን የሚያሳይ ደረሰኝ ማቅረብ እንደሚገባዉ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ቼኩ የተመለሰዉ በስህተት መሆኑን ገልፆ ለተጠሪ በፃፈዉ ደብዳቤም ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ማድረጉን የሚያሳይ ደረሰኝ ካቀረበ በድጋሚ ሊያጣራ እንደሚችል አመልክቷል፡፡ ይህ በአጠቃላይ የሚያሳየዉ አመልካች ገንዘቡን ገቢ ሳያደርግ ገቢ እንዳደረገ ተቆጥሮ ቼኩ የተመለሰለት በስህተት መሆኑን ገልፆ ለተጠሪ የፃፈዉ ደብዳቤም ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ አለማድረጉን አመልካች እራሱ እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ቼኩ ለተጠሪ የተመለሰለት በስህተት መሆኑን በመግለጽ አመልካች በኂላ ላይ የፃፈዉ ደብዳቤ ቀደም ሲል ገንዘቡ ገቢ መደረጉን አረጋግጦ ቼኩን ከምስጋና ጭምር ለተጠሪ በመመለስ የሰጠዉን ማረጋገጫ ሊያስተባብል የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢሉአባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ፍርድ የግራ ቀኝ ክርክር እና የቀረበዉን ማስረጃ መሠረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 127837 በቀን 14/03/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/207712 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ሽሮ የኢሉአባቦራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/24452 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.chilot.me

የሰ/መ/ቁጥር 135197

ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካች፡ - አቶ ደለሳ ሌጅሳ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ፍቃዱ ጫላ - ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ማሚቱ ጀቤሳ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 228415 ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም ያሳለፈውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በጉድሩ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በጣልቃ ገብነት ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት አቶ ታሪኩ ፊጤ 2ኛ ተጠሪን ዋስ አድርገው በ19/05/2002 ዓ.ም በተፃፈ ውል ብር 10,000.00 ተበድረው ገንዘቡን እስከ 30/05/2004 ዓ.ም ከፍሎ የማይጨርስ ከሆነ ብር 30,000.00 የሚያወጣውን በኮምቦልቻ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኝ ቤታቸውን እንድወስድ ተስማምተን ገንዘቡን በጊዜው ሳይመልሱልኝ በ2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ የቤቱን ስመሃብትነት ወደ ስሜ እንዲያዛውሩ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ቢታዘዝም ለክሱ የሰጡት መልስ የለም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት በ01/10/06 በተደረገ ውል በብር 30,000.00 2ኛ ተጠሪና ልጃቸው ወ/ሮ ጌጤ ጀቤሳ (በሥር 2ኛ ጣልቃ ገብ) ከሸጡልኝ በኋላ በጋራ ለኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ማመልከቻ አስገብተን እያለ በመካከላችን ያለው ውል ሳይፈርስ ከከሳሽ ጋር የሃሰት ውል አዘጋጅተው በዚህ ቤት ላይ እየተከራከሩ ስለሆነ ወደክርክሩ ገብቼ የባለንብረትነት መብቴን እንዳስከብር በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጣልቃ ገብ ወደክርክሩ እንዲገቡ ተፈቅዶ 2ኛ ተጠሪ ለጣልቃ ገቡ አቤቱታ በሰጡት መልስ በመካከላችን ውል የለም፤ ቤቱን አልሸጥኩም፤ ገንዘብም አልወሰድኩም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል እና የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት ከመረመረ እና የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር አጣርቶ እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ ያቀረበው የውል ሰነድ የግዥና ሽያጭ ውል መደረጉን የሚገልፅ አይደለም፤ የከሳሽ ምስክር ቤቱን በዕዳ ለዋስትና አስይዞታል ቢሉም በእዳ ለዋስትና መያዙን የሚያሳይ በከተማ አስተዳደሩ የተመዘገበ ነገር የለም፤ የማይንቀሳቀስ ንብረት በዕዳ ሲያዝ በጽሁፍ ሆኖ በማይንቀሳቀሰ ንብረት መዝገብ ላይ ካልተመዘገበ ውጤት አይኖረውም፤ በመሆኑም ከሳሽ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽ ከልጇ (በሥር 2ኛ ጣልቃ ገብ ሆነው የተከራከሩ ወ/ሮ ጌጤ ጀቤሳ) ጋር በመሆን ቤቱን ለአመልካች ሸጠው ስሙ እንዲዞር በከተማው አስተዳደር አስገብተው ከፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ስለተሰጠ ብቻ ስሙ ሳይዞር መቅረቱ ስለተረጋገጠ ተከሳሽ ቤቱን ለጣልቃ ገብ (የአሁን አመልካች) ሊለቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም ተጠሪዎች ቅሬታቸውን በይግባኝ ለሆሮ ጉድሩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክርክሩን ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የብድሩ መክፈያ ጊዜ ጥር 30/2004 ዓ.ም ካለፈ በኋላ የብድር ውል መሆኑ ቀርቶ ወደ ሽያጭ ውል የሚለወጥ በመሆኑ፤ 2ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ለቀረበው ክስ መልስ ባይሰጡም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ቤቱን በህይወት ከሌለው ባለቤታቸው ጋር በመሆን አስይዘው ብር 10,000.00 በመበደር እና በተባለው ቀን ካልመለሱ ቤቱን ለመልቀቅ መስማማታቸውን ገልፀዋል፤ የ1ኛ ተጠሪ ጥያቄም ቤቱ ለዕዳው ይዋል የሚል ነው፤ በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች አልሸጥኩለትም ብለው እየተከራከሩ የሥር ፍርድ ቤት መያዣው አልተመዘገበም በሚል የከሳሽን (1ኛ ተጠሪን) ጥያቄ ውድቅ አድርጎ ቤቱ ለጣልቃ ገብ (ለአመልካች) እንዲለቀቅ መወሰኑ የህግ መሰረት የለውም በማለት ውሳኔውን ሽሮ ቤቱን 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ እንድትለቅ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው በ1ኛ ተጠሪ ባለቤት ስም የሚታወቀውን ቤት 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች በሽያጭ አስተላልፈው በገዥ (በአሁን አመልካች) ስም እንዲዛወር ለኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ማመልከታቸውን ስለማስገባታቸው አስተዳደሩ ለሥር ፍርድ ቤት ምላሽ የሰጠ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች አልሸጥኩም ብላለች፣ ሟች ባለቤቴ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ አስይዞ ብር 10,000.00 ተበድሮ ለመመለስ ባለመቻሉ ተጨማሪ ብር 20,000.00 ከ1ኛ ተጠሪ ተቀብለናል ፣ ቤቱ ለዕዳችን እንዲውል ለ1ኛ ተጠሪ ሰጥተናል በሚል ተከራክረዋል በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ የሥር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ተከራካሪዎቹ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር እና የሥር ፍርድ ቤቶች ካረጋገጧቸው ፍሬ ነገሮች አንፃር በህጉ አግባብ የተቋቋመና መብትና ግዴታ የሚፈጥር ሽያጭም ሆነ የመያዣ ውል መኖር አለመኖሩን እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው ያሳለፉት ውሳኔ ህጉን መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የጣልቃገብ አቤቱታ ክርክር የተነሳበትን ቤት በ01/10/06 በተደረገ ውል በብር 30,000.00 ከ2ኛ ተጠሪ እና ከልጃቸው ገዝተው ለኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ማመልከቻ አስገብተው እንደነበር በመግለጽ የሚከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በመካከላችን ውል የለም፣ ቤቱን አልሸጥኩም፣ ገንዘብም አልወሰድኩም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ሽያጩን የካዱ በመሆኑ አመልካች እንደክርክራቸው የሽያጭ ውል መደረጉን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሰረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ውል ማስተላለፍ ጥንቃቄ እና ጥበቃ የሚሻ በመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውል የሚደረግበት ስርዓት (ፎርም) የተለየና ጥብቅ መስፈርት የሚከተል መሆኑን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውሉ ሁለት መስፈርቶችን ማሟላት የሚጠበቅበት ሲሆን የመጀመሪያው ውሉ በጽሁፍ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ውሉ በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ፊት መከናወን የሚኖርበት መሆኑ ነው፡፡ ህጉ ይህ እንዲሆን የሚጠይቀው በተዋዋዮች መካከል በህግ ፊት የሚፀና ውል እንዲኖር

ለማድረግ ነው። በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 21448 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል።

በተያዘው ጉዳይ ከፍሲል እንደተመለከተው አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት በውል የገዙ መሆኑን በማንሳት የሚከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው የሽያጭ ውል የለም በማለት ተከራክረዋል። አመልካች በግራ ቀኙ መካከል በህጉ መስፈርቶች መሰረት የሽያጭ ውል መደረጉን የሚያስረዳ ማስረጃ ማቅረባቸው አልተረጋገጠም። በሌላ በኩል ተጠሪ በመንደር የተደረገ ስምምነት በመያዝ ከአመልካችና ከልጃቸው (የሥር 2ኛ ጣልቃ ገብ) ጋር በመሆን በከተማው አስተዳደር ማመልከቻ አስገብተው ከፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ስለተሰጠ ስሙ ሳይዞር ቀርቷል መባሉ በህጉ አግባብ የተቋቋመ ውል አለ እንዲባል በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት የሚተካ አይሆንም። ስለሆነም በህጉ አግባብ የተቋቋመ የሽያጭ ውል በሌለበት የስር ፍርድ ቤት በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የሽያጭ ውል አለ በማለት ተጠሪ ለአመልካች ቤቱን ሊለቁ ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል።

በሌላ በኩል የሥር ከሳሽ (የአሁን 1ኛ ተጠሪ) ባቀረቡት ክስ የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት አቶ ታሪኩ ፊጤ በ19/05/2002 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ብር 10,000.00 ተበድሮ ገንዘቡን እስከ 30/05/2004 ዓ.ም ከፍሎ የማይጨርስ ከሆነ ብር 30,000.00 የሚያወጣውን የተበዳሪ ቤት እንድወስድ ተስማምተናል፤ ገንዘቡን በጊዜው ሳይመልሱልኝ በ2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ 2ኛ ተጠሪ መያዣ የተደረገውን የቤቱን ስመሃብት ወደ ስሜ እንዲያዛውሩ ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርበዋል።

የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ 2ኛ ተጠሪ ስመሃብት እንዲያዛውሩ በፍርድ እንዲወሰን ቢሆንም ሥም የማዛወር ተግባር የአስተዳደር ሥራ በመሆኑ ተጠሪ ስመሃብቱን ወደ ስሜ እንዲያዛዉሩ ይወሰንልኝ በሚል ያቀረቡት አቤቱታ የክስ ምክንያት አለው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም። የ1ኛ ተጠሪ ክስ በመያዣ ውሉ መሰረት የቤቱን ስመሃብት አስተዳደሩ እንዲያዛውርላቸው 2ኛ ተጠሪ ተገቢውን ይፈፅሙልኝ በሚል የቀረበ ከሆነም 2ኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ለክሱ በቀጥታ የሰጡት መልስ ባለመኖሩና ልጃቸውም የመያዣውን ውል ሳይሆን የሽያጩን ውል በማመን ይከራከሩ ስለነበር በቅድሚያ በህጉ ፊት የሚፀና ውል መኖር አለመኖሩን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል።

የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዣ በማናቸውም አይነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆን ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ

ርስት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ማንኛውንም አይነት ውጤት እንደማያስገኝ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3052 ይደነግጋል፡፡ ከዚህም ሌላ በፍ/ብ/ህ/ቁ 3060 እንደተደነገገው ዕዳው እንዲከፈል በተወሰነበት ጊዜ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው የመያዣ መብት ያገኘበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይወስዳል የሚል ስምምነት ሁሉ ተቀባይነት እንደሌለው ተመልክቷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለሰጡት ብድር ቤቱን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3052 በሚደነግገው አግባብ መያዣ ስለማድረጋቸው የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም በህጉ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ ውል አለ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ በሌላም በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ለክሱ መልስ ባይሰጡም የብድር ዕዳው መኖሩን እና ቤቱም መያዣ መደረጉን በመግለፅ የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው እንደነበር በውሳኔው አመላክቶ ቤቱን 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲለቁ በማለት ውሳኔ ቢሰጥም ውሳኔው በፍ/ብ/ህ/ቁ 3060 በግልፅ የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ቤቱ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲለቀቅ የተሰጠው ውሳኔ ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የሽያጭ ውል አለ በማለት ተጠሪ ለአመልካች ቤቱን ሊለቁ ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስም ይዛወርልኝ ጥያቄን አላግባብ ተቀብሎ በህጉ ተቀባይነት የሌለውን ስምምነት መሰረት በማድረግ ውሳኔ ማሳለፉ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎቶች ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የጉድሩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 17506 በ06/01/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 17718 በ08/07/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 205415 በ14/08/2007 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ እና የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 228415 በ21/02/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ይህ ውሳኔ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ከፈልን የሚሉትን ገንዘብ ለማስመለስ የሚያቀርቡት ክስ ቢኖር የሚከለክል አይሆንም ብለናል፡፡

3. በዘህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰበር መ/ቁ/ 136262

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡ ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች ፡ የቤንሻንጉል ጉ/ክልል ዓቃቤ ህግ

ተጠሪ ፡ መሀሪ ታደሰ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ፡፡**

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የወንጀል ክርክር የሚመለከት ነዉ ፡፡ አመልካች ተጠሪ ላይ የመሰረተዉ ክስ ይዘት የወ/ህግአንቀጽ 631/1/ለ ላይ የተደነገገዉን በመተላለፍ በ21/06/08 ዓ.ም ከቀኑ በ8፡00 ሰዓት ላይ እድሜዉ 8 ዓመት ከሆነዉ ግል ተበዳይ እያሱ ቦጋለ የተባለዉን ህጻን ልጅ ሰዉነታችንን እንታጠብ በሚል ሰበብ አታሎ ወደ ወንዝ ወስዶ የግብረሰዶም ፈጽሟል የሚል ሲሆን ተጠሪ ክዶ በመከራከሩ ጉዳዩን በመጀመሪያ ዳኝነት የተመለከተዉ የፓዌ ወረዳ ፍ/ቤት በዓቃቤ ህግ ማስረጃ የተመሰከረና ተጠሪ በመከላከያ ማስተባበል አለመቻሉን አረጋግጦ በተከሰሰበት አንቀጽ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ሰጥቶ ቅጣትን በተመለከተ የተጠሪ እድሜ 15 ዓመት መሆኑን በሌላ በኩል የግል ተበዳይ እድሜ ከ13 ዓመት በታች ሆኖ ድርጊቱ የተፈጸመዉ በጫዋታ ዉስጥ መሆኑን ምክንያት በማድረግ በ15 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል ፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሠኝቶ ለመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ ያስመዘገበዉ እድሜ 13 ሲሆን ፓዌ ሆስፒታል የተጠሪ እድሜ ከ14-16 መካከል የሚገመት መሆኑን በመግለጹ ሊወሰድ የሚገባዉ እድሜ 14 ዓመት እንደሆነ እና ቅጣቱም ሲወሰን ስለህጻናት መብት ደህንነት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህገ መንግስትና በወ/ህጉ አንቀጽ 157 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተመለከተዉን መሰረት በማድረግ የተጠሪ እድሜ ከ9-15 እድሜ ክልል ዉስጥ ከመሆኑ አኳያ ሊፈጸም የሚገባዉ የጥንቃቄ እርምጃ ብቻ ነዉ በማለት ተጠሪ እናቱ ዘንድ ሆኖ በፖሊስ በኩል ክትትል እንዲደረግበት በወ/ህ/ አንቀጽ 159/2/ መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም ፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮ ከፍተኛዉ ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ የተላለፈዉን የጥፋተኛነት ዉሳኔ ተቀብሎ ቅጣትን በተመለከተ ለእናቱ በአደራ እንዲሰጥ የመወሰኑን አግባብነት በተመለከተ ከወ/ህ/ አንቀጽ 159 /2/ አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል ፡፡ተጠሪን በመወከል የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከላካይ ጠበቃ የሰጠዉ መልስ ባጭሩ በወ/ህጉ አንቀጽ 168/2/ መሰረት የቅጣቱ ጣሪያ 10 ዓመት ላይ እንዲወሰን ዓቃቤ ህግ የጠየቀዉ ተገቢ መሆኑን በሌላ በኩል ተጠሪ አካለ መጠን ያልደረሰ አጥፊ በመሆኑና በአካባቢዉ የፀባይ ማረሚያ ባለመኖሩ ፀባዩን በቅርብ ለመከታተል ለእናቱ እንዲሰጥ  መደረጉ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡ መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለዉ የወ/ህግ አንቀጽ 631/1/ለ ተላልፎ መገኘቱ  ተረጋግጦ ነዉ ፡፡በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ ልዩነት የተፈጠረዉና እዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ያከራከረዉ የቅጣት ዉሳኔ በተመለከተ ነዉ ፡፡ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የሚያስቀጣዉ ከ15-25 ኣመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ነዉ ፡፡ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ሲፈጽም እድሜዉ 14 ኣመት ስለመሆኑ ማስረጃ የመመርመርና የማጣራት ስልጣን በህግ የተሰጠዉ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አረጋግጧል ፡፡ አቃቤ ህግ የተጠሪ እድሜ ከዚህ በላይ ስለመሆኑ

አላረጋገጠም እነዚህን በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬነገሮች መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበዉ ከወ/ህ/አንቀጽ 159/2/ አንጻር ለመመርመር ነዉ ፡፡ የዚህን ድንጋጌ ይዘት ከመመርመራችን በፊት አጠቃላይ ስለወጣት ጥፋተኞች በወ/ህጉ የተመለከተዉን መሰረታዊ መርህ ማየት ተገቢ ነዉ ፡፡የወ/ህጉ አንቀጽ 52 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንደተመለከተዉ ህጻናትና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች የወንጀል ሃላፊነትና የቅጣት ሁኔታ ለይቶ በጠቅላላዉ ክፍል አስቀምጧል ፡፡ ይኸዉም እድሜያቸዉ ዘጠኝ ዓመት ያልሞላቸዉ ህጻናት በወንጀል ድርጊት በሃላፊነት እንደማይጠየቁ ፤እድሜያቸዉ ከ9-15 ዓመት የሆናቸዉ ወጣት አጥፊዎች ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኙም ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች እንደሚወሰዱባቸዉ ፤እድሜያቸዉ ከ15-18 ዓመት የሆኑት ወጣት አጥፊዎች የወንጀል ሃላፊነት እና መደበኛ ቅጣት እንደሚወሰንባቸዉ ነገር ግን የቅጣቱ መጠንና አተገባበሩ ላይ ከአዋቂ ሰዉ ልዩነት ያለዉ መሆኑን እንገነዘባለን ፡፡ ስለሆነም በወጣት አጥፊዎች ላይ የሚወሰነዉ ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች በእነዚህ ድንጋጌዎች የተመለከተዉን መርህ የተከተለ እንዲሆን ህጉ ያስገድዳል ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም እድሜዉ 14 ኣመት መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ቅጣትን አስመልክቶ ተፈጻሚነት ያለዉ የወ/ህጉ አንቀጽ 53 መርህ እና ይህንኑ ተከትሎ በአንቀጽ 157-168 የተመለከተዉ ዝርዝር ሁኔታዎች ናቸዉ ፡፡ከዚህ አንጻር የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ የተወሰነዉን የጥፋተኝነትና 15 ኣመት ጽኑ እስራት ቅጣት አጽንቶ አፈጻጸም በተመለከተ በወ/ህጉ አንቀጽ 159/2/ መሰርት በእናቱ ዘንድ ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግበት ትዕዛዝ መስጠቱ መነሻ ምክንያቱ በክልሉ ዉስጥ የወጣት ጥፋተኞች ፀባይ ማረሚያ ተቋም ባለመኖሩ ስለመሆኑ ተረጋግጧል ፡፡ በእኛም በኩል እንደተመለከትነዉ እድሜዉ ከ9-15 ኣመት የሆነ ወጣት ከባድ ወንጀል ፈጽሞ ቢገኝና የጥንቃቄ እርጃዎች ቢወሰንበት ይህ ሊፈጸም የሚገባዉ በጠባይ ማረሚያ ተቋም መሆን እንደሚገባ የወ/ህ/አንቀጽ 168/1/ሀ ያስገነዝባል ፡፡ ከዚህ ባሻገር በተለየ ሁኔታ ወደ እስር ቤት የሚላከዉ ጥፋተኛዉ አደገኛና ሰላምን የሚያዉክ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ከአንቀጽ 168/1/ለ ይዘት መረዳት ይቻላል ፡፡

ከዚህ አግባብ ተጠሪ የፈጸመዉ ድርጊት ከባድ ወንጀል ቢሆንም አደገኛና ሰላምን የሚያዉክ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ለቤተሰብ ሊሰጥ አይገባም በማለት ዓቃቤ ህግ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ወጣት ጥፋተኛ ላይ የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈጻጸም በተቻለ መጠን አጥፊዉን በማረም መልካም ዉጤት ሊያስገኝ በሚያስችል አግባብ ሊፈጸም እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ/120332 ላይ ከሰጠዉ ፍርድ መገንዘብ ይቻላል ስለሆነም በክልሉ ዉስጥ ለወጣት ጥፋተኞች የሚያገለግል ጠባይ ማረሚያ ተቋም በሌለበት ሁኔታ ፤ተጠሪ አደገኛ መሆኑም ባልተረጋገጠበትና በወላጅ እናቱ ቁጥጥር ስር ሆኖ የጠባዩ ሁኔታ ክትትል ቢደረግበት የተሻለ ዉጤት የማይመጣ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ የወ/ህጉ ስለወጣት ጥፋተኞች የደነገገዉን የጥንቃቄ እርምጃዎች ያገናዘበ ዉሳኔ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚያሰኝ ሆኖ አላገኘንም ፡፡

ከዚህ ባሻገር ዓቃቤ ህግም ሆነ የተጠሪ ተከላካይ ጠበቃ ተጠሪ ላይ የተወሰነዉ ቅጣት በወ/ህጉ አንቀጽ 168/2/ መሰረት እንዲታረም ያቀረቡትን ጥያቄ አግባብነት ተመልክተናል በዚህ ድንጋጌ እንደተመለከተዉ ወጣት ጥፋተኛ የፈጸመዉ ወንጀል ከባድነትና ጥፋቱንም በፈጸመበት ጊዜ የነበረዉን የእድሜ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ታስሮ የሚቆይበት ጊዜ ልክ ፍርድ ቤቱ እንደሚወስንና ጊዜዉም ከ1-10 ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ይደነግጋል ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት አንቀጽ 631/1/ለ የሚያስቀጣዉ ከ15-25 ዓመት ጽኑ እስራት በመሆኑ ወንጀሉ ከባድ ሲሆን ተጠሪ ወንጀሉን ሲፈጽም እድሜዉ 14 ኣመት መሆኑና ድርጊቱም የተፈጸመዉ በጫዋታ መካከል መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ ፡፡ የእስር ጊዜዉ ይህንን ፍሬነገርና ህጉን መሰረት አድርጎ መወሰን ሲገባ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ ይዘት ብቻ መሰረት በማድረግ የ15 ኣመት እስራት መወሰናቸዉ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል በዚሁ አግባብ ተጠሪ ላይ በስር ፍ/ ቤት የተወሰነዉ የ15 ዓመት እስራት ቅጣት በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/195/2/ለ/2 መሰረት በማሻሻል በ2 ዓመት እስር እንዲቀጣ ወስነናል ፡፤የእስራት አፈጻጸሙን በተመለከተ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ ህግ ስህተት ባለመገኘቱ ጸንቷል ፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1ኛ.በፓዌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ/09364 በ06/11/08 ዓ.ም በተጠሪ ላይ የተሰጠዉና እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት የጸናዉ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ጸንቷል ፡፡

2ኛ.እስር ቅጣቱ በወ/መ/ህግ/ስ/ስ ቁ/195 /2/ለ/2 መሰረት ወደ 2 ኣመት ተሻሽሏል አፈጻጸሙን በተመለከተ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ /ቤት በመ/ቁ/12794 በ15/02/09 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ ጸንቷል ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ.መ.ቁ.126529

ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1.ዓሊ መሐመድ

2. ተኽሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

**አመልካች**........የሰቆጣ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት --- ዐ/ህግ አሳምር ጌጤ ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ**..............ቄስ ሙሉጌታ ተረፈ ------ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የአንድ ክላሽ መሳሪያ እና ከመሰል 30 ጥይት ግምት ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-11989 የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በሰቆጣ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ተከሳሽ በሰቆጣ ወረዳ ቀበሌ 02 ነዋሪ ሲሆን በቀበሌዉ ሚሊሻ በኩል የማዕከል አስተባባሪ ኃይል አመራር ሆኖ ከሰቆጣ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት በሞዴል 22 በ30/1/2007 ዓ.ም ወጪ አድርጎ የወሰደዉን የንምራ ቁጥር 8072 የሆነ ሰ/ከ/ክላሽ 1/አንድ/ ካዝና እና ከመሰል 30 ጥይት ጋር የወሰደ ስለሆነ ይህን የመንግስት የጦር መሣሪያ እንዲመልስ፣ ካልሆነ ግምቱን የክላሽ 30,000 /ሰላሳ ሺ.ህ/ እና ጥይቱን 100*30=3,000 /ሶስት ሺ.ህ/ እንዲከፍል እንዲወሰንልን በማለት ከሷል፡፡

የሥር ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ በክሱ ላይ የተጠቀሰዉን ክላሽ ጠመንጃ በ30/1/2007 ዓ.ም በ6,000 /ስድስት ሺ.ህ/ ብር ዋስትና በመፈጸም ማዉጣቴ አይካድም፣ ይሁን እንጂ በ20/8/2007 ዓ.ም ከሰቆጣ ከተማ 02 ቀበሌ ከቄስ ወልዴ አያሌዉ ቤት አድሬ መሳሪያዉ ጠፋኝ፣ ተከሳሽ በዚህ ምክንያት በወንጀል ተከስሼ የእስራት ቅጣት ተወስኖብኝ ስለምገኝ

ድጋሚ ልከሰስ አይገባም፣ ተከሳሽ መጠየቅ ያለብኝ ወድጄ የፈረምኩት ብር 6,000 /ስድስት ሺህ/ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ይህን መሳሪያ መዉሰዱን ስላልካደ ግምቱን መክፈል ያለበትም በአማራ ብ.ክ.መ. መስተዳድር መመሪያ በ30/7/2007 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣዉ የመሳሪያ ግምት ለክላሽ ዋጋ 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና ለ30 ጥይት ብር 3,000 /ሶስት ሺህ/ በአጠቃላይ ብር 33,000 /ሰላሳ ሶስት ሺህ/ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡የሥር ከሳሽ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በድምጽ ብልጫ በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ተከሳሽ ይህን ክላሽ መሳሪያ ሲረከብ በሥራ ላይ በነበረዉ መመሪያ ቁጥር 44/2001 አንቀጽ 17 /2/ መሰረት የክላሽ ዋጋ የተተመነዉ ብር 6,000 /ስድስት ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ ብር 10 የነበረ በመሆኑ በዚህ አግባብ ሲታይ የሥር ተከሳሽ የክላሽ መሳሪያ ዋጋ ብር 6,000 /ስድስት ሺህ/ እና የ30 ጥይት ዋጋ ብር 300 /ሶስት መቶ/ ለሥር ከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔዎች በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ15/7/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት በአጭሩ፡--ተጠሪ ያጠፋዉን የመንግስት የጦር መሣሪያ /ክላሽ/ ዋጋዉን መክፈል የሚገባዉ መሣሪያዉ ጠፋ ባለዉ ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም በሥራ ላይ በነበረዉ የአማራ ክልል መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ባካሄደዉ 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 15ኛ መደበኛ ስብሰባ በማሻሻል ባወጣዉ የመንግስት የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን መመሪያ መሰረት መሆን ሲገባዉ መሣሪያዉ ለተጠሪዉ ሲሰጥ የነበረዉን የመሳሪያ ግምት መሰረት በማድረግ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣ተጠሪ የአከራካሪዉን የጦር መሳሪያ ግምት ሊከፍለዉ የሚገባዉ መሳሪያዉን ሲረከብ በነበረዉ መመሪያ ቁጥር 44/2001 ነዉ ወይስ

መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በተሻሻለዉ መመሪያ ሊሆን ይገባዋል፣ የሚለዉን ነጥብ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ቢታዘዝም ለተጠሪ መጥሪያ ለማድረስ ተጠሪ በቀበሌዉ እንደማይኖር ስለተረጋገጠ ምስክሮች ባሉበት ለሚስቱ መጥሪያ የተሰጠ መሆኑን አመልካች በአቤቱታ በማረጋገጡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

በዚህ መዝገብ የተደረገዉ ክርክር ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነዉን የመንግስት የጦር መሳሪያ የሆነዉን በክሱ የተመለከተዉን ክላሽ ፈርሞ ከአመልካች ጽ/ቤት ከወሰደ በኋላ ሳይመልስ በመቅረቱ የአሁን አመልካች የዚህ መሳሪያ ከመሰል ጥይት ዋጋ ጋር እንዲከፈለዉ ባቀረበዉ ክስ ዳኝነት መጠየቁ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክርክር መሳሪያዉን መዉሰዱን ሳይክድ በ20/8/2007 ዓ.ም የጠፋበት እንደሆነ በመግለጽ፣ የመሳሪያዉን ዋጋ መክፈል ከአለበት መሳሪያዉን በተረከበ ጊዜ በነበረዉ ዋጋ ተመን መሆኑን እንደሚገባ ገልጾ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን ተጠሪ ይህን መሳሪያ በተረከበበት ወቅት በ30/1/2007 ዓ.ም በሥራ ላይ የነበረዉ መመሪያ ቁጥር 44/2001 ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 /2/ መሰረት የአንድ ክላሽ ዋጋ ብር 6,000 /ስድስት ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ ብር 10 /አስር/ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን የአማራ ብ/ክ/መ/ መስተዳድር ምክር ቤት መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ባካሄደዉ 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 15ኛ መደበኛ ስብሰባ የመንግስት የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን በማሻሻል ባወጣዉ መመሪያ ቁጥር 11/4050 በ30/7/2007 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣዉ መሰረት የአንድ ክላሽ ዋጋ ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ ብር 100 እንዲሆን ተወስኗል፡፡ ይህ ከሆነ ከመጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በክልሉ የመንግስት የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን በተመለከተ ተፈጻሚነት ያለዉ መመሪያ መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣዉ መመሪያ እንጂ የቀድሞ መመሪያ ቁጥር 44/2001 ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ የተሻሻለ መመሪያ ከወጣ በኋላ የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን የተሻሻለ እና የተለወጠ በመሆኑ፣ በተጠሪ እጅ

የነበረዉ ክላሽ ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ ብር 100 /መቶ/ ነዉ እንጂ በቀድሞ መመሪያ የተመለከተዉ ዋጋ ሊሆን አይችልም፡፡ በተጠሪ እጅ የነበረዉ የክላሽ መሳሪያ ከመጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ዋጋዉ የተለወጠ በመሆኑ ተጠሪዉ መሳሪያ በተረከብኩ ጊዜ በነበረዉ ተመን ልጠየቅ ይገባል በማለት በሥር ፍ/ቤት የቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ መሳሪያዉ ጠፍቷል ባለ ወቅት ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም እና አመልካች ክስ ባቀረበዉ ጊዜ በሥራ ላይ ያለዉ መመሪያ በመሆኑ፣ ተፈጻሚነት እና አግባብነት ያለዉ መመሪያ ይኸዉ መመሪ ሆኖ ሳለ የቀድሞ መመሪያ ቁጥር 44/2001 መሰረት በማድረግ ተጠሪ የዚህ የክላሽ መሳሪያ ግምት ይክፈል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-11989 የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሰቆጣ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.0-05073 ሐምሌ 7 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.01-02040 በ22/11/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የአሁን ተጠሪ መሳሪያዉ ጠፋብኝ ባለ ወቅት በሥራ ላይ ባለዉ የመንግስት የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን በተሻሻለዉ መመሪያ መሰረት የክላሽ ዋጋ ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ በብር 100 የ30 ጥይት 3,000 /ሶስት ሺህ/ በአጠቃላይ ብር 33,000 /ሰላሳ ሶስት ሺህ/ ብር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
5. አመልካች በዚህ ችሎት የደረሰበት ወጪና ኪሳራ የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

የሰ/መ/ቁ. 133667

ታህሳስ 24 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኛች---- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች -----ብዙአየሁ ሾኔ የቡና ተከል ልማት ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠ/መኮንን በቀለ

ተጠሪ------------ቢ.ዲ.ኤፍ.ኤስ. ኢትዩጵያ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር- አቶ ንጉስ ሁነኛው ባለቤት ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሁከት ይወገድልኝ ክስን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ክርክሩ የጀመረው በሊሙ ኮሳ ወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ ስር ከሣሽ የአሁን ተጠሪ ተከሣሽ ደግሞ አመልካች በመሆን ተከራክረው ተከሣሽ ሁከት እንዲያቆም የተሰጠው ፍርድ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች በመፅናቱ ምክንያት የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

በስር ቀርቦ የነበረው ክስ እንደሚያመለክተው ከ2000 ዓ.ም.ጀምሮ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ማስረጃ ያወጣሁበትን እና ልዩ ልዩ ተክሎችን ያለማሁበትን ይዞታዬን በ5000 ሄክታር ላይ የሚገኘውን ድንበሩ በክሱ ላይ የተገለፀው አዋሣኞች ያሉትን በምዕራብ በኩል ወደ ድንበሬ በመግባት መኖሪያ ቤቴን እና በ57 ሄክታር ላይ የሚገኘውን ቡና ግንቦት 2006 ዓ.ም. ድንበር አልፎ በመያዝ በምሥራቅ እና በደቡብ በኩል በማስፋፋት ይዞ የሚገኝ ስለሆነ ተከሣሽ ሁከት በመፍጠር ንብረቴን የያዘብኝ ስለሆነ ሁከት አቁሞ ይህንን ንብረቴን እንዲለቅልኝ እና የክሱን ወጪና ኪሣራ ጭምር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት የአሁን ተጠሪ ክስ አቅርቧል፡፡

ተከሣሽም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ለክርክር መነሻ የሆነው መሬት ላይ ከሣሽ መብት የለውም፣ ምክንያቱም 57 ሄክታር መሬትን ጨምሮ 5000 ሄክታር

መሬት በቀን 14/9/2006 ዓ.ም. በቁ DH/INV/J/883/06 ከኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተፃፈ ደብዳቤ ከከሣሽ ላይ ተወስዶ ወደ መሬት ባንክ እንዲ ገባ ሆኗል ፣ ሌላው ክሱ ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ቀደም ብሎ መሬቱ በሚገኝበት ቀበሌ መታየት ያለበት በመሆኑ በቀጥታ ለፍርድ ቤቱ መቅረቡን እቃወማለሁ ፣ ክስ የቀረበበት ይዞታ በየትኛው ቀበሌ እንደሚገኝም አልገለፀም በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚሉትን መቃሚያዎች ካቀረበ በኃላ የፍሬ ነገር መልሱን አቅርቧል፡፡ ይዘቱም የገፋሁት መሬት የለም፣ በአለው የመንግሥት መመሪያ መሠረት የኪራይ ውል ለ45 ዓመት ፈጽሜ በ12/6/2002 ዓ.ም. የተሰጠኝ ደብዳቤ በሕጋዊ መንገድ ከዞኑ ኢንቨስትመንት መስተዳድር የተሰጠኝ ስለመሆኑ ማስረጃ ያለኝ ስለሆነ ከሣሽ በመሬቱ ላይ መብት ስለሌለው ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲል አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን በቃል ካከራከረ በኂላ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ውድቅ ማድረጉን፣ ፍሬ ጉዳዩን አስመልክቶም ግራ ቀኙን ካዳመጠ በኂላ የግራ ቀኙን ምስክሮች መስማቱን፣ በቀረበው ማስረጃም ከሣሽ ክርክር ከተነሳበት መሬት ውስጥ 57 ሄክታር መሬት እስከ ግንቦት ወር 2006 ዓ.ም.ይዞ እየተጠቀመበት የነበረ መሆኑን፣ ከ 2006 ዓ.ም. ግንቦት በኂላ ግን ተከሣሽ ይህንኑ መሬት ይዞ እየተጠቀመበት የሚገኝ መሆኑን ፍርድ ቤቱ መገንዘቡን፣ ተከሣሽ ግን ይዞታው የእኔ ነው ከማለት ውጭ ክርክር በተነሳበት መሬት ላይ ሁከት ስለመፍጠሩ እና ስላለመፍጠሩ የገለፀው ነገር አለመኖሩን፣ የተጠየቀው ዳኝነት የይዞታ ጥያቄ ሳይሆን የሁከት በመሆኑ ተከሣሽም ወደ ከሣሽ ይዞታ በመግባት አለቅም ማለቱ በምስክር የተረጋገጠ በመሆኑ ሁከት በመፍጠር በኃይል የያዘውን 57 ሄክታር የቡና መሬት እና የቆርቆሮ መኖሪያ ቤት ለከሣሽ ሊለቅ ይገባል ሲል በመ/ቁ/ 12766 ታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መወሰኑን የውሣኔው ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች ይግባኝ ብሎ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በመ/ቁ/ 34182 የካቲት 7 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና ይግባኙን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም በሚል አጽንቶታል፡፡ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታም አጣሪው ጉዳዩን ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙን ችሎቱ አስቀርቦና አቤቱታውን መርምሮ የስር ፍርድ

ቤቶች ውሣኔ የተፈፀመበት መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት በመ/ቁ/ 240932 ጥቅምት 07 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲል ጥቅምት 25 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች በአቤቱታው አጥብቆ ስህተት ናቸው በማለት የሚያነሳቸው ነጥቦች በአጭሩ፡- የክልሉ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን አከራክሮ ውሣኔ ለመስጠት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም፣ ምክንያቱም ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ መሠረት የተሰጣቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው በመሆኑም የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህን ስህተት ማረም ይጠበቅባቸው የነበረ በመሆኑ እንዲታረምልን፣

መደበኛ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብለው ለማከራከር ሥልጣን የላቸውም፣ ምክንያቱም ጉዳዩ የኢንቨስትመንት መሬትን የተመለከተ በመሆኑ ያለአግባብ ተይዞብኛል የሚል ወገን በቅድሚያ መሬቱን ለፈቀደው ኢንቨስትመንት ቦርድ አቅርቦ ውሣኔ ሳያሰጥ በቀጥታ ለመደበኛ ፍርድ ቤት መቅረብ አይችልም፡፡ በመሆኑም አስተዳደራዊ ውሣኔ ያላገኘን ጉዳይ በቀጥታ የወረዳ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ማከራከሩና ውሣኔ መስጠቱ ስህተት ነው ይባልልን፣

የጅማ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 43 መሠረት ወደ ክርክር እንዲገባ ጠይቀን መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል፣ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠረ ስለመሆኑ በአግባቡ አልተጣራም በሚል ሰፊ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ክርክር የተነሳበት ይዞታ ለኢንቨስትመንት የተሰጠ ከመሆኑ አኳያ በቅድሚያ ለኢንቨስትመንት በቦርድ ቀርቦ እልባት ሊያገኝ ይገባዋል በማለት የሰበር መ/ቁ. 46220 ተጠቅሶ የቀረበው መቃወሚያ እና የጅማ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በአመልካች የቀረበው ጥያቄ በሥር ፍ/ቤቶች የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ይቅረብ በሚል በያዘው ጭብጥ መነሻነት መዝገቡ ሊቀርብ ችሏል፡፡

አቤቱታው እና የማስቀረቢያ ነጥቡ ለተጠሪ ደርሶት የመከላከያ መልሱን እንዲያቀርብ ከመጥሪያ ጋር የተላከለት በመሆኑ ጥር 08 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ በአጭሩ፡- አመልካች ጠቅሰው ያቀረቡት የሰበር ውሣኔ የሊዝ አዋጅን መሠረት ያደረገ እንጂ የገጠር መሬትን የሚመለከት ባለመሆኑ አግባብ አይደለም፣ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድ የቀረበውን ክስ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፣ ፍርድ ቤቱም ሁከት መፈጠር አለመፈጠሩን ጭብጥ በመያዝ አጣርቶ የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው፣ በዚህ ክርክር ሂደት ይዞታው በተጠሪ እጅ እንዴት እንደገባ እንዲመረመርለት አመልካች ሲያቀርብ የነበረው መከራከሪያ ከሰበር መ/ቁ፤ 70801 ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ መታለፉ በአግባቡ ነው፣ የሶስተኛ ወገንን ጣልቃ ገብነት አስመልክቶ ለቀረበው አቤቱታም የጅማ ዞን አስተዳደር በጉዳዩ ጣልቃ እንዲገባለት ጥያቄ አቅርበው ጉዳዩ በይግባኝ ደረጃ በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ እና በመታየት ውድቅ አድርጎ ያለፈውን አመልካች ግን ጭራሽ ይሄ ጉዳይ እንዳልታየ አድርጎ ያቀረበው አቤቱታ ስህተት በመሆኑ ውድቅ ይደረግልን በሚል መልስ ከሰጠው በአጭሩ መዝግበናል፡፡ አመልካችም የቀድሞውን አቤቱታ በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገብ ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ መልስ እና የመልስ መልሱን ከስር ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በግራ ቀኙ መካከል እያከራከረ ያለው የኢንቨስትመንት መሬት መሆኑ ከላይ ተመልክተናል፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አቅርቦት የነበረው ክስ ከላይ እንደተመለከትነው ይዞታን ገፍቶ በውስጡ ካለ የቆርቆሮ ቤት እና ተክሎች ጋር ይዞብኛል ሁከት ይወገድልኝ የሚል ሲሆን የስር ተከሣሽ /አመልካች / በፍሬ ጉዳይ ከመታየቱ በፊት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አለኝ በማለት በቅድሚያ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን የለውም ጉዳዩ በገጠር መሬት ላይ የተነሳ ክርክር በመሆኑ በቅድሚያ መሬቱን ለፈቀደው አካል ቀርቦ መታየት ይገባዋል የሚል እና ሌሎች መቃወሚያዎችን ጨምሮ ማቅረቡን ተመልክተናል፡፡

አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አኳያ ለፍርድ ቤቱ የቀረበውን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች እና ተጠሪ ከመንግሥት በሊዝ የኢንቨስትመንት መሬት በኪራይ የያዙ መሆኑን ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ከያዝኩት የኢንቨስትመንት መሬት ላይ ተከሣሽ ገፍቶ 57 ሄክታር መሬት ይዞብኛል እንዲሁም በቦታው ላይ ያለ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰራ ቤት እና ተክሎችንም የያዘብኝ ስለሆነ ሁከት ፈጥሮብኛል የሚል ሲሆን ስር ተከሣሽ በበኩሉ ገፍቼ የያዝኩት መሬት የለም ከመንግሥት በህግ አግባብ የተሰጠኝ ነው በማለት በፍሬ ነገር መልሱ አቅርቧል፡፡ ወደ ፍሬ ነገር ክርክራቸው ከመገባቱ በፊት በቅድሚያ መታየት ያለበት የቀረበው ጉዳይ  የሚገዛበትን ህግ መመልከት ተገቢ ሲሆን ክርክር ያስነሳው መሬት የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል በመሆኑ የሚገዙበት ህግ ሊሆን የሚችለው የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 138/2000 ነው፡፡

በዚህ አዋጅ ላይ ሁለት ኢንቨስተሮች / ግለሰቦች/ የይገባኛል ክርክር በሚያነሱበት ጊዜ ምን እንደሚሆን የደነገገው ነገር የለም፡፡ በፌዴራል የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 32 ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ካለው አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት አካል አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል ይላል ይህ ማለት ግን ሁለት ኢንቨስተሮች የይገባኛል ክርክር በሚያነሱበት ጊዜ ጉዳያቸው የት እንደሚዳኝ የሚገልጽ ድንጋጌ አላስቀመጠም፡፡ በመሆኑም የአመልካች እና የተጠሪ ጉዳይ በተጠቀሱት ሁለት አዋጆች ላይ አለመግባባት ሲፈጠር ማን እንደሚዳኛቸው ያልተቀመጠ በመሆኑ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት መሄዱ የግድ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በክልልም በፌዴራልም የሚሰጥ ሲሆን ክርክር ባስነሳው መሬት ላይ ግራ ቀኙ ያወጡት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የፌዴራል ከሆነ ጉዳያቸው ሊታይ የሚችለው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሲሆን፣ ፈቃድ ያገኙት ግን በክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ከሆነ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታይ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ከሁለቱ አንዱ ወገን የፌዴራል ተመዝጋቢ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6  መሠረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይሆናል፡፡

አመልካች እና ተጠሪ ኃላፊነቱ የተ/የግል ማህበር መሆናቸውን አሰያየማቸው የሚገልጽ ሲሆን የንግድ ማህበር እስከሆኑ ድረስ ተመዝጋቢነታቸው በፌዴራል መንግስት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የተነሳው ክርክር በሁለት የህግ ሰውነት ባላቸው አካላት መሃከል በመሆኑ በፌዴራልም ሆነ በክልሉ የኢንቨስትመንት አዋጅ ውስጥ በእንደዚህ አይነት አካላት መሃከል ግጭት /አለመግባባት /ሲፈጠር አለመግባባቱ የሚፈታበትን መንገድ በግልጽ ያልደነገገ በመሆኑ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት መሄዱ የግድ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ መቅረብ የነበረበት በፌዴራል ፍርድ ቤት መሆኑ የግድ ሆኖ በህገ መንግሥቱ ለክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳይን እንዲያዩ በተሰጠው ውክልና መሠረት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክሱ መቅረብና መስተናገድ ሲገባው የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ሳይኖረው ተቀብሎ መወሰኑ እና የበላይ ፍርድ ቤቶችም የስር ፍርድ ቤት የፈፀመውን ስህተት ሳያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሣኔ

1. የሊሙ ኮሳ ወረዳ ፍ/ቤት በ18/4/2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ፣ የጅማ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በ7/6/2008 ዓ.ም. በመ/ቁ/ 34182 ላይ የሰጠው ፍርድ እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 240932 ጥቅምት 07 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በህግ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ውሣኔ ከማሰጠት የዚህ ፍርድ መሰጠት አያግዳቸውም፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ላወጡት ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ካ/የ

የሰ/መ/ቁ. 134681

ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ሳዲቅ አብዱራህማን

2 አቶ ቢሊሳ አብዱራህማን ጠበቃቸው አቶ ዝናቡ አክሊሉ ቀረቡ

3 አቶ ኡስማን አህመድ

ተጠሪዎች፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት - ዐቃቤ ህግ አቶ ኬኔዲ አለማየሁ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የክርክሩ ምክንያት ያለአግባብ የተወሰደ የካሳ ገንዘብ ይመለስ የሚል ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ለድሬዳዋ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆን አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘትም፡- የአሁኑ አመልካቾች እና የዚህ ሰበር ተካፋይ ያልነበሩት የሥር 3ኛ ተከሳሽን ጨምሮ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ የሌላቸውን ንብረት ወይም ይዞታ በማስመዝገብ የሌላ ሰው የሆነውን ይዞታ የእኛ ነው በማለት ትርፍ ገንዘብ ብር 131,797.73 /አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከሰባ ሶስት ሳንቲም/ እንዲመልሱ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሾች መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ነገሩ ላይም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የድሬዳዋ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ክርክር እና የምስክሮችን ቃል እንዲሁም የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ የሥር ተከሳሾች ካላቸው ይዞታ መሬት ትርፍ መሬት በማስመዝገብ የወሰዱትን በክሱ ላይ የተጠቀሰውን ብር 131,797.73 /አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከሰባ ሶስት ሳንቲም/ ተመላሽ እንዲያደርጉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም የአሁኑ አመልካቾች ይግባኝ ለድሬዳዋ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የከተማ አስተዳደሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ለማስለወጥ ሲሆን ይዘቱም፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የፍትሓብሔር ዳኝነትን በሚመለከት በቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33 ሥር ከተደነገገው ውጪ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚነሱ የፍትሓብሔር ክርክሮችን፣ የይዞታና ያልተገባ ጥቅም ተወስዷል በሚል የሚቀርቡ ክርክሮች ሰምቶ ማስረጃ ተቀብሎ የመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አከራካሪ የሆነው የይዞታ ባለቤትነት ጥያቄው የሚታየው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም የከተማው ሰበር ሰሚ ማየት ሲገባው ለከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀረበበትንና የተያዘበትን አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም የግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የነገሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ እንደተገነዘብነው የሥር 1ኛ- 3ኛ ያሉት ተከሳሾች በቀድሞ ልኬት መሠረት 4.6647 ሄክታር ሲሆን የወሰዱት የመፈናቀያ ካሳ ብር 183,664.50 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ተሰርቶ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በድጋሚ ጂ.ፒ.ኤስ መለኪያ መሥሪያ መሠረት የተለካው የመሬት

መጠን 3.271 ሄክታር የመፈናቀያ ካሳ ክፍያ ብር 128,789.97 /አንድ መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከዘጠና ሰባት ሳንቲም/ መከፈል ሲገባ በሌላቸው መሬት መጠን 1.304 ሄክታር በማስመዝገብ ብር 54,874.53 /አምሳ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ አራት ብር ከሃምሳ ሶስት ሳንቲም/ ትርፍ ገንዘብ ወስደዋል፣ የሥር 4ኛ ተከሳሽ /የአሁኑ 3ኛ አመልካች/ የሆኑት ደግሞ በቀድሞ ልኬት መሠረት 5.4570 ሄክታር ሲሆን የመፈናቀያ ካሳ ብር 190,995.00 /አንድ መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አምስት ብር/ ተሰርቶ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በአዲስ መልክ ሲለካ 3.2592 ሄክታር መሬት ሆኖ የመፈናቀያ ካሳ ግምቱ ብር 114,072. /አንድ መቶ አስራ አራት ሺህ ሰባ ሁለት ብር/ መክፈል ሲገባ በሌላቸው መሬት መጠን 2.1978 ሄክታር በትርፍነት በማስመዝገብ ብር 76,923.00 /ሰባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሶስት ብር/ ትርፍ ክፍያ ተፈጽሞላቸዋል የሚል ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ የሥር ከሳሽ /የአሁኑ ተጠሪ/ እንዲመለስ የጠየቀውን ገንዘብ የሥር ተከሳሾች /የአሁኑ አመልካቾች/ እንዲመልሱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ በዋናነት ሊታይ የሚገባው የሥር ፍርድ ቤት የቀረበውን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡ አንድ ፍርድ ቤት አንድን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን በመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር ሥልጣን ሊኖረው ይገባል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ሥልጣንን በተመለከተ የአሁኖቹ አመልካቾች የራሳቸው ያልሆነን የሌላ ግለሰብን ይዞታ ጨምረው በማስለካት ከመንግሥት ተጨማሪ የካሳ ክፍያ የወሰዱ በመሆኑ ምክንያት የማይገባቸውንና የማይመለከታቸውን ስለወሰዱ እንዲመልሱ የቀረበ ክስ በመሆኑ በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 31 (1) እንደተመለከተው የከተማውን ማስተር ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የይዞታ ባለቤትነት፣ ፍቃድ አሠጣጥ ወይም ይዞታ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ ክሶችን የማየት ሥልጣን የከተማው ፍርድ ቤት ስለሆነ ክስ መስርተን ውሳኔ ማሰጠታችን እንዲሁም የካሳው ጉዳይም ከይዞታው ጋር የሚገናኝ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትም ሥልጣኑን መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አግባብ ስለሆነ የህግ ስህተት ስለሌለ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡ ለዚህ ሥልጣን ጉዳይ ዋና መሠረት ተደርጎ የተነሳውን የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ 416/1996 አንቀጽ 31 /1/ መመልከት ለክርክሩ ህጋዊ እልባት ለመስጠት ያስችላል፡፡

የድሬዳዋ አስተዳር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 31 (1) ድንጋጌ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

- የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የይዞታ ባለቤትነት በተመለከተ የሚነሱ ክሶችን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን፣

- የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የፈቃድ አሰጣጥ በተመለከተ የሚነሱ ክሶችን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን፣

- የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የቦታ አጠቃቀም በተመለከተ የሚነሱ ክሶችን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን እንዳለው ተደንግጓል፡፡

ይህ ድንጋጌ በግልጽ እንደሚያመለክተው የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ለማስፈጸም ሲባል ከይዞታ ባለቤትነት፣ ከፍቃድ አሰጣጥ እና ከቦታ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚነሱ ክርክሮችን የከተማው ፍርድ ቤት ለማየት እንዲችል በህግ አውጪው የተሰጠ ሥልጣን ነው፡፡ ነገር ግን ከያዝነው ጉዳይ ወይም የክርክር ዓይነት ጋር ተያይዞ የተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን አይደለም፡፡

በመሠረቱ አሁን እያከራከረ ያለው ጉዳይ በአዋጁ አንቀጽ 31 /1/ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ሳይሆን አመልካቾች የራሳቸው የእርሻ ይዞታ መሬት ያልሆነ ወይም የይዞታው ባለቤት ያልሆኑበትን የሌላ ሰው እርሻ መሬት ይዞታ በትርፍ አስለክተው የማይገባቸውን ገንዘብ ወስደዋል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ በዚህ መሠረት ክርክሩ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የተነሳ የእርሻ መሬት ባለይዞታነት ይገባኛል ጥያቄን መሠረት በማድረግ የተነሳ በመሆኑና ባለይዞታው ማን እንደሆነ አከራክሮ በመለየት በትርፍ መሬት ይዞታ ተሰጥቶ የነበረው ትርፍ የካሳ ገንዘብ እንዲመለስ የሚለውን የፍትሓብሔር ክርክር የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 31 /1/ መሠረት ለከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ሥልጣን ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም የሥረ ነገሩን ለመስማት ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የሌለው በሆነ ጊዜ ስለሚፈጸም ሥነ ሥርዓት የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 9 በግልጽ ያስቀመጠውን ድንጋጌ የሥር ፍርድ ቤቶች ባለማጤን ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር

ሥልጣን የላቸውም ተብሎ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያለአግባብ በማለፍ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር በመግባት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡

ውሳኔ

1. የድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.01913 ግንቦት 3 ቀን 2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት 01075 በቀን 19/3/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች አይተው ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን የላቸውም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4. በቀን 12/04/2009 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡

5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይላክላቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

የሰ/መ/ቁ/ - 137353

ጥር 22 ቀን 2010ዓ.ም

**ዳኞች፡-**ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

**አመልካች**፡- ወ/ሮ አዛለች አጎናፍር ጠበቃ ሚልኪያስ ቡልቻ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ገብርኤል አካባቢ ቀበሌ ጽ/ቤት ዐ/ሕግ አይናዲስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ጉዳዩ ያላግባብ የተያዘ ቤት ይለቀቅልኝ በሚል የቀረበዉን ዳኝነት መሠረት በማድረግ የተሰጠዉን ፍርድ በመቃወም የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ። ክርክሩ የተጀመረዉ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘትም፤ በጎንደር ከተማ ገብርኤል አካባቢ ክ/ከተማ በ 735 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያላቸዉን ቤት ተጠሪ ያላግባብ በመያዝ ለግለሰቦች እያከራየ መሆኑን፣ ቤቱ በመንግስት ያልተወረሰ መሆኑን ገልጸዉ እንዲመለስላቸዉ ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት የከንቲባ ጽ/ቤቱ ቤቱ እንዲመለስላቸዉ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም ተጠሪ ቤቱን ለማስረከብ ፍቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሰዉ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክባቸዉ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የሚያሳይ ነዉ።

ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ መልስ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ የፕራይቬታይዘሽን ኤጀንሲ በመሆኑ ክሱ ለፍርድ ቤቱ ሊቀርብ እንደማይገባዉ እንዲሁም ክሱ በይርጋ

የሚታገድ ስለመሆኑ ገልፆ የመጀመሪያ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ ማስረጃ አለማቅረቡን እና ቤቱ የሚገኝበት ቦታ ስፋትም አመልካች እንደሚሉት 735 ካ/ሜ ሳይሆን 182 ካ/ሜትር መሆኑን እና ቤቱም የመንግስት እንጂ የአመልካች አለመሆኑን በመግለጽ የቀረበዉ ክስ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ፤ ቤት ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚለዉን ጭብጥ በማስረጃ አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የፐራይቬታይዘሽን ኤጀንሲ እንጂ የመደበኛ ፍርድ ቤት አለመሆኑን እንዲሁም አመልካች ከክሳቸዉ ጋር አያይዘዉ ያቀረቡት የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታም በ1965 ዓ.ም የተሰጠ በመሆኑ በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን አያሳይም በማለት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት አላገኝም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 26/08/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበዉ 3 ገጽ የሰበር አቤቱታ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮም ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በሚል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ እንዲከራከር በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ መዝገቡን ለማስቀረብ ከተያዘዉ ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከግራ ቀኝ ክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ላቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት

የግላቸዉ መሆኑን እና ተጠሪ ያላግባብ መያዙን ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የአመልካች አለመሆኑን በመግለጽ የተከራከረ መሆኑን ነዉ፡፡ የስር የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ ለማድረግ የቻለዉ በአንድ በኩል ቤቱ የተወረሰ መሆን አለመሆኑን በማስረጃ አጣርቶ ለመወሰን ፍርድ ቤት ስልጣን የለዉም በማለት በሌላ በኩል አመልካች ያቀረቡት ማመልከቻ በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሠረቱ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌለዉ መሆኑን እንደተገነዘበ ይህኑን ጠቅሶ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር ከመግባቱ በፊት ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን ገልፆ የቀረበዉን የክስ አቤቱታ ከመመለስ አልፎ ፍሬ ነገርን በተመለከተ ዉሳኔ መስጠት እንደማይችል በፍ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 231(1-2) ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የስር ፍርድ ቤት በአንድ በኩል ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም እያለ፣ በሌላ በኩል ግን አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ፍሬ ነገሩን በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ አይደለም በማለት የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት እንመልከት፡፡ በህግ ለሌላ አካል በግልጽ እስካልተሰጠ ድረስ በፍርድ የሚያልቁ ጉዳዮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን የፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ስር ከተመለከተዉ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከስልጣን ጋር በተያያዘ ክርክር ሲኖር ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያላቸዉ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ የማየት ስልጣን በህግ ለሌላ አካል የተሰጠ መሆኑ አለመሆኑን በአግባቡ የማረጋገጥ ግዴታ እና ኃላፊነት ያለባቸዉ ሲሆን፤ ይህን አለማድረግ በዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብት ላይ አሉታዊ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል መሆኑንም መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡

የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም ሲል ለሰጠዉ ዉሳኔ በዋቢነት የጠቀሰዉ አዋጅ ቁጥር 110/87 እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 30631 የሰጠዉን ዉሳኔ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 4(1) እና (2) መሰረት ከአዋጅ ዉጪ የተወሰዱ ንብረቶችን የባለቤትነት ሁኔታ የማጣራትና የመወሰን ስልጣን ለፕራይቬታይዘሽን

ኤጀንሲ ይሰጣል፤ አዋጅ ቁጥር 572/2000 ከአዋጅ ዉጪ የተወሰዱ ንብረቶችን ለማስመለስ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እና ያላግባብ የተወረሱ የመንግስት ንብረቶችን እንደገና ለማስመለስ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን አይቶ የመወሰኑ ስልጣን የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይሁንና ያላግባብ በከተማ አስተዳደር ወይም በቀበሌ የተያዘን ቤት ለማስመለስ የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ ለየትኛዉ አካል እንደሚቀርብ በሁለቱም አዋጆች በግልጽ አልተደነገገም፡፡ ፍርድ ቤት በዋቢነት የጠቀሰዉ በሰ/መ/ቁጥር 30631 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ሲታይ ከአዋጅ ዉጪ የተወረሱትን ቤቶች ለማስመለስ የሚቀርብ ዳኝነትን እንጂ የምርጫ ቤት ያላግባብ ተይዟል በሚል የቀረበዉን ክርክር መነሻ ያደረገ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የጠቀሰዉ የሰበር ዉሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) አኳያ ለተያዘዉ ጉዳይ በዋቢነት ሊጠቀስ የሚገባዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በከተማ አስተዳደር ወይም በቀበሌ ያላግባብ የተያዘን የምርጫ ቤት ለማስመለስ የሚቀርበዉን ክስ የማየት ስልጣን በህግ ለሌላ የመንግስት አካል ባልተሰጠበት ሁኔታ፣ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 30631 የሰጠዉ ዉሳኔም ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት የሌለዉ ሆኖ እያለ፤ መደበኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በሚል የደረሰበት ድምዳሜ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑን በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 00562 በቀን 01/03/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-22362 በቀን 11/09/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ፍርድ በማጽናት፣ የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን እንደገና በማንቀሳቀስ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢዉን ዉሳኔ ይሰጥበት ዘንድ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

የሰ.መ.ቁ.133309

ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡…1.ዳኜ መላኩ

2. ተኽሊት ይመሰል

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-….. አቶ ለማ ማሙዬ- ቀርበዋል

ተጠሪ፡-………..በአዳማ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 12 ጽ/ቤት -ነ/ፈጅ አቶ ነቢ ፈይሶ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የመንግስት ቤት ለማስለቀቅ የቀረበ ክስን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.232835 በ7/2/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ተከሳሽ የቤት ቁጥር 286.04 ከከሳሽ በዉል የተከራየ ቢሆንም በሚስቱ በወ/ሮ ዘነበች ተክሌ ስም የቤት ቁጥር 202 ሰርቶላት ተጠቃሚ አድርጓት እያለ በቀበሌ ቤት ዉስጥ መኖር ስለማይገባዉ ተከሳሽ ቤቱን እንዲለቅልን በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ባለቤቴ ያልተጠናቀቀ ቤት አግኝታ ነበር፣ ቤቱን አልገባንበትም፣ ይህ ቤት በእዳ ምክንያት በፍ/ቤት ዉሳኔ የተወሰደ ስለሆነ የመንግስት ቤት ሊለቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ በባለቤታቸዉ ስም የሰሩትን ቤት ወደ ልጃቸዉ ያዛወሩ ስለሆነ በዉላቸዉ እና በመመሪያዉ መሰረት የመንግስት ቤት ይዘዉ የሚቀጥሉበት አግባብ ስለሌለ ቤቱን ለከሳሽ እንዲለቅ በማለት

ወስኗል። የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በይግባኝ በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ባይ በሚስታቸዉ ስም የተሰራዉ ቤት በእዳ ምክንያት በፍ/ቤት ዉሳኔ በአፈጻጸም ከፍላጐታቸዉ ዉጭ ስለተወሰደ፣ ይህን ለልጃቸዉ በዘዴ አዛዉረዉ አስወስደዋል የሚባልበት ምክንያት ስለሌለ፣ ይህን የመንግስት ቤት ሊለቁ አይገባም በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ወስኗል። የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት እና የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔዎችን በመሻር የሥር የወረዳ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስቀየር ነዉ።

የአሁን አመልካች በ18/2/2009 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሥር ፍ/ቤት ያልተነሳዉን ክርክር የኪራይ ዉል ጊዜ ገደብ ማለቁን በተመለከተ በማንሳት ቤቱን እንዲለቅ መወሰኑ ስህተት ነዉ። አመልካች በባለቤታቸዉ ስም ሰርቷል የተባለዉ ቤት ከአቅም በላይ በሆነና በእዳ ምክንያት በፍ/ቤት ዉሳኔ ከእጃችን መዉጣቱ እየታየ ቤት ነበራቸዉ በሚል ምክንያት የተከራየሁትን ቤት እንዲለቅ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል።

ይህ ችሎት አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪ በ27/6/2009 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትና የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለዉም ተብሎ እንዲጸናልን፣ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ተድርጎልን ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት የሚገባዉ ነጥብ የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን የመንግስት ቤት እንዲለቁ የተሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል። ከሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች የመንግስት ቤት ከተጠሪ በኪራይ ዉል ተከራይተዉ ሲኖሩ እንደነበር፣ አመልካች በባለቤታቸዉ ስም በአዳማ ከተማ ዉስጥ የመኖሪያ ቤት መስራታቸዉ እና ይህን በባለቤታቸዉ ስም

የተሰራዉን ቤት ያበደርኳቸዉን ገንዘብ አልከፈሉኝም በሚል በእዳ ምክንያት ልጃቸዉ በፍ/ቤት ከሷቸዉ ዉሳኔ ተሰጥቶ በአፈጻጸም ተወስዶብናል በማለት የፍ/ቤት ዉሳኔ ማቅረባቸዉን ያመለክታሉ፡፡

ነገር ግን በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የቤት ኪራይ ዉል አንቀጽ 8 (6) እና በመመሪያ ቁጥር 10/2006 አንቀጽ 15.2 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አንድ የመንግስት ቤት ተከራይ የራሱ ቤት ካገኘ የመንግስት ቤትን በተከራይነት ይዞ መቀጠል እንደማይችልና የመንግስት ቤት መልቀቅ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንጻር የግራ ቀኛቸዉ ክርክር ሲታይ የአሁን አመልካች በባለቤታቸዉ ስም የሰሩትን ቤት የልጃቸን እዳ አለበት በማለት እርስ በእርሳቸዉ ተካሰዉ እና እዳም እንዳለ አምነዉ ዉሳኔ እንዲሰጥ በማድረግ የምንከፍል ገንዘብ የለንም በማለት ቤቱን ለልጃቸዉ ማስረከባቸዉ ሲታይ፣ በባለቤታቸዉ ስም የሰሩትን ቤት እና የመንግስት ቤት ይዘዉ ለመቀጠል በማሰብ የተደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር የሚታመን ተግባር እንዳልሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች በባለቤታቸዉ ስም የሰሩትን ቤት በዚህ አግባብ ወደ ልጃቸዉ ስም አዛዉረዉ የመንግስት ቤትን ይዘዉ የሚቀጥሉበት አግባብ የለም፡፡ የሥር የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የመንግስት ቤት የኪራይ ዉል ዓላማ ካለመገንዘብ የተነሳ የኪራይ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ እና ያልታደሰ በመሆኑ ዉሉ ተቋርጧል በማለት የያዘዉ አቋም ተገቢ ባይሆንም በዉጤት ደረጃ አመልካች የመንግስት ቤት በኪራይ ይዘዉ መቀጠል እንደሌለባቸዉ አቋም በመያዝ የሥር የወረዳ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ዉሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር የወረዳ ፍ/ቤት እና የሥር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች በኪራይ ዉል መነሻነት ሲኖሩበት የነበረዉን የመንግስት ቤት ለቀዉ ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የሰጡት ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ነዉ ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉ ሳ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.232835 በ07/2/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**መ/ይ**

የሰበር መዝገብ ቁጥር 140538

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-አቶ ወርቁ ታደሰ → ጠበቃ ሱልጣን ሰይፍ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጅራተ ኢልፈታ → ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ሸዋ ዞን የባኮትቤ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰውን 0.25 ሔክታር መሬት ማረሚያ ቤት እያሉ በ2000 ዓ.ም አመልካች በሕገወጥ መንገድ ለከብቶች ግጦሽ የያዘባቸው መሆኑን በመግለጽ መሬቱን ለቀው እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ የአከራካሪው መሬት ስፋት አንድ ሔክታር መሆኑን፤ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ለ42 ዓመታት ይዘው የሚጠቀሙበት እና ተጠሪ ተጠቅሞበት የማያውቅ በመሆኑ ይርጋ የሚያግደው መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ መሬት በሚሰፈርበት ጊዜ ዳገታማ መሬት ነው ተብሎ ያልተሰፈረላቸው መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት የወረዳውን መሬት አጠቃቀም እና አሥተዳደር ጽ/ቤት አከራካሪው መሬት የማን እንደሆነ እና በማን ሥም እንደተሰፈረ አጣርቶ እንዲገልጽ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠቃሹ አካል ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ አከራካሪው መሬት ለተጠሪ የተሰፈረ መሆኑ እና አመልካች ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ከብቶችን እያሰማራበት ያለ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡ የአመልካች ምስክሮች ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል  የመሬት ኮሚቴ መሬት የአርሶ አደሩ ነው ተብሎ በተመራበት ዘመን አከራካሪውን መሬት  ለአመልካች የሰጠው መሆኑን፤መሬቱ የግጦሽ መሆኑን እና አመልካች ከብቶች የሚያሰማራበት መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች  ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል አከራካሪው መሬት የተጠሪ መሆኑን እና አመልካች ለረጅም ጊዜ ከብቶችን ሲያሰማራበት የቆየ መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በግራቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች እና በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የቀረበውን ማሥረጃ ከመረመረ በኋላ የቀረቡት ማሥረጃዎች አከራካሪው መሬት የተጠሪ መሆኑን ስለሚያረጋግጡ አመልካች መሬቱን ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሠኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ያቀረብኩት የይርጋ መቃወሚያ ታልፎ በፍሬጉዳይ ላይ የሰጠሁት አማራጭ መልስ ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች አከራካሪውን መሬት ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ  ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን መሬት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በሕገወጥ መንገድ መያዙ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ታልፎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በሰጡት መልስ ተጠሪ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ በመሬቱ ስጠቀም እንደነበረ ተረጋግጧል፤አመልካች ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ መሬቱን ይዥለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር ሐሰት ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡ አመልካች አከራካሪውን መሬት ለረጅም ጊዜ ከብቶችን በማሠማራት የሚጠቀምበት መሆኑ በሥር ፍ/ቤት ቀርበው ከተሰሙት የግራቀኙ ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡ የወረዳውን መሬት አጠቃቀም እና አሥተዳደር ጽ/ቤት ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽም አመልካች ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ አከራካሪውን መሬት ከብቶችን በማሠማራት የሚጠቀምበት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አከራካሪውን መሬት በሕገወጥ ውል መነሻነት የያዙት ስለመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር የለም፡፡

የኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አሥተዳደር ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32 አርሶአደሩ በመሬቱ ላይ ያለውን መብት ለማስጠበቅ በአሥራሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ.ቁ 43226፣79394 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ ሕገወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በሕጉ የተመለከተው የይርጋ የጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን መሬት ከአሥራሁለት ዓመት በላይ ከብቶችን በማሠማራት የሚጠቀሙበት መሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማሥረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አከራካሪውን መሬት ሕገወጥ በሆነ ውል መነሻነት የያዙት ስለመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር የሌለ በመሆኑ አመልካች መሬቱን ለረጅም ጊዜ የሚጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት አለው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አመልካች መሬቱን እንዲለቅላቸው ያቀረቡት ክስ በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32 በይርጋ የሚታገድ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች አከራካሪውን መሬት ከአሥራሁለት ዓመት በላይ ይዞ የሚጠቀምበት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የተጠሪን ክስ በይርጋ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች መሬቱን ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል

በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራው ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ሸዋ ዞን የባኮትቤ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20876 ሕዳር 08 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 58734 ሕዳር 13 ቀን 2009 ዓ.ም በትዕዛዝ፤በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 254595 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

**-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ ቁጥር 149962

ቀን 25/7/2010 ዓ/ም

ዳኞች

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች - አቶ ስለሽ ዋለልኝ -አልቀረበም

ተጠሪ - የአማራ ብ/ክ/መ. ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ ስሜነህ ታደሰ ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ህዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 68301 ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ በስር ውሳኔ ሰጪ አካላት የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ መሆኑ በደንብ ቁጥር 104/2004 ተመልክቶ እያለ በአማራ ብ/ክ/መ. ሕገ መንግስት በክልል ጉዳይ የበላይና የመጨረሻ ስልጣን ያለው መሆኑ

በግልጽ ተቀምጦ እያለ የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከአማራ ብ/ክ/መ. የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የድስፒሊን ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ የአማራ ብ/ክ/መ. የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የምርምርና የህግ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው ክስ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ለከፍተኛ ትምህርት በተላከበት ወቅት በሌላ የመንግስት መ/ቤት ተቀጥሮ ከሁለት የመንግስት መስሪያ ቤት ደሞዝ በመውሰድ የማጭበርበር የድስፕሊን ጥፋት ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ ተከሳሽም ሁለት ቦታ እንዳልሰራ የሚከለክል ህግ የለም፡፡ የሰራሁት የኢኮኖሚ ችግር ስለገጠመኝ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የኮሚሽኑ የድስፒሊን ኮሚቴ አከራክሮ ተከሳሽ በኮሚሽኑ ደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 72(19) ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለው ሌላ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሟል፡፡ በአንድ መንግስት ሁለት መ/ቤት ተቀጥሮ ከሁለት ቦታ ደሞዝ ማግኘት ህጋዊ አይደለም የተቀጠረው ዝውውር ሲፈፀም የተሰጣቸውን ክሊራንስ በመጠቀም በመሆኑ ማጭበርበር ፈጽሟል፡፡ ለትምህርት ተልኮ በቋሚነት ተቀጥሮ ሙሉ ጊዜውን ተጠቅሞ ትምህርቱን ይከታተላል ማለትም አይቻልም፡፡ በመሆኑም ጥፋተኛ ነው ብለነዋል፡፡ ቅጣቱ በደንቡ ቁጥር 104/2004 እንቀጽ 72(19) የተከሰሰ ቢሆንም በደንቡ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 72(13) ማጭበርበር ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ስላገኘነው በደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 71(ረ) መሰረት ከስራ ይሰናበት ሲሉ የውሳኔ ሃሳብ አቀረቡ፡፡ የበላይ ሃላፊውም የዲስፕሊን ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ በማጽደቅ ከስራ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ለኮሚሽነሩ ይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ኮሚሽነሩም ተከሳሽ የአሁን አመልካች ከስራ እንዲሰናበት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ለአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 68301 ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥረ ነገር ስልጣን በክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 67(2ሐ) ማንኛውም የክልሉ ፍ/ቤቶች በመጨረሻ በሚሰጧቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፡፡ ሥልጣኑ ከተግባራዊነቱና የመንግስት ስልጣን ክፍፍል በተለይም ሕገ መንግስታዊ ትርጉምንም የመዳኘት ስልጣን ለፍ/ቤት ካለመስጠቱ አኳያ ከአስተዳደር አካሉ የሚነሱ ጉዳዮችን ሁሉ በሰበር የሚታይበት የህግ ስርዓት አለመዘርጋቱን የሚጠቁም ነው፡፡

ይልቁንም የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በፍ/ቤት የሚታረመው እንደ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 ያሉ ህጎች በፍ/ቤት እንዲታዩ በግልጽ ሲደነግጉና ሲመራ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በመርህ ሁሉም የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በፍርድ ቤት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 223/07 አንቀጽ 17(2) አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ለማስተናገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በአማራ ብ/ክ/መ. የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የተሰጠውን የዲስፒሊን ውሳኔ በሰበር የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከክልሉ ደንብ ቁጥር 104/04 አንቀጽ 75(3) እና ከኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(2/3) መሰረት መጣራት ያለበት በመሆኑ ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪም ጥር 15 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ መልስ በአማራ ብ/ክ/መ. ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 75(3) መሰረት የኮሚሽኑ የበላይ ሃላፊ በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን የተደነገገ በመሆኑ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 67(2/3 ሐ/መ) መሰረት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ጥር 28 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የስር የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍርድ ቤት ከተሰጡ የመጨረሻ ውሳኔና መሰረታዊ የህግ ስህተት ካላባቸው ውሳኔ ውጪ በአስተዳደራው ውሳኔ ሰጪ አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎችን ለማየት ሥልጣን የለኝም፡፡ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ስልጣን በአማራ ብ/ክ/መ. ህገ መንግስት አንቀጽ 67(2ሐ) ድንጋጌ መሰረት ማንኛውም ክልላዊ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ በሰጡባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ በመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ. ሥነ ምግባርና ፀረ

ሙስና ኮሚሽን የተሰጠውን የዲስፒሊን ውሳኔ ለማየት ሥልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ይሁንና የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2) የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል ሲል ደንግጓል፡፡ አንቀጽ 80(3ለ) ደግሞ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት ለማየት ሥልጣን ይኖረዋል ሲል ደንግጎ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 9(1) ሕገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሆነና ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር መቃረን እንደሌለበት ደንግጓል፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ. ህገ መንግስት አንቀጽ 67(2ሐ) ድንጋጌ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3ለ) ጋር የሚቃረን አይደለም፡፡ ይሄውም የአማራ ብ/ክ/መ. ህገ መንግስት አንቀጽ 67(2ሐ) ድንጋጌ ማንኛውም ክልላዊ ፍ/ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል ሲል መደንገጉ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት በፍ/ቤቶች የተሰጡ የመጨረሻ ውሳኔ ብቻ እንደሆነ ትርጉም ሊሰጠው የማይገባና በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ድንጋጌ መሰረት በክልል ጉዳዮች የተሰጡ የመጨረሻ ውሳኔም ጭምር የማየት ስልጣን እንዳለው ሊወሰድ የሚገባ ነው፡፡ እንዲሁም በተሻሻለው የአብክመ. የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 75(3) እና በሌሎችም አዋጆች "በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል" በሚል ተገልጸው የሚገኙት ድንጋጌዎች በይግባኝ ደረጃ ቀርበው ለመታየት የማይችሉ የመጨረሻ ውሳኔዎች መሆናቸውን የሚገልጽ እንጂ በሰበር ሰሚው ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ጉዳዮች ለማረም የሚቀርቡ ጉዳዮችን የሚጨምር አይደለም፡፡ በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ስር እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ህገ መንግስቱ ማንኛውም ሰው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ከሆነ ለፍ/ቤቶች አቅርበው ፍትህ የማግኘት መብት ሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጪ አካላት የተሰጡ የዲስፕሊን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን መሆኑ የክልሉ ሕገ መንግስት ያልከለከለውና የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ሥልጣኑ

እንዳለው ደንግጎ እያለ ጉዳዩ በተሻሻለው የአብክመ. የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 75(3) መሰረት ጉዳዩ በይግባኝ ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ሆኖ እያለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ጉዳዮችን ተቀብሎ የማየት ስልጣን እያለው ሥልጣን የለኝም ሲል አቤቱታውን መዝጋቱ ከህጉ ድንጋጌ ትርጉም ውጪ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 68301 ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሁን አመልካች የቀረበለትን አቤቱታ የሰበር ሰሚው ችሎት ስልጣን በመሆኑ አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መልስንለታል፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ.137939

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - ፍፁም ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር -ጠበቃ አሽናፊ አርአያ -ቀረቡ

ተጠሪ - የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት - ነ/ፈ ፍቅሬ ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ተጠሪ ጽ/ቤት ለአመልካች በቁጥር 714 በስሙ መዝግቦ የሰጠውን የኢንዱስትሪ ንድፍ ጥበቃ ሰርተፍኬት በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(2)(ሀ) የተቀመጠውን የአዲስነት መስፈርት አሟልቶ የተሰጠ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ያሳለፈውን ውሳኔ እና ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔው የሚነቀፍበት የህግ ስህተት የለም በማለት ያሳለፈውን ብይን በመቃወም ነው፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በላይነህ ደቻሳ የተባሉ ግለሰብ በጠበቃቸው በኩል ለተጠሪ ጽ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ለአሁን አመልካች በማመልከቻ ቁጥር ET/ID/2015/2433 በቀን 19/02/2008 ዓ.ም በቁጥር 714 ተመዝግቦ የተሰጠው ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት የአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(1)(2) ድንጋጌዎችን ሳያሟላ ያላግባብ የተሰጠው በመሆኑ ሰርተፍኬቱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ጽ/ቤትም አቤቱታውን ተቀብሎ አከራካሪ የሆነው ንድፍ በጽ/ቤቱ በመዝገብ ከመግባቱ በፊት በታይላንድ እና በኢትዮጵያ የሚታወቅ መሆኑን ከቀረቡት ማስረጃዎች ተገንዝቤያለሁ፤ ንድፉ አዲስነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የተሰጠው ሰርተፍኬት እንዲሰረዝ ተወስኗል፡፡

አመልካች የካቲት 13/2009 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተፈፀመ የሚሉትን የህግ ስህተት በመዘርዘር ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ ባጭሩ፡-

- የኢንዱስትሪ ንድፍ ምዝገባም ሆነ ስረዛን በተመለከተ ተፈጻሚነት ያለው ህግ የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና ኢንዱስትሪ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 ሲሆን አዋጁ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ይሰረዝልኝ አቤቱታ ሊቀርብ የሚገባው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በግልፅ የደነገገ በመሆኑ የተጠሪ ጽ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ይሰረዝልኝ አቤቱታን የማየትም ሆነ የመወሰን ስልጣን ሳይኖረው ጉዳዩን ተቀብሎ በማየት ውሳኔ መስጠቱና የጽ/ቤቱ ዳይሬክተር ውሳኔውን ማፅደቃቸው የህግ መሰረት የሌለው ነው እንዲባል፤
- ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም ተጠሪ ጽ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውን ህግ አላግባብ በመተርጎም በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(2) መሰረት "የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ህግ የአዲስነት መስፈርት ፍጹማዊ ወይም በየትም ቦታ ከታወቀ ንድፍ የተለየ እንዲሆን ይጠይቃል" ከማለቱም በተጨማሪ "የቀረበው ንድፍ በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ሃገር አምሳያ ሊኖረው አይገባም " በማለት በአዋጁም ሆነ በማንኛውም ደንብም ሆነ መመሪያ ውስጥ ያልተገለፀ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት የአመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ አዲስነት፣ ፍፁማዊነት እና በሌላ ሃገር አምሳያ የሌለው ሊሆን ይገባዋል በማለት የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ይህን ትርጉም ተከትሎ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ይህን ሳያሟላ የተሰጠ በመሆኑ ሊሰረተዝ ይገባዋል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ ስህተት በመሆኑ እንዲታረም፤
- አመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ ሠርተፍኬት የተሰጠኝ ጽ/ቤቱ በአግባቡ አጣርቶ እና መርምሮ ህግን በተከተለ መንገድ ሲሆን ተጠሪ ጽ/ቤት ሰርተፍኬት ለመስጠጥ የመረመረበት መንገድም ሆነ የምርመራው ውጤት ትክክል አይደለም የሚል ክርክር ሲመጣ የምርመራውን ውጤት፣ የምርመራውን ሂደት ሆነ ሌሎች ምርመራውን የተመለከቱ አጠቃላይ ማስረጃዎች በራሱ በተጠሪ እጅ እያሉ እና የአመልካችም ክርክር ጽ/ቤቱ አስቀድሞ ምርመራውን በትክክል ማድረጉን የሚገልፅ ሆኖ እያለ የተጠሪ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በእጁ ያለውን ማስረጃ ሳይመረምር (ሳያጣራ) የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፤
- እንዲሁም ተጠሪ ጽ/ቤት በአዋጅ እንዲያስፈጽማቸው ከተሰጡት የፖሊሲ አላማዎች በተቃራኒ የሰጠውን ሰርተፍኬት እና እሱን ተከትሎ የሚሰጠውን ጥበቃ በማመን ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አውጥተው ስራ የሚሰሩትን ኢንቨስተሮች መተማመኛ እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ውሳኔ መስጠቱ ከተቋቋመለት አላማ እና ከመሰረታዊ

የአዕምሯዊ ንብረት ፖሊሲ የሚጣረስና ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የአመልካችን የተመዘገበ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃ እንዲያደርግ ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

የሰበር ቅሬታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ሚያዚያ 17/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፡-

- በተጠሪ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 320/95 ለተጠሪ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል የምዝገባ ማመልከቻዎችን በመቀበል አስፈላጊውን ምርመራ በማካሄድ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ሲሆን፤ ህጎቹ ያስቀመጧቸውን መስፈርቶች ሳያሟሉ የተመዘገቡ ማመልከቻዎች ላይ አቤቱታ ሲቀርብ ምዝገባውን የመሰረዝ ስልጣን (ፈራሽ የማድረግ) እንዳለው ተጠሪ የሚያስፈጽማቸውን ህጎች አውደ ንባብ (contextual interpretation) መሰረት በማድረግ የሰበር ችሎቱ አስቀድሞ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ተጠሪ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ ጥያቄን ተቀብሎ ያስተናገደው ህጉ በሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፤
- ተጠሪ የአዋጁን የአዲስነት መመዘኛ በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ምዝገባው እንዲሰረዝ አድርጓል በሚል የቀረበውን ቅሬታ በተመለከተም አዋጁ ለጥበቃ ብቁነት ያስቀመጠው የአዲስነት ጠባይ ፍፁማዊ ወይም ሁሉን አቀፍ (absolute or qualified universal novelty) የተባለው ሲሆን ንድፉ አዲስ መሆኑ የሚረጋገጠው በኢትዮጵያ ወይም በቀረው የአለም ክፍል አምሳያ ከሌለው ነው፤ ፍፁማዊ መመዘኛ የተባለውም ፍለጋው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይወሰን በሁሉም የአለም ክፍል መሆኑን ለማመልከት ነው፤ ስለሆነም የኢንዱስትሪ ንድፉ አዲስ ነው የሚባለው በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ እና ከምዝገባ ቀን ወይም እንደ አግባቡ ከቀዳሚ ቀን በፊት ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ያልተገለፀ ሲሆን በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ በህጉ በግልጽ የተመለከተውን በማዛባት የቀረበ ነው፤
- ለአመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ ሠርተፍኬት የተሰጠው ጽ/ቤቱ በአግባቡ አጣርቶ እና መርምሮ ሲሆን ተጠሪ በእጁ ያለውን ማስረጃ ሳይመረምር (ሳያጣራ) የሰጠው የመሰረዝ ውሳኔ ስህተት ነው በሚል የቀረበውን ቅሬታ በተመለከተም ተጠሪ ማመልከቻውን ለምዝገባ ለመቀበል ያካሄደው ምርመራ በአዋጁ አንቀጽ 48(1) የተመለከቱት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ በመሆኑ፤ በፎርማሊቲ ምርመራ ላይ ብቻ የተመሰረተ የምዝገባ ሥርዓት በንድፉ አዲስነት ላይ የሚደረግን

ፍለጋ (search) እና የማሰረዳት ሽክም በገበያ ውስጥ ጥቅም አለን ወደሚሉ ሰዎች የማዛወር ውጤት ያለው በመሆኑ በምዝገባው ተገቢነት ላይ የሚነሳን ተቃዉሞ ለመፍታት ጽ/ቤቱ ምርመራ ያደርጋል፤ የአመልካች ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባም አዲስነት የለውም ተብሎ እንዲሰረዝ የተወሰነው በዚሁ አግባብ ነው፤

- ተጠሪ የሰጠው የኢንዱስትሪ ንድፍ ሰርተፍኬት እንዲሰረዝ አቤቱታ ሲቀርብ የራሱን አሰራር መከላከል እየተገባው እንዲሰረዝ ማድረጉ የተቋቋመበትን ዓላማ ይቃረናል መባሉም ስህተት ነው፤ አመልካች የንድፉ ፈጠራ የራሱ ቢሆን ኖሮ ንድፉ ከመመዝገቡ በፊት ታይላንድ ሀገር የሚገኘው ፓይኒር ኢንተርናሽል ኮርፖሬሽ አምርቶታል ተብሎ ለቀረበው አቤቱታ በቂ ማስተባበያ ማቅረብ በቻለ ነበር፤ አመልካች የቀረበበትን አቤቱታ በበቂ ሁኔታ ሳያስተባብል ስላስመዘገበ ብቻ ባለመብት የሚሆንበት አሰራር ፍትሃዊ አይሆንም፤ ስለሆነም የአመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ አዲስ አይደለም ተብሎ ምዝገባው እንዲሰረዝ የተሰጠው ውሳኔ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔውን ማጽናቱ በአግባቡ ነው እንዲባል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር ግንቦት 18/2009 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ እና ግራ ቀኙ በሰበር ያደረጉትን ክርክር ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የችሎቱን ምላሽ የሚጠይቁት አብይ ነጥቦች ፡-

1ኛ) ተጠሪ ጽ/ቤት የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ አቤቱታን ተቀብሎ የማየትም ሆነ የመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም?

2ኛ) ስልጣን አለው ቢባል የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 የአዲስነት መስፈርትን አስመልክቶ የደነገገው አላግባብ ተተርጎሞ ውሳኔ ተሰጥቷል? ወይስ አልተሰጠም?

3ኛ) ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው ሰርተፍኬት እንዲሰረዝ የተወሰነው በህጉ አግባብ ተጣርቶ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡ በዚሁ ቅድመ ተከተል ተመልክናቸዋል፡፡

ቀዳሚውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች በቅሬታው በአዋጅ ቁጥር 123/1987 ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ አቤቱታ ሊቀርብ የሚገባው ለከፍተኛ

ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በግልፅ የደነገገ በመሆኑ የተጠሪ ጽ/ቤት የይሰረዝልኝ አቤቱታን የማየትም ሆነ የመወሰን ስልጣን ሳይኖረው ጉዳዩን ተቀብሎ በማየት ውሳኔ መስጠቱ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ስልጣን ሳይኖረው የሰጠው ውሳኔ እንዲሻር የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ ጥያቄውን ተቀብሎ ያስተናገደው ህጉ በሰጠው ሥልጣን መሰረት ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 59025 እና 71216 በሰጠው ትርጉም የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና ኢንዱስትሪ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987'ን ጨምሮ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 320/1995 እና ጽ/ቤቱ የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች አዋጆች ዝርዝር ይዘት በመመርመር አቤቱታ የሚቀርብበትን እና በይግባኝ የሚስተናገድበትን ሥርዓት በተመለከተ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ (የይሰረዝልኝ አቤቱታን ጨምሮ) ቅሬታ ያለው ወገን የሚኖረው መብት በይግባኝ ሥርዓት የማስከበር እንጂ ቀጥታ ክስ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አለመሆኑን፤ ይግባኙ መቅረብ ያለበትም ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርዴ ቤት መሆኑን ወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት ለተያዘው ጉዳይም በተመሳሳይ ተፈጻሚ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪው ጽ/ቤት የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ አቤቱታን ተቀብሎ የማየትም ሆነ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበው ቅሬታ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ተጠሪ ጽ/ቤት የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ አቤቱታን መርምሮ ለመወሰን ስልጣን አለው ብለናል፡፡

ሁለተኛው ነጥብ በአዋጅ ቁጥር 123/1987 የአዲስነት መስፈርትን አስመልክቶ የተደነገገው አላግባብ ተተርጎሞ ውሳኔ ተሰጥቷል በሚል የቀረበውን ቅሬታ የተመለከተ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው "የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ህግ የአዲስነት መስፈርት ፍጹማዊ ወይም በየትም ቦታ ከታወቀ ንድፍ የተለየ እንዲሆን ይጠይቃል" እንዲሁም "ንድፉ በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ሃገር አምሳያ ሊኖረው አይገባም " ተብሎ በተጠሪ ጽ/ቤት በኩል በህጉ ያልተገለፀ የተሳሳተ ትርጉም ተሰጥቶ ይህን ትርጉም ተከትሎ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ይህን ሳያሟላ የተሰጠ በመሆኑ ሊሰረተዝ ይገባዋል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ ስህተት በመሆኑ እንዲታረም ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አዋጁ ለጥበቃ ብቁነት ያስቀመጠው የአዲስነት ጠባይ ፍፁማዊ ወይም ሁሉን

አቀፍ መሆኑንና ንድፉ አዲስ መሆኑ የሚረጋገጠው በኢትዮጵያ ወይም በቀረው የአለም ክፍል አምሳያ ከሌለው ስለመሆኑ በህጉ የተደነገገ መሆኑን በማንሳት ተከራክሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(1) ድንጋጌ መሰረት አዲስነት እና ተግባራዊ ተፈፃሚነት ያለው ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በአዋጁ መሰረት ጥበቃ እንደሚደረግለት ተመልክቷል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 46(2)(ሀ) እንደተደነገገውም አንድ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዲስ ነው የሚባለው …

> ”የንድፉ ዋና ዋና ባህሪያት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ እና ከምዝገባ ቀን ወይም እንዳግባቡ ከቀዳሚ ቀን በፊት ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ያልተገለፀ ሲሆን ነው:: በንድፎቹ መካከል ያሉ የተለዩ ገፅታዎች ልዩነት በጥቃቅን ዝርዝሮች ከሆነ ተመሳሳይ ናቸው ተብለው ይወሰዳሉ“፡፡ የዚሁ ድንጋጌ እንግሊዝኛ ቅጅም
>
> “industrial design shall be considered new when the sum total of its essential features is different from that of another design known either in Ethiopia or abroad and has not been disclosed for more than one year before the date of filing of the application for registration or, where appropriate, before the priority date. Designs shall be deemed to be identical if their specific features differ only in immaterial details” በማለት ይደነግጋል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ንድፉ አዲስ መሆኑ የሚረጋገጠው በኢትዮጵያ ወይም በቀረው የአለም ክፍል አምሳያ ከሌለው ስለመሆኑ በህጉ የተደነገገ መሆኑን በማንሳት ያቀረበው ክርክር የሚነቀፍ ባይሆንም አንድ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዲስ ነው የሚባለው የንድፉን ዋና ዋና ባህሪያት መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ከፍ ሲል ከተመለከትነው የህጉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የንድፉን ዋና ዋና ባህሪያት ለይቶ ተመሳሳይነት አላቸው ወይም የላቸውም በማለት መወሰን የሚቻለው ደግሞ የእያንዳንዱን ዲዛይን ዋና ዋና ባህሪያት በቅድሚያ በመለየት ከሌላው ጋር በማነፃፀር ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ አዲስነት፣ ፍፁማዊነት እና በሌላ ሃገር አምሳያ የሌለው ሊሆን ይገባዋል በማለት የተሳሳተ ትርጉም ተሰጥቷል በማለት ያቀረበው ክርክር ከፍሲል የተመለከተውን የህጉን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት

ባይኖረውም የአከራካሪው ንድፍ ዋና ዋና ባህሪያት ተለይተው የተሰጠ ውሳኔ ስለመሆኑ መዝገቡ ስለማያሳይ ውሳኔው በዚህ ረገድ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ከዚህ ጋር የተያያዘው ሌላው ነጥብ ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው ሰርተፍኬት እንዲሰረዝ የተወሰነው በህጉ አግባብ ተጣርቶ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የንድፉን አዲስነት ለመወሰን የአከራካሪው ንድፍ ዋና ዋና ባህሪያት ተለይተው ሊታወቁ ይገባል፡፡ የአንድ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ዋና ዋና ባህሪያት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ መሆኑ የሚረጋገጠው ደግሞ በዘርፉ ያለውን የዳበረ እውቀት እና ልምድ መሰረት ዝርዝር ማጣራት በማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ክርክር ባስነሳው ንድፍ ዋና ዋና ባህሪያት ላይ እውቀቱ ያላቸው ባለሙያዎች የሚሰጡት ምስክርነት ለጉዳዩ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ጽ/ቤት ለአመልካች ሰርተፍኬት ሰጥቶት የነበረው በኢትዮጵያ ገበያ በኢንተርኔት በተደረገ ተመሳሳይ ንድፍ ፍለጋ ሪፖርት መሰረት ንድፉ አዲስ ነው ተብሎ ሲሆን ሰርተፍኬቱ የተሰረዘውም ሰርተፍኬቱ የተገኘበትን የምርመራ ሪፖርት ትክክለኛነት አመልካች (በላይነህ ደቻሳ) ሞግቶታል የአሁኑ አመልካችም ይህን ማስተባበል አልቻለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ጽ/ቤት በዚህ መልኩ ሰርተፍኬት የሚሰጥና የሚሰርዝ ከሆነ አሰራሩ ህጉን የተከተለ ካለመሆኑም በላይ ተቋሙ በአዋጅ የተቋቋመለትን አላማ ዳር የማያደርስ በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ ጽ/ቤት በህጉ እንደተመለከተው የአከራካሪውን ንድፍ አዲስነት ለመወሰን የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ዋና ዋና ባህሪያት በመለየት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ ወይም ተመሳሳይነት ያለው ስለመሆኑ በዘርፉ ያለውን የዳበረ እውቀት እና ልምድ መሰረት በማድረግ ዝርዝር ማጣራት በማድረግ መወሰን ሲገባው በዚህ መልኩ ሳያጣራ እና ሳያረጋግጥ ውሳኔ ላይ መድረሱ ጉዳዩ የሚገዛበትን ህግ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በቁጥር ኢ/አ/ን ይ/ስ/ኮ መ/ቁ 02/2008 ሚያዚያ 18/2008 ዓ.ም ለአመልካች በቁጥር 714 በስሙ ተመዝግቦ የተሰጠው ሰርተፊኬት በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(2)(ሀ) የተመለከተውን

የአዲስነት መስፈርት አሟልቶ የተሰጠ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ፤ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 180621 ያሳለፈው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጉዳዩን በህጉ አግባብ በማጣራት የአከራካሪውን ንድፍ አዲስነት ለመወሰን የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ዋና ዋና ባህሪያት በመለየት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ ወይም ተመሳሳይነት ያለው ስለመሆኑ በዘርፉ ያለውን የዳበረ እውቀት እና ልምድ መሰረት በማድረግ ዝርዝር ማጣራት አድርጎ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡተዘግቷል ወደመዝገብቤትይመለስ፡፡

ቅ/ህ                                                  የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሃሣብ

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 5 ስር የተመዘገበው ዳኛ ከሌሎች ባልደረቦቼ የተለየሁትበት ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46/2/ሀ/ ስር የተደነገገውን የአዲስነት መስፈርት አሟልቶ የተሰጠ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተጠሪ አመልካች ባቀረበው የኢንዱስትሪ ንድፍ ጥበቃ ሰርተፍኬት ጥያቄ ላይ ምዝገባውን ተጠሪ ከአከናወነ በኋላ በተቃዋሚ ወገን በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ምዝገባውን መሠረዙ ራሱ የሰጠውን የቀደመ ውሣኔ እራሱ የሚሰርዝበት አግባብ የለም ይህን ውሣኔ መስጠት የሚገባው መደበኛ ፍርድ ቤት ነበር በሚል የግል አቋም ያለኝ በመሆኑ ነው፡፡

ምክንያቱም ተጠሪ የአመልካችን የኢንዱስትሪ ንድፍ የመዘገበው እስከመጨረሻው ማጣራት አድርጎ እና አንድ ሥራ ሲመዘገብ ሊያሟላ የሚችለውን መስፈርት ሁሉ አሟልቶ ተቃዋሚ ካለም ንድፉ ከመመዝገቡ በፊት ማስታወቂያ አውጥቶ ተቃዋሚ ባለመኖሩ እና ራሱ ተጠሪ የሚጠበቅበት ማጣራት ከኢንተርኔት ጭምር ካጣራ በኋላ መመዝገቡን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

አንድን ተግባር በራሱ አጣርቶ የመስራት ኃላፊነት ያለበት ክፍል አጣርቻለሁ ብሎ ወስኖ በህግ አግባብ ምዝገባውን ካከናወነ በኋላ ምዝገባው በተከናወነበት እና ፈቃድ በተሰጠበት ጊዜ በሚሰጥ የጊዜ ገደብ ያልቀረበ እና ያልተቃወመን አካል ከጊዜ ገደቡ በኋላ በመምጣት ይህ ምዝገባ እንዲሰረዝ ቢጠይቅ መ/ቤቱ በራሱ ማጣራት የማያደርግ እና ጥያቄው እንደቀረበ የሚያስተናግድ እና ምዝገባ አከናውኖ ሰርተፊኬት የሚሰጥ ቢሆን ኑሮ ቅሬታ አቅራቢ የሚመጣ ቢሆን የሚቀበል እና እንደገና የምዝገባውን ሁኔታ የሚመለከትበት አግባብ የሚኖር ሲሆን ነገር ግን ራሱ አጣርቶ የወሰነውን ውሣኔ ተቃዋሚ በቀረበ ቁጥር እንደገና የራሱን ውሣኔ የሚመረምር እና የሚለውጥ ከሆነ ፍትሐዊነትን የሚያዛባ ይሆናል የሚል አቋም አለኝ፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተመሣሣይ ጉዳይ በመ/ቁ/ 71216 በሆኑት መዛግብት የሰጠውን ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 2/9/ እና 15 ፣ በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 2/1/ እና 54 ፣ በአዋጁ በሚገዙ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የመመልከት ሥልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን በግልጽ በማስቀመጥ ነገር ግን ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ/ 59025 በሆነው መዝገብ ላይ የህግ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የተሰጠ ውሣኔ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በእነዚህ ሁለት መዛግብት የቀረበው ክርክር የሚያመለክተው ቀጥታ ክስ ሊቀርብ ይገባል ወይንስ በይግባኝ ነው መታየት ያለበት የሚል መሆኑን ለእኔ ያስገነዝበኛል፡፡

1) ይህ ማለት ሁለት አይነት ጉዳይ ላይ ተጠሪ መ/ቤት ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑን በመጀመሪያ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት አንድ ንድፍ ይመዝገብልኝ እና ሰርተፊኬት ይሰጠኝ የሚል አመልካች ሲመጣ ራሱም በማጣራት እና ተቃዋሚ ካለ በጋዜጣ ጭምር በመጥራት የሚያስተናግድ እና ምዝገባውን የሚያከናውን መሆኑን ሲሆን በዚህ የማስታወቂያ ጥሪ መሠረት የሚመጣ ተቃዋሚ ካለ ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክር ጭምር በመስማት የቀረበው ንድፍ ሊመዘገብ ይገባል ወይም ሊመዘገብ አይገባም በማለት ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑን ስንገነዘብ ፣
2) ደግሞ ምዝገባ ከማድረጉ በፊት በራሱ አጣርቶ እና ተቃዋሚም ጠርቶ ሳይቀርብ ቀርቶ ምዝገባውን ካከናወነ እና ሰርተፊኬት ከሰጠ በኋላ የሚቀርብ ተቃውሞ

የሚስተናገድበት ሥርዓት ያለ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ በሁለተኛው የምዝገባ ስርዓት ውስጥ በግራ ቀኝ የሚደረግ ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥርዓት የሙግት አካሄድ አቤቱታ መልስ እና የመልስ መልስ ተደርጐ ተጠሪም ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ የሚያሳርፍበት ሥርዓት የለም፡፡

በእኔ አመለካከት በመጀመሪያው የምዝገባ ሂደት ተደርቶ ተቃዋሚ ቀርቦ ግራ ቀኝ ቀርበው ተከራክረው መልስ የመልስ መልስ እና ሙግት አከናውነው ተጠሪ የሚሰጠው ንድፉ ይመዝገብ ወይም አይመዝገብ በሚል ውሣኔ በይግባኝ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሄዱ ተገቢ ሲሆን ነው ባይ ነኝ፡፡

የሰ/መ/ቁ/ 59025 በሆነው መዝገብ ላይ ቀድሞ የተሰጠው ውሣኔ ከላይ በ1ኛ ነጥብ ላይ የተቀመጠውን የሚመለከት በመሆኑ አሁን ከቀረበው ጉዳይ የሚለይ እንጂ ተመሣሣይ ነው ሊባል የሚገባው ባለመሆኑ ቀድሞ በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የተሰጠው የሰበር ሰሚ ችሎቱ ትርጉም ገዢ ሊሆን የሚገባው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ራሱ አጣርቶ ሌላ ተቃዋሚ በሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ሳይቀርብ የሰጠውን የንድፍ ምዝገባ እና ሰርተፊኬት በሌላ ጊዜ ተቃዋሚ መጥቷል በሚል ራሱ መልሶ የሚሽርበት አካሄድ ተገቢ ባለመሆኑ ከዛም ሂደት በኋላ የሚቀርብ የምዝገባ መቃወሚያ ለመደበኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ራሱም ንድፉን ካስመዘገበው ሰው ጋር ተከሳሽ በመሆን በቀጥታ ክስ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚገባ መሆን ይኖርበታል እንጂ በይግባኝ የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ ሆኖም አብላጫው ድምጽ ትርጉም የተሰጠበት የሰበር ውሣኔ ገዢ ነው በማለት አቋም የያዘ በመሆኑ በቀደመው ጊዜ በተመሣሣይ ጉዳይ ከላይ በተጠቀሱት የሰበር መዛግብት ላይ የሰጠው ውሣኔ በእኔ እምነት ሊተረም እና ሊስተካከል የሚገባው ነው በሚል ፓናል ተቋቁሞ በ7 እና ከዛ በላይ በሆኑ ዳኞች ተመርምሮ አቋሙ ሊለወጥ የሚገባው ነው እንጂ ተጠሪ ራሱ ውሣኔ ሰጥቶ ራሱ ጉዳዩን እንደገና አይቶ የሚወስንበት አግባብ ሊኖር አይገባም ተጠሪ ጉዳዩን ያየው ያለስልጣኑ ነው እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በይግባኝ ደረጃ ተቀብሎ ማስተናገዱ ሊታረም የሚገባ ነው በሚል ከባልደረቦቼ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

የሰ/መ/ቁ/ - 136024

ጥቅምት 21 ቀን 2010ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ቢልልኝ ጌታነህ - ጠበቃ ፋንታሁን አባተ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ገብራይ ተከስተ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበዉ ክስ፤ የወፍጮ ድርጅቱን በዉስጡ ካሉት ሦስት የተለያየ የፈረስ ጉልበት ካላቸዉ ወፍጮዎች እና ሚዛን ጋር በወር ብር 7,000.00 ኪራይ እየከፈለ ከ26/11/2004 እስከ 26/11/2006 ዓ.ም ድረስ እንዲጠቀምበት ለአመልካች ማከራየቱን እና የኪራዩ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላም አመልካች የወፍጮ ድርጅቱን ከነሙሉ ዕቃዉ አለማስረከቡን እና ቀሪ የኪራይ ገንዘብም ያልከፈለዉ መሆኑን በመግለጽ አመልካች ወፍጮዎቹን፣ የወፍጮ ድርጅቱን እና ሚዛኑን እንዲመልስለት፣ እንዲሁም የዉሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለዉን የኪራይ ገንዘብ ብር 21,000.00 እና ወፍጮዎቹን እስኪረከባቸዉ ድረስ ያለዉ የድርጅቱ ኪራይ ታስቦ እንዲከፍለዉ ይወሰንለት ዘንድ የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ለክሱ መሠረት ያደረገዉ ዉል በ25/12/04 ዓ.ም በተደረገ ሌላ ዉል መተካቱን እና በኋለኛዉ ዉል መሠረትም የዉሉ ጊዜ እስከ 25/12/06 ዓ.ም

የሚቆይ በመሆኑ ተጠሪ ድርጅቱን እንዲለቅለት ከፈለገ የሦስት ወር ጊዜ መስጠት ስላለበት የመጠየቂያ ጊዜዉ ያልደረሰ መሆኑን፣ በወር ለመክፈል የተስማማዉ ኪራይም ብር 7,000.00 ሳይሆን ብር 350.00 መሆኑን እና ጊዜዉ ሲደርስ ወፍጮዎቹን ከነሚዛኑ ለተጠሪ እንደሚያስረክብ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ የቀረበዉን የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ፤ በኋላ ላይ ተደርጓል የተባለዉ ዉል በህግ አግባብ የመጀመሪያዉን ዉል የተካ አለመሆኑን በመግለጽ አመልካች ወፍጮዎቹን እንዲመልስ፣ እንዲሁም ከነሐሴ ወር 2006 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 08 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ያለዉን ኪራይ ብር 30000.00 ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ የወፍጮ ድርጅቱ እንዲታሸግ የተደረገዉ በአመልካች ጥፋት ምክንያት መሆኑን በመግለጽ ከታህሳስ 09 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ያለዉን የኪራይ ገንዘብ ብር 110133.00 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 28/04/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃዉ አማካይነት በቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፤ የወፍጮ ድርጅቱ ከታህሳስ 09 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት እንዳይሰጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታሽጎ እንዲቆይ ተደርጎ እያለ ለእነዚህ ጊዜያት ኪራይ እንዲከፈል በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልፆ ታርሞ እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮም የወፍጮ ቤት ድርጅቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታሽጎ በነበረበት ወቅት ያለዉን ኪራይ አመልካች እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ፣ ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ጥሪ ተደርጎለታል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በቀን 20/06/09 ዓ.ም በጠበቃዉ አማካይነት ተዘጋጅቶ በቀረበ መልስ፤ ወፍጮ ቤቱ ሊታሸግ የቻለዉ በአመልካች

እምቢተኝነት ምክንያት በመሆኑ ድርጅቱ ታሽጎ ለቆየባቸዉ ጊዜያት ጭምር አመልካች ኪራዩን እንዲከፍል የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሊሻር አይገባዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በዚህ ላይ ያቀረበዉ የመልስ መልስም ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ መዝገቡን ለማስቀረብ ከተያዘ ጭብጥ፣ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የወፍጮ ድርጅት ከታህሳስ 09 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሳይሰጥ ታሽጎ የቆየ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ታሽጎ እንዲቆይ የተደረገዉም ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በግራ ቀኝ መካከል ሲደረግ በነበረዉ ክርክር ምክንያት ጉዳዩን የያዘዉ ፍርድ ቤት ታህሳስ 08 ቀን 2007 በሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ምክንያት በመሆኑም ላይ ግራ ቀኝ አልተካካዱም፡፡ በሌላ በኩል በግራ ቀኝ መካከል በተደረገ ዉል መሠረት አመልካች የወፍጮ ድርጅቱን ኪራይ ለመክፈል የሚገደደዉ እንዲሁም ተጠሪ ኪራዩን ከአመልካች የመጠየቅ መብት የሚኖረዉ ድርጅቱ የወፍጮ አገልግሎት ሲሰጥ ብቻ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በርግጥ የዉሉ ጊዜ ካበቃ በኋላም ቢሆን ተጠሪ ድርጅቱን እስከሚረከብበት ጊዜ ድረስ ያለዉን ኪራይ አመልካች ለመክፈል ይገደዳል፡፡ ይህም የሚሆነዉ ድርጅቱ የወፍጮ አገልግሎቱን የሚሰጥ ሲሆን ወይም አገልግሎቱ እንዳይሰጥ የተደረገዉ በአመልካች ጥፋት ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡

የወፍጮ ደርጅቱ ከፍ ሲል በተመለከቱት ጊዜያት አገልግሎት እንዳይሰጥ የተደረገዉ በአመልካች ጥፋት ምክንያት ሳይሆን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን ሊሰጥ የቻለዉም ድርጅቱ እንዲታሸግ እና አገልግሎት እንዳይሰጥ ታግዶ እንዲቆይ ተጠሪ በመጠየቁ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በአንድ በኩል ወፍጮዉ ተገቢዉን አገልግሎት እንዳይሰጥ እና ታሽጎ እንዲቆይ አስደርጎ እና በዚህም ምክንያት አመልካች ከወፍጮዉ ገቢ ባላገኘበት ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ታሽጎ ለቆየበት ጊዜ ኪራይ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉ ዳኝነት ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወፍጮዉ ታሽጎ ለቆየበት ጊዜ ያለዉን ኪራይ አመልካች እንዲከፍል የሰጠዉ

ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/174062 በቀን 15/02/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 133803 በቀን 20/04/09 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/122163 በቀን 07/01/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. ዕግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.chilot.me